# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ

# ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የንግድ ሕግ

# (ረቂቅ)

# <u>አዋጅ ቁጥር…./2012 ዓ.ም</u>

# <u>የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የንግድ ሕግ</u>

## መቅድም

የኢኮኖሚ ዕድገትን እና የሕዝብ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ለንግድ ሥራ ጽኑ የሕግ መሠት መጣል የግድ ይላል፡፡ በ1952 ዓ.ም የወጣው የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ ለዚህ ዓላማ ከግብ መድረስ አስፈላጊውን መደላድል የሚያኖር ነበር፡፡ ከዘመኑ የኢትዮጵያ የዕድገት ደረጃ አኳያ ሲታይ ከጊዜው እጅግ የቀደመ ነበር ማለትም ይቻላል፡፡

ሆኖም ሕጉ ከወጣበት ጊዜ አንስቶ ባለፉት ስልሳ ዓመታት ብዙ ነገሮች ተለውጠዋል፡፡ ንግድ እና የመዋዕለንዋይ ፍሰት እጅግ ከመጨመራቸውም በላይ እያደር ድንበር-ዘለል ባህሪ እየተላበሱ መጥተዋል፡፡ እነዚህ ክስተቶች በተለይ ኢትዮጵያ ገበያ-መር ስርዓት መከተል ከጀመረችበት ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ ሕጉ በተግባር እንዲፈተሽ ዕድል ፈጥረዋል፡፡ በመሆኑም ሕጉ ውስጥ አንዳንድ ክፍተቶች እና ጉድለቶች ታይተዋል፡፡ ለአፈጻጸም የማይመቹ እና ለተለያዩ ትርጉሞች የተጋለጡ ብዙ ድንጋጌዎች እንዳሉበትም ግልጽ ሆኗል፡፡ በአጭሩ ለመጪዎቹ ዓሰርት አመታት የንግድ እንቅስቃሴን ለመምራትና ለመግዛት ቀርቶ ዛሬ ኢትዮጵያ ለደረሰችበት የኢኮኖሚ እንቅስቀሴ ደረጃም ቢሆን ሕጉ የተሟላ እና በቂ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ስለዚህ የነጋዴዎቸን፣ የባለሀብቶችን እና በሕጉ ጥቅማቸው በቀጥታ የሚነካ ባለድርሻ አካላት መብቶችን በሚዛናዊ ሁኔታ ለማስተናገድ፤ የኢትዮጵያን ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት በማረጋገጥ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴን ለማስፋፋት ብሎም የዜጎችን የኑሮ ደረጃ ለማሳደግ የንግድ ሕጉን ዘመናዊ ማድረግ የግድ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**1.** <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ሕግ “የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር ------/2020” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**2.** <u>የተሻሩ እና ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎችና አሰራሮች</u>

**1.** በአዋጅ ቁጥር 166/1952 የወጣው የንግድ ሕግ መጽሐፍ አንድ፣ ሁለት እና አምስት ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን ጀምሮ ተሽረዋል፡፡

**2.** ከዚህ ሕግ ጋር የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ሕግ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት የለውም፡፡

**3. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>**

1. ይህ ሕግ ከመጽናቱ በፊት በፍርድ ቤት ወይም ከፊል የዳኝነት ስልጣን ባላቸው አካላት በመታየት ላይ ያለ ጉዳይ በቀድሞው ህግ መሰረት ይዳኛል፡፡

3. ይህ ሕግ ከመጽናቱ በፊት በዚህ ሕግ አንቀፅ **2** መሰረት በተሻሩ ህጎች መሠረት የተሰጠ ውሳኔ የጸና ነው፡፡

4. ግልጽ የሆነ ተቃራኒ ድንጋጌ በሌላ ሕግ ከሌለ በቀር የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 166/1952 መጽሐፍ ሦስት እና አራት የፋይናንስ አገልግሎቶች መድብል (ኮድ) እስኪወጣ ድረስ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

**<u>4. ደንብ የማውጣት ሥልጣን</u>**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**<u>5. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>**

አግባብ ያለው የመንግስት አካል ይህን አዋጅና እና በዚህ ሕግ አንቀፅ 4 መሰረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም መመሪያ ሊያወጣ ይቸላል፡፡

**<u>6. ሕጉን ስለማሻሻል</u>**

ይህንን ሕግ ለማሻሻል የሚቀርብ ማንኛውም የማሻሻያ ሀሳብ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተገቢው ምክክር ተደርጎበት ለህግ አውጪው አካል የሚላከው በፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በኩል ይሆናል፡፡

**<u>7. ሕጉ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ ሕግ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ____________ ቀን 2012 ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አንደኛ መጽሐፍ

## ስለ ነጋዴዎችና ስለ ንግድ መደብሮች

## ርዕስ አንድ

## በነጋዴዎች ላይ ስለሚፈጸሙ ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## ምዕራፍ አንድ

## የንግድ ሥራ በሚሠሩ ሰዎች ላይ ስለሚፈጸም ሕግ

**አንቀጽ 1 ስለ የፍትሐ ብሔር ሕግ ተፈጻሚነት**

በዚህ ሕግ በተለየ ሁኔታ እስካልተደነገገ ድረስ የንግድ ሥራ በሚሠሩ ሰዎችና በንግድ ማኅበሮች ላይ የፍትሐ ብሔር ሕግ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 2 ስለ ባሕር ሕግ ተፈጻሚነት**

የንግድ ሥራቸው ከባሕር ንግድ ሥራ ጋር የተያያዘ በሆኑ ሰዎችና የንግድ ማኅበሮች በባሕር ሕግ ውስጥ ተገቢ የሆኑት ልዩ ውሳኔዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

**አንቀጽ 3 ስለ ሰዎችና የንግድ ማኅበሮች**

በተፈጥሮ ሰዎች ላይ ብቻ ተፈጻሚ የሚሆኑት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ በሰዎች ላይ ተፈጻሚ የሆኑት የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች በንግድ ማኅበራት ላይም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡ የንግድ ማኅበራትን የተመለከቱ የመጽሐፍ ሁለት እና ሦስት ልዩ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ናቸው፡፡

**አንቀጽ 4 ይህ ሕግ የማይፈጸምባቸው ተቋማት**

(1) በሕግ የተቋቋሙ ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው የአስተዳደር አካላት፣ የኃይማኖት ድርጅቶች፣ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች እና የኅብረት ሥራ ማኅበራት በዚህ ሕግ በአንቀጽ 5 የተመለከተውን ሥራ ቢሠሩም አንኳን ግልጽ የሆነ ተቃራኒ የህግ ድንጋጌ እስከሌለ ድረስ የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ አይሆኑባቸውም፡፡

(2) በዚህ አንቀጽ በንኡስ አንቀጽ (1) የተደነገገው በሕግ በተቋቋሙ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

## ምዕራፍ ሁለት፡፡

## ነጋዴ ናቸው የሚባሉ ሰዎች

**አንቀጽ 5፡ ነጋዴዎች የሚባሉ ሰዎች**

የሞያ ሥራቸው አድርገው ጥቅም ለማግኘት ሲሉ በተለይ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ሥራዎች የሚሠሩ ሰዎች ነጋዴዎች ናቸው፡፡

(1) የሚንቀሳቀሱ ወይም የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን ገዝተው ባሉበት ሁኔታ ወይም ቀያይረው ወይም አሻሽለው መልሰው የሚሸጡ፤

(2) ተንቀሳቃሽ ወይም የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን ገዝተው የሚያከራዩ፤

(3) በሕግ ለንግድ አላማ እንዲውል በተሰጠ መሬት ላይ ባለመብት በመሆን የእርሻና የደን ልማት ሥራ የሚሰሩ፤

(4) በሕግ የገጠር መሬት ለመጠቀም ባለመብት ከሆኑ ሰዎች ውጪ ያሉ ሌሎች ሰዎች አነስተኛ ከሆነው መጠን በላይ እንስሶችን የማርባት ስራ እና ከእንስሶች የሚገኙ ምርቶችን የማምረት ሥራ የሚሰሩ፤

(5) አነስተኛ ከሆነው መጠን በላይ ዓሳ የሚያጠምዱ እና የሚያረቡ፤

(6) በፍትሐ ብሔር ሕጉም ሆነ በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት የዕቃ ማከማቸት አገልግሎት የሚሰጡ፤

(7) የዕደ-ጥበብ ባለሙያ ከሚሰራው መጠን በላይ በሆነ መንገድ የማዕድን፣ የነዳጅ ዘይት ወይንም የጋዝ ፍለጋ ሥራ የሚሰሩ፣ የሚቆፍሩ እና የሚያወጡና ለነዚሁ ደጋፊ አገልግሎቶች የሚሰጡ፤

(8) የዕደ-ጥበብ ባለሙያ ከሚሰራው መጠን በላይ በሆነ አኳኋን ለህንፃ፣ ለመንገድም ሆነ ለሌሎች ዓይነት ግንባታ ሥራዎች አገልግሎት የሚውል የድንጋይ ማውጣት እና መፍለጥ ሥራዎችን የሚሰሩ፤

(9) የዕደ-ጥበብ ባለሙያ ከሚሰራው መጠን በላይ በሆነ መንገድ የጨው ማዕድንን የሚያወጡ፤

(10) የምግብ ዕቃዎችን፣ በተፈጥሮ የሚገኙም ሆነ ሌሎች ጥሬ ዕቃዎችንና በግማሽ የተሰሩ ዕቃዎችን ጨምሮ ከማንኛውን ዓይነት ግዙፍነት ካላቸው ተንቀሳቃሽ ነገሮች ሌሎች ዓይነቶች ግዙፍነት ያላቸው ተንቀሳቃሽ ዕቀዎችን የዕደ-ጥበብ ባለሙያ ከሚሰራው በላይ አድርገው የሚያመርቱ፣ የሚለዋዉጡ፣ የሚቀይሩና እነዚህን የሚጠግኑ፤

(11) የዕደ-ጥበብ ባለሙያ ከሚሰራው መጠን በላይ በሆነ አኳኃን ቤትን፣ ህንፃን፣ መንገድንና ማንኛውንም ሌላ ዓይነት የግንባታ ሥራና የግንባታ ሥራዎች ንኡሳን ክፍሎችን የመስራት፣ የመጠገንና የማፅዳት ሥራ የሚሰሩ ፤

(12) የዕደ-ጥበብ ባለሙያ ከሚሰራው መጠን በላይ በሆነ አኳሃን በሌላ ሰው የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የመደልደል፣ የመደደቅ፣ የውሃ መውረጃ ቦዮች የመሰንጠቅ ስራ የሚሰሩ፤

(13) ሰዎችን፣ እቃዎችን፣ እንደ ፖስታ ባሉ የተያዙ መልእክቶችን ጨምሮ የዕደ-ጥበብ ባለሙያ ከሚሰራው መጠን በላይ በሆነ አኳኃን ማንኛውንም ዓይነት የማጓጓዝ፣ እቃዎችን የማሸግና ከዚሁ ጋር የተያያዙ ስራዎችን የሚሰሩ፤

(14) ውሃን በተለያየ መንገድ የማቆር እና የማሰራጨት ስራዎች፤

(15) ደረቅና ፍሳሽን ጨምሮ ማንኛውንም ቆሻሻ የማጓጓዝ፣ የማስወገድ ወይም መልሰው ለጥቅም እንዲውሉ የማድረግ ሥራዎችን የዕደ ጥበብ ባለሙያ ከሚሰራው በላይ በሆነ መንገድ የሚሰሩ፤

(16) ኤሌክትሪክ፣ ጋዝ፣ ታፍኖ የተያዘ ንፋስ፣ የማሞቂያና የማቀዝቀዣ ሥራ የሚሰሩ፣ የሚያመነጩ፣ የሚያሰራጩ፣ የሚያከፋፍሉ እና የሚሸጡ፤

(17) የዕደ-ጥበብ ባለሙያ ከሚሰራው መጠን በላይ በሆነ መንገድ ተቀሳቃሽ እና የማይንቀሳቀሱ ነገሮችን የመጠገን፣ የማጠብ እና የማፅዳት ሥራዎችን የሚሰሩ፤

(18) በወረቀት የሚታተሙን ማንኛውንም ዓይነት የህትመት ስራዎቸን ማተሚያ ቤት በማቋቋም ማተም፤ እንዲሁም በማንኛውም መንገድ የድምፅም ሆነ ተንቀሳሽ ምስልን ጨምሮ የምስል ቀረፃ ሥራ የሚሰሩ፤

(19)በወረቀት ህትመት፣ በፎቶግራፍ፣ በድምፅ (ኦዲዮ) ወይንም የድምፅ እና የምስል (ኦዲዮቪዥዋል) ቀረፃ አማካኝነት ወይም በቴሌቪዥን፣ በራዲዮ፣ በኢንተርኔት ወይንም ማንኛውንም ዓይነት ስራን ወደ ህዝብ ማቅረቢያ መንገድ በመጠቀም ሥራን አትመው የሚያቀርቡ፤

(20)ለህዝብ የመዝናኛ ትርዕይት አዘጋጅተው የሚያቀርቡ እና የመጫወቻ እና የመዝናኛ ስፍራዎችን ለህዝብ አገልግሎት የሚከፍቱ፤

(21)የንግድ ትርዕይቶችንና ከነዚሁ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸውን ስራዎች የሚሰሩ፣

(22)የራዲዮ እና የቴሌቪዥን ጣቢያ አቋቁመው ፕሮግራሞችን የሚያሰራጩ፤

(23)መረጃ ወይንም ዜናና ማንኛውንም ዓይነት ወሬ የማስተላለፍ ስራ የሚሰሩ፤

(24)ሽቦም ሆነ ሽቦ-አልባ በሆነ መንገድ እንዲሁም የሳተላይት እና የኢንተርኔት ቴክኖሎጂን በመጠቀም ሰዎችን የማገናኘት (ኮሙኒኬሽን) ስራዎችን የሚሰሩ፤

(25)የኮምፒዩተር እና ሶፍትዌር ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም መረጃዎችን የማስተናገድ፣ የማቀናበር፣ የማቅረብ ወይም የማስቀመጥ ስራዎችን ሰርተው ለህዝብ አገልግሎት በኢንተርኔት የሚያቀርቡ እና እነዚሁ መረጃዎችን ደምበኞቻቸው በኢንተርኔት እንዲያገኙ ቦታና ኮምፒዩተር የሚያቀርቡ፤

(26)በህግም ሆነ በልምድ የባንክ፣ የኢንሹራንስና የፋይናንስ አገልግሎት ስራዎች ተብለው የሚመደቡትን እና ከነዚሁ ጋር ተያያዥነት ያላቸውንና ለነዚሁ ድጋፍ የመስጠት ስራ የሚሰሩ፤

(27)የመኝታ እና የመስተንግዶ አገልግሎት የመስጠት፣ የምግብ ቤት፣ ምግብ አብስሎ የማቅረብ፣ የቡና ቤት፣ የመጠጥ ቤት፣ የምሽት መዝናኛ (ክለብ) እና ተመሳሳይ ስራዎችን የሚሰሩ፤

(28)ስለሌሎች በመሆን ስብሰባዎችን፣ ድግሶችን እና ግብዣዎችን የሚያዘጋጁና የሚያስተባብሩ፤

(29)የጉዞ ወኪልነት ሥራ የሚሰሩና ጉዞዎችን የሚያስተባብሩ፤

(30)የውበት እና የሰውነት መጠበቂያ፣ የፀጉር ማስተካከል፣ ማንኛውንም ዓይነት ስፖርትንና ሰውነት ማሸትን ጨምሮ ሁሉም ዓይነት የጤንነት መጠበቂያ አገልግሎቶችን የሚሰጡ፤

(31)በልምድ ወይንም በትምህርት የሚገኙ ሳይንሳዊ፣ ቴክኒካዊ እና ሙያዊ ዕውቀቶችን በመጠቀም አነስተኛ ከሆነው መጠን በላይ በሆነ ሁኔታ የማማከር እና መሰል የዕውቀት አገልግሎቶችን የሚሰጡ፣

(32)አነስተኛ ከሆነው መጠን በላይ በመደራጀት የሰዎችን ሆነ የእንስሶች የጤና ምርመራ እና የህክምና አገልግሎት መስጠት እንዲሁም ጤንነትን ለመጠበቅ ወይንም ለመከላከል የሚያስችሉ የምክር፣ ክትትል እና የእንክብካቤ ሥራዎችን መሥራት፤

(33)አነስተኛ ከሆነው መጠን በላይ በመደራጀት የትምህርት አገልግሎት መስጠት እና የዕውቀት ማስተላለፍ እና ማሰራጨት ሥራዎችን የሚሠሩ፤

(34)የንግድ ወኪል፣ የኮሚሽን ወኪል፣ የንግድ ደላላ እና የአክሲዮን ደላላ በመሆን ሥራ የሚሠሩ እና እንዲሁም ደግሞ ማንኛውንም ዓይነት የሰዎችን የአገናኝነት ሥራ የሚሠሩ፤

(35)አነስተኛ ከሆነው መጠን በላይ የንብረትም ሆነ የግል ደህንነትን የመጠበቅ አገልግሎት የሚሰጡ፤

(36)ሰነድ ማዘጋጀትን፣ ማባዛትን ጨምሮ ማንኛውንም ዓይነት የቢሮ ሥራን የሚደግፉ አገልግሎችን አነስተኛ ከሆነው መጠን በላይ መስጠት፣

(37)የቀብር ሥራና እና ተያያዥነት ያላቸውን ስራዎች፡፡

**አንቀጽ 6 በአነስተኛ መጠን ስለሚሠሩ ሰዎች**

(1) በዚህ ሕግ በአንቀጽ 5 በንኡስ አንቀጽ (4)፤(5)፤ (31)፤ (32)፤(33)፤(35) እና (36) የተመለከቱትን ተግባራት በአነስተኛ መጠን የሚሠሩ ሰዎች ነጋዴዎች አይባሉም፡፡

(2) አንድ ሰው በአነስተኛ መጠን ሰራ የሚባለው ሥራውን ብቻውን ወይንም ከሦስት ተቀጣሪ ሠራተኞች ወይም ሥራ ተለማማጅ ሠራተኞች በላይ ሳይኖረው የሚሠራ እና ሥራውን ለማካሄድ ከሚያስፈልገው ውጪ ግብዓት ሳያከማች ያካበተውን ልምድ ወይንም በትምህርት ያገኘውን ዕውቀት ወይንም ደግሞ ሁለቱንም በመጠቀም ሥራውን የሚሠራ ሲሆን ነው፡፡

(3) በአነስተኛ ደረጃ ሥራን የሚያከናውኑን በሚመለከት ዝርዝር ሕግ ሊደነገግ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 7 የእጅ ሥራ ጥበበኞች**

(1) ነጋዴዎችን የሚመለከቱ የዚህ ሕግ ማናቸውም ድንጋጌዎች በእጅ ሥራ ጥበበኞች (በዕደ-ጥበብ ባለሙያዎች) ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም፡፡

(2) የዕደ-ጥበብ ባለሙያዎች ማለት የእጅ ጥበብ ሙያ ኖሮአቸው ብቻቸውን ወይም በቤተሰብ አባላት እየተደገፉ ከሦስት ተቀጣሪ ሠራተኞች ወይም ተለማማጅ ሠራተኞች በላይ ሳይኖራቸው የሚሰሯቸውን ሥራዎች ለመሥራት ከሚያስፈልጋቸው መጠን በላይ ግብዓት(ጥሬ ዕቃ) ሳያከማቹ እንደዚህ ያለውን ራሱን የቻለ ሥራ እያከናወኑ በእጅ ሥራቸው ብቻ የሚኖሩ ሰዎች ናቸው፡፡

(3) የእጅ ስራ ጥበበኞች ሥራቸውን በአመዛኙ በእጃቸው እተጠቀሙ የሚሠሩ ሲሆኑ፤እንደ ሁኔታው በአነስተኛ መሣሪያ(ማሽን) ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡

(4) የእጅ ጥበበኞችን ሥራ የሚመለከት ልዩ ሕግ ሊወጣ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 8 የእርሻና የደን ማልማት ሥራዎች**

(1) በዚህ ሕግ በአንቀጽ (5) በንኡስ አንቀጽ (4) እና (5) ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማናቸውም ከእርሻ፣ ከደን ማልማት፣ ከችግኝ ማብቀል፤ ከእንስሳት ማርባት ጋር ወይንም የግጦሽ ሣር ከማሳደግ ጋር የተያያዙ ስራዎችን የሚሰሩ እና ከሚጠቀሙበት መሬት ያገኟቸውን ምርቶች የሚሸጡ ወይም ከሚጠቀሙበት መሬት ባገኙት አላባ እየቀለቡ ያረቧቸውን እንስሳት የሚሸጡ ሰዎች፤ እንዲሁም የዘወትር ልማድ መሠረት በማድረግ ከሚያለሙት ወይም ከሚያዙበት መሬት ላይ ያገኙትን ሰብል ወይም የእንስሳት ተዋኦዎችን አቀናብረው የሚሸጡ ሰዎች ነጋዴዎች አይባሉም፡፡

(2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተዘረሩትን ሥራዎች ግለሰቦች፣ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ወይም መሰል ማኅበራት ቢሠሩም ነጋዴዎች አያሰኛቸውም፡፡

**አንቀጽ 9 ስለ ንግድ ማኅበሮች**

(1) በመመሥረቻ ጽሑፋቸው መሠረት ወይም በተግባር ማናቸውንም በዚህ ሕግ አንቀጽ **(5)** የተገለጹትን ሥራዎች የሚሠሩ የንግድ ማህበሮች ዓይነተኛ የንግድ ጠባይ ያላቸው ማኅበሮች ናቸው፡፡

(2) የአክሲዮን ማኅበሮችና ኃላፊነታቸው የተወሰነ የግል ማኅበሮች ዓላማቸው ምንም ዓይነት ቢሆን ዓይነተኛ የንግድ ማኅበሮች ናቸው፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## የንግድ ሥራ ለመሥራት ችሎታ ስለሌላቸው ሰዎች

### አንቀጽ 10 ችሎታ የሌላቸው ሰዎች

(1) አግባብ ባለው ሕግ ድንጋጌ መሠረት ችሎታ የሌላቸው ሰዎች ማንኛውንም የንግድ ሥራ መሥራት አይፈቀድላቸውም፡፡

(2) በዚህ ሕግ በአንቀጽ **12 እና 13** የተደነገገው ተፈፃሚ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ እነዚህ ችሎታ የሌላቸው ሰዎች የንግድ ሥራ ቢሠሩ ነጋዴ አይሆኑም፤ የሠሩትም ሥራ በሕግ መሠረት ፈራሽ እንዲሆን መጠየቅ ይቻላል፡፡

### አንቀጽ 11 ስለ ሞግዚት

አግባብ ባለው ህግ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ሞግዚት የሆነ ሰዉ አካለ መጠን ባልደረሰው ሰው ስምና ስለእርሱ ሆኖ የንግድ ሥራ ሊሠራ አይችልም፤ ይህ ድንጋጌ በፍርድ ለተከለከለ ሰው ሞግዚትም የጸና ይሆናል፡፡

### አንቀጽ 12 በሞግዚት ከመተዳደር ነጻ ስለወጣ አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ

አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት ከሞግዚት አስተዳደር ነጻ የወጣ አካለ መጠን ያላደረሰ ልጅ የንግድ ሥራ ሊሠራ ይችላል፡፡

### አንቀጽ 13 አካለ መጠን ያላደረሰ መሆኑ በሦስተኛ ወገኖች ላይ የሚያስከትለው ውጤት

የዚህ ሕግ አንቀጽ 103 እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ተቃራኒ ድንጋጌ ቢኖርም እንኳን አንድ የንግድ ሥራ የሚሠራ አካለ መጠን ያላደረሰ ልጅ አካለ መጠን እንደደረሰ አድርጎ ራሱን በንግድ መዝገብ አስገብቶ ከተገኘ፤አካለ መጠን ያላደረሰ መሆኑን ምክንያት አድርጎ በሦስተኛ ወገኖች ላይ መከራከሪያ ሆኖ ሊቀርብ አይችልም፡፡

### አንቀጽ 14 በፍርድ የተከለከለ መሆንን ስለማስታወቅ

በዚህ ሕግ አንቀጽ 103 የተደነገገው ቢኖርም በፍርድ የተከለከለ ሰው መሆኑ በንግድ መዝገብ ካልገባ በቀር በሦስተኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ሊሆን አይችልም፡፡

## ምዕራፍ አራት

## የተጋቡ ሰዎች ስለሚያደርጉት የንግድ ሥራ

### አንቀጽ 15 ያገቡ ሰዎች የንግድ ሥራ ለመሥራት ስላላቸው መብት

አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ባል ወይም ሚስት ካልተቃወመ በቀር ያገባ ሰው ልክ እንዳላገባ ሰው ሁሉ የንግድ ሥራ መሥራት ይችላል፡፡

### አንቀጽ 16 መቃወሚያውን ስለማስታወቅ

(1) በባልና ሚስት መካከል በአንቀጽ 15 መሠረት የሚደረገው መቃወሚያ ለሚነግደው ባል ወይም ሚስት እንዲደርሰው ለማድረግ በማናቸውም መንገድ ማስታወቅ ይቻላል፡፡

(2) እንደዚህ ያለው መቃወም በንግድ መዝገብ ካልገባ በቀር ሦስተኛ ወገኖችን መቃወሚያ ሊሆን የሚችለው ተቃውሞው መኖሩን በሚያውቁ ሰዎች ላይ ነው፡፡

**<u>አንቀጽ 17 መቃወሚያውን ስለማንሳት</u>**

(1) የሚነግደው ባል ወይም ሚስት ተቃውሞው የቤተሰቡን ጥቅም የሚጎዳ መስሎ የታየው እንደሆነ መቃወሚያው እንዲነሣለት ጉዳዩን ለሽምግልና ዳኞች ማቅረብ ይችላል፡፡

(2) የሽምግልና ዳኞች መቃወሚያው እንዲነሣ ከወሰኑ ተቃውሞው የተነሣለት ነጋዴ ባል ወይም ሚስት ይህንኑን በንግድ መዝገብ እንዲገባ ማድረግ አለበት፡፡

**<u>አንቀጽ 18 የሚነግደው ባል ወይም ሚስት ስለተዋዋለው ዕዳ</u>**

የሚነግደው ባል ወይም ሚስት የተዋዋለው ዕዳ እንደ ባልና ሚስት የጋራ ዕዳ ተቆጥሮ ከባል ወይም ከሚስት የግል ንብረትና የጋራ ንብረት እንዲከፈል ሊጠየቅ ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 19 መቃወሚያው ስለሚኖረው ውጤት</u>**

በዚህ ሕግ በአንቀጽ 15 መሠረት ባል ወይም ሚስት ያቀረበው መቃወሚያ በደንቡ መሠረት በንግድ መዝገብ የገባ እንደሆነ ወይም አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ (2) በሚደነግገው መሰረት መቃወሚያው መኖሩ የታወቀ ከሆነ የሚነግደው ባል ወይም ሚስት ዕዳ የሚከፈለው ከዚሁ ሰው የግል ንብረት ላይ ብቻ ነው፡፡

**<u>አንቀጽ 20 ባልና ሚስት ተባብረው ስለሚሠሩት ሥራ</u>**

አንዱ ለሌላው ሠራተኛ መሆኑ ማስረጃ ካልቀረበበት በቀር ባልና ሚስት በአንድነት በሚነግዱበት ጊዜ ሁለቱም ነጋዴዎች ናቸው ተብለው ይቆጠራሉ፡፡

## <u>ምዕራፍ አምስት</u>

## <u>የንግድ ሥራን የመሥራት መብት</u>

**<u>አንቀጽ 21 የንግድ ሥራን የመሥራት ነጻነት</u>**

በሕግ ተለይተው የተከለከሉ ነገሮች ወይም ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር እንዳይደረግ የተደረጉ ውሎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ማንኛውም ሰው ወይም የንግድ ማኅበር ማንኛውንም የንግድ ሥራ የመሥራት መብት አለው፡፡

**<u>አንቀጽ 22 በሕግ ስለ ተከለከሉ ወይም ስለ ተወሰኑ ነገሮች</u>**

(1) አንዳንድ ሰዎች በተወሰኑ የንግድ ሥራዎች ወይም ከሥራቸው ጋር በማይስማሙ የንግድ ሥራዎች እንዳይሠማሩ በሕግ መገደብ ወይም መከልከል ይቻላል፡፡

(2) የተወሰኑ ነጋዴዎችን በተመለከተ ልዩ ሁኔታዎችን (ግዴታዎች) ማለትም እንደ እድሜ፣ የብቃት መመዘኛ፣ ዜግነት ወይም ልዩ ፍቃድ መቀበልን የመሳሰሉትን በሕግ ሊወሰን ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 23 በሕግ የተከለከለውን መተላለፍ ስለሚያስከትለው ውጤት</u>**

(1) በሕግ የተከለከሉትን ወይም ወይም ከያዙት ሥራ ጋራ የማይስማማ በመሆኑ የተከለከለ ሆኖ ሳለ ወይም ሕጋዊ የሆኑትን ልዩ ግዴዎችን (ሁኔታዎች) ሳያሟሉ የንግድ ሥራ ሲሠሩ የተገኙ ሰዎች አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

(2) ሆኖም ነጋዴዎች ሆነው የሠሩትን ሥራ የማይጸና ለማድረግ፤ ሕግ ሳይፈቅድ የሠራሁት ነውና አይጸናብኝም ብለው መከራከሪያ ሊያደርጉት አይችሉም፡፡ ነጋዴ የሆነው ሰው ላሉበት ግዴታዎች ሁሉ ተገዳጅ ይሆናሉ፤ ነገር ግን በነጋዴነት ስም ከሦስተኛ ወገኖች ጋራ መደራደር ወይም መከራከር አይችሉም፡፡

**<u>አንቀጽ 24 ስለ ሲቪክ ማኅበሮች</u>**

የገንዘብ ትርፍ ለማግኘት ያልተቋቋሙ ሲቪክ ማኅበሮች የንግድ ሥራ ለመሥራት የሚችሉበት ሁኔታና ውጤቱ በሕግ ሊወሰን ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 25 ስለ ንግድ ማኅበሮች</u>**

የንግድ ማኅበሮች እንዲሠሩ ያልተፈቀደላቸውን የንግድ ሥራ ወይም የንግድ ሥራዎችን ለመሥራት በሕግ አስፈላጊ የሆኑትን ሕጋዊ ግዴታዎች ሳይፈጸሙና ሳያሟሉ ለመሥራት አይፈቀድላቸውም፡፡

**<u>አንቀጽ 26 በመንግሥት ሕግ የሰውነት መብት ስለተሰጣቸው አካላት</u>**

የመንግሥት አስተዳደር ፣ ወይም የሃይማኖት ወይም ሌሎች የሕዝብ ተቋማት የንግድ ሥራ ለመሥራት ስለሚችሉበት ሁኔታና ውጤቱ በሕግ ሊወሰን ይችላል፡፡

## <u>ርዕስ ሁለት</u>

## <u>የንግድ ረዳቶች እና ወኪሎች</u>

### <u>ምዕራፍ አንድ</u>

### <u>ስለ ንግድ ሠራተኞች</u>

**<u>አንቀጽ 27 ትርጓሜ</u>**

(1) የንግድ ሠራተኞች ማለት በሥራ ውል መሠረት ለአንድ ነጋዴ ሥራ የተቀጠሩና የጉልበት ሥራ ያልሆነ ሥራ የሚሠሩ የሽያጭ ሠራተኛ፤፣ ጸሐፊ፣ የሒሳብ ሠራተኛ፣ መርማሪ፣ ወይም አስተዳዳሪ በመሆን ከነጋዴው ጋር ተባብረው የሚሠሩና ነጋዴውን የሚያግዙ ሰዎች ናቸው፡፡

(2) የነጋዴው ሠራተኞች ነጋዴዎች አይደሉም፡፡

**<u>አንቀጽ 28 በሥራ ውል ላይ ተፈጻሚ ስለ ሚሆን ህግ</u>**

የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የንግድ ሠራተኞችአግባብ ባለው የአሠሪና ሠራተኛ ሕግ መሠረት ይተዳደራሉ፡፡

**<u>አንቀጽ 29 የግል ንግድ ማቋቋምን ስለ መከልከል</u>**

(1) አንድ የንግድ ሠራተኛ ስለ ራሱም ሆነ ስለ ሦስተኛ ወገን ሆኖ እሱን የቀጠረው ነጋዴ ከሚሠራው የንግድ ሥራ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ሌላ የንግድ ሥራ ለመሥራት አይፈቀድለትም፡፡

(2) ሠራተኛው በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ **(1)** የተደነገገውን ክልከላ ጥሶ በተገኘ ጊዜ ቀጣሪው ኪሣራ መጠየቅ ይችላል፣ የሥራውንም ውል ለመሰረዝ ወይም ውሉን አላድስም ለማለትም በቂ ምክንያት ይሆናል፡፡

(3) በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 2589፤ 2590 እና 2592 በተመለከተው ሁኔታ መሠረት ካልሆነና ነጋዴው በቂ ካሣ ለሠራተኛው ለመክፈል ካልተስማማ በስተቀር ለንግድ ሥራ የተቀጠረው ሠራተኛ የውሉ ዘመን ካለቀ በኋላ ተወዳዳሪ የሚሆን የንግድ ሥራ አይሠራም የሚል የውል ቃል የሥራ ውሉ ውስጥ ማስገባት አይቻልም፡፡

**<u>አንቀጽ 30 ውክልና</u>**

(1) የንግድ ሠራተኞች በግልጽ ወይም በዝምታ በተደረገ ስምምነት የነጋዴው ወኪል ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

(2) የወኪልነቱን ስልጣን መሻር የሠራተኛው የሥራ ውል መሰረዝን ሊያስከትል አይችልም፡፡

**<u>አንቀጽ 31 ዕቃ ለመሸጥ ኀላፊ የሆነ ሠራተኛ ስላለው ሥልጣን</u>**

(1) አንድ ሱቅ ውስጥ ዕቃ ለመሸጥ ኀላፊነት የተሰጠው ሠራተኛ እንደ ሱቁ ባሕሪይና መደበኛ የንግድ እንቅስቃሴ ዕቃዎቹን ለመሸጥና ለመረከብ ውክልና እንዳለው ሆኖ ይቆጠራል፡፡

(2) ለልዩ ሒሳብ እንዲከፈል የተደረገ ካልሆነ በቀር የተሸጡትን የሸቀጦች ዋጋ ለኔ ክፈሉ ማለት ይችላል፡፡

(3) በተለይ ስልጣን ካልተሰጠው ወይም ነጋዴው የፈረመበትን ደረሰኝ ካላቀረበ በቀር ሠራተኛው ከሱቁ ውጭ የዕቃ ሽያጭ ዋጋ እንዲከፈለው ለመጠየቅ አይችልም፡፡

**<u>ምዕራፍ ሁለት</u>**

**<u>ስለ ሥራ አሥኪያጅ</u>**

**<u>አንቀጽ 32 ትርጓሜ</u>**

(1) ሥራ አስኪያጅ ማለት በነጋዴው ስም ሆኖ በውክልና እንዲፈርምና እንዲያስተዳድር በግልፅ ወይም በዝምታ ሥልጣን የተሰጠው ሰው ነው፡፡

(2) ሥራ አስኪያጁ ነጋዴ አይደለም፡፡

**<u>አንቀጽ 33 ሥራ አስኪያጁን ስለ ማስታወቅ</u>**

(1) ነጋዴው ሥራ አስኪያጅ ሲሾም በንግድ መዝገብ እንዲመዘገብ ማድረግ ይገባዋል፡፡

(2) ነጋዴው ሥልጣን የሰጠውን ሥራ አስኪያጅ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሠረት በንግድ መዝገብ ሳያስገባ ቢቀርም ሥራ አስኪያጁ ከተሾመበት ጊዜ ጀምሮ ሥራውን ለማከናወን ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 34 ስለ ሥራ አስኪያጁ ሥልጣን</u>**

(1) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያገናኙት ጉዳዮች ሁሉ ሥራ አስኪያጁ ከንግድ ሥራው ጋር በተያያዘ የሥራ አመራር ስራዎችን ለማካሄድ፤ ስምምነት እና የሚተላለፉ የንግድ ሰነዶችን ለመፈረም ጭምር ሙሉ ሥልጣን እንዳለው ይቆጠራል፡፡

(2) በግልፅ ሥልጣን ካልተሰጠው በስተቀር ሥራ አስኪያጁ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን በመያዣ መስጠት፣ መሸጥ ወይም መለወጥ፣ የንግዱን መደብር መሸጥ፣ ማከራየት ወይም ለዕዳ ማስያዝ አይችልም፡፡

**<u>አንቀጽ 35 ሥልጣን መቀነስ</u>**

(1) የሥራ አስኪያጁን ሥልጣን የአንድ የንግድ ቅርንጫፍ ሥራን ለማስኬድ ብቻ የተወሰነ ለማድረግ ይቻላል፤ ስለሆነም እንደዚህ ያለው የሥልጣን መቀነስ ማስታወቂያ በንግድ መዝገብ ካልገባ በዚህ ሕግ አንቀጽ 103 እንደተመለከተው በሦስተኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ሊሆንባቸው አይችልም፡፡

(2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) ከተመለከተው ውጪ ያለ ማናቸውም የሥልጣን መቀነስ በሦስተኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ሊሆንባቸው አይችልም፡፡

**ምዕራፍ ሦስት**

**<u>ስለ ንግድ ተላላኪዎችና እንደራሴዎች</u>**

**<u>አንቀጽ 36 ስለ ንግድ ተላላኪዎች</u>**

(1) የንግድ ተላላኪዎች ማለት መኖሪያቸው የንግዱ መደብር ዋና መሥሪያ ቤት ባለበት የሆነና ከነጋዴው ጋር በተዋዋሉት የሥራ ውል መሠረት ከነጋዴው ጋራ የሚሠሩ፤ነጋዴው እያዘዛቸው የነጋዴው ደንበኞች በሚገኙበት ቦታ እየተዘዋወሩ በነጋዴው ስምና ምትክ ሆነው ዕቃ የሚያቀርቡ ወይም አገልግሎት የሚሰጡ ሰዎች ናቸው፡፡

(2) ሌላ የውል ቃል ከሌለ በቀር የንግድ ተላላኪዎች የተዋዋሏቸው ውሎች ነጋዴው እንዲያጸድቃቸው ለእርሱ መቅረብ አለባቸው፡፡

(3) የንግድ ተላላኪዎች ነጋዴዎች አይደሉም፡፡

(4) የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የውጭ አገር የንግድ ተላላኪነትን በሚመለከት ዝርዝሩ አግባብ ባለው ሕግ ይወሰናል፡፡

**አንቀጽ 37 ስለ ንግድ እንደራሴዎች**

(1) የንግድ እንደራሴዎች ማለት መኖሪያቸው የወካዩ ነጋዴ የንግድ መደብር ዋና መሥሪያ ቤት ባለበት ሥፍራ ያልሆነና ከነጋዴው ጋራ በተዋዋሉት የሥራ ውል መሠረት ነጋዴው እንዲሠሩ እያዘዛቸው በተወሰኑ ቦታዎች ብቻ የነጋዴው ደንበኞችን እየጎበኙ በነጋዴው ስምና ምትክ ሆነው ዕቃ የሚያቀርቡ ወይም አገልግሎት የሚሰጡ ሰዎች ናቸው፡፡

(2) ሌላ የውል ቃል ከሌለ በቀር የንግድ እንደራሴዎች የተዋዋሏቸው ውሎች ነጋዴው እንዲያጸድቃቸው አስፈላጊ ሳይሆን ነጋዴው የሚገደድባቸው ይሆናሉ፡፡

(3) የንግድ እንደራሴዎች ነጋዴዎች አይደሉም፡፡

(4) የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የውጭ አገር የንግድ እንደራሴነትን በሚመለከት ዝርዝሩ አግባብ ባለው ሕግ ይወሰናል

**አንቀጽ 38 የግል ንግድ**

(1) በሥራ ውላቸው ውስጥ ስምምነት ካላደረጉ በቀር የንግድ ተላላኪዎችና የንግድ እንደራሴዎች ስለ ራሳቸውም ሆነ ስለሌላ ሦስተኛ ወገን ሆነው እነሱን የቀጠራቸው ነጋዴ ከሚሠራው የንግድ ሥራ ጋራ ተመሳሳይ የሆነ የግል ንግድ ሊነግዱ አይችሉም፡፡ የግል ንግድ ሲነግዱ በተገኙ ጊዜ በዚህ ሕግ አንቀጽ 40 እና 41 የተነገረውን ክፍያም ሆነ ካሣ መከፈል መብታቸውን ያጣሉ፡፡

(2) የንግድ ተላላኪዎችና የንግድ እንደራሴዎች የግል ንግድ እንዲነግዱ በተፈቀደላቸው ጊዜ በዚህ ሕግ በአንቀጽ 29(2) የተጻፈው ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 39 ለሌሎች ነጋዴዎች ተተክቶ ስለ መሥራት**

(1) ተቃራኒ የውል ቃል ከሌለ በቀር የንግድ ተላላኪዎችና እንደራሴዎች በውል ግዴታ ለገቡለት ነጋዴ ብቻ እንጂ ስለሌሎች ነጋዴዎች ተተክተው መሥራት አይችሉም፡፡ለሌሎች ነጋዴዎች ተተክተው ሲሠሩ በተገኙ ጊዜ በአንቀጽ 40 እና 41 የተደነገገውን ካሣ የመከፈል መብታቸውን ያጣሉ፡፡

(2) በምንም አኳኋን ቢሆን ግዴታ የገቡለት ነጋዴ ከሚሸጠው ዕቃ ወይም ከሚሰጠው አገልግሎት ጋራ ተመሳሳይ የሆነ ዕቃ ለመሸጥ ወይም አገልግሎት ለመስጠት ለሌላ ነጋዴ ተተክቶ ለመሥራት አይፈቀድላቸውም፡፡

**አንቀጽ 40 ስለ ክፍያ**

(1) የንግድ ተላላኪዎችና የንግድ እንደራሴዎች የሚከፈላቸው በደመወዝ ወይም በኮሚሽን ወይም ሁለቱንም በማጣመር ሊሆን ይችላል፡፡

(2) ክፍያቸው በሥራ ውላቸው መሠረት ያልተወሰነ እንደሆነ በልማድ መሠረት ይወሰናል፡፡

**አንቀጽ 41 ውል እንዳይቀጥል በተሰረዘ ጊዜ ስለሚያገኙት ካሣ-**

(1) የንግድ ተላላኪዎችና የንግድ እንደራሴዎች ውላቸው ላልተወሰነ ጊዜ የሆነ እንደሆነና ነጋዴው ያለበቂ ምክንያት ውሉን በሰረዘ ጊዜ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ካሣ የማግኘት መብት አላቸው፡፡

(2) ማናቸውም የንግድ ተላላኪዎች ወይም የንግድ እንደራሴዎች አንዳች ጥፋት ሳያደርጉ ላልተወሰነ ጊዜ የተዋዋሉትን ውል ነጋዴው የሰረዘው፤ወይም ለተወሰነ ጊዜ የተዋዋሉትን ውል ነጋዴው ሳያድስላቸው የቀረ እንደሆነ ባቀረቡአቸው ደንበኞች ወይም ባስገኙት ወይም ባስፋፉት ገበያ ወይም ባስገኙት ወይም በተገኘው ጥቅም ልክ ካሣ የማግኘት መብት አላቸው፡፡

## ምዕራፍ አራት

## ስለ ንግድ ወኪሎች-

### አንቀጽ 42 ትርጓሜ

(1) የንግድ ወኪል ማለት ከነጋዴው ጋር ለመሥራት በሥራ ውል የተቀጠረ ሳይሆን ራሱን ችሎ የሚሠራ፤ በተወሰነ ስፍራ ሁኖ ወይም ለተወሰኑ የነጋዴው ደምበኞች ሁልጊዜ የነጋዴው እንደራሴ ሊሆን በነጋዴው ስም እና ምትክ እንዲሰራ ወይም ውል እንዲዋዋል ውክልና የተሰጠው ሰው ወይም የንግድ ማኀበር ነው፡፡

(2) በውክልና ስምምነቱ በተለየ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር የንግድ ወኪሉ ስለ ነጋዴው ሁኖ የተዋዋላቸው ውሎች በነጋዴው መጽደቅ ሳያሻቸው የጸኑ ናቸው፡፡

(3) የንግድ ወኪል የውክልና ሥራ እየሠራ የደላላነትም ሥራ መሥራት ይችላል፤ ለሁሉም ቢሆን ነጋዴ ይባላል፡፡

### አንቀጽ 43 የንግድ ወኪል ብቸኛ ወኪል ስለመሆኑ

በውክልናው ውል ውስጥ በተለየ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር አንድ የንግድ ወኪል በውሉ በተገለጸው ስፍራ የወካዩ ብቸኛ ወኪል ነው፡፡

### አንቀጽ 44 የንግድ ወኪል ግዴታዎች

(1) የንግድ ወኪል መልካም ነጋዴ የሚያደርገውን ጥንቃቄ ሁሉ በማድረግ የወካዩን ጥቅም በትጋት መጠበቅ ይገባዋል፡፡

(2) ከዚህ የሚከተሉትንም ይፈጽማል፤

(ሀ) የወካዩን ትእዛዞች ሁሉ ይፈጽማል፡፡

(ለ) የተዋዋላቸውን ውሎች ወይም ሊዋዋል የተነጋገረባቸውን ውሎች ሁሉ ለወካዩ ያሳውቃል፡፡

(ሐ) ስለ ሥራው በየጊዜው ለወካዩ ሪፖርት ያደርግለታል፤ እንዲሁም በሚሠራበት ሥፍራ ስላለው የገበያ ሁኔታ ጠቃሚ የሆኑትን መረጃዎች ሁሉ ያስታውቀዋል፡፡

(3) የውክልናው ውል ከተፈጸመ በኋላም ቢሆን የንግድ ወኪሉ ወካዩ የገለጸለትን የንግድ ምስጢር ወይም ወኪል ሆኖ ሲሠራ ያወቃቸውን የንግድ ምስጢሮች ማውጣት ወይም ሊጠቀምባቸው አይችልም፡፡

**አንቀጽ 45 ተመሳሳይ የግል ንግድ ማቋቋም ክልክል ስለ መሆኑ**

(1) አንድ የንግድ ወኪል ወካዩ ከሚሰራቸው ንግዶች ጋራ የማይመሳሰሉትን ማናቸውንም የግል ንግድ ሊነግድ ይችላል፡፡ ነገር ግን ወካዩ ከሚሠራው ንግድ ጋራ የሚመሳሰል የንግድ ሥራ ለመሥራት አይችልም፡፡ ወኪሉ ይህንን ክልከላ በጣሰ ጊዜ የውክልናው ስምምነት እንዲሰረዝ ይደረጋል፤ኪሣራም እንዲከፍል ይጠየቃል፡፡

(2) በውክልና ውል ሌላ ስምምነት ካላደረጉ በቀር አንድ የንግድ ወኪል በተወከለበት ስፍራ ወካዩ ከሚሠራቸው የንግድ ሥራዎች ጋራ ተመሳሳይ የንግድ ሥራዎች ለማይሠሩ ለሌሎች ነጋዴዎች ወኪል ሊሆን ይችላል፡፡

(3) በምንም ሁኔታ ቢሆን አንድ የንግድ ወኪል፤ ወኪል በሆነበት ስፍራ ወካዩ ከሚሰራቸው የንግድ ሥራዎች ጋር ተመሳሳይ የሆኑ የንግድ ሥራዎች ለሚሰሩ ነጋዴዎች ወኪል ሆኖ መሥራት አይፈቀድለትም፤ ይህን ክልከላ ጥሶ የተገኘ የንግድ ወኪል ውሉ ተሰርዞ ኪሣራም እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

**አንቀጽ 46 የወካዩ ግዴታዎች**

ወካዩ በተቻለው መጠን የወኪሉ ሥራ የተቃና እንዲሆንለት የሚቻለውን ሁሉ ያደርግለታል፤ መረጃዎችና የዕቃ ዐይነቶች እንዲደርሱት ያደርጋል፡፡

**አንቀጽ 47 ወጪዎችን ስለ መከፈል**

ሌላ ስምምነት ካላደረጉ በቀር በወኪልነት ለሚመራው ሥራ የተደረጉትን መደበኛ ወጪዎችና ለአንዳንድ ጉዳይ የተደረገውን ወጪ ወኪሉ ይከፈለኝ ብሎ ለመጠየቅ መብት የለውም፤ ሆኖም ወኪል አድራጊው ላሠራቸው ሥራዎች ወኪሉ የከፈላቸውን ገንዘብ እንዲሁም በወኪል አድራጊው ትእዛዝ ያወጣቸውን ልዩ ወጪዎች ወኪል አድራጊው ለወኪሉ ሊከፍለው ይገባል፡፡

**አንቀጽ 48 ስለ አበል**

(1) አንድ የንግድ ወኪል በእርሱ አማካይነት ለተነጋገራቸው ወይም ለፈጸማቸው ሥራዎች (ንግዶች) ሁሉ አበል ሊከፈለው ይገባል፤ ሌላ ውሳኔ ከሌለ በቀር እርሱ በተወከለበት ቦታ ወይም በውክልና ውሉ ከተሸፈኑ የነጋዴው የተወሰኑ ደንበኞች ጋር ወካዩ ቢሆን ወይም የወካዩ ሌላ ወኪል ቢሆን ለፈጸሙዋቸው ሥራዎች አበል የመቀበል መብት አለው፡፡

(2) የንግዱ ወኪል ለተዋዋላቸውና ለጨረሳቸው ውሎች ወኪል አድራጊው በአደረገው ነገር ምክንያት ፍጻሜ ያላገኙ ቢሆኑም አበሉ ለወኪሉ ሊከፈለው ይገባል፡፡ ሆኖም ውሎቹ በወካዩ በኩል ፍጻሜ ያላገኙት በወኪሉ ጥፋት የሆነ እንደሆነ ወኪሉ አበል የማግኘት መብቱን ያጣል፡፡

(3) የአበሉ ክፍያ በውክልናው ውላቸው መሠረት ይወሰናል፤ ውል ከሌለ በልማድ መሠረት ይወሰናል፡፡

**አንቀጽ 49 ወኪሉ ሥራውን ራሱ መፈጸም የሚገባው ስለ መሆኑ**

የውክልና ውል የሚደረገው የወኪሉን የግል ብቃት ወይም ችሎታ በመገንዘብና መሠረት በማድረግ ስለሆነ አንድ የንግድ ወኪል የውክልናውን ውል ለሌላ ሰው ማሳለፍ ወይም በእርሱ ምትክ ሌላ ሦስተኛ ወገን መተካት አይፈቀድለትም፡፡

**አንቀጽ 50 የውክልና ውልን ስለማቋረጥ**

(1) የንግድ ውክልና የሚቋረጠው፤

(ሀ) ተስማምተው የወሰኑት የውል ዘመን ሲኖር፤የውሉ ዘመን ሲያበቃ፤

(ለ) ለነጋዴው ወኪል የሆነው ሰው ሲሞት፣ ችሎታ ሲያጣ ወይም ሲከሥር፤

(ሐ) ወኪል ሆኖ ሲሠራ የነበረው የንግድ ማህበር ሲፈርስ፤

ነው፡፡

(2) ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የውክልና ውል ከሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች አንደኛው ማስጠንቀቂያ በመስጠት ሊያቋርጠው ይችላል፡፡ ለውክልና መቋረጥ በቂ ምክንያት ካለ ማስጠንቀቂያ መስጠት አያስፈልግም፡፡

(3) የማስጠንቀቂያው ጊዜ በውክልናው ውል ይወሰናል፡፡ ይህ በሌለ ጊዜ በልማድ ይወሰናል፡፡ በመጀመሪያው ዓመት ውስጥ ሲሆን ካንድ ወር የማያንስና ከመጀመሪያው ዓመት በኋላ ሲሆን ከሁለት ወር የማያንስ መሆን አለበት፡፡

**<u>አንቀጽ 51 ውል ሲቋረጥ ስለሚከፈል ካሣ</u>**

ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገን የውክልና ውል ወካዩ ያለ በቂ ምክንያት ያቋረጠ እንደሆነ ወኪሉ በወካዩ ስም ሆኖ ያገለገለበት ጊዜ፤ያቀረባቸው (ያመጣቸው) ደንበኞች፤ወይም የፈጠረው ወይም ያስፋፋው ገበያ ወይም መልካም ስም ወይም ሌሎችም እነዚህን የመሳሰሉ የሰጣቸው ፍሬዎች ታስበው በርትዕ የሚገባ ካሣ የማግኘት መብት አለው፡፡

**<u>አንቀጽ 52 ውሉ በተቋረጠበት ጊዜ ያልተጠናቀቁ ሥራዎች</u>**

(1) የውክልና ውል በሚቋረጥበት ጊዜ ሁሉ ወኪል ሆኖ ሲሰራ የነበረ ሰው ወይም ወራሹ ወይም የንግድ ማህበር ውሉ ከመቋረጡ በፊት ለተደራደራቸው ወይም ለጨረሳቸው (ለተዋዋላቸው) ውሎች ሁሉ አበል ሊከፈለው ይገባል፡፡

(2) ውሉ እንደተቋረጠ ማናቸውም አበሎችና የሚከፈሉ ወጪዎች ወካዩ ወዲያውኑ መክፈል አለበት፡፡

**<u>አንቀጽ 53 የውክልና ውል ከተቋረጠ በኋላ ተመሳሳይ የግል ንግድ ሥራ መስራት ስለ ሚከለከልበት ሁኔታ</u>**

(1) የውክልና ውሉ ከተቋረጠ በኋላ የንግድ ወኪሉ ወካዩ ከሚሠራው የንግድ ሥራ ጋራ ተመሳሳይ የሆነ የንግድ ሥራ በግሉ እንዳይሠራ ወይም ከወካዩ የንግድ ሥራ ጋራ ተመሳሳይ የሆነ ንግድ ለሚነግድ ነጋዴ ወኪል ወይም እንደራሴ ሆኖ እንዳይሰራ በውክልና ውል ውስጥ ስምምነት ሊደረግ ይቻላል፡፡

(2) ተቃራኒ ስምምነት ቢኖርም እንኳን ክልከላው የሚጸናው በጽሑፍ የተደረገ እንደሆነ፤ ክልከላው ተፈጻሚ የሚሆንበት ስፍራን ወይም የነጋዴውን ደንበኞች ወይም ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች በግልጽ ለይቶ ያሰቀመጠ እንደሆነ፤ለወኪሉ ተገቢ ካሣ የተቆረጠ እንደሆነ እና ክልከላውም ከሦስት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ የተደረገ እንደሆነ ነው፡፡

**ምዕራፍ አምስት**

**<u>ስለ ደላሎች</u>**

**<u>አንቀጽ 54 ትርጓሜ</u>**

(1) ደላሎች ማለት ውል የሚዋዋሉ ሰዎችን ይልቁንም እንደ ሺያጭ፤ኪራይ፤ኢንሹራንስ፤የማመላለሻ ውል እንደዚህ ያሉትን ውሎች የሚዋዋሉ ሰዎችን ፈልገው የሚያገናኙና የሚያዋውሉ፤ራሱን የቻለ የሙያ ተግባራቸው አድርገው ጥቅም ለማግኘት የሚሠሩ ሰዎች ወይም ይህንኑ የደላላነት ሥራ የሚሠራ የንግድ ማኅበር ነው፡፡

(2) ደላሎች አስማሚ ሆነው የሚያስፈጽሚቸው ውሎች ዓይነትና ግብ ወይም የሚያገናኙዋቸው ሰዎች ማንነት ወይም ሁኔታ ሳይታይ ነጋዴዎች ይባላሉ፡፡

(3) ደላላ ሁለቱም ተስማሚዎች በውላቸው በግልጽ ያስቀመጡት ድንጋጌ ከሌለ በስተቀር ሁለቱን ተስማሚዎች በመወከል እነሱን ተክቶ ገንዘብ ለመቀበልም ሆነ ማንኛውንም ወደ ተግባር የሚያስገባ እንቅስቃሴ ማድረግ የለበትም፡፡

## አንቀጽ 55 ለተዋዋዮች ስለ ማስታወቅ

(1) በልማድ የታወቀ ካልሆነ ወይም ሌላ ስምምነት ካልተደረገ በቀር ተዋዋዮቹ በጉዳዩ ውል ለማድረግ የተስማሙ እንደሆነ ውሉ የሚደረግበትን ሁኔታ ለተዋዋዮች ሁሉ ወዲያውኑ ደላላው ማስታወቅ አለበት፡፡

(2) በልማድ የታወቀ ካልሆነ ወይም ሌላ ስምምነት ከሌለ በቀር በዚህ ዓይነት የተዘጋጀውን ውል ባለጉዳዮቹ ካላጸደቁት በቀር በእነርሱ ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

## አንቀጽ 56 ስለ ደላላው ኀላፊነት

ደላላው በሁለቱም ወገኖች ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት ኀላፊ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 57 ስለ ደላላው አበል

(1) ደላላው አስማሚ ሆኖ ውሉን ካስጨረሰ (ካዋዋለ) በኋላ ወሉ ቢፈጸምም ባይፈጸምም አበል ሊከፈለው ይገባል፡፡

(2) በልማድ የታወቀ ካልሆነ ወይም ሌላ ስምምነት ካልተደረገ በቀር አበሉን የሚከፍለው የደላላውን አገልግሎት የጠየቀው ወገን ብቻ ነው፡፡

(3) አበሉ በስምምነቱ ውስጥ ይወሰናል፤ወይም ባልተወሰነበት ጊዜ በልማድ መሠረት ይቆረጣል፤የተስማሙበት አበል ከባድ መስሎ ሲታየው ወይም ደላላው ከሰጠው አገልግሎት ጋራ ተመዛዛኝ አለመሆኑ ሲታየው ፍርድ ቤቱ ለመቀነስ ሥልጣን አለው፡፡

(4) ደላላው ለደምበኛው (አገልግሎቱን ለጠየቀው ወገን) ያሉበትን ግዴታዎች ተላልፎና ይልቁንም የደምበኛውን ጥቅም በሚጎዳ አኳኃን ለሌላ ሦስተኛ ወገን ጥቅም የሠራ እንደሆነ ወይም ደምበኛው ሳያውቅ ከሦስተኛው ወገን ክፍያ የተቀበለ እንደሆነ አበል የማግኘት መብቱ ቀሪ ይሆናል፡፡

## ምዕራፍ ስድስት

## ስለ ኮሚሽን ወኪሎች

**አንቀጽ 58 ትርጓሜ**

(1) የኮሚሽን ወኪል ማለት ራሱን ችሎ፤ የሞያ ተግባሩ አድርጎ፤ ጥቅም ለማግኘት ስለ ወኪሉ ሆኖ በራሱ ስም ሸቀጦችን ወይም የሚንቀሳቀሱ ዕቃዎችን ወይም እነዚህን የመሳሰሉ ማናቸውንም ንብረቶችን በስሙ የሚገዛ ወይም የሚሸጥ ወይም ስለ ወኪሉ ሆኖ በስሙ የመጓጓዣ ውል የሚዋዋል ሰው ወይም የንግድ ማኅበር ነው፡፡

(2) የኮሚሽን ወኪል የሚያዋውላቸው ተዋዋይ ወገኖችና የውሎቹ ዐይነትና ግብ እግምት ውስጥ ሳይገባ ነጋዴ ይባላል፡፡

**አንቀጽ 59 የፍትሐ ብሔር ሕግ ተፈጻሚ ስለመሆኑ**

በፍትሐ ብሔር ሕግ በቁጥር 2234-2352 የተጻፉት ድንጋጌዎች በኮሚሽን ወኪል ውል ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

**አንቀጽ 60 ስለ አክስዮን ደላሎች**

(1) በአክሲዮን ገበያ የሚሠሩ ደላሎች የኮሚሽን ወኪል ናቸው፡፡

(2) በሌላ ሕግ በልዩ ሁኔታ ካልተደነገገ በቀር የአክስዮን ደላሎች በኪሚሽን ወኪል ደንብ ይተዳደራሉ፡፡

## ርዕስ ሦስት

## ስለ ሒሳብ

### ምዕራፍ አንድ

### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ 61 ሒሳብ መያዝ ግዴታ ስለ መሆኑ**

ማንኛውም የንግድ ሥራ የሚሠራ ነጋዴ ወይም የንግድ ማኅበር እንደሚሠራው የንግድ ሥራ ስፋትና ዓይነት በንግድ ሥራ ልምድና ደንብ መሠረት የሚያስፈልግ የሒሳብ መዝገቦችና ሰነዶች ሊኖሩት ይገባል፡፡

**አንቀጽ 62 ስለ አነስተኛ ንግድ ነጋዴዎች**

(1) የአነስተኛ ንግድ ነጋዴዎች የሒሳብ መዝገብ ከመያዝ ነጻ ናቸው፡፡

(2) የአነስተኛ ንግድ ሥራ አሰራር እና የካፒታል መጠን በሕግ ይወሰናል፡፡

**አንቀጽ 63 ነጋዴዎች መያዝ ስለሚገባቸው የሒሳብ መዝገቦችና ሰነዶች**

ነጋዴዎች መያዝ ስለሚገባቸው የሒሳብ መዝገቦችና ሰነዶች እንዲሁም ስለ ሒሳብ መዝገብ አያያዝ ደንቦች ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

**አንቀጽ 64 የንግድ ማኅበሮች ልዩ ደንቦች**

ስለ ንግድ ማኅበሮች በዚህ ሕግ በሁለተኛው መጽሐፍ የተነገሩት ልዩ ደንቦች የተጠበቁ ናቸው፡፡

**አንቀጽ 65 የሒሳብ መዝገቦችን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ስለ መመዝገብ**

(1) ነጋዴዎች አጠቃላይ የሒሳብ እንቅስቃሴያቸውን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ መመዝገብ ይችላሉ፡፡
(2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ(1) መሠረት የሚያዙ የሒሳብ መዝገቦች ልክ በእጅ ጽሑፍ የሚያዙ የሒሳብ መዝገቦች ወይም የማመዛዘኛ ሒሳብ መዝገቦች ማሟላት የሚገባቸውን ወይም መያዝ ያለባቸውን ፎርማሊቲዎች ማካተት አለባቸው፡፡
(3) በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደረገ ምዝገባ ልክ በጽሑፍ እንደተያዘ ምዝገባ ተቆጥሮ በማንኛውም ጊዜ ነጋዴው እንደ ማስረጃ ሊጠቀምበት ይችላል፡፡

**አንቀጽ 66 የንግድ መዝገቦችን ጠብቆ ስለ ማኖር**

ማንኛውንም የሒሳብ መዝገቦችና የሒሳብ ሰነዶች የመጨረሻው ጽሕፈት ከተጻፈባቸው ቀን ጀምሮ ወይም ሰነዶቹ ከተጻፉበት ቀን አንስቶ ወደፊት ላሉት ዐሥር ዓመታት ድረስ ጠብቆ ማኖር ይገባል፡፡

**አንቀጽ 67 ስለ ወጪና ገቢ ደብዳቤዎች፡፡**

የገቡት ደብዳቤዎች፤መልዕክቶች ወይም ቴልግራሞች ዋናዎቻቸውን፤ እንዲሁም የተላኩት ደብዳቤዎች፤ መልዕክቶች ወይም ቴሌግራሞች ግልባጮቻቸው በፋይል አግብቶ ለዐሥር ዓመታት ድረስ ጠብቆ ማኖር ይገባል፡ ፡

**ምዕራፍ ሁለት**

**የሒሳብ መዝገቦቹን ማስረጃ ስለ ማድረግ**

**አንቀጽ 68 መዝገቦች ስለ ባለመዝገቡ ማስረጃ ስለ መሆናቸው**

ፍርድ ቤቱ በፍትሐ ብሔር ሕግ በቁጥር 2016 የተመለከተውን መመልከት ግዴታ ሳይኖርበት ክርክሩ የተነሳው በነጋዴዎች ወይም በንግድ ማኅበሮች መካከል ስለ ንግዳቸው ጉዳይ ሲሆን ስለ ሒሳብ መዝገቦች አያያዝ በዚህ ሕግ በተጻፉት ደንቦች መሠረት የተዘጋጁ መዝገቦች ከሆኑ የንግድ መዝገቦችን ለባለመዝገቡ ጥቅም በማስረጃነት ሊቀበላቸው ይችላል፡፡

**አንቀጽ 69 መዝገቦች በባለመዝገቡ ላይ ማስረጃ ስለ መሆናቸው**

(1) የንግድ መዝገቦች በባለመዝገቡ ላይ አስረጂ ይሆናሉ፡፡

(2) ስለሆነም  በመዝገቡ ለመጠቀም የሚፈልገው ሰው እሱ ለሚለው ቃል ተቃራኒ የሚሆኑትን ቃሎች ከመዝገቡ ማስቀረት አይችልም፡፡

## ርዕስ አራት
## ስለንግድ መዝገብ

### ምዕራፍ አንድ
### ስለ ንግድ መዝገብ አቋቋም

**አንቀጽ 70 ስለ ፌዴራሉ የንግድ መዝገብ**

(1) የንግድ እና ኢንዱስተሪ ሚኒስቴር አገር አቀፍ ተፈጻሚነት ያለው የፌዴራል የንግድ መዝገብ ያቋቁማል፤ ያስተዳድራል፡፡

(2) ሚኒስቴሩ በዚህ ሕግ መሠረት የነጋዴዎችንና የንግድ ማኀበሮችን ምዝገባ የማከናወን ኃላፊነት አለበት፡፡

(3) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም፤ እንዲሁም በአንቀጽ 71 ሥር ስለ ክልሎች የንግድ መዝገቦች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሚኒስቴሩ የንግድ ምዝገባ ኃላፊነቱን ለሌላ የፌዴራል መንግሥት ተቋም በከፊል በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 71  ስለ ክልሎች የንግድ መዝገቦች**

(1) በዚህ ሕግ በአንቀጽ 70 (1)  እና (2)  የተደነገገው ቢኖርም ክልሎች እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የራሳቸውን የንግድ መዝገብ በማቋቋም የንግድ ምዝገባ ለማከናወን ይችላሉ፡፡

(2) በዚህ አንቀጽ በንኡስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቋቋሙት የክልሎች የንግድ መዝገቦችና አስተዳደራቸው እንዲሁም የንግድ ምዝገባ ለማከናወን ሥልጣን ያለው አካል፤ ኃላፊነትና ተግባር ክልሎች በሚያወጡት ሕግ መሠረት ይወሰናል፡፡

(3) የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ  ቢኖርም የንግድ ምዝገባ የሚያከናውን ማንኛውም የክልል አካል ምዝገባውን ማከናወን ያለበት በዚህ ሕግ በርዕስ አራት ሥር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በጥብቅ በመከተል መሆን አለበት፡፡

**አንቀጽ 72  ስለ ማዕከላዊ የንግድ ምዝገባ የመረጃ ቋት**

(1) የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አገር አቀፍ ተፈጻሚነት ያለው ማዕከላዊ የንግድ ምዝገባ የመረጃ ቋት ያደራጃል፤ ያስተዳድራል፡፡

(2)  የመረጃ ቋቱ በዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተደራጀና በሚኒስቴሩ ድረ-ገጽ በኩል ለሕዝብ ክፍትና ተደራሽ መሆን አለበት፡፡

(3) የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሚከተሉትን ተጨማሪ ተግባራት ያከናውናል፡፡

(ሀ) በየክልሉ ባሉት ልዩ ልዩ መዝገቦች የተጻፉትን የያንዳንዱን የተመዘገበውን

ሰው የሚመለከቱ አስረጂዎች በሙሉ መቀበልና በመረጃ ቋቱ ውስጥ መመዝገብ ወይም ማስገባት፡

(ለ) በዚህ ሕግ በሁለተኛው መጽሐፍ የተነገሩትን ማኅበሮች የሚመለከቱ ጽሑፎች፤ሰነዶች፤ማስታወቂያዎች መቀበልና በመረጃ ቋቱ ውስጥ መዝግቦ ማስቀመጥ፤

(ሐ) ስለ ንግድ መዝገቦች የወጡት ሕጎችና ደንቦች በትክክል መፈጸማቸውን መከታተልና ማረጋገጥ፡፡

**አንቀጽ 73 ስለ ማስታወቅ**

(1) በንግድ መዝገብ አማካኝነት የሚደረግ ማስታወቅ የሚፈፀመው ነጋዴው መዝገብ ለመያዝ ሥልጣን ባለው ኃላፊ ዘንድ ቀርቦ የሚሰጠውን መግለጫ በማስመዝገብ ነው፤በንግድ መዝገቡ የተደረገውም ምዝገባ የጸና የሚሆነው ምዝገባው ከተደረገበት ዕለት ቀጥሎ ካለው የሥራ ቀን ጀምሮ ነው፡፡

(2) በንግድ ማኅበሮች የሚሰጡ መግለጫዎች ምዝገባን በተመለከተ የዚህ ሕግ ሁለተኛው መጽሐፍ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

**አንቀጽ 74 ስለ ኀላፊነት**

የንግድ ምዝገባ የሚያከናውን አካል፣ ሰራተኞቹ ከምዝገባ ጋር በተያያዘ ለሚያደርሱት ጉዳት ከሠራተኞቹ ጋራ ባንድነት እና በነጠላ ተጠያቂ ይሆናል።

**አንቀጽ 75 የንግድ መዝገብ ለሕዝብ ክፍት ስለ መሆኑ**

(1) የንግድ መዝገብ ለሕዝብ ክፍት መሆን አለበት፡፡ማንኛውም ሰው የተወሰነውን ክፍያ ከፍሎ በመዝገብ የገባውን መረጃ ለማየት ወይም ግልባጭ ወይም ከመዝገቡ አጭር የተውጣጣውን ቃል እንዲሰጠው ወይም የሚፈልገው ጉዳይ ያልተመዘገበ ከሆነም አለመመዝገቡን የሚያረጋግጥ ማስረጃ እንዲሰጠው ሥልጣን ያለውን መዝጋቢ መጠየቅ ይችላል፡፡

(2) መዝጋቢው የተጠየቀውን አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

**አንቀጽ 76 በነጋዴው ወረቀቶች ላይ መግባት ስለ ሚያስፈልጉ ነገሮች**

ማናቸውም በንግድ መዝገብ የተመዘገቡ ነጋዴዎች ሁሉ በሚሠሩባቸው ወረቀቶች ላይ ሁሉ የተመዘገቡበትን ቦታ እና የምዝገባ ቁጥራቸውን መግለጽ አለባቸው፡፡

**አንቀጽ 77 የምዝገባ መረጃዎችንና ሰነዶችን ለማዕከላዊ የንግድ ምዝገባ ቋት ስለ ማስተላለፍ**

በዚህ ሕግ መሠረት የንግድ ምዝገባ ያከናወነ ማንኛውም የፌዴራል ወይም የክልል ተቋም የያንዳንዱን የመዘገበውን ነጋዴ ወይም የንግድ ማኅበር የሚመለከቱ መረጃዎችንና ሰነዶችን ምዝገባውን እንዳከናወነ ወዲያውኑ ለማዕከላዊ የንግድ ምዝገባ የመረጃ ቋት የማስተላለፍ ግዴታ አለበት፡፡

**ምዕራፍ ሁለት**

**በንግድ መዝገብ ስለሚገቡ ጉዳዮች**

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ ድንጋጌዎች**

**አንቀጽ 78 በመዝገቡ ስለሚገቡ ጉዳዩች**

ማናቸውም ዋና ወይም ተጨማሪ ወይም ማሚያ ሆነው የሚመዘገቡ፤ እንዲሁም የተደረጉ ለውጦች ወይም የተሰረዙ ጉዳዮች ሁሉ በንግድ መዝገብ መግባት አለባቸው፡፡

**አንቀጽ 79 በመዝገብ የማግባቱ ሥነ ሥርዓት**

(1) በመዝገብ ማስግባት የሚቻው ለመመዝገብ የሚያመለክተው ሰው በጽሑፍ መግለጫውን ባቀረበ ጊዜ ነው፡፡

(2) በመዝገብ የማስግባቱ ተግባርም ሆነ የጽሑፍ መግለጫው ለንግድ ምዝገባ ዓላማ ተብሎ በተለየ ሁኔታ የተዘጋጀና መዝጋቢው አካል በሚያስተዳደረው ድረ-ገጽ በመረጃ መረብ ዓማካይነትም ሊከናወን ይችላል፡፡

(3) ከመዝገቡ ውስጥ የሚሰረዝ ነገር ሲኖር በዚህ ሕግ በአንቀጽ 96 በተመለከተው ባለሥልጣን ሲታዘዝ ሊሰረዝ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 80 የመግለጫውን ቃል ትክክለኛነት ስለመቆጣጠር**

(1) ለመመዝገብ የሚያመለክተው ሰው የሚያቀርበውን የማመልከቻ ቃል ትክክለኛነት መዝጋቢው ማጣራት አለበት፤ አንድ ሰው በነጋዴነት ለመመዝገብ ካመለከተ አመልካቹ ምዝገባ የተጠየቀበትን የንግድ ሥራ ለመሥራት የሚያስችለውን ህጋዊ መመዘኛዎች ሁሉ ያሟላ መሆኑን መዝጋቢው ማረጋገጥ አለበት፡፡

(2) መዝጋቢው በሕግ የታዘዙት ነገሮች ሁሉ በመግለጫው ውስጥ መጻፋቸውን እንዲሁም ለመግለጫው በደጋፊነት የቀረቡለት የጽሑፍ ማስረጃዎች ከመግለጫው ቃል ጋር የሚጣጣሙ መሆኑን ማጣራት አለበት፤

(3) መዝጋቢው አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ሌሎች ተጨማሪ ሰነዶችና መረጃዎች እንዲቀርቡለት አመልካቹን ሊጠይቅ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 81 በመዝጋቢው አካልና በአመልካቹ መካከል ስለሚነሣ ክርክር**

በመዝጋቢው አካልና ለምዝገባ በአመለከተው ሰው መካከል የሚነሳው ማንኛውም ክርክር ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ይወሰናል፡፡

**ክፍል ሁለት**

**ስለ ምዝገባ**

**<u>አንቀጽ 82 በንግድ መዝገብ መመዝገብ ግዴታ ስለ መሆኑ</u>**

(1) በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ የንግድ ሥራ የሚሠራ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም የውጭ አገር ዜጋ ወይም የንግድ ማኅበር መመዝገብ አለበት፡፡

(2) የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ በተለይ በሚከተሉት ሰዎች ላይ ይፈጸማል፡፡

(ሀ) በዚህ ሕግ በአንቀጽ 5 መሠረት ነጋዴ በሆነ በማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም የውጭ አገር ሰው፤

(ለ) በዚህ ሕግ በአንቀጽ 9 በተመለከተው የንግድ ማኅበር ፤

(ሐ) በማናቸውም የንግድ ሥራ በሚሠሩ የውጭ አገር የንግድ ድርጅቶችና በማናቸውም የውጭ አገር መንግሥት የንግድ እንደራሴዎችና ወኪሎች ወይም የመንግሥት ማኅበሮች ወይም ድርጅቶች ላይ፡፡

(3) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2)(ሐ) በተመለከቱት ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ልዩ ደንብ ይወጣል፡፡

**<u>አንቀጽ 83 በንግድ መዝገብ ለመመዝገብ ማመልከቻ ማቅረብ ግዴታ ስለ መሆኑ</u>**

(1) አንድ ሰው በራሱ ወይም በወኪሉ አማካይነት በነጋዴነት ለመመዝገብ ማመልከቻ ካላቀረበ በስተቀር በነጋዴነት ሊመዘገብ አይችልም፡፡

(2) ነጋዴው የንግድ ሥራውን ከመጀመሩ በፊት ማመልከቻውን ማቅረብና መመዝገብ አለበት፡፡

(3) ማመልከቻው በዚህ ሕግ በአንቀጽ 79(2) በተደነገገው መሠረት መዚጋቢው አካል በሚያስተዳደረውና በሚቆጣጠረው ድረ-ገጽ ላይ በመረጃ መረብ አማካይነት ሊቀርብ ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 84 ቀድሞ የተመዘገበውን ነጋዴ ስለ መሰረዝ</u>**

(1) አንድ የንግድ መደብር ከተሸተጠ ወይም ከተከራየ የቀድሞ ነጋዴ ምዝገባ እስካልተሰረዘ ድረስ ገዥው ወይም ተከራዩ ሊመዘገብ አይችልም፡፡

(2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የንግድ መደብሩን የሸጠው ወይም ያከራየው ነጋዴ ከአንድ በላይ የንግድ መደብሮች ያሉት ከሆነ እና የሸጠው ወይም ያከራየው የተወሰኑትን የንግድ መደብሮች ብቻ ከሆነ ነጋዴው ከንግድ መዝገብ አይሰረዝም፡፡ በንግድ መዝገብ ውስጥ ስለተሸጠው ወይም ስለተከራየው መደብር የገባው መረጃ ብቻ ይሰረዛል፡፡

**<u>አንቀጽ 85 ስለ መመዝገቢያ ስፍራ</u>**

(1) ማንኛውም ነጋዴ ወይም የንግድ ማኅበር በንግድ መዝገብ የሚመዘገበው የንግድ ሥራው ዋና መሥሪያ ቤት ባለበት ስፍራ ሥልጣን በተሰጠው መዝጋቢ አካል ነው፡፡ የንግድ ሥራውን ዋና መሥሪያ ቤት አድራሻ የመምረጥ መብት የነጋዴው ነው፡፡

(2) በሕግ በተለየ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር የንግድ ሥራው ዋና መሥሪያ ቤት በውጭ አገር የሆነ ነጋዴ ወይም የንግድ ማኅበር የንግዱ ቅርንጫፍ ወይም ወኪል መሥሪያ ቤት ባለበት ስፍራ ሥልጣን በተሰጠው መዝጋቢ አካል ይመዘገባል፡፡

**<u>አንቀጽ 86 ተደራራቢ ዋና ምዝገባ የተከለከለ ስለ መሆኑ</u>**

(1) ማንም ነጋዴ ወይም የንግድ ማኅበር በተለያዩ ክልሎች የተለያዩ የንግድ ሥራዎችን የሚሠራ እንኳን ቢሆን በዋናነት በንግድ መዝገብ መመዝገብ የሚችለው በአንድ ስፍራ ብቻ ነው፤ በአንድ መዝገብ ውስጥም ከአንድ የበለጠ የምዝገባ ቁጥር ሊሰጠው አይችልም፡፡

(2) ነጋዴው በዋናነት ከተመዘገበበት ቦታ በተጨማሪ በተለያዩ ክልሎች የሚነግድ ከሆነ ወይም ቅርንጫፎች ወይም ወኪል መሥሪያ ቤቶች ካሉት መጀመሪያ የተመዘገበበት ዋናው መዝገብ እየተጠቀሰ በአጭር ቃል በየክልሎቹ መመዝገብ አለበት፡፡

**<u>አንቀጽ 87 ነጋዴው በመጀመሪያ በዋና መዝገብ ሲገባ ማጻፍ ስለ ሚገባው ነገር</u>**

አንድ ነጋዴ መጀመሪያ ዋና ምዝገባ ለማድረግ ማመልከቻ ሲያቀርብ ከዚህ የሚከተሉትን መግለጽ አለበት፡፡

(ሀ) የነጋዴው ሙሉ ስም ከነአያት፤ ካለው የቤተ ዘመድ ስም ጨምሮ፤

(ለ) የተወለደበትን ቀንና ቦታ፤

(ሐ) ዜግነቱን፤

(መ) የግል አድራሻውን፤

(ሠ) አካለ መጠን ያላደረሰ በሆነ ጊዜ የንግድ ሥራ እንዲሠራ ሞግዚቱ የፈቀደበትን ቀን፤

(ረ) ያገባ ከሆነ ጋብቻው የተፈጸበትን ቀንና ቦታ እንዲሁም የጋብቻ ውል መኖር አለመኖሩን፤የጋብቻ ውል ካለ ውሉ የተቀመጠበትን ቦታ ወይም በእጁ የሚገኘውን ሰው ስም፤

(ሰ) የንግዱን ዓላማ፤

(ሸ) ንግዱን ያቋቋመው ወይም የገዛው ወይም የተከራየው እርሱ መሆኑን ፤ኪራይ ከሆነ ያከራዩን ስምና ሌሎች ለምዝገባ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን፤

(ቀ) የንግዱን ስም፤

(በ) የንግዱን ምልክት (ካለው)፤

(ተ) የንግዱ መደብር የሚገኝበትን አድራሻ፤

(ቸ) ነጋዴው በተመዘገበበት ሥፍራ ወይም በሌላ ቦታ ሌሎች የንግድ መደብሮች፤ቅርንጫፎች ወይም ውክልናዎች ያሉት እንደሆነ የሚገኙበትን አድራሻ፤

(ኀ) የቅርንጫፎች ሥራ አስኪያጆች ያሉ እንደሆነ ሥልጣናቸው ቅርንጫፉን በማስተዳደር ብቻ የተወሰነ መሆን አለመሆኑን፤

(ነ) ያለው እንደሆነ ለመነገድ የንግድ ፈቃድ የተሰጠበትን ቀን፡፡

**<u>አንቀጽ 88 የሚመዘገበው በአጭር ቃል በሆነ ጊዜ ሊጻፍ የሚገባው ነገር</u>**

በአጭር ቃል ለመመዝገብ ማመልከቻ የሚያቀርብ ነጋዴ ከዚህ የሚከተሉነት መግለጽ አለበት፡፡

(ሀ) የነጋዴው ሙሉ ስም ከነአያት፤ ካለው የቤተዘመድ ስሙን፤

(ለ) ዜግነቱን፤

(ሐ) የግል አድራሻውን፤

(መ) የንግዱን መደብር፤የቅርንጫፉን ወይም የወኪሉን ስም፤

(ሠ) የንግድ መደብሩ፣ ቅርንጫፉ፤ ወይም ወኪሉ የሚገኝበትን አድራሻ፤

(ረ) የንግዱን ዓላማ፤

(ሰ) የሥራ አስኪያጁን ስምና ሥልጣኑ ቅርንጫፉን በማስተዳደር ብቻ የተወሰነ መሆን አለመሆኑን፤

(ሸ) የንግድ ፈቃድ የተሰጠበትን ቀን፤ ቢኖር፤

(ቀ) በዋናነት የተመዘገበበትን ቦታና የምዝገባ ቁጥሩን፡፡

**አንቀጽ 89. የንግድ ማኅበሮች**

በዚህ ሕግ በሁለተኛው መጽሐፍ የተመለከቱት አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች በንግድ ማኅበሮች ምዝገባ ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## ክፍል ሦስት

## በመዝገብ የገባን መረጃ ስለመለወጥ ወይም ተጨማሪ መረጃ በመዝገብ ውስጥ ስለማካተት

**አንቀጽ 90 የተመዘገበውን ስለ መለወጥ**

(1) ማንኛውም የተመዘገበ ሰው በመዝገብ ውስጥ የገባን መረጃ የሚለውጥ አንድ ሁኔታ (ወይም አድራጎት) ሲከሰት ሁኔታው ከተከሰተበት ቀን አንስቶ ባሉት ሁለት ወራት ውስጥ ከመዘገቡ የገባው መረጃ እንዲለወጥ ማመልከት አለበት፡፡

(2) በንኡስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቀርበውን ማመልከቻ ማንኛውም በሕግ ያገባኛል የሚል ሰው ማቅረብ ይችላል፡፡

(3) በተለይም ሥራ አስኪያጁ ሲሻር የተመዘገበው እንዲለወጥ መደረግ አለበት፡፡

**አንቀጽ 91 ስለ ሰዎች በተጨማሪ ስለ ማስመዝገብ**

(1) የተፈጥሮ ሰው የሆነ ነጋዴ ከዚህ የሚከተሉት በተጨማሪ እንዲመዘገቡለት መጠየቅ ይችላል፤

(ሀ) ጋብቻውን፤ጋብቻው የተፈጸመበትን ቦታና ቀን እንዲሁም ፤የተፈራረሙት የጋብቻ ውል ካለ የተፈራረሙበትን ቀንና ቦታ ወይም ያለ እንደሆነ ውሉ የተቀመጠበትን ቦታ ወይም ሰው ስም፤

(ለ) ፍርድ ቤት ጋብቻው እንዲፈርስ የወሰነ እንደሆነ ውሳኔን፤

(ሐ) ነጋዴው ችሎታ የሌለው ነው ተብሎ በፍርድ የተከለከለ መሆኑን ፍርድ ቤት የወሰነበት፤

(መ) ሚስት ወይም ባል ተቃውመው እንደሆነ ስለ ንግዱ ሥራ ያቀረቡትን መቃወሚያ፤

(ሠ) በዚህ ሕግ በአንቀጽ 17 መሠረት መቃወሚያ የተነሳበትን (ቀሪ የሆነበትን)፤

(ረ) አዲስ ሥራ አስኪያጅ መሾሙን፤

(2) በንኡስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቀርበውን ማመልከቻ ማንኛውም በሕግ ያገባኛል የሚል ሰው ማመልከት ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 92 ስለ ንግድ ማኅበሮች በተጨማሪ ስለሚመዘገቡ ጉዳዮች</u>**

የንግድ ማኅበሮችን ምዝገባ በተመለከተ በዚህ ሕግ ሁለተኛው መጽሐፍ አግባብ ባላቸው ድንጋጌዎች የተመለከቱት ተጨማሪ ነገሮች መመዝገብ አለባቸው፡፡

**<u>አንቀጽ 93. ስለ መክሰር የሚሰጥ ፍርድ</u>**

ስለ መክሰር ወይም ዕዳን መልሶ ስለማደራጀት የሚፈረደውን ፍርድ በዚህ ሕግ በሦስተኛው መጽሐፍ በተነገረው ተገቢ ድንጋጌ መሠረት በተጨማሪነት ማስመዝገብ ይገባል፡፡

**<u>ክፍል አራት</u>**

**<u>ከመዝገብ ስለመሰረዝ</u>**

**<u>አንቀጽ 94 መነገድን ስለመተው</u>**

(1) ማንኛውም ነጋዴ የንግድ ሥራውን በማንኛውም ምክንያት የተወ ወይም የንግድ መደብሩን ያከራየ እንደሆነ የንግድ ሥራውን ከተወበት ወይም መደብሩን ካከራየበት ጊዜ አንስቶ ከሁለት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ከመዝገብ እንዲሰረዝ ማመልከት አለበት፡፡

(2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የንግድ መደብሩን የተወው ወይም ያከራየው ነጋዴ ከአንድ በላይ የንግድ መደብሮች ያሉት ከሆነ እና የተወው ወይም ያከራየው የተወሰኑትን የንግድ መደብሮች ብቻ ከሆነ ነጋዴው የተወውን ወይም ያከራየውን መደብር በተመለከተ አስፈላጊው ማስተካከያ በንግድ መዝገብ ውስጥ እንዲገባ ማመልከት አለበት፡፡

**<u>አንቀጽ 95 የነጋዴው መሞት</u>**

(1) ነጋዴው በሞተ በሁለት ወር ውስጥ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር የሟች ሚስት ወይም ባል ወይም የሟች ወራሾች ምዝገባው እንዲሰረዝላቸው ማመልከት አለባቸው፡፡

(2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) የተጠቀሱት ባለመብቶች በጋራ ባለቤትነት ንግዱን ማካሄድ የሚቀጥሉ ከሆነ አዲስ ምዝገባ እንዲደረግላቸው ማመልከት አለባቸው፡፡

(3) የጋራ ባለቤትነቱ ሲቀርና ሲካፈሉ፣ ንግዱ የተላለፈለት ሰው በዚህ አንቀጽ በንኡስ አንቀጽ (2) መሠረት የተደረገው ምዝገባ እንዲሰረዝለትና አዲስ ምዝገባ እንዲደረግለት ማመልከት አለበት፡፡

**<u>አንቀጽ 96 ምዝገባን በትዕዛዝ ስለ ማሰረዝ</u>**

(1) መዝጋቢው መሥሪያ ቤት ነጋዴው የንግድ ሥራውን ማቆሙን ወይም የተመዘገበውን ንግድ ለማከሄድ ችሎታ የለውም ተብሎ የተወሰነበት መሆኑን ባወቀ ጊዜ በራሱ ተነሳሽነት ምዝገባውን መሰረዝ ይችላል፡፡

(2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት የተሰጠውን ውሳኔ ራሱ ነጋዴው እና ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት እንዲያውቁት መደረግ አለበት፡፡

## ምዕራፍ ሦስት
## ስለ ቅጣት

## ክፍል አንድ
## ስለ ወንጀል ቅጣት

### አንቀጽ 97 ሳይመዘገቡ ስለ መቅረት

በዚህ ሕግ መሠረት መመዝገብ እያለበት ሳይመዘገብ የቀረ ወይም መመዝገብ ያለበትን ነገር ያላስመዘገበ ማንኛውም ሰው ጥፋተኛ መሆኑ ከተረጋገጠ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 434 መሠረት ይቀጣል፡፡

### አንቀጽ 98 ሆነ ብሎ ትክክለኛ ያልሆነ መግለጫ መስጠት

ስለሚመዘገበው ጉዳይ ሆነ ብሎ ትክክለኛ ያልሆነ መግለጫ የሰጠ ማንኛውም ሰው ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 379 መሠረት ይቀጣል፡፡

## ክፍል ሁለት
## ፍትሐ ብሔራዊ ማስገደጃ (ቅጣት)

### አንቀጽ 99 መዝገብ መግባት ስለ ሚያስከትለው ውጤት

(1) ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበበት በስተቀር ማንኛውም በመዝገብ የገባ ሰው ወይም የንግድ ማኅበር ነጋዴ ነው ተብሎ ይገመታል፡፡

(2) ማንኛውም የተመዘገበ ሰው ወይም የንግድ ማኅበር ነጋዴ ላለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ አይፈቀድለትም፤ ነጋዴነት የሚያስከትለውንም ኀላፊነት ሁሉ ይቀበላል፡፡

### አንቀጽ 100 በመዝገብ ሳይገቡ መቅረት ስለሚሰጠው ውጤት

(1) ማንኛውም ነጋዴ የሆነ ሰው በዚህ ሕግ መሠረት መመዝገብ የሚገባው ሆኖ ሳይመዘገብ የቀረ እንደሆነ እንደ ነጋዴ ተቈጥሮ ኃላፊ ይሆናል፡፡

(2) አግባብ ያላቸው የዚህ ሕግ ሁለተኛ መጽሐፍ ድንጋጌዎች በንግድ ማኅበሮች ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

### አንቀጽ 101 ምዝገባን ያለማሰረዝ የሚያስከትለው ውጤት

የንግዱን መደብር ያስተላለፈ ወይም ያከራየ ነጋዴ ምዝገባውን ከማሰረዙ በፊት ከመደብሩ ጋር በተያያዘ መደብሩ በተላለፈለት ሰው ወይም መደብሩን በተከራየው ሰው ላይ ለሚደርስ ዕዳ ከዚሁ ሰው ጋር በአንድነትና በተናጠል ኃላፊ ይሆናል፡፡

### አንቀጽ 102 በመዝገብ የገባ ጉዳይ ስለሚያስከትለው ውጤት

(1) ማንኛውም ሰው በንግድ መዝገብ እንዲገባ ያደረገው ጉዳይ ትክክል ባይሆንም የተመዘገበውን ቃል መሰረት አድርገው በሰሩ ሰዎች ላይ የተፈጠረውን ስህተት መቃወሚያ አድርጎ እንዲያቀርብ አይፈቀድለትም፡፡

(2) ሦስተኛ ወገኞች በንግድ መዝገብ በትክክል የገባውን ጉዳይ አላወቅንም ነበር ብለው ማስረጃ ማቅረብ አይፈቀድላቸውም፡፡

**<u>አንቀጽ 103 ነጋዴ የሆነውን ሰው የሚመለከቱ ጉዳዮች ሦስተኛ ወገኞችን መቃወሚያ ስላለመሆናቸው</u>**

ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ነጋዴ የሆነውን ሰው የሚመለከቱ ጉዳዩች በንግድ መዝገብ ያልተመዘገቡ ቢሆኑም ቅን ልቡና ባላቸው ወገኖች ላይ መቃወሚያ ሆነው ሊቀርቡ አይችሉም፡፡

(ሀ) የነጋዴው አካለ መጠን ያለመድረስ፣

(ለ) የነጋዴው ማግባት፣

(ሐ) የነጋዴው የጋብቻ ውል፣

(መ) የነጋዴው ጋብቻ መፍረስ፣

(ሠ) የነጋዴው ችሎታ ማጣት፣

(ረ) በዚህ ሕግ በአንቀጽ 15 መሠረት የቀረበ መቃወሚያ፣

(ሰ) የሥራ አስኪያጁ ሥልጣን አንድ ቅርንጫፍ ወይም ወኪል ጽሕፈት ቤት በማስተዳደር ብቻ የተወሰነ መሆኑ፣

(ሸ) የሥራ አስኪያጁ መሻር ወይም ከሥራ መሰናበት፡፡

**<u>አንቀጽ 104 የንግድ ማኅበሮችን የሚመለከት ጉዳዮች ሦስተኛ ወገኖችን መቃወሚያ ስላለመሆናቸው</u>**

በንግድ መዝገብ ውስጥ ከገባው ቃል ውስጥ ያለ ካልሆነ በቀር የንግድ ማኅበሮችን የሚመለከቱ የሦስተኛ ወገኖችን መብት መቃወሚያ ለመሆን የማይችሉት ጉዳዮች በዚህ ሕግ በሁለተኛው መጽሐፍ ውስጥ ተደንግገዋል፡፡

**<u>አንቀጽ 105 በደንብ ስለሚወሰኑ ጉዳዮች</u>**

በዚህ ሕግ አንቀጽ 71(2) የተደነነገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ርዕስ የተካተቱትን ድንጋጌዎች ለማስፈጸም የምንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይወጣል፡፡

## <u>ርዕስ አምስት</u>

## <u>ስለንግድ መደብር (መድበል)</u>

### <u>ምዕራፍ አንድ</u>

### <u>ጠቅላላ ድንጋጌ</u>

**<u>አንቀጽ 106 ትርጓሜ</u>**

የንግድ መደብር (መድበል) ማለት ግዙፍነት የሌለው ተንቀሳቃሽ ንብረት ሆኖ በዚህ ሕግ አንቀፅ 5 የተጠቀሱትን የንግድ ሥራዎች ለማካሄድ የተሰበሰቡና የተደራጁ የሚንቀሳቀሱ ንብረቶችን ሁሉ ያካትታል፡፡

**አንቀጽ 107 ነጋዴዎችና የንግድ መደብር**

(1) ማንኛውም ነጋዴ አንድ የንግድ መደብር ሥራን ያካሂዳል፡፡

(2) ነጋዴ የተለያዩ የንግድ ሥራዎችን ለመሥራት በርካታ የንግድ መደብሮችን ሊያንቀሳቅስ ይችላል፡፡

(3) ነጋዴ የንግድ ሥራውን የሚያካሂደው በንግድ መደብር ባለቤትነት፣ በአላባ ተጠቃሚነት ወይም በተከራይነት ሊሆን ይችላል፡፡ እንደ ነጋዴ የሚቆጠረው በንግድ መደብሩ የሚነግድ ሰው ብቻ ነው፤ መደብሩ የተከራየ እንደሆነ ባለቤቱ ወይም አከራዩ ነጋዴ ሊባል አይችልም፡፡

**አንቀጽ 108 ስለ ዋና የንግድ መደብርና ቅርንጫፎች ወይም ወኪል ጽህፈት ቤቶች**

(1) አንድ የንግድ መደብር በአንድ ዋና የንግድ መሥሪያ ቤት የተወሰነ ለመሆን ይችላል፡፡ እንዲሁም የዋናው መሥሪያ ቤቱ አካል እንደሆኑ የሚቆጠሩ የቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ወይም የወኪል ጽሕፈት ቤቶች ሊኖረው ይችላል፡፡

(2) የንግድ መደብሩ ዋና መሥሪያ ቤት ሳይሸጥ ወይም ሳይከራይ አንድ ቅርንጫፍ ወይም ወኪል ጽህፈት ቤት የተሸጠ ወይም የተከራየ እንደሆነ እንደ ንግድ መደብር ሽያጭ ወይም ኪራይ ይቆጠራል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት
## የንግድ መደብር የተቋቋመባቸው ነገሮች
## ክፍል አንድ
## በንግድ መደብር ውስጥ ስለሚገኙ ነገሮች

**አንቀጽ 109 ስለ መልካም ስምና ግዙፍነት ስለሌላቸው ነገሮች**

(1) የንግድ መደብር በዋነኛነት የንግዱን መልካም ስም ይይዛል፤

(2) የንግድ መደብር ሌሎች ግዙፍነት የሌላቸው ነገሮችን በተለይም

(ሀ) የንግድ ስም፣

(ለ) የንግድ ምልክትና ሌላ የንግድ ስራ የሚካሄድበት ልዩ መገለጫ፣

(ሐ) የንግዱ ሥራ የሚከናወንበትን ቦታ የመከራየት መብት፣

(መ) የአእምሮአዊ ንብረቶች፤ ፣

(ሠ) ከነጋዴው ጋር ሳይሆን ከንግድ መደብሩ ጋር የተያያዙ ሌሎች ልዩ መብቶች፤

ሊያካትት ይችላል፡፡

**አንቀጽ 110 ግዙፍነት ስላላቸው ነገሮች**

የንግድ መደብር ግዙፍነት ያላቸው እንደ መሣሪያዎች፤ ወይም ዕቃዎችና ሸቀጣ ሸቀጦች የመሳሰሉ ነገሮች ሊያካትት ይችላል፡፡

**አንቀጽ 111 ገንዘብ የመጠየቅ መብቶችና ዕዳዎች**

(1) የንግድ መደብር የንግድ ሥራ የሚከናወንበትን ቦታ ከመከራየት መብት በስተቀር የነጋዴውን ገንዘብ የመጠየቅ መብትና ዕዳን አይጨምርም፡፡

(2) የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም አግባብ ባለው ሕግ የንግድ መደብር ሲተላለፍ ስለሚጠበቁበት የሰራተኞች መብቶች፣ ስለሰራተኞች ውሎች ቀጣይነት እንዲሁም የመድን ዋስትና ያለው ንብረት የተላለፈለት ሰው የሚኖረው መብት በተመለከተ የተደነገጉት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ናቸው፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለ መልካም ስምና ጥበቃው

### አንቀጽ 112 ትርጓሜ

መልካም ስም ማለት ከንግድ መደብር ሥራ አካሄድ የተፈጠረ ዋጋ ሲሆን፤ይህም ዋጋ ከነጋዴው ዕቃ (ሸቀጥ) ወይም አገልግሎት ከሚፈልጉት ሦስተኛ ወገኖች ጋራ በሚደረገው ግንኙነት ሁሉ የተገኘ ነው፡፡

### አንቀጽ 113 መልካም ስምን ስለመጠበቅ

የነጋዴው መልካም ስም ተገቢ ያልሆነ የውድድር ሥራ እንዳይሠራ የማይገባ ውድድርን ለማስቀረት በተለይ በዚህ ሕግ አንቀጽ 29፤39፤53፤118፤130፤131፤166፤167 የውድድር ሥራ የተከለከለ በሚያደርጉት ድንጋጌዎች እና ስምምነቶች መሠረት ይጠበቃል፡፡

### አንቀጽ 114 ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ሥራ

(1) ነጋዴው በውድድር ሥራ ጥፋት ፈጽሞ በተገኘ ማናቸውም ሰው ላይ በፍትሐ ብሔር ሕግ ከውል ውጭ ስለሚኖር ኃላፊነት በሚደነግገው አንቀጽ 2057 መሠረት ኪሣራ ለማግኘት ክስ መመሥረት ይችላል፡፡

(2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ስለማይገባ የንግድ ውድድር ሥራና ስለሚያስከትለው ውጤት ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

### አንቀጽ 115 ስለ ንግድ ስም፤ ንግድ ምልክት እና አእምሮአዊ ንብረቶች

የንግድ ስምንና የንግድ ምልክትን እንዲሁም የአእምሮአዊ ንብረቶች አስተዳደርን በተመለከተ አግባብነት ያላቸው የፍትሐ ብሔር ሕግ እና የልዩ ሕጎች ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## ክፍል ሦስት፡፡

## ስለንግድ ቦታ ኪራይ ውል መብት

### አንቀጽ 116 የፍትሐ ብሔር ሕግ ተፈፃሚ ስለመሆኑ

በዚህ ክፍል የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው የማይንቀሳቀስ ንብረት ኪራይ ውሎችን የሚመለከቱ የፍትሐ ብሔር ሕግ ድንጋጌዎች በንግድ ቦታ ኪራይ ውል መብት ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

### አንቀጽ 117 የንግዱ ዓይነት

በንግድ ቦታ ኪራይ ውል ውስጥ ተከራዩ የሚሰራው የንግድ ዓይነት ተጠቅሶ እንደሆነ ተከራዩ በዚህ ቦታ ሌላ ዓይነት ንግድ ሊያከናውን አይችልም፤ ሌላ ዓይነት ንግድ ሲያከናውን ቢገኝ ውሉ ሊሰረዝ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 118 አከራዩ ተመሳሳይ ንግድ ሥራ እንዳይሰራ ስለ መከልከሉ**

(1) ለንግድ አገልግሎት የሚውል ቦታ ባለቤት ንግዱ የሚከናወንበትን ቦታ በውል ካከራየ በኋላ በዚሁ ቦታ ላይ ተከራዩ ከሚያካሂደው ንግድ ጋር የሚመሳሰል ሥራ መሥራት አይችልም፤

(2) አከራዩ በንዑስ አንቀፅ (1) የተከለከለውን ቢተላለፍ ካሳ ከፍሎ የንግድ መደብሩም እንዲዘጋ ይደረጋል፡፡

**አንቀጽ 119 የኪራይ ውል ለሌላ ማስተላለፍን ወይም የተከራየውን ለሌላ ማከራየትን ስለሚከለክሉ የውል ቃሎች**

(1) በፍትሐ ብሔር ህጉ ቁጥር 2959 የተደነገገው ቢኖርም እንኳን ተከራዩ የንግድ መደብሩን ለገዛው ሰው ንግዱ የሚከናወንበት ቦታ የሚመለከተውን የኪራይ ውል አያስተላልፍም ወይም የተከራይ ተከራይ አድርጎ አያከራይም ወይም የኪራዩን ውል ለማስተላለፍ ወይም የተከራይ ተከራይ አድርጎ ለማከራየት የባለቤቱ ፈቃድ ያስፈልጋል የሚሉ የውል ቃሎች ሁሉ ዋጋ አይኖራቸውም፡፡

(2) እንዲሁም የተከራዩን የኪሳራ ሒሳብ አጣሪ ሆኖ ለተሾመ ሰው በዚህ ሕግ ሦስተኛ መጽሐፍ መሠረት የታወቁለትን መብቶች የሚነፍጉ ወይም የሚገድቡ የውል ቃሎች ሁሉ ዋጋ አይኖራቸውም፡፡

**አንቀጽ 120 የኪራይ ውልን ስለማቋረጥ**

(1) የንግድ መደብር ለዕዳ ዋስትና ተሰጥቶ እንደሆነ አከራዩ በስምምነት ወይም በኪራይ ውሉ መሠረት ውሉን ለማቋረጥ የሚያስችለውን ድንጋጌ በመጠቀም ውሉን ለማቋረጥ ሀሳብ ያለው ሲሆን ይህን የንግድ መደብሩን መያዣ አድርገው ገንዘብ ላበደሩ ሰዎች ውሉ ከሚቋረጥበት ቀን ቢያንሰ ከአንድ ወር በፊት በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

(2) በዚህአንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት ማስታወቂያ ካልወጣ በስተቀር የንግድ መደብሩን መያዣ አድርገው ገንዘብ ባበደሩት ሰዎች ላይ የውሉ መቋረጥ መቃወሚያ አይሆንም፡፡

**አንቀጽ 121 ስለተከራዩ መክሰር**

(1) ተከራዩ በከሰረ ጊዜ መክሰሩ በራሱ የኪራይ ውሉን ያቋርጣል የሚል ስምምነት አይፀናም፤

(2) ተከራዩ በከሰረ ጊዜ የተከራዩ የኪሳራ ሒሳብ አጣሪ እና አከራዩ በዚህ ሕግ በሦስተኛው መፅሐፍ በተደነገጉት መብቶቻቸው ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡

**ምዕራፍ ሶስት**

**ስለ ንግድ መደብር ሽያጭ**

**ክፍል አንድ**

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ 122 የፍትሐ ብሔር ህግ ተፈጻሚ ስለመሆኑ**

የዚህ ምዕራፍ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 2266-2367 የተመለከቱት ድንጋጌዎች በንግድ መደብር ሽያጭ ላይ ተፈጻሚዎች ይሆናሉ፡፡

**አንቀጽ 123 የተፈጻሚነት ወሰን**

(1) የንግድ መደብር ሽያጭን የሚመለከቱ የዚህ ምዕእራፍ ድንጋጌዎች፡-

(ሀ) በንግድ መደብር ላይ በሚደረግ ማናቸውም ዓይነት ሽያጭ ወይም ማስተላለፍ፤ ሌላ ነገር በማስመሰል የተደረገም ቢሆን፤

(ለ) የጋራ ባለሀብቶቹ ባቀረቡት ጥያቄ በሚደረግ የሐራጅ ሽያጭ፣

(ሐ) ካሳን ጨምሮ በሚደረግ ማናቸውም ክፍፍል፤ እንዲሁም ሽያጩ ወይም የሙብት ማስተላለፉ ወይም ክፍፍሉ የንግድ መደብሩን ወይም መልካም ስሙን የሚመለከት ሲሆን፤ ወይም ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቱን ወይም ወኪል ጽህፈት ቤቱን የሚመለከት ሆኖ ነገር ግን ዋናውን የንግድ መደብር ወይም የቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቱን ወይም የወኪል ጽህፈት ቤቱን መልካም ስም ሳይጨምር በሚደረግ ሽያጭ ወይም ማስተላለፍ ወይም ክፍፍል፤

ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

(2). የዚህ ምዕራፍ ድንጋጌዎች ሽያጩ የንግድ መደብርን ወይም የንግድ መደብር መልካም ስምን የሚመለከት ካልሆነ ወይም በማድበስበስ (በመደበቅ) ይህን የሚያደርግ ካልሆነ በስተቀር የንግድ መደብርን የተለያዩ አካላት ነጣጥሎ በሚደረግ ሽያጭ ላይ ተፈፃሚ አይሆኑም።

## ክፍል ሁለት
## መሟላት ስለሚገባቸው ሥርዓቶች

**አንቀጽ 124 ሽያጭ በጽሁፍ ስለመሆኑ**

የንግድ መደብር ሽያጭ በጽሁፍ ካልሆነ ዋጋ አይኖረውም፡፡

**አንቀጽ 125 በሽያጩ ውል ውስጥ መጠቀስ ስላለባቸው ነገሮች**

የንግድ መደብር ሽያጭ ውል የሚከተሉትን መጥቀስ አለበት፡-

(1) በመጨረሻዎቹ ሦስት የበጀት ዓመታት ወይም ሻጭ የንግድ መደብሩን ካቋቋመው ወይም ከገዛው ሦስት ዓመት ያልሞላው ከሆነ ከተቋቋመበት ወይም ከተገዛበት ጊዜ አንስቶ ያደረገውን አጠቃላይ ሽያጭና ያገኘው ትርፍ፤

(2) የንግድ መደብሩ ስራ የሚከናወነው በኪራይ ቦታ የሆነ እንደሆነ የኪራይ ውሉ የተደረገበትንና የሚያበቃበትን ቀን እንዲሁም የአከራዩን ስምና አድራሻ፤

(3) የንግድ መደብሩ በዋስትና ከተያዘ በዋስትና መያዙ።

**<u>አንቀጽ 126 ውሉን ስለማፍረስ</u>**

(1) በዚህ ሕግ አንቀጽ 125 የተመለከቱት ነገሮች ባለመሟላታቸው ምክንያት በገዢው ላይ ጉዳት የደረሰ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ከተረዳ በገዢው ጠያቂነት ውሉን ሊያፈርሰው ይችላል፡፡

(2) በዚህ ሕግ አንቀጽ 125 መሠረት በተሰጠ የተሳሳተ መረጃ ምክንያት ገዢው ላይ ጉዳት የደረሰ መሆኑን ፍድ ቤቱ ከተረዳ በገዢው ጥያቄ ውሉን ማፍረስ ወይም ዋጋውን መቀነስ ይችላል፡፡

(3) የዚህን አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት ያደረጉ ክሶች የሽያጭ ውሉ ከተደረገበት አንስቶ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለባቸው፡፡

**<u>ክፍል ሦስት</u>**

**<u>የሻጭ ግዴታዎች</u>**

**<u>አንቀጽ 127 የማስረከብ ግዴታ</u>**

(1) ሻጭ የንግድ መደብሩን ለገዢው ማስረከብ አለበት፤

(2) ተቃራኒ የሆነ ስምምነት ከሌለ በስተቀር የንግድ መደብር ሽያጭ የንግድ መደብሩ ውስጥ የሚካተቱን ነገሮች ሁሉ ለገዢው መሸጥን ያመለክታል፡፡

(3) ሻጭ የንግድ በደብሩን መልካም ስም ለገዢው ለማስተላለፍ የሚያስችሉ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችንና መረጃዎችን ሁሉ ለገዢው መስጠት ይኖርበታል፡፡

(4) የአእምሮአዊ ንብረት መብቶች ማስተላለፍን በተመለከተ አግባብነት ያላቸው የፍትሐ ብሔር ሕግና የልዩ ሕግ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

**<u>አንቀጽ 128 ስለ ሒሳብ መዝገቦች</u>**

(1) ሻጩና ገዢው ሺያጩ በሚፈጸሚበት ቀን የሒሳብ መዝገቦችን ያረጋግጣሉ የሒሳብ መዝገቦች እና ሰነዶችን የሚያመለክት አንድ ዝርዝር ጽሑፍ ያዘጋጃሉ፡፡

(2) ሻጩ የሒሳብ መዝገቦቹን፤ ማስረጃዎቹን፤ የተለዋወጣቸውን ደብዳቤዎች ያስቀራል፡፡ ተቃራኒ ስምምነት ቢኖርም እንኳን መዝገቦቹንና ሰነዶቹን እስከ ሁለት ዓመት ጠብቆ በማኖር ገዢው በፈለገ ጊዜ እንዲያያቸው መፍቀድ አለበት፡፡

**<u>አንቀጽ 129 ስለንግድ ሥራ የመጻጻፍ ደብዳቤዎች</u>**

ስለ ተሸጠው የንግድ መደብር ጉዳይ ከሽያጩ በኋላ ለሻጩ የሚደርሱትን ደብዳቤዎችና ሌሎች ጽሑፎች ሻጩ ወዲያውኑ ለገዢው ማስተላለፍ አለበት፡፡

**አንቀጽ 130 ሻጩን እንዳይወዳደር ስለመከልከል**

(1) ሻጩ ከሽያጭ ቀን አንስቶ እስከ 5 ዓመት ድረስ በተሸጠው የንግድ ሥራ ዓይነትና በተሸጠውም የንግድ ቤት አካባቢ በገዢው ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ማናቸውም ሥራ መሥራት አይችልም፡፡

(2) በሽያጭ ውሉ ውስጥ ሻጩ ንግድ መክፈት የሚከለከልበትን ቦታና የተከለከለውንም የንግድ ዓይነት ወስኖ ማስፈር ይቻላል፤ ሆኖም የዚህ ዓይነት የውል ቃል የሚጸናበት ከዓምስት ዓመት መብለጥ አይችልም፡፡

**አንቀጽ 131 ከገዥ እንደ ገና የገዙ ሰዎች መብት**

ሻጩ የመወዳደር ሥራ እንዳይሠራ በዚህ ሕግ በአንቀጽ 130 የተጣለበት ክልከላ የንግድ መደብሩ አካል እንደሆነ ይቆጠራል፤ ይህም ለገዥውና ለወራሾቹ ጥቅም ብቻ ሳይሆን የንግድ መደብሩን ከገዥ እንደ ገና ለገዙትም ሀሉ የጸና ይሆናል፡፡

## ክፍል አራት

## የገዢው ግዴታዎች

**አንቀጽ 132 ዋጋ የመክፈል ግዴታ**

ገዢው በሽያጭ ውል በተስማሙት መሠረት ዋጋውን መክፈል አለበት፡፡ ስለአከፋፈሉ በውሉ የተለየ ስምምነት ከሌለ ዋጋው የሚከፈለው በጥሬ ገንዘብ ይሆናል፡፡ ሆኖም ማናቸውም ዓይነት ተቃራኒ የውል ቃል ቢኖርም የዚህ ሕግ አንቀጽ 134 ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 133 ሽያጩን የማስታወቅ ግዴታ**

ገዢው በዚህ ሕግ ከአንቀጽ 136 እስከ 142 በተመለከተው መሠረት ሽያጩ በማስታወቂያ እንዲወጣ ማድረግ አለበት፡፡

**አንቀጽ 134 ስለ ሽያጭ ዋጋ ክፍያ መታገድ**

(1) ሽያጩ ከተፈፀመ በኋላ መቃወሚያ የሚቀርብበት ቀን እስከሚያበቃ፣ ወይም መቃወሚያ ቀርቦም ከሆነ የገንዘብ ጠያቂዎች መብት በስምምነት ወይም በፍርድ ቤት እልባት እስከሚያገኝና ለገንዘብ ጠያቂዎች እስኪከፈላቸው ድረስ የሽያጩ ገንዘብ ለሻጭ ሳይከፈል በገዥው እጅ ታግዶ ይቆያል፡፡

(2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ከመፈፀሙ በፊት የተደረገ ማናቸውም ክፍያ ወይም የመብት ማስተላለፍ ወይም ክፍያ የመጠየቅ መብትን መተው ከሻጩ ላይ ገንዘብ ጠያቂዎች በሆኑት ሰዎች ላይ መቃወሚያ ሊሆን አይችልም፤

(3) በሽያጭ ውል ውስጥ ገዢው የሽያጩን ገንዘብ ባንድ ሦስተኛ ሰው እጅ በአደራ ያስቀምጣል ተብሎ ለመስማማትም ይቻላል፡፡ በስምምነቱ መሰረት ገንዘቡ በአደራ ከተቀመጠ ሻጩ ለገዢው ከሚኖርበት ተጠያቂነት

ነፃ ይሆናል፡፡ ገዢው ይህን በማድረግ ለሻጩ ካለበት ዕዳ ነጻ ቢሆንም ከሻጭ ላይ ገንዘብ ጠያቂዎች ለሆኑት የሚኖርበትን ሀላፊነት አያስቀርም፡፡

**<u>አንቀጽ 135 የሻጭ ዋስትናዎች</u>**

ሻጩ ዋጋው በሙሉ እስኪከፈለው ድረስ ስለገንዘቡ አከፋፈል ከዚህ በታች ከአንቀጽ 139 እስከ 142 በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት በተሸጠው ንብረት ላይ ህጋዊ የሆነ የመያዣ መብት ያለው ሲሆን ውል ይፍረስልኝ ብሎ ክስ የማቅረብ መብትም አለው፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>ሽያጮችን በማስታወቂያ ስለማዉጣትና ከሻጭ ላይ ገንዘብ ጠያቂዎች ስለሚኖራቸው መብቶች</u>

**<u>አንቀጽ 136 ሽያጩን በማስታወቂያ ስለማውጣት</u>**

(1) ማናቸውም የንግድ መደብር ሽያጭ የንግድ መደብሩ ዋና መሥሪያ ቤት በሚገኝበት አካባቢ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ታትሞ መውጣቱን ገዢው ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

(2) የተሸጠው የንግድ መደብር በልዩ ልዩ ሥፍራ የቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ወይም የወኪል መሥሪያ ቤቶች ያሉት እንደሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ማስታወቂያው የሚደረገው እያንዳንዱ የቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ወይም ወኪል መሥሪያ ቤት በሚገኝበት አካባቢ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ነው፡፡

**<u>አንቀጽ 137 በማስታወቂያዉ ስለሚጠቀሱ ነገሮች</u>**

በዚህ ሕግ አንቀጽ 136 መሠረት የሚወጣ ማስታወቂያ፤

(1) የሻጭንና የገዢን ስሞችና አድራሻዎች፣

(2) የንግድ መደብሩን ዓይነትና አድራሻ፣

(3) ከንግድ መደብሩ ጋር የተሸጡ የቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ወይም የንግድ ወኪል መሥሪያ ቤቶች የሥራቸውን ዓይነትና አድራሻቸውን፣

(4) የሽያጩን ዓይነት፣ ቀንና ዓመት ምሕረቱን

(5) የሽያጩን ዋጋ፤

(6) የንግድ መደብሩ ዋና መስሪያ ቤት ባለበት ስፍራ የፍርድ ቤት መጥሪያን ለመቀበል የመረጠዉን አድራሻ፤

መጥቀስ ይገባቸዋልይኖርበታል፡፡

**አንቀጽ 138 ማስታወቂያው የሚወጣበት ጊዜ**

(1) በዚህ ሕግ አንቀጽ 136 መሠረት ማስታወቂያው ሽያጩ ከተከናወነበት ቀን ጀምሮ በሠላሳ ቀናት ውስጥ መውጣት ይኖርበታል፡፡

(2) ዘግይቶ የሚወጣ ማስታወቂያ የጸና ይሆናል፡፡ ነገር ግን ማስታወቂያው በመዘግየቱ ምክንያት በሻጭ ላይ ወይም ከሻጩ ላይ ገንዘብ ጠያቂ በሆኑ ሰዎች ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ገዥ ተጠያቂ ሊሆን ይችላል፡፡

**አንቀጽ 139 የሽያጩ ገንዘብ ለሻጩ እንዳይከፈለው ስለሚቀርቡ መቃወሚያዎች**

(1) ከሻጩ ገንዘብ ጠያቂ የሆነ ሁሉ ክፍያ የሚጠይቅበት ጊዜ ያልደረሰ ቢሆንም እንኳን የመጨረሻው ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለሻጩ ዋጋ እንዳይከፈለው ለማድረግ ለፍርድ ቤት በማመልከት መቃወሚያው ለገዢው መጥሪያ መቀበል በሚገባው አድራሻ እንዲደርሰው ማድረግ አለበት፡፡

(2) የመቃወሚያውም ማስታወቂያ የተቃዋሚውን ስምና አድራሻ እንዲሁም የሚፈልገውን ገንዘብ መጠንና መነሻ ምክንያቱን በትክክል መግለጽ አለበት፡፡

(3) በዚህ ሕግ አንቀጽ 136 መሠረት ማስታወቂያ ሳይወጣ ከቀረ ወይም ማስታወቂያው በአንቀጽ 137 የተዘረዘሩትን ያልገለጸ እንደሆነ መቃወሚያ ለማቅረብ የተወሰነውን ጊዜ መጠበቅ ሳያስፈልግ መቃወሚያውን በማናቸውም ጊዜ ማቅረብ ይቻላል፡፡

(4) በመቃወሚያው ላይ ወሳኔ እስከሰጥ ድረስ በገዢው እጅ ወይም በአደራ አስቀማጩ ሦስተኛ ወገን እጅ ታግዶ የተቀመጠውን የሽያጭ ገንዘብ መክፈል ወይም ማስተላለፍ አይቻልም። እንዲሁም የዚህ ሕግ አንቀጽ 134 ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ።

**አንቀጽ 140 መቃወሚያዎችን ውድቅ ስለማድረግ**

ሻጩ ያልተሟሉ ወይም በወቅቱ ያልቀረቡ ወይም ያለበቂ ምክንያት የቀረቡ መቃወሚያዎችን ፍርድ ቤቱ ውድቅ እንዲያደርግ መጠየቅ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 141 የሽያጩን ገንዘብ ስለማከፋፈል**

(1) የንግድ መደብሩ የሽያጭ ገንዘብ በንግድ መደብሩ ላይ የመያዣ ዋስትና ባላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች እና ገንዘቡ ታግዶ እንዲቆይ ማመልከቻ ባቀረቡ ገንዘብ ጠያቂዎች መካከል በስምምነት ወይም በፍርድ ውሳኔ መሠረት እንዲከፋፈል ይደረጋል፡፡

(2) ከክፍፍሉ በኋላ ትርፍ ገንዘብ ካለ ለሻጩ ይሰጣል፡፡

**አንቀጽ 142 ገንዘብ ጠያቂዎች በሐራጅ ዋጋ አብልጠው ስለመስጠታቸው**

(1) በንግድ መደብሩ የመያዣ ዋስትና ያላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች እና በዚህ ሕግ አንቀጽ 141 ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱት መቃወሚያ ያቀረቡት ገንዘብ ጠያቂዎች የንግድ መደብሩ የሽያጭ ዋጋ ለሚፈልጉት ክፍያ የማይበቃ የሆነ እንደሆነ ገንዘብ ጠያቂዎቹ የንግድ መደብሩ በሐራጅ እንዲሸጥ ፍርድ ቤቱን መጠየቅ ይችላሉ፡፡

(2) ፍርድ ቤቱም የንግድ መደብሩ በውሉ በተመለከተው ዋጋ ላይ አንድ አሥረኛው ተጨምሮበት በሐራጅ እንዲሸጥ ያዝዛል፡፡

(3) በሐራጅ አብልጦ የሚገዛ ሦስተኛ ወገን የሆነ ገዢ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ የንግድ መደብሩ ከፍተኛ ዋጋ ለሰጠው ገንዘብ ጠያቂ በሐራጅ ይሸጣል፡፡

## ምዕራፍ አራት

## የንግድ መደብር በዋስትና መያዣ ስለማድረግ

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 143 መያዣ ማድረግ ስለመቻሉ

(1) የንግድ መደብርን ለዋስትና መያዣ ማድረግ ይቻላል፡፡ መያዣውም የዋስትና መብት ይሰጣል፡፡

(2) የንግድ መደብርን ለዋስትና መያዣ ማድረግ ከሕግ ወይም ከውል ሊመነጭ ይችላል፡፡

(3) በንግድ መደብር ላይ የሚደረገው ማናቸውም ዓይነት ከሕግ ወይም በውል የሆነ የዋስትና መያዣ መብት አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ካልተመዘገበ በቀር ሦስተኛ ወገኖችን መቃወሚያ ሊሆን አይችልም፡፡

(4) በተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ ስለሚመሰረት የዋስትና መያዣን በተመለከተ አግባብነት ባለው ሕግ የተደነገጉት ልዩ ደንቦች እንደተጠበቁ ሆነው በንግድ መደብር ላይ በሚመሰረት የዋስትና መያዣ ላይ የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

### አንቀጽ 144 ከሕግ የመነጨ የዋስትና መያዣ

(1) ቀጥሎ የተመለከቱት ሰዎች በንግድ መደብር ላይ ከህግ የመነጨ የዋስትና መያዣ መብት አላቸው፤

(ሀ) የሽያጭ ገንዘብ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ያልተከፈለው የንግድ መደብር ሻጭ፤

(ለ) ነጋዴው ከከሰረ ከነጋዴው ገንዘብ ጠያቂዎች፡፡

(2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ለ) ለተመለከተው ከሕግ በመነጨ የዋስትና መያዣ መብት ላይ የዚህ ሕግ ሦስተኛው መጽሐፍ ተገቢ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## ክፍል ሁለት

## ሻጩ በንግድ መደብር ላይ ስላለው ከሕግ የመነጨ የዋስትና መያዣ መብትና ውሉ እንዲፈርስ የመጠየቅ መብት

### አንቀጽ 145 ከሕግ የመነጨ የዋስትና መያዣ

(1) የንግድ መደብር የሽያጭ ዋጋ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ያልተከፈለው የንግድ መደብር ሻጭ ላልተከፈለው ዋጋ በንግድ መደብሩ ላይ ከህግ የመነጨ የዋስትና መያዣ መብት አለው።

(2) የንግድ መደብር ሽያጩ በጽሑፍ ካልሆነና ከሕግ የመነጨው የዋስትና መያዣ መብትም አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ካልተመዘገበ በንዑስ አንቀጽ(1) የተመለከተው ከሕግ የመነጨ የዋስትና መያዣ መብት አይጸናም፡
፡

(3) ከሕግ የመነጨ የዋስትና መያዣ ምዝገባ ዝርዝሩ በልዩ ሕግ ይወሰናል፡፡

**<u>አንቀጽ 146 ውሉ እንዲፈርስ የመጠየቅ መብት</u>**

ዋጋው ያልተከፈለው ሻጭ ውሉ እንዲፈርስ የመጠየቅ መብት አለው፡፡ ሻጩም ሦስተኛ ወገኖችን ሊከራከርበት የሚችለው ከሕግ የመነጨ የዋስትና መያዣ በሕግ በሚጸና ከኳኃን ተመዝግቦና በመዝገቡም ውስጥ ውሉን የማፍረስ መብት ያለው መሆኑ በተለይ ተጠብቆለት እንደሆነ ነው፡፡

**<u>አንቀጽ 147 ውል ማፍረስን ለመጠየቅ ስለሚቀርብ ክስ</u>**

(1) የሽያጩ ዋጋ ሳይከፈል በመቅረቱ በዚህ ሕግ አንቀጽ 146 መሰረት ውሉ እንዲፈርስ የሚጠይቅ ሻጭ ከዋጋው የቀረው ገንዘብ ምን ያህልም ቢሆን በሽያጩ ውል ውስጥ ካልተመለከቱት አዳዲስ ከተጨመሩት ንብረቶች በስተቀር ክስ በጀመረበት ጊዜ የተገኘውን የመደብሩን ንብረት ባለበት ሁኔታ በሙሉ መልሶ መውሰድ አለበት፡፡

(2) ከሻጭና ከገዥ መብት ጋር በተያያዘ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ የተሸጠው መደብር ንብረት ዋጋ ከፍ ወይም ዝቅ ማለት ግምት ውስጥ መግባት አለበት፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>
## <u>በንግድ መደብር ላይ ስለሚደረግ ከውል የመነጨ የዋስትና መያዣ</u>

**<u>አንቀጽ 148 ከውል የመነጨ የዋስትና መያዣ ሁኔታዎች</u>**

(1) በፍትሐ ብሔር ሕግ መሠረት ችሎታ ያለውና የንግድ መደብር ባለቤት (ባለሃብት) የሆነ ማንኛውም ሰው ንግዱን ራሱ ባያካሄደውም እንኳ የንግድ መደብሩን በውል የዋስትና መያዣ ሊያደርገው ይችላል።

(2) ይህም የዋስትና መያዣ ውል በጽሁፍ ካልተደረገ በተዋዋይ ወገኖች መካከል አይጸናም፡፡ የዋስትና መያዣ ውሉም አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ካልተዘገበ ሦስተኛ ወገኖችን መቃወሚያ ሊሆን አይችልም፡፡

(3) ከውል የመነጨ የዋስትና መያዣ ምዝገባ ዝርዝሩ በልዩ ሕግ ይወሰናል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>
## <u>የዋስትና መያዣ ያላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች በንግድ መደብሩ ላይ ያሏቸው መብቶች</u>

## አንቀጽ 149 ስለ ንግድ መደብር መሸጥና ማከራየት

(1) ተቃራኒ የሆነ የውል ቃል ቢኖር እንኳ ባለዕዳው የንግዱን መደብር ለመሸጥ ወይም በሌላ መንግድ ለማስተላለፍ ወይም ለማከራየት መብት አለው።

(2) ስለሆነም የንግዱን መደብር ቢሸጥ ወይም በሌላ መንገድ ቢያስተላለፍ ወይም ቢያከራይ በዋስትና መያዣው መሠረት የሚፈለግበትን ገንዘብ ባለዕዳው ወዲያውኑ ይከፍላል በማለት መዋዋል ይቻላል። ይህም የውል ቃል ውሉ በሚመዘገብበት ጊዜ በመዝገብ ውስጥ ካልተጠቀሰ ዋጋ አይኖረውም።

## አንቀጽ 150 ስለ ዋስትና መያዣ ዋጋ መቀነስ

ባለዕዳው በተለይም የንግዱን መደብር ወደሌላ ቦታ በማዛወሩ፣ ወይም የንግዱ መደብር ሥራ የሚከናወንበትን ቦታ ኪራይ ባለመክፈሉ፤ወይም የሸቀጦቹ ብዛት እየቀነሱ እንዲሄዱ በማድረግ የንግዱን መደብር ዋጋ እንዲቀንስ ካደረገ ወይም ዋጋው ይቀንሳል ተብሎ ከተገመተ ማናቸውም ገንዘብ ጠያቂ አዲስ ዋስትና እንዲሰጠው መጠየቅ ይችላል፡፡ ባለዕዳው አዲስ ዋስትና ካላቀረበ ከባለዕዳው ላይ የሚፈልገው ገንዘብ ወዲያውኑ እንዲከፈለው ፍርድ ቤቱን መጠየቅ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 151 የንግድ መደብሩን ወደ ሌላ ስፍራ ስለማዛወር

(1) የንግድ መደብሩን ወደ ሌላ ስፍራ ለማዛወር የሚፈልግ ባለእዳ የንግድ መደብሩን የዋስትና መያዣ አድርገው ለያዙት ገንዘብ ጠያቂዎች ማስታወቅ አለበት፡፡ሆኖም ገንዘብ ጠያቂዎች መዛወሩን እንዲያውቁ ያልተደረገ እንደሆነ ወይም እንዲያውቁት ከተደረገው የማዛወሪያ ቀን ቢያንስ ከአንድ ወር በፊት አስቀድሞ ዝውውሩ ከተፈፀመ ገንዘብ ጠያቂዎቹ እዳቸው እንዲከፈል ወዲያውኑ መጠየቅ ይችላሉ፡፡

(2) የንግድ መደብሩን በዋስትና የያዙ ገንዘብ ጠያቂዎች በቦታው መዛወር ምክንያት የመደብሩ ዋጋ ይቀንሳል ብለው የሚገምቱ እንደሆነ በአንቀጽ 150 የተሰጣቸውን መብት መጠቀም ይችላል።

(3) ገንዘብ ጠያቂዎች በንግድ መደብሩ መዛወር ከተስማሙና የንግድ መደብሩ የተዛወረው በተመዘገበበት ክልል ውስጥ የሆነ እንደሆነ ዝውወሩን መሰረት አድርጎ ምዝገባው እንዲስተካከል መጠየቅ አለባቸው፡፡ የንግድ መደብሩ ቀድሞ ከተመዘገበበት ክልል ውጭ የተዛወረ እንደሆነ ገንዘብ ጠያቂዎቹ የተዛወረው የንግድ መደብር አዲሱ ዋና መሥሪያ ቤቱ በሚገኝበት ክልል የዋስትና መያዣው እንደ አዲስ መመዝገቡን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

(4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሰረት ምዝገባው የተስተካከለ ወይም አዲስ ምዝገባ የተከናወነ እንደሆነ ማስተካከያው ወይም አዲሱ ምዝገባ የመጀመሪያው ምዝገባ ከተከናወነበት ጊዜ ጀምሮ የጸና ይሆናል።

## አንቀጽ 152 ስለ የመከታተል መብት

(1) መያዣ የሆነው መደብር ወደ ማንም እጅ ቢተላለፍ መያዣነቱ የሚከተለው ስለሆነ የዋስትና መያዣ ያለው ገንዘብ ጠያቂ መያዣው ለሦስተኛ ወገን ተላልፎም ቢገኝ ለማስያዝ ይችላል፡፡

(2) ይህንንም የያዘው ሦስተኛ ወገን የሆነው ሰው በዋስትና መያዣነት ገንዘብ ጠያቂዎች ለሆኑት የሚፈልጉትን ገንዘብ በሙሉ ካልከፈላቸው በስተቀር መያዣ የሆነ የንግድ መደብር እንዳይያዝ ለማድረግ አይቻልም፡፡

**አንቀጽ 153 የዋስትና መያዣ የአፈጻጸሙ ወሰን**

(1) በዋስትና መያዣነት መሰረት የንግድ መደብሩ እንዲከበር (እንዲያዝ) ሲታዘዝ በዚሁ ጊዜ የንግድ መደብሩ በሚገኝበት ሁኔታ፤ እንዲሁም የመደብሩ አካል የሆኑ ንብረቶች የዋጋቸው ዝቅተኛነት ወይም ከፍተኛነት ከግምት ውስጥ ሳይገባ ባሉበት ሁኔታ መያዣው ይጸናባቸዋል፡፡

(2) የዋስትና መያዣው ተፈፃሚ የሚሆነው በመዝገቡ ውስጥ በግልፅ በተመለከቱት የንግድ መደብሩ ንብረቶች ላይ ነው።

**አንቀጽ 154 የቀደምትነት መብት**

(1) ከንግድ መደብር ሽያጭ ዋጋ ላይ የዋስትና መያዣ ያላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች የቀዳሚነት መብት አሏቸው፡፡

(2) የዋስትና መያዣ ያላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች የቀደምትነት ደረጃ በተመዘገቡበት ቀን ቅደም ተከተል መሠረት ይወሰናል። ሆኖም የዋስትና መያዣቸውን በአንድ ቀን ውስጥ ያስመዘገቡ ገንዘብ ጠያቂዎች እኩል ደረጃ ይኖራቸዋል።

(3) ሆኖም ሻጩ በንግድ መደብሩ ላይ ያለው ከሕግ የመነጨ የዋስትና መያዣ ከውል ከመነጨ የዋስትና መያዣ ቅድሚያ ይኖረዋል።

**አንቀጽ 155 የዋስትና መያዣ ያለው ከሰረው ባለዕዳ ገንዘብ ጠያቂዎችን መቃወም ስለመቻሉ**

በንግድ መደብር ላይ የተመዘገበ የዋስትና መያዣ ያላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች ከከሰረው ባለዕዳ ገንዘብ በሚጠይቁት ላይ መቃወሚያ ስለሚያደርጉበት ሁኔታ በዚህ ሕግ በሦስተኛ መጽሐፍ የተመለከቱት አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ ፡፡

## ምዕራፍ አምስት

## የንግድ መደብርን ስለ ማከራየት

**አንቀጽ 156 የፍትሐ ብሔር ሕግ ተፈጻሚ ስለመሆኑ**

(1) የንግድ መደብርን ለማከራየት ይቻላል።

(2) በዚህ ሕግ ከአንቀጽ 157 እስከ 167 የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው የንግድ መደብር ኪራይን በተመለከተ በፍትሐ ብሔር ሕግ በቁጥር 2896-2974 የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ።

**አንቀጽ 157 የኪራይ ውልን በጋዜጣ ስለማስታወቅ**

(1) የንግድ መደብር የኪራይ ውል በጽሑፍ ካልሆነና ከተዋዋይ ወገኖች ባንዱ አመልካችነት የንግድ መደብሩ ዋና መሥሪያ ቤት በሚገኝበት አከባቢ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ካልወጣ ሦስተኛ ወገኖችን መቃወሚያ ሊሆን አይችልም፡፡

(2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚወጡ ማስታወቂያዎች፡-

(ሀ) የአከራዩንና የተከራዩን ስምና አድራሻ፣

(ለ) ውሉ የተደረገበት ቀንና የውሉን ዓይነት፣

(ሐ) የንግድ መደብሩን አላማና አድራሻ፣ እና

(መ) የኪራዩ ውል ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ፤

መግለፅ አለበት።

**<u>አንቀጽ 158 የንግድ ምዝገባን ስለ ማስተካከል</u>**

(1) በኪራይ የተሰጠው የንግድ መደብር ባለቤት (ባለሃብት) ከንግድ መዝገብ ስሙን ማሰረዝ አለበት፡፡ ሆኖም አከራዩ በኪራይ ውሉ ውስጥ ያልተካተቱ ሌሎች መደብሮች ያሉት እንደሆነ ስሙ ከንግድ መዝገብ ሳይሰረዝ የተከራየውን መደብር በተመለከተ አግባብ ያለው ለውጥ በንግድ መዝገብ ውስጥ እንዲገባ ይደረጋል፡፡

(2) ተከራዩም በዚህ ሕግ ርዕስ አራት በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት የራሱን ስም በንግድ መዝገብ ውስጥ ማስመዝገብ አለበት፡፡

**<u>አንቀጽ 159 ስለ ንግድ መደብር አከራይ ኃላፊነት</u>**

በዚህ ሕግ በአንቀጽ 157 እና 158 በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት አስፈላጊው ሁሉ እስኪሟላና ከተሟላበትም ቀን አንስቶ ባለው አንድ ወር ጊዜ ውስጥ ተከራዩ የንግድ መደብሩን ሥራ በማከናወን ሂደት ለገባው እዳ ሁሉ የንግድ መደብሩ ባለቤት ከተከራዩ ጋራ በአንድነትና በተናጠል ኃላፊ ይሆናል፡፡

**<u>አንቀጽ 160 በንግድ ወረቀቶች ላይ ተከራይ መሆኑን ስለ መጥቀስ</u>**

ተከራዩ በንግድ ወረቀቶች ላይ ሁሉ ተከራይነቱን ‹‹ተከራይ›› የሚል ቃል ጨምሮ ካልገለፀ የኪራይ ውሉ ፈራሽ ሊሆን ይችላል።

**<u>አንቀጽ 161 ስለ ተከራዩ ግዴታዎች</u>**

ተከራዩ የተስማማበትን ኪራይ በትክክል ካልከፈለ ወይም እንደ መልካም ነጋዴ ለንግድ መደብሩ ጥቅም ካላስገኘ ወይም ስራውንም በንግዱ መደብር ዓይነት በትክክል ካላካሄደ፤ የኪራይ ውሉ ፈራሽ ይሆናል፡፡

**<u>አንቀጽ 162 የዋስትና ገንዘብ ስለ ማስቀመጥ</u>**

(1) ተከራዩ ለአከራዩ ወይም ለሦስተኛ ወገኖች ያሉበትን ግዴታዎች የሚፈጽም መሆኑን ለማረጋገጥ የሚስችል በውሉ ከተወሰነው ኪራይ በላይ ዋስትና እንዲያስይዝ በውሉ ውስጥ ሊጠየቅ ይችላል፡፡

(2) ተቃራኒ የሆነ ስምምነት ቢኖር እንኳ ተከራዩ ለአከራዩ ያሉበትን ግዴታዎች የፈጸመ ሲሆንና በዚህ ሕግ በአንቀጽ 164(3) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ገንዘብ ጠያቂዎች እንዲያዝ ያላመለከቱ እንደሆነ የኪራይ ውሉ እንደተቋረጠ ተከራዩ የሰጠው ዋስትና ሙሉ ለሙሉ ይመለስለታል።

**<u>አንቀጽ 163 ንግዱ በተከራዩ በራሱ መከናወን ያለበት ስለመሆኑ</u>**

የኪራዩ ውሉ የተከራዩን የግል ብቃት መሠረት አድረጎ የተደረገ በመሆኑ ተከራዩ ከአከራዩ የጽሑፍ ፈቃድ ሳያገኝ ውሉን አሳልፎ ለሌላ ሰው መስጠት አይችልም፡፡

**አንቀጽ 164 የኪራዩ ውል ጊዜ ማብቃቱን በጋዜጣ ስለ ማስታወቅ**

(1) የኪራዩ ውል ጊዜ ማብቃቱ በዚህ ሕግ አንቀጽ 157(1) በተደነገገው መሠረት በጋዜጣ እንዲታተም መደረግ ይኖርበታል፡፡

(2) በንዑስ ቁጥር (1) መሠረት የሚወጣውም ማስታወቂያ፡-

(ሀ) የከራዩና የተከራዩን ስምና አድራሻ፤

(ለ) የንግዱ መደብር ዓይነትና አድራሻ፤

(ሐ) የኪራይ ውሉ ዘመን ያበቃበትን ቀን፤

(መ) በአንቀጽ 162 መሠረት በዋስትና የተቀመጠ ገንዘብ ካለ ልኩ መጻፍ አለበት፡፡

(3) በአንቀጽ 162 መሠረት በዋስትና የተያዘው ገንዘብ ከመጨረሻው የማስታወቂያ ቀን አንስቶ አንድ ወር ሳይሞላ ለተከራዩ የተመለሰለት እንደሆነ ሦስተኛ ወገኖች ላይ ለሚደርስ ጉዳት የንግዱ መደብር ባለቤት ኃላፊነት አለበት፡፡

**አንቀጽ 165 ስለ ተከራዩ ዕዳዎች አከፋፈል አስገዳጅነት**

የኪራይ ውሉ ጊዜ ሲያበቃ ተከራዩን ገንዘብ ጠያቂ ለሆኑት ሰዎች ያሉበትን ዕዳዎች ወዲያውኑ እንዲከፍል ያስገድደዋል።

**አንቀጽ 166 አከራዩ ተወዳዳሪ የሆነ ንግድ እንዳያካሂድ ስለ መከልከሉ**

(1) የንግዱን መደብር ያከራየ ባለቤት የኪራይ ውሉ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ተመሳሳይ የንግድ ዓላማ ያለውን ሌላ የንግድ መደብር በማቋቋም ወይም በመግዛት ወይም በሌላ መንገድ እንዲተላለፍለት በማድረግ ተከራዩን በንግድ ሊወዳደረው አይችልም።

(2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን ግዴታውን ባለቤቱ ተላልፎ ቢገኝ ኪሣራ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡ ያቋቋመውም የንግድ መደብርም እንዲዘጋ ሊደረግ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 167 ተከራዩን ተወዳዳሪ የንግድ ሥራ እንዳይሠራ መከልከል ስለ መቻሉ**

(1) የኪራዩ ውል ከተፈጸመ በኋላ ተከራዩ የንግዱ መደብር ባለቤት የሚሰራውን የንግድ ሥራ ዓይነት በመሥራት እንዳይወዳደር በውል ለመስማማት ይቻላል።

(2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ክልከላ ከአምስት ዓመት መብለጥ አይችልም።

## ምዕራፍ ስድስት
## የንግድ መደብርን ለማኅበርተኝነት ድርሻ መዋጮ ስለ ማድረግ

**አንቀፅ 168 መዋጮን በግልጽ ማስታወቂያ ስለ መግለጽ**

የንግድ መደብርን በመቋቋም ወይም በመካሄድ ላይ ላለ የንግድ ማኅበር ለማኅበርተኝነት ድርሻ መዋጮ እንዲሆን ከተደረገ በዚህ ሕግ በአንቀጽ 157 (1) እንደተመለከተው ታትሞ መታወቅ አለበት፡፡

**አንቀጽ 169 በማስታወቂያ ላይ ስለሚገለጹ ነገሮች**

በአንቀጽ 168 መሠረት የሚወጣው ማስታወቂያ፡-

(1) የመዋጮ አድራጊው ስምና አድራሻ፣

(2) መዋጮ የሆነው የንግድ መደብር ዓላማና አድራሻ፣

(3) መዋጮ የተደረገለን የንግድ ማኅበር ስም፤ ዓይነትና የዋናው መሥሪያ ቤት አድራሻ፣

(4) የማኅበሩ የመመስረቻ ጽሑፍ የወጣበትን ቀን፣

መግለጽ ይኖርበታል።

**አንቀጽ 170 መዋጮን ስለ መቃወም**

(1) በአንቀጽ 168 መሠረት የመጨረሻው ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን አንስቶ በአንድ ወር ጊዜ በማኅበርተኝነት መዋጮ ከሚሰጠው ሰው ላይ ገንዘብ ጠያቂ የሆኑ ሁሉ የዕዳው መክፈያ ጊዜ ያልደረሰም ቢሆን ለንግድ ማኅበሩ ዋና መሥሪያ ቤት በጽሑፍ በማስታወቅ የቀረበው የማኅበርተኝነት መዋጮው እንዳይደረግ መቃወም ይችላሉ፡፡

(2) ማስታወቂያ ሳይወጣ ከቀረ ወይም ማስታወቂያው ዋጋ የሌለው በሆነ ጊዜ የተወሰነውን ጊዜ መጠበቅ ሳያስፈልግ ገንዘብ ጠያቂው በማናቸውም ጊዜ ለመቃወም ይችላል።

**አንቀጽ 171 ማኅበርተኞቹ መውሰድ ስለሚችሉት እርምጃ**

(1) ማንኛውም ማኅበርተኛ በአንቀጽ 170 መሠረት መቃወሚያው ከቀረበበት ጊዜ አንስቶ በአንድ ወር ውስጥ በመቋቋም ላይ ያለው ማኅበር እንዲፈርስ ወይም ቀድሞ ለነበረ ማኅበር የተደረገው መዋጮ እንዲሰረዝ ፍርድ ቤትን ለመጠየቅ ይችላል።

(2) በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ተቃውሞ ካልቀረበና መዋጮው ከተሰረዘ የንግድ ማኅበሩና መዋጮ አድራጊው በአንድነትና በተናጥል ተጠያቂዎች ናቸው።

# ሁለተኛ መጽሐፍ

# የንግድ ማኅበራት

## ርዕስ አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ 172 ትርጓሜ**

1) የንግድ ማኅበር ማለት ሰዎች መዋጮ አዋጥተው በህብረት በኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ በመሰማራት ከሚገኘው ትርፍ ተካፋይ ለመሆን በመመስረቻ ጽሑፍ አማካኝነት የሚያቋቋሙት ማኅበር ነው፡፡
2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም ባለአንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር እንደ ማኅበር ይቆጠራል፡፡

**አንቀጽ 173 የመመስረቻ ጽሑፍ**

1) የመመስረቻ ጽሑፍ ማለት የንግድ ማኅበር ለመመስረት የሚዘጋጅ ሰነድ ነው፡፡
2) የመመስረቻ ጽሑፍ ናሙና የንግድ ማኅበራትን በሚመዘግብ መስሪያ ቤት ሊዘጋጅ ይችላል፡፡
3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ስር የተመለከተው ቢኖርም፤ የማኅበርተኞች የመዋዋል ነጻነት የተጠበቀ ነው፡፡ በተለይም የማኅበርተኞች ስምምነት በመንግስት መስሪያቤት በሚዘጋጅ ናሙና እንዲገደብ የሚያዝ ማንኛውም ሕግም ሆነ አሰራር ዋጋ አይኖረውም፡፡

**አንቀጽ 174 የንግድ ማኅበር ዓይነቶች**

የንግድ ማኅበር ዓይነቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

1) የኅብረት ሽርክና ማኅበር፤
2) ሁለት ዓይነት ኃላፊነት ያለበት የሽርክና ማኅበር፤
3) ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር፤
4) የእሽሙር ማኅበር፤
5) የአክሲዮን ማኅበር፤
6) ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር፤
7) ባለአንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር፡፡

**አንቀጽ 175 የንግድ ማኅበር ሕጋዊ ሰውነት ስለሚያገኝበት ሁኔታ**

ከእሽሙር ማኅበር በስተቀር ሁሉም የንግድ ማኅበራት በንግድ መዝገብ እንደተመዘገቡ የሕግ ሰውነት ያገኛሉ፡፡

**አንቀጽ 176 የንግድ ማኅበር ስም**

የንግድ ማኅበር ስም ሊኖረው ይገባል፡፡ ስሙም ከሌላ ነጋዴ ወይም ማኅበር ጥቅም ጋር የሚጋጭ እንዲሁም ለሕግና ለሕዝብ ሞራል ተቃራኒ መሆን የለበትም፡፡

**አንቀጽ 177 የንግድ ማኅበር ስለሚቋቋምበት ሁኔታ**

ማንኛውም የንግድ ማኅበር በመመስረቻ ጽሑፍ ካልተቋቋመ በስተቀር ውጤት አይኖረውም፡፡

**አንቀጽ 178 ፈራሽ ስለሆኑ ስምምነቶች**

የማኅበሩን ትርፍ ወይም ኪሳራ ለአንድ ወይም ለተወሰኑ አባላት ብቻ እንዲሆን የሚያደርግ ስምምነት ፈራሽ ነው፡፡

**አንቀጽ 179 ስለውክልና**

1) ማንኛውም ማኅበር ስለውክልና በተመለከተው ህግ መሰረት ውክልና የሰጣቸው ሰዎች ለሰሩት ስራ ባለመብትና ባለ እዳ ይሆናል፡፡
2) ማኅበሩ ውክልና በሰጣቸው ሰዎች መከሰስ ወይም መከሰስ ይችላል፡፡
3) ለንግድ ማኅበሩ እንዲደርስ የተጻፈ ማንኛውም መጥሪያ ለማህበሩ ዋና መስሪያ ቤት እንዲደርስ መደረግ አለበት፡፡

**አንቀጽ 180 የሚተላለፉ የግዴታ ወረቀቶች**

ከአክሲዮን ማኅበር በስተቀር ሌሎች የንግድ ማኅበራት የሚተላለፉ የግዴታ ወረቀቶችን ማውጣት አይችሉም፡፡

**አንቀፅ 181 የንግድ ማኅበር ስለሚፈርስበት ሁኔታ**

የንግድ ማኅበር በሚከተሉት ምክንያቶች ይፈርሳል፡-

1) የተቋቋመበትን ዓላማ ሲፈጽም ወይም ለመፈጸም ሳይችል ሲቀር፤
2) የማኅበሩ አባላት እንዲቀጥል ካልተስማሙ በስተቀር የማኅበሩ የቆይታ ጊዜ ሲጠናቀቅ፡፡
3) ማኅበርተኞች የንግድ ማህበሩ እንዲፈርስ ሲስማሙ፡፡
4) በማኅበሩ አባላት መካከል ተቃራኒ ስምምነት ቢኖርም እንኳ በማኅበሩ አባላት ጥያቄ ፍርድ ቤት በበቂ ምክንያት ማኅበሩ እንዲፈርስ ሲወስን፤ ወይም
5) የማኅበሩ መክሰር በፍርድ ቤት ሲወሰን፡፡

**አንቀጽ 182 ከንግድ መዝገብ ስለመሰረዝ**

1) አንድ የንግድ ማኅበር ሲፈርስና ሒሳቡ ተጣርቶ እንዳበቃ የሒሳብ አጣሪዎች ማኅበሩ ከንግድ መዝገብ እንዲሰረዝ ለንግድ ማኅበር መዝጋቢው አካል ማመልከት አለባቸው
2) የንግድ ማኅበሩ መሰረዝ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ከተገለጸበት ቀን ጀምሮ ሕጋዊ ሰውነቱን ያጣል፡፡

## ርዕስ ሁለት
## የኅብረት ሽርክና ማኅበር

### ምዕራፍ አንድ
### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ 183 ትርጓሜ**

የኅብረት ሽርክና ማኅበር ማለት እያንዳንዱ ማህበርተኛ ለማኅበሩ ግዴታዎች ከማሕበሩ ጋር በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ የሚሆንበት የንግድ ማኅበር ነው፡፡ ማንኛውም ተቃራኒ ስምምነት ሦስተኛ ወገኖችን መቃወሚያ ሊሆን አይችልም፡፡

**አንቀጽ 184 የማኅበሩ ስም**

1) ማኅበሩ የሁሉንም ሽሪኮች ስም ወይም ቢያንስ የሁለት ሽሪኮችን ስም የያዘ መጠሪያ ይኖረዋል፡፡ ከሽሪኮቹ ስም ቀጥሎም "የኅብረት ሽርክና ማኅበር" ተብሎ መጻፍ አለበት፡፡ የማኅሩ ስም ከሽሪኮች ስም በስተቀር ሌላ ስም ሊኖርበት አይችልም፡፡
2) ስሙ በማኅበሩ ስም ላይ የተገለጸ ሽሪክ ከማኅበሩ የወጣ እንደሆነ የማኅበሩ ስም መለወጥ አለበት፡፡
3) የማኅሩ ሽሪክ ያልሆነ ሰው እያወቀ ስሙ በማኅበሩ ስም ውስጥ ሲጻፍ ያልተቃወመ እንደሆነ እንደሌሎች አባላት ለማኅበሩ ግዴታዎች ኃላፊ ይሆናል፡፡

### ምዕራፍ ሁለት
### የማኅበሩ አመሠራረት

**አንቀጽ 185 የማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ**

የማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን መያዝ ይኖርበታል፡-

1) የማኅበሩን ስም፤
2) የማኅበሩን ዋና መሥሪያ ቤትና እንዳሉም ቅርንጫፎችን፤
3) የእያንዳንዱን ሽሪክ ስም፣ አድራሻና ዜግነት፤
4) ማኅበሩ የተመሠረተበትን ዓላማ፤
5) እያንዳንዱ ሽሪክ ያዋጣውን የገንዘብ መጠን፤ የተከፈለው የዓይነት መዋጮ ከሆነ የገንዘብ ግምቱን እና የአገማመት ዘዴ፤
6) የሙያ አገልግሎት መዋጮ ያዋጣ አባል ካለ ያለበትን ግዴታ፤
7) የእያንዳንዱን ሽሪክ የትርፍ እና የኪሳራ ተከፋይነትና የትርፍ አከፋፈል ሁኔታ፤
8) የማኅበሩን ስራ አስኪያጅና እንዳለም ወኪል እንዲሁም የሥራ ስኪያጁን ስልጣንና ተግባር፤

**9)** ማኅበሩ የሚቆይበትን ጊዜ፤

**10)** በሕግ ወይም በሸሪኮች ስምምነት እንዲካተቱ የተወሰኑ ሌሎች ጉዳዮችን፡፡

**<u>አንቀጽ 186 የመዋጮ ዓይነትና መጠን</u>**

**1)** እያንዳንዱ ሸሪክ ጥሬ ገንዘብ፣ የሚንቀሳቀስ ወይም የማይንቀሳቀስ ንብረት፣የሞያ አገልግሎት፣ የንግድ ምልክት፣ መልካም ስም፣ ፓተንት፣ የሊዝ መብት፣ የአላባ ጥቅም ወይም ሌላ የዓይነት መዋጮ መክፈል አለበት፡፡

**2)** መዋጮው የማኅበሩ ሃብት እንዲሆን ወይም ማኅበሩ እንዲጠቀምበት ሆኖ ሊከፈል ይችላል፡፡

**3)** ሸሪኮች ለማኅበሩ የሚያስገቡት መዋጮ የማኅበሩን ዓላማ ለማሳካት የሚያስፈልገው ዓይነትና መጠን እንዲሁም ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በስተቀር መጠኑ እኩል መሆን አለበት፡፡

**4)** የዓይነት መዋጮ ግምት በሸሪኮች ስምምነት ይወሰናል፡፡

**5)** በዓይነት የተከፈለ መዋጮ ግምት ከዋጋው በላይ ሆኖ ከተገኘ ያዋጣው ሸሪክ በግምቱና በትክክለኛው ዋጋው መካከል ያለውን ልዩነት በጥሬ ገንዘብ መክፈል አለበት፡፡ ልዩነቱን በጥሬ ገንዘብ መክፈል ካልቻለ ድርሻው በትክክለኛው ግምት መሠረት ይሆናል፡፡

**<u>አንቀጽ 187 ዋስትና</u>**

**1)** የሙያ አገልግሎትን ሳይጨምር የዓይት መዋጮ የከፈለ ሸሪክ ያለበት ዋስትና በፍትሐብሔር ሕጉ የሽያጭ ውል ክፍል ስለሻጭ ግዴታ በተደነገገው መሠረት ይሆናል፡፡

**2)** የተከፈለው መዋጮ በንብረት የመጠቀም መብት ብቻ ከሆነ መዋጮውን የከፈለው ሸሪክ ያለበት ዋስትና በፍትሐብሔር ሕጉ የኪራይ ውል ክፍል የአከራይን ግዴታ በሚመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ይሆናል፡፡

**3)** የተደረገው መዋጮ ገንዘብ የመቀበል መብት ከሆነ መዋጮውን ያደረገው ሸሪክ ያለበት ዋስትና በፍትሐብሔር ሕጉ የብድር ውል ክፍል የተበዳሪን ግዴታ በሚመለከቱ ድንጋጌዎች መሠረት ይመራል፡፡

**<u>አንቀጽ 188 ለመድረስ የሚችል አደጋ</u>**

**1)** ለማኅበሩ የተከፈለው መዋጮ ንብረት ከሆነ በንብረቱ ላይ ሊደርስ የሚችል አደጋ በፍትሐብሔር ሕጉ ሽያጭን በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ለማኅበሩ ይተላለፋል፡፡

**2)** ለማኅሩ የተከፈለው መዋጮ በንብረት የመጠቀም መብት ብቻ ከሆነ በንብረት ጥቅሙ ላይ ለሚደርስ አደጋ ያዋጣው ሸሪክ ኃላፊ ይሆናል፡፡

**<u>አንቀጽ 189 መዋጮ በጊዜው አለመከፈል የሚያስከትለው ኃላፊነት</u>**

መዋጮ በወቅቱ ያልከፈለ ሸሪክ መክፈል ከነበረበት ቀን ጀምሮ ለማኅበሩ ወለድ መክፈል አለበት፡፡

**<u>ምዕራፍ ሦስት</u>**

**<u>የማኅበሩ ሸሪኮች መብቶችና ግዴታዎች</u>**

**<u>አንቀጽ 190 የማኅበሩ ሽሪኮች መብቶች</u>**

እያንዳንዱ የማኅበሩ ሽሪክ የሚከተሉት መብቶች አሉት፡-

**1)** በማኅበሩ ስብሰባዎች የመሳተፍና ድምጽ የመስጠት፤

**2)** ከማኅበሩ ትርፍ ድርሻውን የመካፈል፤

**3)** ስለማኅበሩ አሰራር ጥያቄ የማቅረብ፣የሒሳብ መግለጫዎችን እና ሰነዶችን የማየት፤ ማስታወሻ የመውሰድ፤

**4)** የማኅበሩ ቆይታ ከአንድ ዓመት በላይ ሲሆን በየዓመቱ መጨረሻ የሥራ ክንውን ሪፖርት እንዲቀርብ የመጠየቅ፤

**5)** ማኅበሩ ሲፈርስ ከማኅበሩ ሃብት ድርሻውን የመካፈል፤ እና

**6)** ሌሎች ከማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ ወይም ከማኅበር ሽሪክነት የሚመነጩ መብቶችንና ጥቅሞችን የማግኘት፡፡

**<u>አንቀጽ 191 የማኅበሩ ሽሪኮች ግዴታዎች</u>**

**1)** እያንዳንዱ የማኅበሩ ሽሪክ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ግዴታዎች አሉበት፡-

**(ሀ)** የማኅበሩን መዋጮ በወቅቱ የመክፈል፤

(ለ) የማኅበሩን ዓላማ ለማሳካት በትጋትና በጥንቃቄ የመሥራት፤

**(ሐ)** ለግልም ሆነ ለሦስተኛ ወገን ጥቅም የማኅበሩን ጥቅም የሚጎዳ ተግባር አለመሥራት፤

**(መ)** ለማኅበሩ ዕዳዎች በአንድነትና በነጠላ ተጠያቂ የመሆን፤

**(ሠ)** ሌሎች ከመመስረቻ ጽሑፍና ከማኅበሩ ሽሪክነት የሚመነጩ ግዴታዎችን የመወጣት፡፡

**2)** ከማኅበሩ ላይ ገንዘብ የሚጠይቁ ሰዎች ማኅበሩ ያለበትን ዕዳ እንዲከፍል አስቀድመው ማስጠንቀቂያ ካልሰጡ በስተቀር የማኅበሩ ሽሪኮችን መጠየቅ አይችሉም፡፡ ሆኖም ሽሪኮች ትርፍ ሳይኖር እንደትርፍ ድርሻዎች ከማኅበሩ ገንዘብ ተቀብለው እንደሆነ የተቀበሉትን ገንዘብ እንዲመልሱ በማናቸውም ጊዜ ሽሪኮችን በቀጥታ መጠየቅ ይችላሉ፡፡

**<u>አንቀጽ 192 የትርፍና ኪሳራ ክፍፍል መሰረት</u>**

1) ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በቀር እያንዳንዱ ማኅበርተኛ ለማኅበሩ ያስገባው የመዋጮ ዓይነትና ዋጋ ምንም ቢሆን ከማህበሩ ትርፍና ኪሳራ እኩል ድርሻ አለው፡፡

**2)** የተደረገው ውል የትርፍ አከፋፈልን ወይም የኪሳራ አከፋፈልን ብቻ የተመለከተ እንደሆነ የተመለከተው ውሳኔ በትርፍም ሆነ በኪሳራው ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**<u>አንቀጽ 193 አዲስ ሽሪክ ስለማስገባት</u>**

በማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ የተለየ ድንጋጌ ከሌለ በስተቀር አዲስ ሸሪክ ወደ ማኅበሩ ማስገባት የሚቻለው ሁሉም የማኅበሩ ሸሪኮች ሲስማሙበት ነው፡፡

**<u>አንቀጽ 194 የማኅበሩ ድርሻዎች ለሌላ ማህበርተኛ ስለሚተላለፉበት ሁኔታ</u>**

በማኅበሩ የመመስረቻ ጽሑፍ የተለየ ድንጋጌ ከሌለ በስተቀር አንድ ሸሪክ ድርሻውን ለሌላ የማኅሩ አባል የማስተላለፍ መብት አለው፡፡

**<u>አንቀጽ 195 ከማኅበሩ የወጣ ሸሪክን ድርሻ ስለመክፈል</u>**

1) አንድ ሸሪክ ድርሻውን ለሌላ ማህበርተኛ ወይም ለሦስተኛ ወገን ሳያስተላልፍ ከማህበሩ ከወጣ እና ማኅበሩ ሥራውን ከቀጠለ በማህበርተኞቹ ስምምነት መሰረት የሚወሰን ክፍያ ይሰጠዋል፡፡
2) ስለዚህ ጉዳይ ስምምነት የሌለ እንደሆነ በማኅበሩ ውስጥ የነበረው ገቢ የተደረገ መዋጮ፤የማህበሩ እዳዎች ከተከፈሉ በኋላ ከሚቀረው ተራፊ ሀብት ወይም የተጠራቀመ ትርፍ የራሱን ድርሻ እና በወጣበት ወቅት በመሰራት ላይ የነበሩ ስራዎች የሚያስገኙት ትርፍ ግምት ውስጥ ያስገባ መጠን ታስቦ በገንዘብ ይከፈለዋል፡፡

**<u>አንቀጽ 196 ከማኅበሩ የወጣ ሸሪክ ተጠያቂነት</u>**

ከማኅበር የወጣ ሸሪክ ከመውጣቱ በፊት ማኅበሩ ለገባባቸው ዕዳዎችና ኃላፊነቶች ከማኅበሩ ጋር በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ ይሆናል፡፡ ሆኖም የማህበሩ ገንዘብ ጠያቂዎች ከፈቀዱ ኃላፊነቱ በሱ እግር ለተተካው ሰው ይተላለፋል፡፡

**<u>አንቀጽ 197 ከድርሻ የሚገኝ ጥቅምና መብትን ለሦስተኛ ወገኖች ስለማስተላለፍ</u>**

**1)** አንድ ሸሪክ የሌሎችን ሸሪኮች ፈቃድ ሳይጠይቅ በማኅበሩ ውስጥ ካለው ድርሻ የሚገኙ መብቶችና ጥቅሞችን ሦስተኛ ወገኖች እንዲጠቀሙባቸው ማድረግ ይችላል፡፡
**2)** ከድርሻ የሚገኙ መብቶችና ጥቅሞች ሦስተኛ ወገን እንዲጠቀምባቸው የሚያደርግ ስምምነት ማኅበሩን ግዴታ ውስጥ አያስገባውም፡፡ እንዲሁም የማኅበር ሸሪክነት መብት አያሰጥም፡፡

**<u>ምዕራፍ አራት</u>**

**<u>የማኅበሩ ሥራ አመራር</u>**

**<u>አንቀጽ 198 የማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ</u>**

**1)** ማኅበሩ ሸሪክ በሆኑ ወይም ባልሆኑ በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ሥራ አስኪያጆች ይመራል፡፡
**2)** የሥራ አስኪያጆች ቁጥር ከአንድ በላይ በሚሆንበት ጊዜ የሥራ ድርሻቸው ተለይቶ በጽሑፍ መገለጽ አለበት፡
:

**<u>አንቀጽ 199 የሥራ አስኪጁ ሥልጣንና ተግባር</u>**

**1)** ሥራ አስኪያጁ የማኅበሩን ዓላማ ለማሳካት በማኅበሩ ስም ማንኛውንም ሕጋዊ ተግባር ያከናውናል፡፡

2) የሥራ አስኪያጁን ሥልጣን የሚገድቡ ስምምነቶች ሦስተኛ ወገኖችን መቃወሚያ የሚሆኑት በንግድ መዝገብ የተመዘገቡ ወይም ሦስተኛ ወገኖች የሥራ ኃላፊነቱን የሚያዉቁ መሆናቸው የተረጋገጠ እንደሆነ ነው፡፡

3) የማኅበሩ ቆይታ ከአንድ ዓመት በላይ ሲሆን ሥራ አስኪያጁ በየዓመቱ መጨረሻ የማኅበሩን የሥራ ክንውን ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሸሪኮች ማቅረብ አለበት፡፡

**አንቀጽ 200 በሥራ አስኪያጅነት ሥልጣን አላግባብ መገልገል**

1) ሥራ አስኪያጁ በማኅበሩ ስም ለግል ጥቅሙ የሰራ እንደሆነ በቅን ልቦና ከሥራ አስኪያጁ ጋር ግንኙነት ላደረጉ ሦስተኛ ወገኖች ማኅበሩ ኃላፊ ነው፡፡ ሆኖም እነዚህ ሦስተኛ ወገኖች ሥራ አስኪያጁ የማኅበሩን ስም ያላግባብ መገልገሉን የሚያውቁ መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ኃላፊነቱ የሥራ አስኪያጁ ብቻ ይሆናል፡፡

2) ሥራ አስኪያጁ የማኅበሩን ስም ሳይጠቅስ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር ስምምነት ካደረገ ለግል ጉዳዩ እንዳደረገው ይቆጠራል፡፡ ሆኖም ሥራ አስኪያጁ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር ያደረገው ስምምነት ለማኅኑ ጥቅም የሆነ እንደሆነ ማኅበሩ ኃላፊ ይሆናል፡፡

3) ሥራ አስኪያጁ ከስልጣኑ በላይ ለሚሠራው ሥራ ሁሉ ኃላፊነቱ የማኅበሩ ሳይሆን የሥራ አስኪያጁ ብቻ ነው፡፡

**አንቀጽ 201 ከማኅበሩ ጋር የሚደረግ ስምምነት**

ሥራ አስኪያጁ የሁሉንም የማኅኑ ሸሪኮች ፈቃድ ካላገኘ በስተቀር ለግል ጉዳዩ ወይም ለሦስተኛ ወገኖች ጥቅም ከማኅበሩ ጋር ስምምነት ማድረግ አይችልም፡፡

**አንቀጽ 202 ውድድርን ስለመከልከል**

ማንኛውም የማኅበሩ ሸሪክ ሌሎች ሸሪኮች ካልፈቀዱ በስተቀር ማኅበሩ የሚያከናውቸውን ተመሳሳይ ሥራዎች ለራሱም ሆነ ለሦስተኛ ወገኖች ጥቅም ማከናወን አይችልም፡፡ እንዲሁም የአንድነትና የነጠላ ተጠያቂነት የሚያስከትል ተመሳሳይ ዓላማ ባለው ሌላ ማኅበር ውስጥ ሸሪክ መሆን አይችልም፡፡

**አንቀጽ 203 ሥራ አስኪያጁን ስለመሻር**

1) በመመስረቻ ጽሑፍ ወይም በማሻሻያው የተሾመ የማህበሩ አባል የሆነ ሥራ አስኪያጅ የመመስረቻ ጽሑፍ ወይም ማሻሻያው በሚጸድቅበት ሥነ-ሥርዓት መሠረት በሸሪኮች ሊሻር ይችላል፡፡

2) የማህበሩ አባል ያልሆነ ሥራ አስኪያጅ እንዲሁም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ያልተሾመ የማሕበሩ ሸሪክ ሥራ አስኪያጅ በሸሪኮች በድምጽ ብልጫ ከሥራ አስኪያጅነት ሊሰናበት ይችላል፡፡

3) በማንኛውም ሸሪክ ጥያቄ በበቂ ምክንያት ሥራ አስኪያጁን ፍርድ ቤት ይሸረዋል፡፡

**አንቀጽ 204 የማኅበሩ ውሳኔ አሰጣጥ**

1) የማኅበሩን መመስረቻ ጽሑፍ ለመለወጥ ወይም ጠበቃ ለመሾም ወይም በማኅበሩ ከተለመደው ሥራ ውጭ ለማከናውን የማኅበሩ ሸሪኮች ሙሉ ስምምነት ያስፈልጋል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ሸሪኮች ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ እንዲተላለፉ ሊስማሙ ይችላሉ፡፡ ሸሪኮች የዚህ አይነት ስምምነት ያላደረጉ እንደሆነ ውሳኔዎች የሚተላለፉት በሙሉ ድምጽ ይሆናል፡፡

3) ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በስተቀር እያንዳንዱ ሸሪክ የሚኖረው ድምጽ እኩል ይሆናል፡፡

## ምዕራፍ አምስት

## የማኅበሩ መፍረስና ሒሳብ መጣራት

### አንቀጽ 205 የማኅበሩ ማፍረሻ ምክንያቶች

**1)** የዚህ መጽሐፍ ጠቅላላ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ማኅበሩ የሚፈርሰው ቀጥሎ በተመለከቱት ምክንያቶች ነው፡-

**(ሀ)** ማኅበሩ የተቋቋመው ላልተወሰነ ጊዜ ወይም ከማኅበሩ ሸሪክ በአንዱ እድሜ ልክ ድረስ ከሆነ ወይም በመመስረቻ ጽሁፉ ውስጥ የማፍረስ መብት ተጠቅሶ እንደሆነ ማንኛውም ሸሪክ በቅን ልቦና የስድስት ወራት የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት እንዲፈርስ ሲጠይቅ፤

**(ለ)** ከማኅበሩ ሸሪኮች አንዱ በአካል ጉዳት ወይም በሕመም ወይም በማንኛውም ሌላ ምክንያት የማኅበሩን ሥራ ለማከናውን ያልቻለ እንደሆነ፤

**(ሐ)** በማኅበሩ ሸሪኮች መካከል አብሮ ለመሥራት የማያስችል አለመግባባት ሲፈጠር፤

**(መ)** ከማኅበሩ ሸሪኮች አንዱ ሲሞት ወይም የማህበርተኛው መክሰር በፍርድ ሲወሰን ወይም ሸሪክ ለመሆን ችሎታ ሲያጣ፤

**(ሠ)** ከማኅበሩ ሸሪክ የግል ገንዘብ ጠያቂዎች ያለውን ድርሻ በሙሉ ሲወስዱ ወይም በቀሪው ድርሻ እንዲቀጥል ሌሎች የማኅበሩ ሸሪኮች የማይስማሙ ከሆነ፤

**2)** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (**1**) ላይ የተጠቀሰው ቢኖርም ቀጥሎ በተጠቀሱት ምክንያቶች ማኅበሩ ሳይፈርስ ሊቀጥል ይችላል፡-

**(ሀ)** ከሸሪኮች አንዱ ማኅበሩ እንዲፈርስ ጥያቄ ሲያቀርብና ቀሪዎቹ ሸሪኮች የሸሪኩን ድርሻ ከፍለው ማኅበሩ እንዲቀጥል ሲስማሙ፤ወይም

**(ለ)** ለሞተው ሸሪክ ወራሾች ወይም ችሎታ ላጣው ሸሪክ ሞግዚት ወይም ለከሰረው ሸሪክ ንብረት ጠባቂ የሚችን ወይም ችሎታ ያጣውን ሸሪክ ወይም የከሰረውን ሸሪክ ድርሻ በመክፈል ማኅበሩ እንዲቀጥል ስምምነት ሲደረግ፡፡

### አንቀጽ 206 ማኅበሩን በማፍረስ ሂደት የሥራ አስኪያጆች ስልጣንና ተግባር

1) ሥራ አስኪያጆች ማኅበሩን ለማፍረስ ሂሳብ አጣሪ እስኪሾም ድረስ የነበራቸውን ስልጣን እንደያዙ ይቆያሉ፡፡ ሆኖም ማኅበሩ እንዲፈርስ ከተወሰነ በኋላ አዲስ ሥራ መጀመር አይችሉም፡፡

2) ሥራ አስኪያጆች ለሒሳብ አጣሪዎች የማህበሩን ንብረትና ማንኛውንም አስፈላጊ ሰነድ ማስረከብና እስከ ርክክቡ ቀን ድረስ ያከናወኑትን ሥራ ማስረዳት አለባቸው፡፡

3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ሂሳብ አጣሪው የጠየቀ እንደሆነ የማህበሩን ሂሳብ የማጣራት ሥራ ከተጀመረ በኋላ የማፍረሱን ሂደት ለማጠናቀቅ የሚያስፈልጉትን አስተዳደራዊ ተግባራት ብቻ ያከናውናሉ፡፡

## አንቀጽ 207 ሒሳብ አጣሪዎችን ስለመሾም

1) ማኅበሩን ለማፍረስ የመጨረሻ ሒሳብ የሚጣራው በመመስረቻ ጽሑፍ ወይም በማኅበሩ ሸሪኮች ሙሉ ስምምነት በተመደቡ አንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ሒሳብ አጣሪዎች ነው፡፡

2) የማኅበሩ ሸሪኮች የማይስማሙ ከሆነ ፍርድ ቤት  አንድ ወይም ከአንድ በላይ ሒሳብ አጣሪ ይሾማል፡፡

## አንቀጽ 208 የሒሳብ አጣሪዎች ሥልጣንና ተግባር

1) ሒሳብ አጣሪዎች የማኅበሩ የመጨረሻ ሂሳብ እንዲጣራ አስፈረላጊ የሆኑትን ተግባሮች ሁሉ ይፈጽማሉ፡፡ ስልጣንና ተግባራቸው የሚከተሉትን ያካትታል፡-

(ሀ) ተጀምረው የነበሩ ሥራዎችን የማገባደድ፤

(ለ) የማኅበሩን የሃብትና ዕዳ መግለጫ የማዘጋጀት፤

(ሐ) የማኅበሩን ሃብት የመሰብሰብ፤ የማኅበሩን ንብረት የመሸጥ፤ የማኅበሩን ዕዳ ከማኅበሩ ሃብት ወይም እንዳስፈላጊነቱ ከሸሪኮች ሌላ ገንዘብ ሰብስቦ ለገንዘብ ጠያቂዎች የመክፈል፣

(መ) በማኅበሩ ስም በፍርድ ቤት፣ በአስተዳደር አካላት ወይም በግልግል ዳኝነት የመከራከርና ጉዳዮችን የማስፈጸም፣

(ሠ) የማኅበሩን ሃብት ለሸሪኮች የማከፋፈል፤

(ረ) ማኅበሩን ለማፍረስ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባራትን የማከናወን፡፡

2) የሥራ አስኪያጆችን ተጠያቂነት የሚመለከቱት የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች  በሒሳብ አጣሪዎች ላይም ተፈጻሚነት አላቸው፡፡

## አንቀጽ 209 ሒሳብ አጣሪዎች ስለሚሻሩበት ሁኔታ

ሒሳብ አጣሪዎች በሸሪኮች ሙሉ ስምምነት ወይም በአንድ ሸሪክ ጥያቄ  በፍርድ ቤት ሊሻሩ ይችላሉ፡፡

## አንቀጽ 210 መዋጮን ስለመመለስ

1) ማኅበሩ ሲፈርስ የማኅበሩ ዕዳዎች ከተከፈሉ በኋላ እያንዳንዱ ሸሪክ የከፈለው መዋጮ ይመለስለታል፡፡

2) ማኅበሩ እንዲጠቀምበት ብቻ የዓይነት መዋጮ ገቢ ላደረገ ሸሪክ ማኅበሩ ሲፈርስ ያስገባው መዋጮ በዓይነት ይመለስለታል፡፡

3) የማኅበሩ ሃብት እንዲሆን የዓይነት መዋጮ ገቢ ያደረገ ሸሪክ ማኅበሩ ሲፈርስ ያስገባውን መዋጮ በዓይነት መልሶ መውሰድ አይችልም፡፡ ሆኖም የዓይነት መዋጮውን ሲያስገባ የነበረውን የገንዘብ ግምት የመቀበል መብት አለው፡፡

4) አገልግሎትን እንደመዋጮ ያቀረበ ማኅበርተኛ መዋጮ ሲያደርግ ለአገልግሎቱ በተሰጠው ግምት መሰረት ያቀረበው አገልግሎት በገንዘብ ተተምኖ ይመለስለታል፡፡

**አንቀጽ 211 የትርፍና ኪሳራ አከፋፈል**

1) የማኅበሩ ዕዳዎች ከተከፈሉና እያንዳንዱ ሸሪክ የከፈለው መዋጮ ከተመለሰ በኋላ ትርፍ ካለ በአባለቱ መካከል ይከፋፈላል፡፡

2) የማኅበሩ ዕዳዎችና ወጪዎች ከተከፈሉ በኋላ የማኅበሩ ገንዘብ ለሸሪኮች የሚመለሰውን መዋጮ ለመከፈል የማይበቃ ከሆነ ኪሳራው በሸሪኮች መካከል ይከፋፈላል፡፡

3) በመመስረቻ ጽሑፉ ሌላ የአከፋፈል ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር ትርፍና ኪሳራው በሸሪኮች መካከል እኩል ይከፋፈላል፡፡

## ርዕስ ሦስት

## ሁለት ዓይነት ኃላፊነት ያለበት የሽርክና ማኅበር

**አንቀጽ 212 ትርጓሜ፡-**

ሁለት ዓይነት ኃላፊነት ያለበት የሽርክና ማኅበር ማለት የማኅበርተኞች ኃላፊነት የተለያየ የሆነበት ማኅበር ነው፡፡ ኃላፊነታቸው ያልተወሰነ ሸሪኮች ለማኅበሩ ግዴታዎች በሙሉ ከማኅበሩ ጋር በአንድነትና በተናጠል ኃላፊነት ያለባቸው ሲሆን ኃላፊነታቸው የተወሰነ ሸሪኮች ደግሞ መዋጮ ለማድረግ ቃል በገቡት መጠን ብቻ ለማኅበሩ ግዴታዎች ኃላፊ የሚሆኑ ናቸው፡፡

**አንቀጽ 213 የማኅበሩ ስም**

1) ሁለት ዓይነት ኃላፊነት ያለበት ማኅበር የማኅበር ስም ይኖረዋል፡፡

2) የማኅበሩ ስም ኃላፊነታቸው ያልተወሰነውን ሸሪኮች ስም የሚይዝ ሆኖ ከሸሪኮች ስም ቀጥሎ "ሁለት ዓይነት ኃላፊነት ያለበት የሽርክና ማኅበር" ተብሎ መጻፍ አለበት፡፡

3) ኃላፊነቱ የተወሰነ ሸሪክ ስሙ ከማኅበሩ ስም ውስጥ እንዲገባ የፈቀደ እንደሆነ ሦስተኛ ወገኖች በቅን ልቦና ከማኅበሩ ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት ምክንያት ለሚመጡ የማኅበሩ ግዴታዎች ልክ ኃላፊነታቸው ያልተወሰነ ሸሪኮች እንደሆኑት ሁሉ ከማኅበሩ ጋር በአንድነትና በተናጠል ኃላፊ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 214 የማኅበሩ መመሥረቻ ጽሑፍ**

የማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ በዚህ ሕግ አንቀጽ 185 ሥር ከተዘረዘሩት ጉዳዮች በተጨማሪ ኃላፊነታቸው ያልተወሰነውን እና የተወሰነውን ሸሪኮች ስም ለይቶ መያዝ አለበት፡፡

**<u>አንቀጽ 215 የማኅበሩ መዋጮ</u>**

1) መዋጮን የሚመለከቱት የዚህ ሕግ አንቀጽ 186 ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡
2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ኃላፊነታቸው የተወሰነ የማኅበሩ ሸሪኮች የሙያ መዋጮ ማዋጣት አይችሉም፡፡

**<u>አንቀጽ 216 ኃላፊነታቸው ያልተወሰነ ሸሪኮች መብትና ግዴታ</u>**

1) በዚህ ህግ የኀብረት ሽርከና ማኅበር ሸሪኮችን መብትና ግዴታ የሚመለከቱት ድንጋጌዎች ኃላፊነታቸው ባልተወሰነ የማኅበሩ ሸሪኮች ላይ ተፈጻሚነት አላቸው፡፡
2) በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ ወይም በሸሪኮች ውሳኔ የማኅበሩ ሸሪክ ያልሆነ ሥራ አስኪያጅ ካልተሾመ በስተቀር ሥራ አስኪያጅ መሆን የሚችሉት ኃላፊነታቸው ያልተወሰነ ሸሪኮች ናቸው፡፡

**<u>አንቀጽ 217 የጥቅም ግጭት</u>**

ሌሎች የማኅበሩ ሸሪኮች ካልፈቀዱ በስተቀር ማንኛውም ኃላፊነቱ ያልተወሰነ ሸሪክ ማኅበሩ የሚሠራቸውን ተመሳሳይ ሥራዎች ለራሱ ወይም ለሦስተኛ ወገን ለማከናወን እንዲሁም በአንድነትና በተናጠል ኃላፊ በሚያደርግ ተመሳሳይ ዓላማ ባለው ሌላ ማኅበር ውስጥ አባል መሆን አይችልም፡፡

**<u>አንቀጽ 218 ኃላፊነታቸው የተወሰነ የማኅበሩ ሸሪኮች መብትና ግዴታ</u>**

1) ከማኅበሩ ላይ ገንዘብ ጠያቂዎች ኃላፊነታቸው የተወሰነ ሸሪኮችን ለማኅበሩ ያልከፈሉትን መዋጮ ገቢ እንዲያደርጉ ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡
2) ኃላፊነታቸው የተወሰነ የማኅበሩ ሸሪኮች በተረጋገጠ የሂሳብ ሚዛን መሠረት በቅን ልቦና የተቀበሉትን የትርፍ ድርሻ እንዲመልሱ አይገደዱም፡፡
3) ኃላፊነታቸው የተወሰነ የማኅበሩ ሸሪኮች በውክልናም ሆነ በሌላ በማንኛውም ሁኔታ የማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ መሆን አይችሉም፡፡ ክልከላውን የተላለፈ ኃላፊነቱ የተወሰነ የማኅበሩ ሸሪክ በሥራው ምክንያት ለሚመጡ ግዴታዎች ኃላፊነታቸው ካልተወሰነው ሸሪኮች ጋር በአንድነትና በተናጠል ኃላፊ ይሆናል፡፡ ይህን ክልከላ ከተላለፈባቸው ጊዜያት ብዛት እና ከጉዳዩ ክብደት አኳያ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለሁሉም የማኅበሩ ግዴታዎች ወይም ለተወሰኑ የማኅበሩ ግዴታዎች ብቻ ከማኅበሩ ጋር በአንድነትና በተናጠል ኃላፊ ነው ተብሎ ሊወሰን ይችላል፡፡
4) ኃላፊነታቸው የተወሰነ የማኅበሩ ሸሪኮች የሚከተሉትን ተግባራት ቢያከናውኑ የሥራ አስኪያጅነት ሥራ እንደሰሩ አይቆጠርም፡-

(ሀ) በማኅበሩ ውስጥ በሚደረጉ ምክክሮች ተካፋይ መሆን፤

**(ለ)** ከማኅበሩ ጋር ግዴታ መግባት፤

**(ሐ)** የሥራ አስኪያጆችን ሥራ መቆጣጠር፤

**(መ)** ለማኅበሩ አስተያየትና ምክር መስጠት፤

**(ሠ)** ሥራ አስኪያጆች ከሥልጣናቸው በላይ እንዲሠሩ መፍቀድ፡፡

5) ኃላፊነታቸው የተወሰነ የማኅበሩ ሸሪኮች በማኅበሩ ተቀጥረው ከሥራ አስኪያጅነት ውጪ የሆነ ሥራ መሥራት ይችላሉ፡፡

6) ተቃራኒ ስምምነት ቢኖርም፤ ኃላፊነታቸው የተወሰነ የማኅበሩ ሸሪኮች ስለማኅበሩ አካሄድ ጥያቄ የማቅረብ፣ ሰነዶችንና የሂሳብ መግለጫዎችን የማየት እና ማስታወሻ የመውሰድ መብት አላቸው፡፡

7) ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በስተቀር፤ ኃላፊነቱ የተወሰነው ሸሪክ መሞት፣ መክሰር፣ችሎታ ማጣት እና መሰል ምክንያቶች የማኅበሩ ማፍረሻ ምክንያቶች ሊሆኑ አይችሉም፡፡

**<u>አንቀጽ 219 ድርሻዎችን ስለማስተላለፍ፤</u>**

1) ኃላፊነታቸው ያልተወሰነ ሸሪኮች በሙሉ እና ኃላፊነታቸው ከተወሰነው ሸሪኮች አብላጫዎቹ ካልተስማሙ በስተቀር የማኅበሩን ድርሻዎች ለሦስተኛ ወገን ማስተላለፍ አይቻልም፡፡

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (**1**) ድንጋጌ ቢኖርም ሸሪኮች በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ ከዚህ የተለየ ድምጽ እንዲኖር ሊስማሙ ይችላሉ፡፡

3) የማኅበሩ ገንዘብ ጠያቂዎች ካልፈቀዱ በስተቀር ኃላፊነቱ ያልተወሰነ ሸሪክ ድርሻውን ከማስተላለፉ በፊት ከማኅበሩ ዕዳዎች ጋር በተያያዘ የነበሩትን ግዴታዎች ለማውረድ አይችልም፡፡

**<u>አንቀጽ 220 ተፈጻሚነት ያላቸው የዚህ ህግ ድንጋጌዎች</u>**

ከዚህ በላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በዚህ ህግ ከአንቀጽ **187** እስከ **211** ስር የተመለከቱት የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች ሁለት አይነት ኃላፊነት ባለው የሽርክና ማኅበር ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## <u>ርዕስ አራት</u>

## <u>ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር</u>

**<u>አንቀጽ 221 ትርጓሜ</u>**

1) ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር ማለት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች የሙያና ለሙያው ደጋፊ የሆነ አገልግሎት ለመስጠት የሚያቋቁሙት የማኅበርተኞቹ ኃላፊነት በመዋጮዋቸው የተወሰነ የንግድ ማኅበር ነው፡፡

2) ለዚህ ማኅበር አላማ “የሙያ አገልግሎት” ማለት አግባብ ባለው አካል በተሰጠ የሙያ ፈቃድ መሰረት የሚሰጥ አገልግሎት ነው፡፡

3) “ለሙያው ደጋፊ የሆነ አገልግሎት” ማለት በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ሙያዎች ስር ያለና የሙያ አገልግሎቱን ለመስጠት አስፈላጊ የሆነ ተዛማጅ አገልግሎት ነው፡፡

**አንቀጽ 222 የማኅበሩ ባሕሪያት**

1) ማኅበሩ ከሸሪኮቹ የተለየ የሕግ ሰውነት አለው፡፡

2) የሸሪኮች መሞት፣ መክሰር፣ ከማኅበሩ መውጣት ወይም በሸሪኮች ላይ የሚደረግ ሌላ ማንኛውም ዓይነት ለውጥ በማኅበሩ ሕልውና፣ መብት ወይም ግዴታ ላይ ተጽዕኖ አይኖረውም፡፡

**አንቀጽ 223 የማኅበሩ ስም**

ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር ከሌላ ነጋዴ ወይም ማኅበር ጥቅም ጋር የማይጋጭ፣የሦስተኛ ወገኖችን መብት የማይነካ እና የተቋቋመበትን ዓላማ የሚገልጽ ማኅበርተኞች የፈቀዱት የመጠሪያ ስም ይኖረዋል፡፡ ከማኅበሩ ስም መጨረሻ ላይ “ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር” የሚል ሐረግ መጨመር አለበት፡፡

**አንቀጽ 224 የማኅበሩ ሸሪኮች**

1) የማኅበሩ ሸሪኮች ሊሆኑ የሚችሉት አግባብ ካለው አካል የሙያ አገልግሎት ለመስጠት ፈቃድ የተሰጣቸው ባለሙያዎች ወይም ከማኅበሩ ጋር ተመሳሳይ ወይም ተያያዥ የሆነ አገልግሎት የሚሰጡ ኃላፊነታቸው የተወሰነ የሽርክና ማኅበራት ናቸው፡፡

2) የማኅበሩ ዋና ሥራ አስኪያጅ ማኅበሩ አገልግሎት በሚሰጥበት ሙያ ፈቃድ ያለው የተፈጥሮ ሰው መሆን አለበት፡፡

**አንቀጽ 225 የማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ ይዘት**

የማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ በዚህ ሕግ አንቀጽ 185 ሥር ከተዘረዘሩት በተጨማሪ የሙያ አገልግሎት የሚሰጠውን የእያንዳንዱን ሸሪክ የሙያ አይነትና የፈቃድ ቁጥር መያዝ አለበት፡፡

**አንቀጽ 226 የማኅበሩ መዋጮ**

መዋጮን የሚመለከቱት የዚህ ሕግ አንቀጽ 186 ድንጋጌዎች ለዚህ ማኅበርም እንደአግባብነቱ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

**አንቀጽ 227 የጥቅም ግጭት**

ሙያን በሚመለከት የወጡ አግባብ ያላቸው ሕጎች እንደተጠበቁ ሆኖ ማንኛውም ሸሪክ ማኅበሩ የሚሠራቸውን ተመሳሳይ ሥራዎች ለራሱ ወይም ለሦስተኛ ወገን ለማከናወን ወይም ለተመሳሳይ ዓላማ በተቋቋመ ማኅበር ሸሪክ መሆን የሚችለው ሁሉም የማኅበሩ ሸሪኮች ሲስማሙ ብቻ ነው፡፡

**አንቀጽ 228 የማኅበሩ ኃላፊነት ወሰን**

1) ሸሪኩ ወይም ሠራተኛው የማኅበሩን ሥራ በሚያከናውንበት ወቅት ሆን ብሎ ወይም የማታለል ተግባር በመፈጸም ወይም በቸልተኝት ለሚፈፅመው ጥፋት ወይም ለሚያደርሰው ጉዳት ጥፋቱን ካደረሰው ሸሪክ ወይም ሠራተኛ ጋር ማህበሩ በአንድነትና በተናጠል ተጠያቂ ይሆናል፡፡
2) ጉዳቱ የደረሰበት ሰው ጉዳት አድራሹ ሸሪክ ወይም ሠራተኛ ሥራውን ለማከናወን ኃላፊነት ያልተሰጠው መሆኑን የሚያውቅ የነበረ ከሆነ ማኅበሩ ተጠያቂ አይሆንም፡፡
3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ከተመለከተው ውጪ ከውል ወይም በሌላ በማንኛውም ሁኔታ ለሚመጣ ግዴታ ኃላፊ የሚሆነው ማኅበሩ ነው፡፡
4) ማኅበሩ በሸሪኮች ወይም በሰራተኞች በሚፈጸም የሙያ ጥፋት ምክንያት ለሚደርስ ጉዳት ካሣ የሚሆን የመድን ሽፋን ሊኖረው ይገባል፡፡ መጠኑም አግባብ ባለው አካል ይወሰናል፡፡

**አንቀጽ 229 ሸሪክ ከማበሩ ስለሚወጣበት ሁኔታ**

1) አንድ ሸሪክ ከማኅበሩ ሊወጣ የሚችለው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው፡-

**(ሀ)** በመመስረቻ ጽሑፍ በተለየ ሁኔታ ካልተመለከተ በስተቀር በራሱ ፈቃድ ለማኅበሩ የሦስት ወራት የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በጽሑፍ በመስጠት፤

**(ለ)** ሲሞት ወይም ሕጋዊ ሰውነት ያለው አካል በሆነ ጊዜ ሲፈርስ፤

**(ሐ)** የግል ገንዘብ ጠያቂዎች ያለውን ድርሻ በሙሉ ሲወስዱ፣ ሲያሸጡ ወይም በሻሪኩ ላይ የኪሳራ ውሳኔ ሲወሰንበት፣

**(መ)** የሸሪኩ የሙያ ፈቃድ ሲሰረዝ ወይም ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በስተቀር የሙያ ፈቃዱ ለረጅም ጊዜ ሲታገድ፤

**(ሠ)** በሕመም ወይም በአካል ጉድለት ወይም በሌላ በማንኛውም ምክንያት ለዘለቄታው የሸሪክነት ግዴታውን ለመወጣት የማያስችለው ሲሆን፤ ወይም

**(ረ)** በበቂ ምክንያት ፍርድ ቤት ከማኅበሩ እንዲወጣ ሲወስን፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ) የተመለከተውን ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ ከማኅበሩ የወጣ ሸሪክ በዚህ ምክንያት በማኅበሩ ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ተጠያቂ ይሆናል፡፡
3) አንድ ሸሪክ ከማኅበሩ ከመውጣቱ በፊት ለሦስተኛ ወገኖች የነበረበት ዕዳ እና ኃላፊነት ከማኅበሩ በመውጣቱ ቀሪ አይሆንም፡፡
4) አንድ ሸሪክ ከማኅበሩ ከወጣ ማኅበሩ ሸሪኩ ስለመውጣቱ ማኅበሩ በተመዘገበበት የንግድ መዝገብ ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡

**አንቀጽ 230 ከማኅበሩ የወጣ ሸሪክ ድርሻ**

1) አንድ ሽሪክ ድርሻውን ማህበርተኞች ዘንድ ተቀባይነት ላገኘ ሌላ ማህበርተኛ ወይም ሦስተኛ ወገን ሳያስተላልፍ በሞት፣ በኀመም፣በኪሳራ ወይም በሌላ ማናቸውም ምክንያት ከማህበሩ የወጣ እንደሆነ በእርሱ እግር ተተክቶ ድርሻውን የመጠየቅ መብት ላለው ሰው ድርሻው ተሰልቶ በገንዘብ ይሰጠዋል፡፡ በሞተው ወይም በወጣው ሰው ምትክ በማኅበሩ አባል የመሆን መብት የለም፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የድርሻ ዋጋ ሲሰላ የወጣው ሽሪክ ማኅበሩ ውስጥ የነበረው ገቢ የተደረገ መዋጮ፣የማህበሩ እዳዎች ከተከፈሉ በኋላ ከሚቀረው ተራፊ ሀብት ወይም የተጠራቀመ ትርፍ ውስጥ እርሱ የነበረው ድርሻ እና በወጣበት ወቅት በመሰራት ላይ የነበሩ ሥራዎች የሚያስገኙት ትርፍ ግምት ውስጥ መግባት አለበት፡፡

**አንቀጽ 231 ስለማኅበሩ ውሳኔ አሰጣጥ**

**1)** በማኅበሩ መመስረቻ ጽሁፍ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በስተቀር የማኅበሩን የመመስረቻ ጽሑፍ ለማሻሻል የማኅበሩ አባላት 2/3 (ሁለት ሦስተኛ) ይሁንታ ያስፈልጋል፡፡ ሌላ ማንኛውም ውሳኔ በአብዛኛዎቹ አባለት የድምጽ ድጋፍ ሊደረግ ይችላል፡፡

**2**) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) የተገለጸው ቢኖርም የማኅበሩን ዜግነት ለመለወጥ ወይም የሥራ መስክ ለመለወጥ የሚተላለፍ ውሳኔ የማኅበሩ አባላት ሦስት አራተኛ ስምምነት ማግኘት አለበት፡፡

**አንቀጽ 232 የማኅበሩ ማፍረሻ ምክንያቶች**

**1)** በዚህ ሕግ አንቀጽ 181 የንግድ ማኅበርን ለማፍረስ የተመለከቱ ጠቅላላ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የሽሪኮች ቁጥር ወደ አንድ ዝቅ ሲልና በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ሌላ ሽሪክ መተካት ሳይቻል ሲቀር ማኅበሩ እንዲፈርስና ሂሳቡ እንዲጣራ መደረግ አለበት፡፡

**2)** የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የስድስት ወራት የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት በማኅበሩ የቀረው ሽሪክ ጥያቄ ሲያቀርብና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የንግድ ማኅበር መዝጋቢው አካል የስድስት ወራቱ የጊዜ ገደብ በሦስት ወራት እንዲራዘም ሊፈቅድ ይችላል፡፡

**3)** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተደነገገው መሠረት ካልሆነ በስተቀር የሽሪኮች ቁጥር ከሁለት በታች መቀነሱን የሚያውቅ ሽሪክ ማኅበሩ በዚህ ሁኔታ ከስድስት ወራት በላይ ስራውን እንዲቀጥል ካደረገ ለማኅበሩ ዕዳና ግዴታዎች ከማኅበሩ ጋር በአንድነትና በተናጠል ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 233 ተፈጻሚነት ያላቸው የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች**

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ከአንቀጽ 187 እስከ 211 ስር የተመለከቱ የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች ኃላፊነቱ በተወሰነ የሽርከና ማኅበር ላይ እንደአግባብነታቸው ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## ርዕስ አምስት

## የእሽሙር ማኅበር

**አንቀጽ 234 ትርጓሜ**

የእሽሙር ማኅበር ማለት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች በመመስረቻ ጽሑፍ መሠረት የሚያቋቁሙት በሦስተኛ ወገኖች የማይታወቅ የሕግ ሰውነት የሌለው የንግድ ማኅበር ነው፡፡ ስለሌሎች የንግድ ማህበሮች የተደነገጉት የማስመዝገብ ስርዓቶች በዚህ ማኅበር ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም፡፡

**አንቀጽ 235 የማኅበሩ በሦስተኛ ወገኖች መታወቅ**

የማኅበሩ መኖር በሦስተኛ ወገኖች ከታወቀ ከዚያ ጊዜ አንስቶ ማኅበሩ ከእነዚህ ወገኖች ጋር በሚኖረው ግንኙነት እንደ ኅብረት ሽርክና ማኅበር ይቆጠራል፡፡

**አንቀጽ 236 ስለማኅበሩ መዋጮ**

1) በዚህ ሕግ አንቀጽ 186 ስለመዋጮ የተደነገገው ለእሽሙር ማኅበርም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
2) ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በስተቀር እያንዳንዱ ሽሪክ ለከፈለው መዋጮ ባለቤትነቱን እንደያዘ ይቆያል፡፡

**አንቀጽ 237 ድርሻን ስለማስተላለፍ**

ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በስተቀር በማኅበሩ ውስጥ ያለን ድርሻ ማስተላለፍ የሚቻለው ሁሉም ሽሪኮች ሲስማሙ ብቻ ነው፡፡

**አንቀጽ 238 የማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ**

1) ማኅበሩ ሽሪክ ወይም ሽሪክ ባልሆነ በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ሥራ አስኪያጆች ይመራል፡፡
2) ሥራ አስኪያጅ ያልተሾመ እንደሆነ ሁሉም ሽሪኮች የሥራ አስኪያጅነት ስልጣን ይኖራቸዋል፡፡

**አንቀጽ 239 የማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር**

1) የማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር በመመስረቻ ጽሑፉ ይወሰናል፡፡ ሆኖም ይህ ውሳኔ ለሦስተኛ ወገኖች መቃዎሚያ ሊሆን አይችልም፡፡
2) ሥራ አስኪያጁ የማኅበሩን ሥራዎች ለሽሪኮቹ የማስረዳት ግዴታ አለበት፡፡ ይህን ግዴታ የሚያስቀር ማንኛውም ስምምነት ዋጋ አይኖረውም፡፡
3) የማኅበሩ ሽሪኮች የሥራ አስኪያጁን ሥራ መቆጣጠር ይችላሉ፡፡

**አንቀጽ 240 የማኅበሩን ሥራ አስኪያጅ ስለመሻር**

የማኅበሩ ሽሪክ የሆነ ሥራ አስኪያጅ በበቂ ምክንያት ሊሻር ይችላል፡፡

**አንቀጽ 241 ማኅበሩ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር ስላለው ግንኙነት**

1) ለሦስተኛ ወገኖች የሚታወቀው የማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ ብቻ ነው፡፡ ለማኅበሩ ዕዳዎች እና ግዴታዎች ኃላፊና ተጠያቂ የሚሆነውም እሱ ብቻ ነው፡፡

2) የማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ ያልሆነ ሸሪክ ለማኅበሩ ዕዳዎች ለሥራ አስኪያጁ ተጠያቂ የሚሆነው በማኅበሩ መመሥረቻ ጽሑፍ በተወሰነው መጠን ብቻ ነው፡፡

3) ሥራ አስኪያጅ ያልሆነ ሸሪክ በማኅበሩ ሥራ አመራር ተካፋይ ከሆነ ለሦስተኛ ወገኖች ከሥራ አስኪያጁ ጋራ በአንድነት እና በተናጠል ኃላፊ ሆናል፡፡

4) ማንኛውም የማኅበሩ ሸሪክ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር ግንኙነት ማድረግ የሚችለው በራሱ ስም ብቻ ነው፡፡

**አንቀጽ 242 የማኅበሩ ማፍረሻ ምክንያቶች**

1) የንግድ ማኅበራት የሚፈርሱበትን ሁኔታ የሚመለከቱት ጠቅላላ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ማኅበሩ የሚፈርሰው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው፡-

**(ሀ)** ሸሪኮች ማኅበሩ እንዲፈርስ በሙሉ ድምጽ ሲስማሙ፤

**(ለ)** ማኅበሩ የተቋቋመው ላልተወሰነ ጊዜ ሲሆን ከሸሪኮች አንዱ እንዲፈርስ ለማኅበሩ ጥያቄ ያቀረበ እንደ ሆነ፤

**(ሐ)** ሁሉም የማኅበሩ ድርሻዎች በአንድ አባል የተያዙ እንደሆነ፤

**(መ)** ማኅበሩ እንዲቀጥል የሚያደርግ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በስተቀር ከማኅሩ ሸሪኮች አንዱ የሞተ ወይም የከሠረ ወይም ችሎታ ያጣ እንደሆነ፤

**(ሠ)** በመመሥረቻ ጽሑፉ ለሥራ አስኪያጁ ማኅበሩን ለማፍረስ ሥልጣን ተስጥቶት ከሆነ ሥራ አስኪያጁ ማኅበሩ እንዲፈርስ ሲወስን፤

2) ማንኛውም ተቃራኒ ስምምነት የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) ድንጋጌን ተፈጻሚነት የሚያስቀር አይሆንም፡፡

**አንቀጽ 243 ሸሪክን ከማኅበሩ ስለማስወጣት**

1) በአንድ ሸሪክ ጥፋት ምክንያት ማኅበሩ እንዲፈርስ ለፍርድ ቤት ጥያቄ ሲቀርብና ሌሎች ሸሪኮች ማኅበሩ እንዳይፈርስ ሲያመለክቱ ፍድር ቤቱ ማኅበሩ እንዲፈርስ በመወሰን ፋንታ ጥፋተኛ የሆነውን ሸሪክ ከማኅበሩ እንዲወጣና ማኅበሩ እንዲቀጥል ለማዘዝ ይችላል፡፡

2) አንድ ሸሪክ ከማኅበሩ የሚወጣበት ምክንያት በመመስረቻ ጽሑፉ ሊወሰን ይችላል፡፡

3) ከማኅበሩ እንዲወጣ የተደረገ ሸሪክ በወጣበት ጊዜ የነበረው ድርሻ እንዲከፈለው የመጠየቅ መብት አለው፡፡

**አንቀጽ 244 ተፈጻሚነት ያላቸው የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች**

ከላይ በዚህ ርዕስ ሥር የተዘረዘሩት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ስለኅብረት ሸርክና ማኅበር የወጡት ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው በእሽሙር ማኅበር ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## ርዕስ ስድስት

## የአክሲዮን ማኅበር

### ምዕራፍ አንድ

### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ 245 ትርጓሜ**

1) የአክሲዮን ማኅበር ማለት ዋና ገንዘቡ (ካፒታሉ) አስቀድሞ ተወስኖ በአክሲዮን የተከፋፈለና ሀላፊነቱ በማኅበሩ ሃብት ብቻ የተወሰነ ማኅበር ነው፡፡
2) የባለአክሲዮኖቹ ኃላፊነት ለማኅበሩ ቃል የገቡትን መዋጮ በመክፈል የተወሰነ ነው፡፡

**አንቀጽ 246 የማኅበሩ ስም**

የአክሲዮን ማኅበር የሚጠራበት ስም ይኖረዋል፡፡ ከሌላ ነጋዴ ወይም ማኅበር ጥቅም ጋር የሚጋጭ እስካልሆነና የሌሎች ሦስተኛ ወገኖች መብት እስካልተነካ ድረስ የማኅበሩ መጠሪያ በማኅበርተኞች ስምምነት ይወሰናል፡፡ ከስሙ መጨረሻ ላይ "የአክሲዮን ማኅበር" የሚል ሐረግ መጨመር ይኖርበታል፡፡

**አንቀጽ 247 የማኅበሩ አነስተኛ ዋና ገንዘብ እና አክሲዮን ላይ የሚጻፈው ዋጋ**

1) የማኅበሩ ዋና ገንዘብ (ካፒታል) ከኃምሳ ሺህ የኢትዮጵያ ብር ያነሰ ሊሆን አይችልም፡፡
2) እያንዳንዱ አክሲዮን ላይ የሚጻፈው ዋጋ ከአስር ብር በታች ሊሆን አይችልም፡፡

**አንቀጽ 248 አክሲዮኑ ለሕዝብ ክፍት የሆነ የአክሲዮን ማኅበር አደራጅና አባላት**

1) አደራጅ ማለት አክሲዮኑ ለሕዝብ ክፍት የሆነ ማኅበር ምስረታን ያነሳሳ፤ መግለጫ አዘጋጅቶ ሰዎች ማኅበሩን እንዲቀላቀሉ የጋበዘ ወይም በአጠቃላይ የማኅበሩን ምስረታ ዓላማ አድርጎ ይህንኑ ለማስፈጸም የተንቀሳቀሰና ማኅበሩ የማይመሰረት ከሆነ ባለመመስረቱ ምክንያት ለሚመጣ ጉዳት ኃላፊነት የሚወስድ ሰው ነው፡፡ ከአደራጅ ጋር ባደረገው ውል መሰረት ለማኅበሩ ምስረታ አስፈላጊ የሆነ ጥናት፣ የሙያ ድጋፍ እና መሰል አገልግሎት ያቀረበ ባለሞያ አደራጅ አይደለም፡፡
2) የአክሲዮን ማኅበር በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ የተፈጥሮ ሰዎች ወይም ህጋዊ ሰውነት ባላቸው ሰዎች ሊደራጅ ይችላል፡፡ አደራጅ የማኅበሩ ባለአክሲዮን የመሆን ግዴታ የለበትም፡፡
3) የአክሲዮን ማሕበር አባላት ቁጥር ከአምስት ባለአክሲዮኖች በታች መሆን የለበትም፡፡

**አንቀጽ 249 ለአደራጅነት ብቁ ስላለመሆን**

በንግድ ማኅበር አደራጅነት፣ ዳይሬክተርነት፣ ሥራ አስኪያጅነት፣ተቆጣጣሪነት፣ ኦዲተርነት ወይም በሌሎች የአመራር ኃላፊነቶች ላይ ተመድቦ ሲሰራ ከኃላፊነቱ ጋር በተያያዘ ወይም በማናቸውም ሌላ ሁኔታ በእምነት

ማጉደል፣ በስርቆት፣ በውንብድና ወይም ሌላ ተመሳሳይ ወንጀል ጥፋተኛነቱ የተረጋገጠ ሰው አባልነቱ ለሕዝብ ክፍት የሆነ የአክሲዮን ማሕበር አደራጅ መሆን አይችልም፡፡

**<u>አንቀጽ 250 የአደራጆች ኃላፊነት</u>**

1) አደራጆች ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ጉዳዮች ለተዋዋሉዋቸው ሰዎች፣ ለባለአክሲዮኖችና ለሦስተኛ ወገኖች በአንድነትና በተናጠል ኃላፊነት አለባቸው፡፡

(ሀ) ማኅበሩን ለማቋቋም ሲሉ ለገቧቸው ግዴታዎች፤

(ለ) የማኅበሩ ዋና ገንዘብ በሙሉ ስለመፈረሙና የተከፈለው ዋና ገንዘብ በማኅበሩ ስም ገቢ ስለመሆኑ፤

(ሐ) ለማኅበሩ በዓይነት የተከፈሉ መዋጮዎች በዚህ ህግ አንቀጽ 257 መሠረት የተገመቱ ስለመሆኑ፤

(መ) ማኅበሩን ለማቋቋም ለሕዝብ ያቀረቡት መግለጫ ትክክለኛ ስለመሆኑ፤

(ሠ) የማኅበሩ የአመሠራረት ሂደት ህጋዊ አሠራርን የተከተለ ስለመሆኑ፤

(ረ) የማኅበሩ የምስረታ ሂደት በኦዲተር የተመረመረ ስለመሆኑ፤

(ሰ) ማኅበሩ ባለመመስረቱ ምክንያት የከፈሉት መዋጮ እንዲመለስላቸው ለሚጠይቁ አክሲዮን ለመግዛት የፈረሙ ሰዎች በዚህ ህግ መሰረት ገንዘባቸውን ከነወለዱ ጋር የመመለስ፤ እና

(ሸ) ሌሎች ከምስረታ ሂደት ጋር ግንኙነት ላላቸው ጉዳዮች በሙሉ፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌዎች መሠረት በአደራጆች ላይ የሚቀርብ የኃላፊነት ክስ ተጎጂው ጉዳቱን እና ለጉዳቱ ኃላፊ የሚሆነውን ሰው ካወቀበት ቀን ጀምሮ እስከ አምስት ዓመት ድረስ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል፡፡ በሌላ በማንኛውም ሁኔታ ጉዳት ከደረሰበት ቀን አንስቶ በአስር ዓመት ውስጥ ክስ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል፡፡

**<u>አንቀጽ 251 ማኅበሩን ለማደራጀት የተገቡ ግዴታዎችና የተደረጉ ወጪዎች</u>**

1) በማኅበሩ ምስረታ ሂደት አደራጆች የገቧቸው ግዴታዎች ወይም ያወጧቸው ወጪዎች ለማኅበሩ ምስረታ አስፈላጊ ከሆኑ ወይም በፈራሚዎች ጠቅላላ ጉባኤ ከጸደቁ ወደ ማኅበሩ ይተላለፋሉ፡፡
2) በማንኛውም ምክንያት ቢሆን ማኅበሩ ሳይቋቋም ከቀረ አደራጆች ለገቡት ግዴታና ላወጡት ወጪ አክሲዮን ለመግዛት የፈረሙ ሰዎች ኃላፊነት የለባቸውም፡፡

**<u>አንቀጽ 252 የማኅበሩ መስራቾች</u>**

1) የተወሰኑ ሰዎች ለሕዝብ ጥሪ ሳያደርጉ የአክሲዮን ማኅበር ምስረታን የተመለከቱ የዚህ ሕግ ድንጋጌዎችን በማሟላት በመካከላቸው የአክሲዮን ማኅበር ያቋቋሙ እንደሆነ ማኅበርተኞቹ መስራቾች ይባላሉ፡፡

2) በሌላ ሕግ የተለየ ቁጥር ካልተወሰነ በቀር፤ የአክሲዮን ማኅበር መስራቾች ቢያንስ አምስት መሆን አለባቸው፡
፡

**<u>አንቀጽ 253 የአደራጆችና የመስራቾች ልዩ ጥቅም</u>**

1) አደራጆች ወይም እንደነገሩ ሁኔታ መስራቾች በባለአክሲዮንነት ከሚያገኙት ጥቅም በተጨማሪ ማኅበሩ ትርፍ ማግኘት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ከማኅበሩ የተጣራ ትርፍ ከሀያ በመቶ ያልበለጠ ልዩ ጥቅም ከሦስት ዓመታት ላልበለጠ ጊዜ ሊከፈላቸው ይችላል፡፡ የክፍያው መጠን፣ ክፍያ የሚፈጸምባቸው ዓመታት አመራረጥ እና መሰል ዝርዝር ሁኔታዎች በመመስረቻ ጽሑፉ ይወሰናል፡፡
2) አደራጆችም ሆኑ መስራቾች በዚህ አንቀጽ ከተመለከተው ውጭ ሌላ ማንኛውም ዓይነት ልዩ ጥቅም ከማኅበሩ ሊያገኙ አይችሉም፡፡
3) በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚሰጥ ጥቅም በጥሬ ገንዘብ መከፈል አለበት፡፡ የአደራጆች እና የመስራቾች የድካም ዋጋ አክሲዮን በመስጠት መከፈል አይቻልም፡፡

**<u>ምዕራፍ ሁለት</u>**

**<u>የማኅበሩ አመሰራረት</u>**

**<u>አንቀጽ 254 ለማኅበሩ ምስረታ የሚያስፈልጉ ጠቅላላ ሁኔታዎች</u>**

1) ሌሎች የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም የአክሲዮን ማኅበር ከመመስረቱ በፊት፡-

(ሀ) የማኅበሩ ዋና ገንዘብ በሙሉ ለማዋጣት መፈረም እና፤

(ለ) በጥሬ ገንዘብ በተሸጡ አክሲዮኖች ላይ ከተጻፈው ዋጋ ውስጥ ቢያንስ አንድ አራተኛው በመመስረት ላይ ባለው ማኅበር ስም በተከፈተ ዝግ የባንክ ሒሳብ መቀመጥ አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ለ) መሠረት የተቀመጠውን ገንዘብ ማኅበሩ በንግድ መዝገብ ሳይመዘገብ ከተቀመጠበት ሂሳብ ማውጣት አይቻልም፡፡
3) የአክሲዮን ሽያጭ ገንዘብ ባንክ መቀመጥ ከጀመረበት ቀን አንስቶ በዚህ ሕግ አንቀጽ 259 መሰረት በሚቀርበው የማኅበሩ መግለጫ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማኅበሩን ማስመዝገብ ካልተቻለ በማኅበሩ አባልነት መቀጠል የማይፈልጉ ፈራሚዎች ገንዘባቸው ከባንክ ወለድ ጋር እንዲመለስላቸው መጠየቅ ይችላሉ፡፡ ገንዘቡ እንዲመለስ ጥያቄ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ በሰላሳ ቀናት ውስጥ አደራጆች ለንግድ ማኅበር መዝጋቢው አካል መዋጮው እንዲመለስ ማሳወቅ አለባቸው፡፡ መዝጋቢው አካልም ለጥያቄ አቅራቢው ፈራሚ መዋጮው እንዲመለስለት የሚመለከተውን ባንክ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡ ሆኖም የማኅበሩ ምስረታ በቀሪዎቹ ፈራሚዎች ሊቀጥል ይችላል፡፡
4) አደራጆች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት መዋጮው ለፈራሚዎች እንዲመለስ እንዲያደርግ ለንግድ ማኅበር መዝጋቢው አካል በወቅቱ ያላሳወቁ እንደሆነ ማሳወቅ ከነበረባቸው ጊዜ ጀምሮ የሚታሰብ በባንክ ወለድና በሕጋዊ ወለድ መካከል ያለውን ልዩነት በአንድነትና በተናጠል የመክፈል ግዴታ አለባቸው፡፡

**<u>አንቀጽ 255 የማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ ይዘት</u>**

ማንኛውም የአክሲዮን ማኅበር የሚቋቋመው በመመስረቻ ጽሑፍ ነው፡፡ የመመስረቻ ጽሑፍ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን መያዝ ይኖርበታል፡-

1) የማኅበሩን ስም፤
2) የማኅበሩን ዋና መስሪያ ቤትና እንዳሉም ቅርንጫፎቹን፤
3) የማኅበሩን ባለአክሲዮኖች ስም፣ አድራሻ፣ ዜግነት፣ የፈረሙትን የአክሲዮን ብዛትና የተከፈለውን የገንዘብ መጠን፤
4) ማኅበሩ የሚሠማራበትን የስራ መስክና ዓላማ፤
5) የማኅበሩን የተፈረመ ዋና ገንዘብና ከተፈረመው ዋና ገንዘቡ ውስጥ የተከፈለውን የገንዘብ መጠን፤
6) አክሲዮን ላይ የሚጻፈው ዋጋ፣ የአክሲዮኖችን ብዛት፣ ዓይነትና መደባቸውን፤
7) የዓይት መዋጮ ገቢ ያደረገውን ባለአክሲዮን ስም፣ግምቱንና የአገማመቱ ሁኔታ፣ የዓይነት መዋጮው የሚኖረው አገልግሎት፣ገቢ ለተደረገው የዓይነት መዋጮ የተሰጠውን የአክሲዮን ብዛት፤
8) የትርፍ አከፋፈል ሁኔታ፤
9) ለማኅበሩ አደራጆች የሚሰጠውን ልዩ ጥቅም መጠንና አከፋፈል፤
10) የማኅበሩን ዳይሬክተሮች እና ስራ አስኪያጆች ብዛትና ሥልጣን፤
11) ማኅበሩ ተቆጣጣሪ ቦርድ ካለው የቦርዱ አባላትን ብዛት እና ስልጣን፤
12) የኦዲተሮችን ብዛት፤
13) ማኅበሩ የሚቆይበትን ጊዜ፤
14) ማኅበሩ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት የሚያስታውቅበትን መንገድና ጊዜ፣
15) የማኅበሩን ሥራ አመራር፣ በማኅበሩና በባለአክሲዮኖች ወይም በባለአክሲዮኖች መካከል ያለውን ግንኙነት የሚመለከቱ ጉዳዮች፤ እና
16) በሕግ ወይም በባለአክሲዮኖች ስምምነት እንዲካተቱ የተወሰኑ ሌሎች ጉዳዮችን፡፡

**<u>አንቀጽ 256 መዋጮ</u>**

ከሙያ አገልግሎት በስተቀር በዚህ ሕግ አንቀጽ 186 የተጠቀሱት የገንዘብና ሌሎች የዓይነት መዋጮዎች እንደአግባብነታቸው ለአክሲዮን ማኅበር ተፈጻሚነት አላቸው፡፡

**<u>አንቀጽ 257 የዓይት መዋጮ አገማመት</u>**

1) የዓይነት መዋጮ የከፈለ ፈራሚ የባለሙያ ግምት ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡
2) የግምት ሪፖርቱ መዋጮ የተደረጉትን ንብረቶች፣ የእያንዳንዱን የዋጋ ግምት እና የአገማመቱን ዘዴ በዝርዝር መግለጽ ይኖርበታል፡፡ ሪፖርቱም ከመመስረቻ ጽሑፉ ጋር መያያዝ አለበት፡፡
3) በዓይነት የተከፈለው መዋጮ ግምት የማኅበሩን ዋና ገንዘብ ለማዋጣት የፈረሙት ሰዎች ጉባኤ ከመደረጉ በፊት በአደራጆችና በምስረታ ኦዲተር መረጋገጥ አለበት፡፡

4) የሚመሰረተው ማኅበር አክሲዮኑ ለህዝብ ክፍት ያልሆነ የአክሲዮን ማኅበር የሆነ እንደሆነ በዓይነት የተከፈለው መዋጮ ግምት በማኅበሩ መስራቾች መረጋገጥ አለበት፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) ግምቱ የፀደቀ ቢሆንም የዳይሬክተሮች ቦርድ እና ኦዲተሮች ማኅበሩ በንግድ መዝገብ በተመዘገበ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የዓይነት መዋጮውን ግምት ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለባቸው፡፡ እንዲሁም የተዋጣው ንብረት እንደነገሩ ሁኔታ በማሕበሩ ስም መመዝገቡንና አስፈላጊው የንብረት ባለቤትነት ማስረጃ በማኅበሩ ስም መዘጋጀቱን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት በተደረገው ማጣራትና ምርምራ በመዋጮነት የቀረበው ንብረት ዋጋ ግምት በአስር በመቶ እና ከዛም በላይ አንሶ ከተገኘ መዋጮውን ያስገባው ባለአክሲዮን ልዩነቱን ማሟላት አለበት፡፡ መዋጮውን ያስገባው ባለአክሲዮን ልዩነቱን ካላሟላ የባለአክሲዮኑ የአክሲዮን ድርሻ እና የማኅበሩ ዋና ገንዘብ በጎደለው ልክ መቀነስ አለበት፡፡

**አንቀጽ 258 አክሲዮኑ ለሕዝብ ክፍት የሆነ ማኅበር**

አክሲዮኑ ለሕዝብ ክፍት የሆነ ማሕበር ሲመሰረት በዚህ ሕግ ከአንቀጽ 259 እስከ 264 የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

**አንቀጽ 259 የማኅበሩ መግለጫ**

1) ሕዝብ አክሲዮን እንዲገዛ ጥሪ የሚደረገው ሁሉም አደራጆች በፈረሙበት የማኅበሩ መግለጫ አማካኝነት ነው፡፡ መግለጫው የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡-

**(ሀ)** የመመስረቻ ጽሑፉን ረቂቅ፤

**(ለ)** የዓይነት መዋጮ ተደርጎ ከሆነ የባለሙያ ግምት ሪፖርት አጭር መግለጫ፤

**(ሐ)** አክሲዮን ለመግዛት የፈረሙ ሰዎች ክፍያውን የሚያጠናቅቁበት ጊዜ፤

**(መ)** አክሲዮኖቹ የሚሸጡበትን ዋጋ፤

**(ሠ)** አክሲዮን ለመግዛት የፈረሙ ሰዎች የፈራሚዎች ጠቅላላ ጉባኤ ከመደረጉ በፊት ከአክሲዮኖች ዋጋ ላይ መክፈል የሚገባቸውን መጠን፤

**(ረ)** አክሲዮን ለመግዛት ማመልከቻ የሚቀርብበትን ቦታ እና ጊዜ እንዲሁም ገንዘብ ገቢ የሚደረግበት በመመስረት ላይ ባለው ማኅበር ስም የተከፈተው የባንክ ሂሳብን የሚመለከት አስፈላጊ ዝርዝር መረጃ እና

(ሰ) የማኅበሩ የምስረታ ሂደት ተገባዶ ማኅበሩ የሕግ ሰውነት ያገኛል ተብሎ የሚጠበቅበት የጊዜ ገደብ፡፡ የማኅበሩ ምስረታ እንዲገባደድ የሚቀመጠው የጊዜ ገደብ በማንኛውም ሁኔታ ከአምስት ዓመት መብለጥ የለበትም፡፡

2) የማኅበሩን ምስረታ የተመለከተ መግለጫና በዓይነት የተደረገ መዋጮ እንዳለ የባለሙያ ግምት ሪፖርት ቅጂዎች አክሲዮን ለመግዛት የሚፈልጉ ሰዎች ሊመለከቱት በሚችሉበት ቦታ መቀመጥ አለባቸው፡፡

**አንቀጽ 260 አክሲዮን ለመግዛት ስለሚቀርብ ጥያቄ**

1) አክሲዮን ለመግዛት የሚቀርብ ጥያቄ ለዚሁ ተግባር በተዘጋጀ ፎርም ተሞልቶ መቅረብ አለበት፡፡

2) አክሲዮን ለመግዛት ጥያቄ ያቀረበ ሰው በማመልከቻው ፎርም ላይ ስሙንና አድራሻውን፣ለመግዛት የሚፈልገውን የአክሲዮን ብዛትና ያመለከተበትን ቀን እንዲሁም የማኅበሩን መግለጫ፣ ረቂቅ የመመስረቻ ጽሑፍ እና የዓይነት መዋጮ ተደርጎ ከሆነ የባለሙያ ግምት ሪፖርቱን ማንበቡን መግለጽ አለበት፡፡

**<u>አንቀጽ 261 የማኅበሩ የምስረታ ኦዲት</u>**

1) አደራጆች ለማኅበሩ ምስረታ የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች እንደተሟሉ የምስረታ ሂደቱ በውጭ ኦዲተር እንዲመረመር ማድረግ አለባቸው፡፡

2) የኦዲት ምርመራው የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፡-

**(ሀ)** አደራጆች የአክሲዮን ማኅበር ለመመስረት በሕጉ የተቀመጠውን የአደራጅነት መስፈርት የሚያሟሉ ስለመሆኑ፣

**(ለ)** የማኅኑ ዋና ገንዘብ በሙሉ የተፈረመ ስለመሆኑ፤

**(ሐ)** የዓይነት መዋጮዎች ለማኅበሩ ገቢ ስለመደረጋቸው፣ እንዲሁም ዋጋቸው በባለሙያ የተገመተ ስለመሆኑ፤

**(መ)** አክሲዮን ለመግዛት ከፈረሙ ሰዎች የተሰበሰበው ገንዘብ በትክክል በማኅበሩ ሥም በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ውስጥ ገቢ የተደረገ ስለመሆኑ፤

**(ሠ)** ሌሎች የአክሲዮን ማኅበር ለመመስረት በሕግ እና በመመስረቻ ጽሑፍ የተቀመጡ መስፈርቶች የተሟሉ ስለመሆኑ፡፡

3) የኦዲት ሪፖርቱ በኦዲተሩ አማካኝነት ለፈራሚዎች ጉባኤ ቀርቦ መጽደቅ አለበት፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ስር የተዘረዘሩት መስፈርቶች መሟላታቸው በኦዲት ምርመራ ካልተረጋገጠ ማኅበሩ ሊመዘገብ አይችልም፡፡

5) የዓይነት መዋጮው የማይንቀሳቀስ ንብረት ወይም በሕግ የስም ዝውውርና የንብረት ባለቤትነት ማስረጃ የሚያስፈልገው ሌላ ንብረት የሆነ እንደሆነ ሲሆን ንብረቱ በአደራጆች ወይም እንደነገሩ ሁኔታ በመስራቾች ይዞታ ውስጥ መግባቱ በቂ ነው፡፡

**<u>አንቀጽ 262 የፈራሚዎች ጉባኤ</u>**

1) የማኅበሩ የምስረታ ኦዲት ከተጠናቀቀ በኋላ አደራጆች ወዲያውኑ የፈራሚዎች ጉባኤ መጥራት አለባቸው፡፡

2) በዚህ ሕግ አንቀጽ 264 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ስለአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ አጠራርና ውሳኔ የተደነገገው ለፈረሚዎች ጉባኤም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**<u>አንቀጽ 263 የፈራሚዎች ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር</u>**

ጉባኤው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) ማኅበሩን ለማቋቋም የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ፤
2) የማኅበሩን መመስረቻ ጽሑፍ ተወያይቶ ማጽደቅ፤
3) የአደራጆችንና የምስረታ ኦዲተሮችን ሪፖርት ማጽደቅ፤
4) በዓይነት የተደረገ መዋጮ ካለ ግምቱን ማጽደቅ፤
5) የአደራጆችን የትርፍ ድርሻ ልክ መወሰን፤
6) በሕጉ እና በመመስረቻ ጽሑፉ መሠረት በጉባኤው መሰየም ያለባቸውን የማኅበሩ የአስተዳደር አካላት መሰየም፡፡

**<u>አንቀጽ 264 የጉባኤውን ውሳኔዎች የሚመለከቱ ልዩ ድንጋጌዎች</u>**

1) የፈራሚዎች ጉባኤ ያስተላለፋቸው ውሳኔዎች በጽሑፍ ተዘጋጅተው በሁሉም አደራጆች መፈረም ይኖርባቸዋል፡፡ እንዲሁም ለጉባኤው የቀረቡ ሰነዶች ሁሉ ከውሳኔዎች ጋር መያያዝ አለባቸው፡፡
2) ማንኛውም አክሲዮን ለመግዛት የፈረመ ሰው በጉባኤው ስብሰባ ላይ ተካፋይ መሆንና ድምጽ መስጠት ይችላል፡፡
3) የዓይነት መዋጮ ገቢ ያደረጉ ሰዎች በመዋጮው ግምት ላይ እንዲሁም አደራጆች ከትርፍ ላይ ልዩ ጥቅም እንዲያገኙ በሚወሰንበት ጊዜ ድምጽ መስጠት አይችሉም፡፡
4) በፈራሚዎች ጉባዔ በሙሉ ድምጽ ተቀባይነት ካላገኘ በስተቀር፤ በመመስረቻ ጽሑፍ ረቂቅ ላይ መሰረታዊ ለውጥ ማድረግ አይቻልም፡፡ ሆኖም በዓይነት የተደረገ መዋጮን ግምት ወይም ለአደራጆች ከትርፍ ድርሻ ላይ የሚሰጠውን ልዩ ጥቅም የሚመለከት ማሻሻያ በድምጽ ብልጫ ሊወሰን ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 265 ማኅበሩን በንግድ መዝገብ ውስጥ ስለማስገባት</u>**

1) የአክሲዮን ማኅበሩ የተቋቋመው በምንም ዓይነት ቢሆንም በንግድ መዝገብ መግባት አለበት፡፡ ማኅበሩ የሕግ ሰውነት የሚያገኘው በምዝገባ ይሆናል፡፡
2) በሌላ ሕግ በተለየ ሁኔታ የተደነገገ ቢኖርም፤ ማኅበሩን ማስመዝገብ ያለባቸው አደራጆች ወይም እንደነገሩ ሁኔታ መስራቾች ወይም በነዚህ አካላት ውክልና የተሰጠው ሌላ ሰው ነው፡፡
3) በሌላ ሕግ በተለየ ሁኔታ የተደነገገ ቢኖርም፤ ከምዝገባው ማመልከቻ ጋር በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የመመስረቻ ጽሑፍ፣ ማኅበሩ ለሕዝብ ክፍት የሆነ እንደሆነ የማኅበሩ መግለጫ፣ የዓይነት መዋጮዎች እና የምስረታ ኦዲት ሪፖርቶች እንዲሁም የፈራሚዎቸ ጉባዔ ቃለጉባዔ ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡

**<u>አንቀጽ 266 ሕጋዊ ሁኔታዎች ሳይሟሉ የተደረገ ምዝገባ</u>**

1) ማኅበሩ ስለአክሲዮን ማኅበር ምስረታ የተደነገጉት ሕጋዊ ሁኔታዎችን ሳያሟላ ተመዝግቦ መገኘቱ ሕጋዊ ሰውነቱን እንዲያጣ አያደርገውም፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም፤ የገንዘብ ጠያቂዎች ወይም የባለአክሲዮኖች ጥቅም ጉዳት ላይ የሚወድቅ ከሆነ ከገንዘብ ጠያቂዎች ወይም ከባለአክሲዮኖች አንዱ በሚያቀርበው ማመልከቻ

መሰረት ፍ/ቤት ማኅበሩ እንዲፈርስ ወይም ባጭር ጊዜ ውስጥ አስፈላጊው ማስተካከያ እንዲደረግ ሊያዝ ይችላል፡፡ ለፍርድ ቤት ማመልከቻ ማቅረብ የሚቻለው ማኅበሩ በንግድ መዝገብ ከገባበት ጊዜ አንስቶ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ብቻ ነው፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## ስለአክሲዮኖችና የባለአክሲዮኖች መብትና ግዴታ

### አንቀጽ 267 የአክሲዮን አይነቶች

**1)** አክሲዮን በባለአክሲዮኑ ስም በመመዝገብ ወይም ላምጪው በሚል ሊወጣ ይችላል፡፡ ሆኖም ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን አንስቶ ላምጪው በሚል አዲስ አክሲዮን ማውጣት የተከለከለ ነው፡፡

**2)** ተቃራኒ ስምምነት ቢኖርም እንኳ ላምጪው የሚሉ አክሲዮኖች በሚገኙባቸው ማኅበሮች ለአምጪው በሚል የወጡ አክሲዮኖች ባለቤት የሆነ ማንኛውም ሰው አክሲዮኖቹ በስም በሚመዘገብ እንዲለወጡለት ማህበሩ ዘንድ በመቅረብ ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በሦስት ዓመት ውስጥ ማመልከት አለበት፡፡

**3)** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት የአክሲዮን ዓይነት ለመለወጥ የሚያስፈልገውን ወጪ የሚሸፍነው የአክሲዮን ዓይነት እንዲቀየርለት ጥያቄ ያቀረበው ባለአክሲዮን ነው፡፡

**4)** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ስር የተመለከተው የሦስት ዓመት የሽግግር ጊዜ ካለፈ በኋላ ላምጪው በሚል የወጡት አክሲዮኖች የአባልነት መብት አያሰጡም፡፡

### አንቀጽ 268 አክሲዮኖች የሚወጡበት ዋጋ

**1)** ማኅበሩ አክሲዮኖችን አክሲዮኖቹ ላይ ከተጻፈው ዋጋ ባነሰ ማውጣት አይችልም፡፡

**2)** በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ ወይም በባላአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ የተወሰነ እንደሆነ አክሲዮኖችን ከተጻፈባቸው በሚበልጥ ዋጋ ማውጣት ይቻላል፡፡ አክሲዮን ላይ በተጻፈው ዋጋና በሚወጣበት መካከል ያለው ልዩነት የዋጋ ብልጫ ይባላል፡

### አንቀጽ 269 ማኅበሩ በንግድ መዝገብ ከመመዝገቡ በፊት ስለሚሰጥ የአክሲዮን ባለቤትነት የምስክር ወረቀት

ማኅበሩ በንግድ መዝገብ ከመመዝገቡ በፊት የሚሰጥ የአክሲዮን ባለቤትነት የምስክር ወረቀት ዋጋ አይኖረውም፡፡ ሆኖም የአክሲዮን ባለቤትነት የምስክር ወረቀቱን ለማግኘት የተገቡት ግዴታዎችና ኃላፊነቶች እንደተጠበቁ ናቸው፡፡

### አንቀጽ 270 የአክሲዮን አለመከፋፈል

**1)** አክሲዮን አይከፋፈልም፡፡

**2)** ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎች የአክሲዮን የጋራ ባለቤት በሆኑ ጊዜ የባለአክሲዮንነት መብታቸውን መጠቀም የሚችሉት የጋራ ወኪል በመሾም ነው፡፡

**3)** የጋራ ወኪል ባልሾሙ ጊዜ ማኅበሩ ለአንዱ የአክሲዮን የጋራ ባለቤት  የሚሰጠው ማስታወቂያ ወይም መግለጫ ለቀሪዎቹ የአክሲዮኑ የጋራ ባለቤቶችም ጭምር እንደተሰጠ ይቆጠራል፡፡

**4)** የአክሲዮን የጋራ ባለቤቶች ከባለአክሲዮንነት ለሚመነጩ ኃላፊነቶች በአንድነትና በተናጠል ተጠያቂ ናቸዉ፡ ፡

**አንቀጽ 271 በመያዣ ወይም በአላባ ስለሚሰጡ አክሲዮኖች**

**1)** አክሲዮን በመያዣ ወይም በአላባ የተሰጠ እንደሆነ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በስተቀር በማኅበሩ ጉባኤዎች ድምፅ የመስጠት መብት የሚኖረው አክሲዮኑን በመያዣ የያዘው ወይም የአላባ ጥቅም ያለው ሰው ነው፡፡

**2)** አክሲዮኑ አዲስ አክሲዮኖችን ለመግዛት የቀዳሚነት መብት የሚሰጥ ከሆነ ይህ የቀዳሚነት መብት የባለአክሲዮኑ ሆኖ ይቀጥላል፡፡

**3)** በመያዣ ለተሰጠ አክሲዮን የሚከፈል ቀሪ ገንዘብ በማኅበሩ በተጠየቀ ጊዜ ገንዘቡን መክፈል ያለበት ባለአክሲዮኑ ነው፡፡ ባለአክሲዮኑ የተባለውን ገንዘብ ሳይከፍል የቀረ እንደሆነ ማኅበሩ አክሲዮኑን በአንቀጽ **289** መሰረት መሸጥ ይችላል፡፡

**4)** ለአክሲዮኑ የሚከፈል ቀሪ ገንዘብ በማኅበሩ በተጠየቀ ጊዜ አክሲዮን በአላባ የተሰጠው ሰው መክፈል አለበት፡፡ ሆኖም የአላባው ጊዜ ሲጠናቀቅ የከፈለው ገንዘብ እንዲመለስለት የመጠየቅ መብት አለው፡፡

**5)** ድምፅ የመስጠት መብት የሚሰጡ አክሲዮኖችን በመያዣ ወይም በአላባ የያዙ ሰዎች በማኅበሩ መመዝገብ አለባቸው፡፡ ማኅበሩ ከመዘገበ በኋላ የምዝገባ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠት አለበት፡፡

**አንቀጽ 272 አክሲዮን የሚወጣባቸው ዘዴዎች**

1) አክሲዮኖች በወረቀት ወይም ግዙፍነት በሌለው መልክ ሊወጡ ይችላሉ፡፡ አክሲዮኖች የሚወጡበት ዘዴ በማኅበሩ የመመስረቻ ጽሁፍ ወይም በማሻሻያው ይወሰናል፡፡

2) ግዙፍነት የሌለው አክሲዮን ማለት በብሄራዊ ባንክ ፈቃድ በተሰጠው የፋይናንስ ተቋም በኤለክትሮኒክ ዘዴ ተፈጥሮ በፈጠረው ተቋም በኤለክትሮኒክ የአክሲዮን ሒሳብ የሚያዝ አክሲዮን ነው፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) መሰረት የፋይናንስ ተቀቋማት ኤለክትሮኒክ የአክሲዮን ሂሳቦችን መያዝ ከመጀመራቸው በፊት የተቋቋመ ማኅበር በወረቀት የወጡ አክሲዮኖች ግዙፍነት በሌላቸው እንዲተኩ በድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ መወሰን ይችላል፡፡ ሆኖም ውሳኔው የሚጸናው የማኅበሩን አክሲዮኖች በመያዣነት የወሰዱ ገንዘብ ጠያቂዎች ውሳኔውን መቀበላቸው በጽሁፍ ካረጋገጡ ብቻ ነው፡፡

**አንቀጽ 273 የአክሲዮን ምስክር ወረቀት ይዘት**

እያንዳንዱ በወረቀት የሚሰጥ የአክሲዮን ምስክር ወረቀት የሚከተሉትን  መያዝ አለበት፡

1) የማኅበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ፊርማ፤

2) የማኅበሩን ስም፣ ዋና መስሪያ ቤትና ማኅበሩ የሚቆይበትን ጊዜ፤

3) የማኅበሩን ዋና ገንዘብ እና አክሲዮኑ የወጣበትን ዋጋ መጠን፤

4) የማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ የተፈረመበትን ቀን እና ማኅበሩ በንግድ መዝገብ የተመዘገበበትን ቀንና ቦታ፤

5) የአክሲዮኑን መለያ ቁጥር፣ ዓይነት፣መደብ፣ መደቡ መደበኛ ወይም ልዩ መብት የሚሰጥ ስለመሆኑ፣ ልዩ መብት የሚሰጥ ከሆነ የመብቱን ዓይነት፤

6) የአክሲዮኑ ዋጋ በሙሉ ካልተከፈለ የተከፈለውን ገንዘብ መጠን ወይም ዋጋዉ በሙሉ ከተከፈለ ይህንኑ የሚያመለክት መግለጫ፤እና

7) አክሲዮኑ ለውጪ ዜጋ መተላለፍ የሚችል መሆን አለመሆኑን የሚያሳይ መግለጫ፡፡

## አንቀጽ 274 የባለአክሲዮኖች መዝገብ

1) ሥም የተጻፈባቸውን አክሲዮኖች ያወጣ ማኅበር የባለአክሲዮኖችን መዝገብ በዋናው መስሪያ ቤት መያዝ አለበት፡፡ መዝገቡ በወረቀት ወይም ለረጅም ዘመን በሚቆይ የኤለክትሮኒክ ዘዴ መያዝ ይችላል፡፡

2) መዝገቡ የባለአክሲዮኖችን ስምና አድራሻ፣ የአክሲዮኖችን ብዛትና መለያ ቁጥር፣ የተከፈለውን ገንዘብ መጠንና ባለአክሲዮኖቹ የተመዘገቡበትን ቀን መያዝ አለበት፡፡

3) ባለአክሲዮኖችና የሚያገባቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶች መዝገቡን በነፃ መመልከት ይችላሉ፡፡ ባለአክሲዮን ያልሆነ ሌላ ሰው መዝገቡን ማየት የሚችለው ለዚህ ተብሎ ማኅበሩ የወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ ሲፈጽም ነው፡፡

4) ማንኛውም ሰው የተወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ ሲፈጽም የመዝገቡን ግልባጭ ወይም በአጭር የተውጣጣ ጽሑፍ እንዲሰጠው ማኅበሩን መጠየቅ ይችላል፡፡ ማኅበሩ ጥያቄው በቀረበ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ ግልባጩን ወይም በአጭር የተውጣጣውን ጽሑፍ ለጠያቂው መሰጠት አለበት፡፡

5) ጥቅም ካለው ማንኛውም ሰው ወይም ከባለአክሲዮን ጥያቄ ሲቀርብለት አግባብ ያለው የመንግስት አካል በመዝገቡ አጻጻፍ ላይ የተፈጠረ ስህተት እንዲታረም ማድረግ ይችላል፡፡

6) የአክሲዮን መዝገቡ ዝርዝር በትክክል ባለመጻፉ ምክንያት ለሚደርስ ማንኛውም ጉዳት የዳሬክተሮች ቦርድ አባላት በአንድነትና በተናጠል ኃላፊዎች ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ 275 ማኅበሩ የራሱ የሆኑትን አክሲዮኖች ስለሚገዛበት ሁኔታ

1) ማኅበሩ የራሱ የሆኑ አክሲዮኖችን ከማኅበርተኞች መልሶ መግዛት የሚችለው፡-

(ሀ) የባለአክሲዮኖች ጉባኤ ሲፈቅድ፤

(ለ) የሚገዛበት ገንዘብ ከተጣራ ትርፍ ላይ የተነሳ ሲሆን፤ እና

(ሐ) የአክሲዮኖቹ ዋጋ ለማኅበሩ በሙሉ አስቀድሞ የተከፈለ ሲሆን፤

ነው፡፡

**2)** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ማኅበሩ ከማኅበርተኛ የገዛቸውን አክሲዮኖች ዳይሬክተሮች ወደ ሌላ ሰው ሊያስተላልፉ አይችሉም፡፡ አክሲዮኖቹ የሚያስገኙት ድምጽ የመስጠት መብትም ታግዶ ይቆያል፡፡

**3)** ማኅበሩ አክሲዮኖቹን የሚገዛው የባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ የማኅበሩ ዋና ገንዘብ እንዲቀነስ በወሰነው መሰረት ከሆነ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌዎች ተፈፃሚ አይሆኑም፡፡

**4)** ማኅበሩ የራሱ የሆኑትን አክሲዮኖች ከማህበርተኞች በመያዣነት ለመቀበል የፈለገ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ) እና (ሐ) ስር የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## <u>አንቀጽ 276 በአክሲዮኖች ዝውውር ላይ የሚደረግ ገደብ</u>

**1)** በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ ወይም በባላክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ በአክሲዮኖች ዝውውር ላይ ገደብ ሊደረግ ይችላል፡፡

**2)** አክሲዮኖች ከመተላለፋቸው በፊት የዳይሬክተሮች ቦርድ ፈቃድ እንዲጠየቅ በመመስረቻ ጽሑፉ ወይም በአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ሊወሰን ይችላል፡፡ ሆኖም ውሳኔው ውጤት የሚኖረው፡-

(ሀ) አክሲዮኖችን መልሶ የመግዛት የቅድሚያ መብት ለማኅበሩ ወይም ለባለአክሲዮኖቹ የተጠበቀ ከሆነ እና

(ለ) መብቱ የሚሰራበት ሁኔታና የአክሲዮኖቹ መግዣ ዋጋ ቀድሞ የተወሰነ ከሆነ፤ ነው፡፡

**3)** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሰረት የሚደረግ ገደብ አክሲዮን ማስተላለፍን የሚከለክል ወይም አክሲዮን ለማስተላለፍ በሚፈልገው ባለአክሲዮን ላይ ከባድ ጉዳት የሚያደርስ መሆን የለበትም፡፡

**4)** ቅድሚያ የመግዛት መብት የተሰጠው ለማኅበሩ ከሆነ የአክሲዮኖቹ ዋጋ የሚከፈለው ከመጠባበቂያ ገንዘብ ላይ ወይም ከተጣራ ትርፍ ላይ መሆን አለበት፡፡

## <u>አንቀጽ 277 አክሲዮኖችን ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት መስጠት ወይም ለአክሲዮን መግዣ ማበደር ስላለመቻሉ</u>

ማንኛውም ማኅበር የራሱ የሆኑትን አክሲዮኖች በሕግና በመመስረቻ ጽሑፍ የተደነገገ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት መስጠት ወይም ሶስተኛ ወገኖች የማኅበሩን አክሲዮኖች እንዲገዙበት ገንዘብ ማበደር አይችልም፡፡

## <u>አንቀጽ 278 የአክሲዮኖች መደብ</u>

**1)** በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ ወይም በማሻሻያው መሠረት ልዩ መብት የሚያስገኙ የተለያዩ አክሲዮኖች እንዲወጡ ማድረግ ይቻላል፡፡

**2)** አንድ ዓይነት መደብ ባላቸው አክሲዮኖች ላይ የሚጸፈዉ ዋጋና ለባለአክሲዮኖች የሚያስገኙት መብት እኩል መሆን አለበት፡፡

**3)** ለአንድ የአክሲዮን መደብ የተሰጡ መብቶችን መለወጥ የሚቻለው የባለ አክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ለውጡ እንዲደረግ በወሰነበት አኳኃን ልዩ መብት ያላቸው ባለአክሲዮኖች ልዩ ጉባኤ ውሳኔውን ሲያጸድቅ ብቻ ነው፡፡

## አንቀጽ 279 ልዩ መብት የሚያስገኙ አክሲዮኖች

1) ልዩ መብት የሚያስገኙ አክሲዮኖች የሚሰጡት ልዩ ጥቅም ወደፊት የሚወጡትን አክሲዮኖች በቅድሚያ የመግዛትን፣ ከትርፍ በቅድሚያ የመከፈልን ወይም የማህበሩ ንብረት በሚጣራበት ጊዜ መዋጮ ሲመለስ ወይም ተራፊ ሀብት ሲከፋፈል በቅድሚያ ከፍያ የማግኘትንና የመሳሰሉትን ሊያካትት ይችላል፡፡
2) ድምፅ በመስጠት ጉዳይ ላይ ልዩ መብት የሚያስገኙ አክሲዮኖችን ማውጣት ክልክል ነው፡፡
3) በትርፍ አከፋፈልና ማኅበሩ ሲፈርስ በዋና ገንዘቡ አመላለስ ላይ የቅድሚያ መብት ያላቸው ባለአክሲዮኖች ድምፅ መስጠት የሚችሉት የማኅበሩ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ በሚሰጥባቸው ጉዳዮች ብቻ እንዲሆን በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ መወሰን ይቻላል፡፡
4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (3) መሰረት ድምፅ የመስጠት መብት የተገደበባቸው አክሲዮኖች በማኅበሩ ዋና ገንዘብ ውስጥ የሚከወክሉት ከግማሽ በታች መሆን አለበት፡፡

## አንቀጽ 280 ትርፍ ብቻ የሚያስገኙ አክሲዮኖች

1) ማኅበሩ ዋናው ገንዘቡን ሳይቀንስ ካገኘው ትርፍ ወይም ካስቀመጠው መጠባበቂያ ገንዘብ ለባለአክሲዮኖች በአክሲዮኖቻቸው ላይ የተጻፈውን ዋጋ መመለስ ይችላል፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ገንዘብ የተመለሰላቸዉ ባለአክሲዮኖች ትርፍ ብቻ የሚያስገኙ አክሲዮኖችን ይቀበላሉ፡፡ እነዚህ አክሲዮኖች ማኅበሩ ሲፈርስ ገቢ የተደረገውን መዋጮ የመውሰድ መብት አያስገኙም፡፡ ሆኖም ድምፅ የመስጠት መብት፣ እንዲሁም የማኅበሩ ሂሳብ ሲጣራ ለሌሎች ማህበርተኞች መዋጮዋቸው ከተመለሰ በኋላ ከሚተርፈው ገንዘብ ላይ የመካፈል መብት ያስገኛሉ፡፡

## አንቀጽ 281 በጥሬ ገንዘብ የተገዙ አክሲዮኖች አከፋፈል

1) በጥሬ ገንዘብ የሚገዙ አክሲዮኖች በተፈረሙ ጊዜ እጅግ ቢያንስ ከተጻፈባቸዉ ዋጋ አንድ አራተኛ ወይም በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ ከፍ ያለ መጠን ተወስኖ ከሆነ ይኸው ዋጋ በሙሉ መከፈል አለበት፡፡ ዋጋቸው በሙሉ እስኪከፈል ድረስ አክሲዮኖቹ ላምጪው ተደርገው መውጣት አይችሉም፡፡
2) በመመስረቻ ጽሁፉ ያነሰ ጊዜ ካልተወሰነ በስተቀር፤ ያልተከፈለው የአክሲዮኖች ዋጋ ማኅበሩ በንግድ መዝገብ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ እስከ አምስት ዓመት መከፈል አለበት፡፡

## አንቀጽ 282 የአይነት መዋጮ ገቢ የሚደረግበትና አክሲዮኖች የሚተላለፉበት ጊዜ

1) በዓይነት መዋጮ የተደረገው ንብረት የስም ዝውውርና የባለቤትነት ማስረጃ ሰነድ ማውጣት የሚጠይቅ ከሆነ ይህ ተግባር ማኅበሩ ከተመዘገበበት ጊዜ አንስቶ በስድስት ወራት ውስጥ መገባድድ አለበት፡፡
2) በዚህ ህግ ለባለአክሲዮኖች የተሰጡ ሌሎች መብቶች እንደተጠበቁ ሆነው በዓይነት መዋጮ የተገዙ አክሲዮኖች ለባለአክሲዮኑ የሚሰጡትና ለሦስተኛ ወገኖች ሊተላለፉ የሚችሉት ማኅበሩ በንግድ መዝገብ ከተመዘገበ ከአንድ ዓመት በኋላ ነው፡፡

**አንቀጽ 283 በወረቀት የተሰጠ አክሲዮን ባሕሪ**

በወረቀት የወጣ የአክሲዮን ማኅበር ድርሻ (አክሲዮን) የማኅበርተኛነት መብት ከሰነዱ ተለይቶ ሊሰራበት ወይም ሊተላለፍ የማይችል ሰነድ ነው፡፡

**አንቀጽ 284 በወረቀት የወጣ ላምጪው ተብሎ የተጻፈበትን አክሲዮን ስለማስተላለፍ**

1) ላምጪው ተብሎ የተጻፈበት አክሲዮን ከአንድ ሰው ወደ ሌላ የሚዛወረው አክሲዮኑን በመስጠት ብቻ ነው፡ ፡ ሌላ ምንም ዓይነት አሰራር (ፎርማሊቲ) አያስፈልገውም፡፡
2) ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበ በስተቀር ትርፍ ለማከፋፈል፣ በአክሲዮኑ ላይ የተጻፈውን ዋጋ መልሶ ለመቀበል፣ በጠቅላላ ጉባኤ ድምፅ ለመስጠት ወይም በሌሎች አክሲዮኑ የሚያሰጣቸውን መብቶች ለመጠቀም ላምጪው ተብሎ የተጻፈበትን አክሲዮን የያዘ ሰው የአክሲዮኑ ባለቤት እንደሆነ ይቆጠራል፡፡

**አንቀጽ 285 በወረቀት የወጣ ስም የተጻፈበት አክሲዮን ባለቤትነትና ስለሚተላለፍበት ሁኔታ**

1) ስም የተጻፈበት አክሲዮን ባለቤት የሚሆነው በማኅበሩ ዋና መስሪያ ቤት በሚያዘው የባለአክሲዮኖች መዝገብ ውስጥ አክሲዮኑ በስሙ የተመዘገበ ሰው ነው፡፡
2) ስም የተጻፈበት አክሲዮን ወደ ሌላ ሰው የሚተላለፈው አክሲዮኑን በመስጠትና በማኅበሩ የባለአክሲዮኖች መዝገብ አክሲዮኑን በተላለፈለት ሰው ስም በማስመዝገብ ነው፡፡ ምዝገባው የአስተላለፈው ሰውና የተላለፈለት ሰው ስም፣ አድራሻቸውን፣ የተላለፉት አክሲዮኖች ብዛት፣ የተላለፉበት ቀን እና የአክሲዮኖቹ መተላለፍ በማኅበሩ የባለአክሲዮኖች መዝገብ የገባበትን ቀን ማመልከት አለበት፡፡

**አንቀጽ 286 በወረቀት የወጣ አክሰሲዮን በተመለከተ የሚቀርብ መቃወሚያ**

አክሲዮኑ በተላለፈበት ወቅት አምጪው ሆነ ብሎ ማኅበሩን ለመጉዳት እያወቀ ያደረገው ነገር ካልሆነ በቀር ማኅበሩ ካምጪው በፊት የአክሲዮኑ ባለቤት ከነበሩት ሰዎች ጋር በነበረው የግል ግንኙነት ላይ የተመሰረቱ ክርክሮችን አምጪው ላይ መቃወሚያ አድርጎ ማቅረብ አይችልም፡፡

**አንቀጽ 287 በቅን ልቦና የመያዝ ውጤት**

በወረቀት የወጣ አክሲዮን ዝውውርን በሚመለከቱት በዚህ ሕግ ድንጋጌዎች መሰረት በቅን ልቦና አክሲዮን የተላለፈለትን ሰው አክሲዮኑን መልስ ብሎ መክሰስ አይቻልም፡፡

**አንቀጽ 288 ግዙፍነት የሌለው አክሲዮን ስለሚተላለፍበት ሁኔታ**

1. ግዙፍነት የሌለው አክሲዮን በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ፈቃድ በተሰጠው የፋይናንስ ተቋም በሚያዝ የአክሲዮን ሒሳብ ውስጥ አክሲዮኑ የተላለፈለትን ሰው እና የአክሲዮኖቹን መጠን በማመልከት (ሒሳቡን ክረዲት በማድረግ) ይተላለፋል፡፡

2. ግዙፍነት የሌለው አክሲዮን ዝውውር እንዲፈጸም መሟላት ያለበት ስርዓት (ፎርማሊቲ) አክሲዮኑን የፈጠረው የፋይናንስ ተቋም ይወስናል፡፡

3. የውል ወይም የሕግ መሰረት ሳይኖር አክሲዮኖችን ያዛወረ እንደሆነ የፋይናንስ ተቋሙ ኃላፊ ይሆናል፡፡

**<u>አንቀጽ 289 ቀሪ ዋጋቸው ላልተከፈለ አክሲዮኖች ስለሚኖር ኃላፊነት</u>**

**1)** የአክሲዮን ባለይዞታዎች፣ አክሲዮኑ ቀደም ሲል ተላልፎላቸው የነበረ ሰዎች እንዲሁም አክሲዮኑን ከማኅበሩ ለመግዛት የፈረሙ ሰዎች ቀሪ ዋጋቸው ላልተከፈለ አክሲዮኖች ዋጋ ለማኅበሩ በአንድነትና በተናጠል ኃላፊ ናቸው፡፡

**2)** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም አክሲዮን ለመግዛት የፈረመ ወይም ባለአክሲዮን የነበረ ሰው ባለቤትነቱን ያስተላለፈ እንደሆነ ካስተላለፈበት ቀን ጀምሮ ሁለት ዓመት ካለፈ በኋላ ላልተከፈለው ቀሪ ገንዘብ ኃላፊነት አይኖርበትም፡፡

**3)** ቀሪው ገንዘብ በተወሰነው ጊዜ ያልተከፈለ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (**1)** የተጠቀሱት ሰዎች በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ የተለየ የወለድ መጠን ካልተወሰነ በስተቀር ሕጋዊ ወለድ የመክፈል ኃላፊነት አለባቸው፡፡

**4)** ማኅበሩ ባለአክሲዮኑ ቀሪውን ገንዘብ እንዲከፍል የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ከሰጠዉ ከአስራ አምስት ቀናት በኋላ ዋጋቸው በሙሉ ያልተከፈለ አክሲዮኖችን በሀራጅ መሸጥ ይችላል፡፡ በሀራጅ የተሸጡት አክሲዮኖች ተሰርዘው ሌሎች አዳዲስ አክሲዮኖች ለገዥው ይሰጣሉ፡፡

**5)** ገዥ ባለመገኘቱ ምክንያት አክሲዮኑን መሸጥ ካልተቻለ ተጨማሪ ኪሳራ ካለ የመጠየቅ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ አክሲዮኑን ለመውረስና ለአክሲዮኑ አስቀድሞ የተከፈለውን ገንዘብ ለማስቀረት የዳይሬክተሮች ቦርድ ሊወስን ይችላል፡፡

**6)** ቀሪ ዋጋቸው ያልተከፈለ አክሲዮኖች ውርስ እንዲሆኑ በተወሰነበት የሂሳብ ማጠቃለያ ዓመት ውስጥ ያልተሸጡ እንደሆነ አክሲዮኖቹ ተሰርዘው ዋና ገንዘቡ በአክሲዮኖቹ ላይ በተጻፈው ዋጋ መጠን መቀነስ አለበት፡፡

**7)** የገንዘብ መክፈያውን ጊዜ ያሳለፈ ባለአክሲዮን በጉባኤ ላይ ድምፅ የመስጠት መብቱን ያጣል፡፡

**<u>አንቀጽ 290 ለጊዜው የሚሰጥ የምስክር ወረቀት</u>**

**1)** ላምጪው ለሚሉ አክሲዮኖች ላምጪው የሚል ጊዜያዊ የምስክር ወረቀት መስጠት የሚቻለው ዋጋቸው በሙሉ ሲከፈል ነው፡፡ ዋጋቸው በሙሉ ከመከፈሉ በፊት የተሰጠ የምስክር ወረቀት ተቀባይነት የለውም፡፡

**2)** ላምጪው ተብሎ ለተጻፈበት አክሲዮን በባለአክሲዮኑ ስም የተመዘገበ ጊዚያዊ የምስክር ወረቀት የተሰጠ እንደሆነ የምስክር ወረቀቱን ወደሌላ ሰው ማስተላለፍ የሚቻለው ዕዳን ስለማስተላለፍ በተቀመጡ ድንጋጌዎች መሰረት ነው፡፡

**3)** በባለአክሲዮኑ ስም ለተመዘገበ አክሲዮን ለጊዜው የሚሰጥ የምስክር ወረቀት መመዝገብ አለበት፡፡ የምስክር ወረቀቱ ወደሌላ ሰው የሚተላለፈው እነዚህ አክሲዮኖች ስለሚተላለፉበት ሁኔታ በተቀመጠው ድንጋጌ መሰረት ነው፡፡

## አንቀጽ 291 አክሲዮን የሚያስገኛቸው መብቶች

**1)** እያንዳንዱ አክሲዮን ከተጣራው ዓመታዊ ትርፍ እንዲሁም ማኅበሩ ሲፈርስ ከሚቀረው የተጣራ ንብረት ድርሻ የማግኘት መብት ይሰጣል፡፡

**2)** በመመስረቻ ጽሑፉ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በስተቀር የትርፍ ድርሻና ማኅበሩ ሲፈርስ ከተጣራው ንብረት የሚገኘው ድርሻ ባለአክሲዮኑ ለማህበሩ ዋና ገንዘብ ገቢ ባደረገው ንዘብ መጠን ይታሰባል፡፡

**3)** እያንዳንዱ አክሲዮን ድምፅ የመስጠት መብት ይሰጣል፡፡ ለባለአክሲዮኑ ድምጽ የሚሰጠው ክብደት አክሲዮኑ በማኅበሩ ዋና ገንዘብ ውስጥ የሚወክለውን መጠን መሰረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡

**4)** የማኅበሩን ዋና ገንዘብ ለመጨመር በጥሬ ገንዘብ ለመሸጥ የወጡ አክሲዮኖች በሚኖሩበት ጊዜ እያንዳንዱ ባለአክሲዮንበማኅበሩ ውስጥ ባለአክሲዮኑ ባለው የአክሲዮን ድርሻ መጠን በቅድሚያ የመግዛት መብት ይኖረዋል፡፡

**5)** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (**4**) የተመለከተው መብት በዚህ ሕግ አንቀጽ **448** እስከ 457 ስር ባሉት ድንጋጌዎች መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 292 አክሲዮን ሽጦ የመውጣት የአናሳ ባለአክሲዮኖች መብት

1) የማኅበሩን  ዋና ገንዘብ ዘጠና በመቶ የሚወክሉ አክሲዮኖች በአንድ ማኅበርተኛ የተያዙ እንደሆነ አናሳ ባለአክሲዮኖች ማኅበርተኛው አክሲዮኖቻቸውን እንዲገዛቸው የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡
2) ጥያቄ አቅራቢው ባለአክሲዮን አክሲዮኖቹ ስለሚገዙበት ሁኔታ በተለይም የአክሲዮኖቹን ዋጋ ስለወሰነበት መንገድ መረጃ ከጥያቄው ጋር ማቅረብ አለበት፡፡
3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት ጥያቄ የቀረበለት ማኅበርተኛ የቀረበለትን ዋጋ ያልተቀበለ እንደሆነ ማኅበሩ በተመዘገበበት ቦታ ሥልጣን ያለው ፍ/ቤት የአክሲዮኖቹን ዋጋ የሚወስን ባለሞያ መሾም አለበት፡፡
4) አክሲዮኖቹ እንዲገዙለት ጥያቄ ያቀረበው ባለአክሲዮን የአክሲዮኖቹን ዋጋ ለመወሰን የወጣውን ወጪ መሸፈን አለበት፡፡
5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተደነገገው ቢኖርም አክሲዮን እንዲገዛ ጥያቄ የቀረበለት ማኅበርተኛ የሰጠው ዋጋ ተማኙ ባለሞያ ከወሰነው ያነሰ እንደሆነ ወጪውን በከፊል ወይም በሙሉ እንዲሸፍን ፍ/ቤቱ ሊያዘው ይችላል፡፡

## አንቀጽ 293 የማጫረት ግዴታ

ከማኅበሩ ዋና ገንዘብ ውስጥ ሃምሳ በመቶ እና ከዚያ በላይ የሚወክሉ አክሲዮኖችን ለመግዛት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው የግዥ ጥያቄውን ለሁሉም የማኅበሩ አባላት በማቅረብ አጫርቶ የመግዛት ግዴታ አለበት፡፡

## አንቀጽ 294 አክሲዮን ገዝቶ የማስወጣት መብት

1) የማኅበሩን  ዋና ገንዘብ ዘጠና በመቶ የሚወክሉ አክሲዮኖች በአንድ ማኅበርተኛ የተያዙ እንደሆነ ማኅበርተኛው አናሳ ባለአክሲዮኖች አክሲዮኖቻቸውን ሸጠውለት እንዲወጡ የመጠየቅ መብት አለው፡፡

2) ማኅበርተኛው ጥያቄውን ስለ ጠቅላላ ጉባኤ አጠራር በተደነገገው ስርዓት ለሚመለከታቸው ባለአክሲዮኖች በማሳወቅ በአምስት ሳምንት ውስጥ አክሲዮኖቻቸውን እንዲያስተላልፉለት መጠየቅ አለበት፡፡

3) ማኅበርተኛው አክሲዮኖቹ ስለሚገዙበት ሁኔታ በተለይም የአክሲዮኖቹን ዋጋ ስለወሰነበት መንገድ መረጃ ከጥያቄው ጋር ማቅረብ አለበት፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት ጥያቄ የቀረበለት ባለ አናሳ አክሲዮን የቀረበለትን ዋጋ ያልተቀበለ እንደሆነ ማኅበሩ በተመዘገበበት ቦታ ሥልጣን ያለው ፍ/ቤት የአክሲዮኖቹን ዋጋ የሚወስን ባለሞያ እንዲሾምለት ማመልከት ይችላል፡፡

5) ባለሞያ እንዲሾም ለፍ/ቤት ጥያቄ ያቀረበው ባለአክሲዮን የአክሲዮን ዋጋ ለመወሰን የወጣውን ወጪ መሸፈን አለበት፡፡

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) የተደነገገው ቢኖርም አክሲዮን ለመግዛት ጥያቄ ያቀረበው ማኅበርተኛ የሰጠው ዋጋ ተማኙ ባለሞያ ከወሰነው ያነሰ እንደሆነ ወጪውን በከፊል ወይም በሙሉ ማኅበርተኛው እንዲሸፍን ፍ/ቤቱ ሊያዝ ይችላል፡፡

7) በዚህ አንቀጽ መሰረት የአናሳ ባለአክሲዮኖች መውጣት የማኅበሩን አባላት ቁጥር ከአምስት በታች ያወረደው እንደሆነ በሙብቱ የተገለገለው ባለአክሲዮን ከሶስት ወራት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የማህበሩን አባላት ቁጥር መጨመር ወይም የማኅበሩን ዓይነት መለወጥ አለበት፡፡

**<u>አንቀጽ 295 የባለአክሲዮኖች ተጠያቂነት</u>**

በዚህ ሕግ አንቀጽ 245 የተደነገገው ቢኖርም፤ ማንኛውም ወሳኝ ድምጽ ያለው ባለአክሲዮን ከዚህ በታች ከተመለከቱት አንዱን ፈፅሞ ከተገኘ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**1)** የማኅበሩን፣ የባለአክሲዮኖችን ወይም የማኅበሩን ገንዘብ ጠያቂዎችን ጥቅም ጉዳት ላይ የሚጥል ህገ-ወጥ ድርጊት ሆን ብሎ መፈፀም፤

**2)** የማኅበሩን ንብረት ከባለአክሲዮኑ ንብረት ጋር መቀላቀል፤

**3)** የማኅበሩን እና የባለአክሲዮኑን ማንነት አለመነጣጠል፣ ማኅበሩን ለግል ወይም ለሶስተኛ ወገን ዓላማና ጥቅም እንደ ሽፋን መጠቀም፤

**4)** ስለማኅበሩ የፋይናንስ አቋም የማኅበሩ ገንዘብ ጠያቂዎችን ሊያሳስት የሚችል መረጃ ሆን ብሎ ማውጣት፤

**5)** ከገበያ ዋጋ ባነሰ ክፍያ ወይም አግባብ ካለው የማሕበሩ አመራር ውሣኔ እና እውቅና ውጪ የማኅበሩን ሀብት ለራሱ ወይም ለሶስተኛ ወገኖች የግል ጥቅም ማዋል ወይም

**6)** በሕግ ከሚፈቀደው በላይ የትርፍ ክፍያ መፈፀም፡፡

**<u>ምዕራፍ አራት</u>**

**<u>የማኅበሩ ሥራ አመራር</u>**

**<u>ክፍል አንድ</u>**

**<u>ስለማኅበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ እና የተቆጣጣሪ ቦርድ</u>**

## አንቀጽ 296 የማኅበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ

1) የአክሲዮን ማኅበር በባለአክሲዮኖች የሚመረጡ ቢያንስ ሶስት ቢባዛ አስራ ሶስት ዳይሬክተሮች ይኖሩታል፡፡ ከዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት መካከል ከሦስት ሁለት እጅ (2/3ኛ) በማኅበሩ የዕለተለት ስራ አመራር ውስጥ የስራ አስፈጻሚነት (ኤክሰኩቲቭ) ሚና የሌላቸው መሆን አለባቸው፡፡
2) ባለአክሲዮን ያልሆኑ ሰዎች የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ሆነው ሊመረጡ ይችላሉ፡፡ ሆኖም ባለአክሲዮን ያልሆኑት የቦርድ አባላት ቁጥር ከጠቅላላው የቦርድ አባላት ቁጥር ከአንድ ሶስተኛ ሙብለጥ የለበትም፡፡
3) የቦርድ አባላት ትክክለኛ ቁጥር በመመስረቻ ጽሑፍ በግልጽ ባልተመለከተ ጊዜ ቁጥራቸው በአክሲዮን ፈራሚዎች ጉባኤ ይወሰናል፡፡
4) በሕግ የሰውነት ሙብት የተሰጠው ማኅበር ወይም ሌላ ተቋም አስተዳዳሪ (ዳይሬክተር) ሆኖ ሊሾም ይችላል፡፡ ይህ የሆነ እንደሆነ ተመራጩ በሕግ የሰውነት ሙብት የተሰጠው ማኅበር ለተመረጠባቸው ዓመታት የሚያገለግል ቋሚ ተወካይ ወዲያውኑ መመደብ አለበት፡፡ ቋሚ ተወካዩ የለቀቀ እንደሆነ ወይም በሌላ ማንኛውም ምክንያት ኃላፊነቱን መወጣት ያልቻለ እንደሆነ ምትክ ተወካይ በተቻለ ፍጥነት መመደብ አለበት፡፡
5) ቋሚ ተወካዩ በግሉ የማኅበሩ ዳይሬክተር አይደለም፡፡ ሆኖም በግሉ የማኅበሩ ዳይሬክተር እንደሆነ በመቁጠር የፍትሐብሔር እና የወንጀል ተጠያቂነትን ጨምሮ ለሁሉም ግዴታዎች ከወከለው በሕግ የሰውነት ሙብት የተሰጠው ማኅበር ጋር በአንድነት ኃላፊ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 297 ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች

1) የዳሬክተሮች ቦርድ አባል ለመሆን የሚችለው ቀጥሎ የተመለከቱትን መስፈርቶች የሚያሟላ ሰው ነው፡-

*ሀ) በመመስረቻ ጽሑፍ ወይም በሌላ ሕግ ዝቅተኛ እድሜ ተወስኖ ከሆነ የተወሰነውን እድሜ የሚያሟላ፤*

*ለ) መልካም ሥነ-ምግባር ያለው፤*

*ሐ) ከዚህ በፊት በንግድ ማኅበር አደራጅነት፣ ዳይሬክተርነት፣ ሥራ አስኪያጅነት፣ ተቆጣጣሪነት፣ ኦዲተርነት ወይም በሌሎች የአመራር ኃላፊነቶች ላይ ተመድቦ ሲሰራ ከኃላፊነቱ ጋር በተያያዘ ወይም በማንኛውም ሌላ ሁኔታ በእምነት ማጉደል፣ በስርቆት ወይም በውንብድና ወይም ለቦርድ አባልነት ብቁ በማያደርግ ተመሳሳይ ወንጀል ጥፋተኛነቱ ያልተረጋገጠ፤*

*መ) ሌሎች በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ ወይም በሌላ ሕግ የሚገለጹ መስፈርቶች ካሉ እነዚህን መስፈርቶች የሚያሟላ፡፡*

2) ማንኛውም ሰው አንድን ማህበር በዳይሬክተርነት በሚመራበት ጊዜ ሥልጣኑን ከማህበሩ ጥቅም ጋር በሚጋጭ አኳኋን በመገልገል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ያልተገባ ጥቅም ማግኘቱ የተረጋገጠ እንደሆነ ከዳይሬክተርነት መውረድ አለበት፡፡ ይህ ጥፋት ከተረጋገጠበት ጊዜ አንስቶ ለሁለት ዓመት በማንኛውም ማኅበር ዳይሬክተር መሆን አይችልም፡፡

## አንቀጽ 298 ስለዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ሹመት

1) የመጀመሪያዎቹ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት በመመስረቻ ጽሑፍ መሠረት ሊሾሙ ይችላሉ፡፡ ሹመቱ እንዲጸድቅ ለፈራሚዎች ጉባኤ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ ሆኖም ጉባኤው ሹመቱን ካላጸደቀው ሌሎች የቦርድ አባላትን ይመርጣል፡፡
2) ቀጣዮቹ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የሚሾሙት በጠቅላላ ጉባኤ ነው፡፡
3) የዳይሬክተሮች ቦርድ አባለት የሥራ ዘመን ከሦስት ዓመታት ሊበልጥ አይችልም፡፡ ሆኖም በመመስረቻ ጽሑፍ ተቃራኒ ውሳኔ ከሌለ በስተቀር የሥራ ዘመናቸውን ያጠናቀቁ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት እንደገና መመረጥ ይችላሉ፡፡
4) ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫ ድምጽ የሚሰጠው ለእያንዳንዱ አባል በተናጠል ነው፡፡

## አንቀጽ 299 የተለያየ ህጋዊ አቋም ያላቸው ባለአክሲዮኖች በቦርድ ስለሚወከሉበት ሁኔታ

ማኅበሩ የተለያዩ ጥቅሞች የሚያስገኙ የአክሲዮን መደቦች ያሉት እንደሆነ እያንዳንዱ መደብ ቢያንስ አንድ ተወካይ በቦርድ አባልነት መሾም አለበት፡፡

## አንቀጽ 300 የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ

1) የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ መሆን የሚችለው ባለአክሲዮን የሆነ ዳይሬክተር ነው፡፡ በማኅበሩ የዕለተለት ስራ (ኤክሰከቲቭ) አመራር የሚሳተፍ ዳይሬክተር የቦርድ ሰብሳቢ መሆን አይችልም፡፡
2) የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢና እንዳስፈላጊነቱ ምክትል ሰብሳቢ መጀመሪያ አክሲዮን ለመግዛት በፈረሙ አባላት ጉባኤ ወይም በባለአክሲዮኖች ጉባኤ ሊመረጥ ይችላል፡፡ ጉባኤው የቦርዱን ሰብሳቢ ወይም ምክትል ሰብሳቢ ባልመረጠ ጊዜ በዳይሬክተሮች ቦርድ ይመረጣል፡፡
3) የዳይሬክተሮች ቦርድ በራሱ የተመረጠውን ሰብሳቢ ወይም ምክትል ሰብሳቢ በማንኛውም ጊዜ መሻር ይችላል፡፡

## አንቀጽ 301 የተለየ ኃላፊነት

1. የዳይሬክተሮች ቦርድ ከአባለቱ ለአንዱ ወይም ለተወሰኑት በአንድ ወይም ከዛ በላይ በሆኑ ጉዳዮች ማኅበሩን እንዲወክሉ እንዲሁም ሌላ ሥራ እንዲሰሩ የተለየ ኃላፊነት ሊሰጣቸው ይችላል፡፡
2. ቦርዱ አስፈላጊ መስሎ በታየው ጊዜ ሁሉ ከአባላቱ መካከል ጉዳዮችን መርምረው የመፍትሄ ሐሳብ የሚያቀርቡ ኮሚቴዎችን ማቋቋም ይችላል፡፡ ቦርዱ ለራሱ የተሰጠውን የሥልጣን ገደብ ሳያልፍ የሚያቋቁማቸውን ኮሚቴዎች አባላት መምረጥ እና ሥልጣናቸውን መወሰን ይችላል፡፡

3. የዳይሬክተሮች ቦርድ የኦዲት ኮሚቴ ማቋቋም አለበት፡፡ የኦዲት ኮሚቴ አባል መሆን የሚችሉት የቦርዱ አባላት ብቻ ናቸው፡፡ ሆኖም በማህበሩ የስራ አመራር (ኤክሰከቲቭ) ተሳታፊ የሆኑ የቦርድ አባላት የኦዲት ኮሚቴ አባላት መሆን አይችሉም፡፡
4. በቦርዱ ተቃራኒ የሆነ መመሪያ እስካልተሰጠው ድረስ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) መሰረት የሚቋቋመው ኮሚቴ የቦርድ አባል ያልሆኑ ባለሞያዎችን ሀሳብ መጠየቅ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 302 የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ስለሚገቡት ዋስትና**

**1)** ዳይሬክተሮች ሆነው የሚመረጡ ሰዎች የመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና እንዲያስይዙ በመመስረቻ ጽሑፍ ሊወሰን ይችላል፡፡ ይህ የሆነ እንደሆነ የመመስረቻ ጽሑፉ የዋስትናውን ዓይነት፣ መጠን እና አያያዝ በተመለከተ አስፈላጊውን ዝርዝር ማካተት አለበት፡፡

**2)** ዋስትናው የሚለቀቀው የቦርድ አባሉ ስራውን ሲለቅ እና በሥራ ላይ በነበረበት ጊዜ ከማኅበሩ የሚፈለግበት ዕዳ የሌለ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

**አንቀጽ 303 የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ስለመተካት**

**1)** በበጀት ዓመቱ ውስጥ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የቦርድ አባላት የጎደሉ እንደሆነ የቀሩት አባላት የጎደሉትን የሚተኩ አባላት መምረጥ አለባቸው፡፡ የተተኪዎቹ አባላት የሥራ ዘመን የሚያበቃው የጎደሉት አባላት የሥራ ዘመን በሚያበቃበት ጊዜ ነው፡፡

**2)** የተተኪ አባላት ሹመት እንዲጸድቅ ለሚቀጥለው ጠቅላላ ጉባኤ መቅረብ አለበት፡፡ ጉባኤው ሹመቱን ሊያፀድቅ ወይም በምትካቸው ሌሎች ዳይሬክተሮችን ሊሾም ይችላል፡፡ ሹመቱ በጉባኤው ባይፀድቅም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (**1)** መሠረት የተሾሙት የቦርድ አባላት ሹመታቸው ፀንቶ በቆየበት ጊዜ የፈፀሚቸው ስራዎች ዋጋ ይኖራቸዋል፡፡

**3)** የቀሩት የቦርድ አባላት ቁጥር ከጠቅላላ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ቁጥር ከግማሽ በታች የሆነ እንደሆነ የቀሩት አባላት የጎደሉትን ለማሾም አባላቱ ከጎደሉበት ጊዜ ጀምሮ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ጠቅላላ ጉባኤውን መጥራት አለባቸዉ፡፡ በጎደሉት አባላት ምትክ ሹመት እስኪደረግ ድረስ የቀሩት አባላት ማኅበሩን ያስተዳድራሉ፡፡

**4)** ሁሉም የቦርድ አባላት ስራቸዉን የተው እንደሆነ ተቆጣጣሪ ቦርድ ካለ ቦርዱ ከሌለ ደግሞ ኦዲተሮች የቦርድ አባለት እንዲሾሙ ይህ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ጠቅላላ ጉባኤውን መጥራት አለባቸው፡፡

**5)** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (**4)** መሠረት ጠቅላላ ጉባኤው እስከሚሰበሰብ ድረስ ማኅበሩ ተቆጣጣሪ ቦርድ ካለው ቦርዱ ከሌለው ኦዲተሮቹ ማኅበሩን ያስተዳድራሉ፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ኦዲተሮቹ ያከናወኗቸው ሥራዎች በተለዋጭ ኦዲተሮች መመርመር አለባቸው፡፡

**አንቀጽ 304 ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ስለሚከፈል የሥራ ዋጋ**

1) የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ለሚሰጡት አገልግሎት መጠኑ በጠቅላላው ጉባኤ የሚወሰን ከጠቅላላው ወጪ ላይ የሚታሰብ ዓመታዊ የሥራ ዋጋ ሊከፈላቸው ይገባል፡፡

2) በተጨማሪም የማኅበሩ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ከማኅበሩ ዓመታዊ የተጣራ ትርፍ ላይ የተወሰነ ድርሻ ለዳይሬክተሮች እንዲሰጥ ለመወሰን ይችላል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር (2) መሠረት ለቦርድ አባላት የሚሰጠው ጉርሻ በዛው አመት ለባለአክሲዮኖች ሊከፋፈል ከሚችለው የተጣራ ትርፍ አስር በመቶ መብለጥ አይችልም፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) መሰረት ከተጣራ ትርፍ ላይ ለዳይሬክተሮች ክፍያ የሚፈጸመው በዚያው ዓመት ለባለአክሲዮኖች የትርፍ ድርሻ የተሰጠ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡

5) ለቦርድ አባላት የተወሰነው ጉርሻ የሚሰጠው በጥቅል ነው፡፡ ቦርዱ ለአባላቱ ተገቢ መስሎ በታየው መንገድ ያከፋፍላቸዋል፡፡

6) ከማኅበሩ ዋና ገንዘብ ውስጥ ቢያንስ አስር በመቶ በሚወክሉ ባለአክሲዮኖች ጥያቄ ሲቀርብለት የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ለዳይሬክተሮች የተሰጠው ጉርሻ ከማኅበሩ የፋይናንስ ሁኔታ፣ ከሠራተኞች ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም እንዲሁም ጤናማ የንግድ ስርዓት ከመፍጠር አስፈላጊነት አኳያ በማመዛዘን ከፍተኛ ሆኖ ካገኘው ሊቀንሰው ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 305 የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ስለመሻር</u>**

1) ተቃራኒ የሆነ ድንጋጌ በማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ ውስጥ ቢኖርም፤ ጠቅላላ ጉባዔው የቦርድ አባላትን በማናቸዉም ጊዜ መሻር ይችላል፡፡

2) ያለበቂ ምክንያት የተሻረ የቦርድ አባል ወደ ኃላፊነቱ የመመለስ መብት የለውም፡፡ ሆኖም ማኅበሩን የጉዳት ካሳ መጠየቅ ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 306 በማኅበሩ እና ከማኅበሩ ጋር ቅርበት ባላቸው ሰዎች መካከል የሚደረግ ስምምነት</u>**

1) በአንድ ውል ምክንያት የሚፈጠረው የጥቅም ግጭነት መጠን ከማኅበሩ ሀብት አስር በመቶ እና ከዚያ በላይ ሲሆን በቅድሚያ በጠቅላላ ጉባዔ ስለሚፈቀድበት ሁኔታ በአንቀጽ 394 ንዑስ አንቀጽ (4) እና 395 ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በማኅበሩ እና ከማኅበሩ ጋር ቅርበት ባለቸው ሰዎች/ድርጅቶች መካከል የሚደረግ ስምምነት በቅድሚያ በዳይሬክተሮች ቦርድ መፈቀድ አለበት፡፡ ቦርዱ ስምምነቱን በሚያጸድቅበት ጊዜ የጥቅም ግጭት ያለበት የቦርድ አባል ድምጽ መስጠት አይችልም፡፡ የቦርዱን ፈቃድ ሳያገኝ የሚደረግ ስምምምነት አይጸናም፡፡ ፈቃድ ከተሰጠም ጉዳዩን ወዲያውኑ ኦዲተሮች እንዲያውቁት መደረግ ይኖርበታል፡፡

2) ኦዲተሮች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (**1**) ድንጋጌ መሰረት በዳይሬክተሮች ቦርድ በተፈቀዱት ስምምነቶች ላይ ራሱን የቻለ ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባኤው ማቅረብ አለባቸው፡፡ በኦዲተሮች የሚቀርበውም ሪፖርት ስለውሉ ሁኔታ፣ የተፈፀመውን ክፍያ አይነትና መጠን፣እንዲሁም ለጥቅም ግጭት ምክንያት የሆነውን የቅርበት ሁኔታ የሚገልፅ በቂ መረጃ ማካተት ይኖርበታል፡፡ ጠቅላላ ጉባኤውም በሪፖርቱ መሠረት ተገቢ የሆነውን ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**3)** ጠቅላላ ጉባኤው ያጸደቀውን ስምምነት ባለአክሲዮኖች መቃወም የሚችሉት በማኅበሩ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርስ ወይም ስምምነቱ በማታለል የተፈጸመ ከሆነ ብቻ ነው፡፡

**4)** ጠቅላላ ጉባኤው ስምምነቱን ያላጸደቀው በማኅበሩ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርስ ወይም ስምምነቱ በማታለል የተፈጸመ በመሆኑ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር፤ የስምምነቱን ተፈጻሚነት አያስቀረውም፡፡ ስምምነቱ ማኅበሩ ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት ማታለሉን የፈጸመው ወገን እና ማታለሉ መፈጸሙን ወይም ስምምነቱ በማኅበሩ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርስ መሆኑን እያወቁ ወይም ማወቅ ሲገባቸው የፈቀዱ የቦርድ አባላት በአንድነትና በተናጠል ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

**5)** ከዚህ በላይ ባሉት ንዑሳን አንቀጾች የተመለከቱት ድንጋጌዎች ማኅበሩ ለማኅበሩ ቅርበት ካላቸው ሰዎች ጋር እንደማንኛውም ደንበኛ በሚያደረጋቸው መደበኛ ስምምነቶች ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም፡፡

**6)** ለዚህ አንቀጽ ዓላማ ለማኅበሩ ቅርበት ያላቸው ሰዎች ማለት የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

**(ሀ)** የማኅበሩ የቦርድ አባላት፤ ሥራ አስኪያጅ፣ ኦዲተር፣ የተቆጣጣሪ ቦርድ አባላት፣ የማኅበሩ ፀሐፊዎች፤

**(ለ)** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 (ሀ) ከተዘረዘሩት ሰዎች ጋር በፌዴራል የቤተሰብ ሕግ መሰረት የስጋና የጋብቻ ዝምድና ያላቸው ሰዎች፤

**(ሐ)** በዚህ አንቀጽ ንዑስ **6(ሀ)** እና **(ለ)** የተጠቀሱት ሰዎች አመራር፣ ባለድርሻ ወይም ተጠቃሚ የሆኑበት የንግድ ማኅበር ወይም ድርጅት፤

**(መ)** የማኅበሩ እናት ወይም ተቀጥላ የሆነ ኩባንያ፤

**(ሠ)** በመመስረቻ ጽሁፍ ወይም በሕግ ያነሰ የድርሻ መጠን ካልተቀመጠ በስተቀር፤ ከአስር በመቶ ያላነሰ አክሲዮን ከማኅበሩ የገዙ፣ማኅበሩ ባለአክሲዮን የሆነባቸው ወይም እርስ በእርሳቸው አክሲዮን የተገዛዙ የንግድ ማኅበራት፣

**(ረ)** ሌሎች በመመስረቻ ጽሑፍ ወይም በሌላ ሕግ ለማኅበሩ ቅርበት አላቸው ተብለው የተጠቀሱ ሰዎች፡፡

## <u>አንቀጽ 307 ዳይሬክተሮች ከማኅበሩ ብድር እንዳይወስዱ ስለመከልከል</u>

**1)** የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ በቅድሚያ ካልፈቀደ በቀር አንድ ማኅበር ለማኅበሩ ወይም ለእናት ማኅበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ብድር መስጠት ወይም የቦርድ አባላት ከሶስተኛ ወገኖች ጋራ ላሉባቸው ግዴታዎች ዋስ መሆን ወይም ንብረቱን በዋስትና ማስያዝ የለበትም፡፡

**2)** በተጨማሪም ተበዳሪው የእናት ኩባንያ የቦርድ አባል የሆነ እንደሆነ፤ ውሉ በቅድሚያ በእናት ማኅበሩ የባለአክሲዮኖች ጉባዔ መፈቀድ አለበት፡፡

**3)** ጠቅላላ ጉባዔው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ሥር የተመለከቱትን ውሳኔዎች ከማሳለፉ በፊት የውሉን ባህሪ፣ የብድሩን መጠን እና ዓላማ እንዲሁም ከውሉ ጋር በተያያዘ የማህበሩ ሃላፊነት በተመለከተ ነጻ እና ገለልተኛ በሆነ የውጭ ኦዲተር በጽሁፍ ሪፖርት ሊቀርብለት ይገባል፡፡

## <u>አንቀጽ 308 የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔዎች</u>

**1)** ማንኛዉም ውሳኔ የሚተላለፈው ከዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ከግማሽ በላይ በስብሰባው ላይ ሲገኙ ወይም ሲሳተፉ ነው፡፡ በማኅበሩ የመመስረቻ ጽሑፍ ከፍ ያለ የድምጽ ብልጫ እንደሚያስፈልግ ካልተደነገገ በቀር፤ ውሳኔዎች የሚተላለፉት በቦርዱ ስብሰባ ላይ በቀጥታም ሆነ በተወካይ በተገኙት እና በዚህ ሕግ አንቀጽ 309 መሰረት በኤሌክትሮኒክ ዘዴ በተሳተፉት የቦርድ አባላት የድምጽ ብልጫ ነው፡፡ ድምፅ እኩል ለእኩል በሚከፈልበት ጊዜ በመመስረቻ ፅሁፉ ተቀራኒ ድንጋጌ ከሌለ በቀር፤ የቦርዱ ሊቀመንበር የደገፈው ሐሳብ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

**2)** የቦርዱ ውሳኔዎች በቃለ ጉባኤ ተይዘው በስብሰባው ላይ በአካል ወይም በተወካይ በተገኙት የቦድ አባላት እና በማኅበሩ ፀሐፊ መፈረም አለባቸው፡፡ ቃለ ጉባኤው ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ መዝገብ ውስጥ መቀመጥ አለበት፡፡

**3)** የውሳኔዎች ቅጂዎች በቦርዱ ሊቀመንበር እና በማኅበሩ ፀሐፊ መፈረም አለባቸው፡፡

**<u>አንቀጽ 309 በኤለክትሮኒክ ዘዴ ስለሚደረግ የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ</u>**

1) በማኅበሩ የመመስረቻ ጽሁፍ የተጣለ ክልከላ ከሌለ በቀር፤ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ስብሰባ ላይ በቪድዮ ወይም በሌላ የመገናኛ ዘዴ መሳተፍ ይችላሉ፡፡ የመገናኛ ዘዴው የተሰብሳቢዎችን ማንነት ለመለየት የሚያስችል እንዲሁም ውጤታማ ተሳትፎን የሚያረጋግጥ መሆን አለበት፡፡ የመገናኛ ዘዴው ቢያንስ የተሳታፊዎችን ድምጽ ሳይቆራረጥ የሚያስተላልፍ እና ተሰብሳቢዎቹ በአንድ ጊዜ መሳተፍ እንዲችሉ የሚፈቅድ መሆን አለበት፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የሚሳተፉት የቦርድ አባላት ድምጻቸውን በቃል መስጠት ይችላሉ፡፡
3) ከቦርዱ ጠቅላላ አባላት ውስጥ ቢያንስ አንድ ሶስተኛው (ሲሶው) በስብሰባው ላይ በአካል ካልተገኙ በቀር፤ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት በተደረገ ስብሰባ የተላለፈ ውሳኔ አይጸናም፡፡
4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር በተመለከተው አኳኋን ውሳኔ ሊተላለፍባቸው የሚችሉ ጉዳዮች ላይ በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ ገደብ ማድረግ ይቻላል፡፡

**<u>አንቀጽ 310 ስለ ውክልና</u>**

1) በማህበሩ የመመስረቻ ጽሁፍ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በቀር፤ በቦርድ ስብሰባ ላይ አንድ ዳይሬክተሮች ቦርድ አባል በሌላ አባል ሊወከል ይችላል፡፡ ውክልናው በደብዳቤ፣ ፋክስ ወይም ኢመይል ሊሰጥ ይችላል፡፡
2) አንድ የቦርድ አባል በአንድ ስብሰባ ላይ ከአንድ በላይ የሆኑ የቦርድ አባላትን ወክሎ መሳተፍ አይችልም፡፡
3) የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች በሕግ የሰውነት መብት በተሰጠው የቦርድ አባል ተወካይ ላይ ጭምር ተፈተጻሚ ይሆናሉ፡፡

**<u>አንቀጽ 311 ለማኅበሩ ቅርበት ያላቸው ሰዎች መዝገብ</u>**

**1)** ማንኛዉም የአክሲዮን ማኅበር በዋና መስሪያ ቤቱ የማኅበሩ ቦርድ አባላትን፣ የስራ አስኪያጆችን፣ የተቆጣጣሪ ቦርድ አባላትን፣ የኦዲተሮችን፣ የማኅበሩ ፀኃፊዎችን እና በዚህ ሕግ አንቀጽ 306 ንዑስ አንቀጽ

**6 (ለ)፣(ሐ)** እና **(ረ)** መሠረት የተጠቀሱት ሰዎች የግል ሁኔታ፣ ሞያቸዉን፣ በሌሎች የንግድ ማኅበራት ወይም ድርጅቶች ያላቸውን ጥቅም፤ ስራ፣ የቦርድ አባልነት ወይም ሌላ ኃላፊነት ካላቸው ይህንኑ እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን የሚያሳይ መዝገብ መያዝ አለበት፡፡ ዳይሬክተሩ የንግድ ማኅበር የሆነ እንደሆነ የኩባንያው ስምና የዋና መስሪያ ቤቱን አድራሻ ማሳየት አለበት፡፡

**2)** የሚመለከተው የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል፣ የተቆጣጣሪ ቦርድ አባል፣ ኦዲተር እንዲሁም የማኅበሩ ጸሐፊ መዝገቡ ውስጥ በሰፈሩት ጉዳዮች ላይ ለውጥ መደረጉን ካወቀ ይህንኑ ካወቀበት ቀን ጀምሮ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ ለአክሲዮን ማህበሩ ዋና መስሪያቤት ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

**3)** ባለአክሲዮኖች እና የመንግስት መስሪያቤት ተወካዮች መዝገቡን በነጻ ማየት ይችላሉ፡፡ ባለአክሲዮን ያልሆኑ ሰዎች ለዚሁ የተወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ በመፈጸም መዝገቡን የማየት መብት አላቸው፡፡

**<u>አንቀጽ 312 የባለቤትነት ጥቅምን ስለማሳወቅ</u>**

አክሲዮኑ ለሕዝብ ክፍት በሆነ ማኅበር (አንቀጽ 258-260) ውስጥ በተናጠል ወይም ከጥቅም ተጋሪዎቻቸው ጋር በጋራ (የአንድ ቤተሰብ አባላት፣ የተዛመዱ ኩባንያዎች) ቀጥተኛ በሆነ መንገድ ወይም በተዘዋዋሪ፣ የማኅበሩን ዋና ገንዘብ አምስት በመቶ እና ከዛ በላይ የሆነ ድርሻ የያዙ እንደሆነ ማሕበሩ የእነዚህን ባለአክሲዮኖች ስም እና የያዙት ድርሻ መጠን ለንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም አግባብ ላለው ሌላ መስሪያቤት ማሳወቅ አለበት፡
፡

**<u>አንቀጽ 313 በዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የተያዙ አክሲዮኖችና የግዴታ ወረቀቶች መዝገብ</u>**

**1)** ማንኛውም የአክሲዮን ማኅበር፡-

**(ሀ)** በአክሲዮን ማኅበሩ፤

**(ለ)** በተቀጥላ ማኅበሩ፤

**(ሐ)** ተቀጥላ በሆነበት በማናቸዉም እናት ኩባንያ ውስጥ፤

እያንዳንዱ የማኅበሩ የቦርድ አባል ያለውን የአክሲዮን እና የግዴታ ወረቀት ብዛትና ዋጋቸውን የሚያመለክት መዝገብ በዋናው መስሪያ ቤቱ መያዝ አለበት፡፡

**2)** ባለአክሲዮኖች ወይም የግዴታ ወረቀት የያዙ ሰዎች ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ ከመደረጉ በፊት ባለው ጊዜ ውስጥ መዝገቡንና ለጠቅላላ ጉባኤ የሚቀርቡ ሰነዶችን እንዲያዩ ክፍት መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

**3)** መዝገቡ የማኅበሩ ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ በሚካሄድበት ጊዜ በጉባኤው በሚሳተፍ ማንኛዉም አባል እንዲታይ ክፍት መሆን ይኖርበታል፡፡

**4)** አግባብ ያለው የመንግስት አካል በማናቸዉም ጊዜ መዝገቡን ማየት ወይም ግልባጭ ወይም በአጭር የተውጣጣ ጽሁፍ መጠየቅ ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 314 ስለዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት እና ሥራ አስኪያጆች ክፍያ የሚሰጡ መግለጫዎች</u>**

1) ለአመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ የሚቀርበው መግለጫ ለእያንዳንዱ የቦርድ አባል እና ዋና ሥራ አስኪያጅ የተከፈለውን አጠቃላይ የድካም ዋጋ፣ በየጊዜው የተከፈለውን መጠን እና ሌሎች በዓይነት የተሰጡ ጥቅማ ጥሞችን ማሳየት አለበት፡፡

2) ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት እና ለዋና ሥራ አስኪያጅ የተሰጠ ብድር ወይም የተገባ ዋስትና ካለ ለአመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ በሚቀርበው መግለጫ ላይ በግልጽ መመልከት ይኖርበታል፡፡

**<u>አንቀጽ 315 የዳይሬክተሮች ቦርድ ኃላፊነት - ጠቅላላ</u>**

ቦርዱ በሕግ፣ በማኅበሩ የመመስረቻ ጽሑፍ እና በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎች የተሰጡትን ተግባራት የመፈፀም ግዴታ አለበት፡፡ ይህ ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

1) የማኅበሩን ፋይናንስ የማስተዳደር፤ ማኅበሩ በቂ ዋና ገንዘብ እና ክፍያዎችን በወቅቱ የመፈጸም አቅም ያለው መሆኑን የማረጋገጥ፤
2) የማኅበሩ አስተዳደራዊ አደረጃጀት የማኅበሩን የፋይናንስ መግለጫዎችን እና ቁመናን ለመቆጣጠር የሚያስችል መሆኑን የማረጋገጥ፤
3) የማኅበሩን ለአደጋ ተጋላጭነት እና ውስጣዊ አሰራር ለመቆጣጠር የሚያስችል በቂ የአሰራር ሥርዓት የመዘርጋት፤
4) ማኅበሩ ተቆጣጣሪ ቦርድ ያለው እንደሆነ ቦርዱ ሃላፊነቱን በአግባቡ ይወጣ ዘንድ የተሟላ መረጃ በወቅቱ የማቅረብ፤
5) በማኅበሩ ላይ ጉዳት እንዳይደረስ መከላለከል ወይም ጉዳት የሚያደርሱ ነገሮችን መከላከል ካልተቻለ አሉታዊ ተጽእኖአቸውን የመቀነስ፤
6) በዚህ አንቀጽ ከላይ የተዘረዘሩት እንደተጠበቁ ሆነው፤ ቦርዱ የሚከተሉት ኃላፊነቶች አሉበት፡-

(ሀ) የማኅበሩ ባለአክሲዮኖች እና የቦርድ ስብሰባዎች ቃለ ጉባኤ፣ የሂሳብ መዝገብ፣ የባለአክሲዮኖች እና የዳይሬክተሮች መዛግብት እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች እንዲያዙ የማድረግ፤

(ለ) የሒሳብ መዛግብት ለኦዲተሮች በአስፈላጊው ጊዜ ሁሉ እንዲቀርቡ የማድረግ፤

(ሐ) የፋይናንስ እቅስቃሴን ያካተተ ዓመታዊ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባኤ የማቅረብ፤

(መ) በዚህ ሕግ ወይም በመመስረቻ ጽሑፉ መሠረት የማኅበሩን ጉባኤዎች የመጥራት፤

(ሠ) የማኅበሩ ዋና ገንዘቡ ¾ (ሦስት አራተኛ) በኪሳራ ባጣ ጊዜ ወዲያውኑ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ የመጥራት፤

(ረ) በዚህ ሕግ፣ በመመስረቻ ጽሑፍ ወይም በማኅበርተኞች ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ መሰረት የመጠባበቂያ ገንዘብ የማቋቋም እና የመያዝ እና

(ሰ) ማኅበሩ ዕዳውን መክፈል ያቆመ እንደሆነ ከገንዘብ ጠያቂዎች ጋር የመጠባበቂያ ስምምነት እንዲደረግ ወይም የመክሰር ሥነ-ሥርዓት እንዲከፈት ለፍርድ ቤት የማመልከት፡፡

**<u>አንቀጽ 316 የመታመን ግዴታ /ታማኝነት/</u>**

1) የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ማኅበሩን የበለጠ ስኬታማ ያደርጋል ብለው በቅን ልቦና ያመኑበትን እርምጃ መውሰድ አለባቸው፡፡ የመላው ባለአክሲዮኖችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ መስራት ይኖርባቸዋል ፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር የተመለከተውን ኃላፊነት በሚወጣበት ጊዜ አንድ ዳይሬክተር የማኅበሩን የረጅም ጊዜ ጥቅም፣ የሰራተኞች ጥቅም፣ ከማኅበሩ ገንዘብ የመጠየቅ መብት ያላቸውን ሰዎች ጥቅም፣ የማኅበሩ ስራ በማኅበረሰቡ እና በአከባቢው ላይ የሚኖረውን ተጽእኖ ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡

## አንቀጽ 317 በነጻነት የመወሰን ግዴታ

1) አንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ኃላፊነቱን በሚወጣበት ጊዜ በነጻነትና በመሰለው መንገድ መወሰን አለበት፡፡
2) የቦርድ አባሉ ይህ ኃላፊነቱን እንደተላለፈ የማይቆጠረው፤

ሀ) ማኅበሩ ወደፊት የቦርዱ አባላት የሚኖራቸውን ምርጫ የሚገድብ ስምምነት አድርጎ እንደሆነ በስምምነቱ መሰረት ሲሰራ፤ እና

ለ) በማኅበሩ መመስረቻ ጽሁፍ ላይ በተደነገገው ወይም የማኅበርተኞች ጠቅላላ ጉበኤ በወሰነው መሰረት ሲሰራ ነው፡፡

## አንቀጽ 318 ጥንቃቄ እና ትጋት

1) የአንድ ማኅበር የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ኃላፊነቱን በጥንቃቄ፣ በብልሀትና በትጋት መወጣት አለበት፡፡ በጥንቃቄ ወይም በትጋት ጉድለት በማኅበሩ እና በባለአክሲዮኖች ላይ ለሚደርስ ጉዳት ዳይሬክተሩ ተጠያቂ ይሆናል፡፡
2) በዚህ ረገድ የቦርድ አባሉ ኃላፊነት የሚለካው በምክንያታዊ ደረጃ ትጉህ የሆነ የአንድ ማኅበር የቦርድ አባል ሊኖረው ከሚገባ ጠቅላላ እውቀት፤ብልሃትና ጥንቃቄ አንጻር ነው፡፡

## አንቀጽ 319 ውድድርን ስለመከልከል

ጠቅላላ ጉባኤው ካልፈቀደ በስተቀር የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት በራሳቸው ወይም በሦስተኛ ወገኖች ስም ከማኅበሩ ጋር መወዳደር ወይም ተወዳዳሪ በሆኑ የንግድ ማኅበራት ውስጥ በአንድነትና በተናጠል ኃላፊነት ያለበት አባል መሆን አይችሉም፡፡

## አንቀጽ 320 ከጥቅም ግጭት ስለመቆጠብ

1) የአንድ ማኅበር ዳይሬክተር ጥቅሙ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከማኅበሩ ጥቅም ጋር ከሚጋጭበት ወይም ሊያጋጭ ከሚችልበት ሁኔታ ራሱን ማራቅ አለበት፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ክልከላ ማኅበሩ ሊጠቀምባቸው ቢችልም ባይችልም በተለይ ንብረትን፣ መረጃን እና የንግድ ዕድልን መጠቀም በተመለከተ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

3) አንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል የነበረ ሰው ከኃላፊነት ከተነሳ በኋላም ቢሆን አባል በነበረበት ወቅት በስራው ምክንያት ያወቀውን መረጃ እና የንግድ ዕድል መጠቀም አይችልም፡፡
4) በዚህ አንቀጽ የተደነገገው ክልከላ ዳይሬክተሩ ከማኅበሩ ጋር ከሚደርገው የስራ ውል ጋር በተያያዘ ሊነሳ የሚችል የጥቅም ግጭትን አይመለከትም፡፡
5) አግባብነት ባለው የዚህ ሕግ ድንጋጌ መሰረት የዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ በዚህ አንቀጽ የተጣለውን ክልከላ በማንሳት ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 321 የጥቅም ግጭትን ስለማሳወቅ</u>**

1) እያንዳንዱ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል በራሱ እና በማኅበሩ መካከል የጥቅም ግጭት ሊፈጠርበት የሚችል ማንኛውንም ሁኔታ ለቦርዱ ማሳወቅ አለበት፡፡
2) በተለይም ከማህበሩ ጋር ሊደረግ የታሰበ ውል ወይም ሌላ ዓይነት ግንኙነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የቦርድ አባሉን ጥቅም የሚነካ ከሆነ አባሉ ስለጥቅሙ ባህሪ እና መጠን ለተቀሩት ዳይሬክተሮች የተሟላ መግለጫ መስጠት አለበት፡፡
3) ከማኅበሩ ጋር የተደረገ ውል ወይም ሌላ ማንኛውም ዓይነት ግንኙነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የዳይሬክተሩን ጥቅም የሚነካ ከሆነ ዳይሬክተሩ ስለጥቅሙ ባህሪ እና መጠን ለተቀሩት ዳይሬክተሮች መግለጫ መስጠት አለበት፡፡
4) በዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች መሰረት መሰጠት ያለበት ማንኛውም መግለጫ መቅረብ በሚቻልበት ምክንያታዊ ፍጥነት መሰጠት ይኖርበታል፡፡

**<u>አንቀጽ 322 በሦስተኛ ወገን የሚሰጥ ጥቅም</u>**

1) አንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ሥራውን በማከናወን ላይ እያለ በሦስተኛ ወገን ስጦታም ሆነ ሌላ ዓይነት ጥቅም የተሰጠው እንደሆነ የጥቅሙ ተጋሪ ያልሆኑ ዳይሬክተሮችን ወይም የማኅበሩን ጠቅላላ ጉባዔ ሳያስፈቅድ መቀበል የለበትም፡፡
2) ስጦታውን ወይም ጥቅሙን መቀበል የጥቅም ግጭት የሚፈጥርበት ምክንያታዊ ዕድል የሌለ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጣለው ክልከላ ተፈጻሚነት የለውም፡፡
3) በዚህ አንቀጽ የተጣለው ክልከላ ከዳይሬክተርነት በተነሳ ሰው ላይም ጭምር ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**<u>አንቀጽ 323 ድምጽ ላይ ስለሚደረግ ገደብ</u>**

1) በማኅበሩ እና በዳይሬክተሮች ቦርድ አባሉ መካከል የሚደረግ ውልን፣ በሦስተኛ ወገን ለዳይሬክተሩ የሚሰጥ ጥቅምን ወይም የጥቅም ግጭት ሊፈጥር በመቻሉ በቦርድ መጽደቅ ያለበትን ሌላ ማናቸውም ዓይነት ጉዳይን በተመለከተ ቦርዱ ውሳኔ በሚያስተላልፍበት ጊዜ ጉዳዩ የሚመለከተው አባል ድምጽ መስጠት አይችልም፡፡
2) እንዲሁም በዚህ ህግ አንቀጽ 311 ስር በተመለከተው መሠረት ከማኅበሩ ጋር ቅርበት ባላቸው ሰዎች እና በማኅበሩ መካከል የሚደረግ ውልን ወይም ከጉዳየዩ ላይ ዳይሬክተሩ ትርጉም ያለው ጥቅም የሚያገኝ

እስከሆነ ድረስ በማኅበሩና በሌላ ማንኛውም ሰው መካከል የሚደረግ ውልን በተመለከተ ጉዳዩ የሚመለከተው ዳይሬክተር ድምጽ መስጠት አይችልም፡፡

## አንቀጽ 324 የዳይሬክተሮች ቦርድ ስልጣን

1) የዳይሬክተሮች ቦርድ በሕግ፣ በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ ወይም በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎች የሚሰጥ ስልጣን ይኖረዋል፡፡
2) የማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት በአንድነት ስራቸውን የሚያካሄዱና ለማህበሩ እንደራሴ መሆናቸውን ወይም ከእነርሱ ውስጥ አንዱ ለዚህ ተግባር በተለይ ስልጣን ያለው መሆኑን መለየት አለበት፡፡
3) ለማኅበሩ እንደራሴ እንዲሆኑ የተፈቀደላቸዉ ሰዎች በማህበሩ ስም የማኅበሩን ጉዳይ ለመፈፀም አስፈላጊ የሆኑትን ስራዎች ሁሉ በእንደራሴነት የመስራት መብት አላቸዉ፡፡ ስልጣናቸዉ ላይ የሚደረግ ማንኛዉም ገደብ ቅን ልቦና ባላቸዉ ሶስተኛ ወገኖች ላይ ውጤት አይኖረውም፡፡

## አንቀጽ 325 የዳይሬክተሮች ቦርድ አባለት ለማኅበሩ ስላለባቸዉ ተጠያቂነት

1) የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ኃላፊነታቸዉን ባለመወጣታቸው ለሚደርሰው ጉዳት ለማኅበሩ በአንድነትና በተናጠል ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡
2) የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት በተገቢው ጥንቃቄና ትጋት ስለመስራታቸዉ የማስረዳት ሸክም አለባቸው፡፡

## አንቀጽ 326 ዳይሬክተሮችን ከተጠያቂነት ነጻ ስለሚያደርጉ ስምምነቶች

1) ከማኅበሩ ስራ ጋር በተያያዘ በቸልተኝነት፣ ኃላፊነትን ባለመወጣት ወይም በእምነት ማጉደል ምክንያት ሊደርስበት ከሚችል ተጠያቂነት አንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባልን ነጻ ለማድረግ ታስቦ የተደረገ ስምምነት ወይም ድንጋጌ አይጸናም፡፡
2) አንድ ዳይሬክተር ከማኅበር ስራ ጋር በተያያዘ በቸልተኝነት፣ ሃላፊነትን ባለመወጣት፣ በእምነት ማጉደል መክፈል ያለበትን ካሳ በከፊልም ሆነ በሙሉ ማኅበሩ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ እንዲከፍልለት ወይም ዳይሬክተሩ ከከፈለ በኋላ እንዲተካለት የሚደነግግ ስምምነት አይጸናም፡፡
3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር (1) እና (2) ድንጋጌዎች በማኅበሩ መመስረቻ ጽሁፍ፣ ከማኅበሩ ወይም ሌላ አካል ጋር በተደረገ ማንኛውም ውል ውስጥ በሚገኝ ድንጋጌ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
4) የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች በቦርድ አባላት ላይ ሊደርስ የሚችለውን ተጠያቂነት በተመለከተ ማኅበሩን የመድን ሽፋን ከመግዛት አያግዱትም፡፡
5) የመንግስት የአስተዳደር አካላት፣ ገንዘብ ጠያቂዎች፣ ባለአክሲዮኖች ወይም ማኅበሩ ራሱ የቦርድ አባላት ላይ ክስ ያቀረበ እንደሆነ ማኅበሩ ለአባላቱ ራሳቸውን የሚከላከሉበት ገንዘብ ሊያቀርብላቸው ይችላል፡፡ የተረቱ እንደሆነ ዳይሬክተሮቹ ገንዘቡን ለማኅበሩ የመመለስ ግዴታ አለባቸው፡፡

## አንቀጽ 327 መቃወሚያ

1) በቅን ልቦና በተወሰደ የንግድ ውሳኔ ምክንያት በማኅበሩ ላይ ጉዳት ቢደርስ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ካሳ እንዲከፍል የማይገደደው፡-

ሀ) ውሳኔ ያስተላለፈበት ጉዳይ የግል ጥቅሙን የማይመለከት ከሆነ፤

ለ) ስለሚወስንበት ጉዳይ ውሳኔው በተወሰደበት ሁኔታ ውስጥ በዳይሬክተሩ ምክንያታዊ እይታ በቂ ነው ብሎ ያሰበውን ያህል መረጃ ይዞ የወሰነ ከሆነ እና

ሐ) ውሳኔው ማኅበሩን ይጠቅማል የሚል ምክንያታዊ እምነት የነበረው ከሆነ ነው፡፡

2) የቦርዱን ውሳኔ በመቃወም ድምጽ ሰጥቶ ስለተወሰደው ውሳኔ በተቻለ ፍጥነት የውጭ ኦዲተሩን ያሳወቀ ዳይሬክተር ከውሳኔው ጋር በተያያዘ ተጠያቂነት የለበትም፡፡

3) አንድ የቦርድ አባል የወሰደው ውሳኔ የጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔን ወይም የማኅበሩን መመስረቻ ጽሑፍ ወይም ሕግን የተከተለ ከሆነ ውሳኔው ማኅበሩ ላይ ላደረሰው ጉዳት ተጠያቂ አይሆንም፡፡

**<u>አንቀጽ 328 ማኅበሩ በዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ላይ ስለሚያቀርበው ክስ</u>**

**1)** ማኅበሩ ከኃላፊነታቸው ጋር በተያያዘ በዳይሬክተሮች ላይ ክስ ማቅረብ የሚችለው ጠቅላላ ጉባኤው ሲወስን ነው፡፡ ጉዳዩ በዕለቱ በአጀንዳነት ባይያዝም ጠቅላላ ጉባኤው በጉዳዩ ላይ ውሳኔ መስጠት ይችላል፡፡

**2)** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (**1)** መሠረት ክስ እንዲቀርብ ከተወሰነበት ቀን አንስቶ ባሉት 3 (ሦስት) ወራት ጊዜ ውስጥ ማኅበሩ ክሱን ያላቀረበ እንደሆነ ከማኅበሩ ዋና ገንዘብ ቢያንስ አስር  በመቶ ድርሻ ያላቸው ባለአክሲዮኖች በጋራ በማኅበሩ ስም ክስ ማቅረብ ይችላሉ፡፡

**3)** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ስር የተደነገገው ቢኖርም፤ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ  ከማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል፣ የተቆጣጣሪ ቦርድ አባል፣ ዋና ሥራ አስኪያጅ ወይም በዚህ ሕግ አንቀጽ 306 ንዑስ አንቀጽ (6) መሰረት ከአንድ የአክሲዮን ማኅበር ጋር ቅርበት አላቸው ተብለው  ከተዘረዘሩት ሰዎች ጋር ማህበሩ ያደረገው ውል የዚህን ሕግ ድንጋጌዎች ያልተከተለ እንደሆነ በዚህ ምክንያት በማሕበሩ ላይ የደረሰውን ጉዳት በተመለከተ ከማህበሩ ዋና ገንዘብ አስር በመቶ የማያንስ ድርሻ ያላቸው ባለአክሲዮኖች በዚህ ሕግ የተጣለባቸውን ግዴታ ባልተወጡ የማኅበሩ ዳይሬክተሮች ላይ በቀጥታ ክስ ማቅረብ ይችላሉ፡፡

**4)** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ወይም (3) መሰረት ክስ መመስረት ለሚፈልጉ ባለአክሲዮኖች ማኅበሩ ክሱን ለመመስረት አስፈላጊ የሆኑትን ሰነዶች እና ማስረጃዎች ማሳየት እና ኮፒ መስጠት ይኖርበታል፡፡ በተለይም ባለአክሲዮኖቹ የጥቅም ግጭት ይኖርባቸዋል ብለው የሚገምቱዋቸውን ውሎች እና ደጋፊ ሰነዶች የመመርመር መብት አላቸው፡፡

**5)** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ወይም 3 መሰረት በባለአክሲዮኖች የቀረበው ክስ ውጤት ምንም ይሁን ምን ክሱ የቀረበው በቅን ልቦና እስከሆነ ድረስ ማኅበሩ ለባለአክሲዮኖቹ በክሱ ምክንያት ያወጡትን ወጪ መተካት አለበት፡፡

**6)** ማኅበሩ በዳይሬክተሮች ላይ የሚያቀርበውን ክስ ለመተው ወይም በግልግል ለመጨረስ ይችላል፡፡ ሆኖም ክሱን ለመተውና በግልግል ለመጨረስ የሚቻለው ከማኅበሩ ዋና ገንዘብ ቢያንስ አስር በመቶ ድርሻ ያላቸው ባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤው ክስ ለመተው ወይም በግልግል ለመጨረስ የሰጠውን ውሳኔ ያልተቃወሙት እንደሆነ ነው፡፡

## አንቀጽ 329 የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ከማኅበሩ ላይ ገንዘብ ለሚጠይቁ ሰዎች ስላለባቸው ተጠያቂነት

(1) ማኅበሩ ከማኅበሩ ላይ ገንዘብ ለሚጠይቁ ሰዎች ክፍያ መፈጸም የሚችልበት ምክንያታዊ ዕድል እንደሌለ ዳይሬክተሮች ካወቁ በኋላ ወይም ማወቅ ሲገባቸው ማኅበሩ በሥራው የቀጠለ እንደሆነ ዳይሬክተሮቹ በገንዘብ ጠያቂዎች ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ተጠያቂ ናቸው፡፡

(2) የማኅበሩ ንብረት ዕዳውን ለመክፈል የማይበቃ ሆኖ ሲገኝ ገንዘብ ጠያቂዎች ንብረቱ እንዲባክን ወይም እንዲጎድል ባደረጉት ዳይሬክተሮች ላይ በባከነው ወይም በተጓደለው ንብረት መጠን የኃላፊነት ክስ ሊያቀርቡ ይችላል፡፡

(3) ማኅበሩ በዳይሬክተሮች ላይ የሚያቀርበውን ክስ ለመተው ቢወስን ከማኅበሩ ላይ ገንዘብ የሚጠይቁ ሰዎች በዳይሬክተሮች ላይ ክስ ለማቅረብ ያላቸውን መብት አያስቀርም፡፡

## አንቀጽ 330 ባለአክሲዮኖችና ሶስተኛ ወገኖች ስለሚያቀርቡት ክስ

የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች በዳይሬክተሮች ጥፋት ወይም በማጭበርበር ተግባር በቀጥታ በግል የተጎዳ ባለአክሲዮን ወይም ሦስተኛ ወገን ኪሳራ ለማግኘት ያለውን ክስ የማቅረብ መብት አይነኩም፡፡

## አንቀጽ 331 ተቆጣጣሪ ቦርድ

**1)** የአክሲዮን ማኅበር ተቆጣጣሪ ቦርድ እንዲኖረው በመመስረቻ ጽሑፍ ሊወሰን ይችላል፡፡

**2)** ተቆጣጣሪ ቦርዱ በጠቅላላ ጉባኤ የሚሾሙ ቁጥራቸው ከሦስት ያላነሱ ከአምስት ያልበለጡ አባላት ይኖሩታል፡፡

**3)** ጠቅላላ ጉባኤው የተቆጣጣሪ ቦርድ አባላትን በማንኛውም ጊዜ ሊሽራቸው ይችላል፡፡ ከተቆጣጣሪ ቦርድ አባልነት የተሻረ ሰው የተሻረው ካለበቂ ምክንያት ቢሆንም እንኳ ወደ ስራው የመመለስ መብት የለውም፡፡ ሆኖም የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ መልሶ ሊመርጠው ይችላል፡፡

**4)** የተቆጣጣሪ ቦርድ አባል ሆነው መመረጥ የሚችሉት ባለአክሲዮኖች ብቻ ናቸው፡፡

**5)** የተቆጣጣሪ ቦርዱ ተጠሪነት ለባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ይሆናል፡፡

**6)** የተቆጣጣሪ ቦርድ አባላት የማኅበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል መሆን ወይም አመራር ውስጥ መሳተፍ አይችሉም፡፡

**7)** ተቆጣጣሪ ቦርዱ ከአባላቱ መካከል ሰብሳቢ ይመርጣል፡፡ ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ ከአባላት መካከል ጊዜያዊ ሰብሳቢ ይወከላል፡፡ ሰብሳቢው ጊዜያዊ ሰብሳቢ ለመወከል የማይችልበት ሁኔታ ሲኖር አባላት ከመካከላቸው ጊዜያዊ ሰብሳቢ ይመርጣሉ፡፡ ቦርዱ ሰብሳቢውን በማንኛውም ጊዜ ሊያነሳ ይችላል፡፡

**8)** የተቆጣጣሪ ቦርዱ የስብሰባ ጊዜ በመመስረቻ ጽሁፉ ይወሰናል፡፡

**9)** ተቆጣጣሪ ቦርዱ የራሱን ቃለ ጉባኤዎችና ሌሎች አስፈላጊ ሰነዶችን አደራጅቶ ይይዛል፡፡

**10)** ለተቆጣጣሪ ቦርድ አባላት የሚከፈለው የሥራ ዋጋና የአበል መጠን በጠቅላላ ጉባኤ ይወሰናል፡፡

## አንቀፅ 332 የተቆጣጣሪ ቦርዱ ስልጣንና ተግባር

ተቆጣጣሪ ቦርዱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችንና ሌሎች መረጃዎችን የማስቀረብ እና የመመርመር፤

2) የዳይሬክተሮች ቦርድ ጠቅላላ ጉባኤ ለመጥራት ካልቻለ ወይም ፈቃደኛ ሳይሆን ሲቀር ስብሰባ የመጥራትና የመምራት፤

3) በዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ ላይ የመገኘት እና ያለድምፅ የመሳተፍ እና ሀሳብ የመስጠት፤

4) ማህበሩን የሚጐዱ ተግባራት መፈጸማቸዉን ባወቀ ወይም በጠረጠረ ጊዜ ጉዳዩን የመመርመር ወይም እንዲመረመር የማድረግ፤ እንዳስፈላጊነቱም ክስ እንዲመሰረት አስፈላጊውን እርምጃ የመውሰድ፤

5) የማኅበሩ ዳይሬክተሮችና ሌሎች የአመራር አባላት ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እየተወጡ መሆናቸዉን የመቆጣጠር፣ የማኅበሩን ጥቅም የሚጐዳ ተግባር እየፈፀሙ መሆኑ ሲረጋገጥ ይኸው ተግባር እንዲታረም የመጠየቅ፣ ስራቸውን በአግባቡ የማይወጡትን ከኃላፊነታቸው እንዲነሱ እንደ ሁኔታው ለማኅበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም ለማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ሀሳብ የማቅረብ፤

6) የማኅበሩን የፋይናንስ ጉዳዮች የመቆጣጠርና እንዲመረመሩ የማድረግ፤

7) ለጠቅላላ ጉባኤው ሪፖርት የማቅረብ እና

8) ሌሎች በመመስረቻ ጽሑፍ ወይም በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ የሚሰጡትን ተግባራት የማከናወን፡፡

## <u>አንቀጽ 333 የተቆጣጣሪ ቦርድ አባላትን ስለመተካት</u>

1) በበጀት ዓመቱ ውስጥ የተቆጣጣሪ ቦርድ አባላት የጎደሉ እንደሆነ ጠቅላላ ጉባኤው በጎደሉት ምትክ እስኪሾም ድረስ የቀሩት ተቆጣጣሪዎች ስራውን ያከናውናሉ

2) የተተኪ ተቆጣጣሪዎች የሥራ ዘመን የጎደሉት ተቆጣጣሪዎች የሥራ ዘመን እስከሚያበቃበት ጊዜ ድረስ ይሆናል፡፡

3) ሁሉም የተቆጣጣሪ ቦርድ አባላት ስራቸዉን የተው እንደሆነ ጠቅላላ ጉባኤው አዲስ ተቆጣጣሪዎች እስኪሾም ድረስ ኦዲተሮች የተቆጣጣሪዎችን ስራ ያከናውናሉ፡፡

## <u>አንቀጽ 334 የተቆጣጣሪ ቦርድ አባላት ተጠያቂነት</u>

ተቃራኒ ስምምነት ቢኖርም የተቆጣጣሪ ቦርድ አባላት በዚሕ ሕግ፣ በመመስረቻ ጽሑፍ ወይም በጠቅላላ ጉባኤዎች የተሰጣቸውን ኃላፊነት ባለመወጣት ለሚያደርሱት ጉዳት ለማኅበሩ፣ ለባለአክሲዮኖች ወይም ለሦስተኛ ወገኖች በአንድነትና በተናጠል ኃላፊዎች ናቸው፡፡

## <u>አንቀጽ 335 ይርጋ እና ሌሎች መቃወሚያዎች</u>

1) በዚህ ሕግ ድንጋጌዎች መሰረት በዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ወይም እንደነገሩ ሁኔታ በተቆጣጣሪ ቦርድ አባላት ላይ በማኅበሩ፣ በባለአክሲዮኖች ወይም በገንዘብ ጠያቂዎች የሚቀርብ ክስ ተጎጂው ጉዳቱን እና ለጉዳቱ ኃለፊ የሆነውን ሰው ካወቀበት ቀን ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ድረስ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል፡፡ በማናቸውም ሁኔታ ጉዳት ከደረሰበት ቀን አንስቶ እስከ አስር ዓመት ያልቀረበ ክስ በይርጋ ይታገዳል፡፡

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ በዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም የተቆጣጣሪ ቦርድ አባላት ላይ በሚቀርብ የወንጀል ክስ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**<u>አንቀጽ 336 ተፈጻሚነት ስላላቸው ድንጋጌዎች</u>**

የዚህ ሕግ አንቀጽ 297፣ 298 እና 306 ድንጋጌዎች እንዳግባብነታቸው በተቆጣጣሪ ቦርድ አባላት ላይም ተፈጻሚነት አላቸው፡፡

**<u>ክፍል ሁለት</u>**

**<u>የማኅበሩ ዋና ሥራ አስኪያጅና ፀሐፊ</u>**

**<u>አንቀጽ 337 የማኅበሩ ዋና ሥራ አስኪያጅ</u>**

1) ማኅበሩ በዳይሬክተሮች ቦርድ የሚሾም ዋና ሥራ አስኪያጅ ይኖረዋል፡፡ የዋና ሥራ አስኪያጁ ተጠሪነት ለቦርዱ ይሆናል፡፡
2) ቦርዱ ዋና ሥራ አስኪያጁን ከኃላፊነቱ ሊያነሳው ይችላል፡፡ ሥራ አስኪያጁ ከኃላፊነት የተነሳው ካለበቂ ምክንያት ቢሆንም ወደ ኃላፊነቱ የመመለስ መብት የለውም፡፡ ሆኖም ቦርዱ መልሶ ሊሾመው ይችላል፡፡
3) ዋና ሥራ አስኪያጁ የማኅበሩ ተቀጣሪ ነው፡፡ የዳሬክተሮች ቦርድ አባል ሊሆን ይችላል፡፡ ሆኖም የቦርዱ ሊቀመንበር መሆን አይችልም፡፡

**<u>አንቀጽ 338 የማኅበሩ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር</u>**

1) ዋና ሥራ አስኪያጅ የማኅበሩን ጠቅላላ የዕለተ ዕለት ሥራ ይመራል፡፡ በማኅበሩ መመስረቻ ጽሁፍ ተቃራኒ ድንጋጌ ካልኖረ በስተቀር፤ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረግ ግንኙነት ማኅበሩን ይወክላል፡፡
2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ዋና ሥራ አስኪያጅ የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶችን በተለይም የንግድ ወረቀቶችን፣ የሚተላለፉ የግዴታ ምስክር ወረቀቶችን እና የሸቀጥ ማረጋገጫ ሰነዶችን የመፈረም፤ የማስተላለፍ፤

(ለ) በማኅበሩ የመመስረቻ ጽሁፍ የተሰጡትን ተግባራት የማከናውን፤

(ሐ) በዳይሬክተሮች ቦርድ የሚሰጡትን ተግባራት የማከናወን፤ የቦርዱን ውሳኔዎች የማስፈጸም፤

(መ) የማኅበሩን የሥራ ዕቅድ እና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርድ የማቅረብ፤ ሲጸድቅ ተግባራዊ የማድረግ እና

(ሠ) ለማኅበሩ አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞችን የመቅጠር፣ የማስተዳደር እና የማሰናበት፡፡

**<u>አንቀጽ 339 የሥራ አስኪያጁን ሥልጣን የመገደብ ውጤት</u>**

1) የሥራ አስኪያጁን ሥልጣን የሚገድቡ የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔዎች ወይም ሌሎች የውል ቃሎች በንግድ መዝገብ ውስጥ እስካልገቡ ድረስ ውጤት የሚኖራቸው በማኅበሩ እና በሥራ አስኪያጁ መካከል ብቻ ይሆናል፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ማኅበሩ በሥራ አስኪያጁ ስራ የሚገደደው በበቅን ልቦና ከሥራ አስኪያጁ ጋር ውል የገቡ ሦስተኛ ወገኖችን ጥቅም ለመጠበቅ ሲባል ብቻ ነው፡፡

**<u>አንቀፅ 340 የማኅበሩ ፀኃፊ</u>**

1) የአክሲዮን ማኅበር ፀሐፊ ሊኖረው ይገባል፡፡ የፀሐፊው ቅጥርና ስንብት በሥራ አስኪጁ አቅራቢነት በቦርዱ የሚጸድቅ ይሆናል፡፡
2) የማኅበሩ ፀኃፊ ተጠሪነት ለሥራ አስኪያጁ ይሆናል፡፡

**<u>አንቀጽ 341 የማኅበሩ ፀሐፊ ስልጣንና ተግባራት</u>**

የማኅበሩ ፀኃፊ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የማኅበሩን መረጃዎችና መዛግብት የማደራጀትና የመያዝ፤
2) ለሚመለከተው አካል ሪፖርቶችንና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች በወቅቱ የመስጠት፤
3) ለባለአክሲዮኖችና ለሶስተኛ ወገኖች መረጃ የመስጠት፤
4) የባአክሲዮኖችን እና የቦርዱ አባላትን ስብሰባዎች የማዘጋጀት፤
5) ቃለ ጉባኤዎችን ማዘጋጀትና አደራጅቶ የመያዝ፤ እና
6) በሥራ አስኪያጁ እና በማኅበሩ የመመስረቻ ጽሑፍ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት የማከናወን፡፡

**<u>አንቀጽ 342 የማኅበሩ ፀሐፊ ተጠያቂነት</u>**

ተቃራኒ ስምምነት ቢኖርም፤ የማኅበሩ ፀኃፊ በዚህ ሕግ ወይም በመመስረቻ ጽሑፍ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመተላለፍ በማኅበሩ፣ በባለአክሲዮኖች ወይም በሦስተኛ ወገኖች ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት ኃላፊ ነው፡፡

**<u>ክፍል ሶስት</u>**

**<u>ስለኦዲት እና ስልጣን ባለው የመንግስት አካል ስለሚደረግ ምርመራ</u>**

**<u>አንቀጽ 343 ኦዲተሮችን ስለ መሾም</u>**

1) ማንኛዉም የአክሲዮን ማኅበር አንድ ወይም ከአንድ በላይ ነጻና ገለልተኛ የሆኑ የውጭ ኦዲተሮች እና ተለዋጭ ኦዲተሮች ሊኖሩት ይገባል፡፡ ኦዲተሮችን እና ተለዋጭ ኦዲተሮችን የሚሾመው የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ ነው፡፡
2) ከማኅበሩ ዋና ገንዘብ ውስጥ ቢያንስ ሃያ በሙቶ ድርሻ ያለው ባለአክሲዮን ወይም ባለአክሲዮኖች ራሳቸዉ የመረጡትን የውጭ ኦዲተር መሾም ይችላሉ፡፡
3) በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ኦዲተር መሆን ይችላል፡፡
4) የመጀመሪያዎቹ ኦዲተሮች በፈራሚዎች ጉባኤ፤ ቀጣዮቹ ደግሞ በጠቅላላ ጉባኤ ይመረጣሉ፡፡

**አንቀጽ 344 ስለ ኦዲተሮች የስራ ዘመን**

ኦዲተሮች በሥራ ላይ የሚቆዩት፡-

1) በፈራሚዎች ጉባኤ የተመረጡት የመጀመሪያው ጠቅላላ ጉባኤ እስከሚደረግ ድረስ፤

2) በጠቅላላ ጉባኤ የተመረጡት የሶስተኛው በጀት ዓመት ሂሳብ እስከሚጠቃለልበት ጊዜ ድረስ ነው፡፡

**አንቀጽ 345 በኦዲተርነት ለመሾም ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች**

1) የአክሲዮን ማኅበር ኦዲተር ለመሆን የሚችለው ቀጥሎ የተመለከቱትን መስፈርቶች የሚያሟላ ሰው ነው፡-

(ሀ) ከሚመለከተው አካል የሙያ ፈቃድ የተሰጠው፤

(ለ) መልካ ስነምግባር ያለው፤

(ሐ) የማህበሩ ባለአክሲዮን ወይም ሠራተኛ ያልሆነ፤

(መ) በዚህ ሕግ አንቀጽ 306 ንዑስ አንቀፅ 6 በተመለከተው መሰረት ለማኅበሩ ቅርበት ያለው ሰው ያልሆነ፤

(ሠ) ሌሎች በሕግ ወይም በመመስረቻ ጽሑፍ የተቀመጡ መስፈርቶችን የሚያሟላ፡፡

2) የማታለል ድርጊት ካልተፈፀመ በስተቀር፤ በኦዲተር የቀረበን ሪፖርት ጠቅላላ ጉባኤው ካፀደቀው በኋላ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ተጥሰዋል በሚል ምክንያት ብቻ የፀደቀው ሪፖርት ውድቅ አይሆንም፡፡

**አንቀጽ 346 ኦዲተርን ስለመሻር**

ጠቅላላ ጉባኤው በማንኛዉም ጊዜ ኦዲተሮችን መሻር ይችላል፡፡ ሆኖም ያለበቂ ምክንያት የተሻረ ኦዲተር ከማኅበሩ የጉዳት ካሣ መጠየቅ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 347 የኦዲተሮች የሥራ ዋጋ**

የኦዲተሮች የሥራ ዋጋ ክፍያ የሚወሰነው በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ነው፡፡

**አንቀጽ 348 የኦዲተሮች ኃላፊነት**

በሌሎች የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች እንዲሁም አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የኦዲተሮች ኃላፊነቶች የሚከተሉትን ያካትታል፡-

1) ተቀባይነት ያላቸውን የሒሳብ አያያዝ መርሆዎች መሰረት በማድረግ የመስራት፤

2) ትክክለኛ መረጃ የመስጠት፤

3) የማኅበሩን ባለአክሲዮኖች በእኩል ዓይን የማየት፤

4) የሙያ ሥራ ምስጢር የመጠበቅ፤

5) በየዓመቱ የማኅበሩን የንብረት ዝርዝር መዝገብ፣ የሂሳብ ሚዛን እንዲሁም የትርፍና ኪሳራ መግለጫ፣ የሂሳብ መዛግብትና ሌሎች የፋይናንስ ሰነዶችን ትክክለኛነት የመመርመር እና የማረጋገጥ፤

6) በዳይሬክተሮች ቦርድ ለማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ የሚቀርብ ሪፖርት የማኅበሩን አጠቃላይ ሁኔታ በትክክል የሚያሳይ መሆኑን የማረጋገጥ፤

7) በማኅበሩ የመመስረቻ ጽሑፍ ወይም በጠቅላላ ጉባኤው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን የማከናወን፡፡

## አንቀጽ 349 ለጠቅላላ ጉባኤው የሚቀርብ ሪፖርት

1) ኦዲተሮች በዳይሬክተሮች ቦርድ ለማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ በቀረበ ሪፖርት ላይ ያላቸውን አስተያየት የሚገልጽ ሪፖርት በጽሁፍ ለጠቅላላ ጉባኤ ማቅረብ አለባቸው፡፡ የሚያቀርቡት ሪፖርት ኦዲተሮቹ ሥራቸውን እንዴት እንዳከናወኑ ማሳየት ይኖርበታል፡፡

2) ኦዲተሮች በዳይሬክተሮች ቦርድ የቀረበውን የሂሳብ ሪፖርት ጠቅላላ ጉባዔው እንዲያፀድቀው ወይም ውድቅ እንዲያደርገው ሀሳብ ማቅረብ አለባቸው፡፡

3) ኦዲተሮች ስለትርፍ አከፋፈል ዳይሬክተሮቹ ባቀረቡት ሀሳብ ላይ ለጠቅላላ ጉባዔው አስተያየታቸውን መስጠት አለባቸው፡፡

4) ጠቅላላ ጉባኤው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው ሪፖርት ካልቀረበለት በስተቀር በሂሳብ ሚዛን መግለጫው ላይ መነጋገር የለበትም፡፡

## አንቀጽ 350 ተገቢ ያልሆነ ተግባር መፈጸሙን የማስታወቅ ግዴታ

1) ኦዲተሮች ስራቸዉን በሚያከናውኑበት ጊዜ ተገቢ ያልሆነ አሰራር ወይም በሕግ ወይም በመመስረቻ ጽሑፍ የተመለከተውን በመጣስ የተፈፀመ ድርጊት መኖሩን እንዳወቁ ማኅበሩ ተቆጣጣሪ ቦርድ ካለው ለቦርዱ ከሌለው ደግሞ ለዳይሬክተሮች ቦርድ እና ጉዳዩ ከበድ ያለ በሆነ ጊዜ ለጠቅላላ ጉባኤው ማስታወቅ አለባቸው፡፡

2) ኦዲተሮች ስራቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ ወንጀል መፈጸሙን ያወቁ እንደሆነ አግባብ ላለው የመንግስት አካል ማስታወቅ አለባቸው፡፡

## አንቀጽ 351 የማኅበሩን ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ስለመጥራት

1) ሕግ ወይም የማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ በሚጠይቀው መሠረት የዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም ተቆጣጣሪ ቦርድ ጠቅላላው ጉባኤ እንዲሰበሰብ ጥሪ ሳያደርጉ የቀሩ እንደሆነ፣ ጥሪውን ኦዲተሮቹ ማድረግ አለባቸው፡፡

2) ከማኅበሩ ዋና ገንዘብ ውስጥ ቢያንስ አስር በሙቶ ድርሻ ባላቸው ባለአክሲዮኖች ጥያቄ የቀረበላቸው እንደሆነ፤ ኦዲተሮች ጠቅላላ ጉባኤ እንዲሰበሰብ ጥሪ ማድረግ አለባቸዉ፡፡

3) ኦዲተሮች ከአንድ በላይ ከሆኑ በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ በተመለከተው መሠረት በጋራ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲሰበሰብ ጥሪ ማድረግ ይችላሉ፡፡ አስፈላጊ መስሎ ሲታያቸው ስብሰባው ከማኅበሩ ዋና መስሪያ ቤት ወይም በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ ከተጠቀሰው ቦታ ውጭ እንዲደረግ መወሰን ይችላሉ፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ድንጋጌ መሠረት ኦዲተሮች ስብሰባ የጠሩ እንደሆነ የዕለቱን ስብሰባ አጀንዳ ያዘጋጃሉ፤ ስብሰባውን መጥራት ስለአስፈለገበት ምክንያትም ለጠቅላላ ጉባኤው በጽሑፍ ሪፖርት ያቀርባሉ፤ ከኦዲተሮቹ አንዱ ጉባኤውን በሰብሳቢነት ይመራል፡፡

5) ጠቅላላ ጉባኤውን በመጥራት ወይም ባለመጥራት ላይ ኦዲተሮቹ ያልተስማሙ እንደሆነ፣ ከኦዲተሮቹ አንዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (**3)** እና (**4)** የተመለከተውን ስልጣን ተግባራዊ ለማድረግ የማኅበሩ ዋና መስሪያ ቤት በሚገኝበት ቦታ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማመልከት ይችላል፡፡

6) ማኅበሩ በዚህ አንቀጽ መሠረት ስራዎችን ለማከናወን የተደረገውን አስፈላጊ ወጪ ሁሉ መሸፈን አለበት፡፡

## አንቀጽ 352 ስለኦዲተሮች ልጣን

1) ኦዲተሮች አስፈላጊ መስሎ በታያቸዉ በማንኛዉም ጊዜ ምርምራ ወይም ቁጥጥር ለማድረግ ወይም ማንኛውም መረጃ፣ ውል፣ መዝገብ፣ የሂሳብ ሰነድ፣ ቃለ ጉባኤ ወይም ሌላ ሰነድ እንዲቀርብላቸዉ ለመጠየቅ ይችላሉ፡፡ ጥያቄ የቀረበለት ሰው የተጠየቀውን መረጃ መስጠት አለበት፡፡

2) በየዓመቱ በሚደረገውም ሆነ በሌላ ማናቸውም ጊዜ በሚጠራ የባለአክሲዮኖች ጉባኤ ላይ ኦዲተሮች መገኘት አለባቸዉ፡፡

## አንቀጽ 353 የእናት የንግድ ማኅበር ሂሳብን ስለመመርመር

በዚህ ሕግ ወይም በሌላ ማናቸውም ሕግ መሠረት የአንድ የእናት የንግድ ማኅበር ሒሳብ ሲመረመር የተቀጥላ ማኅበሩ የተጠቃለሉ ሒሳቦች መታየት ያለባቸው እንደሆነ ኦዲተሮች በተቀጥላው ማኅበር ሰነዶች ላይ የሂሳብ ምርመራ ማድረግ አለባቸው፡፡

## አንቀጽ 354 የኦዲተሮች ተጠያቂነት

1) ኦዲተሮች ስራቸዉን በሚያከናውኑበት ጊዜ በማኅበሩ፣ በባለአክሲዮኖችና በሶስተኛ ወገኖች ላይ ለሚፈጽሙት ጥፋት በፍትሐብሄር ሕግ መሰረት ኃላፊዎች ይሆናሉ፡፡

2) ማንኛውም ኦዲተር ሆነ ብሎ የንግድ ማኅበሩን አቋም በሚመለከት ትክክለኛ ያልሆነ ሪፖርት ያቀረበ ወይም ያረጋገጠ ወይም ወንጀል መፈጸሙን እያወቀ ለሚመለከተው አካል ያላሳወቀ ወይም የሙያ ሥራ ምስጢር ያወጣ እንደሆነ አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

3) ማንኛውም ኦዲተር ስራ ስለሚያቋርጥበት ሁኔታ በሕግ ወይም በውል የተመለከተውን በመተላለፍ ስራውን በማቋረጡ ምክንያት በማኅበሩ፣ በባለአክሲዮኖችና በሶስተኛ ወገኖች ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 355 ባለአክሲዮኖቹ ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት ስለ ኩባንያው ሁኔታ የሚደረግ ምርመራ

1) ከማኅበሩ ዋና ገንዘብ (ካፒታል) ቢያንስ አስር በመቶ ድርሻ ባላቸው ባለአክስሲዮኖች ጥያቄ የቀረበለት እንደሆነ የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም አግባብ ያለው ሌላ የመንግስት መስሪያ ቤት የማኅበሩ ስራ አመራር አነስተኛ የአክሲዮን ድርሻ ያላቸውን ማኅበርተኞች ወይም ማኅበሩን በሚጎዳ አንኳኋን መከናወኑን እና አለመከናወኑን መርምረው ሪፖርት የሚያቀርቡ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ኢንስፔክተሮች መሾም አለበት፡፡

2) አመልካቹም ማመልከቻ ለቀረበለት አካል አስፈልጊ ናቸው የሚላቸውን ሰነዶች እና ሌላ ማስረጃ መጠቆም አለበት፡፡

3) የምርመራውን ወጪ የሚሸፍኑት ጥያቄ አቅራቢዎቹ ናቸው፡፡ ሆኖም የምርመራው ውጤት የደረሰውን ጥቆማ ትክክለኛነት የሚያስረዳ ሆኖ ከተገኘ ማሕበሩ ለጥያቄ አቅራቢዎቹ ለምርመራው ያወጡትን ገንዘብ መመለስ ይኖርበታል፡፡

__አንቀጽ 356 የግዴታ ምርመራ__

የማሕኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ወይም ፍርድ ቤት ማኅበሩ ላይ ምርመራ እንዲደረግ የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴርን ወይም በሕግ ስልጣን የተሰጠውን ሌላ የመንግስት አካልን መጠየቅ ይችላሉ፡፡ ጥያቄው የቀረበለት አግባብ ያለው መስሪያ ቤት ምርመራ የሚያከናውኑ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ኢንስፔክተሮችን መሾም አለበት፡ ፡

__አንቀጽ 357 አግባብ ያለው የመንግስት አካል በራሱ አነሳሽነት ስለሚያደርገው ምርመራ__

የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም በሕግ ሥልጣን የተሰጠው ሌላ የመንግስት አካል፡-

1) በማኅበሩ ገንዘብ ጠያቂዎች ላይ የማታለል ድርጊት ስለመፈፀሙ ወይም ሊፈፀም የሚችል ስለመሆኑ፤
2) የተወሰኑ ባለአክሲዮኖችን መብት የሚጎዳ ድርጊት ስለመፈፀሙ፤
3) ሕገወጥ የሆነ ወይም የማታለል ድርጊት ያለበት አሰራር በማኅበሩ ውስጥ ስለመኖሩ ወይም
4) የወንጀል ድርጊት ስለመፈፀሙ፤

የሚያሳይ በቂ መረጃ መኖሩን ካመነ ምርመራ እንዲካሄድ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ኢንስፔክተሮችን መሾም ይችላል፡፡

__አንቀጽ 358 በእናትና በተቀጥላ ማኅበራት ጉዳዮች ላይ ኢንስፔክተሮች ስላላቸው ስልጣን__

በዚህ ህግ አንቀጽ **355** ፣ **356** ወይም **357** መሰረት ምርመራ እንዲያካሄዱ የተመረጡት ኢንስፔክተሮች እናት ወይም ተቀጥላ ማኅበሩ ካልተመረመረ የማኅበሩን የስራ አካሄድ በተሟላ ሁኔታ ለመመርመር የማይቻል መሆኑን ካመኑና ይህንኑ ለሾማቸው የመንግስት አካል ሪፖርት ካደረጉ ይኸው አካል ምርመራው እናት ወይም ተቀጥላ ማኅበሩን እንዲጨምር ትዕዛዝ መስጠት ይችላል፡፡

__አንቀጽ 359 ምርመራ የሚደረግበት ማኅበር ስላለበት ግዴታ__

1) ምርመራ እንዲደረግበት ትዕዛዝ የደረሰው ማኅበር የዳይሬክተሮች ቦርድ፣ ካለ የተቆጣጣሪ ቦርድ፣ ሥራ አስኪያጆች፣ የማኅበሩ ፀሐፊ ወይም ሌሎች የሥራ ኃላፊዎች እና እንደራሴዎች ኢንስፔክተሮች የሚጠይቋቸዉን መዛግብትና ሰነዶች ማቅረብና ለሚጠይቋቸዉ ጥያቄዎች የተሟላ መልስ መስጠት አለባቸዉ፡፡

**2)** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሱት የማኅበሩ ኃላፊዎች ኢንስፔክተሮች ስራቸውን በአግባቡ እንዳያከናውኑ መሰናክል የሆኑ እንደሆነ ኢንስፔክተሮች ለሾማቸው አካል ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡ ሪፖርቱ የቀረበለት አካል አግባብነት ባለው ሕግ መሰረት የወንጀል ክስ እንዲቀርብ ጉዳዩን ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ አለበት፡፡

**<u>አንቀጽ 360 የኢንስፔክተሮች ሪፖርት</u>**

**1)** በማኅበሩ ላይ ምርመራው እንዲካሄድ ትዕዛዝ የሰጠው አካል ኢንስፔክተሮቹ ያቀረቡትን ሪፖርት አንድ ቅጂ፡-

(ሀ) ለተመረመረው ማኅበር፤

(ለ) እንዲመረመር ላመለከቱት ባለአክሲዮኖች፤ ወይም

(ሐ) ምርመራውን ላዘዘው ፍርድ ቤት፤

ይልካል፡፡

**2)** በማኅበሩ ላይ ምርመራ እንዲካሄድ ትዕዛዝ የሰጠው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (**1**) በቀረበው ሪፖርት ተገቢ ያልሆኑ ተግባራት መፈጸማቸውን ካረጋገጠ አስፈልጊውን የእርምት እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡

**<u>አንቀጽ 361 ስለ ባለአክሲዮኖች የትውስት ስም</u>**

**1)** ሥልጣን ያለው የመንግስት አካል በአክሲዮን መዝገቡ ላይ የተጻፉ ባለአክሲዮኖች ማኅበሩን በእርግጥ ለሚቆጣጠሩት እና ከውስጡ የገንዘብ ጥቅም ላላቸው ሰዎች ስማቸውን ያዋሱ ስለለመሆኑ በቂ ምክንያት ያለው እንደሆነ፤ የአክሲዮኖቹ ትክክለኛ ባለሀብቶች እነማን እንደሆኑ ለማወቅ ምርመራ የሚያደርጉ ኢንስፔክተሮችን መሾም ይችላል፡፡

**2)** ሥልጣን ያለው የመንግስት አካል ቢያንስ ከማኅበሩ ዋና ገንዘብ አስር በመቶ ድርሻ ያላቸው ባለአክሲዮኖች ጥያቄ ካቀረቡ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ምርመራ እንዲደረግ ማዘዝ ይችላል፡፡

**<u>ምዕራፍ አምስት</u>**

**<u>ስለማኅበሩ ጉባኤዎች</u>**

**<u>ክፍል አንድ</u>**

**<u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>**

**<u>አንቀጽ 362 ጠቅላላ ደንብ</u>**

**1)** የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ሁሉም ባለአክሲዮኖች የሚሳተፉበት የማኅበሩ ከፍተኛ ውሳኔ ሰጭ አካል ነው፡፡

2) በዓመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ባለአክሲዮኖች በአካል በመገኘት ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ወይም ሁሉም ባለአክሲዮኖች የተስማሙ እንደሆነ ስብሰባ ማድረግ ሳያስፈልግ ለውሳኔ በቀረበ ጉዳይ ላይ ሀሳባቸውን በጽሑፍ ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ በመግለጽ ውሳኔ ማስተላለፍ ይችላሉ፡፡

**አንቀጽ 363 ከባለአክሲዮንነት የሚመነጩ መብቶች**

1) በአንቀጽ 391 ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ የተደነገገው ቢኖርም አንድ ባለአክሲዮን በራሱ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር በባለአክሲዮንነቱ ያገኛቸው መብቶች ቀሪ አይሆኑም፡፡
2) ከባለአክሲዮንነት የሚመነጩ መብቶች የሚባሉት በሕግ ወይም በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ መሠረት በጠቅላላ ጉባኤው ወይም በዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ ላይ ጥገኛ ያልሆኑ የማኅበሩ አባል የመሆን፣ በስብሰባ የመካፈል፣ ድምጽ የመስጠት፣ የማኅበሩን ውሳኔ የመቃወም፣ ትርፍና ማኅበሩ ሲፈርስ በመጨረሻ በሚደረገው የሂሳብ ማጣራት ጊዜ ከማኅበሩ ሃብት ድርሻ የመካፈልና የመሳሰሉት መብቶች ናቸው፡፡

**አንቀጽ 364 አናሳ ባለአክሲዮኖችን ከጉዳት ስለመጠበቅ**

ልዩ ጥቅም የሚያሰጡ የአክሲዮን መደቦችን ስለመፍጠር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጠቅላላ ጉባዔ ለተወሰኑ ማኅበርተኞች ያልተገባ ጥቅም የማስገኘት ውጤት ሊኖረው እንደሚችል ግልጽ የሆነ ውሳኔ ማስተላለፍ የለበትም፡፡

**አንቀጽ 365 የጉባኤዎች ዓይነት**

1) የባለአክሲዮኖች ጉባኤዎች ጠቅላላ ወይም ልዩ ለመሆን ይችላሉ፡፡
2) ጠቅላላ ጉባኤዎች መደበኛ ወይም አስቸኳይ ይሆናሉ፡፡ እነዚህም ልዩ ልዩ መደብ ያላቸው ባለአክሲዮኖች በሙሉ ሊሳተፉባቸው የሚችሉ ናቸው፡፡
3) በልዩ ጉባኤ የሚሳተፉት በሚመለከተው መደብ ውስጥ የሚወድቁ ባለአክሲዮኖች ብቻ ናቸው፡፡

**አንቀጽ 366 የማኅበሩ ጉባኤ ጥሪ**

1) የጠቅላላ ጉባኤ ጥሪ የሚያደርጉት እንደነገሩ ሁኔታ የዳይሬክተሮች ቦርድ፣ የተቋቋመ እንደሆነ ተቆጣጣሪ ቦርድ፣ ኦዲተሮች፣ ሒሳብ አጣሪዎች ወይም ፍርድ ቤት ናቸው፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር የተመለከተው ቢኖርም የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም አግባብ ያለው ሌላ የመንግስት አካል ጉዳዩ አንገብጋቢ ሆኖ ሲያገኘው እና በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ስብሰባ መጥራት የማይቻል ወይም ረጅም ጊዜ የሚወስድ ከሆነ በጉዳዩ ያገባኛል በሚል ማንኛውም ሰው ጥያቄ ወይም በራሱ ተነሳሽነት ጉባኤ ሊጠራ ይችላል፡፡ ሆኖም ጉባዔ እንዲጠራ ጥያቄ የቀረበው የማኅበሩን ዋና ገንዘብ አስር በመቶ ወይም ከዛ በላይ በሚወክሉ ባለአክሲዮኖች ከሆነ የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም አግባብ ያለው ሌላ የመንግስት አካል ጉባዔ የመጥራት ግዴታ አለበት፡፡

3) ከማኅበሩ ዋና ገንዘብ ቢያንስ አምስት በመቶ ድርሻ ያላቸው ባለአክሲዮኖች የማኅበሩ ዋና መስሪያ ቤት በሚገኝበት ቦታ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ጥያቄ ሲያቀርቡና ፍርድ ቤቱ ጥያቄው ተገቢ ነው ብሎ ሲያምን ጠቅላላ ጉባኤ እንዲሰበሰብ ጥሪ የሚያደርግና አጀንዳ የሚያዘጋጅ ተወካይ ሊሰይም ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 367 የጉባኤው አጠራር ሁኔታ</u>**

1) በማኅበሩ የመመመስረቻ ጽሑፍ በተጠቀሰው መሰረት ሆኖ ለጉባኤዎች ሁሉ የሚደረጉ ጥሪዎች አገር አቀፍ ስርጭት ባለው ጋዜጣ መደረግ አለባቸው፡፡
2) ሁሉም አክሲዮኖች በባለአክሲዮኖች ስም ተመዝግበው በሚገኙባቸው ማኅበሮች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከቱት ማስታወቂያዎች ፋንታ ጥሪው በማኅበሩ ወጪ ለእያንዳንዱ ባለአክሲዮን በሚላክ የተመዘገበ ደብዳቤ፣ ማህበርተኛው ለዚሁ ዓላማ ለማህበሩ በሰጠው ኢሜይል ወይም ሌላ አስተማማኝ የኤለክትሮኒክ ዘዴ ሊደረግ ይችላል፡፡
3) ማኅበሩ ላምጪው በሚል የወጡ አክሲዮኖች ቢኖሩትም በስም የተመዘገበ አክሲዮን ያለው ባለአክሲዮን የስብሰባ ጥሪዎች በተመዘገበ ደብዳቤ ወይም በኢሜይል ወይም በሌላ አስተማማኝ የኤሌክትሮኒክ ዘዴ እንዲደርሱት ለኩባንያው በጽሁፍ ጥያቄ ካቀረበ የስብሰባ ጥሪዎች በራሱ ወጭ በጠየቀበት አኳኋን ሊላኩለት ይችላሉ፡፡
4) ለሥራ አካሄድና ለባለአክሲዮኖች አመቺ ሆኖ ሲገኝ ለጉባኤዎች የሚደረጉ ጥሪዎች ከዚህ በላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች በተለየ መንገድ እንዲደረጉ በማኅበሩ መመስረቻ ጽሁፍ ላይ መደንገግ ይቻላል፡፡

**<u>አንቀጽ 368 ምልዓተ ጉባኤ ባለመሟላቱ በድጋሜ የሚደረግ የመደበኛ ጉባኤ ጥሪ</u>**

ምልዐተ ጉባኤ ባለመሟላቱ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤው መሰብሰብ ሳይችል የቀረ እንደሆነ ለሁለተኛ ጊዜ ጠቅላላ ጉባኤው እንዲሰበሰብ የሚደረገው ጥሪ የሚደረገው የመጀመሪያው ጉባኤ በተጠራበት አኳኋን እና የጊዜ ገደብ ነው፡፡

**<u>አንቀጽ 369 ምልዓተ ጉባኤ ባለመሟላቱ በድጋሚ የሚደረግ የአስቸኳይ ወይም የልዩ ጉባኤ ጥሪ</u>**

አስቸኳይ ወይም ልዩ ጉባኤ አስፈላጊው ምልዓተ ጉባኤ ባለመሟላቱ ምክንያት ሳይሰበሰብ የቀረ እንደሆነ ሁለተኛ ስብሰባ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ሦስተኛ ስብሰባ በአንድ ሳምንት ልዩነት ውስጥ በአንቀጽ 366 እና 367 በተመለከተው መሠረት መጠራት አለበት፡፡

**<u>አንቀጽ 370 የጉባኤው የማስታወቂያ ጊዜ</u>**

ጠቅላላ ወይም ልዩ ጉባኤ እንዲሰበሰብ የሚደረገው የመጀመሪያው ጥሪ ስብሰባው ከሚደረግበት ቀን ሀያ አራት ቀናት በፊት መደረግ አለበት፡፡

**<u>አንቀጽ 371 በጉባኤው ጥሪ ማስታወቂያ ላይ የሚገለጹ ጉዳዮች፡</u>**

1) የጉባኤው የጥሪ ማስታወቂያ የማኅበሩን ስምና ዓይነት፤የማኅበሩን ዋና ገንዘብ፣የምዝገባ ቁጥር፤ ዋና መስሪያ ቤቱ የሚገኝበትን ቦታ፤ ለአምጪው በሚል የተጻፈባቸው አክሲዮኖች ካሉ የሚቀመጡበትን ቦታና ጊዜ፤ የስብሰባውን ጊዜና ቦታ እንዲሁም ለስብሰባው የሚቀርቡ አጀንዳዎችን መያዝ አለበት፡፡
2) ምልዓተ ጉባኤ ባለመሟላቱ ምክንያት በድጋሚ የሚደረግ የስብሰባ ጥሪ ማስታወቂያ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) ስር ከተመለከቱት በተጨማሪ ጉባኤው ሳይካሄድ የቀረበትን ቀን መጥቀስ አለበት፡፡

**አንቀጽ 372 አጀንዳ**

1) በዚህ ሕግ አንቀጽ 366 ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት ፍርድ ቤት ወይም የሚመለከተው የመንግስት አካል ጉባዔ ስለሚጠራበት ሁኔታ የየተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የጉባኤውን አጀንዳ የሚያዘጋጀው ጥሪ አድራጊው ነው፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ቢኖርም ከማህበሩ ዋና ገንዘብ አምስት በመቶ ድርሻ ያላቸው ባለአክሲዮኖች ተጨማሪ አጀንዳ እንዲያዝላቸው የማድረግ መብት አላቸው፡፡ ጥያቄያቸውን በተቻለ መጠን የስብሰባ ጥሪ ከመደረጉ በፊት ካልሆነም በአንቀጽ 370 መሠረት የስብሰባ ጥሪ በተደረገ በሶስት ቀናት ውስጥ ስብሰባውን ለጠራው አካል በጽሑፍ ማቅረብ አለባቸው፡፡
3) በሕግ ወይም በማኅበሩ የመመስረቻ ጽሁፍ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በስተቀር በአጀንዳው ውስጥ ያልተካተተ ማንኛውም ጉዳይ በጉባኤው ውይይት ሊደረግበት አይችልም፡፡ በአጀንዳነት ባይያዝም ጉባኤው ዳይሬክተሮችን ለመሾምና ለመሻር ይችላል፡፡
4) ምልዓተ ጉባዔ ባለመሟላቱ በዚህ ሕግ አንቀጽ 368 እና 369 በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት በተከታታይ በሚደረጉ የስብሰባ ጥሪዎች መነሻነት የተሰበሰቡ ጉባኤዎች ለመወያየት የሚችሉት ለመጀመሪያው ጉባኤ በተያዘው አጀንዳ ላይ ብቻ ነው፡፡

**አንቀጽ 373 የባለአክሲዮኖች ወኪል**

1) አንድ ባለአክሲዮን በጉባኤው ስብሰባ ላይ መሳተፍ ካልቻለ በወኪል አማካኝነት መሳተፍና ድምጽ መስጠት ይችላል፡፡ ባለአክሲዮኑ በጉባኤው ላይ ወኪል እንዲገኝ ካደረገ ራሱ ለመሳተፍና ድምጽ ለመስጠት አይችልም፡፡
2) የአንድ አክሲዮን ወይም የአክሲዮኖች የጋራ ባለሃብቶች፤ የአክሲዮኖች የአላባ ጥቅም ሰጭና መያዣ የተቀበለ ገንዘብ ጠያቂ ወኪል በሚመለከት የዚህ ሕግ አንቀጽ 271 እና 272 ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 374 ውሳኔ ለማሳለፍ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች**

1) ማንኛውም ጉባኤ ውሳኔ ማሳለፍ የሚችለው ምልዓተ ጉባኤው የተሟላ ሲሆንና በጉባኤው ከተገኙት ባለአክሲዮኖች የአብላጫውን የድምጽ ድጋፍ ሲያገኝ ነው፡፡

2) ለሚተላለፉት ውሳኔዎች መሟላት ያለበት ምልዓተ ጉባኤ የሚሰላው የማኅበሩን ዋና ገንዘብ (ካፒታል) ካቋቋሙት አክሲዮኖች አንጻር ሆኖ ለእያንዳንዱ የጉባኤ ዓይነት በዚህ ሕግ በተወሰነው መሠረት ነው፡፡ በሚካሄዱ ጉባኤዎች ሁሉ አስፈላጊው ምልዓተ ጉባኤ የሚታሰበው በሕግ መሠረት ድምጽ የመስጠት መብት የሌላቸው አክሲዮኖች ከተቀነሱ በኋላ ቀሪዎቹ አክሲዮኖች በማኅበሩ ዋና ገንዘብ ውስጥ ባላቸው ድርሻ/መዋጮ መሠረት ነው፡፡

3) የባለአክሲዮኖች ጉባዔ ለማድረግ የሚያስፈልገውን ምልዓተ ጉባኤና ውሳኔ ለማሳለፍ የሚያስፈልገውን የድምጽ ብልጫ የሚመለከቱትን የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች በማኅበሩ መመስረቻ ጽሁፍ መለወጥ አይቻልም፡፡

**<u>አንቀጽ 375 ማኅበሩ መልሶ የገዛቸው አክሲዮኖች ድምጽ የመስጠት መብት የማያስገኙ ስለመሆኑ</u>**

ማኅበሩ በዚህ ሕግ አንቀጽ **275** ድንጋጌ መሠረት መልሶ በገዛቸው አክሲዮኖች ድምጽ መስጠት አይችልም፡፡

**<u>አንቀጽ 376 የአክሲዮኖች መመዝገቢያ ጊዜ</u>**

ስም የተጻፈባቸው አክሲዮኖች ባለሀብቶች በማኅበሩ መዝገብ የሚጻፉበትና ለአምጭው ተብሎ የተጻፈባቸውን አክሲዮኖች የያዙ ባለአክሲዮኖች በጉባኤው ላይ ለመሳተፍ እንዲችሉ አክሲዮኖቹ በማኅበሩ እንዲቀመጡ የሚደረግበት ጊዜ በመመስረቻ ጽሑፍ ላይ ሊወሰን ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 377 የውክልና ሥልጣን</u>**

የውክልና ሥልጣን ቅጽ ይዘት፣ ውክልናው የሚቀመጥበት ቦታና ጊዜ የሚወሰነው በዳይሬክተሮች ቦርድ ነው፡፡ ሆኖም የጊዜ ገደቡ ስብሰባው ከሚጀመርበት ከሦስት ቀናት በፊት መጠናቀቅ አይችልም፡፡

**<u>አንቀጽ 378 የጉባኤው ተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ</u>**

1) በእያንዳንዱ ጉባኤ ላይ ባለአክሲዮኖች በጉባኤው ላይ መገኘታቸውን የሚያስረዳ የተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ መኖር አለበት፡፡ ሰነዱም በስብሰባው የተገኙትን ወይም ወኪል የላኩትን ባለአክሲዮኖች ስምና አድራሻቸው፣ እያንዳንዱ ባለአክሲዮን ያለውን የአክሲዮን መጠንና የሚሰጠውን የድምጽ ቁጥር የሚያሳይ ዝርዝር መያዝ አለበት፡፡

2) የተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ በስብሰባው መጀመሪያ ላይ በጉባኤው የተገኙ ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎች የፈረሙበት ስለመሆኑ በማኅበሩ ፀሐፊ መረጋገጥ አለበት፡፡

**<u>አንቀጽ 379 የጉባኤው ሰብሳቢ</u>**

1) የማኅበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ የጉባኤው ሰብሳቢ ይሆናል፡፡ ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ሰብሳቢ፣ምክትል ሰብሳቢ በማይኖርበት ጊዜ ከዳይሬክተሮች መካከል በሹመት ቀደምትነት ያለው፣ ቀደምትነት ያለው በማይኖርበት ጊዜ ደግሞ ጠቅላላ ጉባኤው የሚመርጠው ሰው ሰብሳቢ ይሆናል፡፡

**2)** ጉባዔው የተጠራው በማኅበሩ ተቆጣጣሪ ቦርድ፣ በኦዲተሮች፣ በፍርድ ቤት በተሾመ ሰው፣ በሕግ በተፈቀደለት ሌላ የመንግስት ባለስልጣን ወይም በመጨረሻው ሒሳብ አጣሪ የሆነ እንደሆነ የጉባኤው ሰብሳቢ የሚሆነው ጥሪ ያደረገው አካል ነው፡፡

**<u>አንቀጽ 380 የጉባኤው ድምጽ ቆጣሪዎች</u>**

1) ፈቃደኛ ከሆኑ በባለአክሲዮንነትም ሆነ በወኪልነት ስም በጉባኤው ስብሰባ ላይ ከተገኙት ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው ሁለት ባለአክሲዮኖች ድምጽ ቆጣሪ ይሆናሉ፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የድምጽ ቆጣሪ መሆን የሚችሉት ባለአክሲዮኖች ፈቃደኛ ካልሆኑ ወይም በጉባዔው የተገኙት ባለአክሲዮኖች ሌላ ሰው መምረጥ ከፈለጉ ስብሰባው እንደተጀመረ ሁለት ድምጽ ቆጣሪዎችን መምረጥ አለባቸው፡፡

**<u>አንቀጽ 381 የማኅበሩን ሰነዶች የማየት ወይም የመውሰድ መብት</u>**

**1)** ማንኛውም ባለአክሲዮን ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱትንና በማኅበሩ ጽህፈት ቤት የሚገኙትን ሰነዶች በማንኛውም ጊዜ የማየት እና ቅጂዎችን የመውሰድ መብት አለው፡-

**(ሀ)** የማኅበሩን የሒሳብ ሚዛን፣ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ እንዲሁም የንብረት ዝርዝር መዝገብ፤

**(ለ)** ባለፉት የመጨረሻ ሦስት ተከታታይ ዓመታት በዳሬክተሮች ቦርድና
በኦዲተሮች ለጠቅላላ ጉባኤዎች የቀረቡ ሪፖርቶችን፤

**(ሐ)** የጉባኤዎችን ቃለ ጉባኤና በጉባኤው የተሳተፉ ባለአክሲዮኖችን መመዝገቢያ ሰነድ፤

**(መ)** ለጉባኤ የሚቀርበውን የውሳኔ ሃሳብ፤

**(ሠ)** በዚህ ሕግ አንቀጽ 311 ስር የተመለከተውን ለማኅበሩ ቅርበት ያላቸው ሰዎች መዝገብ፤

**(ረ)** በበጀት ዓመቱ በማኅበሩ ውስጥ ከፍተኛ ክፍያ ይከፈለው የነበረውን ሰራተኛ ስምና የተከፈለውን ጠቅላላ ክፍያ መጠን የሚያሳየውን ሰነድ፤

**(ሸ)** የማኅበሩን ባለአክሲዮኖች ዝርዝር የያዘውን ሰነድ፤

**2)** ማንኛውም ባለአክሲዮን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱትን ሰነዶች ለማየት ወይም ቅጂ ለመውሰድ ያቀረበው ጥያቄ በማኅበሩ ተቀባይነት ካላገኘ ለንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም አግባብ ላለው ሌላ የመንግስት አካል በማመልከት ሰነዶቹን የማየት እና ቅጅ የመውሰድ መብት አለው፡፡

**3)** ያልተከፋፈሉ አክሲዮኖችን በጋራ የያዙ ባለአክሲዮኖችና አክሲዮኖችን በአላባ ወይም በመያዣ የተቀበሉ ገንዘብ ጠያቂዎች በዚህ አንቀጽ የተመለከቱ የማኅበሩን ሰነዶች ቅጅ የማግኘት መብት አላቸው፡፡

**<u>አንቀጽ 382 ተጨማሪ መረጃ የማግኘት መብት</u>**

1) አንድ ባለአክሲዮን በአንቀጽ 381 እና በሌሎች የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች ከተመለከቱት በተጨማሪ በጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳ ተደርጎ በቀረበ ጉዳይ ላይ ከድምዳሜ ለመድረስ የሚያስፈልግ ተጨማሪ መረጃ ለጉባዔው እንዲቀርብ የጠየቀ እንደሆነ ቦርዱ አስፈላጊውን መረጃ ለጉባዔው መስጠት አለበት፡፡ ሆኖም መረጃው ይፋ

መደረጉ በሕግ የተከለከለ ከሆነ ወይም በቦርዱ እይታ ማኅበሩ ላይ ቀላል የማይባል ጉዳት የሚያደርስ ከሆነ ቦርዱ መረጃውን ይፋ ማድረግ የለበትም፡፡

2) ቦርዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት መረጃ ያልሰጠ እንደሆነ ጥያቄ አቅራቢው ባለአክሲዮን ክስ ማቅረብ ይችላል፡፡ መረጃውን ይፋ ላለማድረግ በቂ ምክንያት ያለው መሆኑን ማኅበሩ ካላስረዳ በቀር፤ ክስ የቀረበለት ፍ/ቤት ቦርዱ የተጠየቀውን መረጃ እንዲሰጥ ትዕዛዝ መስጠት አለበት፡፡

3) ማኅበሩ የአንድ የተዛመዱ ማኅበሮች ቡድን አባል የሆነ እንደሆነ መረጃ የመስጠት ግዴታው ማህበሩ ከተቀሩት የቡድኑ አባላት ጋር ያለውን ግንኙነት ጭምር ያካትታል፡፡ ማኅበሩ እናት ማኅበር ከሆነ ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሌሎች ማኅበሮችን የሚቆጣጠር ከሆነ መረጃ የመስጠት ግዴታው የቡድኑ አባላትን ሂሳቦች እንዲሁም ስለተቀጥላዎቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት መቅረብ ያለበትን መረጃ ያካትታል፡፡

<u>**አንቀጽ 383 የባለአክሲዮኖች ድምጽ የመስጠት መብት**</u>

**1)** መደበኛ ወይም ትርፍ ብቻ የሚያስገኙ አክሲዮኖችን ለያዘ ባለአክሲዮን ድምጽ የሚሰጠው ዋጋ/ክብደት የሚወሰነው በማኅበሩ ዋና ገንዘብ ውስጥ ባለአክሲዮኑ ባለው ድርሻ መጠን ይሆናል፡፡

**2)** በሕግ መሰረት ድምፅ የመስጠት መብት የሚያሳጡ ሁኔታዎች ከሌሉ በስተቀር እያንዳንዱ አክሲዮን ቢያንስ አንድ ድምጽ የመስጠት መብት ይሰጣል፡፡

<u>**አንቀጽ 384 ድምጽ የመስጠት ገደብ**</u>

አክሲዮኖች የሚሰጡት ከፍተኛ የድምጽ ቁጥር በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ ሊገደብ ይችላል፡፡ ሆኖም ድምጽ የመስጠት ገደብ በሁሉም አክሲዮኖች መደቦች ላይ ልዩነት ሳይደረግ በእኩልነት ተፈጻሚ መሆን ይኖርበታል፡፡

<u>**አንቀጽ 385 የጥቅም ግጭት**</u>

**1)** ማንኛውም ባለአክሲዮን ስለራሱ ወይም ሦስተኛ ወገንን ወክሎ ከማኅበሩ ጋር የጥቅም ግጭት በሚያስነሱ ጉዳዮች ላይ ድምጽ መስጠት አይችልም፡፡

**2)** በተለይም የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ባለአክሲዮን ቢሆኑም የራሳቸውን ሃላፊነት፣ ተጠያቂነት እንዲሁም በማኅበሩ እና በራሳቸው ጥቅም መካከል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግጭት በሚያስነሱ ጉዳዮች ላይ ድምጽ መስጠት አይችሉም፡፡

**3)** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሰረት ድምጽ የመስጠት መብት የማያሰጡ አክሲዮኖች የጉባኤውን ምልዓተ ጉባኤ መሟላት ለመወሰን ይቆጠራሉ፡፡

**4)** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ ድምጽ ከመስጠት መቆጠብ የነበረባቸው ባለአክሲዮኖች ድምጽ በመስጠታቸው ምክንያት የማኅበሩን ጥቅም የሚጻረር ውሳኔ ከተላለፈ በዚህ ሕግ አንቀጽ 391 መሠረት ውሳኔውን መቃወም ይቻላል፡፡

<u>**አንቀጽ 386 ድምጽን በነጻነት የመስጠት መብትን መገደብ የማይቻል ስለመሆኑ**</u>

በባለአክሲዮኖች ጉባኤ ውስጥ ድምጽን በነጻነት የመስጠት መብትን የሚገድብ ወይም የመገደብ ውጤት ያለው ማንኛውም የውል ቃል ዋጋ አይኖረውም፡፡

**<u>አንቀጽ 387 ቃለ ጉባኤ</u>**

**1)** የጉባኤ ውይይት በቃለ ጉባኤ መያዝ አለበት፡፡ ቃለ ጉባኤው በስብሰባው ላይ በተገኙት ዳይሬክተሮች እና በማኅበሩ ፀሐፊ ከተፈረመበት በኋላ በቃለ ጉባኤ መዝገብ ይገለበጣል፡፡ ቃለ ጉባኤው ወደ መዝገብ በትክክል ስለመገልበጡ በማኅበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ ወይም በሌሎች ሁለት የቦርድ አባላት መረጋገጥ አለበት፡፡

**2)** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር የተመለከተው ቢኖርም፤ ጉባዔው ስራ ከመጀመሩ በፊት ስብሰባው ላይ ከተገኙት ባለአክሲዮኖች መካከል በጉባዔው ላይ የተደረገው ውይይት እና የተላላፈው ውሳኔ በትክክል በቃለ ጉባዔ መስፈሩን አረጋግጠው በዳይሬክተሮች ቦርድ እና በማሕበሩ ጸሓፊ ምትክ የሚፈርሙ ሶስት ባለአክሲዮኖችን መምረጥ ይቻላል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ምርጫ በስብሰባው ጥሪ እንደ አጀንዳ ባይያዝም ሊከናወን ይችላል፡፡

**3)** የጉባኤው ቃለ ጉባኤዎች በተለይ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ጉዳዮች መያዝ አለባቸው፡-

**(ሀ)** የጉባኤውን ጥሪ አደራረግ፤

**(ለ)** የስብሰባውን ቦታና ቀን፤

**(ሐ)** አጀንዳዎቹን፤

**(መ)** በጉባኤው የተገኙ የቦርድ አባላትን ስም፤

**(ሠ)** በስብሰባው ላይ የተገኙ አክሲዮኖችን ብዛትና የምልዓተ ጉባኤውን ቁጥር፤

**(ረ)** ለጉባኤው የቀረቡትን ሰነዶች፤

**(ሰ)** የውይይቱን አጭር ማጠቃለያ፤

**(ሸ)** የተሰጡትን ድምጾች ውጤት፣ እና

**(ቀ)** ጉባኤው ያሳለፋቸውን ውሳኔዎች፡፡

**4)** ምልዓተ-ጉባኤው ባለመሟላቱ ምክንያት ጉባኤው ለመሰብሰብ ሳይችል የቀረ እንደሆነ የጉባኤው ሰብሳቢ ይኸው በቃለ ጉባኤ እንዲያዝ ያደርጋል፡፡

**<u>አንቀጽ 388 የቃለ ጉባኤ ቅጂዎች ወይም ግልባጮች</u>**

የቃለ ጉባኤ ቅጂዎች ወይም በአጭር የተዘጋጁ ግልባጮች ተቀባይነት የሚኖራቸው በዳሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ ወይም በስብሰባው ላይ በተገኙ ሁለት የቦርድ አባላት ትክክለኛነታቸው ሲረጋገጥ ነው፡፡

**<u>አንቀጽ 389 ጉባኤውን ለሌላ ጊዜ ስለማስተላለፍ</u>**

1) በጉባዔው ስብሰባ ላይ ከተወከለው ዋና ገንዘብ ቢያንስ አንድ ሶስተኛ ድርሻ ያላቸው ባለአክሲዮኖች ለውይይት በቀረቡት አጀንዳዎች ላይ በቂ የሆነ መረጃ የሌላቸው እንደሆነ ስብሰባው ከሦስት ቀናት ላልበለጠ ጊዜ እንዲተላለፍ መጠየቅ ይችላሉ፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር የተመለከተው መብት በአጀንዳነት በተያዘ አንድ ጉዳይ ላይ ሊሰራበት የሚችለው ለአንድ ጊዜ ብቻ ነው፡፡

**<u>አንቀጽ 390 በስምምነት የሚደረግ የሁሉም ባለአክሲዮኖች ጉባኤ</u>**

1) ስለ ባለአክሲዮኖች ጉባዔ አጠራር የተመለከተውን ሥርዓት ሳይከተሉ ሁሉም የማኅበሩ ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎቻቸው በስምምነት ጉባኤ ማድረግ ይችላሉ፡፡
2) ሁሉም ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎቻቸው በስብሰባው ላይ እስከተገኙ ድረስ በዚህ ሕግ መሰረት በጠቅላላ ጉባዔ ሥልጣን ስር በሚወድቅ ማንኛውም ጉዳይ ላይ መወያየት እና ውሳኔ መስጠት ይችላሉ፡፡

**<u>አንቀጽ 391 የጉባኤው ውሳኔዎች ውጤት</u>**

1) በሕግ ወይም በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ መሠረት በጉባኤ መተላለፍ ሚችሉ ውሳኔዎች በስብሰባው ላይ ባልተገኙ፣ ድምፀ ተአቅቦ ባደረጉ፣ በሃሳብ በተለዩ፣ ችሎታ በሌላቸዉ ወይም ድምፅ የመስጠት መብት በተከለከሉ ባለአክሲዮኖች ላይ ሁሉ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡
2) ማንኛውም በውሳኔው ጥቅሙ የተጎዳ ሰው በሕግና በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመቃረን የተላለፈ ውሳኔ ውድቅ እንዲደረግለት ውሳኔው መተላለፉን ካወቀበት ጊዜ አንስቶ በሶስት ወራት ጊዜ ውስጥ ለፍ/ቤት ማመልከት ይችላል፡፡ ሆኖም ውሳኔው በንግድ መዝገብ የገባ ከሆነ ስለ ውሳኔው መተላለፍ በተጨባጭ አወቀም አላወቀም ውሳኔውን በመቃወም ለፍ/ቤት ማመልከት የሚችለው ውሳኔው በንግድ መዝገብ ከገባበት ቀን አንስቶ በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ ብቻ ነው፡፡
3) ውሳኔውን ውድቅ ለማድረግ ክስ የሚቀርበው የማኅበሩ ዋና መሥሪያ ቤት በሚገኝበት ቦታ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይሆናል፡፡
4) አመልካቹ ለጊዜው ውሳኔው እንዲታገድ ጥያቄ ለፍርድ ቤት ያቀረበ እንደሆነ ፍ/ቤቱ የማኅበሩን ዋና ስራ አስኪያጅ ወይም በክርክሩ ማኅበሩን የወከለው ሌላ ሰው ሃሳብ ከሰማ በኋላ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ የጉባኤው ውሳኔዎች ቢፈጸሙ በማኅበሩ ወይም በክስ አቅራቢው ላይ የማይመለስ ጉዳት ያደርሳሉ ብሎ ሲያምን ውሳኔዎቹ ለጊዜው እንዳይፈጸሙ ሊያግድ ይችላል፡፡
5) ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሰረት እግድ ቢሰጥ በማኅበሩ ላይ ያልተገባ ኪሣራ ሊያደርስ ይችላል ብሎ ካመነ የዕግድ ጥያቄ አቅራቢው ለኪሳራው ተመጣጣኝ የሆነ ዋስትና እንዲያቀርብ ወይም ገንዘብ እንዲያስይዝ ሊያዝ ይችላል፡፡
6) የጉባኤው ውሳኔ በፍርድ ቤቱ ውድቅ ከተደረገ የፍርድ ቤቱ ውሳኔ በሁሉም የማኅበሩ ባለአክሲዮኖች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
7) የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ሦስተኛ ወገኖች በቅን ልቦና ያገኟቸውን መብቶች አያስቀሩም፡፡

**<u>ክፍል ሁለት</u>**

## መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ

### አንቀጽ 392 ሰነዶችን የማየት መብት

በዚህ ሕግ አንቀጽ 381 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ባለአክሲዮን መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ከሚደረግበት ቀን በፊት ባሉት አስራ አምስት ተከታታይ ቀናት በማኅበሩ ዋና መሥሪያ ቤት የሚገኘውን የሃብትና ዕዳ ሒሳብ መግለጫ፤ የትርፍና ኪሣራ ሒሳብ፣ የዳይሬክተሮች ቦርድንና የኦዲተሮችን ሪፖርት እንዲሁም የውሳኔ ሃሳቦችን ማየት ወይም ግልባጭ መውሰድ ወይም በራሱ ወጭ እንዲላክለት መጠየቅ ይችላል፡፡

### አንቀጽ 393 መደበኛ ጉባኤ የሚደረግበት ጊዜ

1) በየዓመቱ እያንዳንዱ የሒሳብ ዓመት ከተዘጋበት ቀን ጀምሮ ባሉት አራት ወራት ውስጥ አንድ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ መደረግ አለበት፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተወሰነው የአራት ወር ጊዜ በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ ወደ ስድስት ወር ሊራዘም ይችላል፡፡
3) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተጨማሪ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔዎች ሊደረጉ ይችላሉ፡፡

### አንቀጽ 394 የመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ሥልጣን

የዚህ ሕግ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የማኅበሩን የሃብትና ዕዳ ሒሳብ መግለጫ፤ የትርፍና ኪሣራ ሒሳብ እንዲሁም የዳይሬክተሮች ቦርድን ሪፖርት፣ የኦዲተሮችን ሪፖርት ካለም የተቆጣጣሪ ቦርዱን ሪፖርት አዳምጦ የማሻሻል ወይም የማጽደቅ፤ ወይም ያለመቀበል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በትርፍ አመዳደብና አከፋፈል እንዲሁም በአጠቃላይ ያለፈውን የሂሳብ ዓመት ማጠቃለያ የተመለከቱ የሒሳብ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ የማሳለፍ፤
2) እንደአስፈላጊነቱ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን፣ የተቆጣጣሪ ቦርድ አባላትን ወይም ኦዲተሮችን የመሾም ወይም የመሻር እንዲሁም የሥራ ዋጋቸውን የመወሰን፤
3) ማኅበሩ የግዴታ ወረቀቶችን እንዲያወጣ የመፍቀድ እንዲሁም ከዚሁ ጋር በተያያዘ ማኅበሩ ስለሚሰጠው መያዣ የመወሰን፤
4) በአንድ ጊዜ ወይም የመጀመርያው ሽያጭ ከተደረገበት ጊዜ አንስቶ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በተለያየ መጠን ከማኅበሩ ሀብት ሀምሳ አንድ በመቶ ወይም ከዛ በላይ የሚሆነውን መጠን ማስተላለፍ የተፈለገ እንደሆነ ይህን የመፍቀድ እና
5) በዚህ ሕግ ለአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ በግልጽ ተለይተው ከተሰጡት ጉዳዮች በስተቀር በሌሎች የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ በሚወስንባቸው ጉዳዮች ላይ ሁሉ ውሳኔ የመስጠት፡፡

### አንቀጽ 395 የጥቅም ግጭት ያለበት ውል የማህበሩን ሀብት አስር በመቶና በላይ የሚሸፍን ሲሆን

1) በዚህ ሕግ አንቀጽ 306 ስር የተመለከቱት ድንጋጌዎች ቢኖሩም የጥቅም ግጭት ያለበት ውል የማኅበሩን ሀብት አስር በመቶ ወይም ከዛ በላይ የሚያህል ንብረት የሚሸፍን ከሆነ ውሉ እንዲደረግ የማኅበሩ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ በቅድሚያ ፈቃድ መስጠት አለበት፡፡

2) ከማኅበሩ ጥቅም ጋር ሊጋጭ የሚችል ጥቅም ያለው ዳይሬክተር፣ ሥራ አስኪያጅ፣ ወይም ባለአክሲዮን የጥቅም ግጭት መንስዔ ሊሆኑ ስለሚችሉ ጉዳዮች በተለይም የጥቅም ግጭቱ ዓይነት፣ መጠን እና የመሳሰሉትን በተመለከተ የተሟላና ትክክለኛ መረጃ ነጻ እና ገለልተኛ ለሆነው የማኅበሩ የውጭ ኦዲተር ማቅረብ አለበት፡፡

3) የማህበሩ የውጭ ኦዲተር የጥቅም ግጭት መኖሩን እና አለመኖሩን፣ ካለም የጥቅም ግጭቱን መንስኤ፣ ዓይነት፣ መጠን እና ከማኅበሩ ጋር የጥቅም ግጭት ያለው ዳይሬክተር፣ ባለአክሲዮን ወይም ሌላ ከማኅበሩ ጋር ቅርበት ያለውን ሰው ማንነት በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ የተሟላ መረጃ ማጠናቀር አለበት፡፡ የሰበሰበውን መረጃ እና የራሱን ምክረ ሃሳብ ውሉ ከመደረጉ በፊት ለማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ ማቅረብ አለበት፡፡

4) ከማኅበሩ ጥቅም ጋር ሊጋጭ የሚችል ጥቅም ከስምምነቱ የሚያገኝ የማኅበሩ ዳይሬክተር ወይም ሌላ ሰው ባለአክሲዮን ቢሆንም ጠቅላላ ጉባዔው ስምምነቱን በተመለከተ ሲወስን ድምጽ መስጠት የለበትም፡፡

5) የማኅበሩ ዳይሬክተሮች በዚህ አንቀጽ ሥር የሚወድቅ የጥቅም ግጭት ሊፈጥር የሚችል ውል እንዲደረግ ጠቅላላ ጉባዔው ከፈቀደበት ጊዜ አንስቶ ዘገየ ቢባል በ72 (ሰባ ሁለት) ሰዓታት ውስጥ እንዲደረግ ስለተፈቀደው ውል ዝርዝር መረጃ የያዘ ሪፖርት ለንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም አግባብነት ላለው ሌላ የመንግስት መስሪያቤት ማቅረብ እና በማህበሩ ድረ-ገጽ እንዲወጣ ማድረግ አለባቸው፡፡ ሪፖርቱ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡-

   ሀ) የሚሸጠውን ወይም የሚገዛውን ንብረት ለይቶ ለማወቅ የሚረዳ መግለጫ፤

   ለ) የሚደረገው ክፍያ ዓይነት እና መጠን እና

   ሐ) ከማኅበሩ ጋር የጥቅም ግጭት ያለበትን ዳይሬክተር፣ ባለአክሲዮን ወይም ሌላ ከማኅበሩ ጋር ቅርበት ያለውን ሰው ስም፣ ለጥቅም ግጭቱ መንስዔ የሚሆነው በማሕበሩ እና ከማሕበሩ ጋር ውል በገባው ድርጅት ውስጥ ያለውን ቀጥተኛም ሆነ ተዘዋዋሪ ጥቅም በግልጽ ማመልከት አለበት፡፡

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (5) በተመለከተው አኳኋን በባለአክሲዮኖች ጉባኤ በቅድሚያ ተፈቅዶ ሪፖርት ያልተደረገ ስምምነት አይጸናም፡፡ በመሆኑም በማህበሩ፣ በባለአክሲዮኖች ወይም በገንዘብ ጠያቂዎች ጥያቄ የቀረበለት እንደሆነ ፍ/ቤት ውሉ እንዲፈርስ ማዘዝ ይችላል፡፡ ፍ/ቤቱ ውሉ እንዲጸና የሚፈቅደው ከውሉ መፍረስ ይልቅ የውሉ መጽናት ለማኅበሩ የበለጠ እንደሚጠቅም ግልጽ የሆነ እንደሆነ ነው፡፡

7) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(6) መሰረት የቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት አግኝቶ የጥቅም ግጭት ያለበት ውል ሲፈርስ ማህበሩ በውሉ ምክንያት ለደረሰበት ጉዳት ካሳ የማግኘት መብት አለው፡፡ በተጨማሪም ከማህበሩ ጋር የጥቅም ግጭት ያለበት ውል የገባው ዳይሬክተር፣ ባለአክሲዮን ወይም በዚህ ሕግ አንቀጽ 306 ንዑስ አንቀጽ (6) መሰረት ከማኅበሩ ጋር ቅርበት ያለው ሌላ ሰው በውሉ ምክንያት ያገኘውን ትርፍ ከነሕጋዊ ወለዱ ለማኅበሩ መስጠት አለበት፡፡

## አንቀጽ 396 ልዩ መርማሪ መሾም

1) ማንኛውም ባለአክሲዮን ወይም ባለአክሲዮኖች ተለይተው የተመለከቱ የማኅበሩ ሥራዎች በማኅበሩ እና በባለአክሲዮኖች ላይ ያላቸው ተጽዕኖ እንዲሁም ከሕግና ከመልካም የንግድ አሰራር አንጻር ምን ያህል ተገቢ እንደሆኑ ገምግሞ ዘገባ የሚያቀርብ ልዩ መርማሪ እንዲሾም ለማሕበሩ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ሐሳብ ማቅረብ ይችላሉ፡፡ ይህ ዓይነቱ ሀሳብ ቢያንስ፡-

   ሀ) ልዩ መርማሪ እንዲሾም የተፈለገበትን ምክንያት፤ እና

   ለ) የምርመራውን አድማስ መግለጽ፤ አለበት፡፡

2) ለማኅበሩ አገልግሎት የሚያቀርብን ሰው እንዲሁም ማኅበሩ አባል የሆነበት ቡድን አባል በመሆኑ የጥቅም ግጭት ሊፈጠርበት የሚችልን ማኅበር ወይም ሰው ልዩ መርማሪ አድርጎ መሾም አይቻልም፡፡

3) የማኅበሩ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ልዩ መርማሪ እንዲሾም የቀረበለትን ሐሳብ ውድቅ ያደረገ እንደሆነ በማኅበሩ ዋና ገንዘብ ውስጥ ቢያንስ 1/10ኛ (ከአስር አንድ እጅ) የሚወክሉ አክሲዮኖች ያሉዋቸው ማኅበርተኞች ጥያቄያቸውን ለፍ/ቤት ማቅረብ ይችላሉ፡፡ ፍ/ቤቱ የማኅበሩ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ልዩ መርማሪ እንዲሾም ትዕዛዝ መስጠት አለበት፡፡ ማኅበሩ የምርመራው አድማስ በማኅበሩ ወይም በሦስተኛ ወገን ጥቅም ላይ ከባድ ጉዳት እንደሚያደርስ ካስረዳ ፍ/ቤቱ ጉዳቱ እንዳይደርስ የምርመራውን አድማስ ማሻሻል ይችላል፡፡

4) ልዩ መርማሪው ስላደረገው ምርመራ ውጤት በጽሁፍ ዘገባ ማቅረብ አለበት፡፡ የምርመራው ውጤት ለማኅበሩ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ መቅረብ አለበት፡፡ የዘገባውን ቅጂ ማኅበርተኞች መውሰድ ይችላሉ፡፡

5) ለልዩ መርማሪው የሚገባውን የድካም ዋጋ ጥያቄ አቅራቢዎቹ መሸፈን አለባቸው፡፡ ሆኖም የምርመራው ውጤት የሕግ፣ የማኅበሩ መመስረቻ ጽሁፍ ወይም የማኅበሩ አስተዳደር ስርዓት መጣስን ያሳየ እንደሆነ ልዩ መርማሪ እንዲሾም የጠየቁት ባለአክሲዮኖች ለመርማሪው የከፈሉትን ገንዘብ ማኅበሩ ሊመልስላቸው ይገባል፡፡

6) ልዩ መርማሪ እንዲሾም የሚቀርብ ሐሳብ የማኅበሩ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ከመደረጉ ከሰላሳ ቀናት በፊት ለማኅበሩ ቦርድ መቅረብ አለበት፡፡

## አንቀጽ 397 በጉባኤው የመተሳተፍ መብት

**1)** ተቃራኒ ድንጋጌ ቢኖርም፤ ማንኛውም ባለአክሲዮን የያዘው የአክሲዮን ብዛት ግምት ውስጥ ሳይገባ በጉባኤው የመሳተፍ መብት አለው፡፡

**2)** በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በስተቀር፤ ማንኛውም ባለአክሲዮን በሌላ ባለአክሲዮን ወይም ባለአክሲዮን ባልሆነ ሰው ሊወከል ይችላል፡፡

## አንቀጽ 398 ምልዓተ-ጉባኤ እና የድምጽ ብልጫ

1) በመጀመሪያው የመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ጥሪ ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸው አክሲዮኖች ውስጥ ቢያንስ የማኀበሩን ዋና ገንዘብ (ካፒታል) አንድ አራተኛ የሚወክሉ ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎች መሳተፍ አለባቸው፡፡

2) ምልዓተ ጉባዔ የሚሰላው በባለአክሲዮኖች ቁጥር ሳይሆን በተወከለው የዋና ገንዘብ (ካፒታል) መጠን ነው፡፡ ጉባዔው ሕጉ በሚያዘው ስርዓት እስከተጠራ እና አስፈላጊው የዋና ገንዘብ መጠን እስከተወከለ ድረስ ውሳኔ ማሳለፍ ይችላል፡፡ በተለይም የተወሰኑ ባለአክሲዮኖች ለመሰብሰብ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ብቻ የማኀበሩ ጠቅላላ ጉባዔ ያለበትን ኃለፊነት እንዳይወጣ አይደረግም፡፡

3) በሁለተኛው ጥሪ ድምጽ የመስጠት መብት ያላቸው አክሲዮኖች የሚወክሉት ዋና ገንዘብ (ካፒታል) ግምት ውስጥ ሳይገባ በተገኙት አክሲዮኖች ጉባኤውን ማካሄድና ውሳኔዎችን ማሳለፍ ይቻላል፡፡

4) የጉባኤው ውሳኔዎች የሚተላለፉት በጉባኤው ከተገኙት ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸው አክሲዮኖች አብዛኛውን ካፒታል በሚወክሉት ድምጽ ከተደገፉ ነው፡፡ ለድምጽ ብልጫ አቆጣጣር ድምጽ ያልተሰጠባቸውም ሆነ ድምጽ ያልተጻፈባቸው የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ከግምት ውስጥ አይገቡም፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለማኀበሩ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤዎች

### አንቀጽ 399 ሰነዶችን የማየት መብት

ከመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ በፊት ባለአክሲዮኖች የማኀበሩን ሰነዶች የማየትና ግልባጮችን የመውሰድ መብት የሚመለከቱት የዚህ ሕግ አንቀጽ 381 ድንጋጌዎች እንደ አግባብነታቸው ለአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤም ተፈጻሚነት አላቸው፡፡

### አንቀጽ 400 የአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ሥልጣን

አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የማኀበሩን መመስረቻ ጽሑፍ የማሻሻል፤
2) የማኀበሩን ዋና ገንዘብ የማሳደግ ወይም የመቀነስ፤
3) የማኀበሩን ዜግነት የመለወጥ፤
4) ማኀበሩ እንዲፈርስ፤ ወደ ሌላ ዓይነት የንግድ ማኀበር እንዲለወጥ፣ እንዲከፋፈል ወይም እንዲዋሀድ የመወሰን፤
5) ሌሎች በሕግ ወይም በመመስረቻ ጽሑፍ በዚህ ጉባኤ እንዲታዩ ተለይተው የተሰጡትን ጉዳዮች የመወሰን፡፡

### አንቀጽ 401 በጉባኤ የመሳተፍ መብት

ተቃራኒ ስምምነት ቢኖርም፤ ማንኛውም ባለአክሲዮን የያዘው የአክሲዮን ብዛት ግምት ውስጥ ሳይገባ በአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤዎች ላይ ሊሳተፍ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 402 ስለአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ድምጽ አሰጣጥና ምልዓተ ጉባኤ**

1) የአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ የጸና የሚሆነው በጉባዔው የተገኙት ድምጽ የመስጠት መብት ያላቸው አክሲዮኖች ከወከሉት ካፒታል ሁለት ሦስተኛውን በሚወክሉት ድምጽ ከተደገፈ ነው፡፡ ለድምጽ ብልጫው አቆጣጠር ስሌት ድምጽ ያልሰጡም ሆነ ድምጽ ያልተጻፈባቸው የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ግምት ውስጥ አይገቡም፡፡

2) አስቸኳይ ጉባኤው የማኅበሩን ዜግነት መለወጥ የሚችለው ድምጽ የመስጠት መብት ያላቸውን ባለአክሲዮኖች ሙሉ ድጋፍ ያገኘ እንደሆነ ነው፡፡

3) አስቸኳይ ጉባዔው አንድ ባለአክሲዮን ከፈቃዱ ውጪ በማህበሩ ውስጥ ተጨማሪ መዋዕለ ንዋይ እንዲያፈስ መወሰን አይችልም፡፡ በመሆኑም ተጨማሪው ገንዘብ ከማህበሩ መጠባበቂያ ገንዘብ ወይም ሊከፋፈል ከሚችል ትርፍ የሚከፈል ካልሆነ በስተቀር፤ በነባር አክሲዮኖች ላይ የተጻፈውን ዋጋ በመጨመር የማኅበሩን ዋና ገንዘብ ማሳደግ የሚቻለው የባለአክሲዮኖች ሙሉ ድጋፍ የተገኘ እንደሆነ ነው፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (**2**) እና (3) የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፤ ምልዓተ ጉባዔ ተሟልቷል የሚባለው፡-

   **(ሀ)** በመጀመሪያው ጥሪ ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸው አክሲዮኖች ውስጥ ቢያንስ የማኅበሩን ዋና ገንዘብ ግማሽ የሚወክሉ ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎቻቸው፤

   **(ለ)** በሁለተኛው ጥሪ ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸው አክሲዮኖች ውስጥ ቢያንስ የማኅበሩን ዋና ገንዘብ ሲሶ የሚወክሉ ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎቻቸው፤

   **(ሐ)** በሶስተኛው ጥሪ ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸው አክሲዮኖች ውስጥ ቢያንስ የማኅበሩን ዋና ገንዘብ አንድ አስረኛ የሚወክሉ ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎቻቸው፤

በጉባዔው የተገኙ እንደሆነ ነው፡፡

**<u>አንቀጽ 403 ከማኅበሩ የመውጣት መብት</u>**

1) የማኅበሩን ዓላማ ወይም ዓይነት ለመለወጥ፣ማኅበሩን ከሌላ ማህበር ጋር ለማዋሀድ ወይም ለመከፋፈል የተላለፈ ውሳኔን የተቃወሙ ባለአክሲዮኖች ከማኅበሩ መውጣት ይችላሉ፡፡

2) ባለአክሲዮኖች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ መሰረት ከማኅበሩ መውጣት የፈለጉ እንደሆነ፡-

   **(ሀ)** ውሳኔ በተሰጠበት ስብሰባ ላይ የተገኙት ባለአክሲዮኖች ስብሰባው ከተጠናቀቀበት ቀን አንስቶ በ ሶስት ቀናት ውስጥ፤

   **(ለ)** ውሳኔ በተሰጠበት ስብሰባ ያልተገኙ ባለአክሲዮኖች ውሳኔው በአገር አቀፍ ጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ ባሉት 15 ቀናት ውስጥ፤

   ከማኅበሩ የመውጣት ውሳኔያቸውን በደብዳቤ ወይም ሌሎች አግባብነት ባለቸው ኤልክትሮኒክ ዘዴዎች ለማኅበሩ ዋና ስራ አስኪያጅ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፡፡

**3)** ከማኅበሩ ለመውጣት የወሰኑት ባለአክሲዮኖች የአክሲዮናቸዉ ዋጋ በገበያ ላይ የተወሰነ ከሆነ ከስብሰባው ቀን በፊት በነበሩት ስድስት ወራት ውስጥ በገበያው በነበረው አማካይ ዋጋ፣ የአክሲዮኖቹ ዋጋ በገበያ ያልተወሰነ ከሆነ በመጨረሻው የሂሳብ ዓመት የሀብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫ ውስጥ በተመለከተው የማኅበሩ ሀብት ውስጥ አክሲዮኖቻቸው በሚወክሉት መጠን ታስቦ ይከፈላቸዋል፡፡

**4)** በዚህ አንቀጽ የተመለከተውን ከማኅበሩ የመውጣት መብት የሚያስቀር ወይም የሚያሳጣ ወይም የመብቱን ተግባራዊነት አስቸጋሪ የሚያደርግ ማንኛውም ተቃራኒ ስምምነት ወይም ውሳኔ ተፈጻሚነት የለውም፡፡

## ክፍል አራት
## ስለማኅበሩ ልዩ ጉባኤ

### አንቀጽ 404 የአንድን መደብ ባለአክሲዮኖች መብቶች ስለመለወጥ

ጠቅላላ ጉባኤው የአንድን መደብ ባለአክሲዮኖች መብቶች ለመለወጥ የሚያስተላላፈው ውሳኔ የፀና የሚሆነው ጉዳዩ የሚመለከተው መደብ ባለአክሲዮኖች ልዩ ጉባዔ በዚህ ሕግ በአንቀጽ 406 በተመለከተው ምልዓተ ጉባኤ እና ድምጽ ሲያጸድቀው ነው፡፡

### አንቀጽ 405 ሰነዶችን የማየት መብት

የዚህ ሕግ አንቀጽ 381 ድንጋጌ በልዩ ጉባኤ ላይም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

### አንቀጽ 406 የልዩ ጉባኤው ምልዓተ ጉባኤና ድምፅ ብልጫ

**1)** በልዩ ጉባኤ ውሳኔ ለማሳለፍ ምልዓተ ጉባዔ የሚኖረው ድምፅ ለመስጠት መብት ያላቸዉ የመደቡ አባል ባለአክሲዮኖች ከሚወክሉት ዋና ገንዘብ፡-

**(ሀ)** በመጀመሪያው ጥሪ ቢያንስ ግማሽ፤

**(ለ)** በሁለተኛው ጥሪ ቢያንስ ሲሶ፤

**(ሐ)** በሶስተኛው ጥሪ ቢያንስ ሩብ፤

ድርሻ የሚወክሉ ባለአክሲዮኖች ራሳቸዉ ወይም በወኪሎቻቸው አመካኝነት ሲገኙ ነው፡፡

**2)** በዚህ ሕግ አንቀጽ 402 ንኡስ አንቀጽ (1) ስር ስለ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ የድምፅ ብልጫና አቆጣጠር የተመለከተው በልዩ ጉባዔም ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

## የዕዳ ሰነዶች

**አንቀጽ 407 ትርጓሜ**

1) የዕዳ ሰነድ ማለት አውጪው ማኅበር ለዕዳ ሰነድ ያዥ የተወሰነ ወለድ በተወሰነ ጊዜ ለመክፈል እና የውሉ ጊዜ ሲጠናቀቅ የተበደረውን ገንዘብ ለመመለስ ግዴታ የገባበት የሚተላለፍ የዕዳ ማረጋገጫ ሰነድ ነው፡፡
2) እኩል ዋጋ የተጻፈባቸው በአንድ ዙር የሚወጡ የዕዳ ሰነዶች ለዕዳ ሰነድ ያዦች እኩል መብት ይሰጣሉ፡፡

**አንቀጽ 408 የዕዳ ሰነዶችን ማውጣት ስለመቻል**

አንድ የአክሲዮን ማኅበር የዕዳ ሰነዶችን በማውጣት መበደር የሚችለው፡-

1) ዋና ገንዘቡ በሙሉ የተከፈለ ከነሆነ፤ እና
2) ቢያንስ ለአንድ ዓመት ሥራ ላይ ቆይቶ በማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ የጸደቀ የሒሳብ ሚዛን ካለው፤

ነው፡፡

**አንቀጽ 409 መውጣት የሚችለው ከፍተኛ የዕዳ ሰነድ መጠን**

1) አንድ ኩባንያ የዕዳ ሰነዶችን በማውጣት መበደር የሚችለው የገንዘብ መጠን በጸደቀው የመጨረሻ የሀብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫ ውስጥ ከተመለከተው የተከፈለ የማኅበሩ ዋና ገንዘብ ሊበልጥ አይችልም፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ቢኖርም፡-

    **(ሀ)** የማኅበሩ የማይንቀሳቀስ ንብረት ለዕዳ ሰነዶች መያዣ ተደርጎ የተሰጠ እንደሆነና የወጡትም የዕዳ ሰነዶች ዋጋ ከመያዣው ዋጋ 2/3 (ሁለት ሶስተኛ) የማይበልጥ እንደሆነ፤ ወይም

    **(ለ)** ከተከፈለው የማኅበሩ ዋና ገንዘብ በላይ የወጡት የዕዳ ሰነዶች በተመዘገቡ ዋስትናዎች ወይም በመንግስት በወጡ የግምጃ ቤት ሰነዶች ወይም መንግስት ዋስትና በገባላቸዉ ቦንዶች ዋስትና የተሰጠባቸው እና ከዋስትናነት ነፃ የመውጫቸው ጊዜ ከዕዳ ሰነዶች መክፈያ ጊዜ የማይቀድም እንደሆነ ወይም መንግስት ወይም አንድ የመንግስት መስሪያ ቤት በየዓመቱ በሚከፍለው ገንዘብ ዋስትና የተገባላቸው እንደሆነ፤

   አንድ ማኅበር በሀብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫዎች ከተመለከተው የተከፈለ ዋና ገንዘብ በላይ የተጻፈባቸው ዋጋ ያላቸው የዕዳ ሰነዶችን ለማውጣት ይችላል፡፡

3) የዕዳ ሰነዶች ዋጋ ተመልሶ ሙሉ በሙሉ እስኪከፈል ድረስ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 (ለ) መሠረት በዋስትና የተሰጡት ሰነዶች በባንክ ውስጥ መቀመጥ አለባቸው፡፡ ለዕዳ ሰነድ ያዥ የሚከፈለውን ወለድ እና ዋስትና የተገባላቸውን የዕዳ ሰነዶች ዋጋ ጥቂት በጥቂት ለመክፈል አስፈላጊ በሆነው መጠን ለእነዚህ የዋስትና ሰነዶች በየዓመቱ የሚከፈለው ገንዘብ በባንክ በዝግ ሂሳብ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ገደብ የማይንቀሳቀስ ንብረት ለማፍራት በሚወሰድ ብድር ወይም እርሻን መያዣ አድርገው በሚያበድሩ ኩባያንዎች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

**<u>አንቀጽ 410 የዕዳ ሰነዶችን ያወጣ ማኅበር ግዴታዎች</u>**

1) ባውጪው ማኅበር ተመልሰው የተገዙ የዕዳ ሰነዶች ይሰረዛሉ፤ እንደገና ለሽያጭም መቅረብ አይችሉም፡፡
2) የዕዳ ሰነዶችን ያወጣ ማኅበር ዋና ገንዘቡን መቀነስ የሚችለው ዋጋቸው ከነወለድ ለአበዳሪዎች ተከፍሎ በተሰረዙት የዕዳ ሰነዶች መጠን ነው፡፡

**<u>አንቀጽ 411 የዕዳ ሰነዶችን ባወጣ ማኅበር የሚደረግ የዋና ገንዘብ ቅነሳ</u>**

በአንቀጽ 410 ንዑስ አንቀጽ (2) ስር የተመለከተው ቢኖርም፤ በመክሰር ምክንያት የማኅበሩን ዋና ገንዘብ መቀነስ የግድ በሆነ ጊዜ የማኅበሩ ዋና ገንዘብ እና በሕግ የተወሰነው የመጠባበቂያ ገንዘብ በመዘዋወር ላይ ካሉት ዋጋቸዉ ያልተከፈሉ የዕዳ ሰነዶች ዋጋ መጠን እስኪስተካከል ድረስ በሕግ ለተወሰነው የመጠባበቂ ገንዘብ የሚደረገው ተቀናሽ የሚሰላው የዕዳ ሰነዶቹ በወጡበት ጊዜ የነበረውን የዋና ገንዘብ መጠን መሰረት በማድረግ መሆን አለበት፡
፡

**<u>አንቀጽ 412 የዕዳ ሰነዶች ስለሚወጡበት ዋጋ</u>**

1) የዕዳ ሰነዶችን ከተጻፈባቸው ዋጋ ከፍ አድርጎ ማውጣት ይቻላል፡፡
2) በልዩ ሁኔታ በሕግ ካልተደነገገ በስተቀር የዕዳ ሰነዶቹን ላያቸዉ ላይ ከተጻፈው ዋጋ ዝቅ አድርጎ ማውጣት አይቻልም፡፡

**<u>አንቀጽ 413 የዕዳ ሰነድ የምስክር ወረቀት ይዘት</u>**

የዕዳ ሰነድ የምስክር ወረቀት የሚከተሉትን ጉዳዮች መያዝ አለበት፡-

1) የማኅበሩን ስም፣ ዓላማ፣ ዋና መሥሪያ ቤት እና በንግድ መዝገብ የተመዘገበበትን ቦታ፤
2) ማኅበሩ የተመሰረተበትንና የሚቆይበትን ጊዜ፤
3) የዕዳ ሰነዶች በወጡ ጊዜ ማኅበሩ ያለው የተከፈለ ዋና ገንዘብ መጠን፤
4) ጠቅላላ ጉባኤው የዕዳ ሰነዶችን ለማውጣት ውሳኔ የሰጠበትን ጊዜና ውሳኔው በንግድ መዝገብ የተመዘገበበትን ቀን፤
5) የዕዳ ሰነድ የምስክር ወረቀቱ ተከታታይ ቁጥርና በላዩ የተጻፈውን ዋጋ፣ የወለዱን መጠንና የመከፈያውን ቀን እንዲሁም ዕዳው የሚመለስበትን ሁኔታ፤
6) የወጡት የዕዳ ሰነዶችን ልክ እና ከዕዳ ሰነዱ ጋር የተያያዙ ልዩ ዋስትናዎችን፣ እንዲሁም እነዚህ ዋስትናዎችን ያቋቋመው የጽሑፍ ውል የተደረገበትን ጊዜ፤
7) አስቀድሞ የወጡ ነገር ግን ቀስ በቀስ ተከፍለው ያላለቁ የዕዳ ሰነዶችን ልክ እና የተገባላቸዉን ዋስትና፤

8) እንደአስፈላግነቱ የዕዳ ሰነድ ያዦች የዕዳ ሰነዶቻቸውን ወደ አክሲዮን ለመለወጥ የተሰጣቸውን መብት ተግባራዊ የሚያደርጉበትን ጊዜ እንዲሁም የአለዋወጡን ሁኔታ፡፡

**አንቀጽ 414 አክሲዮኖችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት**

በዚህ ሕግ ስለአክሲዮኖች አለመከፋፈል፣ አክሲዮኖች ስለሚወጡባቸው ዘዴዎች፣ ስለአክሲዮኖች መተላለፍ እና መቃወሚያዎች የተደነገጉት ድንጋጌዎች በዕዳ ሰነዶች ላይም እንደአግባብነታቸው ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

**አንቀጽ 415 ስለዕዳ ሰነድ ያዦች ጠቅላላ ጉባኤ**

1) በአንድ ጊዜ የወጡ የዕዳ ሰነድ ያዦች የጋራ ጥቅሞቻቸውን ለማስከበር ሲባል ከዚህ በታች ባሉት አንቀጾች በተመለከቱት ሁኔታዎች ራሳቸውን ሕጋዊ ሰውነት በተሰጠው የዕዳ ሰነድ ያዦች ቡድን ሊያደራጁ ይችላሉ፡፡
2) ማንኛዉም ተቃራኒ ስምምነት ቢኖርም በአንድ የዕዳ ሰነድ ያዦች ቡድን ውስጥ የሚገኙ የዕዳ ሰነድ ያዦች በማንኛዉም ጊዜ የዕዳ ሰነድ ያዦች ጠቅላላ ጉባኤ ማድረግ ይችላሉ፡፡

**አንቀጽ 416 የዕዳ ሰነድ ያዦች ጉባኤ አጠራርና አካሄድ**

1) የዕዳ ሰነድ ያዦች ጉባኤ በማኅበሩ ወይም የዕዳ ሰነድ ያዦች ቡድን ወኪል ሰይሞ እንደሆነ በወኪሉ ወይም ካልተከፈሉ የዕዳ ሰነዶች ውስጥ ሃያ በመቶ ድርሻ ባላቸው የዕዳ ሰነድ ያዦች ሊጠራ ይችላል፡፡
2) በዚህ ሕግ ስለ ባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ አጠራር እና ስለስበሰባው አካሄድ የተደነገጉት ድንጋጌዎች እንደ አግባብነታቸው በዕዳ ሰነድ ያዦች ጉባኤ አጠራርና አካሔድ ላይም ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡
3) ባለዕዳ የሆነው ማኀበር ወይም ለብድሩ ዋስ የሆነ ኩባንያ ዳይሬክተሮች፣ የተቆጣጣሪ ቦርድ አባላት፣ ኦዲተሮች፣ ሰራተኞች በዕዳ ሰነድ ያዦች ጉባዔ ላይ ለዕዳ ሰነድ ያዦች ወኪል ለመሆን አይችሉም፡፡
4) ዋጋቸዉ በማሕሩ የተከፈለ የዕዳ ሰነዶች የያዙ ሰዎች በጉባኤዎች ላይ ተሳታፊ ለመሆን አይችሉም፡፡
5) ማኅበሩ መልሶ የገዛቸው የዕዳ ሰነዶችን ይዞ በጉባኤው ተሳታፊ ሊሆን አይችልም፡፡ ይህ ክልከላ ከባለዕዳው ማኅበር ዋና ገንዘብ ቢያንስ ሠላሳ በመቶ በያዙ ሌሎች የንግድ ማህበራት ላይም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
6) የዕዳ ሰነድ ያዦች የሚያካሂዷቸውን ጉባኤዎች ለመጥራት እና ለማካሄድ አስፈላጊ የሆኑ ወጪዎችን ሁሉ የሚሸፍነው ባለ ዕዳው ማኅበር ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 417 የጉባኤው ስልጣን**

1) የዕዳ ሰነድ ያዦች ጉባኤ ለዕዳ ሰነድ ያዦች ጥቅም ጥበቃና ለብድር ውሉ አፈፃፀም የሚያስፈልጉት ጥንቃቄዎች ሁሉ እንዲፈፀሙ ለማድረግና እንዲሁም እነዚህን ጥንቃቄዎች ለማስፈፀም አስፈላጊ ስለሆኑ ወጪዎች ውሳኔ ይሰጣል፡፡
2) በጉባኤው የሚተላለፉት ውሳኔዎች በጉባኤው ባልተገኙና ውሳኔውን በተቃወሙ በአጠቃላይ በሁሉም የዕዳ ሰነድ ያዦች ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

**አንቀጽ 418 ባለዕዳው ማኅበሩ ባቀረባቸው ሃሳቦች ላይ ውሳኔ ስለመስጠት**

1) የዚህ ሕግ አንቀጽ **417** ንዑስ አንቀጽ (**1)** አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የዕዳ ሰነድ ያገኘች ጉባኤ፡-

**(ሀ)** የማኅበሩ ዓይነት ወይም ዓላማ እንዲለወጥ፤

**(ለ)** ማኅበሩ ከሌላ ማኅበር ጋር እንዲቀላቀል ወይም ወደ ሁለትና ከዚያ በላይ ማኅበር እንዲከፈል፤

**(ሐ)** በነባር የዕዳ ሰነዶች ላይ የቀደምትነት መብት የሚያስገኙ ሌሎች የዕዳ ሰነዶች እንዲወጡ፤

ባለዕዳው ማኅበር በሚያቀርባቸዉ ሀሳቦች ላይ ለመምከር ይችላል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የቀረቡትን ሀሳቦች ጉባኤው ባይቀበላቸውም ማኅበሩ ተግባራዊ ሊያደርጋቸዉ ይችላል፡፡ ሆኖም ገንዘባቸው እንዲመለስላቸዉ ለሚጠይቁ የዕዳ ሰነድ ያገኙ ሀሳቦቹን ተግባራዊ ካደረገበት ቀን አንስቶ ባለው የሶስት ወራት ጊዜ ውስጥ መክፈል ይኖርበታል፡፡

3) ጉባኤው ኩባንያው የብድር ሁኔታዎቹን ለመለወጥ በሚያቀርበው ሀሳብ ላይ ሊመክር ይችላል፡፡

4) ጉባኤው የዕዳ ሰነድ ያገኙችን ግዴታ ሊያከብድ በተለይም ተጨማሪ ገንዘብ እንዲያበድሩ ለማስገደድ እንዲሁም በሙሉ ስምምነት ካልሆነ በስተቀር የዕዳ ሰነዶች በአክሲዮኖች እንዲለወጡ ሊፈቅድ ወይም በቡድኑ ውስጥ በሚገኙ የዕዳ ሰነድ ያገኙ መካከል ልዩነት የሚያደርጉ ሁኔታዎችን ሊፈጥር አይችልም፡፡

## <u>አንቀጽ 419 ለውሳኔዎች መፅናት የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች</u>

1) የዕዳ ሰነድ ያገኙ ጉባኤ ድምፅ የመስጠት መብት ካላቸዉ የዕዳ ሰነዶች ቢያንስ አንድ ሶስተኛውን የያዙት አባላት በአካል ወይም በወኪሎቻቸው አመካይነት ከተገኙ ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ መሳተፍ ከቻሉ ውሳኔዎችን ለማሳለፍ ይችላል፡፡

2) በዚህ ሕግ አንቀጽ 418 የተመለከተውን ጉዳይ ለመወሰን ከዕዳ ሰነድ ያገኙ ¾ (ሦስት አራተኛ) በአካል ወይም በወኪሎቻቸው አመካይነት መገኘት ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ መሳተፍ አለባቸው፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተመለከተው ምልዐተ ጉባኤ በመጀመሪያው ጉባኤ ያልተሟላ እንደሆነ የመጀመሪያው ጥሪ በተፈጸመበት ሁኔታና ጊዜ ሁለተኛ ጉባኤ ይጠራል፡፡ ይህም ጥሪ በመጀመሪያው ጥሪ የነበረውን አጀንዳ፣ያለፈውን ጉባኤ ቀንና ውጤቱን ማመልከት አለበት፡፡ በሁለተኛው ጥሪ የተሰበሰበው ጉባኤ የተገኙትን የዕዳ ሰነዶች ቁጥር ግምት ውስጥ ሳያስገባ ውሳኔ ማስተላለፍ ይቻላል፡፡

4) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ድንጋጌ ቢኖርም፤ በአንቀጽ 418 በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ለመወሰን በተጠራው በሁለተኛው ጉባኤ ላይ የዕዳ ሰነዶችን 50% (ሃምሳ በተመቶ) የያዙ አባላት ካልተገኙ በዚያው የጥሪ ሁኔታና ጊዜ ሦስተኛ ጉባኤ ይጠራል፡፡ ይኸው ጉባኤ ውሳኔ ማሳለፍ የሚችለው የዕዳ ሰነዶችን አንድ አራተኛውን የያዙ አባላት ወይም ወኪሎቻቸው ከተገኙ ይሆናል፡፡

## <u>አንቀጽ 420 ስለድምፅ ብልጫ</u>

1) በዕዳ ሰነድ ያገኙ ጉባዔ ውሳኔ ሊተላለፉ የሚችለው በጉባኤው ከተገኙት የዕዳ ሰነድ ያገኙ በአብላጫው ድምፅ ሲደገፍ ነው፡፡

**2)** የዕዳ ሰነዶችን ወደ አክሲዮን መለወጥን ወይም በአንድ ቡድን ውስጥ በሚገኙ የዕዳ ሰነድ ያዦች መካከል ልዩነት የሚያደርጉ ሁኔታዎች መፍጠርን ከሚመለከተው በስተቀር በዚህ ህግ አንቀጽ 418 ውስጥ በተደነገጉት ጉዳች ላይ የሚሰጡ ውሳኔዎች በጉባኤው ከተገኙት የዕዳ ሰነድ ያዦች በሁለት ሶስተኛ ድምፅ መደገፍ አለባቸዉ፡፡

**3)** እያንዳንዱ የዕዳ ሰነድ ቢያንስ አንድ ድምፅ የመስጠት ሙብት የሚያሰጥ ሆኖ፤ የዕዳ ሰነዶቹ ለያዦቻቸው የሚያሰጡት ድምጽ የመስጠት ሙብት የዕዳ ሰነዶቹ ከጠቅላላው የብድር ገንዘብ ውስጥ ካላቸው የድርሻ መጠን ጋር የተመዛዘነ መሆን ይኖርበታል፡፡

## አንቀጽ 421 አንዳንድ ውሳኔዎችን በፍ/ቤት ስለማፀደቅ

**1)** በዚህ ህግ አንቀጽ 418 መሰረት የተሰጡ ውሳኔዎች ጉባኤ በተደረገ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ በማኅበሩ ወይም በዕዳ ሰነድ ያዦች ቡድን ወኪሎች ወይም እነርሱ በሌሉ ጊዜ በማንኛውም የዕዳ ሰነድ ያዥ ለፍርድ ቤት ቀርበው መጽደቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ውሳኔዎቹ በፍርድ ቤት ካልጸደቁ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

**2)** ውሳኔዎቹን የተቃወሙ ወይም በጉባኤው ያልተገኙ የዕዳ ሰነድ ያዦች ውሳኔው እንዳይፀድቅ መቃወም ይችላሉ፡፡

## አንቀጽ 422 የዕዳ ሰነድ ያዦች ቡድን ወኪሎች

**1)** የዕዳ ሰነድ ያዦች ቡድን በዚህ ሕግ አንቀጽ 419 ንዑስ አንቀጽ (1) እና (3) በተመለከተው ምልአተ ጉባኤ እንዲሁም በአንቀጽ 420 ንዑስ አንቀጽ (1) በተጠቀሰው የድምፅ ብልጫ መሰረት በጠቅላላ ጉባኤው በሚሾሙ በአንድ ወይም ከዚያ በላይ ወኪሎች ሊወከል ይችላል፡፡ ጉባኤው በማንኛውም ጊዜ ወኪሎችን ለመሻር ይችላል፡፡

**2)** ጉባኤው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው ምልዓተ ጉባኤና ድምፅ ብልጫ መሰረት የወኪሎችን ስልጣንና የሚከፈላቸውን የሥራ ክፍያ ይወስናል፡፡ ክፍያው የሚሸፈነውም በባለዕዳው ኩባንያ ይሆናል፡፡

**3)** ወኪሎች በአግባቡ በተጠራ የዕዳ ሰነድ ያዦች ጠቅላላ ጉባኤ ያልተሾሙ እንደሆነ እና አስቸኳይ በሆነ ጊዜ በባለዕዳው ኩባንያ ወይም ከጠቅላላ የዕዳ ሰነዶች አምስት በሙቶ የያዙ የዕዳ ሰነድ ያዦች ሲጠይቁ ፍርድ ቤት ወኪሎችን ለመሾም ወይም ለመተካት ይችላል፡፡

**4)** የዚህ ሕግ አንቀፅ **416** ንዑስ አንቀጽ **3** ድንጋጌ በዕዳ ሰነድ ያዦች ወኪል አሿሿም ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 423 የወኪሎች ስልጣን

በዕዳ ሰነድ ያዦች ጠቅላላ ጉባኤ በሌላ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር ወኪሎች የዕዳ ሰነድ ያዦች ቡድን የጋራ ጥቅም በሆኑ ጉዳዮች ላይ በቡድኑ ስም ከዚህ በታች የተመለከቱትን ለመፈጸም ስልጣን ይኖራቸዋል፡-

**1)** ማንኛዉንም የአስተዳደር ስራ የመፈፀም በተለይም ለብድሩ የተሰጡ ዋስትናዎችን የመቀበልና የመጠበቅ፤

**2)** ቡድኑን በፍርድ ቤት ወይም በማንኛውም ሌላ የዳኝነት አካል የመወከል፣

**3)** በማኅበሩ ባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ላይ የመገኘት፤

**4)** የዕዳ ሰነዶችን ለመክፈል በሚደረግ የዕጣ አወጣጥ ስርአት ላይ የመገኘት፡፡

**አንቀጽ 424 ባለዕዳው ማኅበር በከሰረ ጊዜ ወኪሎች ስላሉባቸው ግዴታዎች**

**1)** ባለዕዳው ማህበር መክሰሩ በፍርድ በተወሰነ ወይም የመጠበቂያ ስምምነት በተደረገ ጊዜ የማኅበሩ ዕዳ ያገኙ ቡድን ወኪል ተሹሞ እንደሆነ በቡድኑ ለታቀፉ ሁሉ የባለመብትነታቸውን ማስረጃ ያቀርባል፡፡ እንዲሁም በስማቸው የተላኩ የጥሪ ማስታወቂያዎችን ይቀበላል፡፡

**2)** የዕዳ ሰነድ ያገኙ ወኪል በዕዳ ሰነድ ያገኙ ጠቅላላ ጉባኤ ድምፅ እንዲሰጥ የተወከለ እንደሆነ በኪሳራ ሕግ መሠረት የማኅበሩ ገንዘብ ጠያቂዎች በሚያደርጉዋቸው ጉባዔዎች ላይ የዕዳ ሰነድ ያገኙችን ወክሎ ድምፅ መስጠት ይችላል፡፡ ለማኅበሩ ገንዘብ ጠያቂዎች ምልዓተ ጉባኤና የአብላጫ ድምጽ አቆጣጠር በአንድ ቀን የወጡ የዕዳ ሰነዶች እንደ አንድ ዕዳ ይቆጠራሉ፡፡

**ምዕራፍ ሰባት**

**ስለማኅበሩ ሂሳቦች**

**አንቀጽ 425 ጠቅላላ ድንጋጌዎች**

1) ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት መመዘኛዎች ወይም ሌሎች የሒሳብ አያያዝ መመዘኛዎች ተፈጻሚ እንዲሆኑ የሚደነግጉ ሕጎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፤ የዚህ ምዕራፍ ድንጋጌዎች በአክሲዮን ማኅበራት ላይ ተግባራዊ መደረግ አለባቸው፡፡

2) በሌላ ሕግ በተለየ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር ስለሒሳብ መዛግብት አያያዝ እና አጠባባቅ በዚህ ሕግ መጽሐፍ አንድ ስር የተመለከቱት ድንጋጌዎች በአክሲዮን ማኅበር ሒሳቦች ላይም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

**አንቀጽ 426 ሂሳቦች እና ዓመታዊ ሪፖርት**

**1)** በየሒሳብ ዓመቱ መዝጊያ የዳይሬክተሮ ቦርድ ማኅበሩ ያሉትን ሀብቶች የንብረት ዝርዝር እንዲሁም የሀብትና ዕዳ መግለጫ ማዘጋጀት አለባቸው፡፡

**2)** ዳይሬክተሮች የሀብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫ፣ የትርፍ እና ኪሳራ መግለጫ እንዲሁም ባለፈው የሂሳብ ዓመት የነበረውን የማኅበሩን ሁኔታ እና እንቅስቃሴ በተመለከተ ሪፖርት ማዘጋጀት አለባቸው፡፡

**3)** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (**2)** ስር የተመለከተው ሪፖርት ዝርዝር የትርፍና ኪሳራ መግለጫ፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን፣ ካሉ የተቆጣጣሪ ቦርድ አባላትን እና የኦዲተሮችን ጠቅላላ የክፍያ መጠን የሚያመለክት መግለጫ፣ ስለትርፍ አከፋፈል የቀረበ ሀሳብ ካለ ይህንኑ ማካተት ይኖርበታል፡፡

**አንቀጽ 427 የሒሳብ ሰነዶችን እና ሪፖርቶችን ስለመስጠት**

ለጠቅላላ ጉባኤው ጥሪ ከሚደረግበት ቢያንስ ከ40 ቀናት በፊት የማኅበሩ የንብረት ዝርዝር፣ የሀብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫ፤ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ እና የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት ለኦዲተሮች እና ለንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም ካለ አግባብነት ላለው ሌላ የመንግስት መስሪያቤት መተላለፍ ይኖርበታል፡፡

**አንቀጽ 428 የሀብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫ እና የትርፍና ኪሳራ መግለጫ ስለሚዘጋጅበት ሁኔታ**

1) ጠቅላላ ጉባኤው በኦዲተሮች የቀረበለትን ሪፖርት መሠረት በማድረግ በሌላ ሁኔታ እንዲሰራ ካልወሰነ በስተቀር በየዓመቱ የሚዘጋጀው የሀብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫ እና የትርፍና ኪሳራ መግለጫ አዘገጃጀት፣ አቀራረብና የስሌት ዘዴ ቀደም ባሉት ዓመታት የነበረውን አሰራር የተከተለ እና የማይለወጥ መሆን ይኖርበታል፡፡

2) የትርፍና ኪሳራ መግለጫው ከማኅበሩ ልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎች የመነጩትን ትርፎች ወይም ኪሳራዎች በተለየ ርዕስ ስር ማሳየት ይኖርበታል፡፡

**<u>አንቀጽ 429 ሰለ አባሪዎች</u>**

እንደ ዋስትና የመሳሰሉት በሃብትና ዕዳ ሒሳብ መግለጫ የማይታዩ የግዴታ ውሎች ከማኅበሩ የሃብትና ዕዳ መግለጫ ሒሳብ ጋር አባሪ ተደርገው መያያዝ ይኖርባቸዋል፡፡

**<u>አንቀጽ 430 የአላቂ ንብረቶች መተኪያ ገንዘብና የእርጅና ቅናሽ</u>**

1) ጠቅላላ የመጠቀሚያ ጊዜያቸውን የጨረሱ ንብረቶችን ከማኅበሩ ሀብትነት ለመሰረዝ እንዲቻል ለንብረቶቹ መተኪያ ገንዘብ በየአመቱ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡ በየዓመቱ ታስቦ ተቀማጭ የሚሆነው የመተኪያ ገንዘብ መጠን የማይበቃ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ከዕቃው እርጅና ጋር ተመጣጣኝ እንዲሆን መጠኑ ከፍ ማለት ይኖርበታል፡፡

2) ትርፍ ባይኖርም እንኳ በእያንዳንዱ የሂሳብ ዓመት ማለቂያ የማኅበሩ ንብረቶች መተኪያ ገንዘብ እና የዕርጅና ቅናሽ ሒሳብ ተቀናሽ መሆን ይኖርበታል፡፡

3) የማኅበሩን ዋና ገንዘብ ለመሰብሰብ እና ለመጨመር የተደረጉ ወጪዎች ወጪ ከተደረጉበት ቀን አንስቶ እጅግ ቢዘገይ በአምስተኛው የሂሳብ ዓመት ማለቂያ መተካት ይኖርባቸዋል፡፡

**<u>አንቀጽ 431 የእናት ማኅበር ሂሳቦች</u>**

1) የተቀጥላ ማኅበር ሂሳቦች ለዓመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ የሚያቀርቡት የእናት ማኅበሩ ሂሳቦች በሚያቀርቡበት ጊዜ እና ሁኔታ ይሆናል፡፡

2) ለእናት ማኅበሩ እና ለተቀጥላዎቹ ማኅበራት አንድ የተጠቃለለ የሃብትና ዕዳ የሂሳብ መግለጫ እና የትርፍና ኪሳራ የሂሳብ መግለጫ መዘጋጀት አለበት፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (**2**) የተደነገገው ቢኖርም፤ የዳይሬክተሮች ቦርድ እንደዚህ አይነቱን ሰነድ ማዘጋጀት፡-

**(ሀ)** ሊሆን የማይችል ወይም እጅግ ከባድ ወይም ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ ወይም የየማኅበሩ የገንዘብ ጥቅም ዝቅተኛ ከመሆኑ የተነሳ ለባለአክሲዮኖች የማይጠቅም ከሆነ፤

**(ለ)** እናት ማኅበሩን ወይም ተቀጥላውን የሚጎዳ እና ተቀጥላ ማኅበሩ የሚያከናውነው ስራ የተለያየ ከመሆኑ የተነሳ እንደ አንድ አይነት ማኅበር የማይቆጠሩ እንደሆነና ይኸው ሀሳብ በንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚነስቴር

ወይም አግባብ ባለው የመንግስት አካል የፀደቀ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ **2** የተደነገገው ግዴታ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

## አንቀጽ 432 ስለትርፍ

1) የአንድ ማኅበር የተጣራ ትርፍ የሚባለው የማኅበሩ ጠቅላላ ወጪዎች እንዲሁም የአላቂ ንብረቶች መተኪያ ገንዘብና የእርጅና ቅናሽ ሒሳብ በሂሳብ ዓመቱ ከተገኘው ጠቅላላ ገቢ ከተቀነሰ በኋላ የሚገኘው ትርፍ ነው፡፡

2) የሚከፋፈል ትርፍ ከሂሳብ ዓመቱ ትርፍ ላይ የቀደምት ዓመታት ኪሳራዎች ከተቀነሱ በኋላ በሂሳብ ዓመቱ ትርፍ ላይ በፊት ታስበው ያልተከፋፈሉ ትርፎችን እና ሌሎች ተጨማሪ ገቢዎችን እና በልዩ ሁኔታ ጠቅላላ ጉባኤው ከመጠባበቂያ ገንዘብ እንዲከፈል የፈቀደውን ማንኛውንም ገንዘብ በመጨመር የሚገኝ ትርፍ ነው፡ ፡

3) የጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔም ለትርፍ ተከፋይ የሚሆኑት ገንዘቦች ከየትኛው የመጠባበቂያ ገንዘብ ላይ እንደሚወሰዱ ማመልከት ይኖርበታል፡፡

## አንቀጽ 433 ስለመጠባበቂያ ገንዘብ

1) በትርፍና ኪሳራ ሒሳብ መግለጫ ላይ ከተመለከቱት የተጣሩ ትርፎች ላይ ወደ መጠባበቂያ ገንዘብ ዝውውር ይደረጋል፡፡

2) መጠባበቂያ ገንዘብ የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

**(ሀ)** በሕግ እንዲቀመጥ የተወሰነ መጠባበቂያ ገንዘብ፤

**(ለ)** በማኅበሩ የመመስረቻ ጽሑፍ መሠረት በመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ የተወሰነ የመጠባበቂያ ገንዘብ፤

**(ሐ)** በማኅበሩ የመመስረቻ ጽሁፍ መሰረት ጠቅላላ ጉባኤ እንዲያቋቁም የተፈቀደለት አስገዳጅ ያልሆነ የመጠባበቂያ ገንዘብ፤

**(መ)** በሕግ ወይም በማኅበሩ የመመስረቻ ጽሑፍ ከተመለከተው ውጭ በመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤው የተወሰነ ነፃ የመጠባበቂያ ገንዘብ፡፡

## አንቀጽ 434 በህግ የተወሰነ የመጠባበቂያ ገንዘብ

1) በሌላ ሕግ የተለየ መጠን ካልተወሰነ በስተቀር፤ ከማኅበሩ የተጣራ ትርፍ አምስት በመቶ በየዓመቱ በሕግ ወደተወሰነው መጠባበቂያ ገንዘብ መዛወር ይኖርበታል፡፡ ሆኖም ወደ መጠባበቂያው የተዛወረው ገንዘብ መጠን የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አምስት በመቶ ላይ ሲደርስ የማዛወሩ ተግባር አስገዳጅነት ይቀራል፡፡

2) በማንኛውም ምክንያት በሕግ የተወሰነው የመጠባበቂያ ገንዘብ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) ከተመለከተው መጠን ዝቅ ያለ እንደሆነ ወደዚያው መጠን እንዲመለስ ገንዘብ የማዛወር ግዴታ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 435 አክሲዮንን ከዋጋው በላይ በማውጣት ስለሚቋቋም መጠባበቂያ ገንዘብ

1) የማኅበሩ ዋና ገንዘብ እንዲጨመር የወሰነው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ  አዲስ የሚሸጡት አክሲዮኖች ከተጻፈባቸው ዋጋ (ፓር ቫልዩ) በላይ በሆነ ገንዘብ እንዲሸጡ የወሰነ እንደሆነ በአክሲዮኖቹ ላይ የተጻፈው ዋጋ (ፓር ቫልዩ) እና በተጨባጭ አክሲዮኖቹ የተሸጡበት ዋጋ ልዩነት ወደ የመጠባበቂያ ገንዘብ እንዲዛወር ሊወስን ይችላል፡፡
2) በማንኛዉም ሁኔታ ቢሆን ከዚህ የመጠባበቂያ ገንዘብ ተካፋዮች መሆን የሚችሉት አዲሶቹ አክሲዮኖች ከመሸጣቸው በፊት ባለአክሲዮን የነበሩት ሰዎች ብቻ ይሆናሉ፡፡

**<u>አንቀጽ 436  የትርፍ አደላደልና አከፋፈል</u>**

1) የልዩ ሕግ ድንግጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በአንቀጽ **434** የተመለከተው መጠን ከተጣራው ትርፍ ላይ ወደ መጠባበቂያ ገንዘብ ከተዛወረ በኋላ ቀሪው በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ መሰረት ይከፋፈላል፡፡
2) ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የሚሰጥ ክፍያ በዚህ ሕግ አንቀጽ **304** መሠረት ተፈጻሚ ይናል፡፡

**<u>አንቀጽ 437  የተወሰኑ ወይም በየጊዜው የሚሰጡ ወለዶች</u>**

1) ማኅበሩ ዓመታዊ ትርፍ ባይኖረውም የተወሰነ ወይም በየጊዜው የሚሰጥ ወለድ ለባለአክሲዮኖች ይከፈላል ተብሎ በመስረቻ ጽሑፍ ሊወሰን ይችላል፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (**1**) መሠረት ለባለአክሲዮኖች ወለድ የሚከፈለው ማኅበሩ መደበኛ ሥራውን ለማከናወን የሚያስችል ዝግጅት በሚያደርግበት ጊዜ ዋና ገንዘቡ በባንክ በመቀመጡ በተገኘው ወለድ መጠን ብቻ ይሆናል፡፡ ማኅበሩ መደበኛ ሥራውን እንደጀመረ ለባለአክሲዮኖች ይከፈል የነበረው ወለድ ወዲያውኑ ቀሪ ይሆናል፡፡
3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (**1**) መሠረት ኩባንያው ለባለአክሲዮኖች ወለድ እንዲከፍል በመመስረቻ ጽሑፍ በግልጽ ካልተወሰነ በስተቀር፤ ማኅበሩ ለባለአክሲዮኖች ወለድ አይከፍልም፡፡

**<u>አንቀጽ 438 የትርፍ ድርሻ ክፍያና የባለአክሲዮኖች መብት</u>**

1) ለባለአክሲዮኖች የትርፍ ድርሻ የሚከፈለው በጸደቀው የማኅበሩ የሀብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫ ላይ ከተመለከተው የተጣራ ትርፍ ላይ ብቻ ይሆናል፡፡
2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌን በመተላለፍ የተከፋፈለ የትርፍ ድርሻ እንደ ሀሰተኛ ትርፍ ይቆጠራል፡፡ እንዲከፈል ያደረጉ ሰዎችም በወንጀልና በፍትሐብሔር ኃላፊ ይሆናሉ፡፡
3) ጠቅላላ ጉባዔው ትርፍ እንዲከፋፈል በሚወስንበት ጊዜ የትርፍ ድርሻ የሚከፈልበትን ዘዴ እና የትርፍ ድርሻ ለባለአክሲዮኖች የሚሰጥበትን ቀን በግልጽ ማመልከት አለበት፡፡ ሆኖም የትርፍ ድርሻ የሚከፈልበት ቀን በማናቸውም ሁኔታ የትርፍ ድርሻ እንዲከፋፈል ከተወሰነበት ቀን ጀምሮ ከአራት ወራት መብለጥ የለበትም፡፡
4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ከማብቃቱ በፊት ባለው ጊዜ ውስጥ ጠቅላላ ጉባኤው የፊተኛው ጠቅላላ ጉባኤ ስለ ትርፍ ድርሻ ወይም የመጠባበቂያ ገንዘቦች ክፍፍል የሰጠውን ውሳኔ በበቂ ምክንያት ለማሻሻል ወይም ለመሻር ይችላል፡፡

**5)** የትርፍ ድርሻ እንዲከፈልበት ከተቆረጠው ቀን ጀምሮ አንድ ባለአክሲዮን በሚደርሰው የትርፍ ድርሻ መጠን የማኅበሩ አበዳሪ እንደሆነ ይቆጠራል፡፡

**<u>አንቀጽ 439 የተከፈሉ የትርፍ ድርሻዎች እንዲመለሱ መጠየቅ የማይቻል ስለመሆኑ</u>**

ማኅበሩ በቤተ ዘመድ የተያዘ ወይም የትርፍ ድርሻ ክፍፍሉ የተፈፀመው የሀብትና የዕዳ ሂሳብ መግለጫ ሳይኖር ወይም በአግባቡ የፀደቀን የሀብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫ መሰረት ሳይደረግ ካልሆነ በስተቀር፤ የዚህን ህግ አንቀጽ **438** ድንጋጌዎችን በመጣስ የተከፋፈለን የትርፍ ድርሻ ባለአክሲዮኖች እንዲመልሱ መጠየቅ አይቻልም፡፡

**<u>አንቀጽ 440 የሀብትና የዕዳ ሂሳብ መግለጫን የማጽደቅ ውጤት</u>**

የማኅበሩ የሀብትና የዕዳ ሂሳብ መግለጫ በጉባኤው መጽደቁ ዳይሬክተሮችን፣ የተቆጣጣሪ ቦርድ ካለ አባላቱን፣ ኦዲተሮችን፣ ስራ አስኪያጆችን፣ የማኅበሩን ፀሐፊ እና ሌሎች ኃላፊዎችን በማኅበሩ ከነበረባቸው ኃላፊነት ጋር በተያያዘ ከሚኖርባቸው ተጠያቂነት ነፃ ሊያያደርጋቸው አይችልም፡፡

**<u>አንቀጽ 441 የሀብትና የዕዳ ሂሳብ መግለጫን በማስታወቂያ ስለማውጣት</u>**

የፀደቀው የማኅበሩ የሀብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫ አንድ ቅጅ እንዲሁም ጉባኤው መግለጫውን ያፀደቀበት ውሳኔ ቃለጉበዔ አግባብ ያለው ክፍል የሃብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫው በጸደቀ በሠላሳ ቀናት ውስጥ ለንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም አግባብ ላለው የመንግስት አካል መላክ እና በማህበሩ ድረገጽ ላይ ማውጣት አለበት፡፡

**<u>ምዕራፍ ስምንት</u>**

**<u>የማኅበሩን ዋና ገንዘብ ስለማሳደግና ስለመቀነስ</u>**

**<u>ክፍል አንድ</u>**

**<u>የማኅበሩን ዋና ገንዘብ ስለማሳደግ</u>**

**<u>አንቀጽ 442 የማኅበሩን ዋና ገንዘብ ማሳደጊያ መንገዶች</u>**

**1)** የማህበሩ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ሳይፈቅድ የማህበሩን ዋና ገንዘብ ማሳደግ አይቻልም፡፡

**2)** የማህበሩን ዋና ገንዘብ አዲስ አክሲዮኖችን በማውጣት ወይም የነባር አክስዮኖችን ዋጋ በመጨመር ለማሳደግ ይቻላል፡፡ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ዋና ገንዘቡን ለማሳደግ ሲወስን የሚያድግበትንም መንገድ አብሮ መወሰን አለበት፡፡

**3)** የአዲስ አክሲዮኖች ዋጋ በሚከተሉት መንገዶች ሊከፈል ይችላል፡-

**(ሀ)** በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት፤

**(ለ)** ማኅበሩ ያሉበትን የመክፍያ ጊዜያቸው የደረሰ ዕዳዎች በአክሲዮን በማቻቻል፤

**(ሐ)** መጠባበቂያ ወይም ማኅበሩ ሊያዝባቸው የሚችሉ ሌሎች ገንዘቦችን ወደ ዋናው ገንዘብ በመጨመር፤ ወይም

**(መ)** የዕዳ ሰነዶችን ወደ አክሲዮን በመለወጥ፡፡

**4)** የማኅበሩ ዋና ገንዘብ እንዲያድግ የተደረገው ከመጠባበቂያ ገንዘብ ወይም ለባለአክሲዮኖች ሊከፋፈል ከሚችል ትርፍ ላይ በማንሳት ካልሆነ በስተቀር፤ የነባር አክሲዮኖችን ዋጋ በመጨመር ዋና ገንዘቡን ለማሳደግ የሚቻለው በዚህ ህግ አንቀፅ 402 ንዑስ አንቀጽ (3) በተደነገገው ሁኔታ ብቻ ነው፡፡

## አንቀጽ 443 ለዳይሬክተሮች ቦርድ ስልጣን ስለመስጠት

**1)** የዚህ ሕግ አንቀጽ 442(1) እና (2) እንደተጠበቀ ሆኖ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤው የማኅበሩን ዋና ገንዘብ ለማሳደግ ወይም ለመቀነስ የሰጠውን ውሳኔ ተግባራዊ እንዲያደርግ አስፈላጊውን ስልጣን ለዳይሬክተሮች ቦርድ መስጠት ይችላል፡፡

**2)** የዳይሬክተሮች ቦርድ የማኅበሩን ዋና ገንዘብ እንዲያሳድግ ወይም እንዲቀንስ አስቀደሞ የሚፈቅድ የመመስረቻ ጽሑፍ ድንጋጌ ዋጋ አይኖረውም፡፡

## አንቀጽ 444 የማኅበሩን ዋና ገንዘብ የማሳደግ ውሳኔ ተግባራዊ ስለሚሆንበት ጊዜ

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ የሚያድገው የዕዳ ሰነዶችን ወደ አክሲዮኖች በመለወጥ ካልሆነ በስተቀር ጠቅላላ ጉባኤው ዋና ገንዘቡ እንዲያድግ ከወሰነበት ወይም ከፈቀደበት ጊዜ አንስቶ በ5 (አምስት) ዓመታት ውስጥ ተግባራዊ ካልሆነ ውሳኔው ዋጋ አይኖረውም፡፡

## አንቀጽ 445 አዲስ አክሲዮኖችን ከማውጣት በፊት ዋና ገንዘቡን ከፍሎ ስለማጠናቀቅ

ዋና ገንዘቡ ሙሉ በሙሉ ያልተከፈለ ማኅበር በጥሬ ገንዘብ ወይም የዕዳ ሰነዶችን ወደ አክሲዮን በመለወጥ የሚከፈሉ አዲስ አክሲዮኖችን በማውጣት ዋና ገንዘቡን ማሳደግ አይችልም፡፡

## አንቀጽ 446 አዲስ አክሲዮኖች ስለሚወጡበት ሁኔታ

ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በስተቀር አዲስ አክሲዮኖችን ለማውጣት የሚቻለው ማኅበሩ ስለሚቋቋምበት ሁኔታ በተመለከቱት አግባብ ባላቸው ድንጋጌዎች መሰረት ነው፡፡

## አንቀጽ 447 አክሲዮኖችን እንዲገዛ ሕዝብን ስለመጋበዝ

አዲስ አክሲዮኖችን ለሕዝብ ለመሸጥ የሚደረገው ጥሪ የማኅበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ በፈረመበት መግለጫ አማካይነት ሆኖ መግለጫውም የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ ይኖርበታል፡-

**1)** የማኅበሩን ስምና ዋና መስሪያ ቤት፤

2) ማኅበሩ በንግድ መዝገብ የተመዘገበበትን ቀን፤

3) የማኅበሩን ዋና ገንዘብ መጠን፤ የአክሲዮኖቹን ዓይነትና አክሲዮኖቹ ላይ የተፃፈውን ዋጋ እና ካሉም ልዩ መብት የሚያሰጡ የአክሲዮኖን መደቦች፤

4) የማህበሩን ዳይሬክተሮች፣ ካሉም የተቆጣጠሪ ቦርድ አባላት፣ ሥራ አስኪያጆች እና ኦዲተሮች፤

5) የመጨረሻውን የትርፍና ኪሳራ እንዲሁም የሀብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫ እና የኦዲት ሪፖርት፤

6) ባለፉት የመጨረሻ አምስት ዓመታት ወይም ማህበሩ ከአምስት ዓመታት ያነሰ ቆይታ ያለው እንደሆነ ማኅበሩ ከተመሰረተበት ቀን ጀምሮ የተከፈሉትን የትርፍ ድርሻዎች፤

7) ማኅበሩ ያወጣቸዉን የዕዳ ሰነዶች፤

8) አዲስ የወጡ አክሲዮኖችን አስመልክቶ ጉባኤው ያስተላለፈውን ውሳኔ በተለይ አዲሶቹ አክሲዮኖች ያላቸውን ጠቅላላ ዋጋ፣ ቁጥራቸዉን፣ የተጻፈባቸውን ዋጋ፣ ዓይነታቸውንና የሚወጡበትን ዋጋ፤

9) በዓይነት የተደረጉ መዋጮዎችን እና የተሰጡ ልዩ ጥቅሞችን፤

10) አዲሶቹ አክሲዮኖች ትርፍ ማስከፈል የሚጀምሩበትን ጊዜ፣ የተጣሉባቸውን ገደቦች፣ እንዲሁም የተሰጡ ልዩ መብቶችን፤

11) አክሲዮን ለመግዛት የፈረመው ሰው ግዴታ የሚቆይበትን ጊዜ፡፡

**<u>አንቀጽ 448 አክሲዮኖችን የመግዛት ቅድሚያ መብት</u>**

1) ባለአክሲዮኖች በኩባንያው ውስጥ ባላቸዉ የአክሲዮን መጠን አዲስ አክሲዮኖችን የመግዛት የቅድሚያ መብት ይኖራቸዋል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን መብት የአክሲዮኑ ግዢ ክፍት ሆኖ በሚቆይበት ጊዜ አክሲዮኖች ስለሚተላለፉበት ሁኔታ በተደነገጉት ጠቅላላ ድንጋጌዎች መሰረት ለመሸጥ ወይም ለማስተላለፍ ይቻላል፡፡

3) የዕዳ ሰነዶች በአክሲዮን የሚለወጡ ከሆነ የቀደምትነት መብቱ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባዔ በያዦቹ ምርጫ ወደ አክሲዮን ሊቀየሩ የሚችሉ የዕዳ ሰነዶች እንዲወጡ ሲወስን ባለአክሲዮኖች የቀደምትነት መብታቸውን መተዋቸውን ማመልከት ይኖርበታል፡፡

**<u>አንቀጽ 449 ያልተገዙ አክሲዮኖችን የመግዛት መብት</u>**

በዚህ ሕግ አንቀጽ 448 ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ አዲሶቹ አክሲዮኖች ለመግዛት የቀደምትነት መብት ባላቸዉ ባለአክሲዮኖች ያልተገዙ እንደሆነ አክሲዮኖቹን በቀደምትነት ለመግዛት ከሚችሉት በላይ ጠይቀው ለነበሩት ሌሎች ባለአክሲዮኖች በማኅበሩ ዋና ገንዘብ ውስጥ ባላቸዉ ድርሻ መጠንና ባቀረቡት ጥያቄ ወሰን ውስጥ ይደለደሉላቸዋል፡፡

**<u>አንቀጽ 450 ቀሪዎችን አክሲዮኖች ስለማከፋፈል</u>**

በዚህ ሕግ አንቀጽ 448 እና 449 ድንጋጌዎች መሠረት የማህበሩን ዋና ገንዘብ ለማሳደግ የወጡት አዲስ አክሲዮኖች በሙሉ ያልተሸጡ የሆነ እንደሆነ ያልተሸጡት አክሲዮኖች በአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ መሰረት የማህበሩ አባላት ላልሆኑ ሰዎች ሊሸጡ ይችላሉ ፡፡

**አንቀጽ 451 በቀደምትነት መብት ላይ የሚደረግ ገደብ**

1) የማኅበሩ ዋና ገንዘብ እንዲያድግ የሚወስነው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ በዚህ ሕግ አንቀጽ **448፣ 449** እና **450** የተደነገጉት ሁኔታዎች በሙሉ ወይም በከፊል ተፈፃሚ እንዳይሆኑ ለማድረግ የሚችለው፡-

   **(ሀ)** የማኅበሩ ዋና ገንዘብ እንዲያድግ እና የቀደምትነት መብት እንዲቀር ያስፈለገበትን ምክንያት፣ አዲሶቹን አክሲዮኖች የሚከፋፈሏቸዉ ባለአክሲዮኖች እና ለእያንዳንዳቸው የሚደርሳቸውን የአክሲዮን ብዛት፣ የወጡበትን ዋጋ እና ዋጋው የተወሰነበትን መነሻ የሚገልጽ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት፤ እና

   **(ለ)** የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርትን ትክክለኛነት የሚያረጋግጥ የኦዲተሮችን

   ሪፖርት፤

ከመረመረ በኋላ ይሆናል፡፡

2) አዲስ አክሲዮኖችን የሚከፋፈሉ ሰዎች ለነሱ ጥቅም ሲባል በዚህ ሕግ ከአንቀጽ 448 እስከ 450 የተመለከቱ ድንጋጌዎችን ተፈፃሚነት ቀሪ በሚያደርግ ጉባኤ ላይ ድምጽ መስጠት አይችሉም፡፡
3) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት ለሚሰጠው ውሳኔ የሚያስፈልገው ምልዓተ ጉባኤና የድምፅ ብልጫ የሚሰላው አዲሶቹን አክሲዮኖች በመግዛት የሚከፋፈሉ ሰዎች ያሏቸዉን ወይም የወከሏቸውን አክሲዮኖች ሳይጨምር የማኅበሩን ዋና ገንዘብ በሚሸፍኑት አክሲዮኖች መሰረት ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 452 በአክሲዮን የሚለወጡ የዕዳ ሰነዶችን ስለማውጣት**

1) በአክሲዮን የሚለወጡ የዕዳ ሰነዶችን ለማውጣት በቅድሚያ የአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤውን ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚሰጠው ፈቃድ ባለአክሲዮኖች በአክሲዮን የሚለወጡ የዕዳ ሰነዶችን በተመለከተ የቀደምትነት መብታቸውን ለዕዳ ሰነዶቹ ያገኙ ጥቅም ሲባል የሰጡ ስለመሆኑ መግለጫ መያዝ ይኖርበታል፡፡
3) እንዲህም በሆነ ጊዜ በዚህ ህግ አንቀጽ 451 ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ) የተመለከተው የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት በአክሲዮን የሚለወጡ የዕዳ ሰነድ ያገኙ የቀረበላቸዉን ምርጫ ለመጠቀም የሚችሉበትን ጊዜ እንዲሁም የዕዳ ሰነዶቹ ወደ አክሲዮኖች የሚለወጡበትን ሁኔታ ማመልከት ይኖርበታል፡፡
4) ኦዲተሮች የዕዳ ሰነዶቹ ወደ አክሲዮን የሚለውጡበትን ሁኔታ በተመለከተ ለአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤው በቀረቡ ሀሳቦች ላይ ልዩ ሪፖርት ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡

**አንቀጽ 453 አክሲዮኖችን ለመግዛት ልዩ የቀደምትነት መብት የሚሰጡ ጽሁፎችን ማውጣት ስለመከልከል**

በማናቸውም ሁኔታ የማህበሩን ዋና ገንዘብ ለማሳደግ የሚወጡ አክሲዮኖችን ለመግዛት ልዩ የቅድሚያ መብት የሚያሰጥ ማንኛውንም ዓይነት ሰነድ ማውጣት አይቻልም፡፡

**አንቀጽ 454 አክሲዮን በቅደሚያ ለመግዛት ለባለአክሲዮኖች የሚሰጠው ጊዜ**

ለነባር ባለአክሲዮኖች አክሲዮኖችን ለመግዛት የሚሰጣቸው ጊዜ ማኅበሩ አዲስ አክሲዮኖችን ለሽያጭ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ ከ30 ቀናት ሊያንስ አይችልም፡፡

**አንቀጽ 455 አክሲዮን የመግዛት ጥሪ ስለማድረግ**

1) አዲሶቹን አክሲዮኖች መግዛት የሚጀመርበት ቀን ቢያንስ ግዥ ከሚጀመርበት ከ10 (አስር) ቀናት አስቀድሞ አገር አቀፍ ስርጭት ባለው ጋዜጣ እና አመቺ በሆነ የኤሌክትሮኒክስ ዘዴ አማካኝነት ባለአክሲዮኖች እንዲያውቁት መደረግ አለበት፡፡ ማስታወቂያው የባለአክሲዮኖቹን የቀደምነት መብት፣ አዲስ አክሲዮኖችን መግዛት የሚጀመርበትንና የሚያልቅበትን ቀን፣ አክሲዮኖች የሚወጡበትን ዋጋ እና ወዲያውኑ ተከፋይ መሆን የሚገባውን የአክሲዮን ዋጋ መጠን መግለጽ ይኖርበታል፡፡
2) አክሲዮኖቹ በስም የተመዘገቡ ከሆነ ማኅበሩ የአክሲዮን ሽያጭ ከመጀመሩ አስር ቀናት በፊት ማስታወቂያውን በተመዘገበ ደብዳቤ ለባለአክሲዮኖቹ መላክ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 456 አዲስ አክሲዮኖችን ለመግዛት ስለመፈረም**

1) አዲስ አክሲዮኖችን ለመግዛት መፈረም ዋጋ የሚኖረው ተከፋይ መሆን የሚገባው ገንዘብ አብሮ ከቀረበ ብቻ ይሆናል፡፡
2) የማኅበሩ ዋና ገንዘብ በገንዘብ የሚሸጡ አክሲዮኖችን በማውጣት የሚያድግ ከሆነ በዚህ ሕግ አንቀጽ 267 እስከ 268 ስር የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደአግባቡ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

**አንቀጽ 457 አክሲዮን ለመግዛት መፈረምን ስለማስታወቅ**

የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚከተሉትን ማረጋገጥና በሰነድ እንዲያዙ ማድረግ አለበት፡-

1) አዲስ አክሲዮኖች በሙሉ ለመገዛት መፈረማቸውን፤
2) ከአክሲዮኖቹ ዋጋ መከፈል ያለበት ገንዘብ መከፈሉን፤
3) እንዲጨመር የተወሰነው የማኅበሩ ዋና ገንዘብ በሙሉ መጨመሩን፤እና
4) በተጨመረው የማኅበሩ ዋና ገንዘብ መሠረት የመመስረቻ ጽሑፉ መሻሻሉን፡፡

**አንቀጽ 458 በዓይነት በሚደረግ መዋጮ የማኅበሩን ዋና ገንዘብ ስለማሳደግ**

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ ለማሳደግ የዓይነት መዋጮ የሚከፈል ከሆነ ወይም ልዩ ጥቅሞች ያሉበት እንደሆነ የዚህ ሕግ አንቀጽ 260፣ 261 እና 263 ድንጋጌዎች እንደአግባቡ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

**<u>አንቀጽ 459 የአዲስ አክሲዮኖችን ዋጋ ዕዳን በማቻቻል ስለመክፈል</u>**

1) የማኅበሩን ዋና ገንዘብ ለማሳደግ የወጡ አዲስ የጥሬ ገንዘብ አክሲዮኖች ዋጋ አክሲዮን ለመግዛት መፈረም በተጀመረበት ቀን የመክፈያ ጊዜያቸው በደረሱ የማኅበሩ ዕዳዎች በማቻቻል ሊከፈል ይችላል፡፡
2) አክሲዮኖቹ በዕዳ ማቻቻል መከፈላቸውን የሚያሳይ የሂሳብ መግለጫ በዳይሬክተሮች ቦርድ መዘጋጀትና በኦዲተሮች መረጋገጥ አለበት፡፡ ኦዲተሮቹም በማቻቻል የተከፈለውን ዕዳ መጠን የሚያሳይ ሪፖርት ማዘጋጀት አለባቸው፡፡

**<u>አንቀጽ 460 የመጠባበቂያ ገንዘብ በመጨመር ዋና ገንዘብን ስለማሳደግ</u>**

በዚህ ሕግ አንቀፅ 434 ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ የማህበሩን መጠባበቂያ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ወደ ዋና ገንዘብ በማዛወር የማህበሩን ዋና ገንዘብ ማሳደግ ይችላል፡፡ ሆኖም በሕግ የተወሰነው የመጠባበቂያ ገንዘብ ወደ ማኅበሩ ዋና ገንዘብ እንዲገባ ከተደረገ የቀድሞው በሕግ የተወሰነው መጠባበቂያ ገንዘብ እንደገና እስኪሟላ ድረስ ለባለአክሲዮኖች ማንኛውንም ዓይነት ክፍፍል ማድረግ አይቻልም፡፡

**<u>አንቀጽ 461 የአክሲዮን ዋጋ ጥቂት በጥቂት መልሶ ስለመክፈል</u>**

1) ለባለአክሲዮኖች ለዋናው ገንዘብ ገቢ ያደረጉትን መዋጮ ወይም የአክሲዮን ዋጋ ጥቂት በጥቂት መልሶ ለመክፈል የሚቻለው በመመስረቻ ጽሑፉ በተደነገገው ወይም አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት ብቻ ይሆናል፡፡
2) ለዚህ ተግባር ሊውል የሚችለው ለባለአክሲዮኖች ሊከፈል የሚችል ትርፍ ወይም በዚህ ሕግ አንቀጽ 434 ንዑስ አንቀጽ (1) ከተመለከተው መጠባበቂያ ውጪ ከሆነ የመጠባበቂ ገንዘብ ነው፡፡
3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ተፈጻሚ የሚሆነው በአንድ መደብ ውስጥ የሚገኙ አክሲዮኖችን መልሶ በመግዛት ይሆናል፡፡ ተመልሰው የሚገዙት አክሲዮኖችም በዕጣ ሊመረጡ ይችላሉ፡፡ የዚህ አንቀጽ አፈጻጸም የዋና ገንዘብ መቀነስን ሊያስከትል አይገባም፡፡

**<u>ክፍል ሁለት</u>**

**<u>የማኅበሩን ዋና ገንዘብ ስለመቀነስ</u>**

**<u>አንቀጽ 462 የማኅበሩን ዋና ገንዘብ ለመቀነስ የሚቀርብ ሀሳብ</u>**

የማኅበሩን ዋና ገንዘብ ለመቀነስ የሚቀርብ ሀሳብ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የሚሰጠው ጠቅላላ ጉባኤ ከመጠራቱ ቢያንስ ከ15 ቀናት በፊት በዳይሬክተሮች ቦርድ አማካኝነት ለኦዲተሮች መቅረብ አለበት፡፡ ኦዲተሮችም ዋና ገንዘቡን መቀነስ ያስፈለገበት ምክንያት እና በአቀናነሱ ሁኔታ ላይ ያላቸውን አስተያየት ለጉባኤው ማቅረብ አለባቸው፡፡

**አንቀጽ 463 የማኅበሩ ዋና ገንዘብ ቅነሳን ስለማስታወቅ**

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ ቅነሳ ከተደረገ በንግድ መዝገብ መመዝገብ፣ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣና በማኅበሩ ድረገጽ መውጣት ይኖርበታል፡፡

**አንቀጽ 464 በኪሳራ ምክንያት የማኅበሩን ዋና ገንዘብ ስለመቀነስ**

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ በኪሳራ ምክንያት የተቀነሰ እንደሆነ በዚህ ሕግ ከአንቀጽ 465 እስከ 468 የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

**አንቀጽ 465 የዋና ገንዘብ አቀናነስ ዘዴዎች**

**1)** የማኅበሩን ዋና ገንዘብ መቀነስ የሚቻለው፡-

**(ሀ)** በአክሲዮኖች ላይ የተጻፈውን ዋጋ በመነቀስ፤ ወይም

**(ለ)** ነባር አክሲዮኖችን አነስተኛ ቁጥር ባላቸዉ አዲስ አክሲዮኖች በመለወጥ፤

ነው፡፡

**2)** የማኅበሩ ዋና ገንዘብ የሚቀነሰው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (1) (ለ) በተደነገገው መሠረት ከሆነ ነባር አክሲዮኖችን በአዲስ አክሲዮኖች ለመለወጥ የሚያስችል በቂ አክሲዮኖች የሌሏቸው ባለአክሲዮኖች ጉባኤው በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የጎደሉትን አክሲዮኖች ማሟላት ወይም የያዟቸዉን አክሲዮኖች ለሌሎች ባለአክሲዮኖች መሸጥ ይኖርባቸዋል፡፡

**አንቀጽ 466 ለባለአክሲዮኖች ሊጠበቁ የሚችሉ መብቶች**

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ እንዲቀነስ የሚወስነው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ማንኛውም ትርፍ ከመከፈሉ በፊት ባለአክሲዮኖች በተቀነሰባቸው የአክሲዮን ብዛት ወይም በአክሲዮኖች ላይ የተጻፈው ዋጋ መጠን ማካካሻ እንዲከፈላቸው ሊወስን ይችላል፡፡

**አንቀጽ 467 የገንዘብ ጠያቂዎች መብት**

የማኅበሩን ዋና ገንዘብ ለመቀነስ በአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ከመተላለፉ በፊት የማኅበሩ ገንዘብ ጠያቂዎች የነበሩ ሰዎች ገንዘቡ ካልተከፈላቸዉ ወይም በቂ ዋስትና ካልተሰጣቸው በስተቀር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ ማኅበሩ ባለዕዳ በሆነበት ጊዜ ወደነበረበት መጠን እስኪደርስ ድረስ በአንቀጽ 466 መሰረት የሚሰጥ ውሳኔን ወይም ማንኛውንም ዓይነት የትርፍ ክፍፍልን ለመቃወም ይችላሉ፡፡

**አንቀጽ 468 የማኅበሩ ዋና ገንዘብ በሕግ ከተወሰነው አነስተኛ መጠን በታች መቀነስ**

1) በኪሳራ ምክንያት የማኅበሩ ዋና ገንዘብ በአንቀጽ 247(1) ከተመለከተው አነስተኛ መጠን በታች ከሆነ የቀነሰው የዋና ገንዘቡ መቀነስ በዚህ ሕግ አንቀጽ 463 በተደነገገው መሰረት በንግድ መዝገብ ከተመዘገበበት ቀን አንስቶ ባለው 1 (አንድ) ዓመት ጊዜ ውስጥ ዋና ገንዘቡ ወደ አነስተኛ መጠን ማደግ ይኖርበታል፡፡
2) በዚህ ሕግ በአንቀጽ 467 ሥር የተመለከተው የገንዘብ ጠያቂዎች መብት አይነካም፡፡
3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው መሠረት ዋና ገንዘቡ ካልተስተካከለ ወይም ማኅበሩ ወደ ሌላ ዓይነት ማህበር እንዲለወጥ ካልተደረገ በስተቀር ማንኛውም ጥቅም ያለው ወገን ማኅበሩ እንዲፈርስ ለፍርድ ቤት ማመልከት ይችላል፡፡

<u>**አንቀጽ 469 ኪሳራ ሳይኖር የማኅበሩን ዋና ገንዘብ ስለመቀነስ**</u>

ከኪሳራ ውጭ በሆነ ሌላ ምክንያት የማኅበሩ ዋና ገንዘብ እንዲቀንስ የተደረገ እንደሆነ በዚህ ሕግ ከአንቀጽ 470 እስከ 472 የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

<u>**አንቀጽ 470 የባለአክሲዮኖች እኩልነት**</u>

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ መቀነስ የባለአክሲዮኖችን የእኩልነት መብት ሊያፋልስ አይችልም፡፡

<u>**አንቀጽ 471 የገንዘብ ጠያቂዎች መብት**</u>

1) የማኅበሩ ዋና ገንዘብ የመቀነስ ውሳኔ በዚህ ሕግ አንቀጽ 463 ድንጋጌ መሠረት በይፋ ከመገለጹና በንግድ መዝገብ ከመመዝገቡ በፊት በማኅበሩ ላይ መብት የነበራቸዉ ገንዘብ ጠያቂዎች ዋና ገንዘቡ ከአስር በመቶ በላይ በበሆነ መጠን እንዲቀንስ የተወሰነ እንደሆነ ውሳኔው አገር አቀፍ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በሶስት ወራት ጊዜ ውስጥ ለፍርድ ቤት ተቃውሞ ማቅረብ ይችላሉ፡፡
2) መቃወሚያው የቀረበለት ፍርድ ቤት መቃወሚያውን ወድቅ ለማድረግ ወይም ማኅበሩ ተቃውሞውን ላቀረቡ ገንዘብ ጠያቂዎች ገንዘባቸውን እንዲከፍላቸዉ ወይም በቂ ዋስትና እንዲሰጣቸዉ ሊያዝ ይችላል፡፡
3) የማኅበሩ ዋና ገንዘብ እንዲቀነስ የተላለፈው ውሳኔ ተግባራዊ የሚሆነው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ ነው፡፡

<u>**አንቀጽ 472 የማኅበሩን ዋና ገንዘብ ቅነሳ በቃለ ጉባኤ ስለመመዝገብ**</u>

1) የማኅበሩ ዋና ገንዘብ እንዲቀነስ ከተወሰነበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ውሳኔው በማኅበሩ የቃለ ጉባኤ መዝገብ መስፈር ይኖርበታል፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተዘጋጀው የውሳኔ ቃለ ጉባኤ በማኅበሩ ድረ ገጽ ላይ መውጣት አለበት፡፡

<u>**ምዕራፍ ዘጠኝ**</u>

<u>**ስለ ማኅበሩ መፍረስ እና ሒሳብ መጣራት**</u>

## አንቀጽ 473 ማኅበሩ የሚፈርስባቸዉ ምክንያቶች

**1)** በዚህ ሕግ አንቀጽ 181 የተመለከቱት ጠቅላላ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፤ የአክሲዮን ማኅበር በሚከተሉት ምክንያቶች ይፈርሳል፡-

**(ሀ)** የባለአክሲዮኖች ቁጥር በሕግ ከተፈቀደው ዝቅ ሲልና በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ሌላ አባል መተካት ባለመቻሉ ምክንያት ጥቅም አለኝ በሚል ሰው በቀረበ ማመልከቻ መሰረት የንግድ ማኅበራትን የሚመዘግበው አካል ማኅበሩ እንዲፈርስ ሲወስን፤

**(ለ)** የአስተዳደር አካላት የሌሉት በመሆኑ ምክንያት ጥቅም አለኝ በሚል ሰው ጠያቂነት የንግድ ማህበራትን የሚመዘግበው አካል ማኅበሩ እንዲፈርስ ሲወስን፤

**(ሐ)** ማኅበሩ የዋና ገንዘቡን ሶስት አራተኛ በኪሳራ ሲያጣ፡፡

**2)** የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ) እና (ለ) ድንጋጌዎች ቢኖሩም የንግድ ማኅበራት መዝጋቢው አካል አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የጊዜ ገደቡን ለተወሰነ ጊዜ እንዲራዘም ወይም ማኅበሩ የአስተዳደር አካላትን አሟልቶ ሥራ እንዲቀጥል ሊፈቅድ ይችላል፡፡

**3)** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሐ) እንደተመለከተው ማኅበሩ የዋና ገንዘቡን ሶስት አራተኛ በኪሳራ ያጣ እንደሆነ የዳሬክተሮች ቦርድ የማኅበሩን መፍረስ ወይም መቀጠል የሚወስን አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ መጥራት አለበት፡፡

**4)** የዳይሬክተሮች ቦርድ፣ ካለ የተቆጣጣሪ ቦርድ ወይም ኦዲተሮች ጠቅላላ ጉባኤ መጥራት ያልቻሉ እንደሆነ ጥቅም ባለው ሰው አመልካችነት ፍርድ ቤት ማኅበሩ እንዲፈርስ ሊወስን ይችላል፡፡

**5)** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተደነገገው መሠረት የንግድ ማኅበር መዝጋቢውን አካል ሳያስፈቅዱ ከስድስት ወራት በኋላ ባለአክሲዮኞች እያወቁ ማኅበሩ ሥራውን እንዲቀጥል ያደረጉ ከሆነ ካወቁበት ጊዜ ጀምሮ ማኅበሩ ለሚገባው ማንኛውም ዕዳ በአንድነትና በተናጠል ኃላፊ ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ 474 የማኅበሩን መፍረስ ስለማስታወቅ

**1)** በዚህ ሕግ መሠረት ማኅበሩ እንዲፈርስ በአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ወይም በፍርድ ቤት የተወሰነ እንደሆነ የመፍረሱ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ21 (ሃያ አንድ) ቀናት ውስጥ ማኅበሩ እንዲፈርስ ስለመወሰኑ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣና በማኅበሩ ድረ ገጽ በይፋ መገለጽ አለበት፡፡ ማስታወቂያውም "በመጣራት ላይ ያለ" የሚል ሀረግ ተጨምሮበት የማኅበሩን ስም፣ የዋና ገንዘቡን መጠን፣ የፈረሰበትን ምክንያት፣ የሒሳብ አጣሪውን ስምና አድራሻ እንዲሁም የስልጣን ወሰን መያዝ አለበት፡፡

**2)** ማኅበሩ እንዲፈርስ የተሰጠው ውሳኔ እና በውሳኔው መሠረት ሒሳብ አጣሪ መሾሙን የሚያመለክቱ ሰነዶች በማኅበሩ ዋና መስሪያ ቤት መቀመጥ እንዲሁም በንግድ መዝገብ መመዝገብ አለባቸው፡፡

## አንቀጽ 475 ሒሳብ አጣሪ ስለመሾምና ስለመሻር

1) ሂሳብ አጣሪዎች በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ ያልተሾሙ ከሆነ የማኅበሩን መፍረስ በወሰነው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ይሾማሉ፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው መሰረት ሒሳብ አጣሪዎች ያልተሾሙ ከሆነ በዳይሬክተሮች ቦርድ፣ በተቆጣጣሪ ቦርድ፣ በኦዲተሮች፣ በባለአክሲዮኖች ወይም በገንዘብ ጠያቂዎች አቤቱታ አቅራቢነት በፍርድ ቤት ይሾማሉ፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተሾሙ የሒሳብ አጣሪዎች በአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤው ሊሻሩ ይችላሉ፡፡ እንዲሁም በማንኛወም አካል ቢሾሙም ሒሳብ አጣሪዎችን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተጠቀሱት ሰዎች አመልካችነት በበቂ ምክንያት ፍርድ ቤት ሊሽራቸው ይችላል፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) በተደነገገው መሰረት ሒሳብ አጣሪዎችን የሻረው አካል አዲስ አጣሪዎችን መሾም አለበት፡፡

**<u>አንቀጽ 476 የሒሳብ አጣሪዎች ሥራ መልቀቅ</u>**

1) የማኅበሩ ሒሳብ አጣሪዎች ለሾማቸው አካል የሶስት ወራት የቅድሚያ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ሥራቸውን መልቀቅ ይችላሉ፡፡ አጣሪዎች የተሾሙት በጠቅላላ ጉባኤ ወይም በመመስረቻ ጽሑፍ ከሆነ ማስጠንቀቂያውን ለማኅበሩ ቦርድ ማቅረብ አለባቸው፡፡

2) ሂሳብ አጣሪዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው መሰረት የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሳይሰጡ ሥራቸውን የለቀቁ እንደሆነ በዚህ ምክንያት በማኅበሩ፣ በገንዘብ ጠያቂዎች ወይም በባለአክሲዮኖች ላይ ለሚደርሰው ጉዳት በአንድነትና በተናጠል ኃላፊ ይሆናሉ፡፡

**<u>አንቀጽ 477 ለሒሳብ አጣሪነት ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች</u>**

ሒሳብ አጣሪ ሆኖ መሾም የሚችለው ቀጥሎ የተመለከቱትን መስፈርቶች የሚያሟላ ሰው ነው፡-

1) መልካም ስነ-ምግባር ያለው፤

2) የሒሳብ ማጣራት ሥራ ለማከናወን አስፈልጊ የሆነ ሙያ ያለው፤

3) በንግድ ማኅበር አደራጅነት፣ ዳይሬክተርነት፣ ሥራ አስኪያጅነት፣ በተቆጣጣሪ ቦርድ አባልነት፣ በኦዲተርነት ወይም በሌሎች የአመራር ኃላፊነቶች ላይ ተመድቦ ሲሰራ ከኃላፊነቱ ጋር በተያያዘ ወይም በማንኛውም ሁኔታ የዕምነት ማጉደል፣ የስርቆት፣የውንብድና ወንጀል ወይም ለሂሳብ አጣሪነት ብቁ የማያደርግ ተመሳሳይ ወንጀል ፈፅሞ ጥፋተኛነቱ ያልተረጋገጠ፡፡

**<u>አንቀጽ 478 የሒሳብ አጣሪዎች የሥራ ዋጋ</u>**

1) ሒሳብ አጣሪዎች ለሚሰጡት አገልግሎት የሥራ ዋጋ ይከፈላቸዋል፡፡

2) የሥራ ዋጋ ክፍያው በዚህ ሕግ አንቀጽ 475 መሠረት በሚሾማቸው አካል ይወሰናል፡፡

**<u>አንቀጽ 479 ሒሳብ በሚጣራበት ጊዜ የማኅበሩ ሕጋዊ ሰውነት ቀጣይነት</u>**

1) ሒሳብ ማጣራቱ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ማኅበሩ ከስያሜው ቀጥሎ "በመጣራት ላይ ያለ" የሚል ሐረግ ተጨምሮበት ሕጋዊ ሰውነቱን እና ስሙን እንደያዘ ይቀጥላል፡፡

2) ሒሳብ በሚጣራበት ጊዜ የማኅበሩ አስተዳደር አካላት ማከናወን የሚችሉት ለማጣራቱ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ እና ከአጣሪው ሥልጣን ውጭ የሆኑ ሥራዎችን ብቻ ነው፡፡

## አንቀጽ 480 የከሰረ ማኅበር ሂሳብ ስለሚጣራበት ሁኔታ

1) የማኅበሩ መክሰር በፍርድ ቤት የተወሰነ እንደሆነ ሒሳብ መጣራቱ ኪሳራን በሚመለከቱት የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ይፈጸማል፡፡

2) ስለኪሳራ የሚደነግጉት የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፤ የማኅበሩ ዳይሬክተሮች ማኅበሩን ለመወከል ሥልጣን የሚኖራቸው ለሥራው አስፈልጊ በሆነ መጠን ብቻ ነው፡፡

## አንቀጽ 481 የሒሳብ አጣሪዎች ግዴታና ኃላፊነት

1) በሕግ ወይም በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በስተቀር፤ የሒሳብ አጣሪዎች ግዴታና ኃላፊነት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ዓይነት ይሆናል፡፡

2) ሒሳብ አጣሪዎች የማኅበሩን ንብረቶችና የሒሳብ መዝገቦች ይረከባሉ፡፡ የዳይሬክተሮች ቦርድ ከመጨረሻው የበጀት ዓመት ማብቂያ ጀምሮ ሒሳብ ማጣራቱ እስከተጀመረበት ጊዜ ያለውን የማኅበሩ አስተዳደር የሚመለከት የሥራ ሪፖርት ለሒሳብ አጣሪዎች ያቀርባል፡፡

3) ሒሳብ አጣሪዎችና ዳይሬክተሮች የማኅበሩን ሀብትና ዕዳዎች የያዘ ዝርዝር መዝገብ በጋራ አዘጋጅተው ይፈርማሉ፡፡

4) ማኅበሩ ያለው ሀብት ዕዳዎቹን ለመክፈል በቂ እንደማይሆን ከተገመተ ሒሳብ አጣሪዎች ባለአክሲዮኖች ገቢ ያላደረጉት መዋጮ ካለ ማስከፈል ይኖርባቸዋል፡፡

## አንቀጽ 482 የሒሳብ አጣሪዎች ሥልጣን እና ኃላፊነት

1) በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ ወይም በሾማቸው ጉባኤ የተጣሉ ገደቦች ካሉ እንደተጠበቁ ሆኖ፤ ሒሳብ አጣሪዎች የማጣራቱን ሥራ ለማከናውን ሙሉ የሆነ ሥልጣን ይኖራቸዋል፡፡ በተለይም የማኅበሩን ሀብት በሙሉ ለመሸጥ፣ በፍርድ ቤት ማኅበሩን ለመወከል፣ ክርክር የሚያስነሱ ጉዳዮችን በስምምነት ወይም በግልግል ዳኝነት ለመጨረስ፣ የማኅበሩን ገንዘብ ለመሰብሰብ እና ዕዳዎችን ለመክፈል ይችላሉ፡፡

2) ሒሳብ አጣሪዎች ቀደም ሲል የነበሩ ውሎችን ለማስፈጸም ካልሆነ ወይም የሒሳብ ማጣራቱ ሥራ ካላስገደደ በስተቀር አዲስ ሥራዎችን መጀመር አይችሉም፡፡

3) ሒሳብ አጣሪዎች በሕግ፣ በመመስረቻ ጽሑፍ ወይም በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ከተሰጣቸው ስልጣን ውጭ በመስራታቸው በማኅበሩ ወይም በሦስተኛ ወገኖች ላይ ለሚያደርሱት ጉዳት በአንድነትና በተናጠል ኃላፊ ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ 483 ከዕዳ ክፍያ በፊት የንብረት ክፍፍል ማድረግ የተከለከለ ስለመሆኑ

ማኅበሩ ለገንዘብ ጠያቂዎች ያለበትን ዕዳ በሙሉ ሳይከፍል ወይም ለክፍያ የሚያስፈልገውን ገንዘብ በፍርድ ቤት ሳይቀመጥ ሒሳብ አጣሪዎች የማኅበሩን ሃብት ለባለአክሲዮኖች ማከፋፈል አይችሉም፡፡

## አንቀጽ 484 ገንዘብ ጠያቂዎችን ስለመጥራትና ክፍያ ስለመፈጸም

1) ስማቸው በሒሳብ መዝገብ ውስጥ ለተመለከተ ወይም በሌላ መንገድ ለሚታወቁ ገንዘብ ጠያቂዎች የማኅበሩን መፍረስ በተመዘገበ ደብዳቤ ወይም አስቀድሞ ስምምነት በተደረሰባቸው ሌሎች ዘዴዎች እንዲያውቁት እና የሚጠይቁትን ገንዘብ ሊያስረዱ የሚችሉ ሰነዶችን እንዲያቀርቡ ይገለጽላቸዋል፡፡ ሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች በመመስረቻ ጽሑፉ በተመለከተው አኳኋን እና ሰፊ አገር አቀፍ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ለሦስት ተከታታይ ወራት በወር አንድ ጊዜ የማኅበሩን መፍረስ በመግለጽ እንዲሁም በመኅበሩ ድረ-ገጽ ማስታወቂያ በማውጣት እንዲያውቁት መደረግ አለበት፡፡
2) ለመኅበሩ ገንዘብ ጠያቂዎች የሚደረገው ክፍያ ሒሳብ አጣሪዎች ሥራቸውን በጀመሩበት ጊዜ ባዘጋጁት የሀብትና ዕዳ ሒሳብ መግለጫ መሠረት ይፈጸማል፡፡

## አንቀጽ 485 የገንዘብ ጠያቂዎች መብት ጥበቃ

1) የታወቁ የማኅበሩ ገንዘብ ጠያቂዎች ጥያቄያቸውን ለሒሳብ አጣሪዎች ያላቀረቡ ከሆነ ሊከፈላቸው የሚገባው ገንዘብ መጠን በፍርድ ቤት ሊቀመጥላቸው ይገባል፡፡
2) ለገንዘብ ጠያቂዎች ተመጣጣኝ ዋስትና ካልተገባላቸው ወይም ከማኅበሩ የሚጠየቁ ግዴታዎች እስከሚፈጸሙ ድረስ የሀብት ክፍፍሉ ካልተላለፈ በስተቀር፤ የመፈጸሚያ ጊዜያቸው ያልደረሰ ወይም አከራካሪ የሆኑ ከማኅበሩ የሚጠየቁ ግዴታዎችን ለመፈጸም የሚያስችል ተመጣጣኝ ገንዘብ በፍርድ ቤት መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

## አንቀጽ 486 የመጨረሻ የሃብትና ዕዳ ሒሳብ መግለጫ

1) ሒሳብ አጣሪዎች የማኅበሩ ዕዳ ከተከፈለ በኋላ ከተረፈው ንብረት ላይ እያንዳንዱ አክሲዮን ከሙቶኛ ምን ያህል ሊደርሰው እንደሚችል የሚያሳይ የመጨረሻ የሀብትና ዕዳ ሒሳብ መግለጫ ማዘጋጀት አለባቸው፡፡
2) በመመስረቻ ጽሑፉ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በስተቀር፤ ሒሳብ አጣሪዎች የአክሲዮኖቹ ዋጋ ሙሉ በሙሉ መከፈላቸውንና ከአክሲዮኖቹ ጋር የተያያዙ ቀዳሚ መብቶችን ግምት ውስጥ በማስገባት በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) ላይ የተመለከተውን የድርሻ ክፍፍል ይወስናሉ፡፡
3) ሒሳብ አጣሪዎች የፈረሙበት የሀብትና ዕዳ ሒሳብ መግለጫ እና የኦዲተሮች ሪፖርት በንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም አግባብ ባለው ሌላ የመንግስት አካል ዘንድ መቀመጥ አለበት፡፡
4) ማንኛውም ባለአክሲዮን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (**3**) በተደነገገው መሠረት መግለጫው ከተቀመጠበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት ሦስት ወራት የመጨረሻው የሀብትና ዕዳ ሒሳብ መግለጫ ውድቅ እንዲደረግ ተቃውሞውን ለፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡ ማመልከቻው የሚታየው የሶስት ወሩ የጊዜ ገደብ ካለቀ በኋላ ሲሆን ብዙ ማመልከቻዎች ካሉም በአንድነት ይታያሉ፡፡ ፍርድ ቤቱ በቀረቡት ጉዳዮች ላይ የሚሰጠው ውሳኔ በሌሎች ባለአክሲዮኖች ላይም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**5)** በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (4) በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ አቤቱታ ያልቀረበ እንደሆነ የሀብትና ዕዳ ሒሳብ መግለጫው እንደጸደቀ ይቆጠራል፡፡

**<u>አንቀጽ 487 የሀብት ክፍፍሉን ስለማቆየት</u>**

ገንዘብ ጠያቂዎች ከተከፈሉ በኋላ የተረፈው የማኅበሩ ሀብት ለባለአክሲዮኖች ለማከፋፈል የሚቻለው በዚህ ሕግ አንቀጽ 484 ንዑስ አንቀጽ (1) ሥር በተመለከው አኳኋን ማስታወቂያ አገር አቀፍ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ለሦስተኛ ጊዜ ከወጣ ከአንድ ዓመት በኋላ ነው፡፡ ሆኖም ገንዘብ ጠያቂዎች በክፍፍሉ የማይጎዱ መሆናቸውን ፍርድ ቤቱ ካመነ ከተጠቀሰው ጊዜ በፊት ተራፊው ንብረት ለባለአክሲዮኖች እንዲከፋፈል ሊፈቅድ ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 488 ያልተወሰደን ገንዘብ ስለማስቀመጥ</u>**

አንድ ባለአክሲዮን ከተራፊው ንብረት ላይ የሚገባውን ድርሻ በዚህ ህግ አንቀጽ 486 ንዑስ አንቀጽ (3) መሰረት የሀብትና ዕዳ ሒሳብ መግለጫ እና የኦዲተሮች ሪፖርት አግባብ ባለው የመንግስት አካል ከተቀመጠበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት ሦስት ወራት ውስጥ ያልወሰደ አንደሆነ ሒሳብ አጣሪዎች የባላክሲዮኑን ስም ወይም አክሲዮኖቹ ለአምጪው የሆኑ እንደሆነ የአክሲዮኖቹን ቁጥር በመግለጽ ገንዘቡን በልዩ ሒሳብ ባንክ ያስቀምጣሉ፡፡

**<u>አንቀጽ 489 ማኅበሩን ከንግድ መዝገብ ስለመሰረዝ</u>**

1) የመጨረሻው የሀብትና ዕዳ ሒሳብ መግለጫ ከፀደቀ በኋላ ሒሳብ አጣሪዎች ማኅበሩ ከንግድ መዝገብ እንዲሰረዝ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡
2) ማኅበሩን ከንግድ መዝገብ ባለማሰረዛቸው ምክንያት በማህበሩ አባላትም ሆነ በሌሎች ሦስተኛ ወገኖች ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ሒሳብ አጣሪዎች በአንድነት እና በተናጠል ተጠያቂ ናቸው፡፡

**<u>አንቀጽ 490 የገንዘብ ጠያቂዎች መብት</u>**

**1)** በዚህ ሕግ አንቀጽ 489 መሠረት ማኅበሩ ከንግድ መዝገብ ከተሰረዘ በኋላ የሚመጡ ገንዘብ ጠያቂዎች ባለአክሲዮኖች ከተራፊው ንብረት በደረሳቸው መጠን እንዲከፍሏቸው መጠየቅ ይችላሉ፡፡
**2)** ገንዘብ ጠያቂዎቹ ያልተከፈላቸው በአጣሪዎች ቸልተኝነት ከሆነ ከሂሳብ አጣሪዎች ላይ መብታቸውን መጠየቅ ይችላሉ፡፡

**<u>አንቀጽ 491 የማኅበሩን መዝገቦች ጠብቆ ስለመያዝ</u>**

**1)** የፈረሰው ማኅበር የሒሳብ መዛግብት ለ10 ዓመታት አግባብ ባለው የመንግስት አካል ተጠብቀው መቀመጥ አለባቸው፡፡
**2)** ማንኛውም ሰው የሂሳብ መዝገቦችን ለመመርመር ይችላል፡፡

**<u>ምዕራፍ አስር</u>**

**<u>ስለድረ-ገፅ</u>**

**<u>አንቀጽ 492 ድረ-ገጽ ስለማቋቋም</u>**

እያንዳንዱ የአክሲዮን ማኅበር ድረ ገጽ ሊኖረው ይገባል፡፡

**<u>አንቀጽ 493 ድረ-ገፅ ላይ ስለሚገለፁ ነገሮች</u>**

**1)** የሚከተሉት መረጃዎች በወቅቱ ድረ-ገፅ ላይ መውጣት ይኖርባቸዋል፡-

**(ሀ)** የማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍና ካሉም ማሻሻያዎቹ፤

**(ለ)** ጠቅላላ ጉባኤውን የሚመለከቱ የስብሰባ ጥሪዎችና ተያያዥ መረጃዎች፤

**(ሐ)** የጸደቁ የኦዲት ሪፖርቶች፤

**(መ)** በአንቀጽ 395(5) መሰረት የተዘጋጀ የጥቅም ግጭት የሚያስነሱ ውሎችን የተመለከተ ሪፖርት፣ በዚህ ሕግ ወይም በሌሎች ሕጎች መሰረት ለንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የቀርቡ ዓመታዊ ሪፖርቶች እና መረጃ፣

**(ሠ)** በመመስረቻ ጽሑፍ መሰረት በይፋ መገለጽ ያለባቸው መረጃዎች እና

**(ረ)** ለባለአክሲዮኖች፣ ገንዘብ ጠያቂዎች እና ባለድርሻ አካላት አስፈላጊ የሆኑ የማኅበሩን ጥቅም ላልተገባ ጉዳት የማይዳርጉ ሌሎች መረጃዎች፡፡

**2)** በተቻለ መጠን ድረ-ገጹ የኤሌክትሮኒክ ጉባኤ ለማድረግና በኤሌክትሮኒክ መንገድ ድምጽ ለመስጠት የሚቻልበትን ሁኔታ ማካተት አለበት፡፡

**<u>አንቀጽ 494 መረጃዎች በድረ-ገፁ ላይ ስለሚቆዩበት ጊዜ</u>**

**1)** የሚከተሉት መረጃዎች በድረ-ገጹ ላይ ከወጡበት ቀን ጀምሮ፡-

**(ሀ)** የስብሰባ ጥሪና ተያያዥ መረጃዎች ስብሰባው እስከሚጠናቀቅበት ዕለት ድረስ፤

**(ለ)** የሂሳብ ሰነዶች ለአምስት አመታት፤

**(ሐ)** ሌሎች መረጃዎች ለስድስት ወራት፤

መቆየት አለባቸው፡፡

**2)** ድረ-ገጹ ለማንኛም ሰው ተደራሽ መሆን ይኖርበታል፡፡

**3)** ኩባንያው የድረ-ገፁን ደህንነት ለመጠበቅ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

**<u>ርዕስ ሰባት</u>**

**<u>ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር</u>**

## ምዕራፍ አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 495 ትርጓሜ፡-

1) ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ማለት ዋና ገንዘቡ አስቀድሞ የተከፈለ፣ በአክሲዮን የተከፋፈለ እና ባለአክሲዮኖች መዋጮአቸውን ገቢ እስካደረጉ ድረስ ለማኅበሩ ዕዳ ኃላፊ የማይሆኑበት የንግድ ማኅበር ነው፡፡
2) የማህበሩን አክሲዮኖች ለሕዝብ ክፍት በሆነ ገበያ መሸጥ አይቻልም፡፡
3) የንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም፤ ወሳኝ ድምጽ ያለው ባለአክሲዮን ተጠያቂነትን በተመለከተ በዚህ ሕግ በአንቀጽ 295 ሥር የተደነገገው ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡
4) የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ቁጥር ከሁለት ማነስ ከሃምሳ ሰዎች መብለጥ አይችልም፡
5) ማኅበሩ የሚተላለፉ የግዴታ ወረቀቶችን ማውጣት አይችልም፡፡

### አንቀጽ 496 የማኅበሩ ዋና ገንዘብ

1) የማኅበሩ አነስተኛ ዋና ገንዘብ ከአስራ አምስት ሺሕ የኢትዮጵያ ብር ያነሰ መሆን አይችልም፡፡
2) እያንዳንዱ አክሲዮን ላይ የሚጻፈው ዋጋ ከአስር ብር በታች መሆን አይችልም፡፡ በሁሉም አክሲዮኖች ላይ የተጻፈ ዋጋ እኩል መሆን አለበት፡፡

### አንቀጽ 497 የማኅበሩ ስም

ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር የንግድ ዓላማውን የሚገልጽ ስም ይኖረዋል፡፡ ከማኅበሩ ስም ቀጥሎ "ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር" የሚለው ሐረግ መጻፍ አለበት፡፡

### አንቀፅ 498 የባለ አክሲዮኖች ቁጥር ወደ አንድ ዝቅ ማለት

1) ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር የባለአክሲዮኖቹ ቁጥር ወደ አንድ ዝቅ ካለ እና በስድሰት ወር ጊዜ ውስጥ ሌላ ሰው በባለአክሲዮንነት ካልገባ ማኅበሩ መፍረስ አለበት፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር (1) የተደነገገው ቢኖርም፤ የባለአክሲዮኖች ቁጥር ወደ አንድ ዝቅ ካለበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወራት ውስጥ የመመስረቻ ፅሁፉን በማሻሻል ባለአንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር አድርጎ ማስመዝገብ ይቻላል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## የማኅበሩ ምስረታ

### አንቀጽ 499 ለማኅበሩ ምስረታ የሚያስፈልጉ ጠቅላላ ሁኔታዎች

1) ማንኛውም ኃለፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር የሚመሰረተው ዋና ገንዘቡ በሙሉ ሲከፈል እና የመመስረቻ ጽሁፉ በንግድ መዝገብ ውስጥ ሲገባ ነው፡፡

2) በጥሬ ገንዘብ በተሸጡ አክሲዮኖች ላይ የተጻፈው ዋጋ ማኅበሩ ከመመዝገቡ በፊት በመመስረት ላይ ባለው ማኅበር ስም በተከፈተ ዝግ የባንክ ሂሒሳብ ውስጥ መቀመጥ አለበት፡፡

## አንቀጽ 500 የመመስረቻ ጽሑፉ ይዘት

የማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፡-

**1)** የባለአክሲዮኑን ወይም የባለአክሲዮኖችን ስም፣ ዜግነትና አድራሻ፤

**2)** የማኅበሩን ስም፣ ዋና መስሪያ ቤት፣እንዳሉም ቅርንጫፎቹን፤

**3)** የማኅበሩን የንግድ ዓላማ፤

**4)** የማኅበሩን ዋና ገንዘብ መጠን እና ይኸው በሙሉ የተከፈለ መሆኑን የሚያሳይ መግለጫ፤

**5)** እያንዳንዱ ባለአክሲዮን የከፈለውን የገንዘብ መጠን፤

**6)** በዓይነት የተከፈለ መዋጮ ካለ ግምቱን፤

**7)** እያንዳንዱ ባለአክሲዮን የያዘውን የአክሲዮን ብዛት፤

**8)** የትርፍ አከፋፈል ሥርዓት፤

**9)** ዳይሬክተሮች ካሉት ብዛታቸውንና ሥልጣናቸውን፤

**10)** የሥራ አስኪያጆችን ቁጥርና ሥልጣናቸውን፣

**11)** ኦዲተሮች ካሉ ብዛታቸውን፤

**12)** ማኅበሩ የሚቆይበትን ጊዜ፤

**13)** ማኅበሩ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት የሚያስታውቅበትን መንገድና ጊዜ፤

**14)** እንዲሁም በማኅበሩ ሥራ አመራር፣ በማኅበሩና በአባላት ወይም በአባላት መካከል ያለውን ግንኙነት የሚመለከቱ ጉዳዮችን፤

**15)** ሌሎች በሕግ ወይም በባለአክሲዮኖች ስምምነት እንዲካተቱ የተወሰኑ ጉዳዮችን፡፡

## አንቀጽ 501 ተቀባይነት ያለው መዋጮ

ከሙያ አገልግሎት በስተቀር ሌሎች በዚህ ሕግ አንቀጽ 186 የተመለከቱት የገንዘብና ሌሎች የዓይነት መዋጮዎች ኃላፊነቱ ለተወሰነ የግል ማኅበርም ተፈጻሚነት አላቸው፡፡

## አንቀጽ 502 በዓይነት የተከፈለ መዋጮ

**1)** ባለአክሲዮን በዓይነት መዋጮ የከፈለ እንደሆነ የመመስረቻ ጽሑፉ የመዋጮውን ዓይነትና ዋጋ፣ሌሎች ባለአክሲዮኖች የተቀበሉበትን ዋጋ እና ከማኅበሩ ዋና ገንዘብ ውስጥ በዓይነት ለከፈለው ባለአክሲዮን የተሰጠውን የአክሲዮን ድርሻ መጠን ማሳየት አለበት፡፡

**2)** የዓይነት መዋጮ የሚገመትበት መንገድ በባለአክሲዮኖች ይወሰናል፡፡

3) በዓይነት የተከፈለ መዋጮ በተከፈለበት ጊዜ ለተደረገው ግምት ትክክለኛነት ባለአክሲዮኖቹ ሁሉ ለሦስተኛ ወገኖች በአንድነትና በተናጠል ኃላፊዎች ይሆናሉ፡፡

4) በዓይነት የተከፈለ መዋጮ ግምት ከዋጋው በላይ ሆኖ ከተገኘ በዓይነት ያዋጣው ባለአክሲዮን በግምቱና በትክክለኛ ዋጋ መካከል ያለውን ልዩነት በጥሬ ገንዘብ መክፈል አለበት፡፡ ከዋጋው በላይ ስለመገመቱ ባያውቁም እንኳ ባለአክሲዮኖች ለዚህ ገንዘብ መክፈል በአንድነትና በተናጠል ኃላፊዎች ይሆናሉ፡፡

5) የማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ እና ማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ካለው ቦርዱ በዓይነት የተዋጣው ንብረት እንደነገሩ ሁኔታ በማኅበሩ ስም መመዝገቡን እና አስፈላጊው የንብረት ባለቤትነት ማስረጃ በማሕበሩ ስም መዘጋጀቱን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## ስለአክሲዮኖችና የባለአክሲዮኖች መብትና ግዴታ

### አንቀጽ 503 የአክሲዮኖች ዓይነት

ማኅበሩ ማውጣት የሚችለው በስም የተመዘገቡ አክሲዮኖችን ብቻ ነው፡፡

### አንቀጽ 504 ሰነዶችን የመመርመር መብት

1) አንድ ማኅበርተኛ በማኅበሩ ፋይናንስ ወይም የማኅበርተኛውን ጥቅም በሚነካ ሌላ ጉዳይ ላይ ግምገማ ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑትን የማኅበሩ ሒሳቦች እና ሰነዶች የመመርመር እንዲሁም ጥያቄ የማቅረብ መብት አለው፡፡ ማኅበርተኛው በዚህ መብቱ ለመጠቀም ተወካይ መሾም ወይም ረዳት ይዞ መቅረብ ይችላል፡፡

2) ሆኖም መረጃው ይፋ መደረጉ በሕግ የተከለከለ ከሆነ ወይም ማኅበሩ ላይ ከባድ ጉዳት የሚያደርስ ከሆነ ማኅበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ካለው ቦርዱ ከሌለው ደግሞ ዋና ሥራ አስኪያጁ መረጃውን ወይም ሰነዱን መከልከል አለበት፡፡

### አንቀጽ 505 በመያዣ ወይም በአላባ ስለሚሰጡ አክሲዮኖች

ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በስተቀር፤ አክሲዮን በመያዣ ወይም በአላባ  የተሰጠ እንደሆነ በማኅበሩ ጉባኤዎች ድምፅ የመስጠት መብት የሚኖረው አክሲዮኑን በመያዣ ወይም በአላባ  የሰጠው ሰው ብቻ ነው፡፡

### አንቀጽ 506 የአክሲዮን ምስክር ወረቀት ስለሚይዛቸው ነገሮች

እያንዳንዱ አክሲዮን የሚከተሉትን  መያዝ አለበት፡-

1) የአክሲዮኑ መለያ ቁጥር፣ ቅደም ተከተል፣

2) ማኅበሩ ቦርድ ካለው የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ ከሌለው ደግሞ የሥራ አሲኪያጁን ፊርማ፤

3) የማኅበሩን ስም፣ ዋና መስሪያ ቤትና ማኅበሩ የሚቆይበትን ጊዜ፤

4) የማኅበሩን ዋና ገንዘብና አክሲዮኑ የወጣበትን ዋጋ መጠን፤

5) የማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፉ የተፈረመበትን ቀን፣ ማኅበሩ በንግድ መዝገብ የተመዘገበበትን ቀንና ቦታ፤

6) ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን፡፡

## አንቀጽ 507 ስለአክሲዮኖች መዝገብ

1) የማኅበሩ ዋና መስሪያ ቤት የሚከተሉትን የአክሲዮኖች ዝርዝር በአክሲዮኖች መዝገብ መያዝ አለበት፡-

(ሀ) የባለአክሲዮኖችን ስምና አድራሻ፣ የእያንዳንዱን ባለአክሲዮን ድርሻ እና የአክሲዮኖችን መለያ ቁጥር፣

(ለ) አክሲዮን ሲተላለፍ ዝውውሩን የተመለከተ ዝርዝር ፤

(ሐ) በእነዚህ ዝርዝሮች ላይ የተደረገውን ማንኛውም ማሻሻያ፡፡

2) የአክሲዮን መዝገቡ የመጨረሻ ዝርዝር ከተቀመጠበት ጊዜ ጀምሮ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ) እና (ለ) ስር በተመለከቱት መረጃዎች ላይ ለውጥ ሲኖር በየዓመቱ መጀመሪያ የተደረገውን ለውጥ የያዘ ዝርዝር በቦርዱ ሰብሳቢ ወይም ማህበሩ ቦርድ ከሌለው በሥራ አስኪያጁ ለንግድ እና ኢንዱስተሪ ሚኒስቴር ወይም አግባብ ላለው ሌላ የመንግስት አካል መላክ አለበት፡፡

3) ባለአክሲዮኖች መዝገቡን ያለክፍያ መመልከት ወይም የመዝገቡን ግልባጭ መውሰድ ይችላሉ፡፡ ማኅበሩ ጥያቄው በቀረበ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ግልባጩን ለጠያቂው መስጠት አለበት፡፡

4) ማንኛውም ሦስተኛ ወገን የተወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ በመፈጸም መዝገቡን መመልከት ወይም ግልባጭ እንዲሰጠው ማኅበሩን መጠየቅ ይችላል፡፡

5) በባለአክሲዮን ወይም ጥቅም ባለው ማንኛውም ሰው በመዝገብ አጻጻፍ ላይ ስህተት ያለ ስለመሆኑ ከተገለጸለት የንግድ እና ኢንዱስተሪ ሚኒስቴር ወይም አግባብ ያለው ሌላ የመንግስት አካል እንዲስተካከል ማድረግ ይችላል፡፡ የአክሲዮን መዝገቡ ዝርዝር በትክክል ባለመጻፉ ምክንያት ለሚደርስ ማንኛውም ጉዳት ማኅበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ካለው የቦርዱ አባላት ከሌው ደግሞ ሥራ አስኪያጆች በአንድነትና በተናጠል ኃላፊ ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ 508 አክሲዮኖችን ስለማስተላለፍ

1) በማንኛውም ምክንያት የሚደረግ የአክሲዮኖች ዝውውር በጽሑፍ መሆን አለበት፡፡ ዝውውሩ በአክሲዮኖች መዝገብ ውስጥ ካልገባ በስተቀር በሦስተኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ሊሆን አይችልም፡፡

2) በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በስተቀር አክሲዮኖች በማኅበሩ አባላት መካከል ያለገደብ ሊተላለፉ ይችላሉ፡፡

3) አንድ ማኅበርተኛ አክሲዮኑን የማህበሩ አባል ላልሆነ ሰው ከመሸጡ በፊት ማህበርተኛ ያልሆነው ሰው ያቀረበለትን ዋጋ በመግለጽ አክሲዮኖቹን በዛው ዋጋ እና ሁኔታ እንዲገዙት ለማኅበሩ አባላት ዕድል መስጠት አለበት፡፡

**4)** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ስር የተመለከተው ማስታወቂያ ለማሕበሩ ዋና ሥራ አስኪያጅ በደረሰ በ15 (አስራ አምስት) ቀናት ባለአክሲዮን በሆነ ሰው የውል ሀሳቡ ተቀባይነት ካላገኘ ባለአክሲዮኑ ማኅበርተኛ ያልሆነው ሰው ያቀረበለትን የውል ሀሳብ መቀበል ይችላል፡፡

**አንቀጽ 509 ከማህበሩ ውጪ አክሲዮን ስለማስተላለፍ**

1) በዚህ ሕግ አንቀጽ 508 ንዑስ አንቀጽ (4) ስር የተደነገገው ቢኖርም በመመስረቻ ጽሑፉ ላይ የበለጠ የድምጽ ብልጫ ወይም ሙሉ ድምጽ እንደሚያስፈልግ ካልተወሰነ በስተቀር፤ የማኅበሩ አባል ላልሆነ ሰው የሚደረገው የአክሲዮን ዝውውር ተፈጻሚ የሚሆነው ከማኅበሩ ዋና ገንዘብ ቢያንስ ¾ (ሦስት አራተኛ) ድርሻ ያላቸው ባለአክሲዮኖች ሲደግፉት ነው፡፡
2) ማኅበሩ በመጣራት ላይ ቢሆንም የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንንቀጽ (1) ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 510 አክሲዮን በፍርድ አፈጻጸም ስለማስተላለፍ**

1) የማኅበሩ ባለአክሲዮን ያልሆነ ሰው የአንዱን ባለአክሲዮን ድርሻ በፍርድ አፈጻፀም ያገኘ እንደሆነ የማኅበሩ ባለአክሲዮን ለመሆን በዚህ ሕግ አንቀጽ 509 ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው መሰረት የሌሎችን ባለአክሲዮኖች ድጋፍ ማግኘት አለበት፡፡
2) የማኅበሩ ዋና ገንዘብ 3/4 (ሦስት አራተኛ) ድርሻ ያላቸው አባላት በፍርድ አፈጻጸም አክሲዮን ያገኘው ሰው ማህበሩን እንዲቀላቀል ካልተስማሙ አክሲዮኖቹ ከማህበሩ አባላት መካከል ለመግዛት ፍላጎት ላለው አባል ይተላለፋሉ፡፡ ለመግዛት ፍላጎት ያለው ባለአክሲዮን ካልተገኘ ማኅበሩ ለፍርድ ባለመብቱ የአክሲዮኖቹን ዋጋ መክፈል አለበት፡፡
3) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) መሰረት ማህበሩ አክሲዮኖችን ሲገዛ ክፍያው ለማህበርተኞች ሊከፋፈል ከሚችል የመጠባበቂያ ገንዘብ መፈጸም አለበት፡፡
4) የመጠባበቂያ ገንዘብ ባለመኖሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሰረት ግዥ መፈጸም ካልተቻለ ክፍያው ከዋና ገንዘቡ ይፈጸማል፡፡ ዋና ገንዘቡም በዚህ ልክ እንዲቀነስ ይደረጋል፡፡ ዋና ገንዘቡ ከመቀነሱ በፊት ከማኅበሩ ጋር ለተዋዋሉ ሰዎች በዋና ገንዘቡ ላይ በተደረገው ቅናሽ ልክ ማኅበርተኞች በአንድነት እና በተናጠል ኃላፊ ይሆናሉ፡፡

**አንቀጽ 511 አክሲዮኖችን በውርስ ስለማግኘት**

1) በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በስተቀር፤ አንድ ባለአክሲዮን ሲሞት ወራሾቹ ባለአክሲዮን የመሆን መብት ይኖራቸዋል፡፡
2) ሆኖም ባለአክሲዮን መሆን የማይፈልጉ ከሆነ በመጨረሻው የሃብትና ዕዳ መግለጫ መሠረት የሚቹ አክሲዮን በማህበሩ ሀብት ውስጥ የሚወክለው ድርሻ ከመጠባበቂያ ገንዘብ ሊከፈላቸው ይገባል፡፡
3) ማኅበሩ ለማኅበርተኞች ሊከፋፋል የሚችል በቂ የመጠባበቂያ ገንዘብ ከሌለው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ስር የተመለከተው መብት አይኖርም፡፡

**<u>አንቀጽ 512 ተፈጻሚነት ስላላቸው ድንጋጌዎች</u>**

በዚህ ሕግ ከአንቀጽ **273** እስከ **275** ድረስ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ለዚህ ምዕራፍ እንደአግባብነታቸው ተፈጻሚነት አላቸው፡፡

**<u>ምዕራፍ አራት</u>**

**<u>የማኅበሩ ሥራ አመራር</u>**

**<u>አንቀጽ 513 የማኅበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ</u>**

1) ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር በዳይሬክተሮች ቦርድ እንዲመራ በመመስረቻ ጽሑፍ ሊወሰን ይችላል፡፡
2) የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚኖር ከሆነ የአባላቱ ቁጥር ከሶስት እስከ ሰባት ይሆናል፡፡
3) በዚህ ሕግ ስለአክሲዮን ማኅበር የቦርድ አባላት ሹመት፤ ስለሚገቡት ዋስትና፣ መሻር፣ የስራ ዘመን፣ ውሳኔ አሰጣጥ፣ ተጠያቂነት፣ የአገልግሎት ክፍያ፣ ስልጣንና ተግባር እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ጉዳዮችን በተመለከተ የአንቀጽ 296(4)(5)፣297 እስከ 298፣300 እስከ 312፣ እና 314 እሰከ 330 ድንጋጌዎች ኃላፊነቱ በተወሰነ የግል ማኅበር ዳይሬክተሮች ቦርድ ላይ እንደ አግባብነታቸው ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

**<u>አንቀጽ 514 ስለ ማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ</u>**

1) ማኅበሩ ባለአክሲዮን የሆነ ወይም ያልሆነ በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ የሚሾም አንድ ዋና ሥራ አስኪያጅ ይኖረዋል፡፡
2) ማኅበሩ በዳይሬክተሮች ቦርድ እንዲተዳደር በመመስረቻ ጽሑፍ የተወሰነ እንደሆነ ሥራ አስኪያጁ የሚሾመው በቦርዱ ይሆናል፡፡ ሥራ አስኪያጁ የቦርድ ሊቀመንበር መሆን አይችልም፡፡
3) ሥራ አስኪያጁ የማኅበሩ ተቀጣሪ ነው፡፡

**<u>አንቀጽ 515 የሥራ አስኪያጁ ስልጣን</u>**

1) ማኅበሩ በቦርድ የሚተዳደር ከሆነ ስለስራ አስኪያጅ ሥልጣን በዚህ ሕግ አንቀጽ 337 እስከ 339 የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደ አግባብነቱ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡
2) ማኅበሩ ቦርድ የሌለው ከሆነ ሥራስኪያጁ የማኅበሩንን ዓላማ ለማሳካት በማኅበሩ ስም ለመስራት ሙሉ ስልጣን ይኖረዋል፡፡
3) የሥራ አስኪያጁን ሥልጣን የሚገድቡ የማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ ድንጋጌዎች በማኅበሩ፣ በባለአክሲዮኖች እና በሥራ አስኪያጁ መካከል ካልሆነ በስተቀር ውጤት አይኖራቸውም፡፡

**<u>አንቀጽ 516 የስራ አስኪያጁ ተጠያቂነት</u>**

1) ተቃራኒ ስምምነት ቢኖርም ሥራ አስኪያጁ በሕግ ወይም በመመስረቻ ጽሑፍ የተመለከቱ ድንጋጌዎችን በመተላለፍ ለሚያደርሰው ጉዳት ለማኅበሩ፣ ለባለአክሲዮኖች እና ለሦስተኛ ወገኖች ኃላፊ ነው፡፡

2) ማኅበሩ በመክሰሩ ምክንያት ሀብቱ ዕዳውን ለመክፈል በቂ ሆኖ ያልተገኘ እንደሆነ በከሰረው ማኅበር ንብረት ጠባቂ አመልካችነት ፍርድ ቤት የማኅበሩ ስራ አስኪያጅ እና የቀድሞ ሥራ አስኪያጆች የማኅበሩን ዕዳ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲከፍሉ ለመወሰን ይችላል፡፡

3) የአስተደደር ኃላፊነታቸውን በተገቢው ጥንቃቄና ትጋት መወጣታቸውን ባስረዱ ስራ አስኪያጆች ላይ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

## አንቀጽ 517 ሥራ አስኪያጅን ስለመሻር

1) ሥራ አስኪያጅ ሊሻር የሚችለው በሾመው አካል ነው፡፡ በተለይም በማኅበሩ መመስረቻ ጽሁፍ ተቃራኒ ድንጋጌ እስከሌለ ድረስ ሥራ አስኪያጁ በቦርድ የተሾመ እንደሆነ የአክሲዮን ማኅበር ስራ አስኪያጅ በሚወርድበት አኳኋን ይወርዳል፡፡

2) በማኅበሩ የመመስረቻ ጽሁፍ ላይ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በስተቀር፤ በመመስረቻ ጽሁፍ ላይም ሆነ በባለአክሲዮኖች መደበኛ ጉባዔ የተሾመ ስራ አስኪያጅ በማኅበሩ መደበኛ ጉባዔ ይሻራል፡፡ ሥራ አስኪያጁ ከሃላፊነት የተነሳው ካለበቂ ምክንያት ቢሆንም ወደ ኃላፊነቱ የመመለስ መብት የለውም፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (2) የተመለከተው ቢኖርም በቂ ምክንያት አለ ብሎ ሲያምን ማንኛውም ባለአክሲዮን በሚያቀርበው ጥያቄ መሠረት ፍርድ ቤት ስራ አስኪያጁን ሊሽረው ይችላል፡፡

4) በተሻረው ምትክ ሌላ ስራ አስኪያጅ እስኪሾም ድረስ ጊዜ የሚወስድ ከሆነ እንደቅደም ተከተላቸዉ ምክትል ስራ አስኪያጅ ወይም የዳይሬክተሮች ቦርዱ ሊቀመንበር የተሻረውን ሥራ አስኪያጅ ተክቶ ይሠራል፡፡

## አንቀጽ 518 ስለኦዲተር

1) ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር አስር እና ከዛ በላይ ባለአክሲዮኖች ያሉት እንደሆነ ወይም የማኅበሩ ጠቅላላ ሃብት አምስት ሚሊዮን ብር የሚደርስ ከሆነ ነጻ እና ገለልተኛ የሆነ የውጭ ኦዲተር ሊኖረው ይገባል፡፡

2) ኦዲተር የሚመረጠው በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉበዔ ነው፡፡

3) በዚህ ሕግ ከአንቀጽ 343 እስከ 354 የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደ አግባብነታቸው ኃላፊነቱ በተወሰነ የግል ማኅበር ኦዲተርም ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ስለማኅበሩ ጉባኤዎች

## አንቀጽ 519 የጉባኤ አይነቶች

የማኅበሩ ጉባዔዎች መደበኛ ወይም አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤዎች ናቸው፡፡

## አንቀጽ 520 በኤለክትሮኒክ ዘዴ ስለሚደረግ ጉባዔ

1) በማኅበሩ መመስረቻ ጽሁፍ የተጣለ ክልከላ ከሌለ በስተቀር፤ በማኅበሩ ጉባዔ ላይ በቪድዮ ወይም በሌላ የመገናኛ ዘዴ መሳተፍ ይቻላል፡፡ የመገናኛ ዘዴው የተሰብሳቢዎችን ማንነት ለመለየት የሚያስችል እንዲሁም ውጤታማ ተሳትፎን የሚያረጋግጥ መሆን አለበት፡፡ የመገናኛ ዘዴው ቢያንስ የተሳታፊዎችን ድምጽ ሳይቆራረጥ የሚያስተላልፍ እና ተሰብሳቢዎቹ በአንድ ጊዜ መሳተፍ እንዲችሉ የሚፈቅድ መሆን አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት በአካል ሳይገኙ በጉባዔው የተሳተፉ አባላት ድምጻቸውን በቃል መስጠት ይችላሉ፡፡

3) ከማኅበሩ ጠቅላላ አባላት ውስጥ ቢያንስ አንድ ሶስተኛው (ሲሶው) በስብሰባው ላይ በአካል ካልተገኙ በቀር፤ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት በተደረገ ስብሰባ የተላለፈ ውሳኔ አይጸናም፡፡

4) በኤሌክትሮኒክ ዘዴ በተደረገ ጉባኤ የማኅበሩን መመስረቻ ጽሁፍ ማሻሻል አይቻልም፡፡ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ውሳኔ ሊተላለፍባቸው የሚችሉ ጉዳዮች ላይ በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ ገደብ ማድረግ ይቻላል፡፡

## አንቀጽ 521 መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ

**1)** እያንዳንዱ የሒሳብ ዓመት ከተዘጋበት ቀን ጀምሮ ባሉት አራት ወራት ውስጥ ቢያንስ አንድ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ መደረግ አለበት፡፡

**2)** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተወሰነው የአራት ወራት ጊዜ በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ ወይም አግባብ ባለው የመንግስት አካል ውሳኔ እስከ ስድስት ወራት ሊራዘም ይችላል፡፡

**3)** ጉባኤው የሚጠራው ማኅበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ካለው በቦርዱ፣ ቦርዱ ካልጠራ ወይም ማኅበሩ ቦርድ ከሌለው በስራ አስኪያጅ፣ እነዚህ ካልጠሩ ማኅበሩ ኦዲተር ካለው በኦዲተሩ ወይም ከማህበሩ ዋና ገንዘብ ከግማሽ በላይ ባዋጡ ባለአክሲዮኖች ነው፡፡

**4)** ከማኅበሩ ዋና ገንዘብ ቢያንስ አስር በመቶ ባዋጡ ባለአክሲዮኖች ጥያቄ ከቀረበለት በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (3) የተጠቀሰው አግባብ ያለው አካል ጉባኤ መጥራት አለበት፡፡

**5)** በዚህ አንቀጽ ኃላፊነት የተሰጣቸው አካላት ጉባኤውን ለመጥራት ካልቻሉ ወይም ፈቃደኛ ካልሆኑ ወይም በማንኛውም ባለአክሲዮን ጠያቂነት በቂ ምክንያት ሲኖር ፍርድ ቤት ጠቅላላ ጉባኤውን የሚጠራና የመወያያ አጀንዳ የሚያዘጋጅ ሰው ሊሾም ይችላል፡፡

## አንቀጽ 522 ቃለ ጉባኤ

**1)** የጉባኤዎች ቃለ-ጉባኤ በጽሑፍ መዘጋጀትና በጉባኤው በአካል በተገኙ ባለአክሲዮኖች መፈረም አለበት፡፡

**2)** የጉባኤዎቹ ቃለ ጉባኤ በተለይ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ጉዳዮች መያዝ አለበት፡-

**(ሀ)** የጉባኤውን ጥሪ አደራረግ፤

**(ለ)** የስብሰባውን ቦታና ቀን፤

**(ሐ)** አጀንዳዎችን፤

**(መ)** ቦርድ ካለ በጉባኤው የተገኙ የቦርድ አባላትን ስም፤

**(ሠ)** በስብሰባው ላይ የተገኙ ባለአክሲዮኖች ብዛትና የምልዓተ ጉባኤውን ቁጥር፤

**(ረ)** ለጉባኤው የቀረቡ ሰነዶች፤

**(ሰ)** የውይይቱን አጭር ማጠቃለያ፤

**(ሸ)** የተሰጡት ድምጾች ውጤት፤ እና

**(ቀ)** ጉባኤው ያሳለፋቸውን ውሳኔዎች፡፡

**3)** ምልዓተ-ጉባኤው ባለመሟላቱ ምክንያት ጉባኤው ለመሰብሰብ ሳይችል የቀረ እንደሆነ የጉባኤው ሰብሳቢ ይኸው በቃለ ጉባኤ እንዲያዝ ያደርጋል፡፡

**<u>አንቀጽ 523 ያለጉባኤ የሚሰጡ ውሳኔዎች</u>**

የማኅበሩ አባላት ቁጥር ከአስር የሚያንስ ከሆነ የጉባኤ ጥሪ ሳይደረግ ለእያንዳንዱ ባለአክሲዮን የውሳኔ ሀሳቦችን መላክና በጽሑፍ ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ድምፅ እንዲሰጥ ማድረግ ይቻላል፡፡

**<u>አንቀጽ 524 የባለአክሲዮኖች መብት</u>**

**1)** በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በስተቀር ማንኛውም ባለአክሲዮን በራሱ ወይም በወኪል አማካኝነት በአካል ወይም በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ በጉባኤው ለመሳተፍ እና ድምጽ ለመስጠት ይችላል፡፡

**2)** እያንዳንዱ ባለአክሲዮን በማኅበሩ ውስጥ ባሉት አክሲዮኖች ልክ የድምፅ ብዛት ይኖረዋል፡፡

**<u>አንቀጽ 525 የመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ምልዓተ ጉባኤና አብላጫ ድምፅ</u>**

**1)** ጉባኤ ለማካሄድ ከማኅበሩ ዋና ገንዘብ ከግማሽ በላይ የያዙ ባለአክሲዮኖች ወይም የያዘ ባለአክሲዮን በስብሰባው ላይ መገኘት አለባቸዉ ወይም አለበት፡፡

**2)** ምልዓተ ጉባዔ የሚሰላው በባለአክሲዮኖች ቁጥር ሳይሆን በተወከለው የካፒታል መጠን ነው፡፡ ጉባዔው ሕጉ በሚያዘው ስርዓት እስከተጠራ እና አስፈላጊው የካፒታል መጠን እስከተወከለ ድረስ ውሳኔ ማሳለፍ ይቻላል፡፡ በተለይም የተወሰኑ ባለአክሲዮኖች ለመሰብሰብ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ብቻ የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ ያለበትን ኃለፊነት እንዳይወጣ ማድረግ አይቻልም፡፡

**3)** በመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ የሚተላለፉ ውሳኔዎች በጉባኤው በተሳተፉት ባለአክሲዮኖች ከተያዙት አክሲዮኖች የአብላጫውን ድምፅ ማግኘት አለባቸው፡፡

**4)** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን ምልዕተ ጉባኤ በመጀመሪያው ጉባኤ ማግኘት ያልተቻለ እንደሆነ ባለአክሲዮኖች በተመዘገበ ደብዳቤ ወይም በሌላ አመቺ የኤሌክትሮኒክ ዘዴ በድጋሚ ይጠራሉ፡፡ በድጋሚ በተጠራ ጉባዔ ላይ የተወከለው ዋና ገንዘብ ግምት ውስጥ ሳይገባ በጉባዔው በተወከሉት አክሲዮኖች አብላጫ ድምፅ ውሳኔ ይተላለፋል፡፡

**<u>አንቀጽ 526 የአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ምልዓተ ጉባኤና አብላጫ ድምፅ</u>**

1) የማኅበሩን ዜግነት ለመለወጥ ወይም በነባር አክሲዮኖች ላይ የተጻፈውን ዋጋ ከፍ በማድረግ የማህበሩን ዋና ገንዘብ ለማሳደግ የሚተላለፍ ውሳኔ የሁሉንም ባለአክሲዮኖች ስምምነት ማግኘት አለበት፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ቢኖርም፤ የማህበሩ ዋና ገንዘብ የሚጨምረው ለማህበርተኞች ሊከፋፈል ከሚችል ትርፍ ወይም የመጠባበቂያ ገንዘብ ላይ ተነስቶ ከሆነ የመመስረቻ ጽሀፍ ስለማሻሻል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ስር የተደነገገው ድጋፍ በቂ ነው፡፡
3) በማኅበሩ መመስረቻ ጽሁፍ ላይ ከፍ ያለ ምልዓተ ጉባዔ እና የድምጽ ብልጫ እንዲኖር ስምምነት ከሌለ በስተቀር፤ በመመስረቻ ጽሑፉ ላይ የሚደረግ ማሻሻያ ከማኅበሩ ዋና ገንዘብ ሶስት አራተኛውን ድርሻ በሚወክሉ ባለአክሲዮኖች ድጋፍ ማግኘት አለበት፡፡
4) በመመስረቻ ጽሑፉ ላይ የተደረጉ ማሻሻያዎች በንግድ መዝገብ ውስጥ መግባት አለባቸው፡፡

**<u>አንቀጽ 527 ተፈጻሚነት ያላቸው ድንጋጌዎች</u>**

የዚህ ምዕራፍ ልዩ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የዚህ ሕግ የአንቀጽ 392 እስከ 403 ድንጋጌዎች እንደ አግባብነታቸው ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

## ምዕራፍ ስድስት
## የማኅበሩ ሒሳቦች

**<u>አንቀጽ 528 በሕግ የተወሰነ የመጠባበቂያ ገንዘብ</u>**

የማኅበሩ የመጠባበቂያ ገንዘብ የዋናውን ገንዘብ አስር በመቶ እስከሚሞላ ድረስ ማኅበሩ ከሚያገኘው ትርፍ ቢያንስ አምስት በመቶ በየዓመቱ በመጠባበቂያ ሂሳብ መቀመጥ አለበት፡፡

**<u>አንቀጽ 529 ሐሰተኛ የትርፍ ድርሻ</u>**

1) ሐሰተኛ የሆነ የትርፍ ክፍያ የተቀበሉ ባለአክሲዮኖች እንዲመልሱ መጠየቅ ይቻላል፡፡
2) ሐሰተኛ የሆነ የትርፍ ክፍያ እንዲመለስ የሚቀርብ ጥያቄ ክፍያው ከተፈጸመበት ቀን አንስቶ በአምስት አመታት ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል፡፡

**<u>አንቀጽ 530 ተፈጻሚነት ያላቸው ድንጋጌዎች</u>**

የዚህ ምዕራፍ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፤ በዚህ ሕግ በአንቀጽ **425** እስከ **441** የተዘረዘሩት የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች እንደ አግባብነታቸው ለዚህ ምዕራፍ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## ምዕራፍ ሰባት
## የማኅበሩ መፍረስና ሒሳብ መጣራት

**<u>አንቀጽ 531 የመፍረሻ ምክንያቶች</u>**

በዚህ ሕግ አንቀጽ 186 የተመለከቱት ጠቅላላ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፤ ማኅበሩ አስፈላጊ የሆነ የአስተዳደር አካል የሌለው እንደሆነ በባለአክሲዮን ወይም በገንዘብጠያቂ በሚቀርብ ጥያቄ አግባብ ባለው ፍ/ቤት ትዕዛዝ ይፈርሳል፡፡

**<u>አንቀጽ 532 የማኅበሩ ዋና ገንዘብ ሶስት አራተኛ መጥፋት</u>**

**1)** የማኅበሩ ዋና ገንዘብ ሶስት አራተኛ በኪሳራ ከታጣ የዳይሬክተሮች ቦርድ ካለ ቦርዱ ወይም ከሌለ ስራ አስኪያጁ ስለ ማኅበሩ መፍረስ አለመፍረስ በባለአክሲዮኖች እንዲወሰን ማድረግ አለበት፡፡

**2)** ማኅበርተኞች ማኅበሩ እንዳይፈርስ ከወሰኑ ተጨማሪ መዋጮ በማድረግ የጎደለውን የማኅበሩን ዋና ገንዘብ መተካት አለባቸው፡፡

**3)** ማኅበሩ የዋና ገንዘቡን ሶስት አራተኛ በኪሳራ ማጣቱ ከታወቀበት ጊዜ አንስቶ በ3 (ሦስት) ወራት ውስጥ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተደነገገው ካልተፈፀመ ጥቅም ያለው ሰው ማኅበሩ እንዲፈርስ ለፍርድ ቤት ማመልከት ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 533 ተፈጻሚነት ያላቸው ድንጋጌዎች</u>**

የዚህ ምዕራፍ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፤ በዚህ ሕግ በአንቀጽ **473** እስከ **491** የተዘረዘሩት ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር መፍረስን እና ሒሳብ መጣራትን በሚመለከት ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## <u>ርዕስ ስምንት</u>

## <u>ባለ አንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር</u>

**<u>አንቀጽ 534 ትርጓሜ</u>**

(1) ባለ አንድ አባል ኀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ማለት አንድ ሰው በግሉ በሚሰጠው መግለጫ መሠረት የተቋቋመ የንግድ ማኅበር ነው፡፡

(2) ማኅበሩ ከአባሉ የተለየና የተነጠለ የራሱ የሕግ ሰውነት አለው፡፡

(3) አባሉ የራሱን መዋጮ ሙሉ በሙሉ እስከ ከፈለ ድረስ ማኅበሩ ላይ ለሚፈለገው ዕዳ በግሉ አይጠየቅም፡፡

**<u>አንቀጽ 535 የማኅበሩ ዋና ገንዘብ</u>**

ባለ አንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ዝቅተኛ ዋና ገንዘቡ ከብር 15,000 (አሥራ አምስት ሺ) ማነስ የለበትም፡፡

**<u>አንቀጽ 536 በግል የሚደረግ መግለጫ፤ይዘቱና አኳኃኑ</u>**

(1) ባለ አንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበርን ለማቋቋም አባሉ የሚሰጠው መግለጫ ሰነዶችን ለማረጋገጥ ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት መደረግ አለበት፤ መግልጫውም በንግድ መዝገብ ውስጥ መግባት አለበት፡፡

(2) መግለጫው የሚከተሉትን ነገሮች ማሳየት አለበት፡፡

ሀ) ማኅበሩ አንድ አባል ብቻ ያለው መሆኑን፤

ለ) የአባሉን ስም፤ዜግነትና አድራሻ፤

ሐ) አባሉ የሞተ፣ የጠፋ ወይም በፍርድ የተከለከለ እንደሆነ ስለ ወራሾቹ ወይም ስለ አባሉ ሆኖ ሕጋዊ ተግባራትን እንዲፈጽም የታጨው የንብረት ጠባቂ ሰው ስም፤

መ) ዕጩ ንብረት ጠባቂው ፍቃደኛ ሆኖ ኃላፊነቱን የተቀበለ መሆኑን፤

ሠ) የማኅበሩን ስም፤ዋና መሥሪያ ቤት፤ ካሉትም ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶቹን፤

ረ) የማኅበሩን የንግድ ዓላማ፤

ሰ) የማኅበሩ ዋና ገንዘብ መጠንና፤ይኼው በሙሉ የተከፈለ መሆኑን የሚያሳይ መግለጫ፤

ሸ) በዓይነት የተከፈለ መዋጮ ካለ ግምቱን፤

ቀ) የሥራ አስኪያጁን ስምና ሥልጣን፤

በ) ካለ ኦዲተሩን፤

ተ) ማኅበሩ የሚቆይበትን ጊዜ፤

ቸ) ማኅበሩ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት የሚያስታውቅበተን መንገድና ጊዜ፤

ኘ) ሌሎች በሕግ ወይም በአባሉ እንዲካተቱ የተወሰኑ ጉዳዮችን፡፡

**<u>አንቀጽ 537 ስለ ዕጩ ንብረት ጠባቂ</u>**

(1) ዕጩ ንብረት ጠባቂው ዕጩነቱን የተቀበለ መሆኑን ሰነዶችን ለማረጋገጥ ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት ካላረጋገጠ በስተቀር፤ ባለ አንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ሊመሠረት አይችልም፡፡

(2) አንድ ሰው በአንድ ጊዜ ለተለያዩ ባለ አንድ አባል ኃላፊነታቸው የተወሰነ የግል ማኅበራት የንብረት ጠባቂ ሆኖ መመረጥ አይችልም፡፡

**<u>አንቀጽ 538 ከግለሰብ ነጋዴነት ወደ ባለአንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ስለሚደረግ መለወጥ</u>**

ግለሰብ ነጋዴ የንግድ ሥራውን ወደ ባለ አንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበርነት መለወጥ ይችላል፡፡ ሆኖም ግን ግለሰብ ነጋዴው ባለ አንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ከመመሥረቱ በፊት ለገባበት ዕዳ ሁሉ ከማኅበሩ ጋር በአንድነት እና በተናጠል ኃላፊ ነው፡፡

**<u>አንቀጽ 539 የተከለከለ ምሥረታ</u>**

(1) አንድ ባለአንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ሌላ ባለአንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ሊያቋቁም አይችልም፡፡

(2) ማንኛውም በጉዳዩ ያገባኛል የሚል ወገን በዚህ አንቀጽ በንኡስ አንቀጽ (1) ሥር የተደነገገውን በመተላለፍ የተመሠረተ ማኅበር እንዲፈርስ ማኅበሩ በተቋቋመበት ሥፍራ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ሊያመለክት ይችላል፡፡

(3) በዚህ አንቀጽ በንኡስ አንቀጽ (2) ሥር የተደነገገው ቢኖርም፤ በንኡስ አንቀጽ (1) ላይ የተመለከተውን ክልከላ በመተላለፍ ሦስተኛ ወገኖች ላይ ለሚደርሰው ጉዳት አባሉና ማኅበሩ ባንድነትና በተናጠል ኃላፊ ናቸው፡፡

**<u>አንቀጽ 540 በዓይነት ስለሚደረግ መዋጮ</u>**

(1) አባሉ በዓይነት ያደረገው መዋጮ ካለ የመዋጮው ምንነትና ዋጋው (ወይም ግምቱ) አባሉ በዚህ ሕግ አንቀጽ 536 ንኡስ አንቀጽ(2)(ሸ) መሠረት በሚሰጠው መግለጫ ውስጥ በግልጽ መጠቀስ አለበት፡፡

(2) በዓይነት የተደረገ መዋጮ ካለ አባሉ ግምቱ ትክክል መሆኑን የሚያጣራ የምሥረታ ወቅት ኦዲተር የመሾም ግዴታ አለበት፡፡

(3) ኦዲተሩ በዓይነት የተደረገን መዋጮ ለመተመን የሚጠቀምበትን ዘዴ እራሱ ይወስናል፤ በሚያቀርበው ሪፖርት ውስጥም የተከተለውን ዘዴ መግለጽ አለበት፡፡

(4) አባሉ ያቀረበው የዓይነት መዋጮ ዋጋ ኦዲተሩ ከተመነው ዋጋ በላይ የሆነ እንደሆነ ኦዲተሩ የተመነው ዋጋ የጸና ይሆናል፡፡

(5) የዓይነት መዋጮ ግምት የተጋነነ ከመሆኑ የተነሳ ሦስተኛ ወገኖች ላይ ለሚደርሰው ጉዳት አባሉና ኦዲተሩ በአንድነትና በተናጠል ኃላፊ ናቸው፡፡

(6) በዚህ አንቀጽ በንኡስ አንቀጽ(5) መሠረት የሚቀርብ ክስ የዓይነት መዋጮው በተገቢው ሁኔታ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ በአምስት ዓመት ውስጥ ካልቀረበ ተቀባይነት የለውም፡፡

**<u>አንቀጽ 541 ስለ ዋና ሥራ አስኪያጅ</u>**

(1) ባለ አንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ዋና ሥራ አስኪያጅ ሊኖረው ይገባል፡፡ አባሉ ራሱ ወይም ሌላ ሰው የማኅበሩ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሊሆን ይችላል፡፡

(2) ዋና ሥራ አስኪያጁ በዚህ ሕግ መሠረት አንድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ሥራ አስኪያጅ ያለው ሥልጣን እና ተጠያቂነት ይኖረዋል፡፡

**<u>አንቀጽ 542 የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ</u>**

(1) የማኅበሩ አባል በዚህ ሕግ መሠረት የአንድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር አባላት ጠቅላላ ጉባዔ ያለውን ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

(2) አባሉ በጠቅላላ ጉባዔ ሥልጣኑ ያሳለፋቸው ውሳኔዎች ቃለ-ጉባዔ ስብሰባው በተደረገ ከሦስት ሳምንታት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በጽሑፍ ተዘጋጅተው የማህበሩ ማህደር ውስጥ መቀመጥ አለባቸው፡፡

(3) በማኅበሩ ምሥረታ ጊዜ በተሰጠ መግለጫ ውስጥ የተካተቱትን ነገሮች የሚለውጥ ማንኛውም ውሳኔ ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በንግድ መዝገብ ውስጥ መግባት አለበት፡፡

(4) የአባሉ ውሳኔዎች የዚህን አንቀጽ ድንጋጌዎች ያላሟሉ ቢሆኑ እንኳን በሕግ ፊት የጸኑ ናቸው፤ ሆኖም ጉድለቱ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት አባሉና ማኅበሩ በአንድነት እና በተናጠል ተጠያቂዎች ናቸው፡፡

**<u>አንቀጽ 543 የአባሉ ተጠያቂነት</u>**

ስለ አባል ኃላፊነት ውስንነት በዚህ ሕግ አንቀጽ 534 ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገው ቢኖርም፤ ማንኛውም ባለ አንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር አባል ወይም ማኅበሩ ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ቁጥጥር ያለው ሌላ ሰው ከዚህ በታች ከተመለከቱት አንዱን ፈፅሞ ከተገኘ ከማኅበሩ ጋር በአንድነት እና በተናጠል ተጠያቂ ይሆናል፡፡

1) ማኅበሩን፣ ወይም የማኅበሩን ገንዘብ ጠያቂዎች ጉዳት ላይ የሚጥል ህገ-ወጥ ድርጊት ሆን ብሎ ከፈፀመ፤
2) የባለ አንድ አባል ማኅበር ንብረትን ከራሱ ንብረት ጋር ከቀላቀለ፤
3) የባለ አንድ አባል ማኅበርን እና የራሱን ማንነት ካልነጣጠለ፤
4) ስለ ማኅበሩ የፋይናንስ አቋም የማኅበሩን ገንዘብ ጠያቂዎች ሊያሳስት የሚችል መረጃ ሆን ብሎ ካወጣ፤
5) ያለ ተመጣጣኝ ክፍያ የማኅበሩን ሀብት ለራሱ ወይም ለሶስተኛ ወገኞች የግል ጥቅም ካዋለ፤
6) በሕግ ሊከፈል ከሚችለው በላይ የትርፍ ክፍያ ከፈጸመ፤ ወይም
7) ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትን ከፈጸመ፡፡

**<u>አንቀጽ 544 ሒሳቡን ማጣራት ሳያስፈልግ ማኅበሩ ስለሚፈርስበት ሁኔታ</u>**

(1) ያለበትን ዕዳ በሙሉ የከፈለ ባለ አንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር የፈረሰ እንደሆነ የማኅበሩ ሀብት ሳይጣራና ባለበት ሁኔታ በጠቅላላው ለአባሉ ይተላለፋል፡፡

(2) በማናቸውም ምክንያት ማኅበሩ ከፈረሰ በኋላ ገንዘብ ጠያቂዎች የቀረቡ እንደሆነ አባሉ በግሉ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

(3) በዚህ አንቀጽ በንኡስ አንቀጽ (2) መሠረት የሚቀርበው ክስ ገንዘብ ጠያቂው የማኅበሩን መፍረስ ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በአምስት ዓመት ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል፡፡ የማኅበሩ ሀብት ለአባሉ ከተላለፈ ከአሥር ዓመት በኋላ ምንም ዓይነት ክስ ሊቀርብ አይችልም፡፡

(4) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) (2) እና (3) የተደነገገው ቢኖርም፤ ማኅበሩ ሲፈርስ አባሉ በራሱ ምርጫ መደበኛውን የሒሳብ ማጣራት ሂደት ለመከተል ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 545 ስለ ሌሎች ሕጎች ተፈጻሚነት</u>**

በዚህ ሕግ ስለ ባለ አንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር በተለይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበርን የሚመለከቱት የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች እንደአግባቡ በዚህ ማኅበር ላይም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## ርዕስ ዘጠኝ
## ስለንግድ ማኅበራት መለወጥ

### አንቀጽ 546 ጠቅላላ ድንጋጌ

1) አንድ የንግድ ማኅበር ወደሌላ ዓይነት የንግድ ማኅበር መለወጥ የመመስረቻ ጽሑፉን ከማሻሻል በስተቀር ሕጋዊ ሰውነት ያለው አዲስ ማኅበር መቋቋምን አያስከትልም፡፡
2) የአንድ ማኅበር መለወጥ እንደነገሩ ሁኔታ በአባላቱ ሙሉ ድምፅ፣ በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ ወይም በዚህ ሕግ በተመለከተው አብላጫ ድምጽ ይወሰናል፡፡
3) ማንኛውም የማኅበሩ አባል ያለፈቃዱ ግዴታው ከፍ እንዲል ወይም የአባልነት መብቱን በከፊል ወይም በሙሉ እንዲያጣ ማድረግ አይቻልም፡፡
4) የማኅበሩ የመለወጥ ውሳኔም ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ እና ማኅበሩ ድረ-ገጽ ካለው በድረ-ገጽ መውጣት አለበት፡፡
5) የሶስተኛ ወገኖች መብት እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ማኅበሩ ሲለወጥ የተለወጠበት ማኅበር ዓይነት የሚቋቋምበትን ሁኔታ የሚመለከቱ የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

### አንቀጽ 547 በማኅበሩ መለወጥ ያልተስማሙ ባለአክሲዮኖች መብት

በማኅበሩ መለወጥ ያልተስማሙ ማኅበርተኞች በዚህ ሕግ አንቀጽ 403 ድንጋጌ መሰረት ድርሻቸውን ለማኅበሩ ሸጠው ከማኅበሩ መውጣት ይችላሉ፡፡

### አንቀጽ 548 የገንዘብ ጠያቂዎች መብት

1) የተለወጠው ማኅበር መብትና ግዴታ በንግድ መዝገብ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ለአዲሱ ማኅበር ይተላለፋል፡፡
2) አዲሱ ማኅበር እንደተመዘገበ ወዲያውኑ የቀድሞው ማኅበር ገንዘብ ጠያቂዎች ማስረጃቸውን እንዲያቀርቡና ተቃራኒ ሀሳብ ካላቀረቡ አዲሱ ማኅበር ዕዳ ከፋያቸው መሆኑ ይገለጽላቸዋል፡፡
3) ገንዘብ ጠያቂዎችን ለመጥራት በዚህ ሕግ አንቀጽ 484 የተመለከተው ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት ገንዘብ ጠያቂዎች ገንዘባቸው እስከሚከፈላቸዉ ወይም በቂ ዋስትና እስከሚሰጣቸዉ ድረስ ከማኅበሩ ሀብት ላይ ለአባላት ክፍያ አይፈጸምም፡፡

**5)** ስራ አስኪያጁ ወይም እንደነገሩ ሁኔታው የማኅበሩ ፀሐፊ የቀድሞው ማኅበር መለወጥን ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ እንዲገለፅ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተደነገገው ከተፈፀመ በኋላ የቀድሞው ማኅበር ከንግድ መዝገብ እንዲሰረዝ ማድረግ አላባቸዉ፡፡

**6)** ስራ አስኪያጁ እና የማኅበሩ ፀሐፊ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (**2)** እስከ (**5**) የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ለማስፈፀም በአንድነትና በተናጠል ኃላፊዎች ይሆናሉ፡፡

**<u>አንቀጽ 549 የሸሪኮች ኃላፊነት</u>**

**(1)** የማኅበሩ ገንዘብ ጠያቂዎች የማኅበሩን መለወጥ የተቀበሉ መሆናቸው ካልተረጋገጠ በስተቀር፤ ኃላፊነታቸዉ ያልተወሰነ ሸሪኮች የመለወጡ ውሳኔ በንግድ መዝገብ ከመመዝገቡ በፊት ማኅበሩ ለገባው ግዴታ ከነበረባቸዉ ኃላፊነት ነፃ አይሆኑም፡፡

**(2)** የማኅበሩ ገንዘብ ጠያቂዎች ስለ ማኅበሩ መለወጥ ማኅበሩ ያሳለፈው ውሳኔ በተመዘገበ ደብዳቤ ወይም ቀድመው በመረጡት የኤሌክትሮኒክ ዘዴ ተልኮላቸው ከተላከበት ቀን አንስቶ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ለውጡን እንደሚቃወሙ በግልጽ በጽሑፍ ካላሳወቁ የማኅበሩን መለወጥ እንደተቀበሉ ይቆጠራል፡፡

**<u>ርዕስ አስር</u>**

**<u>የንግድ ማህበራት መዛመድ፣ መዋሃድና መከፋፈል</u>**

**<u>ምእራፍ አንድ</u>**

**<u>የንግድ ማኅበራት መቧደን</u>**

**<u>አንቀጽ 550 ቡድን፡ ትርጓሜ</u>**

1) “ቡድን” ማለት የእናት ኩባንያ እና ተቃራኒ ድንጋጌ እሰከሌለ ድረስ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር የተመዘገቡ የሁሉም ተቀጥላዎቹ ማህበራት ስብስብ ነው፡፡
2) “ተቀጥላ” ማለት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ በሌላ ኩባንያ አመካኝነት በእናት ኩባንያ ቁጥጥር ስር የወደቀ ኩባንያ ነው፡፡
3) “እናት” ማለት በቀጥታም ሆነ በሌላ ኩባንያ አመካኝነት በተዘዋዋሪ ሌላ ኩባንያን በቁጥጥር ስር ያደረገ ኩባንያ ነው፡፡
4) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) ዓላማ “ቁጥጥር” በአንቀጽ 552 ስር የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፡ ፡
5) ለዚህ ርዕስ ድንጋጌዎች ዓላማ « ኩባንያ » ማለት የአክሲዮን ማኅበር፣ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር፤ ባለአንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር እና እንደ ሁኔታው ውጭ አገር የተመዘገቡ ከነዚህ ጋር ተመሳሳይ ባህሪ ያላቸውን የንግድ ማኅበራት ያጠቃልላል፡፡

**<u>አንቀጽ 551 ሙሉ በሙሉ በባለቤትነት የተያዘ ኩባንያ</u>**

“ሙሉ በሙሉ በባለቤትነት የተያዘ ኩባንያ” ማለት ከእናት ኩባንያው እና ከእናት ኩባንያው ሌላ ተቀጥላ ኩባንያ ወይም በእናት ኩባንያው ስም ከሚሠሩ ሰዎች ወይም በእናት ኩባንያው ተቀጥላዎች ስም ከሚሰሩ ሰዎች በስተቀር ሌላ የውጭ ባለአክስዮኖች የሌሉበት ኩባንያ ማለት ነው፡፡

**<u>አንቀጽ 552 ቁጥጥር ፡ ትርጓሜ</u>**

**1)** ለዚህ ምዕራፍ ዓላማ “ቁጥጥር” አለ የሚባለው እናት ኩባንያው ብቻውን ወይም ከሌሎች ባለአክሲዮኖች ጋር በመሆን የተቀጥላ ኩባንያውን የፋይናንስ እና የአሰራር ፖሊሲዎችን የመንደፍ እና የመምራት ስልጣን ሲኖረው ነው፡፡

**2)** የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሁኖ፤አንድ እናት ኩባንያ የአንድን ተቀጥላ ኩባንያ ከግማሽ በላይ ካፒታል የሚወክሉ ድምጽ የመስጠት መብት የሚያጎናጽፉ አክሲዮኖችን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በባለቤትነት ከያዘ በተቀጥላው ላይ ቁጥጥር እንዳለው ይወሰዳል፡፡ ሆኖም፤ እናት ኩባንያው በተቀጥላው ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የያዘው ይህ መጠን ያለው ድርሻ በልዩ ሁኔታ ቁጥጥር እንደማይሰጠው በግልጽ ማሳየት ከተቻለ የ« ቁጥጥር » መኖር ሕጋዊ ውጤቶች አይኖሩም፡፡

**3)** አንድ ኩባንያ በሌላ ኩባንያ ውስጥ ያለው ድምጽ የመስጠት መብት የሚያጎናጽፍ የአክሲዮን ድርሻ የሁለተኛውን ኩባንያ ዋና ገንዘብ ግማሽ ወይም ከዚያም ያነሰ የሚወክል ቢሆን እንኳን ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ሁኔታዎች አንዱ ወይም ከዚያ በላይ ተሟልቶ ሲገኝ በሁለተኛው ላይ ቁጥጥር እንዳለው ይቆጠራል፤

(ሀ) ከሌሎች ባለአክሲዮኖች ጋር በተደረገ ስምምነት ከግማሽ በላይ የሆነውን ድምፅ የመስጠት መብት ከተጎናጸፈ፤

(ለ) በመመስረቻ ጽሑፍ ወይም በሌላ ስምምነት የኩባንያውን የፋይናንስ እና አሠራር ፖሊሲዎችን የመቆጣጠር መብት ከተጎናጸፈ፤

(ሐ) የኩባንያውን ንግድ የመምራት ሥልጣን ካለው የኩባንያው ከፍተኛ የአስተዳደር አካል አባላት መካከል አብዛኛዎቹን የመሾምና የመሻር መብት ካለው፤ ወይም

(መ) የጠቅላላ ጉባዔ ወይም ተመሳሳይ ስልጣን ያለው የኩባንያው ውሳኔ ሰጪ አካል ውስጥ አብላጫ ድምጽን መስጠት ወይም ማግኘት በመቻሉ በተጨባጭ የኩባንያውን ንግድ መቆጣጠር ሲችል፡ ፡

**4)** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ **3 (ሐ)** እና **(መ)** መሰረት ቁጥጥር አለ የሚባለው የኩባንያውን ግማሽ ወይም ከግማሽ የሚያንሱ አክሲዮኖች የያዘው ኩባንያ አንድን ኩባንያ የመምራት ሥልጣን ካለው የኩባንያው ከፍተኛ የአስተዳደር አካል ወይም ውሳኔ ሰጪ አካል አባላት ውስጥ አብዛኛዎቹን ለሁለት ተከታታይ የፋይናንስ ዓመታት መሾም የቻለ እንደሆነ ነው፡፡ በፋይናንስ ዓመቱ ውስጥ ይሄው ኩባንያ በሁለተኛው ኩባንያ ውስጥ ያለው ድምጽ የመስጠት መብት ከጠቅላላው አርባ በመቶ በላይ ሲሆን እና በዚሁ በሁለተኛው ኩባንያ ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከእርሱ የበለጠ የድምጽ ድርሻ ያለው ሌላ

ባለአክስዮን ከሌለ የሁለተኛውን ኩባንያ ከፍተኛ ስራ አስፈጻሚ ወይም ውሳኔ ሰጪ አካል አባላት እርሱ ስለመሾሙ ግምት ይወሰድበታል፡፡

**<u>አንቀጽ 553 ተሳትፎን ስለ መተመን</u>**

1) ቁጥጥር መኖር አለመኖሩን ለመወሰን የድምጽ ተሳትፎ መጠን በሚሰላበት ጊዜ ወድያውኑ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል ድምጽ የመስጠት መብት የሚያጎናጽፉ አዲስ አክሲዮኖችን ከኩባንያው የመግዛት ወይም በለውጥ የማግኘት መብት ታሳቢ ይደረጋል፡፡

2) በተቀጥላ ኩባንያ ውስጥ እናት ኩባያው ያለው የተሳትፎ መጠን ሲሰላ በተቀጥላ ድርጅቱ በራሱ ወይም በተቀጥላው ተቀጥላ ኩባንያዎች የተያዙ ድምጽ የመስጠት መብት የሚያጎናጽፉ አክሲዮኖች ካሉ እነኝህ ድምጽ የሚያስጡ የአክስዮን መብቶች ስሌት ውስጥ መግባት የለባቸውም፡፡

**<u>አንቀጽ 554. ቁጥጥርን የማስታወቅ ኃላፊነት</u>**

1) የእናት ኩባንያው የሥራ አመራር የቁጥጥር ሁኔታ ስለመቋቋሙም ሆነ ስለመቅረቱ ወዲያውኑ ለተቀጥላ ኩባንያው የሥራ አመራር በጽሑፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

2) ተቀጥላ ኩባንያው ማስታወቂያው እንደደረሰው ወዲያውኑ በእናት ኩባንያው ውስጥም ሆነ በሌሎች ኩባንያዎች ውስጥ ያሉትን የአክሲዮኖች ቁጥር እና ድምፅ የሚያሰጡ መብቶችን ለእናት ኩባንያው በጽሑፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡ ተቀጥላው ኩባንያ በውጪ አገር የተመዘገበ ሲሆን እና ተቀጥላውን የሚገዛው የውጭ አገር ሕግ ይህ አይነቱን ግዴታ መወጣት የሚከለክል ከሆነ የዚህ ንዑስ አንቀጽ ድንጋጌ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**<u>አንቀጽ 555 አንድ ኩባንያ ከሌላ ኩባንያ ስለሚኖረው አክሲዮን</u>**

1) ተቀጥላ ኩባንያ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በእናት ኩባንያው ውስጥ ምንም አክሲዮን መያዝ የለበትም፡፡

2) የእናት እና ተቀጥላ ግንኙነት ባይኖርም የአንድ ኩባንያ ዋና ገንዘብ አምስት በመቶ ወይም ከዚያ በላይ የሆነው ድርሻ በሌላ ኩባንያ የተያዘ ከሆነ የመጀመሪያው ኩባንያ በሁለተኛው ኩባንያ ውስጥ አክሲዮኖች ሊኖሩት አይችልም፡፡

3) ሁለት ኩባንያዎች አክሲዮኖቻቸውን የተገዛዙ ሆኖ አንዱ ኩባንያ ከሌላው ኩባንያ ዋና ገንዘብ ውስጥ አምስት በመቶ ወይም ከዚያ በላይ የገዛ ከሆነ ይዞታቸዉን ለንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም አግባብ ላለው ሌላ ባለስልጣን መስሪያ ቤት ማስታወቅ አለባቸው፡፡ ሚኒስቴሩ ወይም ይሄው አካል ኩባንያዎቹ በስምምነት ያላቸውን አክሲዮኖች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ **2** ስር በተመለከተው መሠረት ማስተካከያ እንዲያደርጉ ያሳውቃቸዋል፡፡ በዚህ መሠረት በስምምነት ማስተካከያ ለማድረግ ካልቻሉ ሚኒስቴሩ ወይም ይሄው አካል ከመካከላቸው አነስተኛ ይዞታ ያለው ኩባንያ ይዞታውን እንዲያስተላልፍ ያዘዋል፡፡

4) አንዱ ኩባንያ በሌላው ኩባንያ ውስጥ ያለው ይዞታ እኩል የሆነ እንደሆነና አንደኛው ኩባንያ በሌላኛው ኩባንያ ውስጥ ያለውን አክሲዮን ለማስተላለፍ ያልተስማማ እንደሆነ እያንዳንዳቸው በሌላው ኩባንያ ውስጥ ያለው የአክሲዮን ድርሻ ከአምስት በመቶ ያነሰ እስኪሆን መቀነስ አለበት፡፡

5) ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ላለው ባለስልጣን ይህ ስለመሆኑ የጽሁፍ መግለጫ ማቅረብ አለባቸው፡፡ የዚህ ንዑስ አንቀጽ ድንጋጌ እስኪፈጸም ድረስ መተላለፍ ያለባቸው አክሲዮኖች የሚሰጡት ትርፍ የመካፈልም ሆነ ድምጽ የመስጠት መብት ታግዶ ይቆያል፡፡

## አንቀጽ 556 የእናት ኩባንያው ለተቀጥላ ኩባንያው አመራር/ትእዛዝ/ የመስጠት መብት

1) እናት ኩባንያ እንደባለአክሲዮን በጠቅላላ ጉባዔ በሚሳተፍበት ጊዜ፣ በዳይሬክተሮቹ ቦርድ እንዲሁም በከፍተኛ የሥራ አመራሩ አመካኝነት ለተቀጥላው ኩባንያ አመራር ወይም ትዕዛዝ መስጠት ይችላል፡፡

2) በዚህ ሕግ አንቀጽ 563 እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ስር የተመለከቱት ልዩ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፤ የተቀጥላ ኩባንያው አመራር በእናት ኩባንያው የተሰጠን ትዕዛዝ መፈጸም አለበት፡፡

3) በእናት ኩባንያው ምርጫ ሳይሆን በኩባንያው የመተዳደሪያ ደንብ ወይም በባለአክሲዮኖች ስምምነት ወይም በማናቸውም ሕግ መሠረት የተሾሙ ዳይሬክተሮች እና የስራ አመራር አባላት እናት ኩባንያው የሚሰጠውን ትዕዛዝ ለመከተል አይገደዱም፡፡

4) ሙሉ ለሙሉ በእናት ኩባንያ ባለቤትነት ያልተያዘ ተቀጥላ ኩባንያ ከእናት ኩባንያው በሚሰጥ ትዕዛዝ መሰረት የሚመራ መሆን ወይም አለመሆኑን በንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒቴር ወይም በሚመለከተው ሌላ አካል በሚያዘው የንግድ መዝገብ ውስጥ በግልጽ ማሳወቅ አለበት፡፡

5) ተቃራኒው እስካልተገለጸ ድረስ፣ ሙሉ ለሙሉ በባለቤትነት የተያዘ ተቀጥላ ኩባንያ አመራር ከእናት ኩባንያው መመሪያ/ትዕዛዝ እንደሚቀበል ግምት ይወሰዳል፡፡ ይህም ሲሆን ኩባንያው በንግድ መዝገብ ውስጥ ማስገባት ያለበት ሙሉ ለሙሉ በባለቤትነት ስለመያዙ ብቻ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 557 በተቀጥላ ኩባንያ ደረጃ ስለሚኖር መረጃ የማግኘት መብት

የእናት ኩባንያ የዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም ተመሳሳይ ደረጃ ላይ ያለ የስራ አመራር ክፍል ከተቀጥላ ኩባንያው ማናቸውንም መረጃዎች የማግኘት መብት አለው፡፡ ሆኖም መረጃው መሰጠቱ ተቀጥላውን ኩባንያ በሚገዛ የሌላ አገር ሕግ የተከለከለ ከሆነ ወይም የሦስተኛ ወገኖችን መብት የሚጎዳ ከሆነ ለእናት ኩባንያው መረጃው መተላለፍ የለበትም፡፡

## አንቀጽ 558 አክሲዮን ገዝቶ የማስወጣት መብት

1) የተቀጥላውን ኩባንያ ዋና ገንዘብ እና ድምጽ ዘጠና በመቶ የተቆጣጠረ እናት ኩባንያ በተቀጥላው ውስጥ ያሉት ቀሪዎቹ ባለአክሲዮኖች ድርሻቸውን ሸጠውለት እንዲወጡ የማስገደድ መብት አለው፡፡

**2)** በዚህ ዓይነቱ ግዥ ላይ በዚህ ሕግ አንቀጽ 294(2) እስከ (7) ስር የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

**አንቀጽ 559 የእናት ኩባንያ ባለአክሲዮኖች መብት**

1) የእናት ኩባንያ ባለአክሲዮኖች በቡድኑ ስለታቀፉት ኩባንያዎች እንዲሁም የቡድኑ አባል ስለነበሩት ኩባንያዎች ግንኙነት መረጃ የማግኘትና ልዩ ምርመራ እንዲደረግ የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡
2) የእናት ኩባንያው ባለአክሲዮኖች ተቀጥላ ኩባንያን በተመለከተ በተለይ በዚህ ሕግ አንቀጽ 355፣358 እና 381(1)ሀ እና ለ ስር የተመለከተው መብት አላቸው፡፡

**አንቀጽ 560 በቡድን ውስጥ ስለሚኖር የንግድ ዕድሎች**

በኢትዮጵያ ወይም በውጭ አገር የተመዘገበ እናት ኩባንያ በራሱ ወይም በሌላ ተቀጥላው አመካይነት የተቀጥላ ኩባንያውን የንግድ ዕድል/አጋጣሚ/ መቀማት የለበትም፡፡ ሆኖም በእናት ኩባንያው ካልተሾሙት የተቀጥላው ዳይሬክተሮች ከሌሉም ተቀጥላውን ከማይቆጣጠሩት የተቀጥላው ባለአክሲዮኖች ይሁንታን ካገኘ እናት ኩባንያው በንግድ ዕድሉ መጠቀም ይችላል፡፡ በዚህ አንቀጽ በእናት ኩባንያ ላይ የተጣለው ክልከላ ሙሉ በሙሉ በባለቤትነት የተያዘ ተቀጥላን በተመለከተ ተፈጻሚነት የለውም፡፡

**አንቀጽ 561 ልዩ ምርመራ እንዲደረግ የመጠየቅ መብት**

ከኩባንያው ዋና ገንዘብ አስር በመቶ የሚወክል ድምጽ የመስጠት መብት ያላቸው የተቀጥላ ኩባንያ ባለአክሲዮኖች የተቀጥላውን ጥቅም የሚነካ ውሳኔን በተመለተ በእናት ኩባንያው ላይ ልዩ ምርምራ እንዲደረግ የመጠየቅ በዚህ ሕግ አንቀጽ 559 ስር የተመለከተው ዓይነት መብት አላቸው፡፡

**አንቀጽ 562 አክሲዮን ሽጦ የመውጣት መብት**

**1)** እናት ኩባንያው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከዘጠና በመቶ በላይ የሚሆነውን  ድምፅ የመስጠት መብት የሚያጎናጽፉ አክሲዮኖችን በተቀጥላው ውስጥ በባለቤትነት ከያዘ ሌሎቹ የተቀጥላው ባለአክሲዮኖች እናት ኩባንያው አክሲዮኖቻቸውን እንዲገዛቸው መጠየቅ ይችላሉ፡፡

**2)** የተቀጥላ ኩባንያው ባለአክሲዮኖች እናት ኩባንያው ወይም በእርሱ የተወከለ ሌላ ሰው አክስዮናቸውን እንዲገዛቸው በፍርድ ቤት መጠየቅ ይችላሉ፡፡

**3)** የዚህ ዓይነቱን ሽያጭ አፈጻጸም በተመለከተ በዚህ ሕግ አንቀጽ 292(2) እስከ (5) ስር የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

**አንቀጽ 563 ስለቡድን ጥቅሞች**

1) የተቀጥላ ኩባንያ የሥራ አመራር ወይም ዳይሬክተር በእናት ኩባንያው በተሰጠ መመሪያ አማካይነት ሆነም አልሆነ ከተቀጥላ ኩባንያው ጥቅም ተፃራሪ /ተቃራኒ/ ሊባል የሚችል ውሳኔ በመወሰኑ የተጣለበትን እምነት ወይም ኃላፊነት እንዳልተወጣ የማያስቀጥረው፤

(ሀ) ውሳኔው በአጠቃላይ ቡድኑን የሚጠቅም ከሆነ እና

(ለ) የሥራ አመራሩ የጥቅም መጓደል ወይም ጉዳት ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ ውስጥ ይገኛል በሚባል ጥቅም ይካካሳል ብሎ ከገመተ እና ይኸውም ግምት የሥራ አመራሩ በጊዜው በነበረው መረጃ ላይ መሠረት አድርጎ ብቻ ሳይሆን ውሳኔውን ለመወሰን አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን በሚጠበቅበት ደረጃ አሰባስቦ መሆን ይኖርበታል፤ እንዲሁም

(ሐ) የጥቅም መጓደሉ ወይም ጉዳቱ የኩባንያውን ዘለቄታዊ ህልውና አደጋ ላይ የማይጥለው ሲሆን፤

ብቻ ነው፡፡

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ለ) ሙሉ ለሙሉ በባለቤትነት የተያዘ ተቀጥላ ኩባንያን በተመለከተ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ያልተሟላ እንደሆነ የተቀጥላ ኩባንያው የሥራ አመራር የእናት ኩባንያውን ትዕዛዞች እና መመሪያዎች ላለመቀበል ወይም ላለመፈጸም ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 564 አሳሳች የግብይት አሠራር</u>**

1) የቡድኑን ጥቅም ለማስጠበቅ ተብሎም ቢሆን በእናት ኩባንያው በተሰጡ ትዕዛዞች የተመራ ተቀጥላ ኩባንያ በራሱ ሀብት ወይም አቅም ከተጋረጠበት የመፍረስ ወይም የንብረት መጣራት አደጋ መዳን መቻሉ ተስፋ የሚጣልበት ካልሆነ፣እናት ኩባንያው ይህ ከተከሠተበት ጊዜ ጀምሮ ሳይዘገይ መፍትሄ መሆን የሚችል ሥር ነቀል የመዋቅር ለውጥ በተቀጥላ ኩባንያው ላይ ማካሄድ ወይም የኩባንያው ንብረት እንዲጣራ ሂደቱን መጀመር ይኖርበታል፡፡

2) እናት ኩባንያው የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተላለፈ እንደሆነ የተገለጸው አደጋ ከተፈጠረበት ጊዜ በኋላ ለመነጨ እና ላልተከፈሉ የተቀጥላ ኩባንያው ዕዳዎች ተጠያቂ ነው፡፡

3) እናት ኩባንያው ተቀጥላውን የመራው ተቀጥላውን በሚጎዳ እና የቡድኑን ጥቅም በሚጻረር አኳኋን ከሆነ ጉዳት ባደረሰው ትዕዛዝ ምክንያት ተቀጥላው ለገባበት ያልተከፈለ የተቀጥላው ዕዳ በሙላ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) መሠረት የካሣ መብት ጥያቄ የሚቀርበው በተቀጥላ ኩባንያው ሂሣብ አጣሪ ወይም በንብረት ጠባቂ ብቻ ነው፡፡ ከተቀጥላው ኩባንያ ዕዳ ከአስር በመቶ ያላነሰ ዕዳ የያዙ ባለገንዘቦች ጥያቄ ያቀረቡለት እንደሆነ የኩባንያውን ሂሣብ አጣሪ ወይም እንደነገሩ ሁኔታ ንብረት ጠባቂው ይህንን የመብት ጥያቄ ማቅረብ አለበት፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## የማኅበራት መዋሃድ እና መከፋፈል

### አንቀጽ 565 የማኅበራጽ መዋሀድ

1) የማኅበራጽ መዋሃድ ማለት ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ማኅበራጽ ውህደት በመፍጠር አንድም ማኅበራቱ ተቀላቅለው አንዱ ሌላውን ወይም ሌሎቹን በመዋጥ፣ አልያም ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ማኅበራጽ አዲስ ማኅበር በማቋቋም አዲስ በተቋቋመው ማኅበር ውስጥ ገብተው በመጠቃለል ሊሆን ይችላል፡፡
2) አዲስ ማኅበር በመመስረት የሚደረግ መዋሃድ ማለት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ማኅበራት ሙሉ ንብረታቸውን እና እዳቸውን አዲስ ወደ አቋቋሙት ማኅበር በማስተላለፍ የንብረት ማጣራት ሳይደረግ የሚከስሙበት ሂደት ነው፡፡ ንብረት እና ዕዳቸውን በማስተላለፍ ለከሰሙት ማህበራት ባለአክሲዮኖች ወይም ሸሪኮች በአዲሱ ማህበር ውስጥ ምትክ አክሲዮኖች ወይም ድርሻ ይሰጣል፡፡ እንደነገሩ ሁኔታ ተጨማሪ ጥሬ ገንዘብም ሊከፈላቸው ይችላል፡፡
3) በነባር ማኅበር በመዋጥ የሚደረግ መዋሃድ ማለት አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ማኅበራጽ ሙሉ ንብረታቸውን እና እዳቸውን ወደ ሌላ ነባር ማኅበር በማስተላለፍ የንብረት ማጣራት ሳይደረግ የሚከስሙበት ሂደት ነው፡፡ የተዋጠው ማኅበር ባለአክሲዮኖች ወይም ሸሪኮች ማኅበራቸውን በዋጠው ማኅበር ውስጥ ምትክ አክሲዮኖች ወይም ድርሻ ይሰጣቸዋል፡፡ እንደነገሩ ሁኔታ ተጨማሪ ጥሬ ገንዘብም ሊከፈላቸውም ይችላል፡፡
4) ለመፍረስ በመጣራት ላይ ያለ ማኅበር የንብረት ክፍፍል ከመደረጉ በፊት ከሌላ ማኅበር ጋር ሊዋሀድ ይችላል፡፡
5) ውህደት በማናቸውም የንግድ ማኅበር ዓይነቶች መካከል ሊደረግ ይችላል፡፡

### አንቀጽ 566 የማኅበራት መከፈል

1) የማህበር መከፈል ማለት የአንድ ማኅበር ሙሉ ንብረት እና እዳዎች ከአንድ በላይ ለሆኑ ሌሎች ነባር ወይም አዲስ ለሚቋቋሙ ማኅበሮች ተከፋፍሎ የሚከፈለው ማህበር የሒሳብ ማጣራት ሳይደረግ የሚከስምበት ሁኔታ ነው፡፡ የተከፈለው ማኅበር ባለአክሲዮኖች ወይም ሸሪኮች የማኅበሩን ንብረት በተከፋፈሉት ማኅበራት ውስጥ ምትክ አክሲዮኖች ወይም ድርሻ ይሰጣቸዋል፡፡ እንደነገሩ ሁኔታ ተጨማሪ ጥሬ ገንዘብም ሊከፈላቸው ይችላል፡፡
2) ወደ ነባር ማኅበራት በመጠቅለል የሚደረግ መከፈል ማለት አንድ ማኅበር መላ ንብረቱን እና ዕዳውን ለሌሎች ነባር ማኅበራት አከፋፍሎ የሒሳብ ማጣራት ሳይደረግ የሚከስምበት ሁኔታ ነው፡፡ ለተከፈለው ማኅበር ባለአክሲዮኖች ወይም ሸሪኮች የማኅበሩን ንብረት በተከፋፈሉት ማኅበራት ውስጥ ምትክ አክሲዮኖች ወይም ድርሻ ይሰጣቸዋል፡፡ እንደነገሩ ሁኔታ ተጨማሪ ጥሬ ገንዘብም ሊከፈላቸው ይችላል፡፡
3) አዲስ ማኅበራትን በማቋቋም የሚደረግ መከፈል ማለት አንድ ማኅበር መላ ዕዳውን እና ንብረቱን እራሱ ለአቋቋማቸው ማኅበራት በማስተላለፍ የሒሳብ ማጣራት ሳይደረግ የሚከስምበት ሁናቴ ነው፡፡ ለተከፈለው

ማኅበር ባለአክሲዮኖች ወይም ሽሪኮች የማኅበሩን ንብረት በተከፋፈሉት ማኅበራት ውስጥ ምትክ አክሲዮኖች ወይም ደርሻ ይሰጣቸዋል፡፡ እንደነገሩ ሁኔታ ተጨማሪ ጥሬ ገንዘብም ሊከፈላቸው ይችላል፡፡

**4)** የተወሰነ የሀብት ክፍል መከፈል ማለት የአንድ ማኅበር የተወሰነ እና ተለይቶ ሊቀጥል የሚችልን የንግድ ስራ (ቢዝነስ ዩኒት) ወይም የሀብት ክፍል በመለየት አዲስ ወደሚቋቋም ማኅበር ወይም ነባር ማኅበር በመዋጮነት ማስተላለፍ ማለት ነው፡፡

**<u>አንቀጽ 567 የውህደት ወይም የመከፈል ዕቅድ</u>**

**1)** የውህደት ወይም የመከፈል ዕቅድ በሚዋሀዱት ወይም በመከፈሉ በሚሳተፉት ማኅበራት ተዘጋጅቶ በእያንዳንዱ ማኅበር የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ ወይም ማህበሩ ቦርድ ከሌለው በዋና ስራ አስኪያጅ መፈረም አለበት፡፡

**2)** የውህደት ወይም የመከፈል ዕቅድ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡-

**(ሀ)** የሚዋሀዱትን ወይም የሚከፈሉትን ማኅበራት ዓይነት፣ የንግድ ስምና የዋና መስሪያ ቤት አድራሻ፤

**(ለ)** ውህደቱ ወይም መከፈሉ አዲስ ማኅበር የሚያስገኝ ከሆነ የማኅበሩን ዓይነት፣ የንግድ ስምና የዋና መስሪያ ቤቱን አድራሻ፤

**(ሐ)** የውህደቱ ወይም የመከፈሉ ኢኮኖሚያዊ ምክንያትና ሁኔታ፤

**(መ)** የእያንዳንዱን ማኅበር የፀደቀ ዓመታዊ የተጠቃለለ የሒሳብ ሪፖርት፤

**(ሠ)** ወደጠቅላዩ ወይም አዲሱ ማኅበር የተዛወረውን ሀብት ወይም ተለይቶ ሊቀጥል የሚችል የንግድ ሥራ እና ዕዳ መግለጫ፣ የሀብት ግምትና የአገማመቱን ሁኔታ፤

**(ረ)** በውህደቱ ወይም በመከፈሉ ምክንያት የሚሰጡት አክሲዮኖች ወይም ድርሻዎች የሚደለደሉበት ተመን እና ተጨማሪ የገንዘብ ክፍያ የሚደረግ ከሆነ አወሳሰኑን፣ አክሲዮኖቹ ወይም ድርሻዎቹ ትርፍ ማስገኘት የሚጀምርበትን ቀን እና የዚህ መብት አጠቃቀምን የሚመለከቱ ልዩ ሁኔታዎች ካሉ ሁኔታዎቹን፤

**(ሰ)** በውህደቱ ወይም በመከፈሉ ባለመስማማታቸው ከማኅበሩ ለሚወጡ አባላት የሚሰጠውን የገንዘብ መጠን፤

**(ሸ)** ተጠቅላዩ ወይም ተከፋዩ ማኅበር ያከናወናቸው ተግባራት በጠቅላዩ ወይም አዲስ በሚቋቋመው ማኅበር እንደተከናወኑ መቆጠር የሚጀምሩበትን ቀን፤

**(በ)** ያልተወሰነ ኃላፊነት ያለባቸው ባለድርሻዎች ካሉ ስማቸውን፤

**(ተ)** ከመደበኛ አክሲዮኖች የተለየ ጥቅምና ልዩ መብት የሚያስገኙ አክሲዮኖችን ለያዙ አባላት የሚሰጥ መብትና ጥቅም፤

**(ቸ)** ውህደቱ ወይም መከፈሉ የሚያስከትለውን ግዴታ እና ኃላፊነት እንዲሁም በገንዘብ ጠያቂዎች ላይ የሚኖረውን ተጽዕኖ፤

(ነ) የውህደቱን ወይም የመከፈሉን ዕቅድ ለሚገመግሙት ገለልተኛ ባለሞያዎች ወይም ኦዲተሮች የሚከፈለውን ክፍያ ወይም የሚሰጠውን ልዩ ጥቅም በተመለከተ የተሟላ መረጃ፤ እና

**(ኘ)** በውህደቱ ወይም መከፈሉ ምክንያት አዲስ ማኅበር የሚቋቋም ከሆነ ረቂቅ የመመስረቻ ጽሁፍ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው መረጃዎችን፡፡

**<u>አንቀጽ 568 የውህደት ወይም መከፈል ሪፖርት</u>**

1) በውህደቱ ወይም በመከፈሉ የሚሳተፈው እያንዳደንዱ ማኅበር የዳይሬክተሮች ቦርድ፤ ማሕበሩ ቦርድ ከሌለው ዋናው ስራ አስኪያጅ ለማሕበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የውህደት ወይም የመከፈል ዕቅዱን የሚያብራራ ዝርዝር ሪፖርት በጽሑፍ ማቅረብ አለበት፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ሪፖርት የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡-

**(ሀ)** የውህደቱን ወይም የመከፈሉን ኢኮኖሚያዊ አላማና ካለም ሕጋዊ ምክንያት፤

**(ለ)** የውህደቱን ወይም የመከፈሉን ስምምነት፤

**(ሐ)** ለባለአክሲዮኖች ወይም ለሽሪኮች በለውጥ የሚሰጡት አክሲዮኖች ወይም ድርሻዎች አተማመን እና መጠን እንዲሁም ካለ የማስተካከያ ክፍያ፣

**(መ)** በውህደቱ ወይም በመከፈሉ ባለመስማማታቸው ከማኅበሩ ለሚወጡ አባላት በጥሬ ገንዘብ የሚሰጠዉን ክፍያ፤

**(ሠ)** ውህደቱን በተመለከተ በቅድሚያ ፈቃድ ማግኘት የሚያስፈልግ ከሆነ አግባብ ካለው አካል ፈቃድ የተሰጠ መሆኑን፣

**(ረ)** ውህደቱ ወይም መከፈሉ በውህደቱ ወይም በመከፈሉ ተሳታፊ በሆኑ ማኅበራት ሰራተኞች ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ተጽዕኖ፤ እና

(**ሰ)** ሌሎች አግባብነት ያላቸው መረጃዎችን፡፡

**<u>አንቀጽ 569 የውህደት ወይም የመከፈል ግምገማ</u>**

1) የውህደት ወይም የመከፈል ዕቅድ፤ የውህደት ወይም መከፈል ሪፖርት እና ሌሎች አስፈላጊ የውህደት ወይም መከፈል ሁኔታዎች በነጻ እና ገለልተኛ ባለሞያ መገምገም አለባቸው፡፡
2) በውህደቱ ወይም መከፈሉ የሚሳተፉት ማህበራት እያንዳንዳቸው የየራሳቸው ነጻ እና ገለልተኛ ገምጋሚ ባለሙያ ይሾማሉ፡፡ ሆኖም በውህደቱ ወይም በመከፈሉ የሚሳተፉት ማኅበራት በሙሉ የተስማሙ እንደሆነ በጋራ አንድ ባለሙያ ሊሾሙ ይችላሉ፡፡ ነጻ እና ገለልተኛ ባለሞያው የሚሾመው በዚህ መጽሐፍ የአክሲዮን ማኅበር ኦዲተር አሿሿምን በተመለከተ በተደነገገው ስርዓት መሰረት ይሆናል፡፡
3) በውህደቱ ወይም በመከፈሉ የሚሳተፉ ማኅበራት ለግምገማው አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችንና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን ሁሉ ለገምጋሚ ባለሞያዎች ማቅረብ አለባቸው፡፡

**4)** ነጻ እና ገለልተኛ ገምጋሚው ለሾመው ማኅበር ባለአክሲዮኖች ወይም ሸሪኮች የሚከተሉትን በተመለከተ የራሱን አስተያየት በጽሁፍ ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡-

**(ሀ)** በውህደቱ ወይም በመከፈሉ ተካፋይ ለሆኑ ማኅበራት አባላት በለውጥ የሚሰጡትን አክሲዮኖች ወይም ድርሻ መጠን እና ዓይነት፤ ተመኑ ፍትሐዊ እና ምክንያታዊ ስለመሆኑ የራሱን አስተያየት፤

**(ለ)** በለውጥ የሚሰጡት አክሲዮኖች ወይም ድርሻ መጠን እና አይነት ተመን ለመወሰን ስራ ላይ የዋለው ዘዴ/ቀመር/ ወይም ዘዴዎች ምን እንደሆኑ እና በተያዘው ጉዳይ ትክክለኛ ዘዴ ስለመሆኑ የራሱን አስተያየት እንዲሁም በተመን አሰራሩ ሒደት ያጋጠመ የተለየ የግምት ችግር ካለ ችግሩን መግለጽ፤

**(ሐ)** በውህደቱ ወይም በመከፈሉ ባለመስማማታቸው ከማህበራቱ ለሚወጡ ባለአክሲዮኖች ወይም ሸሪኮች የሚሰጠው ክፍያ ተገቢ ስለመሆኑ፤

**(መ)** የውህደቱ ወይም የመከፈሉ ዕቅድ በጋዜጣ ለሕዝብ ይፋ ከመደረጉ በፊት ከተሳታፊ ማኅበራት ገንዘብ የመጠየቅ መብት ያገኙ ሆኖም የዕዳው መክፈያ ጊዜያቸው ያልደረሰ ገንዘብ ጠያቂዎች መብት ከውህደቱ ወይም ከመከፈሉ በኋላ በቂ ጥበቃ ያለው ስለመሆኑ፤

**(ሠ)** በውህደቱ ወይም በመከፈሉ ተሳታፊ በሆኑት ማኅበራት የፋይናንስ ቁመና ምክንያት በገንዘብ ጠያቂዎች መብት ላይ የተለየ አደጋ የተጋረጠ እንደሆነ ይህንኑ በመግለጽ መደረግ ስላለበት ጥበቃ፡፡

**5)** የንግድ ማኅበራት መዝጋቢው አካል የሚዋሃዱትን ማኅበራት ወይም የሚከፈለውን ማኅበር ዓመታዊ የገንዘብ ዝውውር ወይም የሂሳብ ሚዛናቸውን መነሻ በማድረግ ከተወሰነው መጠን በታች የገንዘብ ዝውውር ወይም የሂሳብ ሚዛን ያላቸው ማኅበራትን ከውህደት ወይም ከመከፈል ኦዲት ግዴታ ነጻ እንዲሆኑ መወሰን ይችላል፡፡

## አንቀጽ 570 ሰነዶችን የማግኘት መብት

**1)** የውህደቱን ወይም የመከፈሉን ውሳኔ የሚያፀድቀው ጉባዔ ከሚደረግበት ቀን አንድ ወር በፊት የውህደት ወይም የመከፈል ዕቅዱ፣ የውህደት ወይም የመከፈል ሪፖርት፣ የገለልተኛ ገምጋሚው ሪፖርት እና ሌሎች ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው መረጃዎች በማኅበሩ ዋና መስሪያ ቤት እና በቅርንጫፎቹ መቀመጥ አለባቸው፡፡

**2)** በውህደቱ ወይም በመከፈሉ ተሳታፊ የሆኑት ማኅበራት አባላት እና የማኅበራቱ ገንዘብ ጠያቂዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (**1**) የተጠቀሱትን ሰነዶች ማየት እና ቅጂ መውሰድ ይችላሉ፡፡

## አንቀጽ 571 የውህደት ወይም መከፈል ውሳኔ

1) ውህደቱ ወይም መከፈሉ የመመስረቻ ጽሑፍን ስለማሻሻል በተደነገገው ስርዓት መሰረት በእያንዳዳቸው በሚዋሃዱት ማኅበራት ወይም በሚከፈለው ማኅበር ጠቅላላ ጉባዔ መወሰን አለበት፡፡

2) ሆኖም የሚዋሃደው ወይም የሚከፈለው የአክሲዮን ማኅበር ከሆነ እና ልዩ መብት ያላቸው ባለአክሲዮኖች በሚኖሩበት ጊዜ የውህደት ወይም የመከፈል ውሳኔው ልዩ መብት ባላቸው ባለአክሲዮኖች ልዩ ጉባዔ ጭምር መጽደቅ አለበት፡፡

## አንቀጽ 572 ዕቅዱን ስለማሳወቅ

1) የመዋሀድ ወይም የመከፈል ዕቅዱ በጠቅላላ ጉባዔ ከፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት ሁለት ወራት ውስጥ በየወሩ አንድ ጊዜ አገር አቀፍ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ለህዝብ መገለፅ አለበት፡፡ እንዲሁም ማስታወቂያው በሚዋሀዱት ወይም በሚከፈለው ማኅበር ዋና መስሪያ ቤት መለጠፍ አለበት፡፡

2) የሚዋሀዱት ወይም የሚከፈለው የአክሲዮን ማኅበር ከሆነ ወይም ባይሆንም ማኅበሩ ወይም ማኅበሮቹ ድረ-ገጽ ካላቸው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ማስታወቂያ በተጨማሪ በማኅበሩ ድረ-ገጽ ላይ መውጣት ይኖርበታል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሰረት ለህዝብ የሚገለፀው ማስታወቂያ የመወሃድ ወይም የመከፈል ዕቅድ፣ የገለልተኛ ባለሞያ ሪፖርት እና የዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም እንደነገሩ ሁኔታ ዋና ስራ አስኪያጅ ያዘጋጀው ሪፖርት የሚገኙበትን ቦታ እና አኳኋን መግለጽ አለበት፡፡ በተጨማሪም ገንዘብ ጠያቂዎች ማቅረብ የሚችሉትን መቃወሚያ የሚያቀርቡበትን የጊዜ ገደብ ማመልከት አለበት፡፡

**<u>አንቀጽ 573 ውህደቱ ወይም መከፈሉ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

የማኅበራት ውህደት ወይም መከፈል የሚፀናው፡-

1) በውህደቱ የተቋቋመው አዲሱ ማኅበር ወይም በመከፈሉ የተቋቋሙት አዲሶቹ ማኅበራት በንግድ መዝገብ ከተመዘገቡበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

2) ውህደቱ ወይም መከፈሉ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተመለከቱት ሁኔታዎች ውጭ የተፈጸመ ከሆነ በነባሩ ማሕበር የመመስረቻ ጽሁፍ ላይ የሚደረገው ለውጥ በንግድ መዝገብ ውስጥ ከገባበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

**<u>አንቀጽ 574 የውህደት እና የመከፈል ውጤት</u>**

1) ውህደት ወይም መከፈል የሚከተሉትን ውጤቶች ያስከትላል፡-

ሀ) የሂሳብ መጣራት ሳያስፈልግ ህልውናውን ያጣው ማኅበር መፍረስን፤

ለ) በውህደቱ ወይም በመከፈሉ ተግባር ምክንያት ህልውናውን ያጣው ማኅበር ሀብትና ዕዳ ወደ ጠቅላዩ ወይም አዲስ ወደ ተመሰረተው ማኅበር መተላለፍን፤

ሐ) በውህደት ወይም በመከፈል ዕቅድ ላይ በተቀመጡ ሁኔታዎች መሰረት ህልውናውን ያጣው ማኅበር ባለአክሲዮኖች ወይም ሽሪኮች በጠቅላዩ ወይም አዲስ በተቋቋመው ማኅበር ውስጥ ምትክ አክሲኖችን የማግኘት እና እንደ አስፈላጊነቱ ተጨማሪ የማካካሻ ክፍያ ማግኘትን፤

መ) የተወሰነ ሃብቱን ከፍሎ አዲስ ማኅበር የመሰረተው ወይም ወደ ሌላ ማኅበር ሃብቱን ያስተላለፈው ማኅበር አባላት እንደ ስምምነታቸው ሁኔታ ሃብቱን በከፈለው፣ አዲስ በተመሠረተው ወይም ሃብቱ በተላለፈለት ማኅበር ውስጥ ድርሻ የማግኘት መብትን፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሐ) እና (መ) ስር የተደነገገው ቢኖርም፤ በሚከፈለው ማኅበር ወይም በሚዋሃዱት ማህበራት አክሲዮኖች ወይም ድርሻ ምትክ በሚከተሉት ሁኔታዎች አይሰጥም፡-

(ሀ) በሚከፈለው ወይም በሚዋሃደው ማኅበር ውስጥ በጠቅላዩ ማህበር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ በሌላ ሰው አመካኝነት ለተያዙ አክሲዮኖች ወይም ድርሻዎች፤ እና

(ለ) የሚከፈለው ወይም የሚዋሃደው ማኅበር በቀጥታ በራሱ ወይም በተዘዋዋሪ በሌላ ሰው አመካኝነት በራሱ ውስጥ ለያዛቸው አክሲዮኖች ወይም ድርሻዎች፡፡

3) ውህደት ወይም መከፈል ከጸናበት ቀን ጀምሮ ውህደቱ ወይም መከፈሉ ፍርስ እንዲሆን መወሰን የሚችለው ፍርድ ቤት ነው፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሰረት ፍርድ ቤት ውህደቱ ወይም መከፈሉ ፍርስ እንዲሆን መወሰን የሚችለው የውህደት ወይም የመከፈል ዕቅዱ በዚህ ህግ በተደነገገው መሰረት ካልተከናወነ ወይም ውህደቱ ወይም መከፈሉ በሚዋሀዱት ወይም በሚከፈለው ማኅበር ባለአክሲዮኖች ጉባዔ ወይም ሸሪኮች ጠቅላላ ስብሰባ ያልጸደቀ ከሆነ ብቻ ነው፡፡

## አንቀጽ 575 በውህደት ወይም በመከፈል ጊዜ የአባላት መብት ጥበቃ

1) ለማኅበሩ አባላት በውህደት ወይም በመከፈል ዕቅድ በተቀመጡት ሁኔታዎች መሠረት ህልውናውን ባጣው ወይም በተከፈለው ማኅበር ውስጥ ከነበራቸው እኩል ወይም ተመጣጣኝ የሆነ ድርሻና መብት በጠቅላዩ ወይም አዲስ በተቋቋመው ማኅበር ውስጥ ይሰጣቸዋል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው መሠረት ለአባላት ህልውናውን ባጣው ወይም በተከፈለው ማኅበር ውስጥ ከነበራቸው ድርሻ ተመጣጣኝ የሆኑ አክሲዮኖች ወይም ድርሻ መስጠት ባልተቻለ ጊዜ፤ ከሰተጧዋቸው አክሲዮኖች ወይም ድርሻዎች ዋጋ አስር በመቶ የማይበልጥ የማስተካከያ ክፍያ በጥሬ ገንዘብ ሊሰጣቸው ይችላል፡፡

3) ህልውናውን ባጣው ወይም በተከፈለው ማኅበር ውስጥ ድምጽ መስጠት የማያስችሉ አክሲዮኖችን ወይም የትርፍ ድርሻ ብቻ የሚያስገኙ አክሲዮኖችን ይዘው ለነበሩ ባለአክሲዮኖች በጠቅላዩ ወይም አዲስ በተመሰረተው ማኅበር ውስጥ ተመሳሳይ ወይም ተመጣጣኝ ጥቅም የሚያስገኙ አክሲዮኖች ሊሰጧቸው ይገባል፡፡

4) በተጠቅላዩ ወይም በተከፈለው ማኅበር ውስጥ ልዩ መብት የሚያስገኙ አክሲዮኖች ይዘው ለነበሩ አባላት ተመጣጣኝ መብት የሚሰጡ አክሲዮኖች ይሰጧቸዋል፡፡

## አንቀጽ 576 የገንዘብ ጠያቂዎች መብት

1) የውህደቱ ወይም የመከፈሉ ዕቅድ በጋዜጣ ለሕዝብ ይፋ ከመደረጉ በፊት ከተሳታፊ ማኅበራት ገንዘብ የመጠየቅ መብት ያገኙ ሆኖም የዕዳው መከፈያ ጊዜ ያልደረሰ ገንዘብ ጠያቂዎች ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ሁኔታ የተሟላ እንደሆነ በቂ ዋስትና እንዲሰጣቸው ለፍ/ቤት ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ፡፡

ሀ) በአንቀጽ 569(4)(መ) መሠረት በገለልተኛ ባለሞያ የተደረገው ግምገማ ከውህደቱ ወይም መከፈሉ በኋላ የገንዘብ ጠያቂዎች መብት በቂ ጥበቃ እንደሌለው ካመለከተ፤ ወይም

ለ) በውህደቱ ወይም በመከፈሉ ተሳታፊ በሆኑት ማኅበራት የፋይናንስ ቁመና ምክንያት በገንዘብ ጠያቂዎች መብት ላይ የተለየ አደጋ የተጋረጠ እንደሆነ ይህን በመግለጽ መደረግ ስላለበት ጥበቃ ገለልተኛ ባለሞያው አስተያየት የሰጠ እንደሆነ፡፡

2) ገንዘብ ጠያቂዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ሀ) እና (ለ) መሰረት በቂ ዋስትና እንዲሰጣቸው ማመልከት የሚችሉት የመወሃድ ወይም የመከፈል ዕቅዱ በዚህ ሕግ አንቀጽ 572 ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለመጀመሪያ ጊዜ በጋዜጣ ለሕዝብ ከተገለጸበተ ቀን አንስቶ በስልሳ ቀናት ውስጥ ብቻ ነው፡፡

3) ፍርድ ቤቱ የሚዋሀደው እያንዳንዱ ማኅበር ወይም የሚከፈለው ማኅበር ያለበትን ዕዳ ለገንዘብ ጠያቂዎች እንዲከፍል ወይም ለዕዳ መከፈያ የሚሆን በቂ ዋስትና እንዲያቀርብ ማዘዝ ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 577 የግዴታ ሰነድ ያዦች መብት</u>**

1) የሚዋሀዱት ማኅበራት ወይም የሚከፈለው ማኅበር የግዴታ ሰነድ ያዦች ጉባኤ ውህደቱን ወይም መከፈሉን ያላፀደቀው እንደሆነ ዕዳ ከፋይ የሆነው ማኅበር የውህደት ወይም የመከፈል ዕቅድ በጋዜጣ ለመጀመሪያ ጊዜ ለህዝብ ይፋ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ባሉት ስልሳ ቀናት ጊዜ ውስጥ ጥያቄ ለሚያቀርቡት የግዴታ ሰነድ ያዦች የሰነዶቹን ዋጋ እና ወለድ በመከፈል ሰነዶቹን መመለስ አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ድንጋጌ ተዋህደው ወይም ተከፍለው አዲስ ማኅበር ለሚመሰርቱ ማኅበራት የግዴታ ሰነድ ያዦች ላይም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

3) ማኅበሩ የግዴታ ሰነዶች ለያዙት አበዳሪዎች የዕዳ ሰነዶቻቸውን ዋጋ እና ወለድ የሚከፍል መሆኑን ያስታወቀ እንደሆነ የዕዳ ሰነድ ያዦች ጉባኤ ማድረግ ሳያስፈልግ የግዴታ ሰነዶቻቸውን ለማህበሩ በመመለስ የሚገባቸውን ክፍያ ማግኘት ለሚፈልጉ ሁሉ ተገቢውን ክፍያ ፈጽሞ ሰነዶቹን ይመልሳል፡፡

4) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ጥያቄ ያላቀረበ የግዴታ ሰነድ ያዥ የጠቅላዩ ወይም የአዲሱ ማህበር ገንዘብ ጠያቂ ይሆናል፡፡

## <u>ርዕስ አስራ አንድ</u>

## <u>በውጭ ሀገር ስለተቋቋመ ወይም በውጭ ሀገር ስለሚሰራ ማኅበር</u>

### <u>ምዕራፍ አንድ</u>

### <u>የውጭ አገር የንግድ ማኅበር ቅርንጫፍ</u>

**<u>አንቀጽ 578 የቅርንጫፍ፣ ትርጓሜ እና አቋም</u>**

1) ቅርንጫፍ ማለት ለአንድ የውጭ አገር የንግድ ማኅበር ወይም የግል ድርጅት ጥቅም በኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ በመሳተፍ ትርፍ ለማግኘት በተደራጀ ሁኔታ የሚሰራ ቋሚ አካል ነው፡፡ ቅርንጫፍ የሚደራጀው ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ሊሆን ይችላል፡፡

2) ቅርንጫፍ ከቅርንጫፉ ባለቤት የንግድ ማኅበር ወይም የግል ድርጅት የተለየ የሕግ ሰውነትም ሆነ ህልውና የለውም፡፡

3) ከቅርንጫፍ እንቅስቃሴ የሚመነጩ ግዴታዎችም ሆነ መብቶች የቅርንጫፉ ባለቤት የሆነው የንግድ ማኅበር ወይም ተመሳሳይ ድርጅት መብት እና ሃላፊነት (ፓትሪሞኒ) አካል ይሆናሉ፡፡

**<u>አንቀጽ 579 የመነገድ መብት</u>**

የውጭ አገር የንግድ ማኅበር ወይም የግል ድርጅት ኢትዮጵያ ውስጥ ቅርንጫፍ ከፍቶ በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ መሳተፍ ይችላል፡፡ ሆኖም መጀመሪያ በንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም በሌላ አግባብ ያለው የባለሥልጣን መስሪያ ቤት በሚያዘው የንግድ መዝገብ ውስጥ መመዝገብ አለበት፡፡

**<u>አንቀጽ 580 ለምዝገባ መቅረብ ያለበት መረጃ</u>**

በሌላ ሕግ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ቅርንጫፍ በንግድ መዝገብ ውስጥ በሚመዘገብበት ጊዜ ከዚህ በታች የተዘረዘረው መረጃ በንግድ መዝገብ ውስጥ መግባት አለበት፡፡

1) ቅርንጫፉ የሚሰማራበት የንግድ/ሥራ/ መስክ፤
2) የቅርንጫፉ ባለቤት የሆነው የንግድ ማኅበር ወይም የግል ድርጅት የሚገዛበት የውጭ አገር ሕግ፤
3) የቅርንጫፉ ባለቤት የሆነው የንግድ ማኅበር ወይም የግል ድርጅት የተመዘገበበት መዝገብ እና የምዝገባ ቁጥር፤
4) የቅርንጫፉ ባለቤት የሆነው የንግድ ማኅበር ወይም የግል ድርጅት ስም እና የማኅበሩን ወይም የድርጅቱን ዓይነት፤
5) ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ ማዋቀር፣ መልሶ ማደራጀት፣ የመክሰር ሥነ ስርዓት ወይም ተመሳሳይ ሂደት የቅርንጫፉ ባለቤት በሆነው የንግድ ማኅበር ወይም የግል ድርጅት ላይ የተጀመረ እንደሆነ ስለጉዳዩ መረጃ፤
6) የቅርንጫፉ ባለቤት የሆነውን የንግድ ማኅበር ወይም የግል ድርጅት የሚገዛው የውጭ አገር ሕግ በሚያዘው መሠረት ተዘጋጅተው እና ኦዲት ተደርገው ለሚመለከተው መሥሪያ ቤት የተላለፉ (ይፋ የተደረጉ) የሒሳብ ሰነዶችን እና
**7)** የንግድ ማኅበሩ ወይም የግል ድርጅቱ የምስረታ የምስክር ወረቀት፣ የመመስረቻ ጽሑፍ እና የተለየ ሰነድ ከሆነ የመተዳደሪያ ደንብ ኮፒዎች እና የነዚህን ሰነዶች የእንግሊዝኛ ወይም የአማርኛ ትርጉም፡፡

**<u>አንቀጽ 581 ስለቅርንጫፍ ሥራ አመራር</u>**

1) አንድ ቅርንጫፍ የራሱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሊኖረው ይገባል፡፡ የቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጅ የሚሆነው የአክሲዮን ማኅበር ዳይሬክተሮች ምልመላን በተመለከተ በዚህ ሕግ አንቀጽ 297 ሥር የተመለከቱትን መመዘኛዎች የሚያሟላ ሰው መሆን አለበት፡፡
2) የቅርንጫፍ ዋና ሥራ አስኪያጅ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የውጭ አገር የንግድ ማኅበርን ወይም የግል ድርጅትን ወክሎ ለመስራት ስልጣን ሊኖረው ይገባል፡፡
3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ሥራ አስኪያጁ ቢያንስ ቢያንስ በክስ ሂደት የውጭ አገር የንግድ ማህበርን ወይም የግል ድርጅትን ለመወከል ስልጣን ይኖረዋል፡፡

**<u>አንቀጽ 582 የቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጅ ግዴታዎች</u>**

በሌላ ሕግ የተጣሉበት ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው፤ የቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጅ የሚከተሉትን የማድረግ ሃላፊነት አለበት፡-

1) የቅርንጫፉ ባለቤት የሆነውን የውጭ አገር የንግድ ማኅበር ወይም የግል ድርጅት የሚገዛው የውጭ አገር ሕግ በሚያዘው መሰረት ተዘጋጅተውና ኦዲት ተደረገው ይፋ የተደረጉትን የሒሳብ ሰነዶች በየዓመቱ የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም አግባብ ያለው ሌላ መስሪያ ቤት በሚይዘው የንግድ መዝገብ ውስጥ የማስገባት፤
2) ገንዘብ ጠያቂዎች የቅርንጫፉ ባለቤት የሆነውን የውጭ አገር የንግድ ማኅበር ወይም የግል ድርጅት የፋይናንስ ቁመና ለመገምገም እንዲችሉ የሚረዳ የሒሳብ ሚዛን ወይም ተመሳሳይ ሰነድ የእንግሊዝኛ ወይም የአማርኛ ትርጉም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ከሚጠየቁት ሰነዶች ጋር በንግድ መዝገብ ውስጥ የማስገባት፤ እና
**3)** የቅርንጫፉ ባለቤት የሆነውን የውጭ አገር የንግድ ማኅበር ወይም የግል ድርጅት በተመለከተ ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር፣ መልሶ ማደራጀት፣ የመክሰር ሥነ ስርዓት ወይም ተመሳሳይ ሂደት የተጀመረ እንደሆነ ጉዳዩን እንዲያውቀ ስለጉዳዩ በንግድ መዝገብ ውስጥ መግለጫ የማስገባት፡፡

## አንቀጽ 583 ከንግድ መዝገብ ስለመሰረዝ

ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የተፈጸመ እንደሆነ ቅርንጫፍ ከንግድ መዝገብ ውስጥ መሰረዝ አለበት፡-

1) የቅርንጫፉ ባለቤት የሆነው የውጭ አገር የንግድ ማኅበር ወይም የግል ድርጅት ከፈረሰ፤
2) ቅርንጫፉ ከተዘጋ፤
3) ቅርንጫፉ ሥራ አስኪያጅ ከሌለው እና ቦታው ክፍት ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ ይህ ሁኔታ በስድስት ወራት ወስጥ ካልተስተካከለ፤
4) ሥራ አስኪያጁ በዚህ ሕግ አንቀጽ 582 መሠረት በንግድ መዝገብ ውስጥ ማስገባት ያለበትን የውጭ አገር የንግድ ማኅበር ወይም የግል ድርጅት የሒሳብ ሰነዶች በምክንያታዊ ፍጥነት በንግድ መዝገብ ውስጥ ካለስገባ፤ እና
5) ከቅርንጫፉ ገንዘብ የመጠየቅ መብት ያለው ሰው የቅርንጫፉ ባለቤት የሆነው የውጭ አገር የንግድ ማኅበር ወይም የግል ድርጅት በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ሀብት ዕዳውን ለመክፈል በቂ ሆኖ እንዳልተገኘ ያረጋገጠ እንደሆነ፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## ስለኢትዮጵያ ሕግ ተፈጻሚነት

## አንቀጽ 584 በውጭ ሀገር ተቋቁሞ ዋና መስሪያ ቤቱ በኢትዮጵያ ስለሚገኝ ማኅበር

አግባብ ያላቸው የዚህ ሕግ እና ሌሎች የኢትዮጵያ ሕጎች ድንጋጌዎች በውጭ ሀገር ተቋቁሞ ዋና መስሪያ ቤቱ ወይም ዋና የንግድ ስራ ቦታው በኢትዮጵያ በሆነ የንግድ ማኅበር ወይም የግል ድርጅት ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

**<u>አንቀጽ 585 በኢትዮጵያ ተቋቁሞ በውጭ አገር ስለሚሰራ ማህበር</u>**

በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት ተቋቁሞ በውጭ አገር በሚሰራ የንግድ ማህበር ወይም ድርጅት ላይ የዚህ ህግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

**<u>አንቀጽ 586 በዚህ ሕግ ከታወቀው የተለየ ቅርጽ ስላለው ማኅበር</u>**

የማኅበሩን ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ በንግድ መዝገብ ስለማስገባት እና ስለዳይሬክተሮች ኃላፊነት የሚመለከቱት የአክሲዮን ማኅበር ድንጋጌዎች በዚህ ሕግ ከታወቀው የተለየ ዓይነት ቅርጽ ባለው የውጭ አገር ማኅበር ላይ እንደአግባብነታቸው ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

**<u>አንቀጽ 587 የውጭ ሀገር ጥቅሞችን በውስጡ ስለያዘ ማኅበር</u>**

የውጭ ሀገር ጥቅሞችን በውስጡ በያዘ ማኅበር ላይ ገደብ የሚጥሉ ወይም ልዩ ሁኔታ የሚያኖሩ ሌሎች የኢትጵያ ሕጎች ተፈጻሚነት የተጠበቀ ይሆናል፡፡

# <u>ሶስተኛ መጽሐፍ</u>

# <u>ለቅድመ ጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር፣ መልሶ የማደራጀት እና የመክሠር ሕግ</u>

## <u>ርዕስ አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

### <u>ምዕራፍ 1</u>

### <u>ዓላማ እና የተፈጻሚነት ወሰን</u>

**<u>አንቀጽ 588</u>** ***<u>የሥነ ሥርዓቶቹ ዓላማ።</u>***

1) ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓት፣ መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት እና የመክሠር ሥነ ሥርዓት ዓላማቸው ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ እና ጊዜውን ጠብቆ በሚከናወን ሥነ ሥርዓት አማካኝነት የኢኮኖሚ መረጋጋትን ማስፋፋት፣ የንብረቱን ዋጋ ከፍ ማድረግ እና የሕግ ተገማችነትንና ግልጽነትን ማረጋገጥ ነው።
2) ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓት ዓላማው የሚመለከታቸው ገንዘብ ጠያቂዎች በሙሉ ድምጽ የሚፈቅዱ ከሆነ የፋይናንስ ችግር ውስጥ ያሉ ተስፋ የሚጣልባቸው ተበዳሪዎች ውልን መሰረት ባደረገ መልኩ በጣም በጊዜ ዕዳቸውን ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ መልሰው እንዲያዋቅሩ እና ሥራቸውን እንዲቀጥሉ ወይም የንግድ ሥራ እንቅስቃሴው በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ የንግድ ሥራ ለመሸጥ እንዲዘጋጁ እንዲችሉ ማድረግ ነው።

3) መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት ዓላማው የሚመለከታቸው ገንዘብ ጠያቂዎች በተወሰነ አብላጫ ድምጽ የሚፈቅዱ ከሆነ መልሶ በማደራጀት ዕቅድ አማካኝነት ገንዘብ ጠያቂዎችን ተጠቃሚ በሚያደርግ መልኩ የባለዕዳውን ዕዳዎች እንዲሁም የሥራ እንቅስቃሴዎች ጊዜውን የጠበቀ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ መልሶ ማደራጀት ወይም የንግድ ሥራ እንቅስቃሴው በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ የንግድ ሥራ መሸጥ ነው።

4) የመክሠር ሥነ ሥርዓት ዓላማው ሀቀኛ ባለዕዳዎች ዕዳቸውን ሙሉ በሙሉ ከከፈሉ በኋላ አዲስ ሕይወት እንዲጀምሩ ለማስቻል ንብረቶቹን አንድ በአንድ በማጣራትም ሆነ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴው በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ የንግድ ሥራ በመሸጥ የባለዕዳውን የንግድ ሥራ የማጣራቱን ሥራ ጊዜውን የጠበቀ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ ማደራጀት እና ዕዳን ለገንዘብ ጠያቂዎች ለመክፈል ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለውን ንብረት ዋጋ ከፍ ማድረግ እንዲሁም ለመክሠሩ ኃላፊ የሆኑ ባለዕዳዎች እና የሥራ አመራሮቻቸው ተገቢውን ኃላፊነት እንዲወስዱ ማድረግ ነው።

## <u>አንቀጽ 589</u> <u>የሥነ ሥርዓቶቹ የተፈጻሚነት ወሰን።</u>

1) በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተመለከቱት ሥነ ሥርዓቶች ሕጋዊ ሰውነት ከሌላቸው የእሽሙር ማኅበሮች ውጭ በነጋዴዎች እና በንግድ ማኅበሮች ላይ እንዲሁም በእጅ ሥራ ጥበበኞች እና ራሳቸውን ችለው የሞያ እንቅስቃሴዎችን በሚያከናውኑ የተፈጥሮ ሰዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ።
2) ባንኮችን እና ሌሎች የገንዘብ ተቋማትን በተመለከተ ለቅድመ ጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓትን፣ መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓትን እና የመክሠር ሥነ ሥርዓትን የሚያስተዳድሩ ልዩ ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተመለከቱት ሥነ ሥርዓቶች በባንኮች እና በሌሎች የገንዘብ ተቋማት ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ።
3) የመንግስት የልማት ድርጅቶችን በተመለከተ ለቅድመ ጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓትን፣ መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓትን እና የመክሠር ሥነ ሥርዓትን የሚያስተዳድሩ ልዩ ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተመለከቱት ሥነ ሥርዓቶች በመንግስት የልማት ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ።
4) ለቅድመ ለጥንቃቄ ሲባል ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓትን፣ መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓትን እና የመክሠር ሥነ ሥርዓትን በተመለከተ ለልዩ የንግድ እንቅስቃሴዎች ልዩ ሕጎች ሊወጡ ይችላሉ።

# <u>ምዕራፍ ሁለት</u>

# <u>ስለክፍያዎች ማቋረጥ እና ስለቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎች</u>

## <u>አንቀጽ 590</u> <u>ክፍያዎችን የማቋረጥ ትርጓሜ።</u>

1) ባለዕዳው የክፍያ ጊዜያቸው የደረሰ እና መክፈል ያለባቸው ዕዳዎችን በተጣራ የገንዘብ ሀብቱ መክፈል ሲያቅተው ክፍያዎች ተቋርጠዋል ይባላል።
2) ለንዑስ አንቀጽ (1) ዓላማ የተጣራ የገንዘብ ሀብት የሚለው መጠባበቂያ ገንዘብ፣ ኦቨርድራፍትን እና ባለዕዳው ማግኘት የሚችላቸው ተመሳሳይ አገልግሎቶችን ይጨምራል።

3) የእፎይታ ጊዜ የተሰጣቸው፣ የታገዱ ወይም ባሉበት እንዲቆዩ ስምምነት የተደረገባቸው ዕዳዎች የክፍያ ጊዜያቸው የደረሰ እና መከፈል ያለባቸው ዕዳዎች ተደርገው አይቆጠሩም።
4) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ዓላማ ዕዳዎች የክፍያ ጊዜያቸው የደረሰ እና መከፈል ያለባቸው ተደርገው የሚቆጠሩት ገንዘብ ጠያቂው ሕጉ የሚጠይቀውን ማሳወቂያ ከሰጠ በኋላ ብቻ ነው።

__አንቀጽ 591__ __ክፍያዎች የተቋረጡበትን ቀን ስለ መወሰን።__

1) ሥነ ሥርዓቶቹን ለመክፈት ፍርድ ቤት ነገሩን በሚሰማበት ወቅት ፍርድ ቤቱ ባለዕዳው ክፍያዎችን እንዳቋረጠ እና ክፍያዎች የተቋረጡበትን ቀን ያረጋግጣል።
2) ፍርድ ቤቱ በራሱ ውሳኔ የባለዕዳውን ጉዳዮች እና እንቅስቃሴዎች የሚመረምር መርማሪ ሊሾም ይችላል። በዚህ መልኩ የሚሾመው መርማሪ መልሶ የማደራጀት ኃላፊው ወይም ለከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ የተሾመ ከሆነ እንዲያግዙት ሊጠይቅ ይችላል።
3) በፍርድ ቤቱ የጊዜ ማራዘሚያ ካልተሰጠ በስተቀር በመርማሪው የተሰበሰቡ መረጃዎች በሙሉ በሠላሳ ቀናት ውስጥ ለፍርድ ቤቱ ይቀርባሉ።
4) ሥነ ሥርዓቱ በተጀመረ በአንድ ዓመት ውስጥ መልሶ የማደራጀት ኃላፊው፣ የከሰረ ሰው ንብረት ጠባቂው፣ ማንኛውም ተቆጣጣሪ፣ ዐቃቤ ሕግ ወይም ማንኛውም ገንዘብ ጠያቂ ክፍያዎች የተቋረጡበትን ቀን መልሶ እንዲመረምር እና እንደገና እንዲወስን ለፍርድ ቤቱ አቤቱታ ሊያቀርቡ ይችላሉ። ፍርድ ቤቱ ለዚህ ዓላማ ሲባል የባለዕዳውን ጉዳዮች እና እንቅስቃሴዎች የሚመረምር ባለሞያ ሊሾም ይችላል።
5) በንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት በፍርድ ቤቱ ከተወሰነው ክፍያዎች ከተቋረጡበት ቀን አንስቶ ሂደቱ እስከተጀመረበት ቀን ድረስ ያለው ጊዜ እንደ አጠራጣሪ ጊዜ ተደርጎ ይቆጠራል። አጠራጣሪ ጊዜው ቢበዛ ከ18 ወራት መብለጥ የለበትም።

__አንቀጽ 592__ __የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎች።__

1) ለዚህ መጽሐፍ ዓላማ የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎች ማለት የመክፈያ ጊዜያቸው የደረሰ እና ተከፋይ ሆኑም አልሆኑም እንደ ሁኔታው መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት ወይም የመክሠር ሥነ ሥርዓት ከመከፈቱ አስቀድሞ የሚቀርቡ ማናቸውም የክፍያ ጥያቄዎች እንዲሁም ወለዳቸውን ጨምሮ ነው።
2) በሂደት ላይ ያሉ ውሎችን በተመለከተ እንደ ሁኔታው መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት ወይም የመክሠር ሥነ ሥርዓት ከተከፈተ በኋላ ውሉ መፈጸም ከመቀጠሉ የሚመነጩ የክፍያ ጥያቄዎች የድህረ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎች ናቸው።
3) በሂደት ላይ ያሉ ውሎች በመልሶ ማደራጀት ኃላፊው ወይም በከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂው፣ በሚቋረጡበት ጊዜ ውሉ ከመቋረጡ የሚመነጩ ቅጣቶች እና ሌላ ዓይነት ካሳዎች የሚቆጠሩት እንደ ቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎች ነው።

<u>**ምዕራፍ ሦስት**</u>

<u>**በሂደት ላይ ያሉ ውሎች አያያዝ**</u>

__አንቀጽ 593__ __በሂደት ላይ ያሉ ውሎች መቀጠል ወይም መቋረጥ__

1) ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር፣ መልሶ የማደራጀት ወይም የመክሠር ሥነ ሥርዓት መከፈቱ በሂደት ላይ ያሉ ውሎች በመቀጠላቸው ላይ ተጽዕኖ አያደርግም።

2) በሂደት ላይ ያሉ ውሎች ማለት የመሠረታዊ አገልግሎቶች ውሎችና ባለዕዳው የንግድ ሥራውን የሚያከናውንባቸው የማይንቀሳቀሱ የንግድ ቦታዎች፣ በባለዕዳውና በቤተሰቡ ይዞታ ስር የሚገኙ የማይንቀሳቀሱ ቦታዎችን የሚጨምር ሆኖ በነዚህ ሳይወሰን ማናቸውም በአንድና ከዚያ በላይ ገንዘብ ጠያቂዎችና በባለዕዳው መካከል የተደረጉ በሂደት ላይ ያሉ ውሎች ሲሆኑ ይኸውም ሥነ-ሥርዓቶቹ በሚከፈቱበት ጊዜ ከተዋዋይ ወገኖች ቢያንስ አንዱ ወገን የውል ግዴታውን ያልተወጣ እንደሆነ ነው።

3) ማንኛውም ተቃራኒ የውል ድንጋጌ ቢኖርም ገንዘብ ጠያቂዎች በሚከተሉት ምክንያቶች ብቻ የተነሳ በሂደት ላይ ያሉ ውሎችን አልፈጽምም ማለት ወይም ማቋረጥ፣ ማፋጠን ወይም ባለዕዳውን በሚጎዳ በማንኛውም መልኩ በውሉ ላይ ለውጥ ማድረግ አይፈቀድላቸውም፡-

   ሀ) ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር፣ መልሶ የማደራጀት ወይም የመክሠር ሥነ ሥርዓት ለመከፈት ጥያቄ በመቅረቡ ወይም በመከፈቱ፤ ወይም

   ለ) ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ በማዋቀር ማዕቀፍ ውስጥ ክፍያ ለማስፈጸም በተናጠል የሚደረጉ ክርክሮች እንዲቋረጡ ጥያቄ በመቅረቡ ወይም በመቋረጣቸው።

4) በሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ መልሶ የማደራጀት ኃላፊው ወይም የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ በሂደት ላይ ያለውን ውል ሊያቋርጡት ይችላሉ፡-

   ሀ) መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት ከሆነ ባለዕዳው ወይም የመክሠር ሥነ ሥርዓት ከሆነ ንብረቱ በሂደት ላይ ያለውን ውል መፈጸሙን ለመቀጠል የሚያስችል ገንዘብ የሌላቸው ከሆነ፤

   ለ) በሂደት ላይ ያለው ውል መቀጠሉ መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት ከሆነ ለባለዕዳው ወይም የመክሠር ሥነ ሥርዓት ከሆነ ለንብረቱ የማይጠቅም ከሆነ፤ ወይም

ሐ) በቶሎ መቋረጡ የገንዘብ ጠያቂዎችን ጥቅም አግባብ ባልሆነ መልኩ የማይጎዳ
ከሆነ።

5) በሂደት ላይ ያለው ውል ስለ መቀጠሉ እንዲወስን ገንዘብ ጠያቂዎች መልሶ ለማደራጀት ኃላፊው ወይም ለከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ጥያቄ ሊያቀርቡ ይችላሉ። መልሶ የማደራጀት ኃላፊው ወይም የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ጥያቄው በደረሳቸው በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ በሂደት ላይ ያለው ውል መቀጠል ወይም መቋረጥ እንዳለበት ወስነው ለገንዘብ ጠያቂዎቹ ውሳኔያቸውን ያሳውቃሉ። በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ውሳኔውን ገንዘብ ጠያቂዎች እንዲያውቁት ካልተደረገ በሂደት ላይ ያለው ውል እንደተቋረጠ ተደርጎ ይቆጠራል።

6) በሂደት ላይ ያሉ ውሎች የቀጠሉ እንደሆነ መልሶ የማደራጀት ኃላፊው ወይም የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ባለዕዳው በውሎቹ መሰረት ያሉበትን ግዴታዎች መወጣቱን ያረጋግጣሉ።

7) ገንዘብ ጠያቂዎቹ ከውሉ የሚመነጭ ማንኛውም የቅድመ-መክሰር የክፍያ ጥያቄ መከፈሉን ውሉ እንዲቀጥል እንደ ቅድመ ሁኔታ አድርገው መጠየቅ አይችሉም።

**አንቀጽ 594 ተቃውሞ**

1) ገንዘብ ጠያቂዎች በሂደት ላይ ያሉ ውሎች እንዲቀጥሉ ወይም እንዲቋረጡ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ተቃውሞ ማቅረብ ይችላሉ። እንዲህ ያለው ተቃውሞ መልሶ የማደራጀት ኃላፊው ወይም የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ውሳኔውን በሰጡ በሰባት ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት።
2) ማንኛውም መቃወሚያ በቀረበ በሰባት ቀናት ውስጥ በተቆጣጣሪ ዳኛው ውሳኔ ይሰጥበታል።
3) ተቆጣጣሪ ዳኛው በሰጠው ውሳኔ ላይ ውሳኔው በተሰጠ በአሥር ቀናት ውስጥ ለፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይቻላል።

**አንቀጽ 595 የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን የንግድ ኪራይ የሚመለከቱ ልዩ ድንጋጌዎች።**

1) በአንቀጽ 593 ውስጥ የተመለከተው ቢኖርም የማይንቀሳቀስ ንብረት የንግድ ኪራይ ውሎች የቀጠሉ እንደሆነ ጊዜው ከማለቁ በፊት ወዲያውኑ ኪራይ እንዲከፈል የሚደነግጉ ማናቸውም የውል ድንጋጌዎች መልሶ በማደራጀት ሥነ ሥርዓት ወቅት ለመጠባበቂያ ጊዜው የመጀመሪያ አራት ወራት ወይም በመክሠር ሥነ ሥርዓት ወቅት በአንቀጽ 744 ውስጥ በተደነገገው መሰረት የንግድ ሥራው ለሚቀጥልበት ጊዜ ያህል ተፈጻሚ አይሆኑም።

2) የማይንቀሳቀስ ንብረት የንግድ ኪራይ ውሎች የቀጠሉ እንደሆነ እና አከራዩ የኪራይ ውሉ በተፈረመበት ወቅት አጠቃላይ የኪራይ ክፍያዎችን የተቀበለ እንደሆነ ወይም እንዲህ ላለው ክፍያ በቂ ዋስትናዎችን ያገኘ ከሆነ አከራዩ ሥነ ሥርዓቱ ከተከፈተ በኋላ የሚፈጠሩ ማናቸውንም ወቅታዊ እና የወደፊት የኪራይ ክፍያዎች መጠየቅ አይችልም።

3) ማናቸውም የውል ድንጋጌዎች ቢኖሩም የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ የኪራይ ስምምነቶችን ለተቀረው ጊዜ ያህል ሊያስተላልፍ ይችላል፤ ሆኖም የንግድ ቦታው የሚሠጠው አገልግሎት ሊቀየር አይችልም። አግባብ በሚሆንበት ጊዜ ተቆጣጣሪ ዳኛው አገልግሎቱ እንዲቀየር ሊፈቅድ ይችላል።

**አንቀጽ 596 ልዩ ሁኔታዎች**

በዚህ ሕግ አንቀጽ 593 ውስጥ የተደነገገው ቢኖርም የሚከተሉት ውሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች ይተዳደራሉ፡-

ሀ) የሥራ ውሎች፤

ለ) የባንክ እና የመድን ውሎች፤

ሐ) የአስተዳደር ውሎች፤

መ) የአክሲዮን ገበያን ጨምሮ በፋይናንስ ገበያዎች ማዕቀፍ ውስጥ የተፈረሙ ውሎች።

## ምዕራፍ አራት

## ስለገንዘብ ጠያቂዎች ጥቅሞችና መብቶች

**አንቀጽ 597 የገንዘብ ጠያቂዎች ጥቅሞች ጥበቃ**

1) በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተቀመጡት ሥነ ሥርዓቶች አጠቃላይ መርህ የገንዘብ ጠያቂዎችን ትክክለኛ ጥቅም ማስጠበቅ ነው።
2) ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ በማዋቀር ሥነ ሥርዓት ውስጥ መልሶ የማዋቀር ዕቅዱ በሁሉም በሚመለከታቸው ገንዘብ ጠያቂዎች ሙሉ ድምጽ መጽደቅ አለበት።
3) መልሶ በማደራጀት ሥነ ሥርዓት ውስጥ መልሶ የማደራጀት ዕቅዱ በሚመለከታቸው ገንዘብ ጠያቂዎች አስቀድሞ በተወሰነ አብላጫ ድምጽ መጽደቅ አለበት እንዲሁም የንግድ ሥራ እንቅስቃሴው በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ የንግድ ሥራ እንዲሸጥ በገንዘብ ጠያቂዎች በአብላጫ ድምጽ መጽደቅ አለበት።
4) በመክሠር ሥነ ሥርዓት ውስጥ በንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያለን ድርጅት በእንቅስቃሴ ላይ እንዳለ በአጠቃላይ ወይም የድርጅቱን ትልቅ ክፍል የመሸጥ ውሳኔ በገንዘብ ጠያቂዎች በአብላጫ ድምጽ መጽደቅ አለበት።

**አንቀጽ 598 የገንዘብ ጠያቂዎች ተሳትፎ**

ገንዘብ ጠያቂዎች በሥነ ሥርዓቶች ወቅት በአጠቃላይ አስተያየታቸውን የማቅረብ እና ፍርድ ቤት ጉዳዮችን በሚሰማበት ጊዜ የመሰማት መብት አላቸው።

**አንቀጽ 599 የመረጃ መብቶች**

1) ማንኛውም ገንዘብ ጠያቂ፣ የገንዘብ ጠያቂዎች ስብስብ፣ የገንዘብ ጠያቂዎች መደብ ወይም ጠቅላላ የገንዘብ ጠያቂዎች ጉባዔው አግባብ የሆኑ ማናቸውንም መረጃዎች ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ ከማዋቀር ዘርፍ ባለሞያው፣ መልሶ ከማደራጀት ኃላፊው እና ከከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ የመጠየቅ መብት አላቸው።
2) እንዲህ ያለው ጥያቄ በጽሁፍ የሚቀርብ ሲሆን ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዘርፍ ባለሞያው፣ መልሶ የማደራጀት ኃላፊው እና የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ጥያቄው በቀረበ በአሥር ቀናት ውስጥ መልስ ይሰጣሉ እንዲሁም በተቻለ መጠን በፍጥነት ለጥያቄው አጥጋቢ ምላሽ ይሰጣሉ።
3) ማንኛውም ጥያቄ ምክንያታዊ ካልሆነ ወይም ከመጠን በላይ ጫና የሚያሳድር ከሆነ ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዘርፍ ባለሞያው፣ መልሶ የማደራጀት ኃላፊው እና ከከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ጥያቄውን ያለመቀበል ይችላሉ።

## ምዕራፍ አምስት

## ሥልጣን

**አንቀጽ 600 የግዛት ሥልጣን።**

1) ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓት፣ መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት እና የመክሠር ሥነ ሥርዓት ላይ በኢትዮጵያ ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት የግለሰቡ መደበኛ ቦታ ወይም የማኅበሩ ወይም በሕግ የሰውነት መብት ያለው ሰው የተመዘገበ ጽ/ቤት በሚገኝበት ቦታ ያለው ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው።
2) ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓትን፣ መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓትን እና የመክሠር ሥነ ሥርዓትን የከፈተው ፍርድ ቤት ከእነዚህ ሥነ ሥርዓቶች በቀጥታ በሚመነጩ እና ከእነሱ ጋር በቅርበት በሚገናኙ የሚከተሉትን ጉዳዮች እንደሚመለከቱት ባሉ ክሶች ላይ ሥልጣን አለው፡-

ሀ) መልሶ የማዋቀር እና መልሶ የማደራጀት ዕቅድ፤

ለ) በንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያለን ድርጅት በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ እንዲሸጥ ማጽደቅ፤

ሐ) በሂደት ላይ ያሉ ውሎች፤

መ) የተቆጣጣሪ ዳኛዎች፣ የባለዕዳው ንብረት ጠባቂዎች፣ ተቆጣጣሪዎች እና ዳይሬክተሮች ኃላፊነት፤

ሠ) የክፍያ ጥያቄዎች አቀራረብ፣ ማረጋገጥ እና አቀባበል፤

ረ) ከንብረት የሚመነጩ መብቶች፤

ሰ) ማቻቻል፤

ሸ) የንብረቶች መሸጥ ወይም መተላለፍ፤

ቀ) የክፍያ ጥያቄዎች ቅደም ተከተል፤

በ) ከሽያጭ የተገኘ ገንዘብ ክፍፍል፤

ተ) የድርጊቶች ፈራሽ መደረግ፤

ቸ) ውሎችን ማጽናት እና ተፈጻሚነት፤

ኀ) የባለዕዳው ነጻ መውጣት፤

ነ) የሥነ ሥርዓቱ መዘጋት።

**<u>አንቀጽ 601</u>** **<u>ስለ ኩባንያዎች ቡድን እና ሥነ ሥርዓትን ስለማቀናጀት</u>**

1) በኩባንያዎች ቡድን ውስጥ የሚገኝ እያንዳንዱ የሕግ ሰውነት ያለው አካል እና ሀብቱ ራሱን የቻለ ነው። ፍርድ ቤቱ በኩባንያዎች ቡድን ውስጥ የሚገኝን አንድ የሕግ ሰውነት ያለው አካል በተመለከተ የተከፈተን ሥነ ሥርዓት በሌላ የሕግ ሰውነት ያለው አካል ወይም የተፈጥሮ ሰው ላይ ተፈጻሚ ሊያደርግ አይችልም።
2) በኩባንያዎች ቡድን ውስጥ የሚገኝን አንድ የሕግ ሰውነት ያለው አካል የተመለከተ ሥነ ሥርዓት በመጀመሪያ የከፈተው ፍርድ ቤት በቡድኑ ውስጥ የሚገኙትን ሌሎች አካላት በተመለከተ ሥነ ሥርዓት ለመክፈት የግዛት ሥልጣን አለው። ፍርድ ቤቱ ቡድኑን ለሚመለከቱ ሥነ ሥርዓቶች በሙሉ አንድ መልሶ የማደራጀት ኃላፊ ወይም የከሰረውን ሰው ንብረት ጠባቂ ሊሾም ይችላል።
3) በኩባንያዎች ቡድን ውስጥ የሚገኙ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሕግ ሰውነት ያላቸው አካላትን የሚመለከቱ ሥነ ሥርዓቶች ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ በአንድ ወይም ከዚያ በላይ ፍርድ ቤቶች የተከፈቱ ከሆነ የቡድኑን

የተለያዩ አባላት በተመለከተ መልሶ የማደራጀት ዕቅድ ለማዘጋጀት ወይም በንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያለን ድርጅት በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ እንዲሸጥ ለማመቻቸት ፍርድ ቤቱ፣ ተቆጣጣሪዎቹ እና ጠባቂዎቹ በተቻለ መጠን ተባብረው እና ተቀናጅተው ይሰራሉ።

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ውስጥ የተመለከተው ትብብር እና ቅንጅት ፍርድ ቤቱ፣ መልሶ የማደራጀት ኃላፊው እና የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ አግባብ ነው ብለው በሚያስቡት ማንኛውም መንገድ ተግባራዊ ሊደረግ የሚችል ሲሆን በተለይም ደግሞ በሚከተሉት መንገዶች ሊከናወን ይችላል፡-

ሀ) መልሶ የማደራጀት ኃላፊዎችን እና የከሰረውን ሰው ንብረት ጠባቂዎችን አቀናጅቶ በመሾም፤

ለ) ማናቸውንም አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች በመለዋወጥ፤

ሐ) የቡድኑ አባላትን ንብረቶች እና ጉዳዮች አስተዳደር እና ቁጥጥር በማቀናጀት፤

መ) ጉዳዮች የሚሰሙበትን ሥርዓት በማቀናጀት፤

ሠ) መልሶ የማደራጀት ዓለም አቀፍ ዕቅዱን የማጽደቅ ወይም በቡድኑ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ወይም የሁሉንም አካላት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ የንግድ ሥራ የመሸጥ ሥራዎችን በማቀናጀት።

__አንቀጽ 602 ሥነ ሥርዓቶችን የመክፈት እና ተያያዥ ፍርዶችን የመስጠት ዓለም አቀፋዊ ሥልጣን__

1) የባለዕዳው ዋና የጥቅም ማዕከል የሚገኘው ኢትዮጵያ ውስጥ ከሆነ ዋናውን ሥነ ሥርዓት ለመክፈት ሥልጣን ያላቸው የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ናቸው። ዋና የጥቅም ማዕከል ማለት መደበኛ በሆነ መልኩ ባለዕዳው ጥቅሙን የሚያስተዳድርበት ስፍራ ሲሆን ይኸውም በሦስተኛ ወገኖች መረጋገጥ መቻል አለበት። ኩባንያን ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ሰውን በተመለከተ ተቃራኒ ማስረጃ እስከሌለ ድረስ የተመዘገበ ቢሮው የሚገኝበት ቦታ ዋና የጥቅም ማዕከል ተደርጎ ይቆጠራል። የተፈጥሮ ሰውን በተመለከተ ተቃራኒ ማስረጃ እስከሌለ ድረስ ዋና የሥራ ቦታው ዋና የጥቅም ማዕከል ተደርጎ ይቆጠራል።
2) ዋና የጥቅም ማዕከሉ ኢትዮጵያ የሆነ ባለዕዳን በተመለከተ ለቅድመ ጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓት፣ መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት እና የመክሠር ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት የሚሰጥ ፍርድ ዓለም አቀፋዊ ተፈጻሚነት አለው።
3) የባለዕዳው ማንኛውም የሥራ ቦታ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ከሆነ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች በሀገር ውስጥ ያሉ ንብረቶችን የሚመለከት ሥነ ሥርዓት ለመክፈት ሥልጣን አላቸው። የሥራ ቦታው ባለዕዳው ሰውን እና ንብረቶችን ተጠቅሞ ጊዜያዊ ያልሆነ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የሚያደርግበት የሥራ ቦታ ነው።
4) ኢትዮጵያ ውስጥ የሥራ ቦታ ያለውን ባለዕዳ የሚመለከት በሀገር ውስጥ ያሉ ንብረቶችን የሚመለከት ሥነ ሥርዓት ተፈጻሚነቱ በኢትዮጵያ ድንበር ውስጥ በሚገኙ የባለዕዳው ንብረቶች የተወሰነ ነው።
5) የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች በዚህ ሕግ አንቀጽ 600 ንዑስ አንቀጽ (2) ውስጥ በተመለከተው መሰረት እንዲህ ካለው ሥነ ሥርዓት በቀጥታ የሚመነጩ እና ከእርሱ ጋር የቅርብ ትስስር ያላቸውን ክሶች የማየት ሥልጣን አላቸው።

**<u>አንቀጽ 603 ዕዳን መክፈል ካለመቻል ጋር ግንኙነት ያላቸውን ፍርዶች ጨምሮ፣ ለውጭ ሀገር ፍርዶች ዕውቅና ስለ መስጠት</u>**

1) ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓትን፣ መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓትን እና የመክሠር ሥነ ሥርዓትን ለመክፈት በሌላ ሀገር ውስጥ ሥልጣን ባለው አካል የተሰጠ ማንኛውም ፍርድ እንዲሁም ዕዳን መክፈል ካለመቻል ጋር ግንኙነት ያላቸው ፍርዶች በኢትዮጵያ የሥልጣን ወሰን ውስጥ ዕውቅና የሚሰጣቸው የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ ነው:-

ሀ) የውጭ ሀገር ፍርዱ መሰረታዊ የሥነ ሥርዓት ፍትህ መርሆዎቿን ጨምሮ የኢትዮጵያን መንግስታዊ ሥርዓት የማይጻረር ከሆነ፤

ለ) የውጭ ሀገር ፍርዱ በማጭበርበር የተገኘ ካልሆነ፤

ሐ) የውጭ ሀገር ፍርዱ የተሰጠው በኢትዮጵያ የሥልጣን ግጭት ሕግጋት መሰረት ሕጋዊ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ከሆነ፤

መ) የውጭ ሀገር ፍርዱ ኢትዮጵያ ከፈረመቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ጋር የሚጣጣም ከሆነ፤

ሠ) ያንኑ ባለዕዳ በተመለከተ በኢትዮጵያ ውስጥ ማንኛውም ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓት፣ መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት ወይም የመክሠር ሥነ ሥርዓት ካልተከፈተ፤

ረ) የውጭ ሀገር ፍርዱ በእነዚሁ ወገኖች መካከል የተፈጠረ ክርክርን በተመለከተ ኢትዮጵያ ውስጥ ከተሰጠ ፍርድ ጋር የማይጋጭ ከሆነ፤

ሰ) የመክሠር ሥነ ሥርዓት ለመክፈት በውጭ ሀገር የተሰጠው ፍርድ ዕውቅና ከተሰጠው በኋላ የሚኖረው ተፈጻሚነት በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙት የባለዕዳው ንብረቶች የተወሰነ ከሆነ፤

ሸ) የውጭ ሀገር ፍርዱ በተሰጠበት ሀገር ውስጥ ተፈጻሚነት ያለው እና ማስፈጸም የሚቻል ከሆነ፤ እና

ቀ) የውጭ ሀገር ፍርዱ በተሰጠበት ሀገር ውስጥ ተፈጻሚነት ካለው እና ማስፈጸም የሚቻል ከሆነ፤ እንዲሁም ዕውቅና ማግኘቱ እና መፈጸሙ የባለዕዳውን የመክሠር ሥነ ሥርዓት በማስተዳደር ሂደት ውስጥ ጣልቃ የማይገባ ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ ከዚያው ባለዕዳ ጋር በተያያዘ የኪሳራ ሥነ ሥርዓት ውስጥ ከተላለፈ የማቋረጥ ወይም ሌላ ትዕዛዝ ጋር የማይጋጭ ከሆነ።

2) ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር፣ መልሶ የማደራጀት፣ የመክሠር እና ዕዳን መክፈል ያለመቻል ሥነ ሥርዓት ለመክፈት በውጭ ሀገር የተሰጠ ፍርድ ወይም ከኪሳራ ጋር ግንኙነት ያለው የውጭ ሀገር ፍርድ ዕውቅና እንዲሰጠው ወይም እንዲፈጸም አቤቱታ በሚቀርብበት ጊዜ የሚከተሉት ማስረጃዎች ለፍርድ ቤቱ መቅረብ አለባቸው:-

ሀ) ከኪሳራ ጋር ግንኙነት ያለው የውጭ ሀገር ፍርድ የተረጋገጠ ቅጂ፤ እና

ለ) የውጭ ሀገር ፍርዱ በተሰጠበት ሀገር ውስጥ ተፈጻሚነት ያለው እና ማስፈጸም የሚቻል መሆኑን ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑ ማናቸውም ሰነዶች፤ ወይም

ሐ) በንዑስ አንቀጽ (ሀ) እና (ለ) ውስጥ የተመለከቱት ማስረጃዎች ያልተገኙ ከሆነ ጉዳዮቹን በተመለከተ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ሌሎች ማናቸውም ማስረጃዎች።

3) ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ወይም ኮንቬንሽኖች እንደተጠበቁ ሆነው መልሶ በማደራጀት ሥነ ሥርዓት ወቅት የንብረት ኃላፊው እና የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ የውጭ ሀገር መንግስታትን ውሳኔ መሰረት ያደረጉ የታክስ ወይም የጉምሩክ ቀረጥ እና ቅጣት ክፍያ ጥያቄዎችን አይቀበሉም።

## ምዕራፍ ስድስት

## ሥነ ሥርዓቶችን የማከናወን ኃላፊነት ያለባቸው ሰዎች እና አካላት

### አንቀጽ 604 የመክሠር ሥነ ሥርዓት ፍርድ ቤት ሥልጣን

1) መልሶ የማደራጀት ወይም የመክሰር ሥነ ሥርዓት የከፈተው ፍርድ ቤት ሁሉንም ሥነ ሥርዓቶች ይቆጣጠራል እንዲሁም ከተቆጣጣሪ ዳኛው ሥልጣን ውጭ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ትዕዛዞችን ይሰጣል። ተቆጣጣሪ ዳኛው በሰጣቸው ትዕዛዞች ላይ የሚቀርቡ ይግባኞችን ይሰማል።
2) ፍርድ ቤቱ በዚህ ሕግ አንቀጽ 600 ንዑስ አንቀጽ (2) ውስጥ የተመለከቱትን ጉዳዮች ጨምሮ መልሶ ከማደራጀት እና ከመክሠር ሥነ ሥርዓት ጋር ግንኙነት ያላቸው ጉዳዮችን በሙሉ የመስማት እና ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን አለው።

### አንቀጽ 605 ተቆጣጣሪ ዳኛ ስለ መሾም

ፍርድ ቤቱ መልሶ የማደራጀት እና የመክሠር ሥነ ሥርዓት ለመክፈት በሚሰጠው ፍርድ ተቆጣጣሪ ዳኛ ይሾማል። ተቆጣጣሪ ዳኛው ከፍርድ ቤቱ አባላት መካከል ይመረጣል፤ ሆኖም ሥነ ሥርዓቱን የሚከፍተው ፍርድ ቤት አባል ሊሆን አይችልም።

### አንቀጽ 606 የተቆጣጣሪ ዳኛው ሥልጣን

ተቆጣጣሪ ዳኛው የሚከተሉት ሥልጣን ይኖሩታል:-

1) ንብረቱን በተመለከተ የሚቀርቡ የቅድመ ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎችን መቀበል፤
2) ንብረቶቹን ጠብቆ ለማቆየት አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን በሙሉ መውሰድ ወይም አግባብ ባላቸው ባለሥልጣን አካላት እንዲወሰዱ ማድረግ፤
3) ከመደበኛ የሥራ ሂደት ውጭ የሆኑ ግብይቶችን ወይም ስምምነቶችን መፍቀድ፤
4) በሂደት ላይ ያሉ ውሎች መቀጠላቸውን ወይም መቋረጣቸውን በተመለከተ ውሳኔ መስጠት፤
5) የቅድመ ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎች እንዲከፈሉ መፍቀድ፤

6) የገንዘብ ጠያቂዎች መደቦች ከሚዋቀሩበት መንገድ ጋር በተያያዘ የሚፈጠሩ ግጭቶች ላይ ውሳኔ መስጠት።

**አንቀጽ 607 ተቆጣጣሪ ዳኛው የሚሰጣቸው ትዕዛዞች**

ተቆጣጣሪ ዳኛው የሚሰጣቸው ትዕዛዞች ለፍርድ ቤቱ መዝገብ ቤት ሹም ሳይዘገይ ገቢ ይደረጋሉ እንዲሁም በአደራ ደብዳቤ ወይም ተቀባዩ ለመቀበሉ ማረጋገጫ ሊሰጥበት በሚችል ሌላ ማንኛውም ኤሌክትሮኒክ መንገድ የሚመለከታቸው ወገኖች በሙሉ እንዲያውቋቸው ይደረጋል።

**አንቀጽ 608 ተቆጣጣሪ ዳኛውን ስለ መተካት**

ፍርድ ቤቱ በማንኛውም ጊዜ በራሱ ተነሳሽነት አሳማኝ ምክንያት ካለ ተቆጣጣሪ ዳኛውን በሌላ ሰው ሊተካ ይችላል።

**አንቀጽ 609 የፍርዶች ተፈጻሚነት**

መክሠርን በሚመለከተው ፍርድ ቤት ወይም በተቆጣጣሪ ዳኛው የተሰጡ ውሳኔዎች፣ ፍርዶች እና ትዕዛዞች በሙሉ ወዲያውኑ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

**አንቀጽ 610 መልሶ የማደራጀት እና የመክሰር ባለሞያዎች**

መልሶ የማደራጀት ኃላፊው እና የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ከእነዚሁ ሞያዎች አባላት መካከል ይመረጣሉ።

**አንቀጽ 611 በሥነ ሥርዓቶች ውስጥ ስለሚሾሙ ሰዎች እና አካላት ቁጥጥር**

1) ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዘርፍ ባለሞያዎች፣ መልሶ የማደራጀት ኃላፊዎች እና የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂዎች ለየሞያቸው አግባብነት ያላቸው የሙያ የሥነ ምግባር ደንቦችን እና የስነ ምግባር ደረጃዎችን የማክበር ግዴታ አለባቸው።
2) በሥነ ሥርዓቶች ውስጥ የሚሾሙ ሰዎችን እና አካላትን ይበልጥ ለመቆጣጠር ልዩ ደንቦች ይወጣሉ።

**አንቀጽ 612 መልሶ የማደራጀት ኃላፊዎች እና የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂዎች ብቃት**

1) ፍርድ ቤቱ መልሶ የማደራጀት ኃላፊዎችን እና የከሰረውን ሰው ንብረት ጠባቂዎች ብቃት እና ተገቢው የሥራ ልምድ ካላቸው የሕግ፣ የሂሳብ ሥራ፣ የኦዲት ሥራ፣ የፋይናንስ፣ የሥራ አመራር እና ተመሳሳይ ባለሞያዎች ውስጥ መርጦ ይሾማል። አግባብ በሚሆንበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ አንድ ሰው ግዴታውን በብቃት ለመወጣት አስፈላጊው ችሎታ አለው ብሎ ሲያምን መልሶ የማደራጀት ኃላፊዎችን እና የከሰረውን ሰው ንብረት ጠባቂዎች ከሌሎች ሞያዎች አባላት ውስጥ መርጦ ሊሾም ይችላል።
2) መልሶ ከማደራጀት ኃላፊዎች እና ከከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂዎች ብቃት፣ አቅም፣ ፈቃድ አሰጣጥ፣ ቁጥጥር፣ ኃላፊነት፣ ከኃለፊነት መነሳት እና የሙያ ስነ-ምግባር ደንቦች ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን የሚያስተዳድሩ ልዩ ደንቦች ይወጣሉ።

**አንቀጽ 613 መልሶ የማደራጀት ኃላፊዎች እና የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂዎች ብቃት እና ታማኝነት**

መልሶ የማደራጀት ኃላፊዎች እና የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂዎች፡-

1) የተሾሙበትን ሥራ ለመሥራት እና የተሰጣቸውን ሥልጣን ተግባራዊ ለማድረግ ብቃት ሊኖራቸው ይገባል፤
2) በታማኝነት፣ ያለወገንተኝነት እና በገለልተኝነት ኃላፊነታቸውን መወጣት አለባቸው፤
3) የብቃት ማነስ፣ ቸልተኝነት፣ ማጭበርበር ወይም ሌላ ጥፋት ከተገኘባቸው በፍርድ ቤቱ ከሃላፊነታቸው ሊነሱ ይችላሉ።

__አንቀጽ 614 መልሶ የማደራጀት ኃላፊዎች እና የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂዎች ኃላፊነት__

1) መልሶ የማደራጀት ኃላፊዎች እና የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂዎች፡-

ሀ) ሥራቸውን በሚሰሩበት ወቅት እንደ መንግስት ባለስልጣናት ይቆጠራሉ፤

ለ) ግዴታዎቻቸውን በሚወጡበት ወቅት አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሁሉ ማድረግ አለባቸው፤

ሐ) በዚህ መጽሐፍ ወይም በሌሎች ደንቦች ውስጥ የተቀመጡ ልዩ የኃላፊነት መንስኤዎች እንደተጠበቁ ሆነው ለሚፈጽሙት ከባድ ቸልተኝነት ወይም ሆነ ብለው ለሚፈጽሙት ጥፋት ኃላፊ ናቸው።

2) መልሶ የማደራጀት ኃላፊውን እና የከሰረውን ሰው ንብረት ጠባቂ የሚተኩት ኃላፊ እና ንብረት ጠባቂ፣ ማንኛውም ተቆጣጣሪ፣ ዐቃቤ ሕግ እና መልሶ በማደራጀት ሥነ ሥርዓት ወቅት ንብረቱ በይዞታው ስር ያለ ባለዕዳ ጉዳዮቹን ለመስማት በብቸኝነት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት መልሶ በማደራጀት ኃላፊው እና በከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ላይ የኃላፊነት ክስ ሊያቀርቡ ይችላሉ።
3) በንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት የሚቀርብ ማንኛውም ክስ ሥነ ሥርዓቱ ከተዘጋበት ጊዜ አንስቶ በአንድ ዓመት ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል። ይህ የጊዜ ገደብ በማንኛውም መልኩ አይቋረጥም ወይም አይታገድም።

__አንቀጽ 615 መልሶ የማደራጀት ኃላፊ እና የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ተደርገው ሊሾሙ የማይችሉ ሰዎች__

1) የሚከተሉት ሰዎች መልሶ የማደራጀት ኃላፊ ወይም የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ተደርገው አይሾሙም፡-

ሀ) በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በሌላ ሀገር ዕምነት ከማጉደል ወይም ከማጭበርበር ጋር ግንኙነት ያለው ማንኛውም ወንጀል በመፈጸም ጥፋተኛ የተባለ ማንኛውም ሰው፤

ለ) የሕዝባዊ ሙብቶቹን የሚከለክል የቅጣት ፍርድ የተፈረደበት ማንኛውም ሰው፤

ሐ) ማንኛውም የባለዕዳው ባለአክሲዮን፣ ሥራ አስኪያጅ ወይም ዳይሬክተር፤

መ) ከማንኛውም የባለዕዳው ባለአክሲዮን፣ ሥራ አስኪያጅ ወይም ዳይሬክተር ጋር አራተኛ ደረጃን ጨምሮ እስከ አራተኛ ደረጃ ድረስ የሚቆጠር የስጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው ማንኛውም ሰው፤

ሠ) ማንኛውም ከባለዕዳው ላይ ገንዘብ ጠያቂ፤

ረ) የጥቅም ግጭት ያለበት ወይም ሊኖርበት የሚችል ማንኛውም ሰው።

2) መልሶ የማደራጀት ኃላፊው እና የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ማንኛውንም የባለዕዳውን ንብረት መግዛት ወይም በሌላ አኳኋን ባለቤት መሆን አይችሉም። ይህን ድንጋጌ በመጣስ የሚፈጸም ማንኛውም ግዢ ወይም የንብረት ባለቤትነት ምንም ውጤት አይኖረውም። ይህን ድንጋጌ የጣሱ መልሶ የማደራጀት ኃላፊዎች እና የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂዎች ከኃላፊነታቸው ይነሳሉ።

**<u>አንቀጽ 616 መልሶ ለማደራጀት ኃላፊዎች እና ለከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂዎች ስለሚከፈል ክፍያ</u>**

1) መልሶ የማደራጀት ኃላፊው እና የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ በተለይም የጉዳዩን ውስብስብነት ከግምት ውስጥ በማስገባት ግዴታዎቻቸውን እንዲወጡ እና ሥልጣናቸውን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ምክንያታዊ የሆነ ክፍያ ይከፈላቸዋል።
2) ፍርድ ቤቱ መልሶ የማደራጀት ወይም የመክሠር ሥነ ሥርዓት ለመክፈት በሚሰጠው ፍርድ ውስጥ ምክንያታዊ የሆነውን ክፍያ ይወስናል።
3) መልሶ የማደራጀት ኃላፊው፣ የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ፣ ማንኛውም የባለዕዳው ሥራ አስኪያጅ ወይም ገንዘብ ጠያቂ በሚያቀርበው አቤቱታ መሰረት ፍርድ ቤቱ ለተቆጣጣሪው በሚከፈለው ክፍያ ላይ ከሁኔታው አንጻር ምክንያታዊ የሆነ ማስተካከያ ሊያደርግ ይችላል።
4) መልሶ የማደራጀት ኃላፊው እና የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ከንብረቱ ላይ ወጪ እና ኪሳራቸውን ለመተካት ከሚከፈላቸው ክፍያ ውጭ ሌላ ማንኛውም ገንዘብ አያገኙም።
5) የክፍያው ዝርዝር ሁኔታዎች በልዩ ደንቦች ሊወሰኑ ይችላሉ።

## <u>ርዕስ ሁለት</u>

## <u>ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓት</u>

**<u>አንቀጽ 617 ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓት ስለ መክፈት</u>**

1) ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓት የሚከፈተው ክፍያዎችን ገና ያላቋረጠ ወይም ክፍያዎችን ካቋረጠ አርባ አምስት ቀናት ያልሞላው እና የኢኮኖሚ ወይም የፋይናንስ ችግር በተጨባጭ ያጋጠመው ወይም ያጋጥመዋል ተብሎ የሚጠበቅ ባለዕዳ ሲያመለክት ብቻ ነው።
2) ባለዕዳው የቅርብ ጊዜ የሒሳብ መግለጫዎቹን፣ የገንዘብ ችግሮቹን ሁኔታ እና የሚፈቱበትን መንገድ የሚያስረዳ ጽሁፍ እንዲሁም የገንዘብ ፍሰት ቅድመ ትንበያ ኪሳራን ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ያቀርባል። ፍርድ ቤቱ አስፈላጊ ናቸው ብሎ የሚያምናቸውን ሌሎች ማናቸውም ሰነዶች እና መረጃዎች ባለዕዳው እንዲያቀርብ ትዕዛዝ ሊሰጥ ወይም እንደ ባንኮች እና የታክስ ባለሥልጣን አካላት ያሉ ሦስተኛ ወገኖችን እንዲያቀርቡ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል።
3) አስገዳጅ የሆኑ የኢትዮጵያ ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው ዕዳን መልሶ ማዋቀር የባለዕዳውን ንብረቶች እና ዕዳዎች ወይም ሌላ ማንኛውንም የባለዕዳውን የካፒታል መዋቅር ክፍል አወቃቀር፣ ሁኔታዎች ወይም

መዋቅር መቀየርን ወይም የንግድ ሥራውን ንብረቶች ወይም ክፍሎች ወይም አጠቃላይ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴውን በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ የንግድ ሥራ መሸጥን እንዲሁም አስፈላጊ የሆኑ ማናቸውንም የሥራ ሂደት ለውጦችን ማድረግን ወይም ከእነዚህ ውስጥ የተወሰኑትን ወስዶ ማቀናጀትን ሊያካትት ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 618</u>** **<u>የሥነ ሥርዓቱ የቆይታ ጊዜ</u>**

1) ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዕቅዱ ከሚመለከታቸው ገንዘብ ጠያቂዎች ጋር በአራት ወራት ውስጥ መጠናቅ ይኖርበታል፡፡
2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም፤ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዕቅዱ በሚመለከታቸው ገንዘብ ጠያቂዎች በሙሉ ድምጽ ተቀባይነት የማግኘት ዕድሉ ሰፊ እንደሆነ ባለዕዳው ካስረዳ ፍርድ ቤቱ ጊዜው እንዲራዘም ሊፈቅድ ይችላል፡፡ ማራዘሚያዎችን እና እድሳቶችን ጨምሮ ዕቅዱ የሚጠናቀቅበት አጠቃላይ ጊዜ ከስምንት ወራት መብለጥ የለበትም፡፡
3) የመክሠር ሥነ ሥርዓት ለመክፈት አቤቱታ ለማቅረብ ባለዕዳው ያለበት ግዴታ ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓቱ ለሚቆይበት ጊዜ ያህል ተቋርጦ ይቆያል፡፡

**<u>አንቀጽ 619</u>** **<u>ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዘርፍ ባለሞያ ስለ መሾም</u>**

የፍርድ ቤቱ ፕሬዝዳንት ባለዕዳው ሀሳብ በሚያቀርብበት ጊዜ ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓቱ ለሚቆይበት ጊዜ ያህል ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዘርፍ ባለሞያ ይሾማል፡፡

**<u>አንቀጽ 620</u>** **<u>ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዘርፍ ባለሞያውን ስለ መተካት</u>**

1) ሥነ ሥርዓቱ በሚካሄድበት ወቅት በማንኛውም ጊዜ ማንኛውም ገንዘብ ጠያቂ ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዘርፍ ባለሞያው እንዲተካ አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
2) ፍርድ ቤቱ አቤቱታውን በራሱ ሥልጣን ሊፈቅድ ይችላል፡፡
3) በንዑስ አንቀጽ (2) ውስጥ የተመለከተው ቢኖርም ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓቱ ከሚመለከታቸው አጠቃላይ የክፍያ ጥያቄዎች ውስጥ ሁለት ሦስተኛው ያላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች እንዲሾም የሚደግፉ ከሆነ ፍርድ ቤቱ አቤቱታውን በመፍቀድ አመልካቹ ይሹም ብሎ ያቀረበውን ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዘርፍ ባለሞያ ይሾማል፡፡

**<u>አንቀጽ 621</u>** **<u>ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዘርፍ ባለሞያው ግዴታዎች</u>**

1) ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዘርፍ ባለሞያው ራሱን ችሎ በመንሳቀስ የሚከተሉትን እንዲሁም ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡-

   ሀ) ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ በማዋቀር ሥነ ሥርዓቱ ውስጥ የሚሳተፉትን ገንዘብ ጠያቂዎች መወሰን፤

   ለ) መልሶ የማዋቀር ዕቅድ በማርቀቅ እና በመደራደር ረገድ ባለዕዳውን እና ገንዘብ ጠያቂዎቹን ማገዝ፤

   ሐ) የገንዘብ ጠያቂዎቹን ስብሰባዎች መጥራት እና በሊቀ መንበርነት መምራት፤

መ) ዕዳን መልሶ በማዋቀር ዕቅድ ላይ ድርድር በሚደረግበት ወቅት የባለዕዳውን እንቅስቃሴዎች መቆጣጠር እና ድርድሩ የሚገኝበትን ደረጃ በተመለከተ በየጊዜው ለፍርድ ቤቱ ሪፖርት ማቅረብ፤

ሠ) ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዕቅዱን ለፍርድ ቤቱ አቅርቦ ማስጸደቅ፤ እና

ረ) እንደሁኔታው በንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያለን ድርጅት በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ እንዲሸጥ ማዘጋጀት።

2) ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዘርፍ ባለሞያው ግዴታዎቹን ለመወጣት የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይችላል፡-

ሀ) ባለዕዳው ወይም ማንኛውም ሦስተኛ ወገን ማንኛውንም አስፈላጊ የሆነ ተጨማሪ የገንዘብ ወይም የሒሳብ መረጃ እንዲያቀርቡ ትዕዛዝ መስጠት፤

ለ) የባለዕዳውን የገንዘብ ሁኔታ እና የንግድ ሥራ ዕቅድ ኦዲት እንዲያደርጉ ጭምር ገለልተኛ ባለሞያዎችን መሾም።

**<u>አንቀጽ 622 ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዘርፍ ባለሞያው ስለሚከፈለው ክፍያ</u>**

በባለዕዳው እና ዕዳን መልሶ በማዋቀር ዘርፍ ባለሞያው መካከል ስምምነት የተደረገበት ክፍያ በሹመቱ ወቅት በፍርድ ቤቱ መጽደቅ አለበት።

**<u>አንቀጽ 623 ሚስጥራዊነት</u>**

ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓት መከፈቱ እንዲሁም በሥነ ሥርዓቱ ወቅት የሚደረጉ የመረጃ ልውውጦች እና ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዕቅዱን ጨምሮ ጥብቅ በሆነ መልኩ በሚስጥር መያዝ አለባቸው፤ እንዲሁም የፍርድ ቤት ሥነ ሥርዓቱ የሚካሄደው በዝግ ችሎት ነው። ይህን ድንጋጌ በማንኛውም መልኩ መጣስ አግባብ ባላቸው ሕጎች መሠረት የፍትሐ ብሔር እና የወንጀል ኃላፊነትን ያስከትላል።

**<u>አንቀጽ 624 በባለዕዳው ይዞታ ውስጥ ስለመሆኑ</u>**

ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ በማዋቀር ሥነ ሥርዓቱ ወቅት መደበኛ የሥራ ሂደቱ በባለዕዳው ይዞታ ውስጥ ይሆናል እንዲሁም ባለዕዳው በመደበኛ የሥራ ሂደት ውስጥ የሚወድቁ ማናቸውንም ውሳኔዎች የማስተላለፍ ሥልጣን አለው። ሆኖም አብዛኛውን ንብረት እንደመሸጥ እና የዋስትና መብት እንደመፍጠር ያሉ ከመደበኛ የሥራ ሂደት ውጭ የሆኑ ማናቸውም ውሳኔዎች ዕዳን መልሶ በማዋቀር ዘርፍ ባለሞያው አስቀድመው መጽደቅ አለባቸው።

**<u>አንቀጽ 625 በተናጠል ስለሚቀርቡ ክሶች መቋረጥ</u>**

1) ዕዳን መልሶ በማዋቀር ዕቅድ ላይ የሚደረገውን ድርድር ለመደገፍ ሲባል፤ ክፍያ እንዲፈጸምለት ጥያቄ ያቀረበ ወይም ክፍያ እንዲፈጸምለት ክስ የመሰረተ ገንዘብ ጠያቂ ጥያቄ ወይም ክስ እንዲቋረጥለት ባለዕዳው ለፍርድ ቤቱ አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል። ፍርድ ቤቱ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዘርፍ ባለሞያውን አስተያየት ሰምቶ ይወስናል።

2) በተናጠል የሚቀርቡ ክሶች መቋረጥ ማለት አንድ ገንዘብ ጠያቂ በአንድ ባለዕዳ ወይም በሦስተኛ ወገን ዋስትና ሰጪ ላይ ክፍያ ለማስፈጸም ያቀረበውን ክስ ለጊዜው ማቋረጥ ነው። ክስ ማቋረጡ ዋስትና ያላቸው እና ቅድሚያ የሚሰጣቸው የክፍያ ጥያቄዎችን ጨምሮ ሁሉንም ዓይነት የክፍያ ጥያቄዎች ይሸፍናል።

3) በተናጠል የሚቀርቡ ክሶች ተቋርጠው የሚቆዩበት አጠቃላይ ጊዜ ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ ከማዋቀር ሥነ ሥርዓቱ መርዘም የለበትም።

**<u>አንቀጽ 626</u>** **<u>በመደበኛ የሥራ ሂደት ውስጥ የሚከሰቱ ዕዳዎችን ስለ መክፈል</u>**

1) በዚህ ሕግ አንቀጽ 625 ውስጥ በተደነገገው መሰረት አስቀድመው ነጠላ እገዳ ከተላለፈባቸው ዕዳዎች በስተቀር ባለዕዳው በመደበኛ የሥራ ሂደት ውስጥ የሚከሰቱ ዕዳዎችን በሙሉ ባለዕዳው መክፈል ይኖርበታል።
2) ባለዕዳው በመደበኛ የሥራ ሂደት ውስጥ የሚከሰቱ ዕዳዎችን በሙሉ መክፈል እንደማይችል አስቀድሞ ከገመተ ባለዕዳው መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት ለመክፈት ያመለክታል።
3) ክፍያ በሚቋረጥበት ጊዜ ባለዕዳው በዚህ ሕግ አንቀጽ 705 ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት የመክሠር ሥነ ሥርዓት ለመክፈት ማመልከት ይኖርበታል።

**<u>አንቀጽ 627</u>** **<u>ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዕቅዱን ስለ ማጽደቅ</u>**

1) ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዕቅዱ ዕዳን መልሶ በማዋቀር ዘርፍ ባለሞያው ድጋፍ በባለዕዳው ይዘጋጃል። ገንዘብ ጠያቂዎቹ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዕቅዱን ለማሻሻል ጥያቄ የማቅረብ እና የአጸፋ-ሀሳብ የማቅረብ መብት አላቸው።
2) ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዕቅዱ ዕዳን መልሶ በማዋቀር ሥነ ሥርዓቱ ውስጥ በሚሳተፉ የሚመለከታቸው ገንዘብ ጠያቂዎች በሙሉ ተቀባይነት ማግኘት አለበት።
3) ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዕቅዱ የሚከተሉትን ጉዳዮች ሊያካትት ይችላል፦

   ሀ) ለሚመለከታቸው ገንዘብ ጠያቂዎች የክፍያ ጥያቄዎች እንደገና የጊዜ ሰንጠረዥ ማውጣት፤

   ለ) የሚመለከታቸው ገንዘብ ጠያቂዎችን የክፍያ ጥያቄዎችን መተው፤

   ሐ) የገንዘብ ዕዳ ሰነዶችን አወጣጥ በሚመለከቱ ሕጎች መሰረት የገንዘብ ዕዳ ሰነዶችን በማውጣት የክፍያ ጥያቄዎችን መፍታት፤

   መ) የሚመለከታቸውን ገንዘብ ጠያቂዎች የክፍያ ጥያቄዎች ወደ አክሲዮን መቀየር፤

   ሠ) የዚህ ሕግ አስገዳጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በገንዘብ ጠያቂው ወይም በሦስተኛ ወገን ኢንቨስተሮች የሚገዛውን የባለዕዳውን ካፒታል መጠን መቀነስ ወይም መጨመር፤

   ሸ) ለገንዘብ ጠያቂው ወይም ለሦስተኛ ወገን ኢንቨስተሮች ነባር አክሲዮኖችን መሸጥ ወይም አዲስ አክሲዮኖችን ማውጣት።

**<u>አንቀጽ 628</u>** **<u>አዲስ ለቀረበ ገንዘብ ስለሚደረግ ጥበቃ</u>**

1) አዲስ የቀረበው ገንዘብ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዕቅዱ በሚጸድቅበት ማዕቀፍ ውስጥ ሆኖ በፍርድ ቤቱ መጽደቅ አለበት። አዲስ የቀረበ ገንዘብ ማለት ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዕቅድን ተግባራዊ ለማድረግ ዕዳን መልሶ በማዋቀር ዕቅዱ ውስጥ ተካትቶ በነባር ወይም በአዲስ አበዳሪ የሚሰጥ እና ተከትሎ በፍርድ ቤቱ የሚጸድቅ ማንኛውም አዲስ የቀረበ ገንዘብ ነው።

2) አዲስ ገንዘብ የሚያቀርቡት ሰዎች ገንዘቡ መቅረቡ አጠቃላይ ገንዘብ ጠያቂዎቹን የሚጎዳ ነው በሚል የፍትሐ ብሔር፣ አስተዳደራዊ ወይም የወንጀል ኃላፊነት አይኖርባቸውም።

3) በኋላ ላይ የመክሠር ሥነ ሥርዓት የተከፈተ እንደሆነ አዲስ የቀረበው ገንዘብ ዋስትና ከሌላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች በፊት ቅድሚያ ይኖረዋል።

**<u>አንቀጽ 629</u>** **<u>ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዕቅዱ በፍርድ ቤት ስለ መጽደቁ</u>**

1) ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዕቅድ በፍ/ቤት መጽደቅ ይኖርበታል።

2) ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዕቅዱን በሚያጸድቅበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ፡-

   ሀ) በተለይም ደግሞ ዋስትና ከመያዝ እና አዲስ ገንዘብ ከሚቀርብበት ማዕቀፍ ጋር በተያያዘ የሦስተኛ ወገኖች ጥቅሞች በበቂ ሁኔታ መጠበቃቸውን፤

   ለ) ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዕቅዱ የባለዕዳውን መክሠር ይከላከላል እና የንግድ ሥራውን አዋጪነት ያረጋግጣል የሚል ምክንያታዊ ተስፋ ያለው መሆኑን ያረጋግጣል።

3) ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዕቅዱ የሚያስቀምጣቸው ሁኔታዎች በባለአክሲዮኖቹ መጽደቅ ያለባቸው እንደሆነ በንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች መሰረት መጽደቅ አለባቸው።

4) አዲስ የቀረበ ገንዘብ ያለ እንደሆነ ልዩ መብት ያለው አዲስ የቀረበ ገንዘብ መጠኑ ምን ያህል እንደሆነ የሚገልጸው የፍርዱ ክፍል ቅጂ ለሕዝብ ይፋ ይደረጋል።

5) ዋስትና ሰጪዎች ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዕቅዱን በማጣቀስ መብታቸውን ሊጠይቁ ይችላሉ። ከዚህ ንዑስ አንቀጽ ጋር በተያያዘ የሚነሳ ማንኛውም ግጭት ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓቱን በከፈተው ፍርድ ቤት ይሰማል።

6) ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዕቅዱ በፍርድ ቤቱ በሚጸድቅበት ጊዜ ተፈጻሚ ይሆናል።

**<u>አንቀጽ 630</u>** **<u>ይግባኝ</u>**

1) ባለዕዳው ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዕቅዱ ውድቅ እንዲሆን ፍርድ ቤቱ በሰጠው ፍርድ ላይ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል።

2) በንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚቀርቡ ይግባኞች ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዕቅዱን ውድቅ የሚያደርገው ፍርድ በተሰጠ በአሥር ቀናት ውስጥ መቅረብ አለባቸው፡፡

**<u>አንቀጽ 631</u>** **<u>በሦስተኛ ወገኖች የሚቀርብ ተቃውሞ</u>**

ሦስተኛ ወገኖች አዲስ የቀረበው ገንዘብ ያለውን ልዩ ጥቅም በመቃወም ለፍርድ ቤቱ አቤቱታ ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡ ተቃውሞው ፍርዱ ይፋ በተደረገ በሃያ ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡

**<u>አንቀጽ 632</u>** **<u>ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዕቅዱን ስለ መተው</u>**

1) ባለዕዳው ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዕቅዱ የሚያስቀምጣቸውን ሁኔታዎች ተግባራዊ ሳያደርግ የቀረ እንደሆነ ማንኛውም ገንዘብ ጠያቂ ፍርድ ቤቱ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዕቅዱን እንዲተው እና መልሶ የማደራጀት ወይም የመክሰር ሥነ ሥርዓት እንዲከፍት አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

2) መልሶ የማደራጀት ወይም የመክሰር ሥነ ሥርዓት መከፈቱ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዕቅዱን መተው ያስከትላል፡፡

3) ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዕቅዱ መተዉ ወደኋላ ተመልሶ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡ በተለይም ደግሞ ገንዘብ ጠያቂዎች ዕዳን መልሶ በማዋቀር ዕቅዱ መሰረት የተቀበሉት ገንዘብ የራሳቸው ይሆናል፤ እንዲሁም መልሰው ሊነጠቁ አይችሉም፡፡ ገንዘብ ጠያቂዎች በዚህ ሕግ አንቀጽ 628 መሰረት ልዩ መብት ካለው አዲስ የቀረበ ገንዘብ ጋር በተያያዘ ያገኙትን ቅድሚያ የማግኘት መብት እንደያዙ ይቀጥላሉ፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ውስጥ የተደነገገው ቢኖርም ዕዳን መልሶ በማዋቀር ዕቅዱ መሰረት ለይገባኛል ጥያቄዎች እንደገና የተዘጋጀው የጊዜ ሰንጠረዥ እና ማንኛውም የጊዜ ማራዘሚያ ወዲያውኑ ተፈጻሚነቱ ያቆማል፡፡ ገንዘብ ጠያቂዎች ዕዳን መልሶ በማዋቀር ዕቅዱ መሰረት የተዉትን ማንኛውንም የይገባኛል ጥያቄ እና የዋስትና መብቶች መልሰው ያገኛሉ፡፡

**<u>አንቀጽ 633</u>** **<u>ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓቱን ስለ ማሻሻል</u>**

1) በዚህ ሕግ አንቀጽ 629 ንዑስ አንቀጽ (6) ውስጥ የተደነገገው ቢኖርም ባለጉዳዮቹ ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዕቅዱን ከጸደቀ በኋላ ለማሻሻል ሊስማሙ ይችላሉ፡፡

2) በዚህ መልኩ የሚደረገው ማሻሻያ በዚህ ሕግ አንቀጽ 629 መሠረት በፍርድ ቤቱ መጽደቅ ሳያስፈልገው በባለጉዳዮቹ ላይ ሕጋዊ እና አስገዳጅ ይሆናል፡፡

**<u>አንቀጽ 634</u>** **<u>ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓት ወደ መልሶ ማደራጀት ሥነ ሥርዓት ወይም የመክሠር ሥነ ሥርዓት ስለሚቀየርበት ሁኔታ</u>**

1) ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ በማዋቀር ሥነ ሥርዓቱ መጨረሻ ላይ ወገኖቹ የተስማሙበት ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዕቅድ ከሌለ ባለዕዳው በሚያቀርበው ጥያቄ መሰረት ፍርድ ቤቱ ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓቱን ወደ መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት ወይም የመክሠር ሥነ ሥርዓት ሊቀይረው ይችላል፡፡

2) ፍርድ ቤቱ፡-

   ሀ) ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዕቅዱ በፍርድ ቤቱ ውድቅ ከተደረገ፤ ወይም

   ለ) ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዕቅዱ ከተተወ፤

   በራሱ ተነሳሽነት ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓቱን ወደ መክሠር ሥነ ሥርዓት ሊቀይር ይችላል።

3) ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዘርፍ ባለሞያው በአንቀጽ 689 መሰረት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴውን በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ የንግድ ሥራ ለመግዛት ጥያቄ ከቀረበለት ባለዕዳው በሚያቀርበው ጥያቄ መሰረት ፍርድ ቤቱ ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓቱን መልሶ ወደ ማደራጀት ሥነ ሥርዓት ሊቀይር ይችላል።

# ርዕስ ሦስት
# መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት

## ምዕራፍ አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 635 መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት ለመክፈት ስለሚቀርብ ጥያቄ

1) ፍርድ ቤቱ፡-

   ሀ) ባለዕዳው መወጣት የማይችለው የገንዘብ ችግር ያገጠመው መሆኑ ሲረጋገጥ እና ክፍያዎችን ያላቋረጠ ከሆነ ወይም ክፍያዎችን ካቋረጠ አርባ አምስት ቀናት ካልሞላው ባለዕዳው ጥያቄ በሚያቀርብበት ጊዜ፤

   ለ) ባለዕዳው ክፍያዎችን ያቋረጠ ከሆነ እና በሂደት ላይ ያለ ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓት ከሌለ፤ ማንኛውም ገንዘብ ጠያቂ ወይም ዐቃቤ ሕግ ጥያቄ በሚያቀርብበት ጊዜ፤

   ሐ) ማንኛውም ገንዘብ ጠያቂ ወይም ዐቃቤ ሕግ የመክሠር ሥነ ሥርዓት ለመክፈት አቤቱታ በሚያቀርቡበት ጊዜ ባለዕዳው ጥያቄ ካቀረበ እና ክፍያ ያቋረጠበት ሁኔታ ከተፈጠረ አርባ አምስት ቀናት እንዳልሞላው ማስረዳት የሚችል ከሆነ፤

መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት ሊከፍት ይችላል።

2) ማንኛውም ገንዘብ ጠያቂ ወይም ዐቃቤ ሕግ በሚያቀርበው ጥያቄ ወይም ፍርድ ቤቱ በራሱ ስልጣን እና ተነሳሽነት ማናቸውንም የንብረታቸውን ክፍል በማጭበርበር ለደበቁ፤ ለማጭበርበር በማሰብ አንዳንድ

ገንዘብ ጠያቂዎችን ሳይገልጹ ለቀሩ፤ ያለምክንያት ኃላፊነታቸውን ከፍ ላደረጉ ወይም ሌሎች ማናቸውንም የማጭበርበር ተግባራት ለፈጸሙ ሀሰተኛ ባለዕዳዎች መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓቶችን አይከፍትም።

**<u>አንቀጽ 636 የባለዕዳው ግዴታዎች</u>**

ባለዕዳው ሥነ ሥርዓቶቹን ከሚቆጣጠሩ ወይም ከሚያከናውኑ ሰዎች እና አካላት ጋር ሙሉ በሙሉ የመተባበር ግዴታ አለበት።

**<u>አንቀጽ 637 መቅረብ ስላለባቸው ሰነዶች</u>**

1) የሚከተሉት ሰነዶች ባለዕዳው መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት ለመክፈት ከሚያቀርበው አቤቱታ ጋር አባሪ ሆነው መቅረብ አለባቸው፡-

   ሀ) የንግድ ማኅበሩ ሦስት የመጨረሻ የሒሳብ ሚዛን ወረቀቶች ወይም የሒሳብ መግለጫዎች፤

   ለ) የትርፍ እና ኪሳራ ሒሳብ፤

   ሐ) ባለዕዳው ለመጠባበቂያ ጊዜው የሚሆን ገንዘብ እንዳለው የሚያሳይ የገንዘብ ፍሰት መግለጫ፤

   መ) የገንዘብ ጠያቂዎችን እና የባለዕዳዎችን ስም እና አድራሻ የያዘ የሚሰበሰቡ ንግድ-ነክ ገቢዎች እና ዕዳዎች ዝርዝር፤

2) ባለዕዳው የተሟሉ ሰነዶችን ለፍርድ ቤቱ ማቅረብ የማይችልበት ሁኔታ ውስጥ ከሆነ ባለዕዳው በአቤቱታው ውስጥ ምክንያቱን ማስረዳት አለበት።

3) ፍርድ ቤቱ ማናቸውንም አግባብነት ያላቸው ተጨማሪ ሰነዶች ባለዕዳው እንዲያቀርብ ሊጠይቅ ወይም ማንኛውም ሦስተኛ ወገን በተለይም ደግሞ ባንኮች እና የመንግስት አስተዳደር አካላት እንደዚያ ያሉ ሰነዶችን እንዲያቀርቡ ሊጠይቅ ይችላል።

4) በገንዘብ ጠያቂዎች የሚቀርበው አቤቱታ በቃለ መሀላ የተደገፈ ሆኖ የሚከተሉትን ሰነዶች ማካተት አለበት፡-

   ሀ)ገንዘብ ጠያቂዎቹ ጊዜው የደረሰ እና መከፈል ያለበት ነገር ግን ያልተከፈለ የክፍያ ጥያቄ እንዳላቸው የሚያሳይ ማስረጃ፤

   ለ) ባለዕዳው ለምን ክፍያዎችን መፈጸም እንዳልቻለ የሚያሳይ ማስረጃ፤

   ሐ) ገንዘብ ጠያቂው መደበኛ የፍትሐ ብሔር ሥርዓቶችን ተከትሎ በባለዕዳው ላይ ያሉትን የክፍያ ጥያቄዎች ለማስፈጸም ያልቻለባቸውን ወይም ከዚህ በኋላ ማስፈጸም የሚችልበት ሁኔታ ውስጥ ያልሆነባቸውን ምክንያቶች የሚያሳይ ማስረጃ፤

   መ) ባለዕዳው ክፍያ ያቋረጠበት ሁኔታ ውስጥ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ።

**<u>አንቀጽ 638 መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት የሚሰጥ ፍርድ</u>**

1) መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት የሚሰጠው ፍርድ በፍርድ ቤቱ ከተሰጠበት ቀን የመጀመሪያው ሠዓት አንስቶ በሁሉም ወገኖች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

2) መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት የተሰጠው ፍርድ ወዲያውኑ ተፈጻሚ ይሆናል።

**<u>አንቀጽ 639 መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት ለመክፈት የቀረበን አቤቱታ ውድቅ በሚያደርግ ፍርድ ላይ ይግባኝ ስለማቅረብ</u>**

1) ባለዕዳው፣ ማንኛውም ገንዘብ ጠያቂ ወይም ዐቃቤ ሕግ ፍርዱ በተሰጠ በአሥር ቀናት ውስጥ መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት ለመክፈት የቀረበን አቤቱታ ውድቅ በሚያደርገው ፍርድ ላይ ይግባኝ ማቅረብ ይችላሉ።
2) ይግባኙ በተፋጠነ ሥነ ሥርዓት ተሰምቶ በሁለት ወራት ውስጥ ውሳኔ ይሰጥበታል እንዲሁም ፍርዱ ወዲያውኑ ተፈጻሚ ይሆናል።

**<u>አንቀጽ 640 መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት ለመክፈት የተሰጠ ፍርድን ስለ መቃወም እና ይግባኝ ስለማቅረብ</u>**

1) መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት የተሰጠው ፍርድ በተሰጠ በአሥር ቀናት ውስጥ ዐቃቤ ሕግ በውሳኔው ላይ ይግባኝ ሊያቀርብ ወይም በፍርዱ ላይ ተቃውሞ ሊያቀርብ ይችላል።
2) መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት አቤቱታ ያላቀረቡ ገንዘብ ጠያቂዎች መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት የተሰጠው ፍርድ በተሰጠ በአሥር ቀናት ውስጥ ፍርዱን ሊቃወሙ ይችላሉ።
3) ይግባኙ በተፋጠነ ሥነ ሥርዓት ተሰምቶ በሁለት ወራት ውስጥ ውሳኔ ይሰጥበታል፤ እንዲሁም ፍርዱ ወዲያውኑ ተፈጻሚ ይሆናል።

**<u>አንቀጽ 641 ይግባኝ የማይቀርብባቸው ፍርዶች</u>**

ተቆጣጣሪ ዳኛውን፣ መልሶ የማደራጀት ኃላፊውን ወይም ተቆጣጣሪዎችን ለመሾም ወይም ለመተካት የሚሰጡ ፍርዶች ይግባኝ ወይም ተቃውሞ ሊቀርብባቸው አይችልም።

**<u>አንቀጽ 642 መልሶ የማደራጀት ኃላፊ ስለ መሾም</u>**

1) ፍርድ ቤቱ በዚህ ሕግ ከአንቀጽ 610 እስከ አንቀጽ 616 በተደነገገው መሰረት መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት በሚሰጠው ፍርድ ውስጥ መልሶ የማደራጀት ኃላፊ ይሾማል። የተወሳሰቡ ጉዳዮች በሚኖሩበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ ሁለት መልሶ የማደራጀት ኃላፊዎችን ሊሾም ይችላል። ፍርድ ቤቱ ባለዕዳው ያቀረበውን ሰው ሊሾም ይችላል።
2) ብዙ ኃላፊዎች በሚሾሙበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ በተናጠል እንዲንቀሳቀሱ ካልፈቀደላቸው በስተቀር በጋራ ይንቀሳቀሳሉ።
3) ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዘርፍ ባለሞያው የንግድ ሥራ እንቅስቃሴው በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ የንግድ ሥራ እንዲሸጥ ያዘጋጀ ከሆነ ፍርድ ቤቱ መልሶ የማደራጀት ኃላፊ አድርጎ ይሾመዋል።

**<u>አንቀጽ 643 መልሶ የማደራጀት ኃላፊውን በሌላ ስለ መተካት</u>**

1) ሥነሥርዓቱ በሚካሄድበት ወቅት በማንኛውም ጊዜ ተቆጣጣሪ ዳኛው፣ ማንኛውም ገንዘብ ጠያቂ፣ ተቆጣጣሪ ወይም ዐቃቤ ሕግ መልሶ የማደራጀት ኃላፊው በሌላ እንዲተካ ለፍርድ ቤቱ አቤቱታ ሊያቀርቡ ይችላሉ።
2) ፍርድ ቤቱ አቤቱታውን ሊፈቅድ ይችላል።

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ውስጥ የተመለከተው ቢኖርም ከአጠቃላይ የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎቹ ውስጥ አብላጫ ቁጥር ያላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች እንዲሾም የሚደግፉ ከሆነ ፍርድ ቤቱ አቤቱታውን በመፍቀድ አመልካቹ ያቀረበውን መልሶ የማደራጀት ኃላፊ ይሾማል፡፡

**<u>አንቀጽ 644</u>** **<u>*መልሶ የማደራጀት ኃላፊው ሥልጣን እና ኃላፊነቶች*</u>**

*መልሶ በማደራጀት ሥነ ሥርዓቱ ወቅት መልሶ የማደራጀት ኃላፊው የሚከተለው ሥልጣን እና ኃላፊነቶች አሉት፡*

-

1) *መደበኛ የሥራ ሂደቱን ማከናወንን በተመለከተ ባለዕዳውን መቆጣጠር፤*
2) *የባለዕዳው ንብረት የሚገኝበትን ትክክለኛ ቦታ ለማወቅ የሚያስችለውን መረጃ ከመንግስት ባለሥልጣን አካላት፣ ከማህበራዊ ዋስትና ተቋማት፣ ከብድር ተቋማት እና ከሌሎች ተቋማት መቀበል፤*
3) *የንብረቶቹን ዝርዝር በማዘጋጀት ረገድ ባለዕዳውን መቆጣጠር፤*
4) *መልሶ የማደራጀት ዕቅዱን በማዘጋጀት ረገድ ባለዕዳውን ማገዝ፤*
5) *አግባብ በሚሆንበት ጊዜ የገንዘብ ጠያቂዎች መደቦችን ማዋቀር፤*
6) *የንግድ ሥራ እንቅስቃሴው በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ የንግድ ሥራ እንዲሸጥ ማዘጋጀት፤*
7) *ከባለዕዳው መደበኛ የሥራ ሂደት ውጭ የሚቀበለውን ማናቸውንም ገንዘብ በንብረቱ ስም የሚከፈት የባንክ ሒሳብ ውስጥ ገቢ ማድረግ፤*
8) *የቅድመ-ኪሳራ ጥያቄዎችን እንዲቀበል ወይም ውድቅ እንዲያደርግ ለተቆጣጣሪ ዳኛው ሀሳብ ማቅረብ፤*
9) *የገንዘብ ጠያቂዎች መደብ ስብሰባ ወይም የገንዘብ ጠያቂዎች ጠቅላላ ጉባዔ ከመደረጉ ቢያንስ አምስት ቀናት አስቀድሞ ለፍርድ ቤቱ መዝገብ ቤት ሹም ገቢ የሚደረግ የባለዕዳውን ጉዳዮች እና ተግባራት የተመለከተ ዝርዝር ሪፖርት አዘጋጅቶ ማቅረብ፤*
10) *የገንዘብ ጠያቂዎች መደቦች ስብሰባ ወይም የገንዘብ ጠያቂዎች ጠቅላላ ጉባዔ ከመደረጉ ቢያንስ አምስት ቀናት አስቀድሞ ለፍርድ ቤቱ መዝገብ ቤት ሹም ገቢ የሚደረግ ለባለዕዳዎች የቀረቡ ዋስትናዎችን ጨምሮ የተዘጋጁትን የተለያዩ መልሶ የማደራጀት ዕቅዶች የተመለከተ ዝርዝር ሪፖርት አዘጋጅቶ ማቅረብ፤*
11) *የገንዘብ ጠያቂዎች መደብ ስብሰባዎችን ወይም የገንዘብ ጠያቂዎች ጠቅላላ ጉባዔዎችን በሊቀ መንበርነት መምራት፤*
12) *በተለይም የባለዕዳውን የፋይናንስ ሁኔታ እና የንግድ ሥራ ዕቅድ ኦዲት እንዲያደርጉ እና የባለዕዳውን የንብረት ዝርዝር እና የዋጋ ግምት እንዲያዘጋጁ ራሳቸውን የቻሉ ባለሞያዎችን እንዲሾም ለተቆጣጣሪ ዳኛው ጥያቄ ማቅረብ፤*
13) *የሚሰጠው አገልግሎት በተቋረጠ በሠላሳ ቀናት ውስጥ ወይም በጣም ቢዘገይ ሥነ ሥርዓቱ በተቋረጠ በሠላሳ ቀናት ውስጥ ለፍርድ ቤቱ ሪፖርት ማቅረብ፡፡*

**<u>አንቀጽ 645</u>** **<u>*ተቆጣጣሪዎችን ስለ መሾም*</u>**

1) *ተቆጣጣሪ ዳኛው ከገንዘብ ጠያቂዎቹ ውስጥ በሚያቀርቡት ጥያቄ መሰረት እስከ አምስት ድረስ ተቆጣጣሪዎችን ይሾማል፡፡ ተቆጣጣሪ ዳኛው አንድ ተቆጣጣሪ ዋስትና ካላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች ውስጥ እና ሌላ አንድ ተቆጣጣሪ ደግሞ ዋስትና ከሌላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች መመረጡን ያረጋግጣል፡፡*

2) ከባለዕዳው ወይም ከባለዕዳው ሥራ አስኪያጅ ጋር እስከ አራተኛ ደረጃ የሚቆጠር የስጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው ማንኛውም ሰው ወይም በባለዕዳው ንብረት ውስጥ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ድርሻ ያለው ማንኛውም ሰው ተቆጣጣሪ ተደርጎ ሊሾም አይችልም፡፡

3) ተቆጣጣሪዎች የሁሉንም ገንዘብ ጠያቂዎች አጠቃላይ ጥቅም ያስጠብቃሉ፤ እንዲሁም መልሶ የማደራጀት ዕቅዱን በማዘጋጀት ረገድ መልሶ ለማደራጀት ኃላፊው ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡

4) ተቆጣጣሪዎች መልሶ የማደራጀት ኃላፊው በሚያጸድቀው መሰረት ወጪያቸውን ለመሸፈን ከሚያገኙት ክፍያ ውጭ ሌላ ማናቸውንም ዓይነት ክፍያ የማግኘት መብት የላቸውም፡፡

5) ተቆጣጣሪዎች ማንኛውንም የባለዕዳውን ንብረት መግዛት አይችሉም፡፡ ይህን ድንጋጌ በመጣስ የሚፈጸም ማንኛውም ግዢ ምንም ዓይነት ውጤት አይኖረውም፤ እንዲሁም ይህን ድንጋጌ የጣሰው ተቆጣጣሪ ተሽሮ በሌላ ሰው ይተካል፡፡

**<u>አንቀጽ 646</u>** **<u>ተቆጣጣሪዎችን ስለ መተካት</u>**

ፍርድ ቤቱ በማንኛውም ጊዜ በራሱ ተነሳሽነት ወይም ተቆጣጣሪ ዳኛው ወይም የተቆጣጣሪው ወይም ዐቃቤ ሕግ በሚያቀርበው ጥያቄ መሰረት አሳማኝ ምክንያት ሲኖር ማንኛውንም ተቆጣጣሪ በሌላ ሰው ሊተካ ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 647</u>** **<u>የተቆጣጣሪዎች ኃላፊነት</u>**

ማንኛውም ተቆጣጣሪ በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችለው በከባድ ቸልተኝነት ወይም ሆነ ብሎ በሚፈጽመው ጥፋት ብቻ ነው፡፡

**<u>አንቀጽ 648</u>** **<u>የፍርድ ማስታወቂያ</u>**

1) የፍርድ መዝገብ ቤት ሹሙ የፍርድ ቤቱ መግቢያ ላይ ማስታወቂያ በመለጠፍ እና በኢትዮጵያ ውስጥ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ላይ ቅጂያቸውን በማሳተም መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት ለመክፈት እና ለመዝጋት የተሰጡ ፍርዶችን ያስታውቃል፡፡

2) የፍርድ መዝገብ ቤት ሹሙ መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት ለመክፈት የተሰጠው ፍርድ አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሰረት በንግድ መዝገብ ውስጥ መግባቱን ያረጋግጣል፡፡

3) መልሶ የማደራጀት ኃላፊው እና የፍርድ መዝገብ ቤት ሹሙ የባለዕዳው የሒሳብ መዛግብት መጨረሻ ላይ መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት የተሰጠውን ፍርድ አስገብተው ማስታወሻ በመጻፍ ይፈርማሉ፤ ከዚያም የሒሳብ መዛግብቱ ለባለዕዳው ተመልሰው ይሰጣሉ፡፡

4) መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት ለመክፈት ወይም ለመዝጋት የተሰጠው ፍርድ ቅጂ ለባለዕዳው፣ መልሶ ለማደራጀት ኃላፊው እና አቤቱታ ላቀረበው ገንዘብ ጠያቂ ፍርዱ እንደተሰጠ ወዲያውኑ ይላካል፡፡ ቅጂው የባለዕዳዎቹን፣ የሥነ ሥርዓቱን ሌሎች ወገኖች፣ መልሶ የማደራጀት ኃላፊውን እና የተቆጣጣሪ ዳኛውን ስም እንዲሁም ፍርዱ ተፈጻሚ የሚሆንበትን ቀን ይገልጻል፡፡

5) የፍርድ ቤቱ መዝገብ ቤት ሹም የፍርዱን ቅጂ ለዐቃቤ ሕግ ይልካል፡፡

6) የንግድ መዝገቡ ላይ አስፈላጊ የሆኑት ማስተካከያዎች እንዲደረጉ የፍርድ መዝገብ ቤት ሹሙ የፍርዱን ሦስት ቅጂዎች የንግድ መዝገቡን ለሚቆጣጠሩት የፌዴራል ወይም የክልል ባለስልጣናት ይልካል፡፡

7) የፍርዱ ቅጂ በባለዕዳው ቅጥር ግቢ እና ባለዕዳው ሥራውን በሚያከናውንበት ማንኛውም ቦታ ይለጠፋል።

**<u>አንቀጽ 649</u>** **<u>ለገንዘብ ጠያቂዎች ስለሚሰጥ ማሳወቂያ</u>**

መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት የተሰጠው ፍርድ በተላለፈ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መልሶ የማደራጀት ኃላፊው፡-

1) መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት ፍርድ የተሰጠበትን ቀን፤
2) የተቆጣጣሪ ዳኛውን እና የመልሶ ማደራጀት ኃላፊውን ስም፤
3) የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎች የሚቀርቡባቸውን ሁኔታዎች፤

የያዘ ማሳወቂያ ለሚታወቁ የባለዕዳው ገንዘብ ጠያቂዎች በሙሉ በአደራ ደብዳቤ ወይም ተቀባዩ ለመቀበሉ ማረጋገጫ ሊሰጥበት በሚችል ሌላ ማንኛውም ኤሌክትሮኒክ መንገድ ይልካል።

**<u>አንቀጽ 650</u>** **<u>የሰነድ ማስረጃ</u>**

ማስታወቂያዎች የግድ እንዲወጡ የሚያስገድዱ ግዴታዎች መሟላታቸውን እና ለገንዘብ ጠያቂዎች ማሳወቂያ መስጠቱን የሚያሳዩ የሰነድ ማስረጃዎች መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓቱ ፋይል ውስጥ በፍርድ ቤቱ መዝገብ ቤት ሹም ይመዘገባሉ።

**<u>ምዕራፍ ሁለት</u>**

**<u>በመጠባበቂያ ጊዜ ወቅት ስለ ባለዕዳው</u>**

**<u>አንቀጽ 651</u>** **<u>የመጠባበቂያ ጊዜ</u>**

1) መልሶ የማደራጀት ሥርዓት እንዲከፈት ፍርድ እንደተሰጠ የመጠባበቂያ ጊዜው የሚጀምር ሲሆን ዓላማውም፡-

    ሀ) መልሶ በማደራጀት ኃላፊው ድጋፍ ባለዕዳው መልሶ የማደራጀት ዕቅድ እንዲያዘጋጅ ማስቻል፤

    ለ) ገንዘብ ጠያቂዎቹ እና መልሶ የማደራጀት ኃላፊው ባለዕዳው ባዘጋጀው መልሶ የማደራጀት ዕቅድ ላይ የማሻሻያ ሀሳቦችን እንዲያቀርቡ ወይም አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ አማራጭ መልሶ የማደራጀት ዕቅድ እንዲያቀርቡ ማስቻል፤

    ሐ) መልሶ የማደራጀት ኃላፊው በተጨማሪ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴው በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ የንግድ ሥራ ለኢንቨስተሮች የሚሸጥበትን ዕቅድ እንዲያዘጋጅ ማስቻል ነው። የንግድ ሥራ እንቅስቃሴው በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ የንግድ ሥራ ለመሸጥ ዝግጅት በሚያደርግበት ጊዜ መልሶ የማደራጀት ኃላፊው

ከዚህ ጋር በተያያዘ የገበያ ጥናት ሊያከናውን ይችላል እንዲሁም ኢንቨስተሮች ጨረታ እንዲያቀርቡ ይጋብዛል።

2) የመጀመሪያው የመጠባበቂያ ጊዜ ርዝመት ቢበዛ በአራት ወር ጊዜ የተገደበ ነው።
3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ውስጥ የተመለከተው ቢኖርም ባለዕዳው፣ ማንኛውም ገንዘብ ጠያቂ፣ ተቆጣጣሪው ወይም መልሶ የማደራጀት ኃላፊው በሚያቀርቡት ጥያቄ መሰረት ፍርድ ቤቱ የመጠባበቂያ ጊዜውን ሊያራዝመው ወይም አዲስ የመጠባበቂያ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል። ፍርድ ቤቱ የጊዜ ማራዘሚያ ሊሰጥ የሚችለው በሚከተሉት ሁኔታዎች መሰረት ማራዘሚያውን ለመስጠት በቂ ምክንያት ሲኖር ብቻ ነው፡-

   ሀ) መልሶ በማደራጀት ዕቅዱ ላይ የሚደረገው ድርድር ተገቢው የአፈጻጸም ደረጃ ላይ የሚገኝ ከሆነ፤ እና

   ለ) ክፍያ ለማስፈጸም በተናጠል የሚደረጉ ክርክሮች በጠቅላላ ተቋርጠው መቆየታቸው የማናቸውንም የሚመለከታቸውን ወገኖች መብቶች እና ጥቅሞች ሚዛናዊ ባልሆነ መልኩ የማይጎዳ ከሆነ።

4) ማራዘሚያዎችን እና እድሳቶችን ጨምሮ የሚሰጠው የመጠባበቂያ ጊዜ አጠቃላይ ርዝመት ከአሥራ ሁለት ወራት መብለጥ የለበትም።

**<u>አንቀጽ 652</u>** **<u>ስለ መጠባበቂያ ጊዜ መቋረጥ</u>**

በአንቀጽ 651 ውስጥ የተመለከተው ቢኖርም፡-

1) መልሶ የማደራጀት ዕቅዱ እንዳይጸድቅ ሊያደርጉ የሚችሉት ገንዘብ ጠያቂዎች ብዛት ድርድሩ እንዲቀጥል የሚያስችል እንዳልሆነ ግልጽ ከሆነ፤ ወይም
2) መልሶ የማደራጀት ኃላፊው የንግድ ሥራ እንቅስቃሴው በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ የንግድ ሥራ ለመሸጥ ምንም ኢንቨስተር ያለማግኘቱ ግልጽ ከሆነ፤ ወይም
3) ባለዕዳው፣ መልሶ የማደራጀት ኃላፊው ወይም ተቆጣጣሪው ጥያቄ ካቀረቡ፤ ወይም
4) ባለዕዳው መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት ከተከፈተ በኋላ የሚፈጠሩ የክፍያ ጥያቄዎችን በተመለከተ የመክፈል ግዴታውን መወጣት ካልቻለ፤

ፍርድ ቤቱ የመጠባበቂያ ጊዜውን ሊያቋርጥ እና መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓቱን ወደ መክሠር ሥነ ሥርዓት ሊቀይረው ይችላል።

**<u>አንቀጽ 653</u>** **<u>በባለዕዳው ይዞታ ውስጥ ስለ መቆየት</u>**

1) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ውስጥ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በመጠባበቂያ ጊዜው ወቅት የባለዕዳው ንብረት እና ጉዳይ በባለዕዳው ይዞታ ውስጥ ይቆያሉ።
2) መልሶ የማደራጀት ኃላፊው ወይም ተቆጣጣሪ ዳኛው አስቀድመው እንዲፈቅዱለት ሳያስፈልገው ባለዕዳው የንግድ ሥራውን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች በሙሉ የማከናወን መብት አለው።

3) መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት ከተከፈተ በኋላ የስጦታ ውሎች እና ዋስትና እና የንብረት የዋስትና መብቶችን ጨምሮ ነገር ግን በዚያ ሳይወሰን ከባለዕዳው መደበኛ የሥራ ሂደት ውጭ የሆኑ ስምምነቶች ወይም ግብይቶች በሙሉ በመልሶ ማደራጀት ኃላፊው አስቀድመው መፈቀድ አለባቸው።

4) መልሶ የማደራጀት ኃላፊው እና ተቆጣጣሪ ዳኛው በማንኛውም ጊዜ የባለዕዳውን የሂሳብ መዛግብት ሊመረምሩ ይችላሉ።

5) መልሶ የማደራጀት ኃላፊው ሆነ ብሎ ገንዘብ ጠያቂዎችን ያለመግለጽን ጨምሮ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ላይ የሚፈጸሙ ማናቸውንም ጥሰቶች እንዲሁም ማንኛውንም የማጭበርበር ድርጊት ለሚመለከታቸው የዐቃቤ ሕግ እና ሕግ አስከባሪ አካላት ማሳወቅ ይኖርበታል።

## <u>አንቀጽ 654 ክፍያ ለማስፈጸም በተናጠል የሚደረጉ ክርክሮች በአጠቃላይ ስለ መቋረጣቸው</u>

1) የመያዣ እና የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ የንብረት ዋስትና ያላቸውን፣ ቅድሚያ ያላቸውን እንዲሁም ባለሀብትነታቸው እንደ ተጠበቀ ሆኖ የተደረጉ የሽያጭ ውሎች ያሏቸው ገንዘብ ጠያቂዎችን ጨምሮ በማናቸውም ገንዘብ ጠያቂዎች ክፍያ ለማስፈጸም በተናጠል የሚደረጉ ክርክሮች በሙሉ ባለዕዳው ወይም መልሶ የማደራጀት ኃላፊው በተናጠል ክፍያ ለማስፈጸም የሚደረጉ ክርክሮች እንዲቋረጡላቸው ጥያቄ ማቅረብ ሳያስፈልጋቸው በመጠባበቂያ ጊዜው ወቅት በሕግ ተቋርጠው ይቆያሉ።

2) ዋስ የሆኑ የተፈጥሮ ሰዎች በመልሶ ማደራጀት ሥነ ሥርዓት ውስጥ በተናጠል ክፍያ ለማስፈጸም የሚደረጉ ክርክሮች እንዲቋረጡላቸው መጠየቅ ይችላሉ።

3) በመጠባበቂያ ጊዜው ወቅት የይርጋ ጊዜ እና ቅድሚያ የማግኘት መብት ይታገዳሉ።

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ውስጥ የተመለከተው ቢኖርም ለባለዕዳው ሰራተኞች የሚከፈል ክፍያ አይቋረጥም።

5) ተቆጣጣሪ ዳኛው፡-

ሀ) ለዕዳ ማስያዣነት የዋሉ ንብረቶች በባለዕዳው ይዞታ ውስጥ ካልሆኑ፤ ወይም

ለ) በተናጠል ክፍያ ለማስፈጸም የሚደረጉ ክርክሮች የንግድ ሥራውን መልሶ የማዋቀር ሥራውን የማስተጓጎል ዕድላቸው አነስተኛ ከሆነ፤ ወይም

ሐ) በተናጠል ክፍያ ለማስፈጸም የሚደረጉ ክርክሮች በአጠቃላይ መቋረጣቸው አንድ ወይም ከዚያ በላይ ገንዘብ ጠያቂዎችን አግባብ ባልሆነ መልኩ የሚጎዳ ከሆነ፤

ሌሎች የክፍያ ጥያቄዎችን በተናጠል ክፍያ ለማስፈጸም የሚቀርቡ ክሶች ላይ ከሚቀመጡ አጠቃላይ እገዳዎች የአፈጻጸም ወሰን ውጭ ሊያደርግ ይችላል።

## <u>አንቀጽ 655 ክፍያ ለማስፈጸም በተናጠል የሚደረጉ ክርክሮች በአጠቃላይ መቋረጣቸው የሚያስከትላቸው ውጤቶች</u>

በመጠባበቂያ ጊዜው ወቅት፡-

1) የመክሠር ሥነ ሥርዓት ለመክፈት ማመልከቻ የማቅረብ ግዴታ ይቋረጣል፤
2) የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎች የመክፈያ ጊዜያቸው ሊፋጠን አይችልም፤
3) በቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎች ላይ የሚታሰበው ወለድ አግባብ ባለው ምጣኔ መሰረት መታሰቡን ይቀጥላል፤
4) ገንዘብ ጠያቂዎች የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎችን መክፈል በተመለከተ ማናቸውንም የሕግ ክርክሮች አይጀምሩም፤
5) ገንዘብ ጠያቂዎች ማናቸውንም የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄ ክፍያ መቀበል አይችሉም።

**አንቀጽ 656 ባለዕዳው የቅድመ-ኪሳራ ክፍያዎችን እንዳይከፍል ስለ መከልከሉ**

1) ባለዕዳው በመጠባበቂያ ጊዜው ወቅት በቅድመ-ኪሳራ ክፍያዎች ላይ የሚታሰቡ ወለዶችን ጨምሮ የቅድመ-ኪሳራ ክፍያዎችን መክፈል የለበትም።
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ውስጥ የተመለከተው ቢኖርም ንብረቶቹ መመለሳቸው ለሀብቱ የሚጠቅም ከሆነ በማስያዣነት ይዞታቸው የተላለፈ ንብረቶችን ጨምሮ ባለዕዳው በዕዳ የተያዙ ንብረቶችን መልሶ በይዞታው ስር እንዲያደርግ ለማስቻል ሲባል ተቆጣጣሪ ዳኛው እንዲህ ያሉ ክፍያዎች እንዲከፈሉ ሊፈቅድ ይችላል።

**አንቀጽ 657 በሂደት ላይ ስላሉ ሥነ ሥርዓቶች**

1) በመጠባበቂያ ጊዜው ወቅት የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄ እስካልቀረበ ድረስ ግልግልን ጨምሮ በሂደት ላይ ያሉ የሕግ ሥነ ሥርዓቶች በሙሉ ይቋረጣሉ።
2) የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄው ተቀባይነት ሲያገኝ መልሶ የማደራጀት ኃላፊው የሥነ ሥርዓቱ አንድ ወገን ሆኖ ሥርዓቱ ይቀጥላል። ሆኖም ግን ሥነ ሥርዓቱ የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄውን መጠን በማረጋገጥ ላይ የተወሰነ ይሆናል።
3) መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት መከፈቱ በሂደት ላይ ካሉ ውሎች የሚመነጭ ማቻቻልን ሳይጨምር የቅድመ-ኪሳራ ክፍያ መክፈልን ወይም ክፍያ ባለመፈጸም ምክንያት በሂደት ላይ ያለ ውል ማቋረጥን በማያስከትሉ ማናቸውም ሥነ ሥርዓቶች ላይ እንዲሁም በተለይም ደግሞ በሚከተሉት ሥነ ሥርዓቶች ላይ ተጽዕኖ አያሳድርም፡-

   ሀ) በባለዕዳው ላይ የሚመሰረቱ የወንጀል ሥነ ሥርዓቶች፤

   ለ) በባለዕዳው ላይ የሚመሰረቱ ሙብት ለማስነገር የሚቀርቡ ክሶች፤

   ሐ) የመንግስትን የመቆጣጠር ሥልጣን ለማስፈጸም የሚደረጉ ሥነ ሥርዓቶች፤

   መ) ታክስ ከመሰብሰብ ውጭ ያሉ የታክስ ኦዲቶች እና ምርመራዎች።

**አንቀጽ 658 የሻጩ ዕቃውን ይዞ የመቆየት መብት**

1) ዕቃዎቹን ባለዕዳው ያልተረከበ ከሆነ ወይም ዕቃዎቹ ለባለዕዳው ወይም የባለዕዳው ተወካይ ለሆነ ሦስተኛ ወገን ካልተላኩ ሻጩ የሸጣቸውን ዕቃዎች እንደያዘ የመቆየት መብት አለው፡፡
2) መልሶ የማደራጀት ኃላፊው ተቆጣጣሪ ዳኛው በሚፈቅድበት ጊዜ የተስማሙበትን ዋጋ ለሻጩ በመክፈል ሻጩ የያዛቸውን ዕቃዎች እንዲያስረክብ ሊጠይቅ ይችላል፡፡
3) መልሶ የማደራጀት ኃላፊው በንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ዕቃዎቹን ለመረከብ ያልጠየቀ ከሆነ ሻጩ ማናቸውንም የተቀበላቸውን ተከታታይ ክፍያዎች እንዲሁም ማናቸውም ለጭነት አገልግሎት ወይም ለማጓጓዣ ወጪዎች፣ ለኮሚሽን፣ ለኢንሹራንስ ወይም ለሌሎች ወጪዎች ከባለዕዳው የተቀበላቸውን ቅድመ ክፍያዎች ለባለዕዳው መመለስ ይኖርበታል፡፡ እንዲሁም ሻጩ እነዚህን ገንዘቦች ራሱ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡ ሆኖም ግን ሻጩ ውልን ካለመፈጸም ጋር በተያያዘ የጉዳት ካሳ እንዲከፈለው ሊጠይቅ ይችላል፡፡

## <u>ምዕራፍ ሦስት</u>
## <u>የባለዕዳው ሀብት</u>

### <u>ክፍል አንድ</u>
### <u>የንብረት ዝርዝር</u>

**<u>አንቀጽ 659</u>** **<u>የንብረት ዝርዝር ስለ ማረጋገጥ</u>**

1) ባለዕዳው መልሶ በማደራጀት ኃላፊ ቁጥጥር ስር ሆኖ መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት በተከፈተ በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ ሁሉንም ንብረቶቹን የያዘ የንብረት ዝርዝር ያዘጋጃል፡፡ ዝርዝሩ በተለይ የሚከተሉትን ያካትታል፡-

   ሀ) የክፍያ ጥያቄያቸውን መጠን፣ ስማቸውን እና አድራሻቸውን የሚገልጽ የገንዘብ ጠያቂዎች ዝርዝር፤

   ለ) ባለሀብትነታቸው እንደ ተጠበቀ ሆኖ የተፈጸሙ የሽያጭ ውሎችን ጨምሮ በሂደት ላይ ያሉ ውሎች፤

   ሐ) በማስያዣነት ይዞታቸው የተላለፈ ንብረቶችን፣ በንግድ ስራው ላይ የተሰጡ መያዣዎችን እና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን ጨምሮ የግል ዋስትናዎች እና ለዕዳ ማስያዣነት የዋሉ ንብረቶች፤

   መ) ባለዕዳው አንደኛው ተካራካሪ ወገን የሆነባቸው በሂደት ላይ ያሉ የሕግ ሥነ ሥርዓቶች፤

   ሠ) በጉምሩክ ሥር ያሉ እና በመጋዘን የተቀመጡ ዕቃዎች፤

   ረ) በኪራይ ቤቶች ውስጥ የሚገኙ ተንቀሳቃሽ ዕቃዎች፤

   ሰ) ታክሶች፣ ቀረጦች እና የማህበራዊ ዋስትና ክፍያዎች፡፡

2) የንብረት ዝርዝሩ በሁለት ቅጂዎች ተዘጋጅቶ አንደኛው ለፍርድ ቤቱ መዝገብ ቤት ሹም ገቢ የሚደረግ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ መልሶ የማደራጀት ኃላፊው ዘንድ ይቀመጣል፡፡

**<u>አንቀጽ 660</u>** **<u>ባለሞያዎችን ስለ መሾም</u>**

ፍርድ ቤቱ ባለዕዳውን እንዲያግዘው ወይም በባለዕዳው ፋንታ የንብረት ዝርዝሩን እንዲያዘጋጅ ገማች፣ የሂሳብ ሥራ ባለሞያ፣ የሰነዶች ምዝገባ ባለሞያ ወይም ሌላ ማንኛውንም ብቃት ያለው ባለሞያ ሊሾም ይችላል፡፡

<u>አንቀጽ 661</u> <u>ከሀብቱ ውጭ የሆኑ ዕቃዎች</u>

በዚህ ሕግ በአንቀጽ 751 እና በአንቀጽ 752 መሰረት መመለስ ያለባቸው ዕቃዎች የባለዕዳው ሀብት አካል ተደርገው አይቆጠሩም፡፡

<u>ክፍል ሁለት</u>

<u>የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎችን ስለ ማቅረብ እና ስለማጣራት</u>

<u>አንቀጽ 662</u> <u>የቅድመ ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎች የሚቀርቡበት ሥርዓት</u>

1) እያንዳንዱ ገንዘብ ጠያቂ መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት ፍርድ በተሰጠ በአራት (04) ወራት ውስጥ ራሱ ወይም በወኪሉ አማካኝነት በአደራ ደብዳቤ ወይም ተቀባዩ ለመቀበሉ ማረጋገጫ ሊሰጥበት በሚችል ሌላ ማንኛውም ኤሌክትሮኒክ መንገድ መልሶ ለማደራጀት ኃላፊው በመላክ የቅድመ ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎቹን ያቀርባል፡፡ ይህ የጊዜ ገደብ ልዩ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ በተቆጣጣሪ ዳኛው ሊራዘም ይችላል፡፡
2) ገንዘብ ጠያቂዎች በሚያቀርቡት ጥያቄ ውስጥ የሚከተሉትን በግልጽ ማስቀመጥ አለባቸው፡-

ሀ)ዋና ክፍያውን እና አግባብ ከሆነ ወለዱን እንዲሁም የመክፈያ ጊዜው የደረሰበትን ወይም የሚደርስበትን ቀን በመግለጽ የቅድመ ኪሳራ የክፍያ ጥያቄውን መጠን፤

ለ) የመጠባበቂያ የክፍያ ጥያቄዎችን በተመለከተ የክፍያ ጥያቄውን መጠን ግምት፤

ሐ) የቅድመ ኪሳራ ክፍያው የቀረበበትን የሕግ አግባብ፤

መ) የገንዘብ ጠያቂውን ስም፣ አድራሻ እና የባንክ ዝርዝር መረጃ፤

ሠ) አለኝ የሚሉትን ማንኛውንም ቅድሚያ የማግኘት መብት እና ቅድሚያ የማግኘት መብቱን የሕግ አግባብነት፤

ረ)ከቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄው ጋር በተያያዘ አለኝ የሚሉትን ማንኛውንም የንብረት ዋስትና ወይም ባለሀብትነታቸው እንደ ተጠበቀ ሆኖ የሚደረጉ የሽያጭ ውሎች እና አለኝ የሚሉት የንብረት ዋስትና የሚሸፍናቸውን ንብረቶች፣ ዋስትናው የተሰጠበትን ቀን እና ዋስትናው የተመዘገበ ከሆነ የምዝገባ ቦታውን እና የምዝገባ ቁጥሩን፤

ሰ)የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄን የሚመለከት ማንኛውንም የግል ዋስትና፣ የዋስትና ሰጪዎቹን ስም እና አድራሻ፣ የዋስትናውን መጠን፣ የተሰጠበትን ቀን እና ዋስትናው በተናጠል፣ በአንድነት ወይም በአንድነትና በተናጠል መሆኑን፤

ሸ) ማንኛውም ሊጠየቅ የሚችል ማቻቻል፤ የሚጠየቅ ከሆነ መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት የተከፈተበት ቀን ላይ በሁለቱም ወገኖች በኩል ያሉትን የክፍያ ጥያቄዎች መጠን፣ ክፍያዎቹ የመክፈያ ጊዜያቸው የደረሰበትን ቀን እና ከማቻቻል በኋላ የሚቀረውን የገንዘብ መጠን፤

3) ገንዘብ ጠያቂዎች የክፍያ ጥያቄያቸውን የሚደግፉ ሰነዶችን ማቅረብ አለባቸው፡፡ ለሚያቀርቧቸው ማስረጃዎችም ደረሰኝ ይሰጣቸዋል።

4) መልሶ የማደራጀት ኃላፊው መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓቱ ከተዘጋ በኋላ ማስረጃዎቹን ይመልሳል እንዲሁም ከአንድ ዓመት በኋላ ማስረጃዎቹን ለመመለስ ኃላፊ አይሆንም።

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄያቸውን እና የዋስትና መብታቸውን ያላቀረቡ ገንዘብ ጠያቂዎች በክፍፍሉ ውስጥ መሳተፍ አይችሉም፡፡ እንዲሁም በንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያለ ድርጅት በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ የተሸጠ እንደሆነ የክፍያ ጥያቄያቸው ለባለሀብቱ ሊቀርብ አይችልም።

**<u>አንቀጽ 663</u>** **<u>የቅመ-ኪሳራ ክፍያ ጥያቄዎችን ከማቅረብ ነጻ የተደረጉ ገንዘብ ጠያቂዎች</u>**

1) የሚከተሉት ገንዘብ ጠያቂዎች የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎችን ከማቅረብ ነጻ የተደረጉ ናቸው፡-

ሀ) ያልተከፈለ ደመወዝ ወይም ከሥራ ውል የሚመነጭ ሌላ ማንኛውንም ክፍያ የሚጠይቁ የባለዕዳው ሠራተኞች፤

ለ) የታክስ እና ቀረጥ ክፍያ የሚጠይቁ የመንግስት አካላት፤

ሐ) አጠቃላይ የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄያቸው ከአንድ ሺህ (1000) ብር በታች የሆነ ገንዘብ ጠያቂዎች።

2) መልሶ የማደራጀት ኃላፊው የባለዕዳውን የሒሳብ መግለጫዎች፣ የደመወዝ መክፈያ ቅጽ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሰነዶች በመገምገም እንዲህ ያሉትን የክፍያ ጥያቄዎች አረጋግጦ ይቀበላል። መልሶ የማደራጀት ኃላፊው በንዑስ አንቀጽ 1 ውስጥ የተመለከቱትን የክፍያ ጥያቄዎች ማረጋገጥ ያልቻለ እንደሆነ ገንዘብ ጠያቂዎች የክፍያ ጥያቄዎቻቸውን የሚደግፉ ማስረጃዎችን እንዲያቀርቡ ሊጠይቅ ይችላል።

**<u>አንቀጽ 664</u>** **<u>የቅድመ ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎች ማረጋገጫ እና መቀበያ ሥርዓት</u>**

1) መልሶ የማደራጀት ኃላፊው የቅድመ ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎችን እና የዋስትና መብቶችን ትክክለኛነት፣ መጠን እና በጊዜው መቅረባቸውን ያረጋግጣል፤

2) ባለዕዳው ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን እና መረጃዎችን በሙሉ መልሶ ለማደራጀት ኃላፊው ማቅረብ ይኖርበታል፤

3) የክፍያ ጥያቄ መኖሩ መልሶ በማደራጀት ኃላፊው የሚጣራ ከሆነ መልሶ የማደራጀት ኃላፊው በአደራ ደብዳቤ ወይም ተቀባዩ ለመቀበሉ ማረጋገጫ ሊሰጥበት በሚችል ሌላ ማንኛውም ኤሌክትሮኒክ መንገድ ለገንዘብ ጠያቂው ያሳውቃል፤ ገንዘብ ጠያቂውም ጥያቄው በደረሰው በስምንት ቀናት ውስጥ ለጥያቄው

መልስ መስጠት አለበት። መልሶ የማደራጀት ኃላፊው የክፍያ ጥያቄዎችን በሙሉ ወይም በከፊል ሊቀበል ይችላል።

4) መልሶ የማደራጀት ኃላፊው በግልጽ ያልተቀመጠ መጠን ያላቸው የክፍያ ጥያቄዎችን ወይም አፈጻጸማቸው ቅድመ ሁኔታ ያለው ዕዳዎችን በጊዜያዊነት ሊቀበል ይችላል።

5) የመጨረሻው የተረጋገጡ እና ተቀባይነት ያገኙ የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎች ዝርዝር መልሶ በማደራጀት ኃላፊው ይፈርምበታል።

6) የቅድመ ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎች እና ዋስትናዎች በጊዜ መቅረባቸውን በተመለከተ የተነሱ ቅሬታዎች በተመለከተ የማደራጀት ኃላፊው በሰጠው ውሳኔ ላይ ውሳኔው በተሰጠ በአሥር ቀናት ውስጥ በተቆጣጣሪ ዳኛው ይወሰናል።

7) የፍርድ ቤቱ መዝገብ ቤት ሹም ተቀባይነት ያገኙ የቅድመ ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎችን እና የዋስትና መብቶችን በሙሉ የያዘውን መጨረሻውን ዝርዝር የሚመለከታቸው አካላት በሙሉ ማግኘት እንዲችሉ ያደርጋል።

## አንቀጽ 665 ክርክር የተነሳባቸው የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎች ላይ የሚሰጥ ፍርድ

1) ተቆጣጣሪ ዳኛው ክርክር የተነሳባቸው የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎችን ጉዳዩ ከሚሰማበት ቀን አምስት ቀናት አስቀድሞ በአደራ ደብዳቤ ወይም ተቀባዩ ለመቀበሉ ማረጋገጫ ሊሰጥበት በሚችል ሌላ ማንኛውም ኤሌክትሮኒክ መንገድ ለሚመለከታቸው አካላት ማሳወቂያ ከተሰጠ በኋላ ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ሕጋዊ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ወይም የፍርድ ጉባዔ ያስተላልፋል።

2) ሕጋዊ ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ወይም የፍርድ ጉባዔ በክፍያ ጥያቄው ላይ ክርክር የተነሳበት ገንዘብ ጠያቂ ፍርድ ቤቱ ወይም ጉባዔው የሚወስነውን የገንዘብ መጠን በተመለከተ መልሶ በማደራጀት ሥነ ሥርዓቱ ላይ እንዲሳተፍ የሚፈቅድ ከፍርድ በፊት የሚሰጥ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

3) ሕጋዊ ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ወይም የፍርድ ጉባዔ የሰጠውን ትዕዛዝ ትዕዛዙ በተሰጠ በሦስት ቀናት ውስጥ በአደራ ደብዳቤ ወይም ተቀባዩ ለመቀበሉ ማረጋገጫ ሊሰጥበት በሚችል ሌላ ማንኛውም ኤሌክትሮኒክ መንገድ ለሚመለከታቸው አካላት ይሰጣል።

4) በትዕዛዙ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ወገን ትዕዛዙ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ በትዕዛዙ ላይ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል።

5) ክርክር የተነሳባቸው የክፍያ ጥያቄዎች መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓቱን መቋረጥ አያስከትሉም። ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ሕጋዊ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይተላለፋሉ። ለጊዜው ተቀባይነት ያገኙት የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎች ሕጋዊ ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ወይም የፍርድ ጉባዔ በሚሰጠው ፍርድ መሰረት ማስተካከያ ይደረግባቸዋል።

## አንቀጽ 666 ጊዜያዊ የክፍያ ጥያቄዎች ዝርዝር በፍርድ ቤቱ መዝገብ ቤት ሹም ዘንድ ስለ ማስቀመጥ

1) የቅድመ ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎች ተረጋግጠው ተቀባይነት ያገኙ ከሆነ መልሶ የማደራጀት ኃላፊው ተቀባይነት ያገኙትን እና ውድቅ የተደረጉትን የክፍያ ጥያቄዎች የሚያሳይ የተረጋገጡ እና ተቀባይነት ያገኙ የቅድመ ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎች ዝርዝር በፍርድ ቤቱ መዝገብ ቤት ሹም ዘንድ እንዲቀመጥ ያደርጋል። በተጨማሪም

በከሰረው ባለዕዳ ንብረቶች ላይ ልዩ ቅድሚያ ይገባኛል የሚሉ ገንዘብ ጠያቂዎችን ዝርዝር ለተቆጣጣሪ ዳኛው ይልካል።

2) መልሶ የማደራጀት ኃላፊው ማንኛውንም የክፍያ ጥያቄ በከፊል ወይም በሙሉ ውድቅ ያደረገ ከሆነ በዝርዝሩ ውስጥ ምክንያቱን በግልጽ ማስቀመጥ ይኖርበታል።

**<u>አንቀጽ 667</u>** **<u>ገቢ መደረጉን ማረጋገጫ ማሳወቂያ</u>**

1) መልሶ የማደራጀት ኃላፊው የተረጋገጡ እና ተቀባይነት ያገኙ የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎች ዝርዝሩን ወዲያውኑ በፍርድ ቤቱ መዝገብ ቤት ሹም ዘንድ እንዲቀመጥ ያደርጋል፡፡ ይህንኑ ዝርዝር በኢትዮጵያ ውስጥ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ላይ እንዲታተም ያደርጋል።
2) መልሶ የማደራጀት ኃላፊው የተረጋገጡ ውድቅ የተደረጉ የክፍያ ጥያቄዎችን በተመለከተ በአደራ ደብዳቤ ወይም ተቀባዩ ለመቀበሉ ማረጋገጫ ሊሰጥበት በሚችል ሌላ ማንኛውም ኤሌክትሮኒክ መንገድ ለሚመለከታቸው ገንዘብ ጠያቂዎች ወዲያውኑ ያሳውቃል።
3) ማንኛውም ገንዘብ ጠያቂ የተረጋገጡ እና ተቀባይነት ያገኙ የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎች ዝርዝሩን ሊቃወም ይችላል፤ ሆኖም ገንዘብ ጠያቂው የሚያስጠብቀው ጥቅም እንዳለው ማስረዳት አለበት። እንዲህ ያለው ተቃውሞ ማሳወቂያው ከደረሰበት ቀን አንስቶ ባሉት አሥር ቀናት ውስጥ ለተቆጣጣሪ ዳኛው መቅረብ አለበት።

**<u>አንቀጽ 668</u>** **<u>የንብረት ዋስትናቸው ወይም ቅድሚያ የማግኘት መብታቸው ላይ ክርክር የተነሳበት ገንዘብ ጠያቂዎች</u>**

1) ማንኛውም ገንዘብ ጠያቂ የንብረት ዋስትና ወይም ቅድሚያ የማግኘት መብት ያለው ከሆነ እና የንብረት ዋስትናው ወይም ቅድሚያ የማግኘት መብቱ ላይ ክርክር የተነሳ ከሆነ ገንዘብ ጠያቂው ዋስትና እንደሌለው ገንዘብ ጠያቂ በሥነ ሥርዓቱ ላይ ሊሳተፍ ይችላል።
2) በንብረት ዋስትና ወይም ቅድሚያ በማግኘት መብት ላይ የሚነሳ ማንኛውም ክርክር በፍርድ ቤቱ ውሳኔ ይሰጥበታል።

**<u>አንቀጽ 669</u>** **<u>በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎቻቸውን ስላላቀረቡ ገንዘብ ጠያቂዎች</u>**

1) በአንቀጽ 662 ውስጥ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎቻቸውን ሳያቀርቡ የቀሩ ገንዘብ ጠያቂዎች ጥያቄዎቻቸውን ያላቀረቡ ቢሆንም በሥነ ሥርዓቱ ውስጥ ይሳተፋሉ። ሆኖም ጥያቄዎቻቸውን ቢዘገይ ሥነ ሥርዓቱ እንዲከፈት የፍርድ ትዕዛዝ በተሰጠ በአንድ ዓመት ውስጥ ማቅረብ አለባቸው።
2) ይህ የአንድ ዓመት ጊዜ አይቋረጥም ወይም አይታገድም።

**<u>አንቀጽ 670</u>** **<u>በአንድነት እና በተናጠል ያለወሰን ዋስትና ያላቸው የክፍያ ጥያቄዎችን ስለ ማስገባት</u>**

የማንኛውም ገንዘብ ጠያቂ የክፍያ ጥያቄ በበርካታ ዋስትና ሰጪዎች በአንድነት እና በተናጠል የተረጋገጠ ወይም ዋስትና የተሰጠው ከሆነ እያንዳንዱ ገንዘብ ጠያቂ እና ዋስትና ሰጪ ማንኛውንም አቤቱታ ከግምት ውስጥ ሳያስገባ ለሙሉ የገንዘብ መጠኑ የቅድመ-ኪሳራ ክፍያ ጥያቄ ማስገባት ይችላል።

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>ከፍያዎች ከመቋረጣቸው አስቀድሞ የተፈጸሙ አጠራጣሪ ድርጊቶች እና ግብይቶች</u>

**<u>አንቀጽ 671</u>** **<u>የግድ ፈራሽ ስለመሆን</u>**

መልሶ የማደራጀት ኃላፊው ጥያቄ በሚያቀርብበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ የሚከተሉትን አጠራጣሪ በሆነው ጊዜ ውስጥ በባለዕዳው የተፈጸሙ ድርጊቶች ፈራሽ ሊያደርግ ይችላል፡-

1) በስጦታ በማስተላለፍ፣ በዕርዳታ፣ መብትን በመሰረዝ ወይም በመተው ለሌሎች ሰዎች የተላለፉ ንብረቶችን ወይም መብቶችን፤
2) ግልጽ በሆነ መልኩ ከሚገባው ባነሰ ዋጋ ለሌሎች ሰዎች የተላለፉ ንብረቶችን ወይም መብቶችን፤
3) በጥሬ ገንዘብ፣ በማስተላለፍ፣ በማቻቻልም ሆነ በሌላ መልኩ ጊዜያቸው ሳይደርስ የተከፈሉ ዕዳዎችን፤
4) ከጥሬ ገንዘብ፣ ወይም ከማቻቻል፣ ወይም ከሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች ወይም በባንክ ሂሳብ ከማዘዋወር ውጭ በሆነ መንገድ የተከፈሉ ጊዜያቸው የደረሰ ዕዳዎችን፤
5) የንብረት መብቶቹ ከመፈጠራቸው በፊት ለተፈረሙ የብድር ውሎች ተንቀሳቃሽ ያልሆነ ንብረት ማስያዣ፣ የተንቀሳቃሽ ንብረት ማስያዣ ወይም ሌሎች የንብረት የማስያዣ መብቶችን በባለዕዳው ንብረቶች ላይ የሚፈጥሩ።

**<u>አንቀጽ 672</u>** **<u>በምርጫ ስለ መሰረዝ</u>**

1) መልሶ የማደራጀት ኃላፊው ጥያቄ በሚያቀርብበት ጊዜ፡-

    ሀ) ባለዕዳው አስቀድሞ ክፍያዎችን ያቋረጠበት ሁኔታ ውስጥ እንደነበረ ገንዘብ ጠያቂው የሚያውቅ ወይም ማወቅ የነበረበት ከሆነ፤ እና

    ለ) ድርጊቱ የባለዕዳውን ንብረት የሚጎዳ ከነበረ ወይም ክፍያው የተፈጸመው ከሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች ቅድሚያ በመስጠት ከነበረ፤

ፍርድ ቤቱ አጠራጣሪ በሆነው ጊዜ ውስጥ በባለዕዳው የተከናወኑ ማናቸውንም ድርጊቶች ፈራሽ ሊያደርግ ይችላል።

2) ድርጊቱ የተፈጸመው ዝምድና ካለው ወገን ጋር ካልሆነ በስተቀር በንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ) ውስጥ በተመለከተው መሰረት ገንዘብ ጠያቂው ያውቅ እንደነበር የማስረዳት ኃላፊነት ያለበት መልሶ የማደራጀት ኃላፊው ነው።

**<u>አንቀጽ 673</u>** **<u>ፈራሽ የማድረግ ክርክር ስለማቅረብ</u>**

1) ፈራሽ የማድረግ ሥነ ሥርዓቱ ለህብቱ ጥቅም ያለው ከሆነ ወይም ድርጊቱ ለገንዘብ ጠያቂዎቹ ምክንያታዊ ያልሆነ ቅድሚያ የማግኘት መብት የሚሰጥ ከሆነ መልሶ የማደራጀት ኃላፊው ድርጊቱ ወይም ግብይቱ ፈራሽ እንዲደረግ ጥያቄውን ለፍርድ ቤት ማቅረብ ይኖርበታል።

2) መልሶ የማደራጀት ኃላፊው ጉዳዩን ለፍርድ ቤት ላለማቅረብ የወሰነ እንደሆነ፡-

ሀ) ማንኛውም ተቆጣጣሪ ወይም ገንዘብ ጠያቂ መልሶ ለማደራጀት ኃላፊው ክስ እንዲያቀርብ መጥሪያ ሰጥቶ ምንም ምላሽ ያላገኘ ወይም አሉታዊ ምላሽ ያገኘ እንደሆነ መጥሪያው በደረሰ በአንድ ወር ውስጥ በራሱ ክስ ሊመሰርት ይችላል፤

ለ) ተቆጣጣሪው ወይም ገንዘብ ጠያቂው ክሱን ያሸነፈ እንደሆነ በክሱ የተነሳ ያወጣቸው ወጪዎች በባለዕዳው ሰው ንብረት ይሸፈናሉ።

**<u>አንቀጽ 674 ከፈራሽነት ውጭ የተደረጉ ድርጊቶች እና ክፍያዎች</u>**

ማጭበርበር ካልኖረ በስተቀር አጠራጣሪ በሆነው ጊዜ ውስጥ በባለዕዳው የተፈጸሙ የሚከተሉት ድርጊቶች እና ክፍያዎች ውድቅ ሊደረጉ አይችሉም፡-

1) መልሶ በማደራጀት ዕቅዱ መሰረት በባለዕዳው የተፈጸመ እና በፍርድ ቤቱ የጸደቀ አዲስ የቀረበ ገንዘብ፣ የተፈጠሩ የዋስትና መብቶች፣ የተሸጡ ንብረቶች፣ የተከፈሉ ዕዳዎች እንዲሁም ሌሎች ማናቸውም ሕጋዊ ድርጊቶች እና ክፍያዎች፤
2) ተንቀሳቃሽ ያልሆነ ንብረት ማስያዣን፣ የተንቀሳቃሽ ንብረት ማስያዣን እና ሌሎች የንብረት የማስያዣ መብቶችን መሸጥ።
3) መደበኛ የንግድ ሥራውን ለማካሄድ አስፈላጊ የሆኑ ንብረቶች ግዢ፤
4) ለዕቃዎቹ እና ለአገልግሎቶቹ አግባብ የሆነ ዋጋ በመክፈል በቅን ልቦና በሦስተኛ ወገኖች የተገዙ ዕቃዎች እና ለሦስተኛ ወገኖች የተሰጡ አገልግሎቶች።

**<u>አንቀጽ 675 ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት ፍርድ ከመሰጠቱ አስቀድሞ የተመዘገቡ መብቶች</u>**

በትክክለኛው መንገድ ከተደረጉ የንብረት ዋስትናዎች የሚመነጩ መብቶች ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት ፍርድ እስከተሰጠበት ቀን ድረስ ሊመዘገቡ ይችላሉ።

**<u>አንቀጽ 676 ይርጋ</u>**

1) በዚህ ክፍል መሰረት ግብይት ወይም ድርጊት ፈራሽ እንዲሆን የሚቀርብ ክርክር መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት ፍርድ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ ከሁለት ዓመታት በኋላ በይርጋ ይታገዳል።

2) ፈራሽ የሚሆኑትን ድርጊቶች እና ግብይቶች ባለዕዳው መልሶ ለማደራጀት ኃላፊው ያላሳወቀ ከሆነ ከላይ የተመለከተው የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው መልሶ የማደራጀት ኃላፊው ድርጊቱ መፈጸሙን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ ይሆናል።

**<u>አንቀጽ 677 ፈራሽ መሆን የሚያስከትላቸው ውጤቶች</u>**

1) ማንኛውም ክፍያ ወይም ማንኛውም ድርጊት ፈራሽ እንዲሆን የሚሰጠው ውሳኔ ወደ ኋላ ተመልሶ ተፈጻሚ ይሆናል።

2) በዓይነት ወደነበረበት መመለስ የሚቻል በማይሆንበት ጊዜ የንብረቱ የገበያ ዋጋ ወደ ሀብቱ ይመለሳል።

3) ፈራሽ መሆኑ የሚመለከተው ንብረት ወይም ሙብት ለሦስተኛ ወገን የተላለፈ በሚሆንበት ጊዜ ከንብረቱ ወይም ከሙብቱ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ጥሬ ገንዘብ ፍርዱ በተሰጠበት ጊዜ ባለው የገበያ ዋጋ መሰረት ተሰልቶ ወደ ሀብቱ ይመለሳል።

4) ፈራሽ መሆኑ ተጽዕኖ የሚያደርግባቸው ገንዘብ ጠያቂዎች ፈራሽ ከመሆኑ የሚመነጩ የቅድሙ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎቻቸውን ማቅረብ ይችላሉ። ሆኖም በዚህ ሕግ በአንቀጽ 669 መሰረት የክፍያ ጥያቄዎቹን ማስገባት ከሚቻልበት ጊዜ ማለፍ የለበትም።

## <u>ምዕራፍ አራት</u>

## <u>መልሶ የማደራጀት ዕቅድ</u>

### <u>አንቀጽ 678</u> <u>መልሶ የማደራጀት ዕቅድ ስለ ማዘጋጀት</u>

1) መልሶ የማደራጀት ዕቅዱ መልሶ በማደራጀት ኃላፊው እገዛ በባለዕዳው ይዘጋጃል።

2) ገንዘብ ጠያቂዎች መልሶ የማደራጀት ዕቅዱ እንዲሻሻል ጥያቄ ማቅረብ እና የአጸፋ ሀሳቦችን ማቅረብ ይችላሉ።

3) አስገዳጅ ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው መልሶ የማደራጀት ዕቅዱ የሚከተሉትን ነገሮች ሊያካትት ይችላል፡-

ሀ) የሚመለከታቸውን ገንዘብ ጠያቂዎች የክፍያ ጥያቄዎች የጊዜ ሰንጠረዥን መልሶ ማዘጋጀት፤

ለ) የሚመለከታቸው ገንዘብ ጠያቂዎች የክፍያ ጥያቄዎች መተውን፤

ሐ)የፋይናንስ ዕዳ ሰነዶችን አወጣጥ የሚቆጣጠሩ ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው የፋይናንስ ዕዳ ሰነዶችን በማውጣት ዕዳዎችን መክፈልን፤

መ) የሚመለከታቸው ገንዘብ ጠያቂዎችን የክፍያ ጥያቄዎችን ወደ አክሲዮን መቀየርን፤

ሠ) የባለዕዳውን ካፒታል በገንዘብ ጠያቂዎች ወይም በሦስተኛ ወገን ኢንቨስተሮች እንዲገዛ መቀነስን ወይም ማሳደግን ወይም ገንዘብ ጠያቂዎችን ወይም ሦስተኛ ወገን ኢንቨስተሮችን በሚጠቅም መልኩ የአክሲዮን ድርሻ መሸጥን፤

ረ) የንግድ ሥራ እንቅስቃሴው በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ የንግድ ሥራ መሸጥን ሳይጨምር ንብረቶችን ወይም የንግድ ሥራውን ክፍሎች መሸጥን፤

4) መልሶ የማደራጀት ዕቅዱ የገንዘብ ጠያቂዎች ምድቦችን ለመከፋፈል ጥቅም ላይ የዋለውን መስፈርት መግለጽ ይኖርበታል።

5) መልሶ የማደራጀት ዕቅዱ ሁልጊዜም "የገንዘብ ጠያቂዎችን የተሻለ ጥቅም ማስጠበቅ" የሚለውን መስፈርት ማሟላት አለበት፤ ይህም ማለት ማንኛውም ተቃውሞ ያለው ገንዘብ ጠያቂ መልሶ በማደራጀት ዕቅዱ መሰረት የሚያገኘው ጥቅም በዚህ ሕግ አንቀጽ 786 መሰረት በመክሠር ሥነ ሥርዓት ወቅት ተግባራዊ የሚደረገው ቅደም ተከተል ተግባራዊ ቢደረግ ከሚያገኘው ጥቅም ጋር ሲነጻጸር ያነሰ መሆን የለበትም።

**አንቀጽ 679 አዲስ የቀረበ ገንዘብ**

1) መልሶ የማደራጀት ዕቅድን ተግባራዊ ለማድረግ አዲስ ገንዘብ በነባር ወይም በአዲስ ገንዘብ ጠያቂዎች ሊቀርብ ይችላል።
2) መልሶ በማደራጀት ዕቅዱ ውስጥ የተካተተ እና በፍርድ ቤቱ የጸደቀ አዲስ ገንዘብ ኋላ ላይ የመክሠር ሥነ ሥርዓት የተከፈተ እንደሆነ ዋስትና ከሌላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች ቅድሚያ ይኖረዋል፤ ነገር ግን በቅድመ ጥንቃቄ መልሶ ማዋቀር ሥነ ሥርዓት ማዕቀፍ ውስጥ ከቀረበ አዲስ ገንዘብ ያነሰ ቦታ ይኖረዋል። ፍርድ ቤቱ ለዕዳ ማስያዣነት ያልዋለ የባለዕዳው ንብረት አዲስ ለቀረበ ገንዘብ ዋስትና እንዲሆን ሊፈቅድ ይችላል፤ እንደዚያ በሚሆንበት ጊዜ የአዲስ ገንዘብ አቅራቢዎች የሚያገኙት ቅድሚያ ዋስትና ያላቸው ገንዘብ ጠያቂዎችን በሚመለከቱ ደንቦች መሰረት ይስተናገዳሉ።

## ምዕራፍ አምስት
## መልሶ የማደራጀት ዕቅዱን ማጽደቅ

**አንቀጽ 680 የገንዘብ ጠያቂዎች መደቦች**

1) መልሶ የማደራጀት ኃላፊው መልሶ የማደራጀት ዕቅዱ በተቀላጠፈ መልኩ እንዲጸድቅ ለማመቻቸት የሚመለከታቸው ገንዘብ ጠያቂዎችን በተለያዩ መደቦች ይከፋፍላል።
2) የገንዘብ ጠያቂዎች መደቦቹ በተጨባጭ መረጋገጥ በሚችሉ መስፈርቶች መሰረት የጥቅም መመሳሰልን የሚያንጸባርቁ መሆን አለባቸው። ቢያንስ ቢያንስ ዋስትና ያለው እና ዋስትና የሌለው የክፍያ ጥያቄ ያላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች በተለያዩ መደቦች ውስጥ ተከፋፍለው መስተናገድ አለባቸው።
3) በባለዕዳው ንብረቶች ላይ የንብረት የዋስትና መብት ያላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች በዋስትናነት የተያዘው ንብረት ሲጣራ የሚኖረው ዋጋ ለማይሸፍነው የክፍያ ጥያቄያቸው መጠን ዋስትና በሌላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች መደብ ውስጥ ይሳተፋሉ።
4) የግል ዋስትናዎች እና የመድን ዋስትናዎች ያሏቸው ገንዘብ ጠያቂዎች ራሱን የቻለ መደብ ሊፈጥሩ ይችላሉ።
5) መልሶ የማደራጀት ዕቅዱ በሰራተኞች የክፍያ ጥያቄዎች ላይ ተጽዕኖ የሚያደርግ ከሆነ የባለዕዳው ሠራተኞች የራሳቸው የሆነ የተለየ መደብ ይኖራቸዋል።
6) ባለአክሲዮኖች ገንዘብ ጠያቂዎች ባይሆኑም የራሳቸው የሆነ የተለየ መደብ ይኖራቸዋል።
7) የመደቦቹ አከፋፈል እና ለመከፋፈል ጥቅም ላይ የዋሉት መስፈርቶች ለፍርድ ቤቱ መዝገብ ቤት ሹም ገቢ ይደረጋል።
8) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ውስጥ የተመለከተው ቢኖርም ባለዕዳው አነስተኛ ወይም መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ ከሆነ ባለዕዳው ወይም መልሶ የማደራጀት ኃላፊው በሚያቀርቡት ጥያቄ መሰረት ተቆጣጣሪ

ዳኛው የሚመለከታቸው ገንዘብ ጠያቂዎችን እና ባለአክሲዮኖችን በተለያዩ መደቦች ከፋፍሎ ላለማስተናገድ ሊወስን ይችላል። ለዚህ ድንጋጌ ዓላማ የግለሰብ ነጋዴ ወይም የንግድ ማኅበር እንደ አነስተኛ ወይም መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ ሆኖ የሚቆጠረው፡-

ሀ) ከአሥር ያነሱ ሰራተኞች ካሉት፤ ወይም

ለ) ባለፉት አሥራ ሁለት ወራት ውስጥ የነበረው የሽያጭ ገቢ ከአምስት ሚሊዮን (5,000,000) ብር በታች ከሆነ (የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ እንደተጠበቀ ሆኖ)፤ ወይም

ሐ) ያለፉትን አሥራ ሁለት ወራት በሚመለከተው የመጨረሻው የሒሳብ መግለጫ መሰረት አጠቃላይ የሀብት መጠኑ ከሃያ ሚሊዮን (20,000,000) ብር በታች ከሆነ ነው።

9) የገንዘብ ጠያቂዎች መደቦችን ከመመደብ ጋር በተያያዘ የሚነሳ ቅሬታ የገንዘብ ጠያቂዎች መደቦቹ አመዳደብ ለፍርድ ቤቱ መዝገብ ቤት ሹም ገቢ ከተደረገበት ጊዜ አንስቶ በአሥር ቀናት ውስጥ በተቆጣጣሪ ዳኛው ይወሰናል፤ በተቆጣጣሪ ዳኛው የተሰጠው ውሳኔ ውሳኔው በተሰጠ በአሥር ቀናት ውስጥ ይግባኝ ሊቀርብበት ይችላል።

**<u>አንቀጽ 681 በገንዘብ ጠያቂዎች ምድቦች ስብሰባዎች እና በገንዘብ ጠያቂዎች ጠቅላላ ጉባዔዎች ላይ የሚኖር የመምረጥ መብትን ስለ መወሰን</u>**

1) በገንዘብ ጠያቂዎች መደቦች ስብሰባዎች እና በገንዘብ ጠያቂዎች ጠቅላላ ጉባዔዎች ላይ ገንዘብ ጠያቂዎች የሚኖሯቸው የመምረጥ መብቶች መልሶ በማደራጀት ኃላፊው ይወሰናሉ እንዲሁም በባለዕዳው የመጨረሻው የተረጋገጠ ሂሳብ ወይም የሂሳብ መግለጫ መሰረት ወለድን ሳይጨምር ካላቸው ዋና የቅድመ-ክፍያ ጥያቄ ጋር የሚመጣጠን ይሆናል።
2) የመምረጥ መብቶቹ የገንዘብ ጠያቂዎች ስብሰባው ከመደረጉ ሦስት ቀናት አስቀድሞ ይወሰናሉ እንዲሁም ሥነ ሥርዓት ከተከፈተ በኋላ የተላለፉ መብቶችን ወይም መልሰው የተከፈሉ የቅድመ-ክፍያ የክፍያ ጥያቄዎችን ከግምት ያስገባሉ። የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎችን መጠን በመወሰን ረገድ መልሶ የማደራጀት ኃላፊው በገለልተኛ ኦዲተሮች እገዛ ሊደረግለት ይችላል።
3) ከገንዘብ ጠያቂዎች መደቦች እና ከየገንዘብ ጠያቂዎች ጠቅላላ ጉባዔዎች ከሦስት ቀን ያነሰ ጊዜ አስቀድሞ የሚደረግ ማንኛውም የቅድመ-ኪሳራ ክፍያዎችን መስጠት እና ማስተላለፍ በሥነ ሥርዓቶቹ ላይ ተፈጻሚ መሆን አይችልም።
4) ድምጽ የመስጠት መብትን መወሰንን በተመለከተ የሚፈጠር ማንኛውም ቅሬታ በተቆጣጣሪ ዳኛው ይወሰናል እንዲሁም ይግባኝ ሊቀርብበት አይችልም።
5) የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎችን በተመለከተ መልሶ የማደራጀት ኃላፊው በዚህ ሕግ አንቀጽ 665 ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት ለጊዜው መቀበልን እንደ አማራጭ ይወስዳል ነገር ግን ተቆጣጣሪ ዳኛው ወይም ሕጋዊ ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ወይም የፍርድ ጉባዔ የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚሰጥ አይጠብቅም።

6) በገንዘብ ጠያቂዎች መደቦች ስብሰባዎች እና በገንዘብ ጠያቂዎች ጠቅላላ ጉባዔዎች ላይ ገንዘብ ጠያቂዎች ያሏቸውን የመምረጥ መብቶች በተመለከተ የሚሰጥ ማንኛውም ውሳኔ ተቆጣጣሪ ዳኛው ወይም ሕጋዊ ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ወይም የፍርድ ጉባዔ የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎችን በመቀበላቸው ላይ ምንም ዓይነት ውጤት አይኖረውም።

**<u>አንቀጽ 682</u>** **<u>የገንዘብ ጠያቂዎች መደቦች ስብሰባዎች</u>**

1) መልሶ የማደራጀት ኃላፊው የመጠባበቂያ ጊዜው ከማብቃቱ በፊት አንድ ወይም በርካታ የገንዘብ ጠያቂዎች መደቦች ስብሰባዎችን ይጠራል።
2) መልሶ የማደራጀት ኃላፊው ከስብሰባው ቀን አሥራ አምስት ቀናት አስቀድሞ በአደራ ደብዳቤ ወይም ተቀባዩ ለመቀበሉ ማረጋገጫ ሊሰጥበት በሚችል ሌላ ማንኛውም ኤሌክትሮኒክ መንገድ ለገንዘብ ጠያቂዎች ያሳውቃል።
3) መልሶ የማደራጀት ኃላፊው በባለዕዳው የተዘጋጀውን መልሶ የማደራጀት ዕቅድ፣ በገንዘብ ጠያቂዎች የቀረቡ ማሻሻያዎችን ወይም የአጸፋ ሀሳቦችን እንዲሁም የንግድ ሥራ እንቅስቃሴው በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ የንግድ ሥራ ለመሸጥ የቀረቡ ሀሳቦችን ለገንዘብ ጠያቂዎች መደቦች ስብሰባዎች ያቀርባል።
4) ባለዕዳው በሁሉም የገንዘብ ጠያቂዎች መደቦች ስብሰባዎች ላይ በአካል ይገኛል እንዲሁም ገንዘብ ጠያቂዎች ያሏቸውን ማናቸውንም ጥያቄዎች ይመልሳል። ገንዘብ ጠያቂው በሕጋዊ ወኪል ሊወከል ይችላል።
5) እንዲህ ባሉት ስብሰባዎች ላይ የተደረጉት ውይይቶች፣ የተሳታፊዎቹ ስም እና የድምጽ አሰጣጥ ውጤቶች በቃለ ጉባዔ ይመዘገባሉ እንዲሁም አግባብነት ያላቸው ሰነዶች በሙሉ ከቃለ ጉባዔው ጋር ይያያዛሉ።

**<u>አንቀጽ 683</u>** **<u>መልሶ በማደራጀት ዕቅዱ ላይ ድምጽ ስለ መስጠት</u>**

1) መልሶ የማደራጀት ኃላፊው በባለዕዳው ተዘጋጅቶ በገንዘብ ጠያቂዎች የተሻሻለውን መልሶ የማደራጀት ዕቅድ እንዲሁም አግባብነት ያለው በገንዘብ ጠያቂዎች የተዘጋጀ ማንኛውንም የአጸፋ ሀሳብ አደራጅቶ እያንዳንዱ የገንዘብ ጠያቂዎች መደብ ድምጽ እንዲሰጥበት ያቀርባል።
2) በእያንዳንዱ የገንዘብ ጠያቂዎች መደብ ውስጥ ካለው አጠቃላይ የክፍያ ጥያቄ ውስጥ ሁለት ሦስተኛው ያላቸው አንድ ወይም ከዚያ በላይ ገንዘብ ጠያቂዎች መልሶ የማደራጀት ዕቅዱ እንዲጸድቅ በጽሁፍ በሚደረግ ስምምነት አማካኝነት ጭምር ድምጽ ሲሰጡ መልሶ የማደራጀት ዕቅዱ ተቀባይነት ያገኛል። ማሳወቂያ ተሰጥቷቸው በስብሰባው ላይ በአካልም ሆነ በሕጋዊ ወኪላቸው አማካኝነት ያልተገኙ ገንዘብ ጠያቂዎች ድምጽ በመስጠት ረገድ ከግምት ውስጥ አይካተቱም።
3) በእያንዳንዱ የገንዘብ ጠያቂዎች መደብ ስብሰባ ላይ ሁለት ሦስተኛ አብላጫ ድምጽ ያላገኘ እንደ ሆነ፤ መልሶ የማደራጀት ዕቅዱ በባለዕዳው እና በአብዛኛዎቹ የሚመለከታቸው ገንዘብ ጠያቂዎች መደቦች ከጸደቀ ተቀባይነት ያገኛል።
4) በዚህ አንቀጽ በንኡስ አንቀጽ (3) የተመለከተው አብላጫ ድምጽ ያልተገኘ እንደሆነ ከአክሲዮን ባለቤቶች መደብ ወይም ንብረት በሚጣራበት ሁኔታ ውስጥ የባለዕዳው ሀብት በሚገመትበት ጊዜ ምንም ክፍያ ከማያገኝ ወይም ምንም ጥቅም ከማይኖረው ሌላ ማንኛውም መደብ ውጭ የሆነ ቢያንስ አንድ የገንዘብ ጠያቂዎች መደብ ዕቅዱን በመደገፍ ድምጽ ከሰጠ ዕቅዱ እንደጸደቀ ይቆጠራል፡፡

5) በስብሰባው ላይ ባይገኙም እንኳን ለገንዘብ ጠያቂዎች ተጨማሪ ማሳወቂያ ሳይሰጥ የገንዘብ ጠያቂዎች መደቦች ስብሰባዎች ወደ ቀጣዩ የሥራ ቀን ሊተላለፉ ይችላሉ።

**<u>አንቀጽ 684 መልሶ በማደራጀት ዕቅዱ በየገንዘብ ጠያቂዎች ጠቅላላ ጉባዔ ስለ መጽደቁ</u>**

1) ማንኛውንም አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ በተመለከተ የገንዘብ ጠያቂዎች መደቦች ያልተመደቡ ከሆነ መልሶ የማደራጀት ኃላፊው መልሶ በማደራጀት ዕቅዱ ላይ ድምጽ ለመስጠት የገንዘብ ጠያቂዎች ጠቅላላ ጉባዔ ሊጠራ ይችላል። የየገንዘብ ጠያቂዎች ጠቅላላ ጉባዔውን ቢያንስ ሁለት ሦስተኛ የክፍያ ጥያቄዎች ያላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች መልሶ የማደራጀት ዕቅዱን ደግፈው ድምጽ ከሰጡ ዕቅዱ ተቀባይነት ያገኛል።
2) የገንዘብ ጠያቂዎች መደቦች ስብሰባዎችን በተመለከተ በአንቀጽ 682 ውስጥ የተቀመጠው ደንብ አስፈላጊው ለውጥ ተደርጎበት ተፈጻሚ ይሆናል።

**<u>አንቀጽ 685 መልሶ የማደራጀት ዕቅዱ በፍርድ ቤት ስለ መጽደቁ</u>**

1) መልሶ የማደራጀት ኃላፊው ተቀባይነት ያገኘውን መልሶ የማደራጀት ዕቅድ የራሱን አስተያየቶች እና ምክረ ሀሳቦች ከያዘ ሪፖርት ጋር አንድ ላይ ለፍርድ ቤቱ ያቀርባል። ይህ ሪፖርት ጉዳዩ በፍርድ ቤቱ ከመሰማቱ ቢያንስ ሦስት ቀናት አስቀድሞ ለፍርድ ቤቱ ይቀርባል እንዲሁም የሥነ ሥርዓቱ አካል የሆኑ ወገኖች በሙሉ በቀላሉ እንዲያገኙት ይደረጋል።
2) ጉዳዩ በሚሰማበት ወቅት መልሶ የማደራጀት ኃላፊው፣ ባለዕዳው እና ገንዘብ ጠያቂዎች ይሰማሉ።
3) መልሶ የማደራጀት ዕቅዱን በሚያጸድቅበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ የሚከተሉትን ነገሮች ያረጋግጣል፡-

ሀ) መልሶ የማደራጀት ዕቅዱ አስፈላጊ በሆነው አብላጫ ድምጽ መጽደቁን እና የባለዕዳውን መክሠር የመከላከል እና የንግድ ሥራውን አዋጭነት የማረጋገጥ ምክንያታዊ ተስፋ ያለው መሆኑን፤

ለ) መልሶ የማደራጀት ዕቅዱ “የገንዘብ ጠያቂዎች የተሻለ ጥቅም” የሚለውን

መስፈርት የሚያሟላ መሆኑን፤

ሐ) ማንኛውም ገንዘብ ጠያቂ መልሶ በማደራጀት ዕቅዱ መሰረት የሚያገኘው ጥቅም በመክሠር ሥነ ሥርዓት ውስጥ ከሚያገኘው ያነሰ ያለመሆኑን፤

መ) የሦስተኛ ወገኖች ጥቅሞች በተለይም ደግሞ አዲስ የዋስትና መብቶችን ከማግኘት እና ከአዲስ የገንዘብ አቅርቦት ማዕቀፍ አንጻር በበቂ ሁኔታ መጠበቁን፤

ሠ) በአንቀጽ 683 ንዑስ አንቀጽ (3) መሰረት የተለያዩ መደቦች ተደምረው የሚገኘው ውጤት በሚወሰድበት ጊዜ ከእነሱ በታች ደረጃ ያለው ማንኛውም መደብ ማንኛውም ክፍያ የሚያገኝ ወይም ማንኛውም ጥቅም የሚኖረው እንደሆነ በመቃወም ድምጻቸውን የሰጡ የሚመለከታቸው ገንዘብ ጠያቂዎች በተመሳሳይ ወይም በእኩል መልኩ ሙሉ ክፍያ ማግኘታቸውን፤

ረ) ተመሳሳይ ደረጃ ያላቸው የገንዘብ ጠያቂዎች መደቦች ተመሳሳይ ወይም እኩል በሆነ መልኩ የክፍያ ጥያቄያቸው እንደሚከፈላቸው፤

ሰ) መልሶ የማደራጀት ዕቅዱን ዓላማዎች ለማሳካት አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ እና መልሶ የማደራጀት ዕቅዱ የማናቸውንም የሚመለከታቸው ወገኖች መብቶች እና ጥቅሞች አግባብ ባልሆነ መልኩ የማይጎዳ በሚሆንበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ በራሱ ተነሳሽነት ከላይ (ሠ) እና/ወይም (ረ) ውስጥ ከተመለከቱት መርሆች ውጭ የሆነ አካሄድ ሊከተል ይችላል፤

ሸ) መልሶ በማደራጀት ዕቅዱ መሰረት ማንኛውም የሚመለከታቸው ገንዘብ ጠያቂዎች መደብ ከሚጠይቀው ሙሉ ክፍያ በላይ ሊቀበል ወይም ይዞ ሊቆይ አይችልም።

4) ዋስ የሆኑ የተፈጥሮ ሰዎች መልሶ የማደራጀት ዕቅዱን ድንጋጌዎች በማጣቀስ ጥቅማቸውን ማስጠበቅ ይችላሉ።

5) መልሶ የማደራጀት ዕቅዱን በማረጋገጥ ወይም ውድቅ በማድረግ የተሰጠው ፍርድ በሁሉም ሰው ላይ አስገዳጅ ይሆናል እንዲሁም በኢትዮጵያ ውስጥ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ላይ ይታተማል።

**<u>አንቀጽ 686</u>** **<u>ስለ መልሶ የማደራጀት ዕቅዱ መሻሻል</u>**

1) መልሶ የማደራጀት ዕቅዱ በፍርድ ቤቱ ከጸደቀ በኋላ ዕቅዱ ሊሻሻል የሚችለው ባለዕዳው ሲስማማ እና ገንዘብ ጠያቂዎች ሙሉ ድምጻቸውን ሲሰጡ ብቻ ነው።

2) እንዲህ ያለው ማሻሻያ በፍርድ ቤቱ መጽደቅ ሳያስፈልገው በባለጉዳዮቹ መካከል ሕጋዊ እና አስገዳጅ ይሆናል።

**<u>አንቀጽ 687</u>** **<u>መልሶ የማደራጀት ዕቅዱ አፈጻጸም</u>**

1) ባለዕዳው በመልሶ ማደራጀት ዕቅዱ ውስጥ በተቀመጡት ሁኔታዎች መሰረት ዕቅዱን ይፈጽማል። በዕቅዱ መሰረት ጊዜው ያልደረሰ እና መከፈል የሌለበት ማንኛውንም ገንዘብ አይከፍልም።

2) ገንዘብ ጠያቂዎች በዕቅዱ መሰረት ጊዜው ያልደረሰ እና መከፈል የሌለበት ማንኛውንም ገንዘብ መጠየቅም ሆነ መቀበል አይችሉም።

3) መልሶ የማደራጀት ኃላፊው መልሶ የማደራጀት ዕቅዱ በፍርዱ ውስጥ በተቀመጠው ሥርዓት መሰረት መፈጸሙን ይቆጣጠራል።

4) መልሶ የማደራጀት ኃላፊው የገንዘብ ጠያቂዎችን ጥቅም የሚጎዳ ማንኛውም ጉዳይ ወይም ድርጊት በሚኖርበት ጊዜ ለፍርድ ቤቱ ወዲያውኑ ያሳውቃል።

5) መልሶ የማደራጀት ኃላፊው በአገልግሎት ዘመኑ ወቅት ያወጣቸውን እና መልሰው ሊከፈሉት የሚገቡትን ወጪዎች እና ክፍያዎች ፍርድ ቤቱ ይወስናል።

**<u>አንቀጽ 688</u>** **<u>መልሶ የማደራጀት ዕቅዱ ስለሚቋረጥበት ሁኔታ</u>**

ባለዕዳው መልሶ በማደራጀት ዕቅዱ ውስጥ የተቀመጡትን ደንቦች ተግባራዊ ሳያደርግ በሚቀርበት ጊዜ ማንኛውም ገንዘብ ጠያቂ፣ ተቆጣጣሪ ወይም ዐቃቤ ሕግ መልሶ የማደራጀት ዕቅዱን ለማቋረጥ እና የመክሠር ሥነ ሥርዓት ለመክፈት ለፍርድ ቤቱ አቤቱታ ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡

## ምዕራፍ ስድስት

## በንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያለን ድርጅት በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ መሸጥ

### አንቀጽ 689 የንግድ ሥራ እንቅስቃሴውን ሦስተኛ ወገን እንዲረከበው ስለሚቀርብ ዕቅድ

1) በንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያለ ድርጅት በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ መሸጥ ለቅድመ ጥንቃቄ መልሶ በማዋቀር ሥነ ሥርዓት ማዕቀፍ ውስጥ መልሶ በማዋቀር ዘርፍ ባለሞያው ወይም መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት ከተከፈተ በኋላ መልሶ በማደራጀት ኃላፊው ሊዘጋጅ ይችላል፡፡
2) ባለዕዳው፣ ዳይሬክተሮቹ እና ባለአክሲዮኖቹ በንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ስራ ላይ ያለ ድርጅት በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ ለመግዛት የመጫረት መብት አላቸው፤ ሆኖም የተቆጣጣሪ ዳኛውን ፍቃድ ማግኘት አለባቸው፡፡
3) መልሶ የማዋቀር ባለሞያው እና መልሶ የማደራጀት ኃላፊው ገንዘብ ጠያቂዎችን ተጠቃሚ በሚያደርግ መልኩ የንግድ ሥራውን ዋጋ ከፍ ማድረግ የሚለውን ዓላማ በመያዝ የሽያጩን ሂደት አግባብ ነው ብለው በሚያምኑት መልኩ ያደራጃሉ፡፡ እንደአስፈላጊነቱ የባለሞያዎችን፣ የአማካሪዎችን ወይም የኢንቨስትመንት ባንኮችን እገዛ ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡
4) መልሶ የማደራጀት ኃላፊው በንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያለ ድርጅት በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ ለመሸጥ ጨረታ ሊያዘጋጅ ወይም በምስጢር እንዲሸጥ ሊያመቻች የሚችለው መልሶ የማደራጀት ዕቅዱ ውድቅ እንደተደረገ ወይም ውድቅ የመደረግ ዕድሉ ሰፊ እንደሆነ ግልጽ ሲሆን ብቻ ነው፡፡
5) የንግድ ሥራው በምስጢር የሚሸጥ ከሆነ የንግድ ሥራው በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ የሚሸጥበትን ዋጋ ከፍ ለማድረግ ሲባል የሚቀርቡት ዋጋዎች በምስጢር ሊያዙ ይችላሉ፡፡
6) በንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያለ ድርጅት በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ እንዲሸጥ መልሶ በማደራጀት ኃላፊው የተዘጋጀ ከሆነ ተፎካካሪ ጨረታዎችን ለማግኘት መልሶ የማደራጀት ኃላፊው መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓቱ ከተከፈተ በኋላ ከቀረቡት ውስጥ የተመረጠውን ዋጋ ለህዝብ ይፋ ያደርጋል፡፡ በፍርድ ቤቱ ከሚወሰነው አግባብነት ካለው ጊዜ በኋላ መልሶ የማደራጀት ኃላፊው የቀረቡትን ዋጋዎች ድምጽ እንዲሰጥባቸው ለገንዘብ ጠያቂዎች ጠቅላላ ጉባዔ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

### አንቀጽ 690 የጨረታ ሥርዓት

1) መልሶ የማደራጀት ኃላፊው ከባለዕዳው ጋር በመተባበር ፍላጎት ላላቸው ማናቸውም ተጫራቾች ተደራሽ የሆነ የመረጃ ክፍል ያደራጃል፡፡
2) ፍላጎት ያላቸው ማናቸውም ተጫራቾች የመረጃ ክፍሉን ከመጠቀማቸው በፊት የሚስጥር ጥበቃ ስምምነት መፈረም ይኖርባቸዋል፡፡

3) ፍላጎት ያለው ማንኛውም ተጫራች የሚከተሉትን ጨምሮ ጨረታውን አግባብ ካላቸው ሰነዶች ጋር ያቀርባል፡-

ሀ) የተጫራቹን የፋይናንስ አቋም፤

ለ) የንግድ ሥራ እንቅስቃሴውን ለመረከብ የሚከፈለውን ገንዘብ ምንጭ፤

ሐ) የንግድ ሥራ ዕቅዱን፤

መ) ለመግዛት የታሰቡትን ንብረቶች ዝርዝር፤

ሠ) የመግዣ ዋጋውን፤

ረ)አስገዳጅ የሆኑ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው ተጫራቹ ለመረከብ ፈቃደኛ የሆናቸውን ሰራተኞች ምድቦች እና ብዛት፤ እና

ሰ) በንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያለ ድርጅት በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ እንዲቀጥል ለተጫራቹ እንዲተላለፍ አስፈላጊ የሆኑትን ውሎች።

**<u>አንቀጽ 691 ውሎች መተላለፍ የሚችሉ ስለ መሆናቸው</u>**

በግል የሚፈጸሙ ውሎችን ጨምሮ የውሎችን መተላለፍ የሚገድቡ ማናቸውም የውል ድንጋጌዎች የንግድ ሥራውን ለማስቀጠል አስፈላጊ እስከሆኑ ድረስ ተፈጻሚ አይሆኑም።

**<u>አንቀጽ 692 ዋስትና ያላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች ስምምነት</u>**

1) ለዕዳ ማስያዣነት የዋሉ ንብረቶች በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ የንግድ ሥራ የሚሸጠው የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ውስጥ የተካተቱ ከሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ማስያዣ ተቀባዮቹ፣ የተንቀሳቃሽ ንብረት ማስያዣ ተቀባዮቹ እና ሌሎች የንብረት ዋስትና ተጠቃሚዎች ስምምነት መገኘት አለበት።
2) ለዕዳ ማስያዣነት የዋለው ተንቀሳቃሽ ወይም የማይንቀሳቀስ ንብረት ዋጋ ዋስትና ከተሰጠው የክፍያ ጥያቄ በላይ ከሆነ መልሶ የማደራጀት ኃላፊው የክፍያ ጥያቄውን በመክፈል ወይም ንብረቱን ተመሳሳይ ዋጋ ባለው ሌላ ንብረት በመተካት የዋስትና ግዴታውን ሊያነሳ ይችላል።
3) ተጠቃሚ የሆነው ገንዘብ ጠያቂ ለዕዳ ማስያዣነት የዋለውን ንብረት ለመልቀቅ ፈቃደኛ ካልሆነ መልሶ የማደራጀት ኃላፊው ለፍርድ ቤቱ አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል። ፍርድ ቤቱ ዋስትና ላለው የክፍያ ጥያቄ ክፍያ እንዲቀበል ወይም ንብረቱ ተመሳሳይ ዋጋ ባለው ሌላ ንብረት እንዲተካ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል።
4) በምትክ የቀረበው ንብረት አስቀድሞ በነበረው ለዕዳ ማስያዣነት የዋለ ንብረት ዋስትና የተሰጠውን የክፍያ ጥያቄ ሙሉ በሙሉ ለመሸፈን የማይበቃ ከሆነ መልሶ የማደራጀት ኃላፊው ልዩነቱን ዋስትና ላለው ገንዘብ ጠያቂ እንዲከፍል ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

**<u>አንቀጽ 693 የንግድ ሥራ እንቅስቃሴውን ለመረከብ የቀረበው ዕቅድ በገንዘብ ጠያቂዎች ጠቅላላ ጉባዔ መጽደቅ</u>**

1) መልሶ የማደራጀት ዕቅዱ በገንዘብ ጠያቂዎች ስብሰባው ወይም በፍርድ ቤቱ ውድቅ ከተደረገ መልሶ የማደራጀት ኃላፊው የንግድ ሥራ እንቅስቃሴው በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ የንግድ ሥራ ለመሸጥ የቀረቡትን ጨረታዎች በገንዘብ ጠያቂዎች ድምጽ እንዲሰጥባቸው ያቀርባል።

2) ገንዘብ ጠያቂዎች ከሚጠይቁት ክፍያ ውስጥ ቢያንስ ሁለት ሦስተኛው ያላቸው በገንዘብ ጠያቂዎች መካከል በጽሁፍ በሚደረግ ስምምነት አማካኝነት ጨምሮ ከደገፉት ጨረታው ተቀባይነት ያገኛል። ማሳወቂያ ተሰጥቷቸው በአካል እንዲሁም በወኪላቸው አማካኝነት ያልተገኙ ገንዘብ ጠያቂዎች ድምጽ ለመስጠት ዓላማ ከግምት ውስጥ አይካተቱም።

**<u>አንቀጽ 694 በንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያለ ድርጅት በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ እንዲሸጥ በፍርድ ቤት ስለ መጽደቁ</u>**

1) በንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያለ ድርጅት በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ የሚሸጥ የሆነ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ በሚያስፈልገው አብላጫ ድምጽ በገንዘብ ጠያቂዎች የጸደቀ መልሶ የማደራጀት ዕቅድ ያለመኖሩን እና የአሸናፊው ተጫራች የንግድ ሥራ ዕቅድ የንግድ ሥራውን አዋጭነት የማረጋገጥ ተስፋ ያለው መሆኑን ያጣራል።

2) ፍርድ ቤቱ በንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያለ ድርጅት የንግድ ሥራውን እንዲቀጥል አስፈላጊ የሆኑት በቀረቡት የግዢ ጥያቄዎች ውስጥ የተዘረዘሩ ውሎች እንዲተላለፉ ትዕዛዝ ይሰጣል፤ እንዲሁም በሕጉ መሰረት ስም እስከሚተላለፍ ድረስ አሸናፊው ተጫራች ሥራ አመራሩን እንዲረከብ ለማስቻል የንግድ ሥራው አሸናፊ ለሆነው ተጫራች የሚተላለፍበትን ቀን ይወስናል።

3) ፍርድ ቤቱ አሸናፊው ተጫራች የገዛቸውን ንብረቶች በነጻነት እንዳይተላለፉ ገደብ ሊያስቀምጥ የሚችለው ቢበዛ ለሁለት ዓመታት ነው።

4) የተላለፉት ንብረቶች የሚሸጡት ከማንኛውም ተጨባጭ፣ ቅድመ ሁኔታ ያለውም ሆነ ሌላ ዓይነት ዕዳ፣ ዕገዳ፣ ክፍያ እና ኃላፊነት እንዲሁም በተለይም ደግሞ ከአካባቢ ክፍያዎች እና ኃላፊነቶች ነጻ ሆነው ነው።

**<u>አንቀጽ 695 በግድ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያለ ድርጅት በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ የንግድ ሥራ የመሸጥ አፈጻጸም</u>**

1) በፍርድ ቤቱ መጽደቁን ተከትሎ መልሶ የማደራጀት ኃላፊው የባለቤትነት ማስተላለፊያ ውልን ጨምሮ አስፈላጊ የሆኑ ውሎች በሙሉ እንዲፈጸሙ ያመቻቻል፤ እንዲሁም በንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያለ ድርጅት በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ መተላለፉን ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎችን በሙሉ ያሟላል።

2) በንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያለ ድርጅት በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ በሽጭ ከመተላለፉ በፊት የሽያጩ አካል ያልሆኑ ንብረቶች ይሸጣሉ እንዲሁም ያልተዘዋወሩ ሰራተኞች ይሰናበታሉ። ከሽያጩ የሚገኘው ገንዘብ በዚህ ሕግ አንቀጽ 786 ውስጥ በተቀመጡት የቅደም ተከተል ደንቦች መሰረት ለገንዘብ ጠያቂዎች ይከፋፈላል።

## <u>ምዕራፍ ሰባት</u>

## <u>መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓቶች መቀየር እና ይግባኝ</u>

**<u>አንቀጽ 696 የመልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓትን ወደ የመክሠር ሥነ ሥርዓት ስለ መቀየር</u>**

በንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያለ ድርጅት በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ እንዲሸጥ ከጸደቀ በኋላ ወይም መልሶ የማደራጀት ዕቅዱ ውድቅ የተደረገ ከሆነ ፍርድ ቤቱ መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓቱን ወደ የመክሠር ሥነ ሥርዓት ይቀይረዋል።

**<u>አንቀጽ 697</u>** **<u>ይግባኝ</u>**

1) ተቃውሞ ያለው ገንዘብ ጠያቂ መልሶ የማደራጀት ዕቅዱን በሚያጸድቀው ፍርድ ወይም በንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያለ ድርጅት በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ እንዲሸጥ በተሰጠው ፍርድ ላይ ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል።
2) ባለዕዳው መልሶ የማደራጀት ዕቅዱን ውድቅ በሚያደርገው ፍርድ ወይም የንግድ ሥራ እንቅስቃሴው በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ የንግድ ሥራ መሸጡን ውድቅ በሚያደርገው ፍርድ ላይ ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል።
3) የተላለፉ ውሎች ተዋዋይ ወገኖች የንግድ ሥራ እንቅስቃሴው በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ የንግድ ሥራ እንዲሸጥ በተሰጠው ፍርድ ላይ ይግባኝ ሊያቀርቡ ይችላሉ፤ ነገር ግን ይግባኝ ማቅረብ የሚችሉት ውሎቹ መተላለፋቸውን በተመለከተ ብቻ ነው።
4) ለባለዕዳው፣ መልሶ ለማደራጀት ኃላፊው እና የሥነ ሥርዓቱ አካል ለሆኑ ወገኖች በሙሉ ስለ ይግባኙ ማሳወቂያ ይሰጣቸዋል።
5) መልሶ የማደራጀት ዕቅዱን በሚያጸድቅ ውሳኔ ላይ ይግባኝ መቅረቡ የዕቅዱን አፈጻጸም መታገድ አያስከትልም።
6) መልሶ የማደራጀት ዕቅዱን በመቃወም የቀረበ ይግባኝ አወንታዊ ውጤት ያገኘ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ፡-

   ሀ) እንደ ሁኔታው ግልጽ የሆነ የሥርዓት ጥሰት ወይም "የገንዘብ ጠያቂዎች የተሻለ ጥቅም" የሚለው መስፈርት ላይ የተፈጸመ ጥሰት በሚኖርበት ጊዜ መልሶ የማደራጀት ዕቅዱን ሊተው፤ ወይም

ለ) ዕቅዱን ሊያጸድቅ እና ጉዳት ለደረሰበት ወገን ካሳ ሊሰጥ ይችላል።

7) ማንኛውም ፍላጎት ያለው ወገን መልሶ የማደራጀት ዕቅዱ እንዲቋረጥ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል።
8) በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚቀርቡ ይግባኞች መልሶ የማደራጀት ዕቅዱን የሚያጸድቀው ወይም ውድቅ የሚያደርገው ፍርድ በተሰጠ በሃያ ቀናት ውስጥ መቅረብ አለባቸው።

**<u>አንቀጽ 698</u>** **<u>የተሸነፉ ተጫራቾች ተቃውሞ</u>**

የተሸነፉ ተጫራቾች የንግድ ሥራ እንቅስቃሴው በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ የንግድ ሥራ እንዲሸጥ በተሰጠው ፍርድ ላይ ተቃውሞ ማቅረብ አይችሉም።

## ምዕራፍ ስምንት
## የዳይሬክተሮች እና ሥራ አስኪያጆች ግዴታዎች

### አንቀጽ 699 የሥራ አስኪያጆች እና ዳይሬክተሮች ግዴታዎች

ኪሳራ ሊከሰት የሚችልበት ሁኔታ በሚኖርበት ጊዜ ሥራ አስኪያጆች እና ዳይሬክተሮች በዋነኝነት፡-

ሀ) የገንዘብ ጠያቂዎችን ጥቅሞች ለማስጠበቅ፤ እና

ለ) ኪሳራን ለመከላከል አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን በሙሉ ለመውሰድ፤

በእምነት ኃላፊነት ተጥሎባቸዋል፡፡

## ምዕራፍ ዘጠኝ
## ቀላል መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት

### አንቀጽ 700 ቀላል መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት ስለ መክፈት

1) ፍርድ ቤቱ፡-

ሀ) ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓት በሂደት ላይ ከሆነ፤

ለ)መልሶ የማደራጀት ዕቅዱ ከፍተኛ ቁጥር ባላቸው ገንዘብ ጠያቂዎቹ የሚደገፍ መሆኑን እና በገንዘብ ጠያቂዎች መደቦች ስብሰባዎች ወይም በየገንዘብ ጠያቂዎች ጠቅላላ ጉባዔ ላይ ድምጽ በሚሰጡ ገንዘብ ጠያቂዎች በአስፈላጊው አብላጫ ድምጽ የመጽደቅ ሰፊ ዕድል እንዳለው ባለዕዳው ካሳየ፤

ቀላል መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት ይከፍታል፡፡

2) በዚህ ሕግ አንቀጽ 637 ውስጥ ከተቀመጡት ሰነዶች በተጨማሪ ባለዕዳው የሚከተሉትን ሰነዶች ያቀርባል፡-

ሀ) ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት የተሰጠውን ፍርድ ቅጂ፤

ለ) ዋና ገንዘብ ጠያቂዎቹ የተስማሙበትን ረቂቅ መልሶ የማደራጀት ዕቅድ፤

ሐ) የንግድ ሥራው መልሶ በማደራጀት ዕቅዱ መሰረት አዋጭ እንደሚሆን የሚያሳዩ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን በሙሉ፡፡

### አንቀጽ 701 የቆይታ ጊዜ

ፍርድ ቤቱ ቀላል መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት በሚሰጠው ፍርድ የሥነ ሥርዓቱን የቆይታ ጊዜ ይወስናል፡፡

**አንቀጽ 702 መልሶ የማደራጀት ኃላፊውን ስለ መሾም**

1) ፍርድ ቤቱ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዘርፍ ባለሞያውን መልሶ የማደራጀት ኃላፊ አድርጎ ይሾማል።
2) መልሶ የማደራጀት ኃላፊው አግባብነት ካለው የገንዘብ ጠያቂዎች መደቦችን በጥንቃቄ ይመድባል እንዲሁም መልሶ የማደራጀት ዕቅዱን ድምጽ እንዲጥበት ለገንዘብ ጠያቂዎች መደቦች ስብሰባዎች ወይም ለየገንዘብ ጠያቂዎች ጠቅላላ ጉባዔ ያቀርባል።

**አንቀጽ 703 አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች**

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር የምዕራፍ ሦስት (የባለዕዳው ሀብት) ድንጋጌዎችን ሳይጨምር የርዕስ ሦስት ድንጋጌዎች በቀላል መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት ላይ ተፈጻሚ ይደረጋሉ።

**አንቀጽ 704 ስለ ቀላል መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት መቋረጥ**

1) መልሶ የማደራጀት ዕቅዱ በገንዘብ ጠያቂዎች መደቦች ወይም በየገንዘብ ጠያቂዎች ጠቅላላ ጉባዔዎች በሚያስፈልገው አብላጫ ድምጽ በገንዘብ ጠያቂዎች ካልጸደቀ ቀላል መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓቱን ያቋርጣል።
2) ሥነ ሥርዓቱን ለማቋረጥ ልክ ውሳኔ ሲሰጥ ቀላል መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓቱ ወዲያውኑ ወደ መልሶ የማደራጀት ዕቅድ ይቀየራል።
3) ንዑስ አንቀጽ (2) ቢኖርም የንግድ ሥራ እንቅስቃሴው በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ የንግድ ሥራ የመሸጥ ዕድሉ ጠባብ በሚሆንበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ በራሱ ሥልጣን ባለዕዳው እና መልሶ የማደራጀት ኃላፊው የሚሉትን ከሰማ በኋላ ቀላል መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓቱን ወደ መክሠር ሥነ ሥርዓት ሊቀይር ይችላል።

## ርዕስ አራት
## የመክሠር ሥነ ሥርዓት

### ምዕራፍ አንድ
### የመክሠር ሥነ ሥርዓት ለመክፈት የሚሰጥ ፍርድ

**አንቀጽ 705 የመክሠር ሥነ ሥርዓት ስለ መክፈት**

1) ክፍያዎችን ያቋረጠ ባለዕዳ አቤቱታ ሲያቀርብ የመክሰር ሥነ ሥርዓት ይከፈታል።
2) ባለዕዳው በዚህ መጽሐፍ ርዕስ ሦስት መሰረት መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት ለመክፈት አስቀድሞ አቤቱታ ያቀረበ ካልሆነ በስተቀር ክፍያዎችን ያቋረጠው ባለዕዳ በጣም ቢዘገይ በአርባ አምስት ቀናት ውስጥ የመክሠር ሥነ ሥርዓት ለመክፈት ለፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረብ አለበት።

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ውስጥ ባለዕዳው ያለበት ግዴታ በኅብረት የሽርክና ማኅበር ውስጥ በእያንዳንዱ ማኅበርተኛ ላይ እንዲሁም ሁለት ዐይነት ኃላፊነት ባለበት የሽርክና ማህበር ውስጥ ኃላፊነታቸው ባልተወሰነ ማሕበርተኞች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

4) የመክሠር ሥነ ሥርዓት፡-

ሀ) ከባለዕዳው ጋር ባንድነትና በተናጠል ኃላፊ የሆኑ ሰዎች፤

ለ)በባለዕዳው ላይ ጊዜው የደረሰ እና መከፈል ያለበት የክፍያ ጥያቄ ያላቸው አንድ ወይም ከዚያ በላይ ገንዘብ ጠያቂዎች፤

ሐ) ከመክሠር ሥነ ሥርዓት ውጭ የባለዕዳውን ንብረት እንዲያጣራ የተሸመ ንብረት አጣሪ፤

መ) ባለዕዳው የንግድ ሥራ ማቋረጡ ባለዕዳውን ከሚመለከት የወንጀል ሥነ ሥርዓት ግልጽ በሚሆንበት ጊዜ ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ፤

አቤቱታ በሚያቀርቡበት ጊዜም እንዲሁ ሊከፈት ይችላል።

5) በባለዕዳው ላይ በመካሄድ ላይ ባለ ሥነ ሥርዓት የተነሳ ባለዕዳው ክፍያዎችን ያቋረጠ መሆኑ ግልጽ በሚሆንበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ በራሱ ተነሳሽነትም እንዲሁ የመክሰር ስነ ሥርዓት ሊያስጀምር ይችላል። ባለዕዳው ክፍያዎችን ያቋረጠ መሆኑን ያረጋገጠው ፍርድ ቤት ጉዳዩን በዚህ መጽሐፍ መሰረት የመክሠር ፍርድ ለመስጠት ሥልጣን ወዳለው ፍርድ ቤት ይልካል።

6) ባለእዳው ከአቤቱታው በተጨማሪ በዚህ ሕግ አንቀጽ 637 ንዑስ አንቀጽ (1) ውስጥ የተዘረዘሩትን ሰነዶች ማቅረብ አለበት።

7) ከአቤቱታቸው በተጨማሪ ገንዘብ ጠያቂዎች በዚህ ሕግ አንቀጽ 637 ንዑስ አንቀጽ (4) ውስጥ የተዘረዘሩትን ሰነዶች ማቅረብ አለባቸው፡፡ እንዲሁም የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ተደርጎ የሚሾመውን ሰው በተመለከተ ሀሳብ ሊያቀርቡ ይችላሉ።

<u>አንቀጽ 706</u> <u>ስለ መክሰር የሚሰጥ ፍርድ</u>

1) ለመጀመሪያ ጊዜ ጉዳዩ በሚሰማበት ጊዜ ወይም አግባብ በሚሆንበት ጊዜ በዚህ ሕግ አንቀጽ 591 ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት የመርማሪው ሪፖርት ሲደርሰው ፍርድ ቤቱ፡-

ሀ) ባለዕዳው የከሰረ መሆኑን ያውጃል፤

ለ) በዚህ ሕግ አንቀጽ 605 መሰረት ተቆጣጣሪ ዳኛውን ይሾማል፤

ሐ)ከዚህ ሕግ አንቀጽ 610 እስከ አንቀጽ 616 በተደነገገው መሰረት የመክሠር ሥነ ሥርዓቱን ለማከናወን የከሰረውን ሰው ንብረት ጠባቂ ይሾማል፤

መ) በዚህ ሕግ አንቀጽ 591 መሰረት ክፍያዎች የተቋረጡበት ቀን መልሶ በማደራጀት ሥነ ሥርዓት ውስጥ ያልተወሰነ ከሆነ ክፍያዎች የተቋረጡበትን ቀን ይወስናል፤

2) በአንድነትና በተናጠል ጠጠያቂ የሆኑ ማኅበርተኞች ባሉት የንግድ ሥራ ማኅበር ላይ የመክሠር ፍርድ በሚሰጥበት ጊዜ ማኅበርተኞቹ የከሰሩ ይሆናሉ። የድርጅቱ እና የማኅበርተኞቹ ንብረቶች ለየብቻ ይስተናገዳሉ እንዲሁም የመክሠር ሥነ ሥርዓቶቹ ለየብቻ ይከናወናሉ።

## <u>አንቀጽ 707</u> <u>ለገንዘብ ጠያቂዎች የሚሰጥ ማሳወቂያ</u>

1) የመክሠር አቤቱታ በገንዘብ ጠያቂዎች፣ በአንድነትና በተናጠል ኃላፊ በሆኑ ማኅበርተኞች ወይም በዐቃቤ ሕግ የቀረበ ከሆነ ፍርድ ቤቱ አቤቱታው መቅረቡን በሰባት ቀናት ውስጥ ለባለዕዳው ያሳውቃል።
2) ባለዕዳው አቤቱታው በቀረበ በሃያ ቀናት ውስጥ የመክሠር አቤቱታውን የሚቀበል ወይም የሚቃወም መሆኑን በመግለጽ መልስ ያቀርባል። ባለዕዳው በዚህ ሕግ አንቀጽ 637 ንዑስ አንቀጽ (1) ውስጥ የተዘረዘሩትን ሰነዶች እንዲሁም ክፍያዎችን ያቋረጠ እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ የሚጠቁሙ ሌሎች ደጋፊ ሰነዶችን ያቀርባል።
3) ባለዕዳው ክፍያዎች መቋረጣቸውን የሚያምን ከሆነ ባለዕዳው የንግድ ሥራው በዚህ መጽሐፍ ርዕስ ሦስት መሰረት መልሶ ለማደራጀት ሥነ ሥርዓት ብቁ እንደሆነ ወይም የመክሠር ሥነ ሥርዓትን በሚመለከተው በዚህ ሕግ
4) ርዕስ አራት

 መሰረት ወደ መክሠር ሥነ ሥርዓት መሄድ እንዳለበት መግለጽ አለበት።

5) ባለዕዳው መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት ለመክፈት ብቁ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ከደረሰበት እና መልሶ የማደራጀት ዕቅዱ ተዘጋጅቶ ሲቀርብ በዚህ መጽሐፍ ርዕስ ሦስት መሰረት አስፈላጊውን ድምጽ እንደሚያገኝ የሚጠብቅ ከሆነ በመክሠር ሥነ ሥርዓት ፋንታ መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

## <u>አንቀጽ 708</u> <u>የንግድ ሥራው ከተቋረጠ በኋላ ስለ መክሠር</u>

1) ምዝገባው ከንግድ መዝገብ የተሰረዘ ባለዕዳ ከንግድ መዝገቡ ከተሰረዘበት ጊዜ አንስቶ ባለው አንድ ዓመት ውስጥ ክፍያዎችን አቋርጦ የነበረ ከሆነ መክሠሩ ሊነገር ይችላል።
2) ነጋዴው የንግድ መዝገብ ውስጥ ተመዝግቦ ያልነበረ ከሆነ ክፍያዎች ከተቋረጡ በኋላ በማንኛውም ጊዜ መክሠሩ ሊነገር ይችላል።

## <u>አንቀጽ 709</u> <u>ከሞት በኋላ የመክሠር ሥነ ሥርዓት ስለ መክፈት</u>

1) ክፍያ አቋርጦ የነበረ አንድ ነጋዴ የሞተ እንደሆነ በሞተ በአንድ ዓመት ውስጥ መክሠሩ ሊነገር ይችላል።
2) እንዲህ ባለው ነጋዴ ላይ፡-

   ሀ) በአንድ ገንዘብ ጠያቂ፤

   ለ) በዐቃቤ ሕግ፤ ወይም

   ሐ) ፍርድ ቤቱ በራሱ ሥልጣን፤

የመክሠር ሥነ ሥርዓት ሊከፍት ይችላል።

3) ማንኛውም ወራሽ በውርስ የተላለፈለት ሀብት ከግል ሀብቱ ጋራ እንዳይደባለቅ ለማድረግ የሞተው ሰው መክሰር እንዲነገር አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል።

4) ነጋዴው ከሞተ በኋላ የመክሠር ሥነ ሥርዓት ለመክፈት የሚሰጠው ፍርድ በፍትሐ ብሔር ሕግ ድንጋጌዎች መሰረት ገንዘብ ጠያቂዎች አግኝተው የነበረውን የንብረት መለየት ጥቅም ውጤት ወዲያውኑ ያስቀረዋል።

**<u>አንቀጽ 710 የፍርድ ማስታወቂያ</u>**

1) በዚህ ርዕስ ውስጥ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር የዚህ ሕግ አንቀጽ 648 ድንጋጌዎች የመክሠር ፍርድን ማስታወቅን በተመለከተ በተመሳሳይነት ተፈጻሚ ይሆናሉ።

2) የተፈጥሮ ሰው የሆነው ባለዕዳ የሞተ እንደሆነ የፍርዱ ቅጂ ወራሽ ካለ ለባለዕዳው ወራሽ ፍርዱ እንደተሰጠ ወዲያውኑ ይላካል።

**<u>አንቀጽ 711 የመክሠር ሥነ ሥርዓት በሚከፍተው ወይም መክፈቱን ውድቅ በሚያደርገው ፍርድ ላይ ስለሚቀርብ ይግባኝ</u>**

1) ባለዕዳው እና ዐቃቤ ሕግ የመክሠር ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት ፍርድ በተሰጠ በአሥር ቀናት ውስጥ በፍርዱ ላይ ይግባኝ ሊያቀርቡ ይችላሉ።

2) ማንኛውም ገንዘብ ጠያቂ እና ዐቃቤ ሕግ የመክሠር ሥነ ሥርዓት መክፈትን ውድቅ ለማድረግ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ሊያቀርቡ ይችላሉ።

3) ይግባኙ በተፋጠነ ሥነ ሥርዓት ተሰምቶ በሁለት ወራት ውስጥ ውሳኔ መሰጠት አለበት፡፡ ውሳኔው ወዲያውኑ ተፈጻሚ ይሆናል።

**<u>አንቀጽ 712 የመክሠር ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት የተሰጠውን ፍርድ ስለ መቃወም</u>**

1) የመክሠር ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት በተሰጠው ፍርድ ላይ መቃወሚያ ሊቀርብ የሚችለው ፈርዱ በተሰጠ በአሥር ቀናት ውስጥ ነው። በሚለጠፉ ወይም ማስታወቂያዎችን ለመቀበል በተፈቀደላቸው ጋዜጣዎች ለሚወጡ ፍርዶች ግን ይህ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ማስታወቂያው ከወጣበት ቀን ጀምሮ ይሆናል።

2) የመክሰር ፍርድ እንዲፈረድ የጠየቀው ሰው በተፈረደው የመክሠር ፍርድ ላይ መቃወሚያ ማቅረብ አይችልም።

3) ባለዕዳው በፍርዱ ላይ የሚያቀርበው መቃወሚያ የፍርዱን አፈጻጸም የማገድ ውጤት አይኖረውም።

**<u>አንቀጽ 713 መቃወሚያ ወይም ይግባኝ ሊቀርብበት ስለማይቻል ፍርድ</u>**

1) የሚከተሉት መቃወሚያ ወይም ይግባኝ ሊቀርብባቸው የማይቻሉ ፍርዶች ናቸው፡-

ሀ) የመክሠር ሥራ ተቆጣጣሪ ዳኛውን ወይም የመክሠር ንብረት ጠባቂውን ለመሾም ወይም ለመሻር የተሰጠ ፍርድ፤

ለ)ነጻ ለመውጣት በሚቀርቡ ጥያቄዎች እና ለባለዕዳው እና ለቤተሰቡ ርዳታ ለማግኘት በሚቀርቡ ጥያቄዎች ላይ ለመወሰን የተሰጠ ፍርድ፤

ሐ) የባለዕዳው ሀብት ንብረት አካል የሆኑ ዕቃዎች ወይም ሸቀጦች እንዲሸጡ የሚፈቅድ ፍርድ፤

መ) የባለዕዳው ንብረት ጠባቂ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት በሰጠው ትዕዛዝ ላይ በቀረበ አቤቱታ ላይ የተሰጠ ፍርድ፤

ሠ) የንግድ ሥራው እንዲቀጥል የሚፈቅድ ፍርድ።

2) የመክሰር ንብረት ጠባቂዎቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (መ) በተመለከተው ጉዳይ ዳኝነት ውስጥ አይቀርብም።

**<u>አንቀጽ 714 መክሰርን ለማስታወቅ የተሰጠውን ፍርድ ስለ ማንሳት</u>**

1) መክሰርን የማሳወቅ ፍርድ በተሰጠበት ቀን እና በመቃወሚያ ወይም በይግባኝ ላይ ውሳኔ በተሰጠበት ቀን መካከል የከሰረው ሰው ለገንዘብ ጠያቂዎች ክፍያ በመፈጸም ከመክፈል ማቋረጥ ሁኔታ ውስጥ የወጣ እንደሆነ ወይም ፍርድ ቤቱ በመክሥር ሥነ ሥርዓት ፋንታ መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት የከፈተ እንደሆነ መክሰሩን ለማሳወቅ የተሰጠው ፍርድ መነሣት አለበት።
2) በማናቸውም ሁኔታ የመክሠሩን ሥነ ሥርዓት የሚያስፈጽሙት ሰዎች የፈጸሟቸው ሕጋዊ የሆኑ ሥራዎች ያስገኟቸው ውጤቶች እንደጸኑ ይቆያሉ።

## <u>ምዕራፍ ሁለት</u>
## <u>የመክሠርን ሥራ የሚያስፈጽሙ ሰዎች እና አካላት</u>

## <u>ክፍል አንድ</u>
## <u>ስለ ፍርድ ቤት</u>

**<u>አንቀጽ 715 ስለ ፍርድ ቤት ሥልጣን</u>**

የዚህ ሕግ አንቀጽ 604 በዚህ ርዕስ መሰረት የመክሠር ሥነ ሥርዓት በሚከፍተው ፍርድ ቤት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

## <u>ክፍል ሁለት</u>
## <u>ስለ ተቆጣጣሪ ዳኛው</u>

**<u>አንቀጽ 716 ስለ ተቆጣጣሪ ዳኛው ሹመት እና ሥልጣን</u>**

የመክሠር ሥነ ሥርዓት ተቆጣጣሪ ዳኛ ለመልሶ ማደራጀት ሥነ ሥርዓት ያልተሾመ ከሆነ በዚህ ሕግ አንቀጽ 605 መሰረት ይሾማል። ተቆጣጣሪ ዳኛው በዚህ ሕግ አንቀጽ 606 ውስጥ የተመለከተው ሥልጣን ይኖረዋል።

**<u>አንቀጽ 717 ስለ የተቆጣጣሪ ዳኛው ሥልጣን</u>**

1) በዚህ ሕግ አንቀጽ 606 መሰረት በዝርዝር ከተሰጠው ሥልጣን በተጨማሪ የመክሠር ሥነ ሥርዓት ተቆጣጣሪ ዳኛው፡-

ሀ. ከመክሠር ሥነ ሥርዓት ጋር በተያያዘ በሚነሱና በፍርድ ቤቱ ሥልጣን ስር በሚወድቁ ክርክሮች ሁሉ ለፍርድ ቤት መግለጫ የማቅረብ፤ የዚሁ መግለጫ መኖርም በፍርድ ቤቱ ውሳኔዎች ውስጥ መጠቀስ አለበት፤

ለ. የባለዕዳው ሀብት ውስጥ ያሉ ንብረቶችን ጠብቆ ለማቆየት አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን በሙሉ የመውሰድ ወይም አግባብ ባላቸው ባለሥልጣን አካላት እንዲወሰዱ የማድረግ፤

ሐ. በሕግ የታዘዘ ሲሆን ወይም አስፈላጊ መሆኑን ካመነ የገንዘብ ጠያቂዎች ኮሚቴ ስብሰባ እንዲደረግ ጥሪ የማድረግ፤

መ. ንብረት ጠባቂው ራሱ እንዲሾም በሕግ ካልታዘዘ በስተቀር የመክሠር ሥነ ሥርዓቱን ለማገዝ አስፈላጊ የሆኑትን ሰዎች የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ እንዲሾማቸው የመፍቀድ፤

ሠ. የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ በከሳሽነት ወይም በተከሳሽነት በፍርድ ቤት እንዲከራከር በጽሁፍ የመፍቀድ፤

ሥልጣን አለው።

2) ተቆጣጣሪ ዳኛው የሚሰጣቸው ሕጋዊ የሆኑ ትዕዛዞች እንደ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ይቆጠራሉ።

## ክፍል ሦስት
## የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ

### አንቀጽ 718 የከሠረውን ሰው ንብረት ጠባቂ ስለ መሾም

1) ፍርድ ቤቱ በዚህ ሕግ ከአንቀጽ 610 እስከ አንቀጽ 616 በተደነገገው መሰረት የመክሠር ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት በሚሰጠው ፍርድ ውስጥ አንድ የከሠረን ሰው ንብረት ጠባቂ ይሾማል።
2) የመክሠር ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት የጠየቀ አንድ ገንዘብ ጠያቂ የከሠረውን ሰው ንብረት ጠባቂ የሚሆነውን ሰው ያቀረበ ከሆነ ፍርድ ቤቱ ገንዘብ ጠያቂው ያቀረበውን ሰው ሊሾም ይችላል።
3) መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት ወደ መክሠር ሥነ ሥርዓት የተቀየረ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ መልሶ የማደራጀት ኃላፊውን የከሠረውን ሰው ንብረት ጠባቂ አድርጎ ይሾማል።

### አንቀጽ 719 የከሠረውን ሰው ንብረት ጠባቂ ስለ መተካት

1) በሥነ ሥርዓቱ ወቅት በማናቸውም ጊዜ የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ፣ ማንኛውም ገንዘብ ጠያቂ፣ የገንዘብ ጠያቂዎች ኮሚቴው ወይም አንድ ዐቃቤ ሕግ የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ በሌላ እንዲተካ ለፍርድ ቤቱ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል።

2) ፍርድ ቤቱ በራሱ ሥልጣን የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂውን በሌላ ሊተካ ይችላል።

3) ፍርድ ቤቱ በተለይም ደግሞ የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ከተቆጣጣሪ ዳኛው ፈቃድ ውጭ የተቀበለውን ማንኛውንም ገንዘብ በዚህ ሕግ አንቀጽ 720 ንዑስ አንቀጽ (1) (ሠ) መሠረት በከሠረው ሰው ሀብት ስም በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ውስጥ ሳያስገባ ከቀረ ወይም ከባንክ ሒሳብ ካስወጣ ፍርድ ቤቱ በራሱ ተነሳሽነት የከሠረውን ሰው ንብረት ጠባቂ በሌላ ሊተካ ይችላል።

4) በንዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም የገንዘብ ጠያቂዎች ኮሚቴው ወይም ከአጠቃላይ የቅድመ-ኪሳራ የገንዘብ ጥያቄዎች መጠን ውስጥ አብዛኛው ያላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች የመከሠር ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት ያመለከተው ሰው እንዲሾም ያቀረበውን የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ እንዲሾም የሚደግፉ ከሆነ ፍርድ ቤቱ ማመልከቻውን ሊፈቅድ እና ያመለከተው ሰው ያቀረበውን ሰው የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ አድርጎ ሊሾም ይችላል።

**<u>አንቀጽ 720</u>** **<u>የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂዎች ሥልጣን እና ግዴታዎች</u>**

1) የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ የሚከተሉት ሥልጣኖች ይኖሩታል፡-

ሀ) በዚህ ሕግ ከአንቀጽ 742 እስከ አንቀጽ 746 በተደነገገው መሰረት በተቆጣጣሪ ዳኛው ቁጥጥር ስር ሆኖ የከሰረውን ሰው ሀብት ማስተዳደር፤

ለ) የባለዕዳው ሀብት በትክክል የሚገኝበትን ሁኔታ ለማወቅ የሚያስችሉትን መረጃዎች ከመንግስት ባለሥልጣን አካላት፣ ከብድር ተቋማት እና ከሌሎች ተቋማት መቀበል፤

ሐ) በዚህ ሕግ ከአንቀጽ 735 እስከ አንቀጽ 741 በተደነገገው መሰረት በባለዕዳው ድጋፍ የሀብቱን የንበረት ዝርዝር ማዘጋጀት፤

መ) የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎችን እንዲቀበል ወይም ውድቅ እንዲያደርግ ለተቆጣጣሪ ዳኛው ምክረ-ሀሳብ መስጠት፤

ሠ) የዳኝነት እና የአስተዳደር ወጪዎችን ለመሸፈን በመከሠር ሥነ ሥርዓት ተቆጣጣሪ ዳኛው የተወሰኑ ገንዘቦችን ቀንሶ የሚቀበላቸውን ገንዘቦች ሁሉ በከሰረው ንብረት ስም የተከፈተ የባንክ ሂሳብ ውስጥ ወዲያውኑ ተቀማጭ ማድረግ፤

ረ) አገልግሎቱን መስጠት ካቋረጠ በኋላ በሠላሳ ቀናት ውስጥ ወይም ቢዘገይ የመክሰር ሥነ ሥርዓቱ ከተቋረጠ በኋላ በሠላሳ ቀናት ውስጥ ለፍርድ ቤቱ ሪፖርት ማቅረብ።

2) የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ሥልጣኖቹ የማይተላለፉ ናቸው፤ ሆኖም ተቆጣጣሪ ዳኛው ከፈቀደለት ለአንዳንድ ሥራ በተለየ ሥልጣኑን ለገለልተኛ ባለሞያዎች ሊያስተላልፍ ይችላል።

**<u>አንቀጽ 721</u>** **<u>ንብረት ጠባቂው በሠራቸው ሥራዎች ላይ አቤቱታን ስለ ማቅረብ</u>**

የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ በሰራው ሥራ ላይ የከሠረው ሰው ወይም ማንኛውም ሌላ ባለጉዳይ ለመከሠር ሥነ ሥርዓት ተቆጣጣሪ ዳኛው ተቃውሞ ማቅረብ ይችላል። ተቆጣጣሪ ዳኛውም በተቃውሞው ላይ በሦስት ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት ይኖርበታል።

## ክፍል አራት
## የገንዘብ ጠያቂዎች ኮሚቴ

### አንቀጽ 722 የገንዘብ ጠያቂዎች ኮሚቴ ስለ ማቋቋም

1) ተቆጣጣሪ ዳኛው የመከሠር ሥነ ሥርዓት በተከፈተ በአሥር ቀናት ውስጥ ከፍተኛ መጠን ያላቸው የክፍያ ጥያቄዎች ካላቸው የገንዘብ ጠያቂዎች መካከል አምስት አባላትን የያዘ የገንዘብ ጠያቂዎች ኮሚቴ ያቋቁማል። የገንዘብ ጠያቂዎች ኮሚቴ ሊቀ መንበርም ከአባላቱ መካከል ይመርጣል።

2) የተቋቋመው የገንዘብ ጠያቂዎች ኮሚቴ እንዲጸድቅ ለፍርድ ቤቱ ይቀርባል።

3) አንድ የገንዘብ ጠያቂዎች ኮሚቴ አባል ከቦታው ሊነሳ የሚችለው ተቆጣጣሪ ዳኛው በሚያቀርበው ሀሳብ መሰረት ፍርድ ቤቱ በሚሰጠው ውሳኔ ብቻ ነው።

4) ሆኖም ግን ተቆጣጣሪ ዳኛው በሌላ እንዲተካ ራሱ ጥያቄ ያቀረበን አባል በሌላ ገንዘብ ጠያቂ ሊተካ ይችላል።

5) ከባለዕዳው ጋር አራተኛ ደረጃን ጨምሮ እስከ አራተኛ ደረጃ ድረስ የሚቆጠር የስጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው ማንኛውም ሰው የገንዘብ ጠያቂዎች ኮሚቴ አባል ተደርጎ ሊመረጥ አይችልም።

### አንቀጽ 723 የገንዘብ ጠያቂዎች ኮሚቴ መብቶች እና ግዴታዎች

1) ፍርድ ቤቱ፣ ተቆጣጣሪ ዳኛው እና የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ አግባብ በሚሆንበት ጊዜ የገንዘብ ጠያቂዎች ኮሚቴው ምክሩን እንዲሰጥ ሊጠይቁት ይችላሉ።
2) የገንዘብ ጠያቂዎች ኮሚቴው ውሳኔዎች በአባላቱ በድምጽ ብልጫ ይወሰናሉ።
3) የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ:-

   ሀ) ሂሳቦቹን ማረጋገጥን፤

   ለ) በባለዕዳው የተዘጋጁ መግለጫዎችን፤ እና

   ሐ) የሕግ ክርክሮችን፤

   በተመለከተ የገንዘብ ጠያቂዎች ኮሚቴውን ምክር ሊጠይቅ ይችላል።

4) የገንዘብ ጠያቂዎች ኮሚቴው የከሰረውን ሰው ንብረት ጠባቂ ይቆጣጠራል።
5) የገንዘብ ጠያቂዎች ኮሚቴው የከሰረውን ሰው ንብረት ጠባቂ ለመተካት ለፍርድ ቤቱ አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል። የገንዘብ ጠያቂዎች ኮሚቴው እንዲህ ያለውን አቤቱታ የሚያቀርበው ከአጠቃላይ የቅድመ-ኪሳራ የገንዘብ ጥያቄዎቹ ውስጥ አብዛኛው ያላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች የባለዕዳው ንብረት ጠባቂ መተካቱን የሚደግፉ ከሆነ ነው።

6) የገንዘብ ጠያቂዎች ኮሚቴው የመክሠር ሥነ ሥርዓቱ የሚገኝበትን ሁኔታ እና የገቢ እና ወጪ ክፍያዎችን ሁኔታ በተመለከተ በማንኛውም ጊዜ መረጃ ሊጠይቅ ይችላል። የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ማናቸውንም ክርክሮች በተመለከተ የገንዘብ ጠያቂዎች ኮሚቴውን ያማክራል።
7) አንድ የገንዘብ ጠያቂዎች ኮሚቴ አባል ኃላፊ የሚሆነው ከባድ ቸልተኝነት ወይም ሆነ ብሎ ጥፋት ከፈጸመ ብቻ ነው።
8) የገንዘብ ጠያቂዎች ኮሚቴው አባላት የሁሉንም ገንዘብ ጠያቂዎች ጥቅም ይወክላሉ።
9) የገንዘብ ጠያቂዎች ኮሚቴው አባላት ምንም ዓይነት ክፍያ አይከፈላቸውም። ሆኖም ወጪዎቹ በከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ በጽሁፍ የጸደቁ ከሆነ ያወጧቸውን ወጪዎች የመጠየቅ መብት አላቸው።

## ክፍል አምስት
## ስለ ዐቃቤ ሕግ

**አንቀጽ 724 በመክሠር ሥነ ሥርዓት ውስጥ ስለ ዐቃቤ ሕግ ሥልጣን**

1) ዐቃቤ ሕጉ የመክሠር ሥነ ሥርዓት ከማስፈጸም ጋር ግንኙነት ያላቸው ማናቸውንም የባለቤትነት ማረጋገጫዎች መዛግብት እና ሰነዶች ተቆጣጣሪ ዳኛው እንዲያቀርብለት የማዘዝ መብት አለው።
2) ዐቃቤ ሕጉ ምርመራዎቹ በሚስጥር መያዝ ያለባቸው ቢሆኑም ባለዕዳውን የሚመለከቱ የወንጀል ክርክሮችን የሚመለከቱ ጨምሮ ለመክሠር ሥነ ሥርዓቱ አግባብነት ያላቸው ማናቸውንም መረጃዎች በሚጠየቅበት ጊዜ ወይም በራሱ ተነሳሽነት ለተቆጣጣሪ ዳኛው የማሳወቅ ግዴታ አለበት።

## ምዕራፍ ሦስት
## የባለዕዳውን ሀብት ስለ መረከብ እና ስለ ማስተዳደር

## ክፍል አንድ
## ባለዕዳው መብቶቹን ስለ መገፈፉ

**አንቀጽ 725 የመብቶች መገፈፍ የተፈጻሚነት ወሰን**

1) የመክሠር ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት ፍርድ በሚሰጥበት ጊዜ ባለዕዳው ንብረቶቹን በተመለከተ ያሉትን መብቶች በጠቅላላ ወዲያውኑ ያጣል።
2) የመክሠር ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት ፍርድ በሚሰጥበት ጊዜ የመክሰስ እና የመከሰስ ችሎታ የሚኖረው የከሰረው ሰው ንብረት አስተዳዳሪ ብቻ ይሆናል። ፍርድ ቤቱ ባለዕዳው ጥያቄ በሚያቀርብበት ጊዜ በማንኛውም ክርክር ውስጥ እንዲሳተፍ ሊፈቅድለት ይችላል።
3) እነዚህን ድንጋጌዎች በመጣስ የሚፈጸሙ ማናቸውም ድርጊቶች በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈጻሚ ሊሆኑ አይችሉም።

4) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ቢኖሩም ባለዕዳው በወንጀል ክርክር ውስጥ እንደ ፍትሐ ብሔር ከሳሽ ካሳ እንደማግኘት ያሉ በእጅጉ ግላዊ የሆኑ መብቶቹን ሊጠቀም ይችላል።

## ክፍል ሁለት
## የአጠባበቅ ሥራዎች

**አንቀጽ 726 የባለዕዳውን መዝገቦች ስለ ማስረከብ እና ስለ መዝጋት**

1) በዚህ ሕግ አንቀጽ 725 ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት እስከሚረከብ ድረስ የአጠባበቅ ሥራዎችን እና በሥራ ዘርፉ በተለመደው አሠራር መሰረት የዕለት ተዕለት ሥራ አመራር ተግባራትን ባለዕዳው ሊያከናውን ይችላል።
2) የመክሠር ሥነ ሥርዓት በተከፈተ በሦስት ቀናት ውስጥ ባለዕዳው ተመርምረው እንዲዘጉ መዝገቦችን ለከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ያስረክባል። እነዚህን መዝገቦች ለባለዕዳው የያዘ ማንኛውም ሦስተኛ ወገን የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ በሚጠይቅበት ጊዜ መዝገቦቹን የማስረከብ ግዴታ አለበት። አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ተቆጣጣሪ ዳኛው መዝገቦቹን እንዲያስረክብ ለማስገደድ ትዕዛዝ ይሰጣል።
3) በዚህ ሕግ አንቀጽ 732 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ባለዕዳው ባለበት መዝገቦቹን ለመዝጋትና ሒሳቡን ለማቆም ባለዕዳውን ይጠራዋል።
4) በዚሁ ጥሪ ባለዕዳው ያልቀረበ እንደሆነ በአርባ ስምንት ሠዓት ውስጥ እንዲቀርብና መዝገቦችንም እንዲያቀርብ በአደራ ደብዳቤ ወይም ተቀባዩ ለመቀበሉ ማረጋገጫ ሊሰጥበት በሚችል ሌላ ማንኛውም ኤሌክትሮኒክ መንገድ ይጠራል።
5) ተቆጣጣሪ ዳኛው ከተስማማ ባለዕዳው ስለ እርሱ ሌላ ሰው ለመወከል ይችላል።
6) ባለዕዳው ራሱ ለመቅረብ ወይም ወኪል ለመላክ እንቢተኛ የሆነ እንደሆነ አስፈላጊውን ነገር እንዲያደርግ የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ለዐቃቤ ሕግ ያሳውቃል።

**አንቀጽ 727 የባለዕዳውን መብቶች ስለ መጠበቅ**

1) የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ሥራውን እንደጀመረ ባለዕዳው ያሉትን መብቶች ለመጠበቅ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ አለበት።
2) ባለዕዳው መልሶ በማደራጀት ወይም የንግድ ሥራው በሚፈርስበት ወቅት ያላስመዘገበውን በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ያለውን የዋስትና መብት እና ሌሎች የዋስትና መብቶች የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ማስመዝገብ አለበት። የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ንብረት ጠባቂ መሆኑን አስረድቶ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ያለው ዋስትና የሚያስመዘግበው በከሰረው ሰው ንብረት ስም ነው።

**አንቀጽ 728 ለተቆጣጣሪ ዳኛው የሚደረግ መግለጫ**

1) ሥራውን በጀመረ በአንድ ወር ውስጥ የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ የባለዕዳውን ጉዳይ ሁኔታ እና የመክሠር ሥነ ሥርዓት የተከፈተባቸውን ምክንያቶች በዝርዝር የሚያስረዳ መግለጫ ለተቆጣጣሪ ዳኛው ይልካል።

2) ተቆጣጣሪ ዳኛውም ሀሳቡን ጨምሮ ይህን መግለጫ ወዲያውኑ ለዐቃቤ ሕግ ያስተላልፋል። መግለጫው በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) በታዘዘው ጊዜ ውስጥ ለዐቃቤ ሕግ ያልተሰጠ እንደሆነ የዘገየበትን ምክንያቶች አስረድቶ ለዐቃቤ ሕጉ ማስታወቅ አለበት።

## ክፍል ሦስት
## የከሰረውን ሰው ንብረት ስለ ማሸግ

### አንቀጽ 729 የከሰረው ሰው ንብረት

1) የከሰረው ሰው ንብረት የሚከተሉትን ያካትታል፡-

ሀ) በአላባ የመጠቀም መብትን ጨምሮ የባለዕዳው የሆኑ ንብረቶች እና መብቶች ሁሉ፤

ለ) በዚህ ሕግ አንቀጽ 803 ውስጥ የተመለከቱት በተጨባጭ ወይም በሕጉ መሰረት ሥራ አስኪያጅ የሆኑ ሰዎች ላይ የሚቀርቡትን ጨምሮ በሦስተኛ ወገኖች ላይ የሚቀርቡ የፍትሐ ብሔር ኃላፊነት ጥያቄዎች፤

2) የከሰረው ሰው ንብረት በዚህ ሕግ አንቀጽ 751 እና አንቀጽ 752 መሰረት የሚመለሱ ንብረቶችን አያካትትም።

### አንቀጽ 730 እሽግን ስለ ማድረግ

1) የባለዕዳውን መክሠር የፈረደው ፍርድ ቤት መክሰሩን ለማስታወቅ በሚሰጠው ፍርድ እሽግ እንዲደረግ ለማዘዝ ይችላል። እሽጉም የሚደረገው በመጋዘኖቹ፣ በሳጥኖቹ፣ በመዝገቦቹ፣ በሰነዶቹ፣ በወረቀቶቹና እንደ አግባብነቱ የባለዕዳው በሆኑት የቤት ዕቃዎች እና የሚንቀሳቀሱ ንብረቶች ላይ ነው።

2) ነገር ግን ባለዕዳው የጠፋ ወይም ንብረቱን የደበቀ ወይም ንብረቶቹን ያለአግባብ የተጠቀመ እንደሆነ የሚመለከታቸው የመንግስት ባለሥልጣን አካላት በፈቃዳቸው ወይም በአንድ ገንዘብ ጠያቂ አመልካችነት የመክሠር ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተዘረዘሩት ዕቃዎች ላይ እሽግን ለማድረግ ይችላሉ።

### አንቀጽ 731 ሊታሸግባቸው የማይችሉ ዕቃዎች

1) በከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ጠያቂነት ፍርድ ቤቱ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ዕቃዎች እሽግ እንዳይደረግባቸው፤ ተደርጎባቸው እንደሆነም እንዲነሳላቸው ለመፍቀድ ይችላል፡-

ሀ) የከሰረው ሰው ግለሰብ ነጋዴ በሚሆንበት ጊዜ በሚሰጠው ዝርዝር ውስጥ በሚገኙት ለከሰረው ሰው እና ለቤተሰቡ አስፈላጊ በሆኑት መሰረታዊ የሆኑ የግል ተንቀሳቃሽ ንብረቶች እና ዕቃዎች፤

ለ) ሥራው እንዲቀጥል የተፈቀደ እንደሆነ ለንግዱ ወይም ለሥራው መካሄድ በሚያገለግሉት ዕቃዎች።

2) የዕቃዎቹን እና ንብረቶቹን ዝርዝር የሚፈርመው አግባብነት ያለው ባለሥልጣን በተገኘበት የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱትን ዕቃዎች እና ንብረቶች ዝርዝር ከነዋጋቸው ያዘጋጃል።

**<u>አንቀጽ 732 ከእሽግ ውስጥ ስለሚወጡ ዕቃዎች</u>**

1) በዚህ ሕግ አንቀጽ 730 ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሒሳብ ሰነዶችና መዝገቦች ታሽገው እንደሆነ ተቆጣጣሪ ዳኛው እና ተገቢው ባለሥልጣን እሽጉን አንስተው ሰነዶቹንና መዝገቦቹን ከዘጓቸው በኋላ ለከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ማስረከብ አለባቸው እንዲሁም ሰነዶቹና መዝገቦቹ የሚገኙበትን ሁኔታ ያመለክታሉ።
2) የመክፈያ ጊዜያቸው አጭር የሆኑትን፤ እሺታ ማግኘት ወይም የአጠባበቅ ተግባር የሚያስፈልጋቸውን በቦርሳው ውስጥ የሚገኙትን የንግድ ወረቀቶች አግባብነት ያለው ባለሥልጣን ከእሽጉ ውጭ በማድረግ ዝርዝራቸውን ከጻፈ በኋላ ገንዘቡ ገቢ እንዲደረግ ወይም አስፈላጊው እንዲፈጸም ለከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ያስረክባል። የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ የወረቀቶቹን ሁኔታ የሚያሳይ መግለጫ አዘጋጅቶ ለፍርድ ቤቱ ያስገባል።

**<u>አንቀጽ 733 ለከሰረው ሰው ስለ ተላከው ደብዳቤ</u>**

1) ተቆጣጣሪ ዳኛው ለከሰረው ሰው የተላኩ ደብዳቤዎች የመክሠር ሥነ ሥርዓት ከተከፈተ በኋላ ወደ ከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ እንዲተላለፉ ትእዘዝ ሊሰጥ ይችላል። የከሰረው ሰው ደብዳቤዎችን በማስተላለፍ ረገድ የከሰረውን ሰው ንብረት ጠባቂ መርዳት አለበት። የከሰረው ሰው ለእሱ የተላኩ ደብዳቤዎች በከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ሲከፈቱ የመገኘት መብት አለው።
2) የግል ደብዳቤዎች በሙሉ በከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ከተጣሩ በኋላ ለከሰረው ሰው ተመልሰው ይሰጣሉ።
3) የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ የከሰረው ሰው የግል ያልሆነ የኢሜይል መለያ እንዲከፍት ይፈቀድለታል። ፍርድ ቤቱ የግል ሚስጥርን ለመጠበቅ ሲባል ንብረት ጠባቂው የከሰረው ሰው የግል ያልሆነ የኢሜይል መለያ በሚከፍትበት ሁኔታ ላይ ገደብ ሊያስቀምጥ ይችላል።

**<u>አንቀጽ 734 እሽግን ስለ ማንሳት</u>**

የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ እሽጎቹ በተደረጉ በአምስት ቀናት ውስጥ የከሰረውን ሰው ንብረት ዝርዝር ለመመዝገብ እሽጉ እንዲነሳ ይጠይቃል።

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>የዕቃ ዝርዝር መዝገብ</u>

**<u>አንቀጽ 735 ጠቅላላ ድንጋጌ</u>**

የዚህ ክፍል አራት የዕቃ ዝርዝር መዝገብ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የዚህ ሕግ አንቀጽ 659 በመክሠር ሥነ ሥርዓቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

**<u>አንቀጽ 736 የሒሳቡን ሚዛን ስለ ማሰናዳትና ስለ መስጠት</u>**

የሒሳቡን ሚዛን የከሰረው ሰው ያልሰጠ እንደሆነ በሚገኙት መዝገቦች፣ የሒሳብ ሰነዶች፣ ወረቀቶችና መረጃዎች መሰረት የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ በአጭር ጊዜ ውስጥ የሒሳቡን ሚዛን አሰናድቶ ለፍርድ ቤቱ መዝገብ ቤት ሹም ይሰጣል።

**<u>አንቀጽ 737 የባለዕዳውን ንብረቶች በንብረት ዝርዝር መዝገብ ስለ ማስገባት</u>**

1) የከሰረው ሰው በአደራ ደብዳቤ ወይም ተቀባዩ ለመቀበሉ ማረጋገጫ ሊሰጥበት በሚችል ሌላ ማንኛውም ኤሌክትሮኒክ መንገድ ከተጠራ በኋላ የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ በከሰረው ሰው ድጋፍ የከሰረውን ሰው ንብረቶች በዕቃ ዝርዝር መዝገብ ውስጥ ያስገባል።
2) የዕቃ ዝርዝር መዝገቡ በሚዘጋጅበት ወቅት የከሰረው ሰው ገንዘብ ጠያቂዎች የሚጠይቋቸውን ገንዘቦች መጠን፣ ስማቸውን እና አድራሻቸውን እንዲሁም በሂደት ላይ ያሉ ውሎችን እና ባለዕዳው ከሳሽ ወይም ተከሳሽ የሆነባቸውን በሂደት ላይ ያሉ ክርክሮች የሚገልጽ የገንዘብ ጠያቂዎች ዝርዝር ለንብረት ጠባቂው ያስረክባል።
3) በዚሁ ጊዜ በዚህ ሕግ አንቀጽ 730 ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የታሸጉ ወይም በዚህ ሕግ አንቀጽ 734 መሰረት ከእሽግ ውስጥ የወጡ ዕቃዎች በሙሉ እንደገና ይመረመራሉ።
4) በጉምሩክ እጅ ያሉ እና በመጋዘን የተቀመጡ ዕቃዎች በዕቃ ዝርዝር መዝገቡ ውስጥ ተለይተው መገለጽ አለባቸው።
5) የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ የዕቃ ዝርዝር መዝገቡን ዋና ቅጂው ይይዛል።
6) የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ የዕቃ ዝርዝር መዝገቡን ለማዘጋጀት ገማች፣ የሒሳብ ሥራ ባለሞያ፣ የሰነዶች ምዝገባ ባለሞያ ወይም ሌላ ማንኛውም ብቁ የሆነ ባለሞያ ሊሾም ይችላል።
7) የዕቃ ዝርዝር መዝገብ ያለመኖሩ የክፍያ ወይም የተመላሽ ክፍያ ክሶችን አያስቀርም።

**<u>አንቀጽ 738 ስለ ታክስ እና ቀረጥ</u>**

1. የከሰረው ሰው የዕቃ ዝርዝር መዝገብ በሚዘጋጅበት ጊዜ ያሉበትን የታክስ እና የቀረጥ ግዴታዎች ለንብረት ጠባቂው መግለጽ አለበት።
2. ንብረት ጠባቂው ባለዕዳው የሰጠውን መግለጫ ለታክስ እና ለማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣናት ያስገባል።
3. ባለዕዳው ንብረት ጠያቂው በጠየቀው በሃያ (20) ቀናት ውስጥ ለመተባበር ፈቃደኛ ካልሆነ ንብረት ጠባቂው ባለዕዳው እንቢተኛ መሆኑን ለተቆጣጣሪ ዳኛው እና ለታክስ እና ለማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣናቱ ያሳውቃል።

**<u>አንቀጽ 739 ከሞት በኋላ ለተገለጸ መክሠር የንብረት ዝርዝር መዝገብ አዘገጃጀት</u>**

መከሠሩ ከሞት በኋላ ተገልጾ የንብረቱም ዝርዝር መዝገብ ያልተዘጋጀ እንደሆነ፤ ወይም የንብረቱ ዝርዝር መዝገብ ከመዘጋጀቱ በፊት ባለዕዳው የሞተ እንደሆነ የንብረት ዝርዝሩ የሚዘጋጀው መዘጋጀቱን የሚቀጥለው ወራሾች ወይም የኑዛዜው አስፈጻሚዎች በተገኙበት ወይም በአደራ ደብዳቤ ወይም ተቀባዩ ለመቀበሉ ማረጋገጫ ሊሰጥበት በሚችል ሌላ ማንኛውም ኤሌክትሮኒክ መንገድ በሚገባ ጥሪ ተደርጎላቸው ካልቀረቡ በሌሉበት ነው፡፡

**አንቀጽ 740 የዐቃቤ ሕግ መብቶች**

1) ዐቃቤ ሕግ የዕቃው ዝርዝር መዝገብ ሲደራጅ ለመገኘት እና ለማየት ይችላል፡፡
2) በማናቸውም ጊዜ መክሠርን የሚመለከቱ ውሎችን፣ ሰነዶችን፣ መዝገቦችን ወይም ወረቀቶችን ሁሉ የማየት መብት አለው፡፡
3) ዐቃቤ ሕግ የዕቃው ዝርዝር መዝገብ ሲደራጅ ለመገኘት እንዲችል የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ሊያሳውቀው ይገባል፡፡

**አንቀጽ 741 የባለዕዳውን ንብረቶች ለንብረት ጠባቂው ስለ ማስረከብ**

የንብረቱ ዝርዝር መዝገብ ከተዘጋጀ በኋላ በዕቃው ዝርዝር መዝገብ ውስጥ የተዘረዘሩት ንብረቶች እንዲሁም ግንኙነት ያላቸው ሰነዶች እና ማስረጃዎች በሙሉ ለንብረት ጠባቂው ይሰጣሉ፡፡ ንብረት ጠባቂውም መረከቡን በዚሁ የዕቃ ዝርዝር መዝገብ ሥር ያመለክታል፡፡

## ክፍል አምስት
## የባለዕዳውን ንብረት ስለ ማስተዳደር

**አንቀጽ 742 የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ጠቅላላ ተግባር**

1) የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ በተቆጣጣሪ ዳኛው ፈቃድ ቶሎ ለብልሽት የሚዳረጉትን ወይም ወደፊት ዋጋቸው ይቀንሳል ተብለው የሚገመቱትን ወይም ለማስቀመጥ ብዙ ወጪ የሚጠይቁትን ዕቃዎች ይሸጣል፡፡ ሽያጮቹ የሚከናወንባቸው ሁኔታዎች እና ሥርዓቶች ተቆጣጣሪ ዳኛው ይወሰናል፡፡
2) የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ገቢ ክፍያዎችን ተቀብሎ በተቆጣጣሪ ዳኛው የተፈቀዱ ወጪዎችን ከቀነሰ በኋላ በንብረቱ ስም በተከፈተው የባንክ ሒሳብ ወዲያውኑ ተቀማጭ ያደርጋል፡፡
3) የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ቢያንስ በየሦስት ወሩ ሂደቱ የሚገኝበትን ደረጃ ለተቆጣጣሪ ዳኛው እና ለዐቃቤ ሕግ ያሳውቃል፡፡

**አንቀጽ 743 አክሲዮኖች እና ቃል የተገቡ ገንዘቦች እንዲከፈሉ ጥሪ ስለ ማድረግ**

1) የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ አክሲዮኖች እንዲከፈሉ ጥሪ የማድረግ እና ቃል የተገቡት ገንዘቦች የመክሠር ፍርዱ በተሰጠበት ቀን የመክፈያ ጊዜያቸው ያልደረሰ ቢሆንም ባለአክሲዮኖች እና ማኅበርተኞች ቃል የገቡትን ገንዘብ እንዲከፍሉ የማዘዝ ሥልጣን አለው፡፡

2) ባለአክሲዮኖች እና ማኅበርተኞች በከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ ማሳወቂያ በተሰጣቸው በአሥር ቀናት ውስጥ ቃል የገቡትን ገንዘብ ያልከፈሉ እንደሆነ የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ የከሰረውን ሰው ንብረት በመወከል ቃል የተገቡትን ገንዘቦች ለማስከፈል ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል።

**አንቀጽ 744 የከሠረውን ሰው የንግድ ሥራ ስለ መቀጠል**

1) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እንደተጠበቀ ሆኖ የመክሠር ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት የተሰጠው ፍርድ የከሠረውን ሰው የንግድ ሥራ ያስቆመዋል።

2) በተቆጣጣሪ ዳኛው መግለጫ እና በገንዘብ ጠያቂዎቹ ኮሚቴ ምክረ ሀሳብ መሰረት ፍርድ ቤቱ የፈቀደለት እንደሆነ የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ የንግዱን ሥራ ለመቀጠል ይችላል። ፈቃዱ የሚሰጠው የባለዕዳውን ንብረት ዋጋ ከፍ ማድረግ ለገንዘብ ጠያቂዎቹ ወይም ለሕዝብ የሚጠቅም በሚሆንበት ጊዜ፤ በተለይም ደግሞ በዚህ ሕግ ከአንቀጽ 747 እስከ አንቀጽ 750 ድረስ በተደነገገው መሰረት በንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያለ ድርጅት በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ ለመሸጥ ዝግጅት ለማድረግ ነው። ፍርድ ቤቱ ቢበዛ ለስድሳ ቀናት ያክል ጊዜ የንግድ ሥራው እንዲቀጥል ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፤ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘውም ለአንድ ጊዜ ብቻ ለዚያኑ ያህል ጊዜ ሊያራዝመው ይችላል።

3) የሚቀጥለውን የንግድ ሥራ ራሱ እንዳይሰራ ለማድረግ ተቆጣጣሪ ዳኛው፡-

   ሀ) የንግዱን ሥራ የሚሰራ ሞግዚት ለማድረግ እንዲችል ለከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ ሥልጣን ሊሰጠው ይችላል። ሞግዚቱ የንግድ ሥራውን ለመሥራት አስፈላጊ የሆኑት ሥልጣናት ይኖሩታል፤ ወይም

   ለ) የንግድ ሥራው እንዲያገግም በማድረግ ረገድ በአንዳንድ የባለዕዳው ሠራተኞች ድጋፍ እንዲደረግለት ለከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ ሥልጣን ሊሰጠው ይችላል።

4) የንግድ ሥራው የቀጠለ እንደሆነ የድህረ-ኪሳራ ገንዘብ ጠያቂዎች በገቡት ውል መሰረት ይከፈላቸዋል። እንዲህ ያሉት ማናቸውም የድህረ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎች ያልተከፈሉ እንደሆነ ዋስትና ከሌላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች ቅድሚያ ይኖራቸዋል፤ ሆኖም ግን የቅደም ተከተል ደረጃቸው በዚህ ሕግ አንቀጽ 786 መሰረት መልሶ በማደራጀት ወይም ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ በማዋቀት ማዕቀፍ ውስጥ ከቀረበ አዲስ ገንዘብ በታች ይሆናል።

**አንቀጽ 745 አዲስ ስለቀረበ ገንዘብ**

1) በልዩ ሁኔታዎች ውስጥ የገንዘብ ጠያቂዎች ኮሚቴ በሚፈቅድበት ጊዜ የከሰረውን ሰው የንግድ ሥራ እንዲቀጥል ለመደጎም አዲስ ገንዘብ እንዲቀርብ ሊፈቀድ ይችላል።

2) አዲስ የቀረበው ገንዘብ ዋስትና ከሌላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች ቅድሚያ ይኖረዋል፤ ሆኖም ግን የቅደም ተከተል ደረጃው በዚህ ሕግ አንቀጽ 786 መሰረት መልሶ በማደራጀት ወይም ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ በማዋቀር ማዕቀፍ ውስጥ ከቀረበ አዲስ ገንዘብ በታች ይሆናል። ፍርድ ቤቱ ለዕዳ ማስያዣነት ያልዋሉ የከሰረው ሰው

ንብረቶች አዲስ ለቀረበ ገንዘብ ዋስትና እንዲሆኑ ሊፈቅድ ይችላል። እንዲህ በሚሆንበት ጊዜም አዲስ ገንዘብ ያቀረቡ ሰዎች የሚያገኙት ቅድሚያ ዋስትና ባላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች ቅደም ተከተል ደንብ መሰረት ይሆናል።

**<u>አንቀጽ 746</u>** **<u>ድርድር እና በስምምነት መቋጨት</u>**

1) ተቆጣጣሪ ዳኛው ከገንዘብ ጠያቂዎች ኮሚቴው ጋር በመመካከር እና የከሰረው ሰው የሚለውን ከሰማ በኋላ ወይም በአደራ ደብዳቤ ወይም ተቀባዩ ለመቀበሉ ማረጋገጫ ሊሰጥበት በሚችል ሌላ ማንኛውም ኤሌክትሮኒክ መንገድ በሚገባ ተጠርቶ ያልቀረበ እንደሆነ በሌለበት የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ የከሠረውን ሰው ንብረት የሚመለከተው ማንኛውንም ዕዳ በድርድር እንዲፈታ ወይም በስምምነት እንዲቋጭ ሊፈቅድ ይችላል።

2) ከአንድ መቶ ሺህ (100,000) ብር በላይ ለሆነ ማንኛውም ድርድር ወይም ስምምነት የከሰረው ሰው አስተያየት ተሰምቶ በፍርድ ቤቱ መጽደቅ አለበት።

## <u>ክፍል ስድስት</u>

## <u>በመክሠር ሥነ ሥርዓት ውስጥ በንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያለ ድርጅት በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ ስለ መሸጥ</u>

**<u>አንቀጽ 747</u>** **<u>ሥርዓት</u>**

በዚህ ሕግ አንቀጽ 744 መሰረት ፍርድ ቤቱ የገንዘብ ጠያቂዎች ኮሚቴውን ምክረ ሀሳብ ከሰማ በኋላ የባለዕዳው የንግድ ሥራ እንዲቀጥል የፈቀደ እንደሆነ የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ በዚህ ሕግ ከአንቀጽ 689 እስከ አንቀጽ 692 በተደነገገው መሰረት በንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያለ ድርጅት በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ እንዲሸጥ ያዘጋጃል፡፡ ሽያጩንም ይፈጽማል፡፡

**<u>አንቀጽ 748</u>** **<u>የንግድ ሥራ እንቅስቃሴውን ለመረከብ የቀረበው ዕቅድ በገንዘብ ጠያቂዎች ኮሚቴ ስለ መጽደቁ</u>**

1) የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ በንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያለ ድርጅት በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ ለመግዛት የቀረቡትን ጨረታዎች በገንዘብ ጠያቂዎች ኮሚቴ ድምጽ እንዲሰጥበት ያቀርባል።
2) የአጠቃላይ የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎቹ ቢያንስ ሃያ አምስት በመቶው ያላቸው አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ገንዘብ ጠያቂዎች በጨረታዎቹ ላይ ድምጽ እንዲሰጥባቸው የገንዘብ ጠያቂዎች ጠቅላላ ጉባዔ እንዲጠራ የከሰረውን ሰው ንብረት ጠባቂ ሊጠይቁ ይችላሉ።
3) ቢያንስ ከገንዘብ ጠያቂዎቹ የክፍያ ጥያቄዎች ግማሹ ያላቸው አንድ ወይም ከዚያ በላይ ገንዘብ ጠያቂዎች በገንዘብ ጠያቂዎች መካከል በሚደረግ የጽሁፍ ስምምነት አማካኝነት ጨምሮ ጨረታውን የሚደግፉ ከሆነ ጨረታው ተቀባይነት ያገኛል። ማሳወቂያ ተሰጥቷቸው ያልተገኙ በአካል ወይም በሕጋዊ ወኪላቸው አማካኝነት ያልተገኙ ገንዘብ ጠያቂዎች ድምጻቸው ከግምት ውስጥ አይካተትም።

**<u>አንቀጽ 749</u>** **<u>በንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያለ ድርጅት በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ እንዲሸጥ ፍርድ ቤቱ ስለ ማጽደቁ</u>**

1) ፍርድ ቤቱ የአሸናፊው ተጫራች የንግድ ሥራ ዕቅድ የንግድ ሥራውን አዋጪነት የማረጋገጥ ምክንያታዊ ተስፋ ያለው መሆኑን ያረጋግጣል፡፡
2) በዚህ ሕግ አንቀጽ 694 ከንዑስ አንቀጽ (2) እስከ (4) በመክሠር ሥነ ሥርዓት ውስጥ በንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያለ ድርጅት በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ በመሸጥ ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

**<u>አንቀጽ 750 የከሰረውን ሰው ሌሎች ንብረቶች ስለ መሸጥ</u>**

በንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያለ ድርጅት በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ የተሸጠ እንደሆነ የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ የተቀሩትን የባለዕዳውን ንብረቶች በዚህ ሕግ ከአንቀጽ 775 እስከ አንቀጽ 779 ድረስ በተደነገገው መሰረት ይሸጣል፡፡

## <u>ክፍል ሰባት</u>
## <u>ንብረትን ስለ ማስመለስ</u>

**<u>አንቀጽ 751 አጠቃላይ መርህ</u>**

1) የመክሠር ሥነ ሥርዓት በተከፈተበት ቀን ላይ በአይነት በባለዕዳው ይዞታ ስር የሆኑ ግዙፋዊ ህልዎት ያላቸው እና የሌላቸው ተንቀሳቃሽ መብቶች፣ ዕቃዎች እና ንብረቶች ባለቤት የሆነው ሰው በዚህ ክፍል ሰባት በተደነገጉት መሰረት ንብረቶቹን የማስመለስ መብት አለው፡፡
2) ለዚህ ክፍል ሰባት ለንብረት ማስመለስ ዓላማና መብቶች፣ ተመላሽ የሚሆኑ ዕቃዎች እና ንብረቶች በተለይ የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

    ሀ) የገንዘብ ሰነዶች፤

    ለ) በአደራ የተቀመጡ ወይም ለሽያጭ የቀረቡ ዕቃዎች፤

    ሐ) ባለሀብትነታቸው እንደተጠበ ሆኖ የተሸጡ ዕቃዎች፤

    መ) ለባለዕዳው የተላኩ እና ባለዕዳው ወይም ባለዕዳውን በመወከል እንዲሸጣቸው ሥልጣን የተሰጠው ሰው በመጋዘኑ የተረከባቸው ዕቃዎች፡፡
3) በገዢው ያልተከፈሉ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ውስጥ ከተመለከቱት መብቶች፣ ዕቃዎች እና ንብረቶች ሽያጭ የሚመነጩ ክፍያዎችን ማስመለስ ይቻላል፡፡

**<u>አንቀጽ 752 ተቀንሰው የተያዙና ለመንግስት ገቢ የሚሆኑ ታክሶችን እና ቀረጦችን ስለ መሰብሰብ</u>**

1. የታክስ ባለሥልጣናት የከሰረው ባለዕዳ ለመንግስት የያዛቸውን ታክሶች የመሰብሰብ መብት አላቸው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው የገንዘብ መጠን አግባብ ባላቸው የታክስ ሕጎች መሰረት የከሰረው ባለዕዳ መክፈል የሚኖርበትን ወለድ እና ቅጣት አይጨምርም፡፡ ወለዱ እና ቅጣቶቹ እንደ የቅድመ-መከሰር የገንዘብ ጥያቄዎች ይቆጠራሉ፤ እንዲሁም በመክሠር ሥነ ሥርዓት ውስጥም እንደዚያ ይቀርባሉ፡፡

**<u>አንቀጽ 753 ንብረትን ለማስመለስ የሚቀርብ ማመልከቻ</u>**

1) በዚህ ክፍል መሰረት ንብረትን ለማስመለስ የሚጠይቁ ሰዎች የመክሠር ሥነ ሥርዓት በተከፈተ በሦስት ወር ውስጥ በአደራ ደብዳቤ ወይም ተቀባዩ ለመቀበሉ ማረጋገጫ ሊሰጥበት በሚችል ሌላ ማንኛውም ኤሌክትሮኒክ መንገድ ለከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ንብረታቸውን ለማስመለስ ማመልከት አለባቸው፡፡
2) የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ማመልከቻው በደረሰው በአንድ ወር ውስጥ በአደራ ደብዳቤ ወይም ተቀባዩ ለመቀበሉ ማረጋገጫ ሊሰጥበት በሚችል ሌላ ማንኛውም ኤሌክትሮኒክ መንገድ ውሳኔውን የሰጠበትን ምክንያቶች ለአመልካቹ በመግለጽ ማመልከቻውን ሊቀበል ወይም ውድቅ ሊያደርግ ይችላል፡፡
3) የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ማመልከቻው በደረሰው በአንድ ወር ውስጥ መልስ ያልሰጠ እንደሆነ ማመልከቻው ተቀባይነት እንዳገኘ ይቆጠራል፡፡
4) የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ማመልከቻውን አልቀበልም ያለ እንደሆነ ማመልከቻውን ያቀረበው የንብረቱ ወይም የመብቱ ባለቤት የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ማመልከቻውን ውድቅ በማድረግ በሰጠው ውሳኔ ላይ ውሳኔው በደረሰው በአንድ ወር ውስጥ ለተቆጣጣሪ ዳኛው ተቃውሞ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
5) ተቆጣጣሪ ዳኛውም ማመልከቻው በደረሰው በአሥራ አራት ቀናት ውስጥ በማመልከቻው ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
6) እንደ አግባቡ ማመልከቻውን ያቀረበው ሰው ወይም የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ተቆጣጣሪ ዳኛው በሰጠው ውሳኔ ላይ ውሳኔው በተሰጠ በአሥር ቀናት ውስጥ ለፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላሉ፡፡
7) ንብረት ለማስመለስ የቀረበው ማመልከቻ ተቀባይነት ካገኘ የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ሥነ ሥርዓቱ ከተከፈተ በኋላ ከንዑስ-ተቀባዩ የተገኙ ማናቸውንም ክፍያዎች ጨምሮ መብቱን፣ ዕቃውን ወይም ንብረቱን ወዲያውኑ ይመልሳል፡፡

## <u>ክፍል ስምንት</u>

## <u>ስለ መያዝ መብት</u>

**<u>አንቀጽ 754 ስለ መያዝ መብት</u>**

1) አንቀጽ 658 በመክሠር ሥነ ሥርዓት ላይ በተመሳሳይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
2) የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ የመያዝ መብትን በተመለከተ የመልሶ ማደራጀት ኃላፊው ያለው ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

## ምዕራፍ አራት
## መከሠርን የሚያሳውቅ ፍርድ የሚያስከትላቸው ውጤቶች

### ክፍል አንድ
### በባለዕዳው ላይ ያሉት ውጤቶች

**አንቀጽ 755 የባለዕዳው ግዴታዎች**

ባለዕዳው በዚህ ሕግ አንቀጽ 636 እና አንቀጽ 637 ስር የተቀመጡትን ግዴታዎች በተሳካ ሁኔታ ይወጣ ዘንድ፤ የንግድ ሥራው ይቀጥል ወይስ አይቀጥል የሚለውን ለመወሰን እንዲረዳ ባለዕዳው በውል ሰነድ ያልተደነገጉትን ጨምሮ የተዋዋይ ወገኖችን ስም ዝርዝር፣ አድራሻ፣ መብቶች እና ግዴታዎች፣ የደንበኞችን ዝርዝር እና ሌሎች ግንኙነት ያላቸውን ሰነዶች ለከሠረው ንብረት ጠባቂ ያስረክባል።

**አንቀጽ 756 የከሠረውን ሰው እንቅስቃሴ ስለመገደብ**

የከሠረው ሰው ተቆጣጣሪ ዳኛው ሳይፈቅድለት በማንኛውም ምክንያት ከመኖሪያ ቦታው ለመራቅ አይችልም። የከሰረው ሰው ይህን ቢተላለፍ አግባብነት ያላቸው የኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆኑበታል። የከሠረው ሰው ሀገር ለቆ ሊሔድ ወይም የመኖሪያ ቦታውን ሊቀይር እንደሚችል የሚያሳዩ በቂ ምክንያቶች ያሉ እንደሆነ የከሠረው ሰው ከመኖሪያ ቦታው ወይም ከዋና የንግድ ሥራው መቀመጫ እንዳይርቅ ገደብ እንዲያስቀምጥበት ተቆጣጣሪ ዳኛው ለፍርድ ቤት ሊያመለክት ይችላል።

**አንቀጽ 757 የከሠረው ሰው ስለ መቀጠሩ**

የመከሠር ሥነ ሥርዓቱን በቀና ለማከናወን በተቆጣጣሪ ዳኛው ፈቃድ ባለዕዳው በከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ሊቀጠር ይችላል።

**አንቀጽ 758 ለከሠረው ሰው እና ለቤተሰቡ ስለሚደረግ ድጋፍ**

የከሠረው ሰው የተፈጥሮ ሰው እንደሆነ እና ኪሣራ ላይ ከሚገኘው ንብረት ውጭ ራሱን እና ቤተሰቡን የሚደግፍበት ገቢ የሌለው ከሆነ የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ በሚያቀርበው ጥያቄ መሰረት ተቆጣጣሪ ዳኛው ለከሠረው ሰው እና ለቤተሰቡ ኪሣራ ላይ ከሚገኘው ንብረት ርዳታ እንዲደረግላቸው ሊያዝ ይችላል።

**አንቀጽ 759 ስለከሠረው ሰው ባል ወይም ሚስት**

1) የከሠረው ሰው ባል ወይም ሚስት የግል ንብረት እስከ ምን ድረስ እንደሆነ አግባብነት ባላቸው የቤተሰብ ሕጎች የሚወሰን ይሆናል።
2) የገንዘብ ጠያቂዎች ኮሚቴው ንብረቱ የተገዛው የከሠረው ሰው ባቀረበው ገንዘብ እንደሆነ ማስረጃ በማቅረብ እንዳግባቡ በከሠረው ሰው ባል ወይም ሚስት የተገዙ ንብረቶች የከሠረው ሰው ንብረት ውስጥ እንዲካተቱ ተቆጣጣሪ ዳኛውን ሊጠይቅ ይችላል።

3) የከሠረው ሰው ባል ወይም ሚስት አንዳንድ የሞያ፣ ሲቪል፣ የንግድ ወይም የእጅ ሙያ አገልግሎቶችን ያቀርቡ የነበረ ከሆነ አገልግሎቶቹ የተሰጡት ጋብቻቸውን በፈጸሙ በአንድ ዓመት ውስጥ ከሆነ ባል ወይም ሚስት አንደኛው ለሌላኛው ከሰጡት አገልግሎት ጋር በተያያዘ ክስ ማቅረብ አይችሉም።

**<u>አንቀጽ 760</u>** **<u>የመክሰስ ወይም የመከሰስ መብትን ስለ ማጣት</u>**

በዚህ ሕግ አንቀጽ 673 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የሚቀርቡ የግል ክርክሮች እንደተጠበቁ ሆነው የከሠረውን ሰው የመክሠር ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት ያደረገው ፍርድ ከተሰጠበት ቀን በኋላ መክሰስ ወይም መከሰስ የሚችለው የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ ነው። ፍርድ ቤቱ ባለዕዳው በሚያቀርበው ጥያቄ መሠረት ባለዕዳው በማንኛውም ክርክር ውስጥ ጣልቃ እንዲገባ ሊፈቅድ ይችላል።

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>በገንዘብ ጠያቂው ላይ ያሉት ውጤቶች</u>

**<u>አንቀጽ 761</u>** **<u>በተናጠል ክፍያ ለማስፈጸም የሚደረጉ ክርክሮች በጠቅላላ ስለ መቋረጣቸው</u>**

1) በዚህ አንቀጽ 761 ንዑስ አንቀጽ 2 እስከ 6 ያሉት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ ሕግ ከአንቀጽ 654 እስከ አንቀጽ 657 ያሉት ድንጋጌዎች በኪሣራ ሥነ ሥርዓት ላይ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።
2) የተፈጥሮ ሰዎችን ጨምሮ ዋስትና ሰጪዎች በመክሠር ሥነ ሥርዓት ውስጥ በተናጠል ክፍያ ለማስፈጸም የሚደረጉ ክርክሮች እንዲቋረጡ መጠየቅ አይችሉም።
3) ንብረቱ ለዕዳ መያዣ በአንድ ገንዘብ ጠያቂ ይዞታ ውስጥ የሚገኝ ካልሆነ በስተቀር የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ ለዕዳ ማስያዣነት የዋሉ ንብረቶችን ጨምሮ ማናቸውንም ንብረቶች ለመሸጥ ሥልጣን አለው።
4) ለዕዳ ማስያዣነት የዋለ ንብረት በይዞታው ውስጥ የሚገኘው ገንዘብ ጠያቂ የንብረት የዋስትና መብቱን ተጠቅሞ ንብረቱን ሊሸጥ ወይም በራሱ ሥልጣን የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ ንብረቱን እንዲሸጠው ሊፈቅድ ይችላል። ለዕዳ ማያዣ የዋለው ንብረት ከክፍያ ጥያቄው በላይ በሆነ ዋጋ ዋስትና ባለው ገንዘብ ጠያቂ የተሸጠ እንደሆነ እላፊው በከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ይሰበሰባል። የተሸጠበት ዋጋ ከክፍያ ጥያቄው በታች ከሆነ ገንዘብ ጠያቂው ለተቀረው ገንዘብ ዋስትና እንደሌለው ገንዘብ ጠያቂ የክፍያ ጥያቄውን ሊያቀርብ ይችላል።
5) የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ የመክሠር ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት ፍርድ በተሰጠ በስድስት ወራት ውስጥ ለዕዳ ማስያዣነት የዋሉ ንብረቶችን ለመሸጥ እርምጃዎችን ሳይወስድ የቀረ እንደሆነ ባለሀብትነቱ እንደ ተጠበቀ ሆኖ የተፈጸመ የሽያጭ ውል ያላቸው ገንዘብ ጠያቂዎችን ጨምሮ በግልጽ በተቀመጡ የከሰረው ሰው ንብረቶች ዋስትና ያላቸው ማናቸውም ገንዘብ ጠያቂዎች የንብረት የዋስትና መብታቸውን ተግባራዊ ሊያደርጉ ይችላሉ።
6) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ሕግ አንቀጽ 751 እና አንቀጽ 752 መሰረት ከከሰረው ሰው ንብረት ውስጥ ዕቃዎችን የማስመለስ መብት ያላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች ሊያስመልሱ ይችላሉ።

**አንቀጽ 762 የተንቀሳቃሽ ንበረት ማስያዣዎች ስለ መመለሳቸው**

በዚህ ሕግ አንቀጽ 656 ንዑስ አንቀጽ (2) በመክሥር ሥነ ሥርዓት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል። በተለይም ደግሞ የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ መልሶ የማደራጀት ኃላፊው ሥልጣናት ይኖሩታል።

**አንቀጽ 763 የወለድ ሒሳብ ስለ መቋረጡ**

1) የማይንቀሳቀስ ንብረት ዋስትና ካላቸው ብድሮች በስተቀር ከከሠረው ሰው ከሚፈለጉት ገንዘቦች ላይ የሚታሰቡት ወለዶች ሁሉ የመክሥር ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት ፍርድ ከተሰጠበት ጊዜ አንስቶ መቁጠር ያቆማሉ።

2) ዋስትና ያሏቸው የብድር ዋና ገንዘብ ወለዶች ለዋስትና ከተመደቡት ንብረቶች ከሚገኙት ገንዘቦች ላይ ካልሆነ በቀር ሊጠየቁ አይችሉም።

**አንቀጽ 764 የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎች የመከፈያ ጊዜ ስለ መድረስ**

1) የመክሥር ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት ፍርድ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎች ሁሉ ወዲያውኑ የመከፈያ ጊዜያቸው የደረሰ እና ተከፋይ ይሆናሉ።

2) በውጭ ምንዛሪዎች የተገለጹ የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎች የመክሥር ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት ፍርድ በተሰጠበት ቀን ሕጋዊ በሆነው ምንዛሪ በአገሩ ገንዘብ ይለወጣሉ።

**አንቀጽ 765 ለአከራዩ ቅድሚያ የሚሰጥ ስለ መሆኑ**

1) በዚህ ሕግ አንቀጽ 595 መሠረት ኪራይ የተቋረጠ እንደሆነ የመክሥር ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት ከተሰጠው ፍርድ አስቀድመው ባሉት ሁለት ዓመታት እና በተያዘው ዓመት የኪራይ ውሉን ከመፈጸም የሚመነጩ የክፍያ ጥያቄዎችን እና ተያያዥ የጉዳት ካሳዎችን ሁሉ በተመለከተ አከራዩ ቅድሚያ ይኖረዋል።
2) አከራዩ የሚያገኘው ቅድሚያ ወሰን ተንቀሳቃሽ ንብረቶቹ የተከራዩ ሆኑም አልሆኑም የተከራየው ቤት ውስጥ የሚገኙትን ተንቀሳቃሽ የቤት እና የቢሮ ዕቃዎች በሙሉ ያካትታል።

## ክፍል ሦስት

## የመክሥር ፍርዱ ከመሰጠቱ አስድሞ ስለ ተሠሩ አጠራጣሪ ሥራዎች እና ግብይቶች

**አንቀጽ 766 ሥራዎቹ ፈራሽ ስለመሆናቸው**

በዚህ ሕግ ከአንቀጽ 671 እስከ አንቀጽ 677 በተደነገገው መሰረት የመክሥር ፍርድ ከመሰጠቱ አስቀድሞ አጠራጣሪ በሆነ ጊዜ ውስጥ በባለዕዳው የተሠሩት ሥራዎች መልሶ በማደራጀት ሥነ ሥርዓት ማዕቀፍ ውስጥ መልሶ በማደራጀት ኃላፊው ፈራሽ ያልተደረጉ እንደሆነ የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ ሥራዎቹ ፈራሽ እንዲደረጉ

ለማድረግ እርምጃዎችን ይወስዳል። ሥራዎቹን ፈራሽ ለማድረግ ዓላማ የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ መልሶ የማደራጀት ኃላፊው ስልጣን ይኖረዋል።

**አንቀጽ 767 ሥራዎች ፈራሽ እንዲሆኑ ክርክር ስለማንሳት**

በዚህ ሕግ አንቀጽ 673 በመክሠር ሥነ ሥርዓት ላይ በተመሳሳይ ተፈጻሚ ይሆናል። በተለይም የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ በተጠቀሰው አንቀጽ መሰረት መልሶ የማደራጀት ኃላፊው ስልጣን ይኖረዋል፤ እንዲሁም የገንዘብ ጠያቂዎች ኮሚቴው በተጠቀሰው አንቀጽ መሰረት ተቆጣጣሪዎች ያላቸው ስልጣን ይኖረዋል።

## ምዕራፍ አምስት
## የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎችን ስለ ማቅረብ እና ስለ መመርመር

**አንቀጽ 768 የሚቀርቡበት እና የሚመረመሩበት ሥርዓት**

የሚከተሉት ድንጋጌዎች እንደ ተጠበቁ ሆነው በዚህ ሕግ አንቀጽ 649 (ለገንዘብ ጠያቂዎች ስለሚሰጥ ማስታወቂያ) እና በዚህ ሕግ ከአንቀጽ 662 እስከ አንቀጽ 670 (የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎችን ስለ ማቅረብ እና መመርመር) የተደነገጉት በዚህ ምዕራፍ 5 የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎችን በማቅረብ እና በመመርመር ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

**አንቀጽ 769 በመክሠር ሥነ ሥርዓቶች ውስጥ ባንድነት እና በነጠላ ተጠያቂ የሆኑ አካላት ላይ የክፍያ ጥያቄዎችን ስለ ማቅረብ**

1) ባለዕዳው ያልተወሰነ ኃላፊነት ያለው ማኅበር የሆነ እንደሆነ በማኅበሩ መክሠር ተመርምረው ተቀባይነት ያገኙ የማኅበሩ ገንዘብ ጠያቂዎች ያቀረቧቸው ዕዳዎች ማኅበርተኞች መክሰራቸው ከማኅበሩ ጋር ባንድነት የተነገረ እንደሆነ ዕዳዎቹ በእያንዳንዱ ማኅበርተኛ መክሠር እንደ ተመረመሩ እና ተቀባይነት እንዳገኙ ይቆጠራሉ።

2) መክፈል ከሚገባቸው በላይ ስለከፈሉት ገንዘብ የእያንዳንዱ ማኅበርተኛ መክሠር በሌላው ማኅበርተኛ መክሠር ላይ ክስ ለማቅረብ የተሰጠው መብት ሳይነካ ከማህበሩ ላይ ገንዘብ ጠያቂ የሆነው ሰው ገንዘቡ በሙሉ እስኪከፈለው ድረስ በሚደረጉት ክፍያዎች ሁሉ ተካፋይ ለመሆን መብት አለው።

3) ከማኅበርተኞቹ ላይ የግል ገንዘብ ጠያቂ የሆኑት ሰዎች በመብታቸው ሊጠይቁበት የሚችሉት ባለዕዳ በሆናቸው ማኅበርተኛ መክሠር ውስጥ ብቻ ነው።

4) ማንኛውም ገንዘብ ጠያቂ ከእርሱ ጋር ገንዘብ ተካፋይ የሆኑትን ገንዘብ ጠያቂዎች መብት ለመቃወም ይችላል።

**አንቀጽ 770 የክፍያ ጥያቄዎችን ስለ መመርመር**

የገንዘብ ጠያቂዎች ኮሚቴ አስቀድሞ የተቋቋመ እንደሆነ ኮሚቴው ወይም ተወካዩ በተገኘበት እንዲሁም በራሱ ተነሳሽነት ከተገኘ ባለዕዳው በተገኘበት ወይም በአደራ ደብዳቤ ወይም ተቀባዩ ለመቀበሉ ማረጋገጫ ሊሰጥበት በሚችል ሌላ ማንኛውም ኤሌክትሮኒክ መንገድ በሚገባ ተጠርቶ ካልቀረበ ባለዕዳው በሌለበት የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎችን ይመረምራል።

## <u>አንቀጽ 771</u> <u>የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄን መቀበልን ስለ ማቋረጥ እና መቃወሚያን ስለ ማለፍ</u>

1) አንድ ዕዳ ጊዜ የሚፈጅ ክርክር ያስነሳ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ወይም ጉባዔ መቃወሚያው እስኪወሰን ድረስ የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄ መቀበሉ እንዲቋረጥ ወይም መቃወሚያው እንዲታለፍ ይወስናል።

2) ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ወይም ጉባዔ መቃወሚያው እንዲታለፍ የወሰነ እንደሆነ በዚያው የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ለጊዜው የክፍያ ጥያቄውን እንዲቀበል ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

3) ዕዳው የወንጀል ክስ የሚያስከትል የሆነ እንደሆነ የመክሠሩን ጉዳይ የሚመለከተው ፍርድ ቤት የመክሠሩ ሥነ ሥርዓት እንዲቋረጥ ለማዘዝ ይችላል። ነገር ግን መቃወሚያው እንዲታለፍ የተወሰነ እንደሆነ በወንጀሉ ክስ ፍርድ እስኪሰጥበት ድረስ ለጊዜው የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄውን እንዲቀበሉት ፍርድ ቤቱ ሊፈቅድ አይችልም። ገንዘብ ጠያቂውም በክርክር ሂደቱ ተሳታፊ ለመሆን አይችልም።

## <u>አንቀጽ 772</u> <u>የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄያቸውን በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ስላላቀረቡ ገንዘብ ጠያቂዎች</u>

1) የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄያቸውን በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ያላቀረቡ ገንዘብ ጠያቂዎች በማንኛውም ክፍያ ውስጥ አይካፈሉም። ሆኖም የመጨረሻው ክፍያ እስኪፈጸም ድረስ መቃወሚያ ለማቅረብ ይችላሉ።

2) የእነሱ መቃወም በመከሠር ሥነ ሥርዓት ተቆጣጣሪ ዳኛው ያዘዛቸውን ክፍያዎች አፈጻጸም ሊያግደው አይችልም። ሆኖም አዲስ ክፍያ የተደረገ እንደሆነ ለጊዜው ፍርድ ቤቱ በሚወስነው ገንዘብ ልክ ተካፋይ ሆነው በመቃወሚያውም ፍርድ እስኪሰጥ ድረስ ድርሻቸው ተጠብቆ ይቀመጣል።

## <u>አንቀጽ 773</u> <u>መብታቸው በኋላ ስለታወቀላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች</u>

መብታቸው በኋላ የታወቀላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች መልሶ በማደራጀት ሥነ ሥርዓት ተቆጣጣሪ ዳኛ ባዘዛቸው ክፍያዎች ላይ ምንም ዓይነት ጥያቄ ማቅረብ አይችሉም። ሆኖም ካልተከፋፈለው ንብረት በመጀመሪያ በሚያደርጉት ክፍያዎች ውስጥ በመጀመሪያው ክፍያ ሊደርሳቸው ይገባ የነበረውን ድርሻ የመውሰድ መብት አላቸው።

## <u>አንቀጽ 774</u> <u>ባንድነት እና በነጠላ ዋስትና ያላቸው የክፍያ ጥያቄዎችን ስለ ማቅረብ</u>

1) በዚህ ሕግ አንቀጽ 670 በመከሠር ሥነ ሥርዓት ላይ በተመሳሳይ ተፈጻሚ ይሆናል።

2) የመጨረሻ ክፍያው በሚሰላበት ጊዜ ዋስትና ሰጪው ለገንዘብ ጠያቂው የፈጸመው ማንኛውም ክፍያ ከግምት ውስጥ ይገባል።

3) የመክሠር ሥነ ሥርዓቱ በሚመለከታቸው በርካታ ዋስትና ሰጪዎች በአንድነት እና በነጠላ የተሰጠ ዋስትና ያለው የክፍያ ጥያቄ የያዘ ገንዘብ ጠያቂ በቅድም-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄው ዋጋ ልክ የቅድም-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎቹን በሁሉም ሥነ ሥርዓቶች ውስጥ ማቅረብና በእያንዳንዱ ሥነ ሥርዓት ውስጥ በሚደረጉትም ክፍያዎች ሁሉ ገንዘቡን በሙሉ እስኪያገኝ ድረስ ተካፋይ ለመሆን ይችላል።

4) አንድ ዋስትና ሰጪ ለገንዘብ ጠያቂው የከፈለ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የቅድም-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄውን ያላቀረበ እንደሆነ ገንዘብ ጠያቂው መብቱ በታወቀለት ገንዘብ መጠን ልክ ካልሆነ በስተቀር በሚደረጉ ክፍያዎች መብቱ አይታወቅለትም።

## ምዕራፍ ስድስት

## ንብረት ማጣራት እና የክፍያ ጥያቄዎችን መክፈል

### ክፍል አንድ

### ንብረት ማጣራት

**አንቀጽ 775 የከሠረውን ሰው ንብረት ስለ ማጣራት**

በዚህ ሕግ አንቀጽ 744 መሠረት የንግድ ሥራው የቀጠለ እንደሆነ የሚቀጥልበት ጊዜ ሲያበቃ የከሠረው ሰው ንብረት እንዲጣራ እና ክፍያ ማግኘት የሚገባቸው ገንዘብ ጠያቂዎች በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በተቀመጠው የክፍያ ቅደም ተከተል መሠረት እንዲከፈላቸው ፍርድ ቤቱ ያዛል።

**አንቀጽ 776 ስለ ንብረቱ ማጣራት**

1) የዚህ ምዕራፍ ልዩ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ መሠረት የባለዕዳውን የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ይሸጣሉ። ከሽያጩም የተገኘው ገንዘብ በዚህ ሕግ አንቀጽ 720 ንዑስ አንቀጽ (1) (ሥ) በተመለከተው መሠረት ይቀመጣል። የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ ገንዘቡ የተቀመጠበትን ደረሰኝ ወዲያውኑ ለተቆጣጣሪ ዳኛው ያቀርባል።

2) የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ ማናቸውንም የባለዕዳውን መብቶች በተመለከተ በዚህ ሕግ አንቀጽ 746 በተደነገገው መሰረት ስምምነት ይፈጽማል።

3) ንብረቶቹ የሚሸጡት ከማንኛውም ተጨባጭ፣ ቅድመ ሁኔታ ካለውም ሆነ ከሌላ ዓይነት ዕዳ፣ ዕገዳ፣ ክፍያ እና ኃላፊነት እንዲሁም በተለይም ደግሞ ከአካባቢ ክፍያዎች እና ኃላፊነቶች ነጻ ሆነው ነው።

**አንቀጽ 777 የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን ስለ መሸጥ**

1) የመከሠር ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት በተሰጠው ፍርድ የተነሳ በዕዳ የመውረሱ ሥራ የተቋረጠ እንደሆነ የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ የበዕዳ ወራሽ በሆነው ገንዘብ ጠያቂ ተተክቶ በዚህ ምዕራፍ ድንጋጌዎች መሰረት መያዣ የሆነውን ንብረት ይሸጣል። የማይንቀሳቀሱ ንብረቶቹን የመሸጡ ሂደት የመከሠር ሥነ ሥርዓት ተቆጣጣሪ ዳኛው ትእዛዝ በሰጠ በስምንት ቀናት ውስጥ ይጀምራል።

2) የማይነቀሳቀሰው ንብረት በግል ቢሸጥ ከሐራጅ ጋር ሲነጻጸር ዋጋው የመጨመር ዕድል ያለው ከሆነ የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ የማይንቀሳቀሰውን ንብረት በግል እንዲሸጥ ተቆጣጣሪ ዳኛው ሊፈቅድ ይችላል።

3) የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ የመከሠር ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት የተሰጠው ፍርድ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በስድስት ወራት ውስጥ የሽያጩን ሂደት ያልጀመረ እንደሆነ የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ በሚጠይቀው መሠረት ፍርድ ቤቱ በበቂ ምክንያት የጊዜ ማራዘሚያ ካልሰጠ በስተቀር ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ በዕዳ የመውረስ ሥልጣኑ ይመለስለታል። ከሽያጩ የሚገኘው ገንዘብ በዚህ ምዕራፍ ድንጋጌዎች መሰረት ይከፋፈላል።

## አንቀጽ 778 የባለዕዳው የንግድ ሥራ ሀብቶች ስለ መሸጣቸው

1) መልሶ በማደራጀት ወይም በመክሰር ሥነ ሥርዓት ውስጥ በንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያለ ድርጅት በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ ያልተሸጠ እንደሆነ የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ግዙፋዊ ህልዎት ያላቸው እና የሌላቸው ንብረቶቹን ጨምሮ የንግድ ሥራውን ሀብቶች ይሸጣል።

2) የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ በሐራጅ ወይም በግል ሽያጭ የመሸጫ ዋጋውን ይበልጥ ከፍ የማድረግ ዕድል ባለው በአንደኛው መንገድ የንግድ ሥራውን ሀብቶች ለመሸጥ ሊወስን ይችላል። የሽያጩን መንገድ በተቆጣጣሪ ዳኛው ያስጸድቃል።

## አንቀጽ 779 የከሰረውን ሰው ንብረቶች በማንኛውም መንገድ ነጣጥሎ ስለ መሸጥ

የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ የተቀሩትን የባለዕዳውን ንብረቶች ሁሉ በሐራጅ ወይም በግል ሽያጭ የመሸጫ ዋጋውን ይበልጥ ከፍ የማድረግ ዕድል ባለው በአንደኛው መንገድ ይሸጣል። የሽያጩን መንገድ በተቆጣጣሪ ዳኛው ያስጸድቃል።

## ክፍል ሁለት
## በየጊዜው የሚከፈሉ ክፍያዎች

## አንቀጽ 780 ጠቅላላ መርሆች

1) በግልጽ የተቀመጡ ለዕዳ ማስያዣነት የዋሉ ወይም ያልዋሉ ንብረቶች ተሸጠው ከሽያጫቸው የተገኘው ገንዘብ በዚህ ሕግ ከአንቀጽ 785 እስከ አንቀጽ 793 በተደነገገው መሰረት የመጨረሻው ክፍያ ከመደረጉ አስቀድሞ የተከፈለ እንደሆነ ከአንቀጽ 780 እስከ አንቀጽ 784 የተደነገገው ተፈጻሚ ይሆናል።

2) ንብረቶቹ የማይንቀሳቀሱም ሆኑ የሚንቀሳቀሱ፣ ግዙፋዊ ህልዎት ያላቸውም ሆኑ የሌላቸው በዚህ ሕግ ከአንቀጽ 780 እስከ አንቀጽ 784 በተደነገገው የከሰረው ሰው ንብረት ውስጥ ከሚገኙ በግልጽ የተቀመጡ ንብረቶች ጋር የተያያዘ የዋስትና መብት ባላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች ላይ ሁሉ ተፈጻሚ ይሆናል።

3) ለዚህ ክፍል ዓላማ በማናቸውም የባለዕዳው ተንቀሳቃሽ ወይም የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ላይ የቀዳሚነት መብት ያላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች በየጊዜው በሚደረጉ ክፍያዎች ውስጥ መሳተፍ ይችላሉ። ሆኖም ግን የሚስተናገዱት ዋስትና እንደሌላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች ነው።

**<u>አንቀጽ 781</u>** **<u>*ዕዳ ያለባቸውን ንብረቶች ስለ መሸጥ እና ስለ ማከፋፈል*</u>**

1) የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ ዕዳ ያለባቸው የማይንቀሳቀሱ ወይም ተንቀሳቃሽ፣ ግዙፋዊ ህልዎት ያላቸው ወይም የሌላቸው የከሠረው ሰው ንብረቶችን የሸጠ እና ከሽያጫቸው የተገኘውን ገንዘብ ለማከፋፈል የወሰነ እንደሆነ ዕዳ ያለባቸውን ንብረቶች ለመሸጥ የወጡት ወጪዎች ከተቀነሱ በኋላ በንብረቶቹ ላይ የዋስትና መብት ያላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች ከሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች አስቀድሞ ይከፈላቸዋል።

2) በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ከንብረቶቹ ሽያጭ ከተገኘው ገንዘብ ላይ የተከፈላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች ከዚያ በኋላ ለሚቀራቸው ተከፋይ ገንዘብ ዋስትና እንደሌላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች ይስተናገዳሉ።

**<u>አንቀጽ 782</u>** **<u>*ዕዳ የሌለባቸውን ንብረቶች ስለ መሸጥ እና ከሽያጩ የተገኘውን ገንዘብ ስለ ማከፋፈል*</u>**

የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ ዕዳ ያለባቸው የከሠረው ሰው ንብረቶች ከመሸጣቸው በፊት ዕዳ የሌለባቸውን ንብረቶች ለመሸጥ እና ከሽያጫቸው የተገኘውን ገንዘብ ለማከፋፈል የወሰነ እንደሆነ በዚህ ሕግ አንቀጽ 783 ውስጥ የቀመጡት ተቀናሾች እንደተጠበቁ ሆነው ተመርምረው መብታቸው የታወቀላቸው ዋስትና እና የቀዳሚነት መብት ያላቸው የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎች ያሏቸው ገንዘብ ጠያቂዎች ከአጠቃላይ የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎቻቸው ጋር ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ ዋስትና ከሌላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች ጋር ሊካፈሉ ይችላሉ።

**<u>አንቀጽ 783</u>** **<u>*ተቀናሾች*</u>**

1) ዕዳ ያለባቸው ንብረቶች ከተሸጡ እና በዚህ ሕግ አንቀጽ 786 መሠረት ዋስትና ያላቸው፣ የቀዳሚነት መብት ያላቸው እና ዋስትና የሌላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች ቅደም ተከተላቸው ከተረጋገጠ በኋላ ዕዳ ካለባቸው ንብረቶች ሽያጭ ከተገኘው ገንዘብ ላይ በቅድሚያ እንዲከፈላቸው የመጠየቅ መብት ያላቸው ዋስትና ያላቸው እና የቀዳሚነት መብት ያላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች ዋስትና ያለው ክፍያቸውን የሚያገኙት ዕዳ የሌለባቸው ንብረቶች ተሸጠው ከተገኘው ገንዘብ ላይ የተቀበሉት ገንዘብ ከተቀነሰ በኋላ ነው።

2) በዚህ መልኩ የተቀነሰው ገንዘብ የከሠረው ንብረት ላይ ተደምሮ በዚህ ሕግ አንቀጽ 786 ውስጥ በተቀመጠው ቅደም ተከተል መሠረት ለገንዘብ ጠያቂዎች የሚከፋፈለው ከሽያጭ የተገኘ ገንዘብ አካል ይሆናል።

**<u>አንቀጽ 784</u>** **<u>ዋስትና ላላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች ከፊል ክፍያ ስለ መፈጸም</u>**

ዋስትና ያላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች ዕዳ ያለባቸው ንብረቶች ተሸጠው የተገኘው ገንዘብ በሚከፋፈልበት ጊዜ ከፊል ክፍያ ያገኙ እንደሆነ፡-

1) ከቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄያዎቻቸው ላይ የቀረው ዋስትና የሌለው ክፍል ዕዳ የሌለባቸው ንብረቶችን ጨምሮ ሌሎች ንብረቶች ከተሸጡ በኋላ ለመጨረሻ ጊዜ ይከፈላል።

2) ገንዘብ ጠያቂዎቹ ከዚህ ከተቀረው ክፍያቸው ውስጥ አስቀድሞ ክፍያ በተደረገበት ወቅት የተቀበሏቸው ማናቸውም ገንዘቦች ዋስትና ካለው ክፍያቸው ላይ ተቀንሶ ለዕዳ ማስያዣነት ያልዋሉ ንብረቶች ላይ ይጨመራል።

**<u>ክፍል ሦስት</u>**

**<u>የመጨረሻ ክፍያዎች</u>**

**<u>አንቀጽ 785</u>** **<u>ዋስትና ያላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች በብቸኝነት ስላላቸው መብት</u>**

1) የተንቀሳሽ እና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች መያዣዎችን ጨምሮ በግልጽ በተቀመጡ ንብረቶች ላይ የንብረት የዋስትና መብት ያላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች ዕዳ ያለባቸውን ንብረቶች ለመሸጥ የወጡ ወጪዎች ከተቀነሱ በኋላ ዕዳ ያለባቸው ንብረቶች ተሸጠው በሚገኘው ገንዘብ ላይ በብቸኝነት መብት አላቸው።

2) እንዲህ ባለው የተጣራ የሽያጭ ዋጋ ያልተሸፈነው የቅድመ-ኪሳራ ክፍያዎች ቀሪ ክፍል ዋስትና እንደሌላቸው የክፍያ ጥያቄዎች ይስተናገዳል።

**<u>አንቀጽ 786</u>** **<u>የክፍያ ቅደም ተከተል</u>**

ለዕዳ ማስያዣነት የዋሉ ንብረቶች ከተሸጡ በኋላ ከሽያጩ ከተገኘው ገንዘብ ላይ የሚቀረው ገንዘብ በሚከተለው የክፍያ ቅደም ተከተል መሠረት ልዩ መብት ላላቸው እና ዋስትና ለሌላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች ይከፋፈላል፡-

1) ሥነ ሥርዓቱን ለማስፈጸም የወጡ ወጪዎች፤

2) ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ በማዋቀር ማዕቀፍ ውስጥ የቀረበ አዲስ ገንዘብ፤

3) መልሶ በማደራጀት ማዕቀፍ ውስጥ የቀረበ አዲስ ገንዘብ፤

4) በመክሠር ማዕቀፍ ውስጥ ተፈቅዶ የቀረበ አዲስ ገንዘብ፤

5) የአዲስ እና በሂደት ላይ ያሉ ውሎች ገንዘብ ጠያቂዎችን ጨምሮ የድህረ-ኪሳራ ገንዘብ ጠያቂዎች፤

6) የሠራተኞች እና የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣናት የክፍያ ጥያቄዎች፤

7) ለመንግስት ታክሶች እና ቀረጦችን ቀንሶ ከያዘ ባለዕዳ ላይ ከሚጠየቁት ውጭ ለፌዴራል፣ ለክልል እና ለአካባቢ የመንግስት ባለሥልጣን አካላት መከፈል ያለባቸው ታክሶች እና ቀረጦች (ነገር ግን ወለድ እና ቅጣትን ሳይጨምር)፤

8) ለከሠረው ሰው እና ለቤተሰቡ ቀለብ እንዲውሉ የታዘዙ ገንዘቦች፤

9) ሌሎች ልዩ መብት ያላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች፤

10) ዋስትና የሌላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች፤

11) በባለዕዳው ላይ የተጣሉ ቅጣቶች።

**<u>አንቀጽ 787 ከደረጃ ዝቅ ብሎ የመከፈል ስምምነት</u>**

ከደረጃ ዝቅ ብሎ የመከፈል የውል ድንጋጌዎች በተለይም ደግሞ በብድር ስምምነቶች ውስጥ የተካተቱ ከሆነ በመክሠር ሥነ ሥርዓት ውስጥ ተፈጻሚ ይሆናሉ፤ እንዲሁም በዚህ ሕግ አንቀጽ 786 ውስጥ በተቀመጠው ቅደም ተከተል ውስጥ ከግምት ውስጥ ይገባሉ።

**<u>አንቀጽ 788 ለሥነ ሥርዓቱ ስለሚወጡ ወጪዎች</u>**

ለሥነ ሥርዓቱ የሚወጡ ወጪዎች ከመክሠር ሥነ ሥርዓት ጋር በተያያዘ የወጡ ወጪዎችን እንዲሁም ወደ መክሰር ሥነ ሥርዓት ከተቀየረ መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት ጋር በተያያዘ የወጡ ወጪዎችን እኩል የሚያካትት ሲሆን ይህም የሚከተሉትን ያካትታል፡-

1) መልሶ ለማደራጀት ኃላፊው፣ ለከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ እና እነሱ ለመለመሏቸው ሰራተኞች የሚከፈሉ ክፍያዎችን፤

2) መልሶ የማደራጀት እና የመክሠር ሥነ ሥርዓቱን ለማከናወን የወጡ ወጪዎችን እና ፍርድ ቤቱ ሊያዛቸው የሚችሉ ሌሎች ወጪዎችን፤

3) መልሶ የማደራጀት ኃላፊው እና የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ ሕጉ ወይም ፍርድ ቤት በፈቀደላቸው መሰረት ተግባሮቻቸውን ለማከናወን ያወጧቸውን ወጪዎች።

**<u>አንቀጽ 789 ክፍያዎች ስለሚከፋፈሉባቸው መርሆች</u>**

1) የሚከፈለው አጠቃላይ የገንዘብ መጠን በተመሳሳይ የቅደም ተከተል መደብ ውስጥ ያሉ የገንዘብ ጠያቂዎችን የክፍያ ጥያቄዎች በሙሉ ለመሸፈን የማይበቃ ከሆነ ገንዘብ ጠያቂዎቹ ከታወቁላቸው የክፍያ ጥያቄዎቻቸው ጋር ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ ይከፈላቸዋል።

2) የሚከፋፈለው አጠቃላይ ገንዘብ የክፍያ ጥያቄዎቹን በሙሉ ለመሸፈን የማይበቃ ከሆነ በቅደም ተከተሉ መሰረት ከላይ ያሉት ገንዘብ ጠያቂዎች ሁሉ ሙሉ በሙሉ ሳይከፈላቸው ከታች ያሉት ገንዘብ ጠያቂዎች አይከፈላቸውም።

## <u>አንቀጽ 790 ክርክር ለተነሳባቸው የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎች ስለሚደረግ ተቀማጭ ሂሳብ</u>

1) ክርክር የተነሳባቸው የክፍያ ጥያቄዎችን ከመቀበል ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክርክሮች ላይ በሚሰጠው ውሳኔ የተነሳ የመጨረሻው ክፍያ አይዘገይም።

2) የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ ከሽያጩ ከተገኘው ገንዘብ ላይ ክርክር የተነሳበትን የክፍያ ጥያቄ ያቀረበው ገንዘብ ጠያቂ የክፍያ ጥያቄው ተቀባይነት ቢያገኝ ኖሮ ይከፈለው የነበረውን ያህል ገንዘብ ቀንሶ ተቀማጭ ሂሳብ ውስጥ ያስቀምጣል፤ እንዲሁም አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ መጨረሻው ክፍፍል ላይ በዚያ መሰረት ማስተካከያ ያደርጋል።

## <u>አንቀጽ 791 ክፍፍልን በተመለከት የቀረበ ሃሳብ</u>

1) የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ በዚህ ሕግ አንቀጽ 786 መሠረት ተቀማጭ የተደረገው ገንዘብ ስለሚከፋፈልበት መንገድ ለገንዘብ ጠያቂዎች ኮሚቴው ሃሳብ ያቀርባል።

2) የገንዘብ ጠያቂዎች ኮሚቴው በሚያቀርበው ምክረ-ሀሳብ መሰረት የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ ባቀረበው ሃሳብ ላይ አግባብነት ያላቸውን ለውጦች ሁሉ አድርጎ የተሻሻለውን የክፍፍል ሀሳብ ተቆጣጣሪ ዳኛው እንዲያጸድቀው ያቀርባል።

3) ተቆጣጣሪ ዳኛው የተሻሻለውን የክፍፍል ሀሳብ ያጸድቃል ለፍርድ ቤቱ የመዝገብ ሹም ገቢ እንዲደረግ ትእዛዝ ይሰጣል።

4) ተቆጣጣሪ ዳኛው የክፍፍል ሀሳቡን ውድቅ ያደረገው እንደሆነ መደረግ አለባቸው የሚላቸውን ማሻሻያዎች ለከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ ያሳውቃል። የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂም በዚያ መሠረት የክፍፍል ሀሳቡን አሻሽሎ የመጨረሻውን የክፍፍል ሀሳብ ለፍርድ ቤቱ የመዝገብ ቤት ሹም ገቢ ያደርጋል።

5) የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ የክፍፍል ሀሳቡ ገቢ መደረጉን በአደራ ደብዳቤ ወይም ተቀባዩ ለመቀበሉ ማረጋገጫ ሊሰጥበት በሚችል ሌላ ማንኛውም ኤሌክትሮኒክ መንገድ ለእያንዳንዱ ገንዘብ ጠያቂ ያሳውቃል።

6) ገንዘብ ጠያቂዎች ማሳወቂያ በደረሳቸው በአሥር ቀን ውስጥ ለተቆጣጣሪ ዳኛው ውሳኔ የሚሰጥበት ተቃውሞ ለማቅረብ ይችላሉ። ተቆጣጣሪ ዳኛው በተቃውሞው ላይ የሚሰጠው ውሳኔም ለፍርድ ቤት ይግባኝ ሊቀርብበት ይችላል።

**አንቀጽ 792 ክፍያ ስለሚፈጸምበት መንገድ**

የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ የክፍያ ጥያቄው ለተመረመረ እና ተቀባይነት ላገኘ ለእያንዳንዱ ገንዘብ ጠያቂ የሚገባውን ክፍያ በዚህ ሕግ አንቀጽ 791 ውስጥ በተመለከተው የመጨረሻ የክፍፍል ሀሳብ መሠረት በዚህ ሕግ አንቀጽ 786 በተደነገገው ቅደም ተከተል በከሠረው ሰው ንብረት ስም ከተከፈተው ሂሳብ ላይ ይከፍላል።

**አንቀጽ 793 ለባለዕዳው ወይም ለባለአክሲዮኖች ስለሚመለሰው ገንዘብ መጠን**

ባለዕዳው ያሉበት ዕዳዎች እና ወጪዎች ሁሉ በሕጉ መሠረት ሙሉ በሙሉ ከተከፈሉ በኋላ የተረፈ ገንዘብ ያለ እንደሆነ ገንዘቡ ለባለዕዳው ይመለሳል ወይም ባለዕዳው ማኅበር ከሆነ በማኅበሩ የመመስረቻ ጽሁፍ እና የመተዳደሪያ ደንብ መሠረት ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ ለባለአክሲዮኖቹ ይመለሳል።

**ምዕራፍ ሰባት**
**የመክሠር ሥነ ሥርዓትን ስለመዝጋት**

**አንቀጽ 794 የመክሠር ሥነ ሥርዓት ስለሚዘጋባቸው ምክንያቶች**

በዚህ ሕግ አንቀጽ 796 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የመክሠር ሥነ ሥርዓት በሚከተሉት ምክንያቶች ሊዘጋ ይችላል፡-

1) ከንብረት ማጣራት የተገኘው ገንዘብ ጨርሶ በማከፋፈል፤
2) የሚበቃ ንብረት ባለመኖሩ፤
3) ከንብረቱ የሚፈለግ ዕዳ ባለመኖሩ።

**አንቀጽ 795 የሚበቃ ንብረት ባለመኖሩ መዝጋት**

1) በመክሠር ሥነ ሥርዓቱ ወቅት በማንኛውም ጊዜ ለማናቸውም ዋስትና ያላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች የሚደረገው ክፍፍል ተጣርቶ የሚቀረው ከንብረቶች ሽያጭ የተገኘው ገንዘብ የሥነ ሥርዓቱን ወጪዎች ለመሸፈን በቂ እንዳልሆነ ግልጽ የሆነ እንደሆነ የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ በሚያቀርበው ጥያቄ መሠረት ፍርድ ቤቱ የመክሠር ሥነ ሥርዓቱ እንዲዘጋ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

2) በመክሠር ሥነ ሥርዓቱ ወቅት በማንኛውም ጊዜ የሚቀረው ንብረት በዚህ ሕግ አንቀጽ 786 በተመለከተው ቅደም ተከተል መሠረት ዋስትና የሌላቸው ገንዘብ ጠያቂዎችን ወይም ልዩ መብት ያላቸው ገንዘብ ጠያቂዎችን ምድብ ለመሸፈን በቂ እንዳልሆነ ግልጽ የሆነ እንደሆነ የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ በሚያቀርበው ጥያቄ መሠረት ፍርድ ቤቱ የመከፈል ዕድላቸው ጠባብ የሆነ የቅድመ-ኪሳራ የክፍያ ጥያቄዎችን የመመርመር እና የመቀበል ሥነ ሥርዓቱ እንዲቆም ሊያዝ እና የመክሠር ሥነ ሥርዓቱ እንዲዘጋ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

3) በመከሠር ሥነ ሥርዓቱ ወቅት በማንኛውም ጊዜ ንብረቶች ተሸጠው የሚተርፍ ምንም የተጣራ ገንዘብ እንደማይኖር ግልጽ የሆነ እንደሆነ የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ በሚያቀርበው ጥያቄ መሠረት ፍርድ ቤቱ የመከሠር ሥነ ሥርዓቱ እንዲዘጋ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

4) የመከሠር ሥነ ሥርዓት መዘጋት ገንዘብ ጠያቂዎች ከክፍያ ጥያቄያቸው ውስጥ ላልተከፈለው ገንዘብ ለባለዕዳው ዕዳ ዋስትና የሰጡትን የግል ዋሶች ለመጠየቅ ያላቸውን መብት አይነካም፡፡

**<u>አንቀጽ 796</u>** **<u>የመከሠር ሥነ ሥርዓትን መልሶ ስለመክፈት</u>**

1) ባለዕዳው ወይም ሌላ ማንኛውም ባለጉዳይ በማንኛውም ጊዜ የሥነ ሥርዓቱን ወጪ ለመሸፈን በቂ ንብረት እንዳለ በማሳየት ወይም ወጪዎቹን ለመሸፈን በቂ የሆነ ገንዘብ የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ ጋር ተቀማጭ በማድረግ የመከሠር ሥነ ሥርዓቱን በመቃወም ለፍርድ ቤቱ ሊያመለክት ይችላል፡፡

2) ባለዕዳው በመጀመሪያ በዚህ ሕግ አንቀጽ 795 መሠረት ከሥነ ሥርዓቱ የሚመነጩትን ወጪዎች መክፈል ይኖርበታል፡፡

**<u>አንቀጽ 797</u>** **<u>ከንብረቱ የሚፈለግ ዕዳ ባለመኖሩ ስለሚደረግ መዘጋት</u>**

1) የገንዘብ መጠየቂያ ሰነዶች ዝርዝር ጽሁፍ ለፍርድ የመዝገብ ቤት ሹም ከተሰጠ በኋላ ባለዕዳው ለከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ የሚከፈሉ ክፍያዎችን ጨምሮ የክፍያ ጥያቄዎችን ሁሉ መከፈሉን ወይም የተጠቀሱትን ወጪዎች በሙሉ ለመሸፈን በቂ የሆነ ገንዘብ የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ ጋር ተቀማጭ ማድረጉን ያስረዳ እንደሆነ ባለ ዕዳው ባቀረበው ጥያቄ መሠረት ፍርድ ቤቱ የመከሠር ሥነ ሥርዓቱ እንዲዘጋ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

2) ፍርድ ቤቱ ውሳኔውን የሚሰጠው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱትን ሁኔታዎች ባለዕዳው ማሟላቱን የሚያመለክተውን በተቆጣጣሪ ዳኛው የቀረበውን መግለጫ መሠረት በማድረግ ነው፡፡

3) ፍርዱ ለባለዕዳው እንደገና መብቶቹን መልሶ በመስጠትና መብቶቹን ካሳጡት ሁኔታዎች ነጻ በማድረግ የመከሠር ሥነ ሥርዓቱን ጨርሶ ይዘጋል፡፡

**<u>አንቀጽ 798</u>** **<u>በንግድ መዝገብ ስለ መመዝገብ</u>**

በዚህ ምዕራፍ ድንጋጌዎች መሠረት ስለ መክሠር የቀረበው ክስ እንዲዘጋ የተወሰነውን ፍርድ በዚህ ሕግ አንቀጽ 710 መሠረት የፍርድ ቤቱ መዝገብ ቤት ሹም በንግድ መዝገብ ማስመዝገብ እና ማስታወቅ አለበት፡፡

## <u>ርዕስ አምስት</u>

## <u>የከሠረው ሰው ከዕዳ ነጻ ስለ መደረጉ</u>

**<u>አንቀጽ 799</u>** **<u>ከዕዳ ነጻ ስለ መደረግ</u>**

1) የተፈጥሮ ሰው የሆነ አንድ የከሠረ ሰው ያልተከፈለ ዕዳ ቢኖርም የመክሠር ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት ፍርድ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ ሦስት ዓመት በኋላ ከዕዳዎቹ ሁሉ ነጻ ይሆናል።

2) የሚከተሉት ነጋዴዎች በንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው መሠረት ከዕዳ ነጻ አይሆኑም፡-

ሀ) ከመክሠር ጋር በተያያዘ ወንጀል ጥፋተኝነቱ የተረጋገጠ ነጋዴ፤

ለ) ንብረት ስለ መደበቁ ወይም ስለ ማሸሹ ማስረጃ የቀረበበት ነጋዴ፤

ሐ) በመክሠር ሥነ ሥርዓት ሂደት ውስጥ ያልተባበረ ወይም በቅን ልቦና ግዴታውን ያልተወጣ ነጋዴ፤ ወይም

መ) የመክሠር ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት በአምስት ተከታታይ ዓመታት ውስጥ መክሠሩ የተነገረ ነጋዴ።

3) የሚከተሉት ዕዳዎች ነጻ አይደረጉም፡-

ሀ)ታክሶች፣ ቀረጦች እና ቅጣቶች እንዲተው የሚፈቅዱ ሌሎች ሕጎች ተፈጻሚነት እንደ ተጠበቀ ሆኖ ከታክሶች እና ከቀረጦች ጋር ግንኙነት ያላቸው ዕዳዎች፤

ለ) ከጋብቻ መፍረስ የሚመነጩ ዕዳዎች፣ ቀለብ፤ እና

ሐ) የወንጀል ቅጣቶች።

## <u>አንቀጽ 800 ከዕዳ ነጻ ለመደረግ አቤቱታ ስለሚቀርብበት ሥርዓት</u>

1) የከሠረው ሰው የመክሠር ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት ፍርድ ለሰጠው ፍርድ ቤት ከዕዳ ነጻ መደረጉን የሚደግፉ አግባብነት ያላቸው ደረሰኞችን እና ሰነዶችን በማያያዝ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል።

2) ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን አቤቱታ ከደጋፊ ሰነዶቹ ጋር ባለዕዳው በሚኖርበት አካባቢ ለሚገኘው ዐቃቤ ሕግ ያስተላልፋል። የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂም አቤቱታው እና ሰነዶቹ እንዲደርሱት ይደረጋል።

3) ፍርድ ቤቱ እና ዐቃቤ ሕጉ የባለዕዳው አቤቱታ ትክክለኛ መሆኑን ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ሁሉ ይሰበስባሉ።

4) የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ እና ዐቃቤ ሕጉ አቤቱታው እና ሰነዶቹ በደረሷቸው በሠላሳ ቀናት ውስጥ በማመልከቻው ላይ መግለጫቸውን ለፍርድ ቤቱ ያቀርባሉ።

## <u>አንቀጽ 801 ለገንዘብ ጠያቂዎች ስለ ማሳወቅ እና ስለ ተቃውሞ</u>

1) ፍርድ ቤቱ ከዕዳ ነጻ ለመደረግ የቀረበው ጥያቄ ማሳወቂያ በባለዕዳው የመክሠር ሥነ ሥርዓት ወቅት መብታቸው ለታወቀላቸው ወይም በከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ በተዘጋጀው የገንዘብ ጠያቂዎች ዝርዝር

ላይ ለተገለጹ ገንዘብ ጠያቂዎች ሁሉ እንዲላክ ትእዛዝ ይሰጣል። ማሳወቂያው በአደራ ደብዳቤ ወይም ተቀባዩ ለመቀበሉ ማረጋገጫ ሊሰጥበት በሚችል ሌላ ማንኛውም ኤሌክትሮኒክ መንገድ ይላካል።

2) በመክሠር ሥነ ሥርዓቱ መሠረት በሙሉ ያልተከፈላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች ማሳወቂያው በደረሳቸው በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ የከሠረው ሰው ለምን ከዕዳ ነጻ መደረግ እንደሌለበት የሚያሳዩ አግባብነት ያላቸው ሰነዶችን በማቅረብ የከሠረው ሰው ከዕዳ ነጻ እንዳይደረግ ተቃውሞ ሊያቀርቡ ይችላሉ።

3) ፍርድ ቤቱ በገንዘብ ጠያቂዎቹ የቀረበውን ተቃውሞ የከሠረው ሰው ከዕዳ ነጻ መደረጉን በተመለከተ የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ ካቀረበው መግለጫ ጋር ለዐቃቤ ሕጉ ይልካል።

4) ፍርድ ቤቱ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ የከሠረውን ሰው እና ተቃውሞ ያቀረቡትን ባለጉዳዮች ጠርቶ በዝግ ጉዳያቸውን ሊሰማ ይችላል።

5) ከዕዳ ነጻ ለመደረግ የሚቀርቡ አቤቱታዎች የቴምብር ቀረጥ፣ የምዝገባ እንዲሁም ሌሎች ማናቸውም ታክሶች እና ክፍያዎች አይከፈልባቸውም።

## <u>አንቀጽ 802 ከዕዳ ነጻ እንዲደረግ ስለሚያዙ ወይም ውድቅ ስለሚያደርጉ ፍርዶች</u>

1) ከዕዳ ነጻ ለመደረግ በዚህ ሕግ አንቀጽ 799 የተቀመጡትን ሁኔታዎች የከሠረው ሰው ያሟላ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የከሠረው ሰው ከዕዳ ነጻ እንዲሆን ውሳኔ ይሰጣል።

2) ፍርድ ቤቱ ከዕዳ ነጻ ለመደረግ የቀረበውን አቤቱታ ውድቅ ያደረገ እንደሆነ የከሠረው ሰው ከዕዳ ነጻ ለመደረግ አቤቱታ ሊያቀርብ የሚችለው ፍርድ ቤቱ ከዕዳ ነጻ መደረጉን ውድቅ ካደረገበት ቀን አንስቶ ከአንድ ዓመት በኋላ ነው።

3) ባለዕዳው ከዕዳ ነጻ እንዲሆን ፍርድ ቤቱ የወሰነ እንደሆነ ውሳኔው በንግድ መዝገብ ውስጥ መመዝገብ አለበት። ከዕዳ ነጻ መደረግ በማንኛውም መልኩ የባለዕዳውን ከንግድ መዝገብ መሰረዝን አያስከትልም።

4) ባለዕዳው ከዕዳ ነጻ መደረጉን በኢትዮጵያ ውስጥ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ላይ ማሳተም ይፈቀድለታል።

## <u>ርዕስ ስድስት</u>

## <u>ስለ ፍትሐ ብሔር ኃላፊነቶች፣ እግዶች፣ ወንጀሎች እና የግል መክሠር</u>

## <u>ምዕራፍ አንድ</u>

## <u>ስለ ሥራ አስኪያጆች እና ሦስተኛ ወገኖች የፍትሐ ብሔር ኃላፊነት</u>

## <u>አንቀጽ 803 ስለ ሥራ አስኪያጆች ኃላፊነት</u>

1) ሥራ አስኪያጁ፡-

ሀ)ክፍያዎች በተቋረጡ በአርባ አምስት ቀናት ውስጥ በከባድ ቸልተኝነት የመክሠር አቤቱታ ባለማቅረብ፤ ወይም

ለ) የገንዘብ ኪሳራ የሚያስከትሉ እንቅስቃሴዎችን በከባድ ቸልተኝነት በመቀጠል፤

ሐ) የንግድ እንቅስቃሴዎችን በግሉ ራሱን ወክሎ በማከናወን እና የድርጅቱን ንብረቶች እንደራሱ ንብረት በመሸጥ እና የራሱን የግል ጉዳዮች ለመደበቅ የድርጅቱን ጉዳዮች እንደ ሽፋን በመጠቀም፤

ጥፋት ከፈጸመ እና ማህበሩ በቂ ንብረት እንዳይኖረው አስተዋጽኦ ካደረገ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ በመክሠር ሥነ ሥርዓት ሂደት ውስጥ አንድ ወይም ከአንድ በላይ በተጨባጭ ወይም በሕግ የማኅበሩ ሥራ አስኪያጆች በድምሩ የማህበሩን ንብረት ዋጋ በቀነሱት እና ኃላፊነቱን በጨመሩት መጠን የማኅበሩን ዕዳዎች በሙሉ ወይም በከፊል እንዲከፍሉ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

2) ማህበሩ በቂ ንብረት እንዳይኖረው አስተዋጽኦ ያደረጉትን የሥራ አመራር ጥፋቶች የፈጸሙት ከአንድ በላይ ሥራ አስኪያጆች የሆኑ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ሥራ አስኪያጆቹን በአንድነትና በተናጠል ተጠያቂ ሊያደርጋቸው ይችላል።

3) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በቀረበ ክርክር ተመላሽ የሆነ ገንዘብ በዚህ ሕግ በአንቀጽ 786 ውስጥ በተቀመጠው ቅደም ተከተል መሠረት ለከሠረው ማኅበር ገንዘብ ጠያቂዎች ይከፈላል።

## <u>አንቀጽ 804 ስለ ገንዘብ ጠያቂዎች ኃላፊነት</u>

1) የብድር አገልግሎት በመስጠት ባለዕዳውን በሚጎዳ መልኩ የደገፉ ገንዘብ ጠያቂዎች ተጠያቂ የሚሆኑት፡-

ሀ) የማጭበርበር ወንጀል የፈጸሙ፤ ወይም

ለ) በተጨባጭ እንደ ባለዕዳው ሥራ አስኪያጅ የሠሩ፤ ወይም

ሐ) ካቀረቡት ብድር ጋር ተመጣጣኝ ያልሆኑ የንብረት ዋስትናዎችን ከባለዕዳው ንብረት ላይ የያዙ፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተቀመጡት ሁኔታዎች በተጨማሪ ገንዘብ ጠያቂዎች ተጠያቂ ሊሆኑ የሚችሉት፡-

ሀ) የብድሩ ደንቦች እና ሁኔታዎች ባለዕዳውን የሚጎዱ የነበሩ፤ እና

ለ)ባለዕዳው ክፍያዎችን ያቋረጠ መሆኑን እና መመለስ የማይችል መሆኑን ያውቁ የነበረ ወይም ሊያውቁ ይገባ የነበረ፤

እንደሆነ ብቻ ነው።

3) የጉዳት ካሳው መጠን ብድሩ ከተሰጠበት ጊዜ አንስቶ በድምሩ የከሠረው ሰው ንብረት ዋጋ ከቀነሰበት እና ኃላፊነቱ ከጨመረበት መጠን ጋር ተመሳሳይ ይሆናል።

## <u>አንቀጽ 805 ስለ ባለአክሲዮኖች ኃላፊነት</u>

በተጨባጭ ሥራ አስኪያጅ የሆኑ ሰዎች በዚህ ሕግ አንቀጽ 803 መሠረት ያለባቸው ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ የባለዕዳው ባለአክሲዮኖች ለባለዕዳው ገንዘብ ጠያቂዎች ኃላፊ የሚሆኑት ባለአክሲዮኖቹ፡-

1) የማጭበርበር ወንጀል የፈጸሙ፤ ወይም

2) የራሳቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ ለባለዕዳው ሥራ አመራር የሰጧቸው መመሪያዎች ባለዕዳው ክፍያዎችን እንዲያቋርጥ ያደረጉ፤

እንደሆነ ብቻ ነው።

**<u>አንቀጽ 806 ስለ ክስ አቅራቢዎች</u>**

1) በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተመለከቱት ክሶች ለፍርድ ቤቱ ሊቀርቡ የሚችሉት በከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ ብቻ ነው።
2) የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ ክስ ላለመመስረት የወሰነ እንደሆነ ማንኛውም ገንዘብ ጠያቂ ለከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ ክስ እንዲመሰርት መጥሪያ ከሰጠ በኋላ መጥሪያው በተሰጠ በአንድ ወር ውስጥ ምንም ምላሽ ያላገኘ ወይም አሉታዊ ምላሽ ያገኘ እንደሆነ ገንዘብ ጠያቂው በግሉ ስለ ከሰረው ሰው ክስ ሊመሰረት ይችላል።
3) ገንዘብ ጠያቂው ክሱን ያሸነፈ እንደሆነ ገንዘብ ጠያቂው በክሱ የተነሳ ያወጣቸው ወጪዎች በከሠረው ሰው ንብረት ይሸፈናሉ።
4) ክሱን ያቀረበው ሰው የማስረዳት ኃላፊነት አለበት።

**<u>ምዕራፍ ሁለት</u>**

**<u>ከመክሠር ስለሚመነጩ የወንጀል ቅጣቶች እና እገዳዎች</u>**

**<u>አንቀጽ 807 በቸልተኝነት ስለ መክሠር</u>**

የኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ ከበድ ያለ ቅጣት የሚደነግግ ካልሆነ በስተቀር፡-

1) ለሌላኛው ተዋዋይ ወገን ያልተገባ ጥቅም የሚሰጡ ውሎችን ሆነ ብሎ የፈጸመ፤
2) የክፍያዎችን መቋረጥ ለማዘግየት በማሰብ ግዢዎችን ፈጽመው ባነሰ ዋጋ መልሶ የሸጠ ወይም የክፍያዎችን መቋረጥ ለማዘግየት በማሰብ ገንዘብ ለማግኘት ጎጂ የሆኑ መንገዶችን የተጠቀመ፤
3) ሕጋዊ ምክንያት ሳይኖራቸው በዚህ ሕግ አንቀጽ 705 መሠረት ክፍያዎች በተቋረጡ በአርባ አምስት ቀናት ውስጥ ክፍያዎች የተቋረጡ መሆኑን ለፍርድ ቤት ያላሳወቀ፤
4) ሆነ ብሎ የሒሳብ መግለጫዎችን ያልተሟላ ያደረገ ወይም የሒሳብ መዛግብትን በመደበኛ በየጊዜው ያልያዘ ወይም ከማኅበሩ አቅም አንጻር የሒሳብ መግለጫ አቀራረብ ስታንዳርዶችን በግልጽ የማያሟሉ የሒሳብ መግለጫዎችን የያዘ፤

ኪሳራው የታወጀ ባለዕዳ ወይም የባለዕዳው ስራ አስኪያጅ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ከስድስት ወራት ባልበለጠ ቀላል የእስር ቅጣት እና በአሥር ሺህ ብር (10,000 ብር) የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

**<u>አንቀጽ 808 በተንኮል ስለ መክሠር</u>**

የኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ ይበልጥ ከባድ የሆነ ቅጣት የሚደነግግ ካልሆነ በስተቀር አንድ ባለዕዳ እና በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ፣ በተጨባጭ ወይም በሕግ አንድን የንግድ ማሕበር ሥራ የመራ ሰው እና የሥራ አስኪያጅ ሕጋዊ ተወካይ ሆኖ ያገለገለ ማንኛውም ሰው፡-

1) የአንድን የንግድ ማኅበር ንብረቶች የበዘበዘ ወይም በሙሉ ወይም በከፊል የደበቀ፤

2) በሒሳብ መዛግብቱ ውስጥ ወይም በሕጉ መሠረት ወይም ሕጋዊ በሆነ መልኩ በተገቡ ግዴታዎች መሠረት የሌለበትን የገንዘብ ዕዳ በተንኮል አለብኝ ብሎ የተናገረ፤
3) የከሠረውን ሰው ኃላፊነት በተንኮል ከፍ ያደረገ፤
4) የፈጠራ የሒሳብ መዛግብት የያዘ ወይም የከሠረውን ሰው የሒሳብ ሰነዶች እና መዛግብት የደመሰሰ፤
5) በግልጽ ያልተሟሉ ወይም በመደበኛ ሁኔታ ያልተያዙ ሒሳቦችን የያዘ፤

እንደሆነ ጥፋተኛ ሆኖ ሲገን ከአንድ ዓመት ያልበለጠ ቀላል እስራት እና የአሥር ሺህ ብር (10,000 ብር) የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

**አንቀጽ 809 ከመክሠር ስለሚመነጭ መታገድ**

1) በዚህ ሕግ አንቀጽ 808 በተደነገገው ወንጀል (በተንኮል መክሠር) ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ማንኛውም ባለዕዳ ወይም ሥራ አስኪያጅ ከተጣለበት ቅጣት በተጨማሪ ወይም በቅጣቱ ምትክ ከሚከተሉት መካከል በአንዱ ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ዕገዳ ሊጣልበት ይችላል፡-
   ሀ) የግለሰብ ንግድን ወይም በማንኛውም የንግድ ሥራ ውስጥ የተሰማራ ማንኛውንም ሕጋዊ ማኅበር ሥራ መምራትን፣ ማስተዳደርን ወይም መቆጣጠርን ጨምሮ በማንኛውም የንግድ ሥራ ውስጥ እንዳይሳተፍ፤
   ለ) በኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ መሠረት በወንጀል ችሎቶች ሊወሰኑ በሚችሉት ሁለተኛ ደረጃ ቅጣቶች መሠረት በሲቪል፣ በፍትሐ ብሔር እና በቤተሰብ መብቶች እንዳይጠቀም መታገድ፤
   ሐ) የመንግስት ሥልጣን እንዳይዝ ወይም የሞያ ወይም የንግድ ማኅበራትን በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ እንዳይመራ መታገድ፤
   መ) በመንግስት የግዢ ውሎች እንዳይሳተፍ፤
   ሠ) የጻፈው ሰው ከአውጪው ባንክ ገንዘብ እንዲያወጣ ከሚፈቅዱ ቼክ ወይም የገንዘብ ሰነድ ውጭ ቼኮችን ወይም የገንዘብ ሰነዶችን እንዳይጽፍ ወይም በባንክ የተረጋገጡ ቼኮችን እንዳይጽፍ መከልከል።
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱትን ክልከላዎች እና እገዳዎች የሚጥለው ፍርድ ቤት የክልከላዎቹን የቆይታ ጊዜ ይወስናል፤ ሆኖም በማናቸውም ሁኔታ ከስድስት ወራት ሊያንስ ሌሎች አስገዳጅ ሕጎች ረዘም ላለ ጊዜ የሚቆይ ዕገዳ የሚጥሉ ካልሆነ በስተቀር ከአምስት አመታት ሊበልጥ አይችልም።

**አንቀጽ 810 በሕግ ሰውነት ባላቸው አካላት ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች**

1) የኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 34 እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ የንግድ ማኅበር በዚህ ሕግ በአንቀጽ 808 በተደነገጉት ወንጀሎች ጥፋተኛ ሊባል ይችላሉ።
2) በንግድ ማኅበር የሚጣለው ቅጣት በኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 90 በተቀመጡት ደንቦች እና ሁኔታዎች መሠረት የሚጣል የገንዘብ ቅጣት ይሆናል።

**አንቀጽ 811 ጥቅም ስለ መስጠት**

1) መልሶ በማደራጀት ወይም በመክሠር ሥነ ሥርዓት ወቅት፡-

   ሀ) የማይንቀሳቀስ ወይም ተንቀሳቃሽ ንብረት በመያዣነት የሰጠ ወይም በዚህ ሕግ አንቀጽ 653 ንዑስ አንቀጽ (3) ከተደነገገው ፈቃድ ውጭ የማስተላለፍ ሥራ የሠራ ወይም በዚህ ሕግ አንቀጽ 656 ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን ክልከላ በመጣስ አንድን ዕዳ በሙሉ ወይም በከፊል የከፈለ፤

   ለ) በዚህ ሕግ አንቀጽ 687 ንዑስ አንቀጽ (1) ስለ የመልሶ ማደራጀት ዕቅድ ኃላፊነቶችን ስለ መክፈል የተቀመጡትን ደንቦች እና ሁኔታዎች በመጣስ ክፍያ የፈጸመ ማንኛውም ባለዕዳ ወይም በተጨባጭ ወይም በሕግ የባለዕዳው የንግድ ሥራ ሥራ አስኪያጅ የሆነ ሰው፤

2) በመጠባበቂያ ጊዜው ወቅት ወይም ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዕቅድ ወይም መልሶ የማደራጀት ዕቅድ ተግባራዊ በመደረግ ላይ እያለ ባለዕዳው የሚገኝበትን ሁኔታ እያወቀ በዚህ ሕግ አንቀጽ 655 ንዑስ አንቀጽ (5) እና በአንቀጽ 687 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ከመደበኛው ውጭ የሆነ ክፍያ የጠየቀ ወይም የተቀበለ ማንኛውም የባለዕዳው ገንዘብ ጠያቂ፤

3) በዚህ ሕግ አንቀጽ 694 ንዑስ አንቀጽ (3) ንብረቶች እንዳይተላለፉ የተቀመጠውን ግዴታ የጣሰ አሸናፊ ተጫራች፤

ጥፋተኛ ሆኖ የተገኙ እንደሆነ ከአንድ ዓመት ባልበለጠ ቀላል የእስራት ቅጣት እና በአሥር ሺህ ብር (10,000 ብር) የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

**አንቀጽ 812 ዝምድና ባላቸው ሰዎች ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች**

የከሠረው ሰው ንብረት አካል ሊሆኑ የሚገቡ ንብረቶችን የበዘበዘ፣ የደበቀ ወይም ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ የያዘ የባለዕዳው ባል ወይም ሚስት፣ አራተኛ ደረጃን ጨምሮ እስከ አራተኛ ደረጃ ድረስ የሚቆጠር የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድ ያለው ሰው ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ከስድስት ወራት ባልበለጠ ቀላል እስራት እና በአሥር ሺህ ብር (10,000 ብር) የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

**አንቀጽ 813 በተቆጣጣሪ ዳኛ፣ መልሶ በማደራጀት ኃላፊ ወይም በከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች**

ማንኛውም ተቆጣጣሪ ዳኛ፣ መልሶ የማደራጀት ኃለፊ ወይም የከሰረው ሰው፡-

1) በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ባሉት ሥነ ሥርዓቶች መሠረት ስራውን በሚያከናውንበት ወቅት የተቀበላቸውን ክፍያዎች ለራሱ ጥቅም በማዋል ወይም እንደማይገባው እያወቀ ሌሎች ሰዎች ክፍያዎችን እንዲፈጽሙለት በማድረግ በፈቃዱ የገንዘብ ጠያቂዎች ወይም የባለዕዳዎች ጥቅም ላይ ጉዳት ያደረሰ፤ ወይም

2) ዓላማው ከገንዘብ ጠያቂዎቹ ወይም ከባለዕዳዎቹ ጥቅም ጋር እንደሚጋጭ እያወቀ የራሱን ሥልጣናት ለራሱ ዓላማ ጥቅም ላይ ያዋለ፤

እንደሆነ ወይም ከአንድ ዓመት ባልበለጠ ቀላል እስራት እና በአሥር ሺህ ብር (10,000 ብር) የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

**አንቀጽ 814 ወንጀሎችን ለፍርድ ስለማቅረብ**

1) ዐቃቤ ሕጉ ወይም የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተመለከቱትን ወንጀሎች ለወንጀል ፍርድ ቤት ማቅረብ አለበት።

2) የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ ወንጀሎች ስኬታማ በሆነ መልኩ ለፍርድ እንዲቀርቡ ለማድረግ ደጋፊ ሰነዶችን፣ ደረሰኞችን እና ሌሎች መረጃዎችን ለዐቃቤ ሕጉ ማስተላለፍ አለበት። ደጋፊ ሰነዶች እና ደረሰኞች እንዲቀርቡ በሚታዘዝበት ጊዜ የፍርድ ቤት መዝገብ ቤት ሹሙ ጋር ይቀመጣሉ።

3) በተንኮል በመከሠር እና ግንኙነት ባላቸው ሌሎች ወንጀሎች ጥፋተኛ ሆኖ መገኘት ባለዕዳው በርዕስ አራት መሠረት የመከሠር ፍርድ ያልተፈረደበት ቢሆንም እንኳን ሊቀጣ ይችላል።

**አንቀጽ 815 በግል ስለ መከሠር**

1) በተጨባጭ ወይም በሕግ የአንድ ማኅበር ሥራ አስኪያጅ የሆኑ ሰዎች የሚከተሉትን ድርጊቶች የፈጸሙ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ በመከሠር ሥነ ሥርዓቱ ሂደት ውስጥ በግላቸው መከሠራቸው እንዲነገር እና የማህበሩን ዕዳዎች በሙሉ ወይም በከፊል እንዲከፍሉ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡-

ሀ) የማህበሩን ንብረት እንደ ራስ ንብረት አድርጎ መሸጥ፤

ለ)ማህበሩን እንደ ሽፋን በመጠቀም የግል ጥቅም ለማግኘት የማኅበሩን ግብይቶች ማከናወን፤

ሐ) የማኅበሩን ንብረት ወይም ገንዘብ ለግል ዓላማዎች ወይም ግለሰቡ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በውስጡ የጥቅም ግንኙነት ላለው ሌላ ማኅበር በሚጠቅም መልኩ መጠቀም፤

መ) ማኅበሩን እንደ ሽፋን በመጠቀም ለራሱ የግል ጥቅም ለማግኘት በግልጽ ትርፋማ ያልሆነ ሥራ ውስጥ መሳተፍ፤

ሠ) የማህበሩን ንብረቶች መበዝበዝ ወይም በሙሉ ወይም በከፊል መደበቅ ወይም በተንኮል ዕዳውዎቹን ከፍ ማድረግ።

2) ከላይ በተመለከተው መሠረት ክስ በማቅረብ የተገኘ ገንዘብ በዚህ ሕግ አንቀጽ 786 ውስጥ በተቀመጠው ቅደም ተከተል መሠረት ለከሠረው ማኅበር ገንዘብ ጠያቂዎች ክፍያ ለመፈጸም ጥቅም ላይ ይውላል።

## ርዕስ ሰባት

## ለአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ስለሚደረግ ቀላል የመክሠር ሥነ ሥርዓት

**አንቀጽ 816 የተፈጻሚነት ወሰን**

1) በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተመለከተው ቀላል የመክሰር ሥነ ሥርዓት ክፍያ ከመቋረጡ በፊት ባሉት 12 ወራት አጠቃላይ የሒሳብ ሚዛናቸው የሀብት መጠን ከሃያ ሚሊዮን (20,000,000) ብር በታች በሆነ ወይም ያለፉት 12 ወራት ዓመታዊ የሽያጭ ገቢያቸው ከአምስት ሺህ (5,000) ብር በታች በሆነ (በየጊዜው የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ ተደርጎበት) ወይም ከ10 በታች ሰራተኞች ባሏቸው ክፍያዎችን ባቋረጡ አነስተኛ ወይም መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።
2) ባለዕዳው ሀቀኝነት የጎደለው እንደሆነ እና በተለይም ደግሞ የተወሰነ የንብረቱን ክፍል የደበቀ፣ አንዳንድ ገንዘብ ጠያቂዎችን በተንኮል ሳይገልጽ የቀረ፣ ኃላፊነቶቹን ያጋነነ ወይም ሌሎች ማናቸውንም የማጭበርበር ድርጊቶች የፈጸመ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ቀላል የመክሠር ሥነ ሥርዓት አይከፍትም።
3) ቀላል የመክሠር ሥነ ሥርዓቱ የሚመለከተው ባለዕዳ በንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ሀቀኝነት የጎደለው ተግባር የፈጸመ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የወሰነ እንደሆነ ቀላል የመክሠር ሥነ ሥርዓቱን ወዲያውኑ ወደ መክሠር ሥነ ሥርዓት ይቀይራል።

**<u>አንቀጽ 817</u>** **<u>ሥነ ሥርዓት ስለ መከፈት</u>**

1) ባለዕዳው ክፍያዎች ከተቋረጡበት ቀን አንስቶ በአርባ አምስት ቀናት ውስጥ ቀላል የመክሠር ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት አቤቱታ ማቅረብ አለበት።
2) ማንኛውም ገንዘብ ጠያቂ ወይም ዓቃቤ ሕግ ባለ ዕዳው ክፍያዎችን ማቋረጡን ያወቀ እንደሆነ ማቋረጡን ካወቀበት ቀን ቀጥሎ ባሉት አርባ አምስት ቀናት ውስጥ ቀላል የመክሠር ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት ለፍርድ ቤት አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል።

**<u>አንቀጽ 818</u>** **<u>ሰነዶችን ስለ ማስገባት</u>**

1) የሚከተሉት ሰነዶች ባለዕዳው ቀላል የመክሠር ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት ከሚያቀርበው አቤቱታ ጋር አባሪ ሆነው መቅረብ አለባቸው:-
   ሀ) የንግድ ማኅበሩ የመጨረሻ የሒሳብ ሚዛን ወረቀት፣ የሒሳብ መግለጫዎች ወይም ሒሳብ፣
   ለ) የገንዘብ ጠያቂዎችን እና የባለዕዳዎችን ስም እና አድራሻ የያዘ የንግድ ነክ ገቢዎች እና ዕዳዎች ዝርዝር፤
   ሐ) የአቅርቦት ውሎችን፣ የኪራይ እና የፈቃድ ውሎችን ጨምሮ በሂደት ላይ ያሉ የዋና ዋና ውሎች ዝርዝር።
2) ባንኮችን እና የመንግስት ባለሥልጣን አካላትን ጨምሮ ባለዕዳው ወይም ሌላ ማንኛውም ሦስተኛ ወገን አግባብነት ያላቸው ማናቸውንም ተጨማሪ ሰነዶች እንዲያቀርቡ ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

**<u>አንቀጽ 819</u>** **<u>የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ</u>**

1) ፍርድ ቤቱ ቀላል የመክሠር ሥነ ሥርዓቱ ለሚቆይበት ጊዜ ያህል የከሠረውን ሰው ንብረት ጠባቂ ይሾማል።

2) የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ገለልተኛ ሆኖ ሌሎች ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን ጨምሮ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡-

ሀ) ቀላል የመክሠር ሥነ ሥርዓት መከፈቱን ለገንዘብ ጠያቂዎች የማሳወቅ፤

ለ) ባለዕዳው ለፍርድ ቤቱ ያቀረባቸው መረጃዎች የተሟሉ እና እውነተኛ መሆናቸውን ማረጋገጥ እና ባለዕዳው የፈጸማቸውን ማናቸውንም ህቀኝነት የጎደላቸው ድርጊቶች ለፍርድ ቤቱ የመግለጽ፤

ሐ) በጨረታ ወይም በግል ሽያጭ የመሸጫ ዋጋውን ከፍ ለማድረግ ይበልጥ ቀልጣፋ በሆነው በአንደኛው መንገድ የባለዕዳውን ንብረቶች በሙሉ የመሸጥ፤

መ) የክፍያ ጥያቄዎቻቸው ተቀባይነት ያገኙ ገንዘብ ጠያቂዎች ዝርዝር ለፍርድ ቤት መዝገብ ቤት ሹሙ እንዲሰጥ የማዘጋጀት፤

ሠ) ከሽያጩ የሚገኘውን ገንዘብ በዚህ ሕግ አንቀጽ 786 መሠረት ባላቸው ቅደም ተከተል መሠረት ለገንዘብ ጠያቂዎቹ የማከፋፈል፤

ረ) የገንዘብ ጠያቂዎች ዝርዝሩን፣ የተሸጡ ንብረቶችን እና የተከፋፈለውን ከሽያጭ የተገኘ ገንዘብን በአጭሩ የሚገልጽ የመጨረሻ መግለጫ ለፍርድ ቤቱ የማዘጋጀት።

3) የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ ሥነ ሥርዓቱ በተከፈተ በአንድ ዓመት ውስጥ ሁሉንም ንብረቶች በመሸጥ ከሽያጩ የተገኘውን ገንዘብ በማከፋፈል ሥራውን ያጠናቅቃል።

4) በዚህ ሕግ አንቀጽ 614 ውስጥ ስለ ኃላፊነት ከተደነገገው በተጨማሪ የከሠረው ሰው ንብረት ጠባቂ ሥነ ሥርዓቱ በተከፈተ በአንድ ዓመት ውስጥ የሁሉንም ንብረቶች የመሸጥ እና ከሽያጩ የተገኘውን ገንዘብ የማከፋፈል ሥራውን ያላጠናቀቀ እንደሆነ የግል ኃላፊነት ሊኖርበት ይችላል።

**<u>አንቀጽ 820</u>** **<u>የቀላል የመክሠር ሥነ ሥርዓት የቆይታ ጊዜ</u>**

የቀላል የመክሠር ሥነ ሥርዓት የቆይታ ጊዜ ከአንድ ዓመት ሊበልጥ አይችልም።

**<u>አንቀጽ 821</u>** **<u>የቀላል የመክሠር ሥነ ሥርዓት መዘጋት</u>**

አንድ ዓመት ካለፈ በኋላ ፍርድ ቤቱ ቀላል የመክሠር ሥነ ሥርዓቱን ይዘጋል።

**<u>አንቀጽ 822</u>** **<u>ከዕዳዎች ነጻ ስለ መሆን</u>**

ቀላል የመክሠር ሥነ ሥርዓቱ በሚዘጋበት ጊዜ የተፈጥሮ ሰው የሆነ ባለ ዕዳ፡-

1) ሃቀኝነት የጎደለው ሆኖ ካልተገኘ፤

2) ባለፉት ሦስት ዓመታት ውስጥ የመክሠር ወይም ቀላል የመክሠር ሥነ ሥርዓት ለመክፈት አቤቱታ አቅርቦ ካልነበረ፤

ቀሪ ያልታወቁ ዕዳዎችን ጨምሮ ከዕዳዎቹ ሁሉ ነጻ ይሆናል።

**<u>አንቀጽ 823</u>** **<u>በሕግ የሰውነት መብት ስለተሰጣቸው ሰዎች ከንግድ መዝገብ መሰረዝ</u>**

ቀላል የመከሠር ሥነ ሥርዓቱ እንደተዘጋ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ባለዕዳ ከንግድ መዝገብ ውስጥ ምዝገባው ይሰረዛል።

**<u>አንቀጽ 824</u>** **<u>ቀላል የመከሠር ሥነ ሥርዓት መልሶ ስለመከፈቱ</u>**

ቀላል የመከሠር ሥነ ሥርዓቱ ከተዘጋ በኋላ ባለዕዳው ማናቸውም የቀሩ ንብረቶች ያሉት እንደሆነ ንብረቶቹን ለመሸጥ እና ከሽያጩ የሚገኘውን ገንዘብ ለማከፋፈል እንዲችል ሥነ ሥርዓቱ በተዘጋ በሁለት ዓመታት ውስጥ ገንዘብ ጠያቂዎች ቀላል የመከሠር ሥነ ሥርዓቱ መልሶ እንዲከፈት ጥያቄ የማቅረብ መብት አላቸው።

**<u>አንቀጽ 825</u>** **<u>የመከሠር ሥነ ሥርዓት መልሶ ስለመከፈቱ</u>**

ቀላል የመከሠር ሥነ ሥርዓት የተዘጋ ቢሆንም አንድ ገንዘብ ጠያቂ ባለዕዳው ሀቀኝነት የጎደለው ድርጊት እንደፈጸመ ማስረዳት ከቻለ ሥነ ሥርዓቱ በተዘጋ በሁለት ዓመት ውስጥ የመከሠር ሥነ ሥርዓት መልሶ እንዲከፈት ጥያቄ የማቅረብ መብት አለው።